# ዙቤይዳ



ኣሌክስ ኣብርሃም

2009

# ዙቤይዳ

Fitsum
to
Hilina
2009

አሌክስ አብርሃም

የካቲት 2008 ዓ.ም

© በክፊልም ሆነ በሙሉ መብቱ የደራሲው ነው

የመጀመሪያ ዕትም - ግንቦት 2007

ሁለተኛ ዕትም - ግንቦት 2007

ሦስተኛ ዕትም - ግንቦት 2007

አራተኛ ዕትም - ሰኔ 2007

አምስተኛ ዕትም - ሰኔ 2007

ስድስተኛ ዕትም - ሐምሌ 2007

ሰባተኛ ዕትም - ነሐሴ 2007

ስምንተኛ ዕትም - የካቲት 2008

ዘጠነኛ ዕትም - ሐምሌ 2008

10ኛ ዕትም 2009

አርትዖት፡- ግሩም ተበጀ

የገፅ ሽፋን ሃሳብ፡- አሌክስ አብርሃም

የገፅ ሽፋን ስዕል፡- ሚሊዮን ብርሃን

የገፅ ሽፋን ቅንብር፡- ሃኒባል ገ/ሕይወት

# ማውጫ


ርእስ ገፅ

1. እሌሐምዳሊላሒ ደህና ናት ! ........ 5
2. በሕይወት አንድ ጥግ ........ 15
3. አንዲት መርፌ ስንቱን ቀዳዳ ትሰፋው ? ........ 22
4. አዋጅና ፀሎት ........ 41
5. "ድንቡሎ ለምን ለምን ሞተ ?!?!" ........ 46
6. ፈገግ ሲቃኙንን ቀምተውን ........ 58
7. አበበ በሶ በላ ........ 63
8. የከቴን ያላየ ኬቲን ያመሰግናል ........ 78
9. አይ ዶንኬር ........ 82
10. አድዋ ዛሬ ናት፣ አድዋ ትላንት... ........ 88
(አንቀፅ 17 ፡ - እኛም መስኮታችንን አንከፍትም፣ እናንተም ሚስቶቻችንን አትዩ !!)
11. 39ኛው ዕቅድ ........ 95
12. ቀስ ብሎ ይቀማል ! ........ 104
13. በክራንችና ጭብጨባ የቆመ ወንበር... ........ 151
14. ባለ ዋሸንቱ ሰማዕት ........ 156
15. ሚስቴን አከሸፏት ........ 160
16. አረንጓዴ መፈከሮች !! ........ 190
17. ፀረ - ሰላሙ ሰርግ ቤት ........ 196
18. እግር በእግር ........ 201
19. ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን... ........ 206
20. ቦግ...እልም !! ........ 228
21. ቀለም አልባው ቀለም ! ........ 235
22. ሊሆን ይችላል !! ........ 241

# አልሐምዱሊላሒ ደህና ናት !

ልክ ከ8ኛ ክፍል ወደ ፱ኛ ክፍል ሳልፍ ደስታ የሚያደርገኝን አሳጣኝ። አበድኩ፤ ልቤ በደስታ ጢ ልትል ደረሰች። የባሰ ደስታዬን ጣራ ያስነካው ጉዳይ ደግሞ ወደ ፱ኛ ክፍል ማለፌ ብቻ ሳይሆን ፱ኛ ክፍል እንድማርበት የተመደብኩበት ትምሕርት ቤት ነበር። ታሪካዊውና ታላቁ ወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት። እውነቱን ለመናገር ያኔ ዩኒቨርስቲ መግባት ራሱ ወይዘሮ ሲኂን እንደ መግባት አያኮራም ነበር። ሰማያዊ ዩኒፎርሙ፣ ምርጥ መምሕራኖቹ፣ የቀለም ቢባል የሙያ…። እንደሡም ከዛ በፊት የራሱ የሆነ ትልቅ የሙዚቃ ትምሕርት ክፍል እና ኦርኬስትራ ቡድን ሁሉ ነበረው።

ረዥምና ግርማ-ሞገስ የተላበሰው ቢጫ ፎቁ ከሩቅ ተጋድሞ ሲታይ ቤተ-መንግሥት እንጂ ትምሕርት ቤት አይመስልም። እንዲያውም ይኼን ሁሉ ዓመት የተማርኩበት ትምሕርት ቤት አሁን ከተመደብኩበት ጋር ሳወዳድረው አመዳም ሆነብኝ፤ ኮሰሰብኝ። የሆነ ከላሰቹን ሳያቸው የዶሮ ቤት መስለው ታዩኝ።

ሞት ይርሳኝ ! እንዲህ በደስታ ሰክሬ ጓደኛዬን፣ አብሮ አደጌን አል አሚንን ረሳሁት። የት ሄደ? ፍለጋ ጀመርኩ። አል አሚን ጓደኛዬ ነው፤ አብሮ አደጌ። ዝምተኛ ልጅ ነው። ድፍን ተማሪው በዝምታውና በጉብዝናው ነበር የሚያውቀው። ትምህርት ቤቱን አካልዬ ሳጣው በትምሕርት ቤታችን የኋላ በር ወጥቼ ሁልጊዜ ወደምንቀመጥባት ትንሽ ሜካ ሄድኩ። ብቻውን ተክዞ ተቀምጧል። አቤት አቀማመጡ ሲያሳዝን። ያ ረዥም ቁመቱ እንደሳንበሳ ጥቅልል ብሎ ውስጡ የሐዘን ምሰር ተሞልቶበት…። ግራ ገባኝ። በዚህ ልዩ ቀን እንኳን አል አሚን ማንም ያዝናል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ምን አስተከዘው ግን? ካርዱን በዓይኔ አይቼዋለሁ፤ 99ነጥብ ምናምን ነቅንቆት ነው ያለፈው። ያውም ከትምህርት ቤቱ አንደኛ ወጥቶ ።

"ምን ሆንክ?" አልኩት፤

"ምንም!"

"ታዲያ ምን እዚህ ጎለተህ?"

"አፍራህ እኮ ወደቀች።" አለኝ እንባ ተናንቆት። ሚ..................ስ.......ኪ.......ን !! እኔም እንደሳንቡሳ እጥፍጥፍ ብዬ አላሚን ጎን ተቀመጥኩ፤ ጠጋ አለልኝ። በቃ ሁለታችንም የሚኒስትሪ ካርዳችንን አንከርፍፈን በትካዜ ቁጭ አልን። ከሩቅ ለሚመለከተን ሰው ካርዱ ወደ ፱ኛ ከፍል በጥሩ ውጤት ያለፍንበት መረጃ ሳይሆን ተከፍሎ የማያልቅ እዳ እንድንከፍል ከፍርድ ቤት የተሰጠን የትዕዛዝ ወረቀት ይመስል ነበር። ሰናሳዝን!! ደሴ ዕውቀት ጮራ ትምሕርት ቤት ጀርባ፣ ጦሳ ተራራ ሥር እኔና አላሚን በትካዜ ተቀምጠን ቀረን።

###

እስካሁን እንደአፍራህ ትልልቅ ዓይኖችና እንደቲማቲም የቀላ ከንፈር ያላት ሴት ዓይቼ አላውቅም። ለነገሩ እኔ ትዝ የሚሉኝ ዓይኖቿና ከንፈሮቿ ናቸው እንጂ አፍራህ "ውብ" የሚለው ቃል የማይገልጻት ጉድ ነበረች። ቁመቷ ምንዘነ! ብሎ የወጣ፣ ፀጉሯ በስፖርት 'ፔሬድ' ጠቅልላ ካሠረችበት ስትፈታው መቀመጫዋ ላይ የሚደርስ...፤ በዚያ ላይ ጥቁረቱ ! በዚያ ላይ ብዛቱ ! "ጥቁር ፏፏቴ !" ("ጥቁር አባይ' ሲባል የአፍራህ ፀጉር ይመስለኝ ነበር።) እጆቿ፣ እግሯ፣ ኧ..........ረ የአፍራህ ቁንጅና ! በመቶ ዓመት አንዴ የሚከሰት ዓይነት ነገር ነው። ወሎ የቆንጆ አገር ሲባል አፍራህ ትዝ ትለኝና "ሃቅ ነው!" እላለሁ። እንዲያውም ወሎ አፍራህን ብቻ ይዞ ከድፍን ኢትዮጵያ ጋር በቁንጅና ቢወዳደር አጠገቡ የሚደርስ ያለ አይመስለኝም።

ታዲያ ይህን ሁሉ ቁንጅና ይዛው ፯ኛ እና ፰ኛ ከፍል እኛ ከፍል ነው የተማረችው። ይሄን ጉድ ችለን መማራችን ተዓምር አይደል ? በዛ አፍላ ዕድሜ ኤርታሌ ላይ ጥደው ነው እኮ ያስተማሩን። ዳኛቸው የሚባል ሌላ 'ክላስ' የሚማር ጓደኛችን ታዲያ ልክ የእረፍት ሰዓት ደውል ሲደወል እንቅፋት እስኪደፋው እየሮጠ እኛ ከፍል ይመጣና አፍራህን እያየ እንዲህ ይለናል፣ "...አፍራህ ያለችበት ክላስ አንድ ቀን ብማር እንኳሌ ይከፈት ነበር...፤ ከመቶው መቶ ነበር የማመጣው፤ መናፈሻ ውስጥ እኮ ነው የምትማሩት፣ ብርቅዬ ድንቅዬ ፍጥረት እየጎበኛችሁ...፤ ቁሪስት ናችሁ'ኮ ቱሪስት፤ በኢትዮጵያ ብቻ፣ በደሴ ብቻ፣ በዕውቀት ጮራ ትምሕርት ቤት ብቻ፣በ፯ኛ ሲ ከፍል ብቻ የምትገኝ ብርቅዬ ፍጥረት እየጎበኛችሁ...።"

እውነት አለው። አፍራህ እነዚያን ዓይኖቿን አንዴ ስታሳርፍብን ልባችን ከቅቤ የተሠራች ይመስል ቅ...ልጥ!! ደግሞ ዓይኖቿን ጨፍና የምትስቀው ነገር አላት፤ አቤት ሲያምርባት!! "አፍራህ! አፍራህ! አፍራህ!" ይላል ሳር ቅጠሉ። ታዲያ እሷ ጋር ለማውራት ለመቀራረብ የማይጥር ማነው?

አፍራህ፣ ወይንሸትና ሰዓዳ አንድ ወንበር ላይ ነበር የሚቀመጡት። እውነቱን ለመናገር አፍራህን ዓይቼ ዳርና ዳር የተቀመጡትን ወይንሸትና ሰዓዳን ስመለከት ሰው አይመስሉኝም። ይቅር ይበለኝ ! ...አፍራህን ዙሪያዋን ለመጠበቅ የተገነቡ ግንቦች መስለው ነው የሚታዩኝ። ለነገሩ ሁላችንም የክላሱ ልጆች የኾንን ዙሪያዋን የበቀልን አረም ነገሮች ነበር የምንመስለው። አፍራህ የምትባል ጉድ እንድታቃጣን መሣላችን ጥሎብን ምን እናድርግ። ገኛ "ሲ" ክፍል ማን አለ ቢባል አፍራህ ብቻ። ሒሳብ አስተማሪያችን ራሳቸው ሰባት ጥያቄ ከጠየቁ አምስቱ ለአፍራህ ነው። በእርግጥ አፍራህ አምስቱንም አትመልስም፤ ግን ፈገግ ይሉላታል። ግንኮ እኛ ሐበሾች ብዙዎቻችን እናስመስላለን እንጂ ሴት አናከብርም፤ የምናከብረው ቆንጆ ሴትን ነው።

ሚስኪን ጓደኛዬ አል አሚን ታዲያ ከዚች ተዓምረኛ ልጅ ፍቅር ያዘው። ያውም የማያፈናፍን፣ ትንፋሽ የማይሰጥ ፍቅር። አል አሚን አባቱ ሞተዋል። እናቱም አቅመ ደካማ ነበሩ፤ እማማ ከድጃ። (ሰጀነት ይበላቸው! ዛሬ በሕይወት የሉም።) ከትምሕርት ቤት መልስ በሶላት ሰዓት መስጊድ ሲሰግዱ የሚገቡ ሰዎችን ጫማ በመጠበቅና በመጥረግ ነበር ራሱንም እናቱንም የሚያስተዳድረው። አፍራህን እንዲፈቀራት የነገረኝ ቤሒሳብ መንምኛ ሳር ካከለ በኋላ ነው።

ሲጀመር አል አሚን ዝምተኛ ልጅ ነው። አይናገር ! አይጋገር ! አንድ ቀን ታዲያ እኛ ቤት ሄደን ሳለ (እናቴ በጣም ነው አል አሚንን የምትወደው...)

"አላሚን!" አለችው፤ ስትጠራው እንደዚህ ነው።

"አቤት!" አለ፤

"ትምርት ከበደህ እንዴ?" አለችው በሐዘን እያየችው።

"አ......ይ!"

"ታዲያ ምነው ጭው አልክ? እስቲ አቡቹ ጋር ይችን ብላ" ብላ እንጀራ እየጋገረች ስለነበር ትኩስ እንጀራ ላይ በርበሬ ነስንሳ ቅቤ ለቅልቃ ሰጠችን። እኔ ሳጥ ሳጥ ሳደርገው አል አሚን የእንጀራውን

“ፍቅር ይዞህ እንዳይሆን”

“ፍቅር አይደለም ባከሀ”

“እና ምንድን ነው?”

“እኔ.....ኛ! ፍቅር ነው መሰለኝ”

በቃ ከዛን ቀን ጀምሮ ወሬው ሁሉ አፍራህ ሆነች።

“አቡቹ! ቅድም ‘ማትስ’ ስንማር አፍራህ ያንን ከባድ ጥያቄ ስትመልሰው አልገረመህም?” ይለኛል።

“አልመለሰችውም እኮ...ተሳስታለች”

"ባከህ ቲቸር ራሳቸው ናቸው የተሳሳቱት" ይለኛል ኮስተር ብሎ። አፍራህ የማትስ ሊቅ፣ አፍራህ የውበት ጥግ (የውበቱ እንኳን እውነት ነው)። አፍራህ ስታድግ ሳይንቲስት እንደምትሆን ሁሉ አል አሚን ይተነብይልኛል። ወይኔ ፍቅር!!

በተደጋጋሚ ስለአፍራህ ከመስማቴ ብዛት አፍራህን እኔም ላፈቅራት ምንም አልቀረኝም። እውነቱን ለመናገር የዛን ጊዜ ክላስ ውስጥ ከነበርነው ሠላሳ ምናምን ወንዶች አስራ ምናምኑ በአፍራህ ፍቅር የተለከፈ ነበር፤ ሒሳብ አስተማሪያችን ጭምር። መቼም ሒሳብ አስተማሪያችን እያካፈሉም፣ እየደመሩም፣ እየቀነሱም፣ እያባዙም ሳያስቧት አይቀሩም። አንዳንዴ ቡዝዝ ብለው መላጣቸው ላይ ላብ ፊጭ ፊጭ እያለ ሲመለከቷት ያሳዝኑኝ ነበር። “ወይኔ ምነው ያችን አመዳም አግብቼ አምስት ልጅ ባልወለድኩ ኖሮ” እያሉ በሚስታቸው የሚቆጩ ነው የሚመስለኝ።

###

እኔና አል አሚን ወደ ቤት ስንሄድ አፍራህና ጓደኞቿን ከሩቅ በቀስታ ተከትለን ነው። አንድ ቀን ታዲያ አፍራህ ማስቲካ ገዝታ (ባናና ማስቲካ) ልጣጩን ጥላው ወደ ጓደኞቿ ተቀላቀለች። እኛ የማስቲካውን ልጣጭ የጣለችበት ቦታ ስንደርስ አል አሚን ተስገብግቦ ቢጫውን የማስቲካ መሸፈኛ ወረቀት አነሳው። የሆነ ከባድ ቅርስ ወድቆ ያገኘ ነበር የሚመስለው። ለራሴ ማመን እስከሚያቅተኝ ለሁለት ዓመት አካባቢ የማስቲካውን ልጣጭ በክብር፣ በታላቅ ክብር አስቀምጦት ነበር። ለእርሱ ብቻ በሚታይ ስውር ቀለም የአፍራህ ምስል የታተመበት እስኪመስለኝ።

አል አሚን እንዲሁ ሲሲቃይ ከረምት ገባ። አፍራህን ለሁለት ወራት መለየት ለአል አሚን የቁም ሞት ነበር። ሱስ ሆናበታለች። አፍራህ ዓለሙን ሁሉ አጨላልሞ በነፍሱ ሰማይ ብቻዋን የደመቀች ኮከብ ነበረች። ቢሆንም እንደለመደው በዝናብ ሳይቀር ከረንቦላ ቤት እየሄደ እዛው ቆሞ አፍራህን ስትወጣ ለማየት ይጣጣር ነበር። ለአስራ አምስት ቀናት ጠብቆ አላያትም፤ ሊያብድ ሆነ።

ታዲያ በመሀሉ በጣም የምንወዳቸው ሼህ ያሲን የሚባሉ ሰውዬ መንገድ ላይ አገኙኝ። የአል አሚን ቁርአን አስቀሪ ናቸው።

"አቡቹ ደህና ዋልክ?"

"ደህና ዋሉ ሸሃችን "

"አልሃምዱሊላሂ...ና እስቲ ወዲህ የማወጋህ ጉዳይ አለኝ" አሉና ከመንገዱ ወደ ዳር ወሰደው እንዲህ አሉኝ፣ "...ጓደኛህ አል አሚን ምን ነክቶት ነው ልጄ? ከቀልቡም አይደለም፤ ቁርአን ቤትም መምጣት ካቆመ ስንት ጊዜው፣ ...ተበላሽቷል ይሄ ልጅ! ጭራሽ ዛሬ እዛ ቁማር የሚጫወቱበት ቤት ቁሞ አየሁት። ጓደኛው ነህ፤ አትመክረውም? ኧረ ቀልቡ ደረቀ...።" ብለው ነገሩኝ። ለአል አሚን አዘንኩ። ማን ያውቃል የልጁን ጉዳት። የዋልንበት ቦታ ሁሉ ያለን እየመሰላቸው ስንቶች በዋልንበት ፈረጁን...

###

አል አሚን አንድ ቀን እየተጣደፈ ቤት መጣ። ከመቻኮሉ ብዛት ድመታችንን በሩ ሥር እንደተኛች ጀራቷን ረግጦ ካቅሟ በላይ አስጮኻት፤

"...አቡቹ...! አቡቹ...! አይገርምም የነአፍራህ ቤት ለካ በሩ እኔ በምቆምበት በኩል አይደለም፤ ... ከኋላ በኩል በዘይት ቤቱ ጋ ነው፤...በዛ በኩል ነው የምትወጣው... ሂሂሂ ተሸውጄ..." አለኝ፤ ሲያወራ በደስታ ፊቱ በርቶ ነበር። "...ዛሬ ባጋጣሚ ቤታቸ በኩል ስሄድ ከእናቷ ጋር ሆና ፊ....ት ለ...ፊት፤ እንደዚህና እንደዛ ...ብቃ ተያየን፤ ወ.....ላሂ አቡቹ ግጥምጥም ነው ያልነው፤ አሉዘቢላሂ ...ልሮጥ ነበር... ሂሂሂሂሂሂሂ" አለና ፍርፍር ብሎ ሳቀ። ድንገት ተነስቶ ቆመና ደግሞ "...እስኪ አየኝ! እንዲህ ሆኜ እኮ ነው ያየችኝ፤ አደብራለሁ እንዴ ...?" አለኝ። ሁለት እጆቹን ግራና ቀኝ እንደ ክንፍ ዘርግቶ አንዴ እኔን አንዴ ራሱን ቁልቁል እየተመለከተ። አሳዘነኝ። የአፍራህን ቅንጡ አለባበስ እና የአላሚንን የተንሸራፈፈ ሸራ ጫማ፣ ያረጀች እና የወየበች 'ቪ' ቅርፅ ቲሸርት በውስጤ እያሰብኩ፣

ኝረ አይደብርም!" አልኩት።

እንደ ሐሞን እየተፍነከነከ መጥቶ አጠገቤ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ። "...አይገርምም ከእናቷ ጋር ሆና በቃ እንደዚህ እና እንደዛ ፊት ለፊት...! እንዴት አምሮባታል አቡቹ ብታያት...! ወላሂ ያች የምታውቃት አፍራህ አይደለችም...! በቃ እንደዚህና እንደዛ እኮ ነው...!" እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ፤ ዓይኖቹ የደስታ፣ የሐዘን፣ የሐፍረት፣ የምኞት ብርሃን ይረጫሉ። ፊቱ ላይ ደስታ እንዳረበበት ልሸኘው ወጣሁ። ልንለያይ ስንል፣ "...አቡቹ ሁለት ብር አለህ እንዴ?" አለኝ እየፈራ። አል አሚን እንኳን ደፍሮ ብር መጠየቅ፣ ያዋሰውን ደብተሩን እንኳን መልሱልኝ ለማለት የሚፈራ ልጅ ነበር። ብር ስላልያዝኩ...ወደ ቤት ተመልሰን ከእናቴ ተቀብዬ ሰጠሁት። ደስ ብሎት ሄደ።

ቆይቼ ስሰማ በአዲሱ የአነአፍራህ በር በኩል አንድ ሻይ ቤት አለች፤ ሻይ ሃምሳ ሳንቲም ነው፤ በሰጠሁት ብር ሻይ እያዘዘ ቁጭ ብሎ አፍራህን ሲጠብቅ ነበር፤ አራቱንም ቀን ግን አላየትም። እናም ከረንቦላ ቤት አካባቢ ያገኘውን የአነአፍራህን ሰፈር ልጅ ጠይቆ አፍራህ አዲስ አበባ ለእረፍት እንደሄደችና ትምሕርት ሲያልቅ እንደምትመጣ አረዳው። ቅስሙ ተሰበረ። ቢሆንም አነአፍራህ ሰፈር መሄድ አላቆመም። በየቀኑ ያንን ሰፈር ሳይረግጥ አይውልም። ሸርፍ ተራ ትርምሱ፣ ግርግሩ፣ ጫት ተራው፣ መኪናው፣ የደሴ አንደኛ "ቀውጢ" ሰፈር...ይሄ ሁሉ ግርግር ግን ከአፍራህ አይበልጥም። አፍራህ ብቻዋን የአንድ ትምሕርት ቤት ወንዶች ነፍስ የተደረደረባት ገበያ አይደለች እንዴ ።

"እሷ ከሌለች ለምን ትሄዳለህ" እለዋለሁ፤

"እኔንጃ!" ነው መልሱ፤ ያሳዝነኛል !!

###

አንድ ቀን ደማሞ ቤት መጣና "አቡቹ ሥራ ልጀምር ነው" አለኝ፤ በደስታ ፍንከንክ ብሎ።

"የምን ሥራ" አልኩት፤

"አይሱዙ መኪና ላይ ረዳትነት"

"ትቀልዳለህ...!?"

"ወላሂ እውነቴን ነው። ከአዲስ አበባ ደሴ የሚመላለስ አይሱዙ ላይ ሥራ ልጀምር ነው። እናቴንም

ነግሬያት አሳምኛታለሁ። መኪናው ቅዳሜ ወደ አዲስ አበባ ይወጣል። አብሬው እሄዳለሁ። ብቻ ቀላል እኮ ነው ሥራው...።" ፊቱ ላይ ተስፋ ይንቀለቀላል። በቀሚሜ‍ጭን እጆቹ ሸራ ሲጎትት፣ የጎማ ብሶን ሲያጠብቅ አስብኩት፣ አልአሚን ትንታግ ተማሪ። ይሄ ፍቅር የሚሉት ነገር ግን ምናይነት ልክፍት ነው በእግዚአብሔር!!

###

አልአሚን ገና በመጀመሪያ ጉዞው ከመኪና ላይ ሲወርድ ወድቆ ግንባሩ ተፈንክቶና ከንዱ ተላልጦ መጣ። ሰው ሁሉ "እንኳን አላህ አተረፈህ!" እያለ አዘነለት። እንዲህ ካልተላላጡና ካልተፈነከቱ የልብን ስብራት፣ የመንፈስን መድቀቅ ዓይቶ የሚያስታምም የለም መቼም። እንዲህ አለኝ፤ አርሜ ፍራሹ ላይ እንደተኛ "አንተ... አፍራህ ያንን ሁሉ መንገድ አልፋ ነው አዲስ አበባ የሄደችው...? እነዛን ተራራዎች ዓይታቸዋለች...፤ ያንን ገደል እያየች ፈርታለች...፤ ደብረሲና ምሳ በልታለች፤ ቆሎም ገዝታ ሊሆን ይችላል...እ!! ጨለማ ዋሻ ውስጥ ስትገባ በፍርሃት ተንቀጥቅጣም ይሆናልኮ።" ኡፍፍፍፍ እንጀቴን በላው። ከላይ እንደኢቃ ተጭኖ አፍራህ ባለፈችበት መንገድ በማለፉ ምናባዊ ዳናዋን ተከትሎ ሲነጉድ ታየኝ። ሚስኪን አልአሚን !

ቀስ በቀስ አልአሚን ነገሮች ሁሉ ተቀላቀሉበት። አንድ ቀን ትምሕርት ቤት ሄደና ጭርር ያለው በር ላይ ያገኛቸውን የትምሕርት ቤታችን ጥበቃ ጋሽ ደምሴን፣"ትምሕርት መቼ ነው የሚጀመረው?" አላቸው፤

"ምን አውቄ ብለህ ልጄ" አሉት። ቀጠል አድረገው-ም "...የኔ ልጅ ኳስ ሲራገጥ ይውላል፣ አንተ ትምርት ናፍቆህ...የወለዱህ አባትና እናት ምንኛ ይኮሩ!! አሰይ!! አሰይ!!"

ትቷቸው ወደ ቤት ተመለሰ፤ በቃ መረጋጋት ኢቃተው፤ተወዛገበ።

###

8ኛ ክፍል በተመለሳይ ለአፍራህ ፍቅሩን ሳይነግራት በየቀኑ እያያት በዓይኖቹ ተስፋ ነፍሱን አፋፍቶ ኖረ። አንድ ቀን "ለአፍራህ ስጦታ ልሰጣት አስብኩ" አለኝ። ገረመኝ ...! ወይኔ ፍቅር ጉድለት ኢይገባው፣ ድህነት እያለሁ ሳለብ አልአሚን አንድ የሃምሳ ብርና ሦስት አስር አስር ብሮች ከኪሱ አውጥቶ አሳየኝ።

"ከየት አመጣኸው?"

"ለረመዳን መፍጠሪያ ሚሚ ጠርጌ ያጠራቀምኩት ነው"

እና ለአፍራህ ስጦታ ለመግዛት በድፍን ደሴ ስጦታ መሸጫ ቤት ዞርን። ለአፍራህ የሚሆን ስጦታ ጠፋ። ስንገዛ ስጦታው ብቻ አይደለም የጠፋው፤ ስጦታ መስጫ ወኔም ነበር። አሁንማ አፍራህን እኔም እንደ አልሚን ሆነኮ የምፈራት። ይሄው ወደ ፱ኛ ክፍል ስናልፍ አፍራህ ወደቀች። አል አሚን ደግሞ እቢን ጥሎ ማለፉን ጠላት አድርጎ ጠመደው።

ወይዘሮ ሲኒን ገባን ። ያንን ሰማያዊ ዩኒፎርም ለብሰን የጊያሳ ደረጃ ላይ ተጀነንበት፤ ተኮፈስንበት። በተለይ ያኔ ሊላኛው 'ሃይ ስኩል' (ሆጤ ይባላል) እዛ ይማሩ የነበሩ ልጆች በእኛ ይቀኑ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ሃሃሃ…በእርግጥ ከዛ ቀይ ሹራባቸው እና አረንጓዴ ካሸመሩ ሱሪያቸው ጋር ሲተያይ እኛ የሲኒን ተማሪዎች አምባሳደር ነበር የምንመስለው፤ የዛሬን አያርገውና። ስንኮፈስ ታዲያ ደረጃችንን እንደ ዶላር እንመነዝረዋለን። "የወይዘሮ ሰኒን ፱ኛ ክፍል የሆጤ 12ኛ ክፍል ጋር ሒሳቡ እኩል ነው።" እያልን ሃሃሃሃ እንደ ሹራባቸው ፊታቸው በብስጭት ይቀላል። ቢሆንም ምርጥ ጓደኞቻችን ነበሩ።

እኔ ልክ ወደ ፲ኛ ክፍል ሳልፍ ደሴን ለቀቅኩ፤ ውድ ጓደኛዬን ከነኮሮ ድቅሲቃሱ ብቻውን ትቼው። በቃ ከአል አሚን ጋር በዛው ተለያየን። ሁልጊዜም ትዝ ይለኝና ምን ሰይጣን እጄን እንደሚይዘው እንጃ ሰልክ እንኳን አልደውልለትም ። በቃ ተለያይተን ቀረን። ሲቆይ ትዝታውም እራሱም ደበዘዘ። በራሴ የሕይወት አዙሪት፣ በራሴ ጓደኞች ተከብቤ አልአሚን ምርጡን ጓደኛዬን ከነመኖሩም ረሳሁት። ሰው ወረተኛ ነው።

###

ወደ ደሴ የተመለስኩት ከአስር ዓመት በኋላ ነበር። የጓደኝነት መንፈሱ ከተማው መግቢያ በር ላይ ቆሞ የጠበቀኝ ይመስል ገና ሸዋ በር ስደርስ አልአሚን ከነናፍቆቱ አእምሮዬን ሞላው። በቀጣዩ ቀን እነ አልአሚን ቤት ስሄድ እናቱ አንደሞቱ፣ አል አሚንም የአይሱዙ ረዳት እንደሆነና ሸርፍ ተራ አካባቢ እንደማይጠፋ አንዲት ልጅ ነገረችኝ፤ የት ነው የማውቀው ብላ በትኩረት እየተመለከተችኝ። ድሮ አውቃታለሁ፤ የነአልአሚን ጎረቤት ነበረች።

ሸርፍ ተራ ሄድኩ። ትርምሱ ብሶበታል። አዳዲስ ሕንጻዎች ወረውታል። ባሊያን በሠራው ጅብሩክ በሚባለው የገበያ አዳራሽ ውስጥ ለውስጥ ብዙ አይሱዙ መኪናዎች የተደረደሩበት መንገድ ላይ አንዲት ትንሽ ሻይ ቤት በረንዳ ስደርስ ብዙ ወጣቶች ተሰብስበው ጫት እየቃሙ ሞቅ ያለ ወግ ይዘዋል። ጠጋ ብዬ አንዱን አልአሚን የሚባል ልጅ ያውቅ እንደሆነ ጠየቅኩት። ፊት ለፊት ያለ ሌላ ሻይ ቤት ጠቆመኝና ወደዛው አቀናሁ።

አልአሚንን አየሁት። ሜቱን በግራ እጁ እንደያዘ በፈገግታ ተቀበለኝ።

"እ.................ኔ አላምንም!! እኔ አላምንም...!! አቡቹ እንዳትሆን...እኔ አላምንም!! የእ......ላህ!!" ተቃቀፍን። አል አሚን እንደዛው ከስት እንዳለ ነው፣ ጥርሱ በሜት በልዟል፣ ሲያየኝ ትንሽ ተሳቀቀ። ተሳቀቅን። አል አሚን እንደዛው ... "የ......አላህ!!" ብሎ እንደገና አቅፎ ይስመኛል። ተያይዘን ትከሻና ትከሻዬን ይዞ ራቅ አድርጎ ያየኝና፣ "የ......አላህ!!" ብሎ እንደገና አቅፎ ይስመኛል። ተያይዘን እዛው ጅብሩክ ፎቅ ላይ ወዳለ ካፌ ገባን።

"እንዴት ነህ አሚ?" ስጠራው እንደዛ ነበር።

"አልሃምዱሊላ...!! ደህና ነህ አቡቹ ...? ማሻ አላህ!! አምሮብሃል!!" አለኝ ትከሻዬን በቀኙ ቸብ ቸብ እያደረገ። እኔ ስላማረብኝ ብቻ አቤት ፊቱ ላይ የነበረው ደስታ!! እኔም እንደዛው ሳልሆን አልቀረሁም የእኔ ግን ስላገኘሁት ነበር። ምሳ እየበላን የባጥ የቆጡን አወራን።

አልአሚን ትምህርቱን ከአስረኛ ክፍል አቋርጧል። እናቱን ለማስታመም ነበር ያቋረጠው። እናቱ አልተረፉም። ከዛ በኋላ መቀጠል አልፈለገም። እዛው ሸርፍ ተራ የድለላ ሥራ እየሠራ፣ ረዳትነትም እየሞከረ ቀልጦ ቀረ። ያ ፈጣንና አስገራሚ አእምሮ የነበረው አልአሚን በቃ ይኼው ሆነ እጣ ፋንታው...።

እየፈራሁ የማይቀረውን ጥያቄ አስከተልኩ፣

"እኔ የምልህ እ....አፍራህስ አለች?"

ዝምምምምምምምምም አለ አልአሚን። እናም ቅሬታ የተቀላቀለ ፈገግታውን እያሳየኝ "አልሃምዱሊላ! ሁለት ቆንጆ ልጆች ወልዳለች። እንዴት ያማምራሉ መሰለህ!" አለኝ። ግራ ገባኝ! ግራ መጋባቴን አይቶ ካለንበት ፎቅ ላይ አሻግሮ ሜፋ የሚታይ ፎቅ በእጁ በያዛት የሜት እንጨት እየጠቆመኝ፣ "...የሱ ነው...አንድ ሃብታም አግብታ ይሄን ፎቅ ሠርተው እየኖሩ ነው። ከስር ያለው ትልቅ ሱቅ የእሷ ነው፣ ሁልጊዜ አያታለሁ፣ ወላሂ...አምሮባታል...!" አለኝ።

ከነቅሬታ ፈገግታው አቀረቀረ። ከረዥም ዝምታ በኋላ የምግብ ጠረጴዛው ላስቲክ ላይ እንባው ጠብ ሲል አየሁት። አቀፌ ወደ ራሴ አስጠጋሁት፣ ከልቤ አዝኜ ነበር። እናም በእቅፌ እያለ ድምፁን ቀንሶ እንዲህ አለ፣ "አልሐምዱሊላሂ! አፍራህ ደህና ናት። አያታለሁ ዛሬም።"

# በሕይወት አንድ ጥግ

ትላንትና እሑድ እነሮዛ ቤት አንድ ሰውዬ መጣና በሩን አንኳኳ። እኔ፣ ሮዛና የሮዛ እናት ተመስጠን ፊልም እያየን ነበር። ሮዛ አብሮ አደግ ጎረቤቴ ናት። አስቴር ደግሞ እናቷ። ለእኔም እናቴ ማለት ነች ኧረ። የእኔና የሮዛ ፍቅር ሉብቻው ነው። ከሕፃንነታችን ጀምሮ ንጹህ የሆነ፣ ምንም የታዊ ከጃሎት ውል ያላለበት ፍቅር እንዳለን አገር መንደሩ ምስክር ነው። ለሀቴ ሮዚ ነው የምላት ። ታዲያ ዩኒቨርስቲ ቆይታ ለአረፍት መምጣቷ ነበር። የሚገረመው እናቴና የሮዛ እናት አስቴር የመረረ ጥል ያላቸው ኩርፈኞች ናቸው። ግን እኔም የእነሮዛ ቤት፣ ሮዛም የእኛ ቤት ልጆች ነን። ሰለእናቴ አስቴር ፊት ከተነሳ፣ "ውይ! ውይ! የሷን ነገር አታንሳብኝ፤ ,ጋኔል...! ምን ያረጋል እንዳንተ ዓይነት መልአክ ወለደች፤" ትለኛለች። እናቴን ለእኔ ታማልኛለች። "ቱ...! ሰው አይደለችምኮ!" ትላታለች ደጋግማ። በእናቴ የመጣብኝን ሰው ይቅር ብዬ አላውቅም። አስቴ ግን ስትረግማት እንኳን ምርቃት የሚመስለኝ ለምን እንደሆነ እንጃ።

ሮዛ እኛ ቤት ስትመጣ ደግሞ እናቴ በተራዋ ለሮዛ ስለእናቷ ከፋት፣ ,ጋኔልነት ትነግራታለች። "እናትሽ ... ምን እናት ናት! እች አቴ... የሰይጣን ቁራጭ! ከጥላዋ የተጣላች! ...እኔ ለሷ እንዲህ አልነበርኩም...!" እያለች። እኔና ሮዚ እናቶቻችንን ረስተን አብሮ ያለ ጓደኝነታችንን ቀጥለን አለን። የሮዚ አባት በሕይወት የሉም። "ችግር የለም አባባን እንካፈላለን" ትላለች አንዳንድ ቀን ስንቃለድ። አባባ የምትለው የእኔን አባት ነው። "እናቶቻችን አባባን እንዳይካፈሉ ብቻ" አላታለሁ ለሮዚ፤ "ባለጌ...! ስድ!" ብላ ትግል ትጀምረኛለች። ቀይ ፊቷ በሐፍረት ይቀላል።

ሮዛ ቆንጆ ናት፤ ግን ምኗ ነው ቆንጆ ቢባል አላውቅም። እንዲሁ ጠቅለል አድርገው ሲመለከቷት በጣም ቆንጆ፣ የምታሳሳ፣ ኑሮ ምቾት ያላት ልጅ ነች። አንዳንዴ ሰውን ሰንወድ ፍቅራችን የወደድነው ሰው ላይ ጎዶሎውን ሞልቶ ያሳየናል መሰል ሮዛ ለእኔ ጉድለት የላትም። አዎ ፍቅር በራሱ ሰልካካ

አፍንጫ፣ ሃር ፀጉር፣ አሎሎ ዓይን፣ ሙሉ ቁመት፣ በረዶ ጥርስ፣ ...ከንፈር ሳይሆን አይቀርም። ለነገሩ ሮዚን የሚጠይቃት ጎረምሳ ብዙንም ለሳቢነቷ ተጨማሪ ምስክር ነው።

ሮዛን የጠየቁትን ጎረምሶች እኔና ሮዚ የዕለት ውሎ መመዝገቢያችን ላይ እንመዘግብ ነበር። የሚገርመው ሮዛን የጠየቁትን ጎረምሶች እኔና ሮዚ የዕለት ውሎ መመዝገቢያችን ላይ እንመዘግብ ነበር። የሚገርመው ዳይሪያችን አንድ ነበረች፣ ሁለታችንም ውሏችንን የምንመዘግብባት። ለሮዛ የሚላክ የፍቅር ደብዳቤን አብረን ነው የምናነበው። እኔም ለሴት የምልከውን አብረን ጽፈን እናውቃለን። ታዲያ ሮዛ ብትሞት ለፍቅር አትሸነፍም፣ ትምሕርቷ ላይ አትደራደርም፤ ልቧ የገባም ወንድ የለም። "ወንዶች ጅል ይመስሉኛል..." ትላለች በተደጋጋሚ።

አባቷ እናቷ ላይ ያደረሰው በደል ሁሉ (ነፍሱን ይማረውና) መጥፎ ጠባሳ ጥሎባታል። አባቷ ሲበዛ መልከመልካም ሽቅርቅር ሰው ነበር። በዛ ላይ አይጠጣ፣ አያጨስ በጊዜ ነው ቤቱ የሚገባው ፤ በጊዜ ገብቶ ታዲያ ዋና ሰራው እናቷን አስቴርን መደብደብ ነበር። እነሮዚ ቤት አባቷ ካመሸ ደስታ ነበር ።እንዴ ! የአስቴርን ጥርሷን ሁሉ አውልቆት ወርቅ ጥርስ አስተክሎላታል። ሮዛ ልብ ውስጥ የነበረውን ወንድን የመሻት ተፈጥሯዊ ስሜት ጣን ነቅሎ ባዶውን ትቶታል። (አሁንም ነፍሱን ይማረውና፤ የሚምረው እንኳን አይመስለኝም...)

እና...ትላንትና እሁድ እነሮዛ ቤት አንድ ሰውዬ መጣና በሩን አንኳኳ። ቡና ተፈልቶ ተመስጠን ፊልም እያየን ነበር። እንዲጋጣሚ ለበሩ የምቀርበው እኔ ስለነበርኩ ተነስቼ በሩን ከፈትኩ። ከተወለደ ጀምሮ ዛሬ ገና የዘነጠ የሚመስል፣ ሙሉ ግራጫ ልብስ የለበሰ፣ ቀጫጫና ረዥም ሰውዬ በሩ ላይ እየተሽቆጠቆጠ ቆሟል። ሰውዬው ሙሉ ልብስ ቢለብሰም ለምን እንደሆነ እንጃ ሙሉ ልብስ የለበሰ አይመስልም። መቼም ሕይወት በሰዎች ዓይን ፊት ሲታነልህ እንኳን ሙሉ ልብስ፣ ሙሉ ብርጌድ አሰልፈህ ብትመጣ ግርማ ሞገስ የሚባል ነገር አይጠጋህም። ቅልል ትላለህ። "ቀትረ ቀላል" ትሆናለህ።

ሰላም አልኩት። እየተሽቆጠቆጠና ዳማከሴ እንደሚያሽ ሰው እጆቹን እርስ በእርስ እያፋተገ ሰላምታዬን ከወገቡ ጎብጦ መለሰልኝ። ከርዝመቱ እና ከእንቅስቃሴው ፍጥነት የተነሳ ለሰላምታ ከወገቡ ሲታጠፍ ከላይ ተምዘግዝጎ የመጣ የሆነ ወገቡ ላይ ተሰብሮ የሚወድቅ ባሕር ዛፍ ነበር የሚመስለው።

"ይ...ሄ የነሮዛ ቤት ነው አይደል...?" አለና፣ ራሱ መልሱን መለሰው። "አዎ ነው አውቀዋለሁ።" አነጋገ የሚርበተበትና ከአፉ የሚወጡት ቃላት በጠባብ በር እንደሚወጣ ብዙ ሕዝብ የሚገፋፉና የሚተሻሹ ይመስላሉ፤ ዝም ብዬ ስመለከተው።

"እ ... የሮዛ እናት ይኖራሉ ወይም አባቷ?" አለና መልስ ለራሱ፣ "አውቃለሁ አባቷ እንኳን በሕይወት የሉም...ግን እናቷ..." ተርበተበተ።

"እናቷ አለች" አልኩት።

"ልግባ ?" ሲል ገነት በር ላይ የቆምኩ መልአክ የሆንኩ እስኪመስለኝ ወደ ቤቱ ውስጥ በጉጉት ዓይኖቹን ልኮ ለማየት እየሞከረ ለመነኝ።

"ግባ..." ብዬ በሩን ለቀቅኩለት፤ ገባ። አረማመዱ የሆነ የሚጮኽ ዓይነት ነው። የሚራመድ ሳይሆን በአንድ እግሩ ብቻ የሚዘል ዓይነት ላይ ታች ያረገርጋል። እድሜው ሠላሳ አምስት ቢሆን ነው። የሮዛን እናት በሁለት እጁ ሰላም ብሎ ወደ ሮዛ ዞረ። ርሷንም በሁለት እጁ ሰላም አላት። ሲመለስ የእኔን እግር ረገጠና ተንገዳግዶ ጠረጴዛው ጫፍ ላይ ተቀምጦ የነበረውን ባዶ ሲኒ ከነበለው። ሲኒው ስር ቀርቶ የነበረው የረጋ የቡና ዝቃጭ ምንጣፉ ላይ ጥቁር ደም መስሎ ተረጨ። *ይሄ ሰው መርዶ ይዞ ነው እንዴ የመጣው? ምን ያደናብረዋል...?*

ከእስቱ ፊት ለፊት ተቀመጠ። ሁላችንም ምን እንደሚል ለመስማት ዓይን ዓይኑን እናየው ጀመር።

"እ ... ሰላም ነዎት ታዲያ እትዬ ...እስቴር?" አለ።

"እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ።" ፊቷ ላይ 'የት ይሆን የሚያውቀኝ' የሚል ግርታ ይታያል። በፈገግታ ልትሸፍነው ብትሞክርም አልተሳካላት።

"ልጆች ሰላም ናቸው...? ማለቴ ልጅዎት...? አዎ አንድ ልጅ ብቻ ነች ያለችም" አለ ወደ ሮዛ እየተ እድርጎ መልሶ እየተሸቆጠቆጠ ወደሚያፍተለትለው መዳፉ አቀረቀረ። ላቡ ቅንድቡ ላይ ችፍፍ ብሎ በግልፅ ይታያል ሲጨንቀው። ደግሞ ያጠናውን ነበር የሚናገረው፤ ያስታውቃል። ላቡን በመዳፉ እንዴ ሞዠቀውና መዳፉን እየተ አድርጎ በኮቱ እጅጌ እንደገና ግንባሩን ጠረገው።

"ደህና ናት!" አለች እስቱ፤ እናም ኮስተር ብላ አየችኝ። ትከሻዬን በቀስታ ወደ ላይ ሰበቅኩት። ያየችኝ "ማነው...?" ማለቷ ሲሆን እኔም በትከሻዬ ምላሰ "እኔ 'ጃ" አልኳት። ለትንሽ ደቂቃ እንግዳውም አቀርቅሮ፣ እኛም እንግዳው ላይ አፍጥጠን እንደቆየን እንግዳው ተናገረ።

"አንተ አብርሃም ነህ ... እዚህ ጎረቤት ያለኸው ልጅ አይደለህም እንዴ...?" አለኝ።

"እ ...አዎ!"

"ያው ሰሮዛ ወንድሟ ማለት ነህ ...! ማዘርም ጋር ትቀራረባለህ ያው ልጃቸው ማለት እኮ ነህ...!"

"አዎ ያው ልጅ ማለት ነው!" አለችው አስቴ።

"ጥሩ! ያው የቤተሰብ ጉዳይ ስለምናወራ ላረጋግጥ ብዬ ነው።" አለ ወደ አስቴ በፈገግታ እየተመለከተ። ፈገግታው ይጨንቃል። ከንፈሮቹ ወይ በደንብ አይከፈቱ፣ ወይ አይገጠሙ፣ እንዲሁ ሄድ መለስ እያሉ ይንቀጠቀጣሉ። በማጭድ የተጋጠ የሚመስል ፂሙ ቅራቅን አጥንታም ጉንጩ ላይ ዘርቶት በሽተኛ አስመስሎታል። ጥላሸት የተዘራበት አጥንታም ጉንጭ ! ደግሞ እኮ ሲያደርጉ አይቶ 'አ' ቅርፅ!! አፋ በፂሙ ተከብቦ ሲታይ በኮሽሽላ ዙሪያውን የታጠረ የደረቀ የውኃ ጉድጓድ ይመስላል። ወቾ ጉድ! ምን ሊል ይሆን...? ጭንቀት ገደለኝ።

"የመጣሁት ሌላ የሚመጣልኝ ሰው ስለሌለ ነው። ላቀው እባላለሁ..." አለና ድንገት ቆሞ አስቴን እጇን ጨበጣት። እኔንና ሮዛን ግን ረሳን። "...እ...ያው የመጣሁት መጥቼ መናገር ስላለብኝ እና ...' ስልኩ ጮኸች። ልክ እንደ አይጥ ነበር ፂው ፂው እያለች የጮኸችው...። ገና ሳያወጣት ስልኳን "ቀድሪ ቀላል" መሆኗን አውቄያታለሁ። እጁን እስከክንዱ ሱሪው ኪስ ውስጥ ከተተና ዙሪያዋን በፕላስቲክ መቀነት የተተበተበች ቀይ ስልክ አወጣ (ይሄው እንዳልኳት ናት፤ ካልኳትም ትብሳለች)። ስልኳን ከኪሱ ሲያወጣት ጩኸቷ ተቋረጠ። የሆነ ነገሯ ኪሱ ውስጥ ስለቀረ እንደገና ኪሱን ፈትሾ ከዳኗኛ ባትሪዋን አወጣ። ተቢታትና ነበር የወጣችው። በጥንቃቄ ገጣጠመና ኮቱ ኪስ ውስጥ አስቀምጦ ወሬውን ቀጠለ።

"...እና የመጣሁት መጥቼ እርስዎን ለማግኘት ነበር። ያው አግኝቼዎታለሁ" ብሎ ፈገግ አለ። አስቴን እንዳገኛት ስራሱ አላመነም መሰል።

"አዎ አግኝተኸኛል...፣ ከየት ነው ግን የመጣኸው? እንደው ዘነጋሁህ መሰል፣ አላወቅኩህም።" አለች በጨዋነት።

"ይ አልዘነጉኝም ...። ድሮም አያውቁኝምኮ" አለ።

እንደዛ ነው? ...እምምም ታዲያ እኔን እንዴት አወቅከኝ?"

ዙቤይዳ

"አላወቅኩትም... ያው ልተዋወቅዎት ነው የመጣሁት።" እልሄን ነበር ያስጨረሰኝ፣ "...ኤጭጭ ወደዚያ! ማን እንደሆንክ ተናገር" ማለት አምሮኝ ነበር። እግዜር ይደለት መንዛዛቱን ቀጠለው።

"ሰው እኮ ደፍሮ ካልተዋወቀ መቼስ..."

"ልክ ነው" አለች እስቱ እንዲናገር ለማደፋፈር እንጂ ያላለቀ ዓረፍተ ነገር መቼም ቢሆን ልክ ሆኖ አያውቅም።

"የመጣሁት ... ለዚህ ነው እኔም"

"ለምን?" አለች እስቱ ኀርሚት።

"ያው ለመተዋወቅና ከተዋወቅን በኋላ አንዳንድ ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ለመነጋገር።"

"ይሄው ተዋወቅን ! እስቲ የመጣህበትን ንገረኝ" እስቱ ትንሽ ኮስተር ያለች መሰለኝ።

"የመጣሁት ያው ሮዛን ... ማለቴ ልጅዎትን ሮዛን ላገባት ስለፈለግኩ እርስዎ እንዲፈቅዱልኝ ነው...! እባክዎትን እማማ እስቴር..." ብሎ ተንደርድሮ እስቱ እግር ስር ተደፋ። ቀስ ብዬ ወደ ሮዛ ዞርኩ። ሶፋ ላይ ሳይሆን ኤሌክትሪክ ወንበር ላይ እንዳስቀመጡት የሞት ፍርደኛ ደርቃ ቀርታለች። ሙልት ያሉ ቀይ ጉንጮቿ ገረጥተው ዓይኗ ባዶ ጠርሙስ መስሏል።

"እረ ተነስ! ተነስ የኔ ልጅ! " አለች እስቱ ምንም ምንም እንዳልጣማት ታስታውቃለች። ልጁ ተነስቶ ቆመና፣ "እሺ አሉኝ ማዘር...?" ሲል በጉጉት ጠየቀ።

"አክብረኸኝ ስለመጣህ ተባረክ...! ግን አሁን ዘመኑ ሰልጥኗል... ማነህ...!"

"ላቀው!" አለ።

"ራሳችሁ ተነጋገሩ እዛው" ብላ ሮዚን አጋፈጠቻት።

ሮዚ በርግጋ ተነሳች፣ ከዛም "ምናይነቱ ነው!" ብላ ወደ ጓዳ ገባች።

እስቱ ግራ ተጋብታ እንዲህ አለችው፣ "እንደው ውጉም ባሕሉም እንዲህ አልነበረም። ቢጠፋ ቢጠፋ ያንተ ቢጤ እንኳን አንድ ሁለት ሰው ይላካል። ስተት ተብሎ ነውር እኮ ነው...እ።"

"አስቤ ነበር..." አለ አንገቱን ደፍቶ፤ "ማን ሰው አጣሁ። ዘመድም የለኝም...፤ እና ደግሞ የምነግራት ሰዎች ሁሉ 'ለራስህ ሳትሆን ሚስት...፣ ጠግበህ ሳትበላ ሌላ እዳ መጨመር' እያሉ አሸማቀቁኝ። አስቤ ነበር፤ ሰው የለኝም። እንጅማ አስቤ ነበር ... ሮዛን ስለወደድኳት ነው...፣ እንደው እሺ ቢሉኝ ቀጥሎ ምን እባቴ አደርግ እንደነበር እንጃ። ራሴ እሷን በማሰብ ከሚፈነዳ እንዲህ ነገሩን አፈንድቼ ይለይለት ብዬ ነው። ሮዛን እወዳታለሁ። ሮዛ ቀይ ቆንጆ ልጅ ናት...፤ ሰው ለራሱ ሽማግሌ ቢሆን አልኩ...፤ ትክክለኛው ሽማግሌ እኔ ነኝ። የሮዛን ፍቅር ምን ያህል እንዳለምኩት የሚያውቅ ሽማግሌ ማን አለ...? በሚድርባት የፈራረሰች ቤት ብርሃን የዘራችው ማናት...? ሮዛ ናት...፤ ሮዛ የእርስዎ ልጅ፣ ማንም እንደ ሰው በማያየኝ አገር፣ እንደ ጥራጊ በተጣልኩበት መንደር ሰው መሆኔን ለልቤ የነገረው የሮዛ ፍቅር ነው...፤ ሮዛ የእርስዎ ልጅ...!" ወደ በሩ መንገድ ጀመረ። አነጋገሩ ተረጋግቶ ነበር - ፍርሀቱ ሁሉ ጠፍቶ።

"...መቼስ የፈጣሪ ትልቅነት፣ ይሄን ፍቅር ሰው እንኳን ቀና ብዬ የማላይ ትንሽ ሰው ላይ ጥሎት ሰው ፊት አቆመኝ። እንደው ሰው ልሁን ብዬ እንጂ እሱስ እሺ ቢሉኝም ሮዛን የት እንደምወስዳት እንጃ..። ሮዛ እኮ...! አራት ዓመት ከልጅነቷ ጀምሮ፣ አስራ ሁለተኛ ክፍል እስክትሆን...፤ ዩኒቨርስቲ እስክትገባ.. ሰወዳት፣ ሰወዳት፣ ሰወዳት፣ ከረምኩ። አልተማርኩም፣ እንደው የእግዜር ነገር እኔ ላይ ይሄን ፍቅር ቢጥለው እኔው ሽማግሌ ሆንኩ። ሆድህን ሳትሞላ ይላሉ- ፍቅር ከሆድ በተረፈ ነገር ይመጣ ይመስል ...ይሄው ሆድህ አልሞላም ብሎ መኝ ተወኝ ። ለራስህ ሳትሆን ይላሉ - ምንድነው እኔ እኔ ማለት...? ለራስ ከሆኑ በኋላ በተረፈው ይፈቀራል እንዴ...? ራስን ጥሎ እንጂ ለሌላው መኖር...! ሮዛን...! የእርስዎን ልጅ ወድጄ ሰንት ዓመት ሙሉ...! ዘመድ የለኝም...! ሮዛን እያሰብኩ ሺ አልፍ ሆኜ ኖርኩ...። ማንም አይደለሁም...። ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ይባል እንጂ ቅሉ፣ ሰለራሴ አብዝቼም አሳንሼም የምቆርሰው የሌለኝ፣ ኑሮ ቆራርሶ እዚህ ያደረሰኝ ከንቱ ነኝ። ሮዛ የአንቱ ልጅ ግን በሕይወቴ ውስጥ ትልቋ ቁራሽ፣ ትልቅ ድርሻዬ ነበረች ! ሮዛ የአንቱ ልጅ...

"...ሳያት እኮ ልቤ ውስጥ ገነት ይፈጠራል። ፍቅሯ እንደ እግዜር የገነቱ አስተዳዳሪ... መንገዱ ምንድነው የሚነጠፍበት...? ሮዛ ስታልፍ ቢጫ ይሆናል፤ ሮዛ ስትስቅ በደስታ አለቅሳለሁ...፤ እጆቿ እንደሩቅ አገር አየችኝ ... ዓይኖቿ አዩኝ ... ቢያንስ የምታይ ሰው ነኝ፤ በከፋም ይሁን በደግ መታየት መኖርን ነው የሚገልፀው። ሮዛ አየችኝ። ዓይኖቿ ከለመናር ፈውሰውኝ ይሄው አለሁ...!" አለና በሐሴት ፈገግ አለ። ከንፈሮቹ አልተንቀጠቀጡም - በነፃነት ፈገገ!

ከተቀመጠበት ተነሳና ከቤት ወጣ። ሲወጣ የበሩ ጉበን እና ቱን ገጨው። ደህና ዋሉም አላለ። ተከትዬው ወጣሁና በሩ ላይ ቆሜ በግርምት አየሁት። ...የማይሰማ ነገር እያነበነበ፣ በጣም የሰፋው ሱሪው፣ እጅግ በጣም የሰፋበት ኮቱ እየተርገበገቡ፣ እየተውለበለቡ - ሆድ የባሰው አገር ባንዲራ መሰለው፣ ወደ ታች ወረደ፣ እየተጣደፈ። ከሩቅ ሳየው አሳዘነኝ። ከዛ በኋላ እስከ ማታ እኔም፣ ሮዛም፣ እስቱም ስለዚህ ጉዳይ አንዲትም ነገር ትንፍሽ አላልንም። በየፊናችን እያሰብነው እንደነበር ግን አያጠየይቅም።

ማታ ወደ ቤቱ ስሄድ ሮዚ ሸኘችኝ። እንደሁሉ ጊዜው እኛ ግቢ በር ላይ ቆመን ከላይ ጨረቃ ከታች የነፍሳት ሲርሲርታ እና የንፋሱ ፉጨት ባየለበት ጨለማ ውስጥ ሮዛ ለስለስ ባለ ድምፅ እንዲህ አለችኝ፣ “አብርሽ የቅድሙ ሰውዬ አሳዘነኝ፤ ሙሉ ቀን ሌላ ነገር ማሰብ አልቻልኩም...”

“እኔስ ብትይ!”

“ግን እዚህ ሰፈር አይተኸው ታውቃለህ እንዴ?”

“እኔ'ጃ አላስታወስኩትም”

ዝምምምምምምምምምምምምምምምምምምምምም ዛፎች ይንኮሻኮሻሉ፣ ነፍሳት ሲር ሲር ፂው ፂው ይላሉ...፤ ጨረቃ እንደ ትልቅ የቅቤ እንክብክብ ወዛም ብርሃኗ በእኛ ላይ እየቀለጠ ፍሰስስ ይላል...፤ የጨለማ ድርቀቱን እያረሰረሰ...

“ቁመቱ ደግሞ ሲያምር!” አለች ሮዛ ልስልስ ባለ እንደ ጨረቃ በሚቀልጥ ድምፅ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድ ስታደንቅ ሰማሁ።

# እንዴት መርፌ ስንቱን ቀዳዳ ትስፋው?

ዙቤይዳ ስልክ ደወለችና "አብርሽ..." አለችኝ፤ ድምጿ ውስጥ ምቾት አለ - አይጎረብጥም። የዙቤይዳ ድምፅ ከዙቤይዳ ቆዳ የተቀመረ ይመስለኛል፤ ቆዳዋ ደግሞ ድምጿን የለበሰ - ሁለቱም ነፍሴን ይለሰልሱኛል።

"ወይዬ የኔ ቆንጆ...! የኔ ማር...! የኔ ለስላሳ...! የኔ ሐር...! የኔ ፍቅር....የኔ ደስታ...! የኔ ...ሳቅ! ...የኔ ፈሺታ !...የኔ ሐሴት !የኔ...

ዙቢይዳ ዝም ብላ ስታዳምጠኝ ቆየችና (ዝምታዋ እስክርቢቶና ወረቀት ይዛ ያልኩትን ሁሉ የምትመዘግብ ነበር የሚያስመስላት)ረጋ ብላ "አባባ ሊያናግሩህ ይፈልጋሉ" አለችኝ።

"ምን...?" ብዬ በድንጋጤ ዝም አልኩ - የጨው አምድ ! ይሄማ ቀልድ ነው ። "ዜድ አንች ደግሞ በማይቀለደው ትቀልጃለሽ"

"ወላሂ እየቀለድኩ አይደለም አብርሽ" አለችኝ። ረዥም ዝምታ መሃላችን ሰፈነ።

"ምነው ድምፅህ ጠፋ...? 'አንበሳ እገድላለሁ የሚለው ባልሽ...ቅጠል ሲንኮሻኮሽ ገደል ገባልሽ' ሂሂሂሂ..." ብላ በሚያምር ሳቋ ተቅጨለጨለች። ይሄው ናት የእኔ ዙቢይዳ፤ በየትኛውም አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ወይ ፍንክች ከሳቋ! የተረጋጋች ! እርጋታዋ ደግሞ የሚያረጋጋ ደግሞ እሷ ላይ ብቻ አይቆምም ይተላለፋል ...እንደሽቶ ከእርሷ ላይ ይነሳና በመረጋጋት ጠረኑ ነፍስን ያውዳል።

"አባባማ ቅጠል ብቻ አይደሉም ትቀልጃለሽ እንዴ...፤ ግንድ ነው የወደቀብኝ" አልኳት። አባባ የምትላቸው አባቷን ጋሽ ጀማልን ነው ። በጣም የሚገርመኝና የሚደንቀኝ ነገር የዙቢይዳ እህትና

ወንድሞች በሙሉ አባታቸውን "አንቱ" እያሉ ነው የሚጠሯቸው ! አንድ ቀን ታዲያ ዙቤይዳን ጠየቅኳት "ዜድዬ እንዴት አባትሽን አንቱ ትያለሽ ?"

"ትልቅ እህቴ ዘሐራ አንቱ ስትል ሰማሁ፣ በዛው ቀጠልኩ። የእኔ ታናናሾችም አንቱ ነው እኮ የሚሏቸው፤" አለችኝ ! ትልቅ እህቷ ዘሐራ ጋር (የዛሬን አያድርገውና) እንግባባ ስለነበር ዘሐራንም ጠየቅኳት፣ "ዘሐራ አባት አንቱ ይባላል እንዴ?"

"ትልቅ ወንድሞችን አንዋር አንቱ እያለ ይጠራቸው ስለነበር በዛው ለመድኩ።" አለችኝ...፤ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አንቱታ። በጣም የሚያስቀው ታዲያ የመጀመሪያው የአንቱታው ጀማሪ ትልቁ ልጅ ኡስማን ሲሆን የጋሽ ጀማል ልጅ ሳይሆን ገና ትዳር እንደመሠረቱ ልጅ ሳይወልዱ በፊት አብሯቸው መኖር የጀመረ የጓደኛቸው ልጅ ነበር። ከዛ በኋላ የተወለዱት ሁሉ አባታቸውን አንቱ እያሉ ቀጠሉ።

የዙቤይዳ አባት ጋሽ ጀማል የተፈሩ፣ የተከበሩ የአገር ሽማግሌ፣ በዛ ላይ አዱኒያ ሞልቶ የተልከሰከሰላቸው ሀብታም ናቸው ! በዓመቱ ለረመዳን ዝሆን የሚያካክሉ በሬዎች እያረዱ ሰደቃ ያበላሉ፣ ሚስኪኖችን ያስፈጥራሉ። ቤታቸው አስፈሪ ግርማ ሞገስ አለው። ወደ ላይ የአጥሩ ግንብ ርዝመት፣ እንኳን ተራማጅ ፍጥረት በራሪም አሰዋፍት የሚዘሉት አይመስሉም። በዛ ላይ አጥሩ ጫፍ ላይ የተጠማዘዘው ሽቦ ... አንዳንዴ የነዙቤይዳን አጥር ስመለከት ከመኖሪያ ቤትነት ይልቅ በሥሩት ወንጀል የዘላለም እስራት የተፈረደባቸው አደገኛ እስረኞች የታጎሩበት እስር ቤት ይመስለኛል።

ታዲያ ፍቅር የሚባል ጉድ የሚያሻግረው ወንዝ፣ የማያዘልለው ከፍታ የለምና መሰላል ሆኖ ይሄን አጥር አዘለለኝ። ምን ማዘለል ብቻ፣ ግቢውን አልፌ፣ የዋናውን ቤት በር በርግጄ እነዙቤይዳ ሳሎን እዛ የሚያምር ምንጣፍ ላይ 'ከነጫማዬ' ሰቆም ቤተሰቡ ተበጣበጠ። ዙቤይዳ የምትባለውን ወርቅ የሆነች ልጃቸውን አፍቅሬ "አገባታለሁ" አልኩ ! ዙቤይዳም ብትሆን የምትይዝ የምትጨብጠውን እስከታጣ አፍቅራኝ ነበር። ግን ዙቤይዳ እንደ እኔ ማሬ፣ ፍቅሬ ጅኒጃንካ አትልም...፤ዝም ብላ ዓለምን በሚያስረሱ ውብ ዓይኖቿ የፍቅር ጅረት እያንረፈች ነፍሴን በሐሴት ታረሰርሰዋለች...።

ዶሮ እንቁላሏን አቅፋ በሙቀቷ ጫጩቶቿን እንደምታስፈለፍል ዙቤይዳም በሩህሩህና ደግ ፀባይ እቅፍ አድርጋኝ ከዚህ ዓለም በሻገተና በከፋት በበሸቀጠ ቅርፊት ያተጠቀለልኩ እኔን በፍቅር ትወልደኛለች። በዓይኗ አቅፍ አድርጋ ታሞቀኛለች። 'ዓይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው' ሲሏችሁ አትስሙ። የዙቤይዳ ዓይን የተፈጠረው እኔን ብቻ ለማየት ነው። አቤት ዙቤይዳ ማየት ስትችልበት ! አስተያየቷ ቅኔ አለው። አስተያየቷ ጀግና ያደርገኛል...፤ አስተያየቷ ሁሉ ነገሯን እንደሰጠችኝ የሚያረጋግጥ

የብርሃን ፊርማ ነው! ዙቤይዳን በሙሉ ልቤ አፈቅራታለሁ።

እናቷ ቢመክሯት፣ አባቷ ቢዝቱና ቢቆጡ፣ ወንድሞቿ በቀን ሁለት ጊዜ (ጧትና ማታ) ቢሸልሉ ቢፎክሩ...ዙቤይዳ የኔ የፍቅር ሰው ወይ ፍንክች !! "አብርሽን እወደዋለሁ! ወላሂ እወደዋለሁ !" ብላቸው አረፍ።

ወንድሟ የዙቤይዳ ነገር አልሆን ቢለው እኔጋ መጣና፣ "ለቀቅ አድርጋት" አለኝ።

"ዜድን እወዳታለሁ! እግዚአብሔርን እወዳታለሁ!" አልኩታ። በዛ በዚህ በመሐላ የታጠረ ፍቅር። በየእምነታችን ለአንድ ፍቅር አምላኮቻችንን ምስክር ጠርተን ወይ ፍንክች አልን። ቤተሰቦቿ ግራ ቢገባቸው ሳይመርቁንም፣ ሳይረግሙንም ግራ እንደገባቸው በቆሙበት እኛም ፍቅራችንን ዓይናቸው ስር ቀጠልን።

ይሄ የዙቤይዳ እኔን ማፍቀሯና ፍቅሯንም አፍ አውጥታ መናገሯ እነዙቤይዳ ቤት ታላቅ ታሪካዊ ድፍረት ተደርጎ ተመዘገበ። የቅድም ቅድም ቅድም አያቶቿ ሁሉ ይሄን ድፍረት ቢሰሙ፣ መቃብራቸውን እየፈነቃቀሉ ተነስተው ሃዘን ይቀመጡ ነበር ። እንደ ቤተሰቦቿ አባባል።

"ይሄ አብርሃም የሚባል ልጅ ፣ወይ አንድ ነገር አስነክቷታል ወይም እህታችንን ኢብሊስ ተጠግቷታል" እለ አሉ ወንድሟ ... ራሷ ዙቤይዳ ናት የነገረችኝ።

"ኢብሊስ ምንድን ነው ዜዮዬ?" አልኳት። ዙቤይዳን ስሟን ሳቀናጣው ዜድ አደርገዋለሁ።

"ኢብሊስማ የሸይጧን አለቃ ነገር ነው" አለችና ከት ብላ ሳቀች።

"አሁንስ ወንድምሽ አበዛው" ወይ አንቺ ትርጉሙን አሳስተሽዋል ...ወይ ወንድምሽ ነገር ፈልጎኛል እንዴ .... አሁን ለኔ አለቃነ.. ፣ ትቶ ምናለ ተራ ሰይጣን ቢያደርገኝ...።"

"ሂሂሂሂሂሂ የኔ ቆንጆ ! ተራ ሰይጣንማ ብትሆን እንዲህ በፍቅር አታሳብደኝም" ብላ በፍቅሯ ቃሳብደኝና ...በሆነ በምወደው አስተያየት ዓይኖቿን ጣል ታደርግብኛለች። ባዮችኝ ቁጥር የሆነ ማዕረግ የተጨመረልኝ ይመስለኛል። የኔ ማር እንዴት እንደማፈቅራት እኮ ! ስትስቅ ብዙ ቀን ምናን እንደምሰማት ታውቃላችሁ? - ጥርሷን !! ያው ጥርሷን ስሜ ስመሰስ እግረ መንገዴን ከንፈሯንም መዘየሬ አይቀርም ታዲያ !

እውነቱን ለመናገር ለዙቤይዳ ነፍስህን ስጥ ብባል እሰጣለሁ…፤አሳሳላታለሁ። ሰው ሲያያት የምታልቅብኝ ነው የሚመስለኝ። እንደ ጣፋጭ ከረሜላ ስሟ አፌ ውስጥ ሲሟሟ ይሰማኛል። ፈሳሹ በጉሮሮዬ እኖርን ልቤን ሁሉ አረስርሶ እስከ እግር ጥፍሬ ውስጤን ሲያጣፍጠው ይታወቀኛል ! እኔ ራሴ ትልቅ ጣፋጭ የሆንኩ ይመስለኛል…፤ንግግሬ ሲጣፍጥ ለራሴ ይሰማኛል !! ዙቤዳ ስሟ ከፊደላት አይደለም የተገፈው … 'አግቹዳርስደፈሬተገፊዴየ' ከሚባል በገነት ከሚገኝ ፍሬ ጭማቂ ነው ተቀምሞ የተሰራው። ይሄ ፍሬ መልአክቶች ለዓመት በዓል የሚመገቡት ጣፋጭ ፍሬ ነው…፤ ቅርፁ የብርቱካን ዓይነት ሆኖ ልጣጩ ከብርሃን የሚሠራ ! እሰይ!! ዙቤይዳዬን እንዲህ ሳደንቃት ሳሞግሳት ባይውጣልኝም ደስ ይለኛል! ይገባታል ! የኔ ውብ !

ዙቤይዳ አገሬን ትመስለኛለች፣ እትብቴ የተቀበረባት አገሬ፤ ፈገግታዋ ባንዲራዬ፣ ዓይኗ መከላከያ ሠራዊቴ፣ ብቸኝነት የሚባል ጠላቴን እያባይቶ የደስታ ባንዲራዬን በልቤ ግዛት ላይ ከፍ አድርጎ የሚያውለበልብ…። ፍቅሯ በምድር የተደበቀ ነዳጅ እና የከበረ ድንጋይ፣ ታማኝነቷ የአገር ሚስጥር…፤ ለየዙሪያዋን ድንበር ካለ እኔ ካለ ልጇ ፈቃድ ማንም የማያልፈው…፣ እኔ ግን የምድህበት፣ዳዴ የምልበት፣ የምቦርቅበት፤ለወግ ለማዕረግ የምበቃበት ምድሬ…ዙቤይዳ አገሬ ናት !

የትኛውንም የመኖሪያ ቤት አጥር ከውጭ ወደ ውስጥ መዘለል ይከብዳል። ከውስጥ ፍቅር ገፍቶት ለሚወጣ ግን ቀላል ነው። ዙቤይዳ ከታላቁ ቤታቸው እየወጣች ለሁለት ዓመታት ዓለማችንን ቀጭተናል። ዓለማችን መተያየት ነው…፤ ዓለማችን መነካካት ነው…፤ዓለማችን እኔ እሷ አጠገብ እሷም እኔ አጠገብ መቀመጣችን ነው። ያ ጊዜ ማንም ምንም የማይልብን ጊዜ ስለነበር ለእኛ ሰርግና ምላሽ ሆኖልን ነበር።

ፍቅራችን ሲጀምር ቤተሰቦቿ ያን ያህል አላሳሰባቸውም። ሲደጋገምም ልጃቸውን አሜዋች ያገኙ መስሏቸው ወንድሞቿ እያምበዛም ፊታቸውን አላጠቆሩብንም ነበር። እንደውም ወንድሞቿ ወደ ሱቃቸው ብቅ ስል በወዳጅነት ያስተናግዱኝ ነበር! ሲቆይ እህቷ ዘሐራ ዓይነውሃዬ እንዳላማራት ለዙቤይዳ ነገረቻት፤ (ዓይነውሃ ምንድነው ግን…?) በጣም ሲቆይ ያበጠው ፈነዳ … ቡምምምምምምምምምምምም። ዙቤይዳ ጋር ሱቃቸው ጎራ ብዬ እያወራን ስንሜውት ቆየንና ልወጣ ስነሳ ያው ሁልጊዜ እንደምናደርገው ከንፈሯን ሳምኳት። እቤት የዙቤይዳን ከንፈር መሳም…የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ መሳም ነበር ለእኔ …፤ ይነዝራል፣ ያንዘረዝራል፤ የሆነ በሰውነቴ የሚል ነገር ሁሉ አእምሮ ውስጥ ይፈጥራል…። ይሄን ከንፈሯን ከምኑ እንደሠራው እንጃ!

እንግዲህ ልክ ዘብይዳን ስስማትና የዙቤይዳ ታላቅ እህት ዘሐራ ወደ ሱቁ ስትገባ እንደ ሒሳብ ቀመር ልክ መጣ ! ተገጣጠምን !! እህቷ በጓይና በብረቱ ስንሳሳም ስታየን በብረት ዱላ እናቷን የነረቷት ይመስል ደርቃ ቀረች። ዘሐራ የዙቤይዳ እህት ቢቃ ያረቀች። እንደው ድንጋጤዋን ስመለከተዉ ድንገት ሳታስበው እሷን የሳምኳት እንጂ እህቷን ስስማት ያጋጠማት አትመስልም ... አደራረሻ ላዩ ሰው እንደገና ነፍስ ዘርታ ትመለሳለች ለማለት ይከብደዋል። ጦርነቱ ተጀመረ!! ከዛን ቀን ጀምሮ ቤተሰቡ በሙሉ ሐሳቡ፣ በሙሉ ሐብቱ ሙሉ ዘመዱ (የሞቱትንም ሳይቀር እያስነሳ...) እኔና ዘብይዳ ላይ አሰለፈ። እኔና ዜድዬ ደግሞ የማይታየው የእሳት ሰረገላ አገሩን ሁሉ ከብቦ እኛን ሲጠብቅ ይታየን ነበርና ማንንም አንፈራም ነበር...ፍቅር !!

"ድሮም እዚህ ሱቅ ሲልከሰከስ አላማረኝም ነበር" አለች ዘሐራ። ዘር ቆጠራው ተጧጧፈ፣ "በዘራችን እንዲህ ዓይነት ወርደት ቅሌት..." እየተባለ ! የአያታቸው ጨዋነት፣ የእናታቸው ትሁትነትና የተመሰገነ ባህሪ፣ የአክስቶቻቸውና የአክስቶቻቸው ልጆች የልጅ ልጆች ስመ መልካምነት ተነሳ ተጣለ። ይሄ ሁሉ የታሪክ ብራና የተዘረጋው በዘር ማንዘራችን ሐጢያት የፈፀመ የለምና ሐጢያተኛዋ ዙቤይዳ ትወጊ፣ ትሰቀል ለማለት አልነበረም -እኔ ለዙቤይዳ እንደማልመጥናት ለማሳመን እንጂ። ገዛም ብሰው ደከሙ እንጂ እኔስ የገረመኝ ምኑ ሆነና፣ ዜድዬን አልመጥናትም ግን ትወደኛለች። እንግዲህ እንኳን አይ ቅድም እያት እስከሰው ዘር ጅማሬ ወደ ኋላ ቢቆጥሩ እኔ ምን ላድርግ - ወደድኳታ !

የእኔና ዙቤይዳን ግንኙነት በመጥፎ ከሚስሉት ሰዎች መካከል ቀንደኛው የዙቤይዳ ወንድሞቿ ጋር ጓደኛ የሆነ ነቢል የሚባል ልጅ ነበር። ነቢል በጣም የሚያሳፍር ባህሪ ያለው ልጅ ነበር ! ሥራ አይሠራም፤ መርካቶ ለመርካቶ እየዞረ ለሀብታም ይላላካል፤ ያው መላላኩን 'ሥራ' ይለዋል። ለዙቤይዳ አባትና ወንድሞችም በዚሁ መላላኩ ቤተሰብ ለመሆን በቅቷል ! ታዲያ ገና ሳያውቀኝ ስሜን በማጥፋት ሥራ ተጠመደ ...።

አንድ ቀን ቤተሰቡ በዙቤይዳ ጉዳይ ሳሎኑን ሞልቶ ሲታመስ ይሄው ነቢል መርዙን ረጨ፣ "አብርሃም የሚባለው ልጅ ጫት ቤት ለጫት ቤት፣ መጠጥ ቤት ለመጠጥ ቤት የሚዞር ሱሰኛ ነው እህታችሁ አጠገብ ድርሽ እንዳይል አንድ ነገር ማድረግ አለብን።" አለ ! ይታያችሁ ዙቤይዳ እዛው ፊቱ ተቀምጣ እኮ ነው እንዲህ የሚዘባርቀው። እኔ የዜድ ንብረት ነኝ...፤ ባለቤቱ ፊት ስለማያውቀው ንብረት ይዘባርቃል...። የዜድ ፊት ቲማቲም እንደመሰለ እንኳን አልታዘበም ...። አውቃለሁ ስሜ በክፉ ሲነሳ ፊቷ እንዴት እንደሚቀየር።

እንግዲህ ይሄ ልጅ…ከባለቤቷ የበለጠ አውቃለሁ ብሎ ቡዳ ሲሆን ምን ይባላል? 'እህታችንን ሲል "ማን ቢወልድ ማን…" ትላለች ዙቤይዳ በሆዷ…፤ እኛና ዜድ ነቢል ዙቤይዳን እንደሚከጅላት ጠንቅቀን እናውቃለን። እንደውም አንዴ አፍ አውጥቶ ጠይቋታል። አሁን አፉን ሞልቶ 'እህታችን ሲል አያፍርም ?! እንደውም እዛ ሱቅ ተኮራምቼ ስውል አንዳንዴ ዙቤይዳ እጇን ይዛ ወስዳ "ሻይ ቡና እንበል" ካላለችኝ እግሬን አላነሳም። እንኳን ሜት ቤት ልዞር…። እንደው አንዳንዱ ሰው አሁ…ብለው ከሰሙት የሚናገረውን አያውቀውም። የነቢል ዘመቻ እንኳን ያው "የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል" እንደሚሉት ነው ፡፡

ዙቤይዳን ያወቅኳት እዚህ ቄራ አካባቢ ከቡልጋሪያ ከፍ ብሎ የከባድ መኪና እቃ መለዋወጫ ሱቅ ውስጥ በሻጭነት ተቀጥሬ ስሠራ ነበር። ሱቃቸው ከምሠራበት ሱቅ ጎን ሲሆን ሱቆቻችን የደንጋይ ቤቶች ስለነበሩ ይቀዘቅዛሉ። ጧት ወንበር ውጭ ጋ እናወጣና ፀሐይ እንሞቃለን። እነዙቤይዳ ሱቅ በር ላይ የአንድ ትልቅ ሕንፃ ጥላ ስለሚያርፍ ፀሐይ ፍለጋ እኔ ወደምሠራበት ሱቅ በር ጠጋ ብላ ነበር የምትቀመጠው። እኔም ወንበር አወጣላትና ጎን ለጎን ተቀምጠን ፀሐያችንን እየኮመኮምን እናወራለን…።

አንዳንዴ እህቷም አብራን ትኖራለች። ብዙ ጊዜ ግን ብቻችንን ነን። ይሄ ቅርርብ ሰቦ ሰቦ ስጋችን ፀሐይ፣ ነፍሶቻችንም ፍቅር ይሞቁ ጀመረ። አንድ ቀን ዙቤይዳ ከመሬት ተነሲታ፣ "ይሄ ፀሐይ ሱሰ ሆነብኝ" አለችኝ - ያዝ እንግዲህ !! በኋላ ፍቅራችን ከለየለት በኋላ "አንተን ማየት ሱስ ሆነብኝ ማለቴ ነበር፤ የማይገባህ ሆንክ እንጂ" ብላ አስቃኛለች። እሷም ስለማይገባት እንጂ እኔም ሱስ ሆናብኝ ነበር። ዙቤይዳ ከቤት ወጥታ የማታውቅ ውብ ልጅ ነበረች። ፀሐይ ሲነካት ታብረቀርቃለች፣ ቆዳዋ ወርቃማ ነው። አላፊ አግዳሚው ባፍጢሙ እስኪደፋ አንገቱን ጠምዝዞ የሚመለከታት ልጅ ነበረች። እንደው ስለወደድኳት ሳይሆን ዙቤይዳ ከቤተሰቦቿ አንደኛ ቆንጆ ነበረች - መመኪያቸው …የቤተሰቡ መመኪያ ! ታዲያ ይችን ልጅ ይገፔ ነው ሁልጊዜ ሱቃችንን ዘጋግተን በአፍሪካ ኅብረት መንገድ ከንዴን ተደግፋ በፍቅር የምንንሳፈፈው - አቤት ያንን መንገድ ስንወደው ]

አባቷ ጋሽ ጀማል ታዲያ መከረውም ዘከረውም በዘመድ አዝማድ ልጃቸውን አስመከረውም አልሆን ሲላቸው ረጋ ብለው ሲያስቡ ቆዩና፣

"ዙቤይዳ!" አሏትልጃቸውን።

"አቤት አባባ!"

"እስቲ ልጁን ጥሪውና እንየው" አሉ። ወንድምና እህቶቿ ተበሳጩ።

"እንዴት አንድ ዱርዬ ቤት ድረስ ይምጣና ላናግር ይላሉ አባባ" አሏቸው።

"እንኳን ፊት ሰጥተውት ልጁ አይናወጣ ነገር ነው አባባ" አለች የዙቤይዳ እህት...(ሚሊየን ጊዜ ስለ

አይናፋርነቱ ነግራኛለች በፊት ፀሐይ ሰንሞቅ ዛሬ ተጣላኝና ...ግዴለም)።

"ቢሆንስ እንየው ማለት ምን ጉዳት አለው? እኔም እናታችሁም እናናግረውና የምንወስነውን

እንወስናለን" ብለው ቆጣ አሉ። ልጆቹም ደንገጥ ብለው ዝም አሉ።

"ግን አባባ እስከዛሬ እንዴት አላወቁትም፣ ቄራ ሱቃችን ጎን ተቀጥሮ የሚሠራው ልጅ እኮ ነው።" አለች

ዘምዘም የምትባለው ሁለተኛዋ ልጅ።

ጋሽ ጀማል አሰቡ አሰቡና፣ "እሃ ይሄ ቀይ መኪና የሚይዘው ልጅነው ?" ብለው ጠየቁ (ቀይ መኪና

የሚይዘው አሠሪዬ ነው)።

"ኧረ አባባ እሱ እንኳን መኪና ሊይዝ ለእግሩም ደህና ጫማ የለውም፤ የሆነ አንጀት የራቀው ላንገሳ

ነገር ነው" አለች ዘሐራ።

"አንቺ እንዲህ አይባልም...፤ዱኒያ ተአላህ ዘንዳ ነው። የምን ትዕቢት ነው" አሉ የዙቤይዳ እናት በቁጣ።

ዘሐራ ደንግጣ ዝም አለች። ይች ጉረኛ፤ የዘሐራ ጉራ ልክ የለውም፣ ትዕቢቷም በጓደኞቿ ሁሉ የታወቀ

ነው። ስለ ሁሉም ነገር ከእኔ በላይ አዋቂ የለም የምትል ልጅ ነበረች። እኔንማ ጥምድ አድርጋ ነው

የያዘችኝ። ሴት ልጅ ጉረኛ ስትሆን እንዴት ያስጠላል?! ባይሆን ኩሩ ስትሆን ይሻላል...።

የሆነ ሆኖ የዙቤይዳ አባት ሊያናግሩኝ ወስነው እንድጠራ አዘዙ። ዙቤይዳም ጠራችኝ። አባቷ ሊያምኑ

መንገድ መጀመራቸውን ገምታ ነበር። ታዲያ ዜድዬ ጋር ተገናኝተን ወደ ቤታቸው መንገድ ስንጀምር

ቀድማ መከረችኝ፤

"አብርሽ!"

"ወይ ዬዜድ!"

"አይዞህ...ቤት ስትገባ ጫማህን አውልቅ እሺ ?"

"እሺ!"

"ደግሞ ማስቲካ በአፍህ እንዳትይዝ፤ አባባ ማስቲካ የሚያላምጥ ሰው አይወዱም።"

"እሺ!" ብዬ በአፌ የያዝኩትን ማስቲካ ልተፋው ስል፤

"ማን አሁን አለህ? ቤት ስትደርስ ነው ያልኩህ" አለችና ሳቀች። እኔ አልሳቅኩም፤ተጨናንቄ ነበር። ማስቲካዬን ወደ አፌ መልሼ ምካሬን ማድመጥ ጀመርኩ።

"ደግሞ አብርሽዬ ብዙ እንዳታወራ፣ በእኔ ለምደህ እንዳትቀባጥር የኔ ማር" ፈገግአለች፤ "እ...ሌላው ነገር...አዎ ነገር ለማለሳለስ ብለህ አንድም ነገር እንዳትዋሽ። የሆነውን የተሰማህን ነገር ብቻ ሃቁን ተናገር።"

"ሃቁን"

"አዎ ሃቁን ! ቢተረፈ በጣም ስለምኮራብህና ምንም ነገር ቢፈጠር እኔ ስለማፈቅርህ እንዳትፈራ የኔ ቆንጆ፤ እሺ አብርሽዬ...!"

"እሺ...!"

"ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ ... ውይ እሺ እሺ ስትል አሳዘንከኝኮ የኔ ሚስኪን ሂሂሂሂ" አለችና ጉንጬን ግጥም አድርጋ ሳመችኝ። በዙቤይዳ ሙጥቅላ መኪና ወደ ቤታቸው መንገድ ጀመርን። በቃ ልቤን በድፍረት ሞልታ ሳሎናቸው ውስጥ ወደ ቆመው ችሎት ላከችኝ። ቤታቸው ስደርስ ተንሸራታቹ በር እንደባቡር እየተንገተገ ተከፈተ። የመቃብሬ ድንጋይ የተከፈተ ነበር የመሰለኝ - ልቤ ይፈራገጣል። ዙቤይዳ ወደ ግቢው ከመግባታችን በፊት በእጇ እጄን ጭምቅ አድርጋ ለቀቀችኝ። የዚድ እጅ አፍ ሆኖ ተናገረ፤ የእኔ እጅ ጆሮ ሆኖ አደመጠው። የተናገረችው ሃቅ ነበር !!

ወደ ግቢው ስገባ ደነገጥኩ። እንዲህ ያምራል ብዬ አላሰብኩም ነበር - ጀነት ! እንዴት ደስ ይላል። እዚህ ግቢ አድጎ እንዴት ሰላማዊ አለመሆን ይቻላል። ዘሐራ ሌላ ቦታ መሆን አለበት ያደገችው - እች ነገረኛ። አሁን ትኖር ይሆን ?

የሳሎኑ በር ሲከፈት አስፈሪው ምኑባፍ አዳራሽ ከሚያክል በር ጋር ጠበቀኝ። እናትና አባቷ በግራ በኩል ከዛም በፊት ከዛም በኋላ አይቼው የማላውቀው አረቢያን መጅሊስ ላይ ተቀምጠዋል። አረቢያን

መጅሊስ ማለት እግር የሌለው ሶፋ ማለት ነው።

ጫማዬን በር ላይ ሳወልቅ ሳንነበስ በእፍጢሜ ልደፋ ነበር። ፍርሐት ከኋላ ገፍቶኝ ሳይሆን አይቀርም። ሳላስነቃ ራሴን ተቆጣጥሬ ጫማዬን አወለቅኩ። ለዚሁ ፕሮግራም የገዛሁት ነጭ ካልሲ እንደበረሬ ተንበገበገ - ኡፍፍፍፍፍፍ ፈርቼ ነበር፣በጣም ፈርቼ ነበር!

በዙቤይዳ መሪነት ኳስ ሜዳ በሚያክለው ምቹ ምንጣፍ ላይ እየተራመድኩ አባትና እናቷ ፊት ቆምኩ። (የቁርጥ ግን ) በፈገግታ ተቀበሉኝ። በአክብሮት ጎንበስ ብዬ በሁለት እጄ አባቷን ጨበጥኳቸው። እሳቸው ግን የቀኝ እጄን መዳፍ ወደ ራሳቸው ሳብ አድርገው አይበሉባዬን ሳሙኝና እንደተጨባበጥን የእሳቸውን መልሰው ወደኔ አስጠጉ፣ እኛቸውን ሳምኩ፣ መልሰው ሳሙኝ፣ መልሼ ሳምኳቸው... መልሰው ሳሙኝ...(ኧረ ስንሳሳም መዋላችን ነው ጎበዝ...)ተዘያየርን። ከእናቷም ጋር በተመሳሳይ ተዘያየርን። በእድሜ ቢገፉም በጣም ቆንጆ ሴትዮ ነበሩ። እንዲሁ የእናቷ ቀልብ እንደወደደኝ ትከሻዬ ነገረኝ። መቼም የኔ ትከሻ ሁልጊዜም እንዳሳሳተኝ ነው።

"ተቀመጥ ልጄ!" አሉኝ አባቷ፤ ፊታቸው ላይ ምንም ነገር ማንበብ አልቻልኩም። ከፉ የለ ደግ፣ ዝም ያለ ፊት። ዞር ብዬ ዙሪያውን ተመለከትኩ፤ የወንበር ዘር በቤቱ ውስጥ የለም፤..."የት ነው የምቀመጠው?" እያልኩ ሳስብ የእኔ መሪ ኮከብ ደረሰችልኝ፣

"...እዚህ ጋ ና አብርሽ፤" ብላ ከወላጆቿ ፊት ለፊት ጥግ ይዞ ወደተጋደመው አረቢያን መጅሊስ መራችኝ። ቀስ ብዬ ተቀመጥኩ፣ አቀማመጤ ጥንቃቄ የተሞላበት ስለነበር ከተሰባሪ ነገር የተሠራሁ መሰለኝ ለራሴ።

አባትና እናት በዛ በኩል አብርሃም ብቻውን በዚህ ተፋጠጥኩ። ፊት ለፊት - በግንባር !ዙቤይዳ አባቷ ጎን ተቀመጠችና ፈገግ አለችልኝ...ልቤ በድፍረት ተሞላ፣ ሚሊየን ታንከኛ፣ ሚሊየን መድፈኛ ጦር በደጀንነት የቆመልኝ ሜጀር ጀኔራል ...! ተዋጊ ጀቶቼ ጠላቴን ሲያደባዩ ከላዬ የሚያንዣብቡልኝ ልበ ሙሉ ጦር የሆንኩ ያህል ተሰማኝ። ዙቤይዳ የኔ ፍቅር፣ የኔ የድፍረት ክብሪት፣ በጀግንነት ልቤን የምትለኩሳት እሳት ከፊቴ ናት -ዓይኖቿ "በሰው እንዳትፈራ" ይሉኛል። ዘራፍ !

እንደው ዘራፌዋ...!

እንደው ዘራፌዋ!

ሰላም አወዳለሁ!

ዘራፍም አልጠላ!

የዕርቅ ሰላም ፍሬ!

የፍቅር መሐላ...። አለች ዘፋኟ እያልኩ በልቤ ስሸልል፣

"ሥራ ደግ ነው?"አሉኝ የዙቤይዳ አባት ረጋ ብለው።

"እግዚአብሔር ይመስገን!"አልኩ።

ጉድፈላ !! ረስቼው ማስቲካውን አፌ ውስጥ ይዤው ነበር የገባሁት...! ዜድ ናት ጉድ የሰራችኝ መጀመሪያ ልጥለው ስር ተወው ባትለኝ ....

"ስምህ ማነውሳ ?" አሉኝ የዙቤይዳ አባት። (ተጀመረ)

"አብርሃም!" አልኩ እንደሳቸው ረጋ ለማለት እየሞከርኩ። ይሄ መረጋጋት የዘር ነው... ልጃቸው ዙቤይዳ ረጋ፣ አባትየው ረጋ፣ እናቲቱም ረጋ – እርጎ ባሕር ውስጥ ያለሁ መሰለኝ።

"ያው በእኛ ኢብራሂም ማለት ነው፤" አሉ የዙቤይዳ እናት። ...ነገሬያችሁ የለ...እማማ – የዜድዬ እናት ቀልባቸው ወዶኛል። ዙቤይዳ ፈገግ አለች። አሪፍ ነው ማለት ነው። በዚህ ጭንቀት ውስጥ እንኳን ሆኜ የዜድ ጥርሶች ይገርሙኛል።

"ቤተሰቦችህ እዚሁ አገር ናቸው...?"

"አዎ!"

"ምን ይሰራሉሳ...?" አባባ በየንግግራቸው መጨረሻ 'ሳ' ይጨምራሉ 'ሳ'ምን ይሆን...?!

"አባቴ የሁለተኛ ክፍል ሒሳብ አስተማሪ ነው፤ እናቴ ሥራ የላትም...የቤት እመቤት ናት "

"አንተስ ምን እየሠራህ ነው ?"

"እእ ያው ተቀጥሬ ሰቅ ውስጥ እሠራለሁ። የማታ በዲፕሎማ አካውንቲንግ እየተማርኩነው።"

ዜድዬን አየኋት፤ፈገግ አለችልኝ። ደጅናችን በፈገግታ መድፍ ጠላት ፍርሀታችን የተደበቀበት፣ ምሽግ እያደባየችው ነው ...፤ ቡምምምምምም!!! የዙቤይዳ ፈገግታ በሕይወት ዘመን ውድ ነገር ብዬ በሚቀመጡበት የአእምሮ ካዝና ውስጥ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ቅርስ ነው።

"ዲፕሎማ...!" አሉ አባቷ፤ የጥያቄም የመገረምም አልነበረም፤ እንዲሁ ነገሩን የሆነ ቦታ የሚያውቁት፣ የሚያውቁበት የጠፋባቸው ዓይነት ነበር።

የዜድ እናት ቀደም ብለው "ዲፕሎማ ማለት እንደ አብዱ ያለ ትምህርት ነው...፤ቀስ ብሎ ደሞ ድግሪ ይጭናል...፤ ከበረታም ሌላውን ነገር ሁሉ ይጭናል፤ ገና ልጅ ነው...ኢይደለም እንዴ አየዋ?" አሉኝ። ኧረ እንዴት ዓይነት መልአክ የሆኑ ምራት ገጠሙኝ። ዜድ አፏን አፍና በሳቅ ትንፈራፈራለች። ልስቅ ፈልጌ ነበር ፤ ግን በየት አባቴ፣ "ማዕዘር ላይ ተሰልፎ መሳቅ ያስመታል" ይሉ ነበር የምሠራበት ሱቅ ዘበኛ መቶ አለቃ ለገሰ...።

"ልክ ነው እማማ!" አልኩ፤

"እናቴዋ...'እማማ' አባባሉ ልክ እንደ አብዱ" አሉና ባለቤታቸውን ተመለከቷቸው። በሴትየዋ ጣልቃ ገብነት የተደሰቱ አይመስሉም። ቢሆንም ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁላቸው። በጣም፣ እጅግ በጣም የገረመኝ ነገር ጋሽ ጀማል ለዙቤይዳ እናት (ለባለቤታቸው) ያላቸው ክብር ! በፊት ዙቤይዳ ስትነግረኝ አላምንም ነበር። ግን በዓይኔ ተመልክቼ አረጋገጥኩ። የዙቤይዳ እናት በባላቸው ፊት ትልቅ ግርማ ሞገስ ነበራቸው።

በዚህች ቅፅበት ዓይኔ ዙቤይዳ እግሮች ላይ አረፈ - ቢቃ ተበላሁላችሁ። ለምን እደብቃለሁ፤ እኔ ከሴት ልጅ ውበት ቀልቤን የሚያስተኝ ነገር ቢኖር የእግር ውበት ነው። ልክፍት አለብኝ። ቆንጆ የሴት እግር ካየሁ አብሾ ነገር ይነሳብኛል። አቤየየየየየየየት የሴት እግር...፤ ቆንጆ የሴት እግር ማየት ስወድ፣ ብዙዎቹ እንዲህ ዓይነቱን ወንድ 'ልክስክስ' ይሉታል። ድፍን የዓለም ሕዝብ ከኋላዬ እየተከተለ በዓለም ቋንቋዎች ሁሉ "...አብርሃም ልክስክስ፣ ለክስካሳ ውሻ!!!" እያለ ቢፎክህ እንኳን እግር ከማየት፣ ቆንጆ የሴት ልጅ እግር ከማድነቅ ወደ ኋላ አልልም።

እኔ ደሄን ሰድብ በፀጋ ተቀብዬ እግር ማየቴን መቼም አላቆምም። የሴት ልጅ እግር የውበት ግን ነው። ለሰርጌ ቀን አይበለውና እግሯ የሚያምር ግን አንገቷ የተቆረጠ ሴት ጎኔ አምጥተው ሚስትህ ናት ቢሉኝ፣ "በደስታ ይሁን በሐዘን..." ብዬ ከመፈረም አልመለሰም። እንዲህ የምንበፈሰፍለት

ዚድዬን እያኳት፤ፈገግ አለችልኝ። ደጃናችን በፈገግታ መድፍ ጠላት ፍርሀታችን የተደበቀበትን ምሽግ እያደባየችው ነው ...፤ ቡምምምምምምም!!! የዙቤይዳ ፈገግታ በሕይወት ዘመን ውድ ነገር ብቻ በሚቀመጡበት የአእምሮ ካዝና ውስጥ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ቅርስ ነው።

"ዲፕሎማ...!" አሉ አባቷ፤ የጥያቄም የመገረምም አልነበረም፤ እንዲሁ ነገሩን የሆነ ቦታ የሚያውቁትና የሚያውቁበት የጠፋባቸው ዓይነት ነበር።

የዚድ እናት ቀደም ብለው "ዲፕሎማ ማለት እንደ አብዱ ያለ ትምህርት ነው...፤ቀስ ብሎ ደሞ ድግሪ ይጭናል...፤ ከበረታም ሌላውን ነገር ሁሉ ይጭናል፤ ገና ልጅ ነው...አይደለም እንዴ እዮዋ?" አሉኝ። ኧረ እንዴት ዓይነት መልአክ የሆኑ ምራት ገጠሙኝ። ዚድ አፏን አፍና በሳቅ ትንፈራፈራለች። ልስቅ ፈልጌ ነበር ፤ ግን በየት አባቴ፣ "ማንባር ላይ ተሰልፎ መሳቅ ያስመታል" ይሉ ነበር የምሠራበት ሱቅ ዘበኛ መቶ አለቃ ለገሰ...።

"ልክ ነው እማማ!" አልኩ፣

"እናቴዋ...'እማማ' አባባሉ ልክ እንደ አብዱ" አሉና ባለቤታቸውን ተመለከቷቸው። በሴትየዋ ጣልቃ ገብነት የተደሰቱ አይመስሉም። ቢሆንም ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁላቸው። በጣም፣ እጅግ በጣም የገረመኝ ነገር ጋሽ ጀማል ለዙቤይዳ እናት (ለባለቤታቸው) ያላቸው ክብር ! በፊት ዙቤይዳ ስትነግረኝ አላምንም ነበር። ግን በዓይኔ ተመልክቼ አረጋገጥኩ። የዙቤይዳ እናት በባላቸው ፊት ትልቅ ግርማ ሞገስ ነበራቸው።

በዚህች ቅፅበት ዓይኔ ዙቤይዳ እግሮች ላይ አረፈ - በቃ ተበላሁላችሁ። ለምን እደብቃለሁ፤ እኔ ከሴት ልጅ ውበት ቀልቤን የሚያሰተኝ ነገር ቢኖር የእግር ውበት ነው። ልከፍት አለብኝ። ቆንጆ የሴት እግር ካየሁ አብሾ ነገር ይነሳብኛል። አቢየየየየየየየየት የሴት እግር...፤ ቆንጆ የሴት እግር ማየት ስወድ፣ ብዙዎቹ እንዲህ ዓይነቱን ወንድ 'ልክስክስ' ይሉታል። ድፍን የዓለም ሕዝብ ከኋላዬ እየተከተለ በዓለም ቋንቋዎች ሁሉ "...አብርሃም ልክስክስ፣ ለክሰካሳ ውሻ!!!" እያለ ቢጮህ እንኳን እግር ከማየት፣ ቆንጆ የሴት ልጅ እግር ከማድነቅ ወደ ኋላ አልልም።

እኔ ይሄን ስድብ በፀጋ ተቀብዬ እግር ማየቴን መቼም አላቆምም። የሴት ልጅ እግር የውበት ጥጌ ነው። ለሰርጌ ቀን አይብለውና እግሯ የሚያምር ግን አንገቷ የተቆረጠ ሴት ጎኔ አምጥተው ሚስትህ ናት ቢሉኝ፣ "በደስታ ይሁን በሐዘን..." ብዬ ከመፈረም አልመለስም። እንዲህ የምንስፈሰፍለት፣

የምማልልሰት፡ የምልከሰከሰሱት፤ ልከሰከሰክሰ የምልሰት የሴት ልጅ እግር እንደኔ እንደኔ በሁለት ትላልቅ ከፍል ይከፈላል፡

1ኛ. የንለም ሴቶች እግር ሁሉ በአጠቃላይ ማለት ነው።

2ኛ. የዙቤይዳ እግር ! ቤቃ እኔን የሚያልከሰክሰኝ፣ በምኞት አፌን የሚያስከፍተኝ፣ ሳመው ሳመው የሚለኝ ይሄ ሁለተኛው እግር ነው። እናም ድንገት ከቀሚሷ ወጣ ብሎ ፍም የመሰለ ተረከዟ፣የሕፃን ልጅ ጣት የመሳሰሉ ጣቶቿ፣ ውሃ የመሰሉ (መስተዋትም ይመስሉኛል) ጥፍሮቿ፣ ምንም ቀለም ሳይቀቡ ደግሞ የቁርጭምጭሚት አጥንቶቿ ብይ ብይ መስለው ጠቆር ያለው አረቢያን መጅሊስ ላይ እንደ እሳት ሲንቀለቀሉ ሳይ ቀልቤን ሳትኩ። ዜድዬ እኮ ለእኔ ሰርክ አዲስ ነች። አይቼ አልጠግባትም ። ትንደርድሬ ሄጄ እግሮቿን ብስማቸው ደስታዬ...! የሆነ ነገር ሂድ ሂድ እያለ ይገፋኛል።

"እ...? "አሉኝ የዜድ አባት

"አ?..." አልኳቸው እኔም፣ የተናገሩትን ባለመስማቴ አፍሬም ደንግጬም ነበር፤ (ታዲያ ምን ላድርግ እኔ የብቸኝነት፣ የከህደት፣ የውሸት፣ የማስመሰል፣ የጥቅም ማሳደድ እና የዘሙት ቆፈን በሚያቆራምደው ከተማ፤ የፍቅር እሳታቸውን ወሊደው እሳት ውስጥ ቆሜ እንዴት ያሉትን ልስማ...? )

"እናቴዋ...ቀልቡን ወሰድ ያደርገዋል አንዳንዴ እንደ አብዱ" አሉ የዜድ እናት (ጎበዝ ኧረ ይሄ አብዱ ማነው...?) ዙቤይዳ ቡፍ ብላ ሳቀች። እናቷም ሰውነታቸው እስኪረግፍ ሳቁ። አባቷ ግን ከስተር እንዳሉ ፂማቸውን በመዳፋቸው እየዳሰሱ ዝም ብለው ቆዩ። በዝምታው ውስጥ ድምፃቸው የሚያማምር ሕፃናት ከሩቅ በስርቅርቅ ድምፃቸው ቁርዓን ሲቀሩ ይሰማል። ለምን እንደሆነ ባላውቅም የሕፃናቱ ድምፅ፣ የአባቷ ዝምታ፣ የዙቤይዳ አቀርቅሮ በክሪሟ መጫወት ተዳምሮ ዜድን ላጣት ከዜድ ጋር ልንለያይ ሴኮንዶች የቀሩ መሰለኝ። ምፅአት መሰለኝ። ድንገት ነው በቃ እንደዚህ የተሰማኝ። እንባዬ ሁሉ ይታገለኝ ጀመረ - እልህ ውስጤ ተንተከተከ።

የዜድዬ እናት ድንገት ዝምታውን ሰብረው፣ "ዘምዘም..." ብለው ተጣሩ ።

"አቤት እማማ !" ብላ የዙቤይዳ እህት ከውስጠኛው ከፍል የግቢ በር የሚያከለውን በጌጥ የተሸቆጠቆጠ ባለሁለት ተከፋች የጣውላ በር ከፍታ ገባች። ዘምዘም ቁመቷ የትየለሌ ነው። በዛ ቁመት ላይ ሙልት ያለ ሰውነቷ ተፈጩምሮበት ከብድ የሚል ነገር አላት። ሳሎኑ ውስጥ መጥታ ስትቆም የሆነ ረዥም ማማ ነገር የቆመ ነበር የሚመስለው፣ አንጋጥጬ ሽቅብ ተመለከትኳት። ከስተር አለችብኝ። አሁን የመረረው

ባሲጋራ መጣ አልኩ በሆዴ። በተቻለኝ መጠን ዘምዘምን ላለማየት ወደ ዙቤይዳ ዞርኩ፤ ፊጋግ አለችልኝ ወደ ዘምዘም በድፍረት ዞርኩ - ቡትሌ አከላ ታየችኝ።አስማተኛው የዜድ ፊገግታ አንኳን አንዲት ሴት ኪሊማንጃሮን በፊቴ ጠጠር ያሳክለዋል። ከፍቅር የሚገዝፍ ነገር የለማ !

"ምሳ አልደረሰም እንዴ…? እንግዳ ጠርታችሁ በራብ ልትገሉት ነው እንዴ" አሉ እማማ። ዘምዘም ከፉ ደግ ሳትናገር ወደ ውስጥ ተመልሳ ገባች። እኛም በዝምታችን እንደፀናን በሩ ተበረገደና የምሳ መፈከር ያነገቱ ሰላማዊ ሰልፈኞች ወደ ሳሎኑ ተግተልትለው ገቡ - አራት እህትና አንዲት ሠራተኛ። ዘሐራም ከሰልፈኞቹ አንዷ ነበረች። የያዘችውን ሰሐን በትኩረት ተመለከትኩት። "እሷ ከያዘችው ሰሐን አልበላም" አልኩ ለራሴ። ሠራተኛዋ ምንጣፉ መሐል ላይ አንድ ሰፊ ክብ ላስቲክ አነጠፈች። ከዛ የምግብ ዓይነት በሚያማምር ሰፋፊ የሸክላ ሰሀኖች ተደረደሩ። ላስቲኩ ላይ ዙሪያውን የተደረደሩትን ነጫጭ ሰሀኖች በክብ ተደርድረው ስመለከት በፀሐይ ዙሪያ ምህዋራቸውን ተከትለው የሚሽከረከሩ ፕላኔቶች ሥዕል ትዝ አለኝ።

ሰልፈኞቹ ወጡና ሌላ ሰሐን ይዘው ተመለሱ (ምንድን ነው ይሄ ሁሉ ጉድ)። ብስኩቱ፣ ጣፋጩ፣ ስሙን የማላውቀው ነገር ሁሉ በዓይነት ተደረደረ። አንድ ነገር ውስጤን በሐዘን ሞላው። ዙቤይዳ ሱቅ ፀሐይ ልንሞቅ ስንቀመጥ የምጋብዛትን በንቦሊኖ ለመብላት ቁርስ ሳትበላ ትመጣ እንደነበር አስታወስኩ። እውነቱን ነው ይሄን ማዕድ ስለ ፍቅር ረግጣ፣ "አብርሽ ኧረ ርቦኛል ቦንቦሊኖ ግዛልኝ…" ትላለች። ፀሐያችንን እየሞቅን ፊት ለፊታችን ካለች ሻይ ቤት ቦንቦሊኖ አዝዘን እየተጎራረስን በሻይ እንበላለን። እንደውም አንድ ጊዜ አረፋ በዓል ሆኖ የነዙቤይዳ ሱቅ ዝግ ነበር፤ እኔ ተቀጥሬ የምሠራበት ሱቅ ደግሞ አልተዘጋም፤ ዙቤይዳ ከቤቷ ሹልከ ብላ መጥታ በበዓሉ ቀን እዛች ሻይ ቤት ሄድንና ቦንቦሊኖ በሻይ በላን። ለረመዳን ሙሉ ቀን ዙቤይዳ ስለማትበላ እኔም ሳልበላ የምውልባቸው ቀናት ይበዙ ነበር።

የዙቤይዳ እናት "በልና ወዲህ፣ ዙቤይዳ ነቅነቅ በይ እንጂ መታጠቢያ ቤቱን አሳይው" አሉ። ዙቤይዳ እየመራች በሚያምረው በር አልፋ ወደ መታጠቢያው ወሰደችኝ። አንዳንድ ነገሮች እሉ በአክብሮት ሲደረጉ ሰድብ የሚሆኑ። የነዙቤይዳ መታጠቢያ ቤት ስፋት የአባቴን መኝታ ቤት ያክላል። የመታጠቢያ ሸክላዎቹ ንጣት፣ የቤቱ አሰደሳች ጠረን አፍ አውጥቶ የሰደበኝ መሰለኝ፤ "አንተ አመዳም ደሀ ልካችንን አየው…" የሚለኝ መሰለኝ። ዙቤይዳ ፈዝዤ መቆሜን ስታይ "ታጠብ…" አለችኝና ዞር ብላ ወደ ኋላ ተመልክታ ማንም አለመኖሩን ካረጋገጠች በኋላ ጉንጬን ሳመችኝ። ከንፈሯ ይሞቃል። የሆነ ርጥበቱ ጉንጬ ላይ የቀረ መሰለኝ። ስትስመኝ ድንጋጤው ይሁን ንዝረቱ አሰበረገገኝ። "ብቻችንን ከሆንን አያስችለኝም ቶሎ ውጣ" አለችኝ እየሳቀች። እና ራሷ እጁን መታጠብ ጀመረች። በመስተዋቱ ውስጥ

ዓይኖቿ አፍጥጠውብኝ ነበር። የመታጠቢያ ቤቱ ውበት ውብቷን አጉልቶት ነው መሰል፤ ዙቤይዳ በጣም አማረችብኝ። ለዚህች ልጅማ 'አንድ ሰውና አንድ ጥይት አስኪቀር...' - ታጥቦን ወጣን።

ወደ ሳሎን ስንመለስ የዙቤይዳ እናት 'ኖር...' አሉኝ፤ አባቷ ግን አሁንም ፂማቸውን እያሻሹ ዝም ብለው ተቀምጠዋል። እንደውም ከቅድሙ በላይ ፊታቸው ተቀያይሮ ቁጣ ነበር ከማንባራቸው የሚስፈነጠረው። ወደ መታጠቢያ ቤቱ እንደገባን የዜድ እናት ጋር የሆነ ነገር እንደተነጋገሩ ገመትኩ። እንዴት ይጨንቃሉ። ዘሐራ ጭልፋ ይዛ ስትገባ፤ እኛ ታጥበን ስንወጣ አንድ ሆነ። እንደው ይህች ልጅ ደንቃራ ነገር ናት ልበል። በግርምት እግሬን ተመለከተችኝ። ዓይኗን ተከትዬ ወደ እግሬ ስመለከት ወደ መታጠቢያ ቤት ስገባ ያደረግኩት የዙቤይዳን ስንደል ጫማ ነበር። ያውም ብዙ ጊዜ እሷ ስታደርግ የምትጫማውን። እሾህ ! ዓይኗ የማያየው ነገር የለም። እኔ ራሴ ጫማ ላድርግ፤ በእግሬ ልሁን ትዝ ያለኝ አሁን ነው።

እንዴት ትንሽ ትራስ ነገር ከተሰደረው ምግብ ፊት ዙቤይዳ አመቻቸችልኝና ተቀመጥኩ። አባቷ ከምግቡ ከምር ወዲያ፤ እኔወዲህ። ምግብን ድንበር አድርገን የተፋጠጥን ጠላቶች። (አንቱ ወዲያማዶ፤ እኔ ወዲህ ማዶ፤ አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ_) መብላት አልቻልኩም። አባቷ ዓይኔን ሳለማየት ሲሸሹ ምግቡ ዘጋኝ። በቤታቸው ምግብ አቅርበው ፊታቸውን ሲያጠቁሩብኝ ለልመና የመጣሁ እስኪመስለኝ አፈርኩ ተሳቀቅኩ ። ዙቤይዳ ገብቷታል። ምንም ነገር ሳትፈራ ሰሀኔ ላይ እንጀራና ንጣቱ የሚገርም ነጭ ቂጣ አድርጋ ወጥ ጨለፈችልኝ። ብዙ ዓይነት ቀለም ካላቸው ሩዞች ጨመረችልኝ። "ብላ አብርሽ_" አለችኝ። የአባቷ ማኩረፍ አስከፍቷታል። ድምፅዋ ውስጥ እልህ አለ። "ወደዳችሁ አልወደዳችሁ ገደል ግቡ..." ዓይነት ነበር የምታሳየኝ ፊት። ግን ሕመሟ አመመኝ። እንደ ውጭ ሰው ሆኜ ሳሰባት ዜድ ያፈቀረችውን ሲገፉባት የሚሰማት ውስጣዊ ሲቃይ ተሰማኝ (የራሴን ሲቃይ ዋጥ አድርጌያት የዜድን ሲቃይ በመንፈሴ ተካፈልኳት ...)።

ከእኔ የበለጠ ማፈሯን የጉንጬቿ ቀላት ይመስክራል። የዜድ እናት ቢጋሽ ጀማል ኩርፊያ ግራ ተጋብተው እንዴ እኔን፤እንዴ ባላቸውን እየተመለከቱ፤ "ብላ እይዞህ...! "ይሉኛል። ጭራሽ የዜድ አባት ሁለት ጊዜ ጎርሰው ሰሀናቸውን አስቀመጡና እጃቸውን ሰብሰብ አድርገው ተቀመጡ። እኔም ከዛ በላይ መብላት አልቻልኩም። እናቷም ብላ ብለው ማስቸገር አልፈለጉም - ገብቷቸዋል። ወጥ የነካ ጣታቸውን እንከርፍፈው ምንጣፍ ምንጣፉን እያዩ ተከዙ...።

ጋሽ ጀማል ከተቀመጡበት ተነሱና ከፉም ደግም ሳይናገሩ ወደ ውጭ ወጡ። ትንሽ ቆይተው ዙቤይዳን

ጠሯት። በሕይወቴ ከሰማኋቸው ሰቆቃዎች ሁሉ የከፋው ሰቆቃ ከበረንዳው መጣ።

"አንቺ ባለጌ አሳዳጊ የበደለሽ፣ እንዴት ወንድ እየጎተትሽ ቤቴ ድረስ..."

"አባባ አንቱ አይደለሁ ጥሪው ያሉኝ - ኸረ አላህን ፍሩ"

"ሰው መስሎኝ ነበራ። ደግሞ አብረሽ ማዕድ ላይ ታቀርቢኛለሽ -የማንም..." ዝምታ። መኪናን ሲነሳ ሰማሁ። በቃ ሔዱ። "ያውልህ ቤቱ እንተን ከማይ..." ያሉኝ መሰለኝ። የዙቤይዳ እናት እኮ እሉ፤ ያፅናኑኝ መስሏቸው፤ "ይሄውልህ ሥራውም ግብሩም እያበሳጫቸው አንዳንዴ እንዲህ ይሆና ላንተም ብቻ አይደለም እየዋ አይዞህ..."። እሳቸውም አንቱ ነው የሚሏቸው ባላቸውን።

እማማን አመስግኜ ወጣሁ። በረንዳ ላይ ዘሐራና እህቶቿ ተቀምጠዋል። የታፈነ ሳቃቸው ፊታቸው ላይ ሊፈነዳ እንዳኮበኮበ ነበረ። የቤት መዓት ጅሬ ! ቁመት ብቻ፣ መልክ ብቻ፣ ቅላት ብቻ - ፍቅር አይገባቸው፣ ሕይወት አይገባቸው - ለነሱ ማግን አገቡ መባል እንጅ ማናቸው መባል እዚህ ግ የሚባል ጉዳይ አይደለም። ይሄ ነው ከብር። ዙቤይዳ ሊፈነዳ የሚታገላት እንባዋን እየታገለች ፊ ላይ ሊገልፁት የማይችሉት ሰቃይ እየታየባት እህቶቿን ላለማየት አንገቷን አቀርቅራ ወደ መኪና መራችኝ። እንዴት በእህትማማቾቹ ፊት ላይ አንድ ጉዳይ እኩል ለሳቅና ለለቅሶ ምክንያት ይሆናል፣

"ዜድ ተመለሽ በእግሬ እሄዳለሁ" አልኳት።

"እሺ አብርሽ" ብላኝ በር ድረስ ሸኘችኝ። እንደ ወትሮው አንድ ላይ ሆነን ሐዘናችንን ከማሸነፍ ይል ለየብቻችን ሽንፈታችንን ልንቀበለው ፈልገናል። መሀላችን የንቀት ቦንብ አፈንድተው በታየኝ አይኗችሁ ባይ በሌለበት ! ዜድ ቶሎ መኝታ ቤቷ መግባትና እልቅሳ ሲወጣላት፣ ሲቃዩን፣ መዝረፍ በእንባ ልትሸኘው ቸኩላለች። አንድ የሆነ ነገራችንን ሰብረውታል። ተሳክቶላቸዋል።

ከትልቁ ግቢ እንደወጣሁ ከት ብዬ ሳቅኩ። እግዜር ይጠብቀኝ እንጂ እብደት ሳይጀምረኝ አልቀረም ካበድኩ አይቀር መንገድ ላይ ከያመረድ እዛች መከረኛ እናቴ ጋር ሄጄ ልበድ ብዬ እርምጃዬ አፈጠንኩት። አእምሮዬ ግን በሚያስፈራ ድምፅ ቁጣውን እያስገመገመ ነበር።

አንዳንዴ መገፋታችን ሳይሆን የተገፋንበት ሁኔታና ቦታ ያመናል። እነዚህ ሰውዬ ሕዝብ የመሰከረላቸው ደግ ጨዋ ሰው ነበሩ። ደሀውን ሁሉ በሬ ጥለው የሚያበሉ። የተጣላን የሚያስታርቁ። እኔ... እኔ እኔ ግን ፍቅርን ተርቤ ቤታቸው ብሄድ ይሄው ገፍተውኛል። ፍቅርን ለመቀበል ደግነት ብቻ

በቃ አይደለም። የተጣላን ማስታረቅ በፍቅር ከራስ ጋር እንደመታረቅ አይከብድም። በሬ አርደው የከተማውን ሁሉ ደሀ የሚያበሉት እነህ ሰው፣ የልጃቸውን ፍቅር ለተራበ አንድ ደሀ ፍርዳቸው ተዛብቷል። እኔን ብቻ አይደለም ልጃቸውንም በፍቅር ረሀብ ገደለዋታል። ልቤን ሰብረውታል። እሺ ምን አደረግኳቸው። ለምን ቢታቸው ጠፉኝ። ሃገኒ ነው "ከሰው ያነሰ..." ሆኖ የታያቸው።

"እግዚአብሔርም አብረሃምን እንዲህ አለው...! ያንተን ዶር፣ ያንተን በግ፣ ያንተን በሬ አልፈልግልህም። ከከብርከኝ ልጅህን ሰዋልኝ። አብርሃምም ልጁን ሊሰዋ በእግዚአብሔር ፊት ኢጋደመው" ለፍቅር የሚሰዋው ለካ ፍቅር የሚሰጣው ሰው ብቻ ነበር። ስለፍቅር ልጅን የሚሰዋ ሲጠፋ ፤ የሰው ልጅ ልብ ይንኮታኮታል። ትዳር ... ትዳር አብሮ መኖር ነው ያለው ማነው? የግራ እግንትን ነጥሎ ሌላ ጎን ላይ ሊገጥሙ ቢሞከሩ ወይ እጥንቱን መስበር አልያም እድሜ ልኩን እንደተዛዘረ ሜማ የተወናከረ ፤ በኩርፊያ ጉንጩን የነፋ ትዳር ተብዬ የሁለት ሰው አሰልቺ ስብሰባ መጥራት ነው ትርፉ። የልጆቻቸውን ፍቅር ቀምተው እየገደሉ "የልጅ ልጅ አየን..." የሚሉ ስግብግብ ራስ ወዳድ አያቶች ስንቱን ትዳር እንደሸነቱ ቲማቲም አቦሸርቀውታል። ያቻትላቸው ልጃቸው ... ስግብግብ ሁሉ !

ማንም ከተረፈው ብር ይሰጣል ። ብርን ታች ላሉ ሰዎች ለመስጠት ደግነት ብቻ በቂው ነው። ራስን ዝቅ አድርጎ ከታችኞቹ ጋር መዋል ግን ከባዱን የፍቅር ቀንበር መሸከምን ይጠይቃል። ማነው በፍቅር ለተጠሙ ደራሽ? የማን ሕንፃ፣ የማን ሸላ ነው የጥላቻ ፀሐይ፣ የመገፋት ሐሩር ሊደረቀው ሚስኪን የፍቅር ጥላውን የሚጥል?! እኔ ለዙቤይዳ ከፉ ነኝ ? ፈጣሪ ይመሰክታል፣ ዙቤይዳን ከቤተሰቦቿ የበለጠ ካልተንከባከብኳት። እንደ ወንድ ይዣት ለመጋደም አልተጣደፍኩም። አዎ ! ዙቤይዳ ከልክላኝ አልነበረም። ተቃቅፈን ባዶ ቤት ማንም በሌለበት፣ "እብርሽ የፈለከውን ጠይቀኝ" ስትለኝ ሰማይና ምድር ሰምተዋል። ነገዋን እንዳላበላሽ፣ የናቁኝ ቤተሰቦቿን አከብሬ ሜኔቷን ሳልነካት ከስሜቱ ይልቅ የዙቤይዳ ክብር የገዘፈብኝ አፍቃሪዋ ነበርኩኮ።

በዚያች በተከራየኋት አንዲት ክፍል ቤት ተንበርክኬ እግሯን ሳጥባት ከሷ ምንም ፈልጌ አልነበረም። ስለማከብራት ስለምወዳት ብቻ! ኤጭ ! ሀብታም ለልጁ ሊያወርስ የሚችለው ነገር የለም ማለት ነው?! ቢያንስ በዚህ በዚህ ምክንያት ልጃችንን እንድታገባት እንፈልግም ቢሉኝ ምናለበት ? የልጃቸው ልብ እንዳይሰበር የእኔን ልብ እንዲህ ማንኮታኮት ነበር አላማቸው? ቤታቸው ጠርተው ማዋረድ? ከነሚያበሉት በሬ ገደል ይግቡ። ደም ከላቸው ብሎ እንቱ ። "ሰው መስሎኝ ነበር" ይላሉ ፡ ሉቃቸው ሄደን ስንገዛቸው ነው ሰው የምንመስላቸው። ቤታቸው ሄደን ፍቅር አከፍሉን ስንል ይንሜንሜሉ !

ከዜድ ጋር ከሳምንት በኋላ ተገናኘን። ለመሰነባበት። ዙቤይዳን ላገባትና ቤተሰቦቿን ኳሚያ ልንላቸው እንችል ነበር። ዙቤይዳም አሁን ነይ ብላት ያ ትልቅ አጥር ሳያግዳት ከድምጿ ቀድማ ትመጣ ነበረች። ግን... ምናችንን በምናችው እንዳከሰፉት እንጃ የዜድን አይን ከዛ በኋላ ማየት እንዳልችል አድርገው አኮላሽተውናል። የሆነ ነገራችን ቀምተውናል፤ ያሉንን እንድናደርግ የፈለጉትን እንድናደርግ በከፋታቸው ማርከውናል። እርስ በራሳችን ብቻ ሳይሆን ስለየራሳችንም ማሰብ እንዳይቻለን አድርገውናል።

ተገናኘን፤ ዜድ አላለቀሰችም። ትከ ብላ ሳታቋርጥ ፊቴን አየችኝ። ፊቷ መቀመጤን በዓይኖቿ ብቻ ማረጋገጥ ያቃታት ይመስል በእጆቿ ፊቴን ዳሰሰችኝ። እንደ ሐውልት ዝም ብዬ በለስላሳ እጆቿ ተዳሰስኩ።

ፊቷ እንደ ወረቀት ገርጥቶ ነበር። ቀስ ብላ ስትነሳ መቆም አቅቷት ተንገዳገደች። እጆቿን ይዤ ደገፍኳት። እስከምትረጋጋ ዓይኖቿን ጨፍና ቆየች። አሁን ግን አንዲት የእንባ ዘለላ ኮለል ብላ በጉንጯ ላይ ወረደች። ዝም ተባብለን ቤቷ ድረስ ሸኘኋት። ሰፈራቸው ደርሰን ሁልጊዜ የምንለያይባት ቦታ ላይ እኔ ስቆም ዜድ አልቆመችም። ዝም ብላ ዞራ ሳታየኝ ወደ ግቢው በር ተጓዘች። የመቃብሩ በር ተከፈተ። መጀመሪያ ግራ እግሯ ፤ከዛ ቀኝ እግሯ ወደግቢው ገባ፣ ቀሚሷ ቀስ እያለ ወደ ውስጥ ገ... ግቢው ተዘጋ !

\###

ሥራ ለቀቁ ከፍለ ሀገር ሄድኩ - ሐረር ! እዛም ኑሮ አልተመቸኝም። ሰው ኑሮ የማይመቸው አካባቢው ስለማይመቸው አይደለም። ውስጡ የማይመቸው ነገር ሲቀመጥ እንጂ ! ዜድስ ብትሆን መች አዲስ አበባ ይመቻታል...፤ የእኔ ዜድ፣ የእኔ ሩቅ። በራሴ ላይ የፈረድኩትን እመከሮ የሌለው እስራት የዙቤይዳንም ሕይወት ያለመበጥበጥ መሐላ ላለማፍረስ ሦስት ዓመታት ጥርሴን ነክሼ ቆየሁ። መራራ የብቸኝነት ኑሮ። ፍቅሬን ስለተቀማሁ ብቻ አይደለም ፍቅሬን ቀምተው ምርኮኛውን እኔን ስዘመናት በሚቆጠቁጥ የንቀት ብትር አድቀቀውኛል፤ እያገገምኩ ነበር ።

ስልክ የለኝም። ለእናቴ በመስመር ስልክ እደውላለሁ። ለዜድ ላለመደወል ሁሉንም አቅሜን ተጠቅሜያለሁ። ስንት ቀን ለእናቴ ስደውል ጣቶቼ ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ለዜድ ሊደውሉ ቃጣቸው፣ ስንት ቀን በባዶ ሜዳ ድምጿን የሰማሁ እየመሰለኝ ወደ ኋላዬ ዞርኩ?! ድምጿን ከሰማሁ በቀጣዩ ቀን አዲስ አበባ ነኝና ራሴን በእሳት እለንጋ እየገረፍኩ የነፍሴ ጀርባ በናፍቆት እየተተለተለ እንደምንም ሦስት ዓመት ቆየሁ !! ሶስት አመት ሞትኩ። ከልሞሉ ትንሳኤ የለም ብዬ።

የአናቴ ለቅሶ አሳቅቆኝ ከሦስት ዓመት በኋላ አዲስ አበባ ተመለስኩ። የአዲስ አበባ መንገዶች ላይ መቆም በባዶ እግሬ የጋለ ምጣድ ላይ ከመቆም በላይ እንደሚያንገበግበኝ ማን አወቀልኝ፣ የተገናሁባት ከተማ፣ እሳሬ አግዳሚው ሁሉ እንደውዳቂ የሚመለከተኝ ውዳቂ የመሆን ስሜት እንደደበተኝ ለማን ልተንፍስ፣ ከተማዋ እንደሰው ጀርባዋን የሰጠችኝ እንደመሰለኝ ማን ይኼንን ግፍ ይመለከታል ?

ዘቢይዳ ማግባቷንና አሁንም እዛው ሱቅ እንደምትሠራ፣ መንታ ልጆች ወልዳ እንደኛው ልጅ እንደሞተባት ሰማሁ። ባለቤቷ ሀብታም ነው አሉ፣ ብዙውን ጊዜ ውጭ ስለሚኖር ዘቢይዳ ቤተሰቦቿ ጋር ነው የምትኖረው። እንደው ዝም ብዬ ሳስብ ቤተሰቦቿ ደስ እንዲላቸው ያገቡት ግን ደግሞ ባሏ አጠገቧ እንዳይኖር ሆን ብላ ይሆን ሰው ያገባችው መሰለኝ፣ ደግሞም ሌላኛው ታሰቤ ቅሬታ ዘራብኝ፣ ኋኔ ነኝ የምስታቀው፣ ዘቢይዳ ከባሏ ጋር በፍቅር ከንፋ ፈስታኝ ዓለሟን ስትቀጭ ነው የኖረችው የሚል ቁስሌ ላይ በርበሬ እንደመነስነስ ያለ ሐሳብ...!

አዲስ አበባ መጥቼ ምን እንደምሰራ ምን እንደማደርግ ግራ ተጋብቼ ቆየሁ። የአዲስ አበባ አየር አፈነኝ፣ መንገዱ ሁሉ የትግሬታ አሜኬላ የተዘራበት ከፉ መሬት መሰለኝ፣ በተቻለኝ ሁሉ ዘቢዳ ጋር ላለመገናኘት እብረን የረገጥነውን መንገድ ላለመርገጥ ስጠነቀቅ ኖሬ አንድ ቀን አረፋ በዓል ሆኖ ሕዝበ ሙስሊሙ አምሮና ተውቦ ወደ ሶላት ሲተም አንድ ነገር ውስጤን ገፋፍቶት በንቀስ እንደሚገፋ ፈስታል እየተወዘወዝኩ መንገድ ገባሁ። ሰው አእምሮውን ማዘዝ የሚችልበት፣ መቆጣጠር የሚችልበት ልክ አለ፤ አሁን የዘቢይዳ ናፍቆት ግድቡን ባለ። ላያት ፈለግኩ፣ ዓይኔ ፈለጋት። አይኔ ራባት፣ እግሬ ወደ ቁራ ተጓዘ...

እኔና ዜድ ውብ የፍቅር ጊዜያት ያሳለፍንበት ሰፈር፣ የዘቢይዳ መኪና ብቅ ስትል ልቤ በደስታ የሚፍለቀለቅበት ሰፈር ... ኡፍፍፍ ገና ጠዋት ነበር ... መንገዱን ተሻግሮ እኔና ዜድ በንበሲዎ የምንበላበት ሻይ ቤት እንዳለች አለች። ገና በጧቱ ተከፍታ ደንበኞቿን እያስተናገደች ነበር። አዳዲስ አስተናጋጆች ወዲያ ወዲህ እየተራራጡ ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ። መንገዱን ተሻግሮ የዜድ ሱቅ ተዘግቶ ይታየኛል። ቀጥ ብዬ ወደ ሻይ ቤቷ ገባሁና እንደ ፅጌሬዳ አበባ ሽታ የሻይ ቤቷን መዓዛ በአፍንጫዬ ሰብው ዜድን ያገኘኋት ያህል ውስጤ በአንዳች እርካታ ተሞላ።

"ምን ልታዘዝ?" አለችኝ አስተናጋጇ።

"ሶንበሲና በሻይ" አልኳት ከፍቷን በዓይኔ እየተመለከትኩ። ሕይወት ግን ምን ዓይነት ጨዋታ ነገር ናት ? ሶንበሲናው በባለ ወንፊት ሰሀን ቀረበልኝ። በፍቅር ገመጥኩት። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም አቅለሸለሸኝ። ምንም ሰላም አልሰማ አለኝ። ተረበሽኩ። ዝም ብዬ ተቀመጥኩ። አንድ በእጁ ሰሐን ትሪ የያዘ አስተናጋጅ ከውጭ እየተጣደፈ ገባና ፀጥ ብሎ እንዲህ አለ፡ "አንድ ሶንበሲና በሻይ ዘቢይዳ ሱቅ"

አስተናጋጇ በግርምት እንዲህ አለችው፤ "ዛሬ አረፉ አይደል እንዴ ዙቢይዳ እንዴ ትገባች ?"

"አንቺ ! ምን የሷ ነገር ነካ ያደርጋታል" አለ አስተናጋጇ። ዙቢይዳን እኮ ነው አይገርምም ? ...ነካ ያደርጋታል ? መግቢያዬ ጠፋኝ። ተቁነጠነጥኩ። እንደውም አፎ ሲንቀጠቀጥ ተሰማኝ። ራሴን ስቼ የምወድቅ መሰለኝ፡፡ ሒሳቤን ከፍዬ ቀስ ብዬ ወጣሁ። እንደ ምንም ዓይኔን ወደ ዙቢይዳ ሱቅ ላከኩት - ዙቢይዳ ! የኔ ዜድ ... ጀርባዋን ለመንገዱ ሰጥታ ፀሐይ የምትሞቅበት ቦታ ላይ ተቀምጣለች - እኔ እሠራበት የነበረው ሱቅ በር ላይ። ፀሐይ የለም ! ክረምት ስለሆነ ደመና አንግርብቦ ነበር። የዜድ ሱቅ በደንብ አልተከፈተም፣ ከሁለቱ ተካፋች በሮች አንዱ ብቻ ነበር ገርበብ ያለው። ቀስ ብዬ ሽቅብ ወደ ሜክሲኮ በእግሬ መንገዴን ተያያዝኩት። አንዳንች ነገር ወደዜድ እየጐተተኝ ነፍሴ እንደድር ከከበባት ስበት እየታገለች ....የህልም ሩጫ በሚመስል እግር መጎተት... ሽቅብ ወደላይ መንገዴን ቀጠልኩ።

እኔና ዙቢይዳ ስከር እብድ የሚያደርግ ፍቅር ውስጥ የወደቅነው ድንገት ነበር። ዛሬም የዙቢይዳን ስም ሳነሳ ሰውነቱ በሆነ ኃይል ይሞላል...ደስታ በመላው አካላቴ እንደ ኸረት ሲፈስ ይሰማኛል - ማን ያምነኛል ብናገረው ? ከተለያየን ከሦስት ዓመት በኋላ እንኳን ጠረኗ አጠገቤ ያለች ያህል ይሸተኛል። ድምጽዋ ይሰማኛል፣ የልብሷ ቀማታ ሳይቀር ይሰማኛል። ነፍስ ጡሮች አማረን እንደሚሉት ዙቢይዳ ከፉኛ ታምረኛለች፣ ድምጿ ያምረኛል፣ ዓይኖቿ ያምሩኛል። እኔስ የማይወለድ ፍቅር ያውም የጨነገፈ ግን ከውስጥ የማይወጣ ፅንስ ፅንሼ የለ ከነፍስ ጡር ምኑን ተሻልኩት። ድፍን አገሩ...በእንጀራ በሌላም ብሶት ያረገዘው ብዙ ብሶት ውል የሚልበትም እልፍ አምሮት አለው !! ማን ማንን ያፅናናል? አምሮታችን እንዳማረን ወደ መቃብራችን እግራችንን እንጎትታለን።

ድንገት ገነት ሆቴል ስደርስ ወደ አፍሪካ ኅብረት ታጠፍኩ። ፀጥ ባለው መንገድ ግራና ቀኝ በተሰለፉት የዘንባባ ዛፎች መሐል እየተጓዝኩ ረዥሙ የአፍሪካ ሕብረት ሕንፃ ከፊቴ ተጋረጠ። አፍሪካዊ ነኝ፤ አፍሪካ ነኝ፤ በአረንጓዴ ምድር የፍቅር ችግር አድርቆኝ ውስጤ ምድረ በዳ የሆነ የአፍሪካ ልጅ ነኝ፤ አፍሪካ፣ አፍሪካ፣ አፍሪካ -

"ስደት" የሚል ቃል አእምሮዬ ውስጥ ፈነዳ !! አዲስ አበባ የእኔ አይደለችም።

# አዋጅና ፀሎት

አባቴ በሕይወቱ የፀለየው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ሁለቱም ጸሎቱ ደርሶለታል ! ... እንደ'ሱ አባባል።

እንደውም አንዳንድ የሥነ መለኮት ትምሕርት ቤቶች "የአቶ ዘውዱ ጸሎት" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አዘጋጅተው የአባቴን ጸሎት ለማስተማሪያነት ይጠቀሙበታል የሚል ወሬ ሰምቻለሁ። እውነት ይሁን አይሁን አላጣራሁም። አንዳንድ ሰዎች "አባቴ ሁለት ጊዜ ብቻ ፀልዮ ሁለቱም ፀሎቱ ደረሰለት" ስላቸው "እኛ የዕለት እንጀራችንን በቀን አስራ አንድ ጊዜ እየደገምን እንጀራችን ሳስቷል፣ የአባትህ ጸሎትና አጠያየቁ እንዴት ቢሆን ነው ከሁለቱ ሁለት ያገኙት" ይሉኛል ... ተገቢ ጥያቄ ነው።

እንግዲህ አባቴ አቢዮት ሲፈነዳ እዚህ አራት ኪሎ አንዲት ትንሽ ቤት ተከራይቶ ራሱ እስኪፈነዳ ስለትዳር ያስብ ነበር። ምንም እንኳን ጥሩ ሥራ ያለው መልከ መልካም ሰው ቢሆንም የወንድም የሴትም ጓደኛ አልነበረውም። ሬዲዮ ሲያዳምጥና ጋዜጣ ሲያነብ ነበር ከሥራ ውጭ ያለ ጊዜውን የሚያሳልፈው። ሰዎች ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር እንዴት ተገናኛችሁ ሲባሉ "ጓደኛዬ ሰርግ ላይ አይቻት፣ አይቼው...የጓደኛዬ አባት ሞተው ቀብር ላይ ሲታለቅስ ይች አያርግበትና የእኔም አባት አንድ ነገር ቢሆን ለቅሶ ታደምቃለች ብዬ አገባኋት..." ሲሉ ይሰማል። አባቴ ግን ብቸኛ ነበር። ሠርግ የሚጠራው የለ! ለቅሶ አይደርስ ! ቆንጆ ሆኖ፣ ጥሩ ሥራ ኖሮት እንዴት ብቸኛ ይሆናል? ራሱም መልስ ያላገኘለት ጥያቄ ነበር።

አንድ ቅዳሜ ቀን ታዲያ በሩ ላይ ቁጭ ብሎ ፀሐይ እየሞቀ መደዳውን የተከራዩት ስድስት ወጣቶች ፍቅረኞቻቸው ጋር ቀሪዎቹ ደግሞ ቤተሰብ ጋር እያሉ እየዘነጡ ሲሄዱ አባቴ ብቻውን ቀረ። ከላይ ፀሐይ ከታች አባቴ!! ዙሪያውን ሲመለከት ሰዎች ቡና ይጠራራሉ። እሱን "ቡና ጠጣ" የሚለው የለም። ክርስትና፣ ልደት፣ ሠርግ፣ ማኅበር፣ ሰው ሁሉ ሲራወጥ አባቴ (ሚስኪን አባቴ) ከሌላ ዓለም እንደመጣ

ፍጥረት በቻውን ዓይኑ በርትቶ እያለ ተቀምጦ ነበር። ሆደ ባሰው፤ ብቸኝነቱ ግዘፍ ተሞላ።

እንዳንዴ የለመደነውም ነገር አዲስ የሚሆንብን አእምሯችን ከልማዱ የሚበረግግበት ጊዜ የሚሰበት ጊዜ አለ። የአባቴ አእምሮ በረገገ፤ ዙሪያውን የከበበውን ብቸኝነት አንስቶ አፈር መብርሩን ማገፋቱን በቶ አሰው። በዚህ ጊዜ አባቴ በቀጥታ ተነስቶ ቤቱ ገባና በሩን ከውስጥ ቆረቆረ እንቡጥ በር አዘጋጉን ላየው ሰው አባቴ ራሱን ሊገድል የወሰነ ሊመስለው ይችል ነበር። ግን ራሱንም ቢያጠፋ እንኳ ተመልካች የለውም። በርከክ ብሎ ታሪካዊ ጸሎቱን ጀመረ…

"ጌታ!" አለው እግዜርን ልክ እንደ ጓደኛው፤ "እኔ ሰው አይደለሁም? አልፈጠርከኝም?…ሁሉ ካ ሰየሰየላኝ ሰው እንዳርቀኝ ያደረከው ምን ሆንኩ ብለህ ነው?…ምን በድዬህ ነው? …እ?…ወይ ቤተሰብ የለኝ፤ ወይ ጓደኛ የለኝ፤…ድምፄን ለመሞከር እንኳን የማናግረው ሰው እንደት ታሳጣኛለህ ነውር አይደለም እንዴ !? ሰው መሀል ፈጥረህ ሰው ማሳጣት?….ተው እንጅ ተው!! ሰሚ ተመሰከ ምን ይፈርዳል…?!" አለና ሰቀ ሰቅ ሰት ሰቅ ሰቀ ብሎ፤ እየየየየየየየየየ ብሎ፤ እንባውን ወደ እርገ ጣራ ረጨው። መቸስ ከአዳም ጀምሮ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የአባቴን ለቅሶ የሚወዳደር እስቃ ተፈልጎ አይገኝም።

ወዲያው እንባው ጣራውን አልፎ፤ ደመናውን ሰርስሮ፤ ሰማይ ቤትን አጥለቀለቀው። ሰማይ ቤ ያለ ነፍስ ሁሉ ተገረመ። "ዝናብ ከላይ ወደታች ነበር የሚዘንበው እንዴት ከምድር ወደሰማይ ይወጣል?" እየተባባለ የሰማይ ቤት ነፍስ ሁሉ መጠለያ ፍለጋ ተራወጠ። እንባው የሰማይ ቤት የሰማይ ወለል አጨቀየው። ምድረ መልአክ ለእግሩ መርገጫ ደረቅ ሰማይ እስኪያጣ!!…ጭራሽ እንባው እንደ ማዕበል እየተናወጠ የእግዜር ዙፋን ሥር ሲደርስ ባሕር መስሎ ረጋ። እግዜርም "ምን መንፋረቅ ነው ዘውዱ! ወንድ አይደለህም እንዴ? በቃህ !" አለና አባቴን ገሰፀው።

አባቴ ሊሰማ ነውና! "አይበቃኝም! ዛሬውኑ ብቸኝነቴ እንዲያበቃ ካላዘዝክ ገና አለቅሳለሁ…አለቅሳለሁ አለቅሳለሁ፤ እህህህህ…እስከመቼ ሰው ይራበኝ፤ እስከመቼ የጎረቤት ቤት ጠባቂ ልሁን…?" ብሎ አለ። አባቴ በለቅሶው መሀል እንፍፍፍፍፍፍ አለና ልክ እንፍታውን ወደ በሩ ሲወረውረው ነው ሰፈ ጓደ መንገዶች ኃይለማርያም ቤተመንግሥት ከኩባ ለመጡ እንግዶች ንግግር ማድረጋቸውን ቀም አደረገ፤ እጃቸውን ጠርተው "ምንድነው?" ብለው ጠየቁ አሉ!! አባቴ አፍንጫውን ቆ የወረወረው ነበር የሚመስለው። በኋላ እግዜር፤ "በቃ እዝዣለሁ ተነስ !" አለው። አባቴ ዓይኑ ቀልቶ

ቀለል ብሎት ውጭ ወጥቶ በሐይ መሞቁን እንደቀጠለ...

ሕዝቡም ቡና ማጠራራቱን ሰቅሶ መደራረሱን እንደቀጠለ....

በጣፋጪ ፀሐይ የግቢው አበቦች በለስላሳው ንፋስ በተስታ እየተወዛወዙ ንቦች ከአበባ አበባ እየበረቁ የአባቴን ቀልብ ወስደውት እያለ...

(ተመልከቱ የግዜርን ተአምር!) አንድ አረንጓዴ ኳስ እየነጠረ...እየተንከባለለ...እየተንከባለለ...ደግሞ እየነጠረ....አባቴ እግር ሥር ሲደርስ ቀጥ ብሎ ቆመ። አባቴ ብድግ ቢያደርገው ኳስ ሳይሆን የተጠቀለለ ቀባ ክር ሆኖ አገኘው። ሳብ ሲያደርገው የከሩ ውል ላይ ሰፈር ሆኖ እየተተረተረ መምጣቱን ተረዳ።

አባቴ ከተቀመጠበት ተነስቶ የተተረተረውን የከር ኳስ በግራ እጁ እንደያዘ በቀኙ ክሩን በኳሱ ላይ እየጠቀለለ፣ እየጠመጠመ...እየጠመጠመ...በጠላ ቤቱ ጋር ታጠፈ። እየጠመጠመ...እየጠመጠመ... ወፍጮ ቤቱን አለፈ። እየጠመጠመ...እየጠመጠመ ወደ ግራ ታጠፈና አንድ አጥር ሥር ደረሰ። እየጠመጠመ ወደ አጥሩ ሲገባ እማይበኛችሁ ድንጋይ ይሁን በድንጋጤ ድንጋይ የምታደርግ መልአከ የመሰለች ልጅ ፊት ግትር!! የተጀመረ ዳንቴል በግራ እጇ ይዛ፣ በቀኟ ኪሮሽ እንደጨበጠች ቆማለች፤ ...ፈገግ አለች ልጅቷ።ወዳ ነው እግዜር ያመጣው ላይ ማነው ፊቱን መቋጠር የሚችል !!

በዛ በኩል ልጅቱ፣ በዚህ በኩል አባቴ ወጥረው የያዙት ክር የእህል ውኃ ገመዳቸው ሆኖ ቁጭ አለ!! አዳሜ በቀለበት መንገድ መኪና ይዘህ ትባዝናለህ፤ እግዜር ከፈለገ በቀጭን የዳንቴል ክር እንዲህ ጎትቶ ገነት ያስገባኻል። ክሩን እየተንቀጠቀጠ ሰጥቷት በፍዘትና በንፍዘት እነደቆመ የልጅቱ አባት ከተፍ ይላሉ።

"ምንድን ነው?" አሉ የወይራ ከዘራቸውን እያመቻቹ። "በረከት አንዳንዴ ከዱላም ጋር አብሮ ሊላክ ይችላል" ይሉ ነበር አባ ፍርዳወቅ።

ልጅት ግን ፈጠን ብላ "ሰርቢሷን ሊከራይ የመጣ ተከራይ ነው" አለች፣ ቀልቧ ሹክ ብሏት...

አባት ተረጋጉ። በረከቱ ዱላውን ጥሎ ብቻውን ኮለል ብሎ መጣ!! የልጅቱ አባት አባቴን ወደ ጓሮ ወሰዱትና የምትከራየውን ሰርቪስ ቤት አሳዩት።ተከራይ አጥታ የከረመች የጭቃ ቤት።

ጊዚያጋ ጣራዋ ትንሽ ያፈሳል። አስቲጠገን ወረቀትና ነጭ ልብስ በዛ በኩል እንዳታስቀምጥ። አልጋህን

ደግሞ በዚህ በኩል ታደርገውና በባልዲ ፍሳሹን ገድበህ ለአንዳንድ ነገር ይሆንሃል፤ ለምሳሌ ካልሲ ለማጠብ...።" አሉ አባትየው። አባቴ ምን ተዳው። ቀጠሉና "መብራት ገና አልገባላትም ለጊዜው ሻማ ትጠቀምና ጡረታዬ ሲመጣ ከዋናው ቤት ጠልፌ አስገባልኻለሁ።" አባቴ "ፀሐይ የመሰለች ልጅ ያለችበት ቤት የምን መብራት ነው!" አለ በሆዱ። በዛኑ ቀን ከሰዓት ጓዙን ጠቅልሎ ልጅቱ ቤት ገባ።

እንግዲህ እየቆየ አባቴና ልጅቱ ተላመዱ። ልጅቱ በሰበብ አስባቡ ብቅ እያለች ታወግዋለች። ሰብ በሚሰልብ ዓይኗ ዓይንዓይኑን እያየች ታወግዋለች። ሥራ ውሎ ሲመጣ ምግብ አዘጋጅታ ቤቱን ጠራርጋ ትጠብቀዋለች። ውሎውን ያወጋሉ፤ ምን ማውጋት ብቻ፤ እየተቆነጣጠጡም፣ እየተጎነታተሉም አራት ወር በደስታ ኖሩ።አባቴ እግዜርን ሰው ሰጠኸኝ ብሎ አላመሰገነውም!! ምክንያቱም እግዜርን ረስቶት ነበር። ኧረ ልጅቱ ራሱንም አስረስታው ነበር።

አባቴ ታዲያ የልጅቱ አባት ጋርም ኮከቡ ገጥሞ ቤተኛ ሆኖ ነበር። ቡና አብረው ይጠጣሉ፤ አንዳንዴ እንደውም ወጣ ይሉና በአባቴ ጋባዥነት አንድ ሁለት ብለው ይመለሳሉ። ምንም እንኳን ደርግ ሥልጣን ይዞ አገር በአዲስ ፍቅርና አዲስ መፈከር እያዥጎደጎደች የነበረ ቢሆንም፣ አባቴ አዲስ አገር የሆነችለት ልጅ ጋር ከፉኛ ተዋድዶ ለአባቷ እንዴት እንደሚነግርና እንዴት ጠቅልሎ ቤቱ እንደሚያስገባት እያሰበ ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር ተአምረኛው አዋጅ የታወጀው። ከአዋጁ በፊት ሁኔታው እንዲህ ነበር።

ልጅት አባቴን "ቡና ጥሪ" ተብላ ቤቱ መሄድ። አባቴ መቼስ ከቡናው ይልቅ ቡና ጠሪዋ ናት ስለ የሆነችበት፤ ካላያት ያዛጋዋል። ልክ አባቴ ክፍል ውስጥ የልጅቱ ውብ ግራ እግር ሲገባና ራዲዮኑ አዋጁን ሲያነብ አንድ ሆነ። "ከአሁን ጀምሮ ቤት ተከራይተህ የምትኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ!! ቤቱን እንድትወርስ መንግሥት ፈቅዷል።...አብረህ የተከራየኸውም ይሁን ቤቱ ጋር ተያያዥነት ያለው በቤቱ ውስጥ የሚገኝ ንብረትም ከአሁን ጀምሮ ያንተው ነው!! ኢትዮጵያ ትቅደም!!" ማርሽ ሙዚቃ ተከተለ።

አባቴ በማርሽ ሙዚቃ ታጅቦ ከኢትዮጵያም ቀድሞ እንደበረኛ ተወረወረና ቆንጂዋን እንቅ አደረገ፤ 'እሜ ቀሊጥ!' አለ፤ አዋጅ አዋጅ ነው!! አባቷም ቢሆኑ አባቴ ልጃቸውን ከቤቱ ጋር በመውሰዱ አላዘኑም። "ቤቴን ተወረስኩ" ከማለት "ለልጄ አወረስኩ" ማለቱ ይሻላል ብለው ትዳሩን መረቁለት። አዋጅ ከምርቃት ጋር እግዜር ሲሰጥ መቸስ እንዲህ ነው። ምድራዊው ንጉሥም ሰማያዊው ጌታም አባቴን ባረኩት። ይሄው ዛሬ በአዋጅ የተጠለፈች ቆንጆ እናትና በአዋጁ ፈውዳላዊ ብቸኝነትን ገርስሶ ነፃ የወጣ አባቴ በፍቅር እኔንና አራት እህቶቼን ወልደው ይኖራሉ። እንደውም የፀሎቱ ርዝራዥ ደርሶኝ

ነው መስል ቆንጆ ሴት ማጥሜ ናት። አንዳንዴ ታዲያ እናቱ አባቱን ሲታበፈራራው እንዲህ ትላለች

"ዋ! ቤት ለባለቤት የተባለ እንደሆን...!"

ታዲያ ባለፈው አባቱ ለአንድ የቀበሌ ሊቀመንበር ይሄን ታሪክ አውርቶ "ጊዜው መልካም ነበር!" ብሎ ወሬውን ቢያሳርግ ሊቀመንበሩ "አቶ ዘውዱ ያለፈ ሥርዓት ናፋቂ ነዎት" ብሎ አባቱን ዘለፈው። ሁለተኛው የአባቱ ፀሎት "ይሄን ቃሌን የሚያጣምም፣ ካለስሜ ስም የሚለጥፍ ሊቀመንበር ንቀልልኝ" የሚል ነበር።

በዛው ቀን ሊቀመንበሩ በግምገማ ከወንበሩ ተነቀለ።

# “ድንቡሎ ለምን ለምን ሞተ?!?!”

ሰፈራችን ውስጥ መከብብ ግሮሰሪ የምትባል አለች። ማታ ማታ ፀሐይ ሲያዘቀዝቅ ትልልቅ ሰዎች በረንዳዋ ላይ ተሰባስበው ኢያወሩ ጅን የሚባል መጠጥ ድርፍጭ ባሉ ብርጭቆዎች የሚጠጡባት። በግሮሰሪዋ ሁሉም ዓይነት መጠጥ ቢኖርም በረንዳ ላይ የሚቀመጡት ሽማግሌና ጎልማሶች ግን ልክ ዕድሜ ይቀጥል ይመስል ጅን ብቻ ነበር የሚጠጡት። በሯ ላይ በግራ በኩል እንደ ኤሊ ፍርግርግ ድንጋይ የለበሰ የሚመስል ግንድ ያለው የዘንባባ ዛፍ የግሮሰሪዋ ግርማ ሞገስ ነው። ይህች የዘንባባ ዛፍ ለጥምቀት ሰፈራችንን አቋርጠዉ የሚያልፉት ሁለት ታቦታት ከመለያየታቸው በፊት የሚቆሙባት የታቦት መቆሚያ ነበረች። ባለቤቱ አባባ መከብብ ይባላሉ።አጭር፣ ሙሉ ፀጉራቸውን ነጭ ሽበት የወረሰው፣ ከባድ ሌንስ ያለው መነፅር የሚያደርጉ ሰውዬ ናቸው።

አባባ መኪብብን ባየኋቸው ቁጥር የሚገርሙኝ ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ግርምቴ አፋቸው ውስጥ ምግብ ኖረም አልኖረም በባዶው ያላምጣሉ። አፋቸው አያርፍም፤ ዝም ብሎ ያላምጣል። በፊት በፊት ማስቲካ የሚያላምጡ ይመስለኝ ነበር። ታዲያ ትልልቅ ሰዎች ማስቲካ ብዙም ስለማያላምጡ አባባ መከብብ ዘመናዊ ሽማግሌ ይመስሉኝ ነበር። በኋላ ከፍ ስል ግን 'ኣንደው ልማድ ኾኖባቸው ነው...' ሲባል ሰማሁ። ሲያወሩ ሁሉ በየመሀሉ ባዶ አፋቸውን እንደሚያላምጥ ሰው እያንቀሳቀሱ አየር ያኝካሉ። ሁልጊዜ ሙልጭ ተደርጋ የምትላጭ ትንሽ አገጫቸው ላይና ታች ከፍ ዝቅ ስትል ነው የምትውለው። ታዲያ አንዳንዴ ሲልኩኝ ፈልገው ወይም ለሆነ ጉዳይ በባዶው በሚያኝኩት አፋቸው “አብራም...!” ሲሉኝ ስሜን አላምጠው የተፉት ይመስለኛል። በዛ እድሜዬ የሚመስለኝ ነገር ይበዛ ነበር።

ሁለተኛው ከአባባ መከብብ የሚገርመኝ ሱሪያቸው ነው። ሱሪያቸው ከታች እስከላይ ይገርመኛል። ከግርጌው እንደጎንጉላ ጨርቅ ወደ አንድ በኩል ተጠምዝዞ ይጠቀለልና ካልሲያቸው ውስጥ

ይጠቀጠቃል። በእርግጥ የእኔም አባት እንደዛ ያደርጋል። ግን አባባ እንደዛ የሚያደርገው ዝናብ ጥሎ ማሬቱ ሲጨቀይ ብቻ ነው። አባባ መኪብብ ግን ሁልጊዜም ነው የሚያጭቁት። ከላይ ደግሞ ጥቁር የቆዳ ቀበታቸው ወገባቸው ላይ ሳይሆን ከእንብርታቸው ከፍ ብሎ ከልባቸው ሥር ... እዛ ላይ ነው ቅብትር ተደርጎ የሚታሰረው። ከነተረቱ ሰፈራችን ውስጥ የሆነ ሰው ሱሪውን ከፍ አድርጎ ከታነበቀ "ምነው እንደአባባ መኪብብ ሱሪህን ደረትህ ላይ ሰቀልከው ?" ይባላል።

ሌላም የረሳሁት ሦስተኛ አስገራሚ ነገር አለ። አባባ መኪብብ ደንበኞቻቸውን እያስተናገዱ (ሁሉም ደንበኞቻቸው በርሳቸው ዕድሜ ስለሆኑ ከደንበኛ ይልቅ ጓደኞቻቸው ይመስሉኛል) ከመኪና ላይ ቢራ እያስወረዱ ወይም ግሮሰሪው በር ላይ በጉርድ የብረት በርሚል የተሞላ ፉርሽካ ተዘርግፎላቸው የሚበሉትን ሦስት ሙኪት በጎቻቸውን እየተመለከቱ የሚሠሩት አንዲት ነገር አለች...፤ ከእጃቸው በማትለየውና የቀንድ እጀታ ባላት የጢም መላጫቸው በደረቁ ጉንጫቸውን፣ አገጫቸውንና የአገጫቸውን ሥር ይፈገፍጋሉ - ሁልጊዜ...። እንደውም ሰው ሰላም ሲሉ የጢም መላጫቸውን በቀኝ እጃቸው ስለሚይዙ ለመጨበጥ አይመቻቸውም። እናም እንደጨበጧት አይበሉባቸውን አዙረው ሰላም ወደሚሉት ሰው እጅ ይዘረጉና ነካ አድርገውት እጃቸውን ይመልሳሉ። ታዲያ የጢም መላጫቸውን የበረንዳዋ መከለያ ብረት ላይ ኳ ኳ አድርገው ያራግፏታል ! ድምፁ አስካሁን ጆሮዬ ላይ አለ።

አባባ መኪብብ በመንደሩ ሰው በሙሉ "ደግ ሰው ናቸው..." ነው የሚባሉት። ግሮሰሪው በር ላይ ለበጎቻቸው ፉርሽካ ከሚቀመጥበት ጎራዳ በርሚል ራቅ ብሎ ሰማያዊ የፕላስቲክ በርሚል በውኃ ተሞልቶ ይቀመጣል። በርሚሉ ጋር በረዶ በመሰለች የኤሌክትሪክ ገመድ ሜፏ ተበስቶ የታሰረ ቢጫ የቲማቲም ሥዕል ያለባት የመርቲ ጣሳ አለች ... በርሚሉና ጣሳው ከድሮ ጀምሮ ስለማይነጣጠሉ በኤሌክትሪክ ገመድ እትብት የተያያዙ እናትና ልጅ ይመስሉ ነበር። እንግዲህ አላፊ አግዳሚ የኔ ቢጤ ውኃ ከጠማው ከዛ በርሚል በጣሳዋ እየጠለቀ ይጠጣል...። ትንሽ ልጆች እንደነበርን ውኃው የተለየ ነገር ስለሚመስለን እኛም እየተደበቅን እንጠጣ ነበር። በኋላ ግን ወላጆቻችን "ማንም በሚጠጣበት እየጠጡ ኮሌራ ሊያመጡብን..." እያሉ ሲቆጡን አቆምን !

ምንጊዜም የቡሄ በዓል ሲሆን የሰፈር ልጆች ተሰባስበን አንደኛ የምንሄደው አባባ መኪብብ ግሮሰሪ ነበር። ፈንታው ድንቡሬ የሚባል ጓደኛችን አውራጅ ይሆናል። አባባ መኪብብ ፈንታውን በጣም ነው የሚወዱት። ጉንጬ ድንቡሞ ያለ ስለሆነ ነው መሰል 'ድንቡሬ' እያሉ ነው የሚጠሩት። በዚሁ ሰበብ ጓደኞችን ፈንታው ፈንታው ድንቡሬ ተብሎ ቀረ። ግሮሰሪዋ በር የዘንባባውን ግንድ ተገን አድርጎ

የተቀመጠ ትልቅ ድንጋይ ላይ ካርቶን ባል አድርጎ እንደ ወንበር በመጠቀም ሊስትሮ ይሠራል። ጫማውን የሚያስጠርገው ደንበኛ ድንጋዩ ላይ ተቀምጦ የዘንባባውን ግንድ ደገፍ ይልና ከድንጋዩ ሥር ብሩሹን ይዞ ለሚጠብቀው ፈንታው እግሩን ያቀብለዋል። ታዲያ ያች ድንጋይ 'የፈንታው ድንኩዬ ድንጋይ' ነው የምትባለው። የእኛ ሰፈር አክሱም ናት... የእኛ ሰፈር ላሊበላ ና ... የእኛ ሰፈር ወቅር የሊስትር ወንበር ናት ... የእኛ ሰፈር አፈ ታሪክም ናት ...!

"በድሮ ጊዜ እግዜር ለቅዱስ ድንቡሎ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፣ 'ልጄ ድንቡሎ ሆይ፣ ሞቅር የእግሬ መርገጫ መሆኑን ሰምተሃል... እንግዲህ እግሬ ምድር ላይ ሲያርፍ የወርቅ ጫማዬን ትቦርሽ ዘንድ የእግሬን ማረፊያ ድንጋይ በዚህ አስቀምጥ ...' የሚል ራዕይ ተገልጦለት ከእንጦጦ ድረስ ይቺን ድንጋይ በኤኔትሬ መኪና አስጭኖ ወደዚህ ሰፈር አመጣት ..."

ታዲያ የሰፈሩ ልጆች ለቡሄ አባባ መከብብ ግሮሰሪ በር ላይ እንሄድና ጭፈራውን እናወርደዋለን። እሳቸውም በጢም መላጫቸው ግራ ቀኝ ጉንጫቸውን በደረቁ እየፈገፈጉና ብረቱ ላይ ኳ ኳ አድርገው እያራገፉ ግጥማችንን በጥሞና ያዳምጣሉ፤

"እዛ ማዶ...

ሆ!

አንድ ሞተር

ሆ!

እዚህ ማዶ!

ሆ !

አንድ ሞተር!

ሆ!

የኔ አባባ መከብብ!

ሆ!

ባለ ዲሞፍተር !

"ሂዱ ወዲያ ! የምን ዲሞክራሲ ነው ..." ይሉና ይቆጣሉ። ረስተነው ነው እንጂ አባባ መኩቡብ የጦር መሣሪያ አይወዱም። እንደውም መሣሪያ ታጥቆ ወደ ግሮሰሪያቸው የሚሄድ ደንበኛ ያስወጣሉ እየተባለ ይወራ ነበር። ታዲያ ይችን አመላቸውን ስለምናውቅ በቁጣቸው እንደነማጥም። ፊንታው ድንቡሎ ወዲያው ግጥሙን ይቀይረዋል ... እሳቸውም ወዳቋረጡት ጢም መላጨታቸው ተመልሰው አንጋጥጠው የአንገቻቸውን ሥር እየፈገፈጉ ዓይኖቻቸውን ጨረር እንዳይወጋቸው ጨፍነው ይሰሙናል ...

"እዛ ማዶ! አንድ አፍንጫ፣

የኔ አባባ መኩቡብ ባለ ወፍራም...!

እዛ ማዶ! አንድ በሬ፣

የኔ አባባ መኩቡብ ጀግና ገበሬ..."

"ሃሃሃሃ እንደሱ ነው የሚባለው ... እደጉ! እደጉ! ... ድንቡሎ! ... ና ወዲህ ...!" ይሉና የጢም መላጫቸውን ወደ ግራ እጃቸው አዘዋውረው በቀኝ እጃቸው አጭሯን የሥራ ገዋን ወደ ቀኝ ገልበው ሱሪያቸው ኪስ ውስጥ እጃቸውን ካስገቡ በኋላ በጣም ብዙ ተዘበራርቆ የተቀመጠ ብር (ድፍን የሞቱና የሃምሳ ብር ኖቶች የሚበዙበት) ዘግነው ያወጣሉ። ከዝግኑ መሃል መርጠው ድፍን አምስት ብር ከለዩ በኋላ (ይሄ ድርጊታቸው ቀልባችንን ስለሚ[illegible] ጭፈራችን [illegible]ቀዛ ይላል...) ሌላውን ብር ወደ ኪሳቸው መልሰው ሲያበቁ ብሩ ላይ ትፍ [illegible] ድንቡሎ ግንባር ላይ ይለጥፉታል (እንደውም ግንባሩ ለሽልማት ይመቻል) ...እኛም ሞቅ ይ[illegible] በአዲስ ጉልበት ምርቃቱንም ለየት ባለ ፋቅር እናኝርጎደጉደዋለን።

"የመኩብቡን ቢት!

ድግምን !!

ዓመት

ድግምን !!

ዐርቅ ይ[illegible]ሰስበት!!

እማማ ንግሥት በወርቅ የተሽቆጠቆጠ ተራራ የሚያህል ሹርባቸው ላይ ነጠላቸውን ጣል አድርገው (ነጠላ የለበሰ ጉብታ...) ነጭ ባለጥልፍ የሐገር ባህል ቀሚስ ደረቱ ላይ ትልቅ መስቀል የተጠለፈበት ቀሚስ ለብሰው ከቤት ብቅ ይላሉ። ባዷቸውን አይደለም...፤ ጋሻ የሚያክል፣ ከስፖንጅ ፍራሽ ላይ የተቆረጠ ትልቅ ቁራጭ ስፖንጅ የመሰለ ድፎ ከፍ አድርገው ይዘው...፤ በዜማችን እየተውረገረጉ ዳቦውን እንደዋንጫ ከፍ አድርገው እያስጨፈሩት ከሚፍለቀለቅ ፈገግታቸው ጋ ብቅ ይላሉ...። አቤት ደስታችን! ምራቃችን በአፋችን ይሞላል። ዳቦውን እንደ ጎበዝ ጎል ጠባቂ የዳንኤል መረቡን በተጠንቀቅ ዘርግቶ ለቆመው አለባቸው ይሰጡታል። በዳንኤሉ ተቀብሎ ጥቅልል ያደርግና ደረቱ ላይ ለጥፎ ያቅፈዋል። ፍጥነቱን ለተመለከተው መልሰው እንዳይቀሙት የፈራ እኮ ነው የሚመስለው !

"ዓመት አውዳመት!

ድገምን!

ዓመት!

ድገምን!

የንግሥትን ቤት!

ድገመን!!

ዓመት!

ድገመን!

ወርቅ ይፍሰስበት ...!"

"እደጉ ልጆቸ እድእግ በሉ...!! ወርቅ ይፍሰስበት ሚለት ትልቅ በረከት ነውኮ...፣ ከወርቅ በሏይ ሙን አለ...? ቡዙ ተብዛዙ ቁሙ ነገር ያቡቋችሁ...! አቡነ አረጋዊ ጩንቅላታቹሁን ይከፋፍተውና ትሙሩቱ ይግባዓባችሁ..." ብለው ይመርቁናል። አፋቸው ይጣፍጣል።

እማማ ንግሥት ኤርትራዊት ናቸው። ታዲያ በአማርኛ ሲያወሩ እንደበታቸው አይጠጉበም። ጥርስ የማያስከድኑ ተጨዋች ናቸው። ሲቆጡም በዚያው ልክ ነው ይባላል - ሲቆጡ አይተናቸው አናውቅም

እንጂ...!! አባባ መኪብብ ታዲያ ሚስታቸውን ሲወዷቸው ልክ የላቸውም። አንድ ቀን እትየ ንግሥ ታመው (የደም ግፊት የሚባል ነገር ነው አሉ) እንቡላንስ ተጠርቶ ጎረቤቱ ሁሉ ሲረረ መኪብብ እንደ ሕፃን ልጅ በሁለት እጆቻቸው ጭንቅላታቸውን ይዘው ስቅስቅ ብለው ሲያለቅሱ ሲጮሁ አይቻቸዋለሁ ! ሰው ሁሉ አያባበላቸው !

"እትየ ንግሥት ... እናቴ፣ እህቴ፣ ጓደኛዬ ሜዳ ላይ እኔን ጥለሽ ..." እያሉ...

ባልና ሚስቱ አንዲት ልጅ አለቻቸው፤ ህይጋ የምትባል፣ ፈረንጅ አግብታ ውጭ አገር የምትኖር፣ በየሦስት ዓመቱ እናትና አባቷን ልትጠይቅ ስትመጣ ከታች ሰፈር ጀምሮ እስከላይ ሰፈር ድረስ ሁሉም ቤት እየገባች ጎረቤቱን ሁሉ ትስምና ሃምሳ ሃምሳ ብር ትሰጣለች። ለትልልቅ ሰዎች ነው የምትሰጠው።... ከእኛ መካከል የሃምሳ ብር እጣ የሚወደቅለት ፈንታው ድንቡሎ ብቻ ነው፤ የፈንታው እናት ሚስኪን ናት...፤ በሽተኛ ስለሆነች ከአልጋ ላይ አትነሳም። ፈንታው አባባ መኪብብ ግሮሰሪ በረንዳ ሥር ጫማ እየጠረገ እና እየተላላከ ነው እናቱን የሚያስታምመው። አባቱ በደርግ ጊዜ ዘምቶ ይሙት ይትረፍ ሳይታወቅ በዛው ቀልጦ ቀርቷል። ያው የህይጋ ሃምሳ ብር ፈንታው ድንቡሎን የሚያካትተው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም !

አንድ ቀን ታዲያ የስፖርት ትጥቅ ለመግዛት ከመንደርተኛው ሳንቲም እንለምናለን። በአጋጣሚ ፊት ለፊታችን ህይጋ አሻንጉሊት የመሰለ ልጇን በደረቷ አቅፋ ስትመጣ ተገጣጠምን። ሌላውን መንደርተኛ ሳንቲም ውለድ እያልን ምናስቆም እኛ፣ ህይጋን ለምን እንደፈራናት እንጃ፤ ብቻ ገለል ብለን አሳለፍናት። በቀጣዩ ቀን ታዲያ አስጠራችንና እንኳን በእውናችን በህልማችንም አስበነው የማናውቀውን የስፖርት ትጥቅ ከነኳሱ ገዛችልን።

አቤ...ት! እንዴት እንደተደሰትን...! ለስንት ዓመት ታሪክ ሆኖ በመንደራችን ተወራ ! "ኳሱ የት ይቀመጥ" በሚል በመካከላችን ከባድ ክርክር ተደርጎ እኔጋ እንዲቀመጥ ተወሰነ። የተሰማኝ ደስታ ወደር አልነበረውም። ግን ምን ያደርጋል አንድ ቀን ያ ሉባዙ ሕፃናት ህልም የነበረ ኳስ ምጥ ይግባ ሰምጥ ሳይታወቅ ጠፋ። የጠፋው ከእኛ ቤት ስለነበር በቡድኑ አባላት ዘንድ ከፉኛ አስተችቶኛል፤ ለረዥም ጊዜ ያኮረፉኝ የሰፈር ልጆችም ነበሩ። በእግር በፈረስ በሰፈራችን ስርቻ ሁሉ ኳሱን ፈልገን ስናጣው በቃ ወደ ጨርቅ ኳሳችን ተመለስን። አሁን ካደግን በኋላ ሳይቀር የኳሱ ነገር ሲነሳ እወቀሳለሁ። እንደውም አሁን ካደግን በኋላ እድሜያችን ሃያዎቹ ውስጥ ገብቶ ተፈሪ የሚባለው የሰፈራችን ልጅ (አሁን አዉስትራሊያ የሚኖር) ኢ-ሜይል ሲያደርግልኝ ስለ ኳሱ ጉዳይ አንስቶ እንዲህ ብሎኛል፤

"አቡቹ እዚህ የፈረንጅ ሕፃናት ኳሶች ይዘው ሲሚወጡ ላይ ያች ህይጋ የገዛችልን የጣልከብን ኳስ ትዘ አያሰቻኝ ይቆጨኛል ሃሃሃሃ" እንረሳም እኮ እንዳንዴ !

***

ድንገት ነበር ነገሮች የተገለባበጡት፣ ልክ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ፣ እንደጎርፍ መጥለቅለቅ ሰፈራችን ውስጥ በአብሮ መኖር የፍቅር ቀለሊ የሆኑ ነዋሪዎችን ከሥራቸው እየመነገለ ድራሻቸውን ያጠፋ ድንገቴ ነውጥ። እንዴት ነው ሰው ድንገት ተነስቶ ትላንት አለፍኩት ወዳለው አረንቋ መልሶ የሚዘፈቀው...? "ሲደርሱብን ምን እናድርግ" ብሎ ነገር ...

"ኤርትራ ወረረችን...!" ተባለ።

"ምናባቷ ቆርባጊት ይች የእናት ጡት ነካሽ!" የሚሉ ደምፍላታም ሰዎች ሰፈሩን ሞሉት። ከየት አመጡት አማርኛውን...? መቻቻብ ታንከ ቢሆን፣ መትረየስ፣ በንብ ምናምን ገዙት ይባላል፣ ወይ በእርዳታ አገኙት...፤ ሰድብ ከየት ተፈበረከ ... ዛቻ መቼ ተረማዞ ነው በዜማ የተወለደው...? ትላንት እንደ ቦብ ማርሊ "ፀበኞች ካልታረቁ!" እያለ ሲያቀነቅን የነበረ ድምፃዊ "ፍለጠው! ቁረጠው!" ዘፈኑን ከየት መዝርጦ ቴሌቪዥኑን ሞላው...፤ ወይስ ሁሉም ዘፋኝ ለክፉ ጊዜ ያስቀመጠው ዘፈን አለው? ለጦርነት ማጥምጊ ዜማ መፍጠር ከፍቅር ዘፈን ይቀላል? ከቀበሌ ኪነት ቡድን እስከ አገር አቀፍ ታላላቅ ዘፋኞች ዘፈናቸው አይሄድ አይመጣ አንድ - "ብለው ፍለጠው ቁረጠው !!"

በዓይን ርግብግቢት ፍጥነት 'ለደኅንነታችሁ' ብለው ደህና ሰዎች ብለን ያመንናቸውን፣ ስንጣላ አስታራቂ፣ ስንቸገር ደራሽ የነበሩት ጎረቤቶቻችንን ሁሉ በአውቶብስ እየጫኑ አባረሯቸው። እማማ ንግሥትን ጨምሮ። ከመወለዳችን በፊት ኤርትራ የሄዱ የማናውቃቸው ብዙ እማማዎች ከዛም ተባርረው መጡ። ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ። ለካስ የመንግሥታት ፍርሃት እንደጅብ ያነከሳል - አገርንም ያስነከሳል...። አሁን እማማ ንግሥት ምናቸው ነው ለደህንነት የሚያሰጋው? በሹሩባቸው ውስጥ ቦምብ እንዳይቀብሩ ነው? ወይስ በድፎቻቸው ውስጥ ጥይት እንዳይደብቁ ...። እማማ ንግሥት 'ለደህንነት ስጋት ናቸው' ተብለው የተባረሩ ቀን ማታ ህልም አለምኩ...

ቀኑ ቡሄ ይመስለኛል። የሰፈር ልጆች እንደልማዳችን ተሰባስበን እማማ ንግሥት በር ላይ ቆመን እንጨፍራለን።

"እዛ ማዶ አንድ በሬ!

እዚህ ማዶ አንድ በረዶ!

የኔ እማማ ንግሥት!

,ፓራ ኮማንዶ ...!"

የእማማ ንግሥት በር ድንገት ብርግድ ብሎ ተከፈተና፣ በወርቅና በሐገር ባህል ቀሚስ የምናውቃቸው እማማ ንግሥት፣ የወታደር ልብስና ከስክስ ጫማ ለብሰው እናታቸውም ላይ የብረት ቆብ ደፍተው ድፎ ሳይሆን ዝናሩ የተንዠረገገ መትረየስ ጠመንጃ ደግነው፣ "አንች ዲቃላ ሁሉ ... በሬ ላይ ሙናበ ትናጫጨለሽ አቡነ አረጋዊ ድራሽ አባትሽን ያጥፉት!" ብለው ታታታታታታታታታታታታታ ቢያደርጉብን በተለይ እኔ ሰውነቴ ተበሳስቶ ወንፊት የሆነ ይመስለኛል...፤ እየጮህኩ ከህልሜ ባነኩ ...፤ እናቴ ከትራስጌ በኩል ቆማ "አቡቹ በሰማም በል ቅዠት ነው...!" ትላለች።

ያየሁትን ህልም ለማሚ ስነግራት ግን ተቆጣች...

"ምን እንደው የዛሬ ልጅ የነገሮችሁን ይዛችሁ ትጋደማላችሁ፣ ቅዠት ይተርፋችኋል ...፤ በል አርፈህ ተኛ!"

***

አባባ መክብብ እትዬ ንግሥት ወደ ኤርትራ ከተባረሩበት ጊዜ ጀምሮ ግራ እግራቸውን ሰብሰቦ ያዛቸው...፤ በከዘራ ድጋፍ ሆነ የሚራመዱት። የጢም መላጫቸውም ከእጃቸው ጠፋች። ነጭና ጥቁር ቡራቡሬ ፂም ትንሽ አገጫቸውን ሸፈነው...፤ ተዘናጉ፤ ሰፈሩ ተዘናጋ ...። አንድ ቀን በግሮሰሪዋ በኩል ሳልፍ አባባ መክብብ ከዘራው እጀታ ላይ የተነባበረ እጃቸው ላይ አገጫቸውን አሳርፈው አፋቸው ባዶ ነገር እያኘከ ትክዝ ብለው ተቀምጠዋል- በቀስታ ወደ ፊትና ኋላ እየተወዛወዙ። ሳልፍ ስል የውሃ ...፤ ንፍስ ካወቅሁ ጀምሮ ከበርሚሉ ተነጥላ የማታውቀው የመርቲ ጣሳ በቦታዋ የለችም። ጣሳዋ ትታሰርባት የነበረችው የኤሌክትሪክ ገመድ ባዶዋን ተንጠልጥላ ነፋስ በቀስታ ይወዘውዛታል!

ከበርሚሉ ራቅ ብሎ ... የፈንታው ድንቡሎ የሊስትሮ ድንጋይ ከዘንባባዋ ሥር ባዶዋን ትታያለች፣ ፈንታው ድንቡሎ "ለአገሩ ዘመተ...!" መባሉን ሰምቻለሁ። ፈንታው ጋር ከደግን በኋላ ብዙም ቀታ ኖሮን አንገናኝም ነበር። ቢሆንም አንዳንዴ በዛ ሳልፍ ሰላም እንባባላለን። ጫማዬንም ይቦርሽልኛል።

እንደውም ወደ ወታደር ቤት ሊሄድ አካባቢ ጫማዬን እየቦረሸልኝ ድንገት የሐፍረት ፈገግታ ፊቱን አጅቦት እንዲህ አለኝ (በወሬ ወሬ ተነስቶ ሳይሆን እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ...)

"አብርሽ የዛን ጊዜ ሀዲጋ የገዛችልን ኳስ ታስታውሲታለህ ?"

"እንዴ ታዲያ ያችን ኳስ ማን ይረሳል...?" ተሳሳቅን። ፈንታው ጫማዬን መቦረሹን ገታ አድርጎ መሬት መሬት እየተመለከተ እንዲህ አለኝ፣

"ያኔ ኳሷን ከግቢ የወሰድኳት እኔ ነበርኩ...፤ አማማ ብር ፈልጋ እጄ ላይ ሳንቲም ስላልነበረኝ ለሆኑ ልጆች ሠላሳ ብር ሸጥኩላቸው።"። ነገሩ አስደነገጠኝ። ፈንታውም ቅሬታ ባረበበት እኔም ግራ በተጋባ ፊት ተሳሳቅን፣ እናም ሁለታችንም ወደ ጥልቅ ዝምታ ገባን። ለምን እንደነገረኝ አልገባኝም ነበር። ፈንታው ኳሷን ወስዶ ይሸጣታል ብሎ የጠረጠረ ያኔ ማንም አልነበረም...፤ ማንም !! አሁን ራሱ ቢነገረው ማን ያምናል! ፈንታው ድንቡሎ ፊቱ ወርቅ ቢዘራ ቅንጣት የማይነካ ንፁህ ደሃ ነው።

ጫማዬን አሰቦርሼ ስነሳ እንዲህ አለኝ፣ "አብርሽ ይቅርታ...!"

"ኧረ ኢታካብድ ይሄ እኮ ተራ ነገር ነው፤" አልኩት፣ ግን ለምን እንደሆነ እንጃ ቶሎ ከአካባቢው መራቅ ፈልጌ ነበር።

###

ወሬው ሁሉ ጦርነት ሆነ ... ሸለላው፣ ቀረርቶው፣ መፎከሩ። እንደ ቀልድ ቃል ጥላቻ ለበሰ። ጥይትና በንብ ለብሶ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ ድንበር ላይ አደረ። ገና እሳቱ ሳይጠፋ...፤ ገና ወጣቶች እየጨፈሩ ወደ ድንበር ሊፋለሙ በሞኮነት መኪና ጨፈቃ መስለው ተጭነው ሲሄዱ...፤ ገና በጠዋቱወደ መንደራችን ሁነኛ ሰው መርዶ ይዞ መጣና እንደ መርፌ የሚወጋ ቀፋፊ ጩሀ መንደራችን ላይ ዘራ ...

"ፈንታው ድንቡሎ ሞተ...!"

ከመጀመሪያዎቹ ዘማቾች መሐል ነበር ፈንታው ድንቡሎ...

አብሮ አደጋችን ፈንታው ሞተ።

ከአባባ መኮብብ ግሮሰሪ በረንዳ ሥር ዛሬም የፈንታው ድንቡሎ ድንጋይ አለች !

ታዲያ መንደርተኛው ተሰባሰበና ለፈንታው አለቀሰ። እዛው አባባ መከብብ በረንዳ ሥር የፈንቷ ድንጋይ ላይ አለቀሰ ጎረቤቱ። አባባ መኩብብ ከዘራቸውን አገጫቸው ሥር አስደግፈው ግራ ቀ እየተወዘወዙ እንጉርጉሮ የመሰለ ዜማ ያወጣሉ። አያለቅሱም፤ ማንንም አይመለከቱም፤ ዝም ብ መወዝወዝ። ሰዉ ተበታትኖ ወደየቤቱ ገብቶ እንኳን መወዛወዛቸውን አላቆሙም - እስከ በተቀመጡበት ... እእእእእእእ...እእእእእእ ..... እያሉ !

###

ቀበሌያችን ግቢ ውስጥ ለዘመቻ የተመለመሉ ወጣቶች የሽኝት ፕሮግራም ነበር። ሰንጋ ተጥሎ፤ ብ በግ ታርዶ፤ ሰዉ ቢራ እየተራጬ፤ ጀግንነታችን እየተወሳ ... እድዋ፤ ማይጨው እየተገረበ፤ አባ ለዘማች ወጣቶች ባንዲራ እያስረከቡ፤ ወጣቶቹ ተንበርከከው ባንዲራውን እየተረከቡ፤ እናቶች እል እያሉ፤ ዘፋኞች ስለአጥንት መከስከስ፤ ስለደም መፍሰስ እየዘፈኑ... "እዝማቹ ሕዝብ፤ ዘማች ሴ ሂዱና ጠላቶቻችሁን አደባዩ!" ብሎ እየላካቸው ...

በቀበሌው አጥር አጠገብ እጆቼን ኪሴና ኪሴ አስገብቼ ወደ ቤቴ እያዘገምኩ ነበር - ወደ አስራ ሁ ሰዓት አካባቢ ይሆናል ማታ። ታዲያ አንድ ውሻ አጥሩ ጥግ የወደቀ የበግ አንጀት እየጎተተ በአ አለፈ...፤ ማመን አልቻልኩም...፤ የእማማ ንግሥት ውሻ "አሲምባ..."

###

"ዘመቻ ፀሐይ ግባት በድል ተጠናቀቀ!" አለ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን። ወጣቶቹ በደስታ አገር ጠበበ በየመንገዱ የደስታ ፌሽታና ጭፈራ ሆነ። የመኪና ጡሩምባ ጩኸት፤ የእናቶች እልልታ፤ የአባቶ ዘራፌዋ ...! የሴቶች ጉሮ ወሸባዬ ... የዘንባባ ዝንጣፊና ባንዲራ የያዙ ወጣቶች የመኪናዎች እቃ መጫ ላይ እንደንብ ሰፍረው ይጨፍራሉ፤ በደስታ ይጮሃሉ። ቴሌቪዥኑ ደጋግሞ የምሥራቹን ያበስራል

ቃለ መጠይቅ በሬዲዮ ለጀግና ወታደሮች ... ለጀግና የጦር መሪዎች፤

"እስኪ የጦር ውሎዎትን ይንገሩን..."

"ሻእቢያ እንደ ፍልፈል ጉድጓድ ቆፍሮ ተደብቆ የነበረ ቢሆንም፤ ከጉድጓዱ በጀግና ልጆቻችን እውተ ቀብረነዋል ...።" ሕዝቡ በጀግኖቹ ኮራ!! አባባ መኩብብ ግሮሰሪያቸው ውስጥ በስልክ እያወሩ ነበ ጭፈራው ያደከመን የሰፈር ልጆች ግሮሰሪዋ በረንዳ ላይ ተሰባሰበን፤ የሰማነውን ጀብዱ በቴሌቪዥ

ያሳዩንን የጀግኖች ውሎ ለመቱና ጊዜ ከአፋችን እየተነጣጠቅን እያወራን ... ያዘዝነውን ቀዝቃዛ ኮካ እንኮነሜለን።

አባባ መከብብ እያዘገሙ ወጡና አጠገባችን የበረንዳውን የብረት ደፍ ደገፍ ብለው ቆሙ። ዞር ብለው ተመለከቱንና እንደ እብድ ክት ክት ብለው ሳቁ ... ሰውነታቸው እየተርገፈገፈ ሳቁ ... ግራ ተጋብተን አየናቸው። አባባ መኩብብ ሚስታቸው እትዬ ንግሥት ከሄዱ በኋላ እንኳን ሲስቁ ይቅርና የተቋጠረ ፊታቸው ሲፈታ አይተን አናውቅም ነበር...።

"ሰማችሁ ልጆቼ...!! ልጄ ህደጋ ከአሜሪካ ደውላ ያለችኝን ሰማችሁ...!" አሉን በግርምት ተራ በተራ እየተመለከቱን...።

"ምን አለች አባባ መከብብ?" በጉጉት ጠየቅናቸው።

"አሁን እናቷ ጋር ኤርትራ ደውላ አናግራት፣ እኔንም ሰላም ልትል ነበር የደወለችው ..... ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ" ብለው ሳቁ። አእምሯቸው የተናጋ መስሎን ፈራን። እንደ ምንም ሳቃቸውን ገቱና ፊታቸውን በምሬት ኩምትር አድርገው፣

"አስመራም ሕዝቡ አደባባይ ወጥቶ ጉሮ ወሸባዬ እየተጨፈረ ነው እኮ ነው የምትለኝ !! ሆሆ ይች አገር እንደ ካሴት ሆነች... በዚህም ዘፈን ...፣ ስትገለበጥም ዘፈን ... ታዲያ ለድንቡሎ ማን ያልቅስ ...? እኮ ድንቡሎ ለምን ሞተ ...?" ብለው አንድ በአንድ ተመለከቱን። ከእኛ መልስ ሲያጡ ወደ ፈንታው ድንቡሎ ድንጋይ ዞረው በትካዜ ጭልጥ አሉ።

የፈንታው ድንቡሎ ቦታ ላይ አንድ ትንሽ ልጅ አዲስ የሲስትሮ ሳጥን ይዞ ተቀምጧል። ቀና ብዬ ግሮሰሪው በር ላይ በግራ በኩል የቆመችውን የዘንባባ ዛፍ ተመለከትኳት...፤ ለጭፈራው ቅጠሎቿን ዘንጥፈናቸው መለመላዋን ቆማለች፤ ብቻዋን የቆመች ዘንባባ ...፤ ከአስመራ ዘንባባዎች መሐል አምልጣ የመጣች መሰለችኝ፣ "እዛም ጭፈራ! እዚህም ጭፈራ...!" ብላ። ዘንባባዎቹ ሁሉ ወደ አስመራ ሲሜኑ በሆነ ተአምር የቀረችም መሰለኝ።

ሄደችም መጣችም ከዘንባባ ጫካዋ የተገነጠለች አብዮተኛ ዘንባባ !!

# ፈገግ ሳቃችንን ቀምተውን

ሁልጊዜ ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እነሳና እማርራለሁ። እናቴ ደግሞ በዚህ ሰዓት እኔን ማየቱ በራሱ ያስቃታል። ያሳቃት ጉዳይ ቢያበሳጨኝም ሳቋ ስለሚያስቀኝ እየሳቅኩ እናደዳለሁ። እናቴ ስትስቅ ማንም አለመሳቅ አይችልም። ዓይኖቿ ይጨፈኑና አንገቷ ጠብ እስኪል ረዥምና በየመሃሉ 'እፎይ' ወይም 'ውይ' የሚሉ እረፍቶች የተከተቱበት ሳቅ…

አባቴ ኮስታራ ነው። እናቴ ፊት ሲሆን ምንጊዜም ላለመሳቅ ይታገላል። በሳቅና በመኮሳተር መካከል ላይ የቆመ ፊት ያለው አባት ደግሞ ያስቃል። "ውይ ስቀህ ብታርፈው ምናለ እንዳልዬ፡ እንዲህ ግዳ የገባው አንበሳ ከምትመስል ሃሃሃሃሃሃሃሃ … ውይ … ሂሂሂሂሂሂሂሂ ፊትህ እኮ ሲያስቅ ሀሀሀሀሀሀሀሀ … በቃ እናቴ አታቆምም…

አንዳንዴ ብቻዋን ሆና በሳቅ ፍርስስስስስ ስትል እደርስና፣ "አረ ማሚ ሰው ጉድ ይልሻል" እላታለሁ።

"ውይ በስማም እቴ ስትገባ አታንኳኳም … ሆሆ አስደነገጥከኝኮ ግላ ቢስ" ትልና በሳቅ ፍርስስስስስ…

"አታየውም ሁለቱ ድመቶች ተባልተው የኩሽናውን ዕቃ ጨረሱት … ስኳር ነሽ፣ ሽሮ፣ በርበሬ ድፍትፍት ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ … ወይ ጉድ ጦርሜዳ" ትላለች የተደፋፋውን እያፋፈሰች። በቃ እናቴ እንዲህ ናት - ሳቅ የተመረቀላት…

ዛሬም ታዲያ ገና በጠዋቱ ሳቋን ጀመረችው።

*አብርሽ ደህና አደር...ክ ኪኪኪኪኪ !!* ሳቋ ለሰላምታ እንኳን ፋታ አልሰጣትም። ፊቷን እየታጠበች ትሲቃለች፣ ቁርስ እየሰራች ብቅ ኢያለች ትስቃለች፣ መናገርማ አትችልም - ሳቋ ስለሚቀድማት መናገር አትችልም።

*አብርሽ... ቁርስ ደርሷል ሀሀሀሀሀሀሀሀሀ... ሃሃሃሃሃሃሃ... ሁሁሁሁሁ ፎይ..* ትስቃለች። ሰሃኑ ከእጇ ሊያመልጣት እስኪደርስ ትሲቃለች። ኢያንዳንዱ ቃሏ ረዥም የሳቅ ጅራት አለው...

"ኧረ ማሚ አይደብርሽም እንዴ..." እላለሁ ብስጭት ብዬ።

"አይ... እኔኮ ሆሆሆሆሆሆሆ ... ያ ... ሳቀኝ ... ሀሀሀ ... ያሳቀኝ ... አብርሽዬ..." ኢያቀራረበች ዓይኖቿን የሞላውን እንባ በክንዷ ትጠርጋለች - በጠዋቱ ይሄን የሚያህል ሳቅ ...!!

አባቴ ያንኑ ግራ የገባው አንበሳ የመሰለ ፊቱን ይዞ ከመኝታ ቤት ብቅ ይላል። አሁን ማሚ በእጇ የያዘችው የሻይ ማንቆርቆሪያ እስኪያመልጣት ሳቋ ወሰኑን አልፎ ይንፎለፎላል ... ወደ አባቴ እያየች...

"ዛሬም እየጠበቀው ነው..." ይላል ወገቡን ይዞ...

"ብደንብ ነዋ ... ሃሃሃሃሃሃ" ትመልሳለች እናቴ።

ጎረቤታችን አቶ ይፍሩ የሚባሉ ሰውዬ አሉ። መኪና አለቻቸው (ካለመኖር የማትሻል) ክርክስ ያለች ዲኤክስ። ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ እቺን መኪና የመግፋት ጎረቤታዊ ግዴታ አለብኝ። ደግሞ ከብደቷ፣ ባቡር የምገፋ ነው የሚመስለኝ። ለንንንንን ካካካካ ትልና ዝም !! እንደገና እንገፋለን። በዋናነት እኔ፣ ኤልያስና ፍቅሩ ነን የምንገፋው። አቶ ይፍሩ በራቸው ላይ ይቆሙና የትም ዓለም ተሰርቶ የማያውቅ 'ስፖርት' (መወራጨት) እየሰሩ ሦስታችንን ይጠብቁናል። ዋናው ሥራቸው እኛን መጠበቅ ነው። ትምሕርት ቤት ለመሄድ በእርሳቸው በር ማለፍ ግዴታ ስለሆነ የትም አናመልጥም።

ከዛ ከቤት ሰወጣ፣ "ወጣት ... የነብር ጣት መጣችሁ ... እስቲ እቺን ነገር እናስነሳት..." ይሉና ወደ ግቢያቸው እየመሩ ያስገቡናል። መግፋት ነው ያችን መኪና (የመኪና ስም አይገዛ)

"ግፋ ግፋ ግፋ ... ትንሽ ... " እንንንንንንንን ... ዝም ! ተግተግተግተተግተተግገተግ ... ዝም ! "በል ግፋ ... አብረሃም ዛሬ ደከም ብለሃል ግፋ እንጂ ... ግፋ ግፋ ... ተርርርርርርርርርር ፈትለክ ... አንዳንዴ መኪናዋ ስትፈተለክ በደረታችን መንገዱ ላይ እንለሸለሻለን።

አሲፓልቱ ላይ እንደተለሸለሸን በጉጉት እናያታለን። እየተንተፋተፈች ከሩቅ በኢብሩ ሱቅ ስትታጥፍ ከወደቅንበት ተነስተን በእፎይታ እጃችንንና ልብሳችንን እያረጋገፍን መንገዳችንን እንቀጥልና በኢብሩ ሱቅ አጥፍ ሰንል ያውም አቀበቱ ላይ ቆማ ትጠብቀናለች።

"ዛሬ ሰይጣኗ መጥቷል ... ወደዛ ሽጮ ካላረፍኩ" እያሉ ይጠብቁናል። ሁልጊዜ ነው የሚሉት። ግን ያበደ እኛን የሚገዛ፣ እብሮ እኛን ካልገዛ በስተቀር።

...ግፋ ...ግፋ ... ተግተግ..ተግትግግተገትግትትግግ ..... ዝም !!

እናቴ ታዲያ የሚያስቃት ይሄ ነው። ቀስ ብላ የቤታችንን መጋረጃ ገለጥ አድርጋ በሳቅ ፍርፍር እያለች፣ "የዛሬው ስፖርት ደግሞ ይለያል" ትላለች። ከዛም፣ "አብርሽዬ ስፖርቱ እኮ ለናንተም ሳይጠቅም አይቀርም" ትልና ፍርሰሰሰሰሰስ በሳቅ !

ትላንት ማታ ታዲያ አባቴ እንዳለ ይሄን ነገር ሰማና ተቆጣ...

"በቃ ከአሁን በኋላ አቸኩላለሁ ይቅርታ ብለህ እለፍ !! መኪና በመግፋት የተዳከመ ሰውነት ይዞ ትምሕርት ቤት ለምን ይሄዳል ... እንዳትገፋ ... እንደ ጎረቤት አንድ ቀን ሁለት ቀን መተባበር እንድ ነገር ነው፤ ሦስት ወር ሙሉ.. ለምን አያሳራም ... እንዴዴዴዴዴዴደዴ ...አያስቅም !!" አለ እናቴን እያየ፣ እናቴ ወደ ውስጥ ገባች ልትስቅ እኮ ነው - አታብሳጭም ? አባቴ ከልቡ በነገሩ ተቆጥቶ ነበር፣ "እንደ ... በሌሊቱ የማንንም ቆርቆሮ..."

"አብርሃም"

"አቤት አባባ"

"ስትገፋ ባይህ ውርድ ከራሴ፣ ቸኩያለሁ ብለህ እልፍ ... እ"

"እሺ"

"አዎ ... ይሉኝታ አያስፈልግም። አንዳንዴም እንደ ፈረንጅ ማሰብ ጥሩ ነው። ማንም የወዘፈውን ሰንገፋ ነው እድሜያችን የገፋው። ሲቆም ደሃው ይገፋል፣ ሲነሳ የሚንፈላሰስበት ሌላ - እንዳትገፋ ...!!

ጆሲና ወረቀት የያዘውን አይለቅ፣ አባቴ እንደመከረኝ አቶ ይፍሩን፣ "ይቅርታ ፈተና ስላለብኝ ዛሬ

አለገፋልዎትም ብዬ በቀጣዩ ቀን አለፍኳቸው። ጓደኞቹም በየራሳቸው ምክንያት አንገፋልዎትም ብለዋቸው ኖሯል..."

ማታ ወደ ቤት ስመለስ ማሚ ገና ስታየኝ ሆዷን ይዛ ሶፋው ላይ ቁጭ ብላ በሳቅ ፍርፍርርርርርርር ... አለች።

የዛሬው ይለያል...

ጉዳዩ እንዲህ ነው - እኔ አቶ ይፍሩ ጋር ስነጋገር አባቴና እናቴ በመስኮቱ መጋረጃ ተከልለው ያዩ ነበር።

'እንቢ' ብዬ ሳልፍ አባቴ በልጁ ኮራ። "ነብዝ የኔ አንበሳ እንዲህ ነው ...! ከዚህ አድሜው በይሉኝታ ከተሸበበ የማንም መጫወቻ ነው የሚሆነው..." አለና፣ "አሁን እንቺም አስኪ ውጣልሽ ሳቂ" አላት እናቴን። እንኳን ተፈቅዶላት እንደውም እንዲያው ናት። አባቴም ሳይስቅ አልቀረም እንደውም ሳይጎነታተሉ አይቀሩም እናቴ እና አባቴ፣ "ውይ አንዳልዬ የጣድኩት እንቀላል አረረ..." እያለች እየሳቀች እየተጎነታተሉ እያለ፣

በር ተንኳኳ...

"ማነው" አለ አባቴ።

"እንደምን አደራችሁ..."

አባቴ በሩን ከፈተ፤ አቶ ይፍሩ ነበሩ። ስሞታ ሊናገሩ ነው ብለው እናትና አባቴ ሲጠብቁ፣

"እንዳለ አባክህ እቺ መኪናዬ ትንሽ አስቸግራኝ የሚገፋልኝ ሰው አጣሁ - ይቅርታ ትተባበረኝ..." ብለውት እርፍ። 'የልጅ አዳ ላባት' ሆነቻ ተረቷ ተገልብጣ !!

"መጣሁ መጣሁ ምን ችግር አለ ደሞ ለጎረቤት..." ሲል እናቴ መኝታ ቤት ገብታ እስከ ምሳ ሰዓት ሳቀች...

ይሄንን ስትነግረኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእናቴ ጋር በሳቅ ተወዳደርኩ።

ማታ አባቴ እንዲህ አለኝ፣

"አብርሽ ክላስ እንዴት ነው..."

"ጥሩ ነው"

"እእ ዛሬ ቢሮ ተቀምጬ ሳስበው ... ማታ የመከርኩህ ነገር ... ልክ አልመሰለኝም - ሶሪ"

"የትኛው ጉዳይ አባባ"

"የአቶ ይፍሩ መኪና ጉዳይ"

"እየሁ ትልቅ ሰው ናቸው። በዛ ላይ ልጆቻቸው ውጭ አገር ነው ያሉት። ብቸኝነቱ አለ። በባሕላችንም ጎረቤት መርዳት ጥሩ ነው። እግዚያብሄርም በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ....ቁጥር.... ልጄ ሆይ ታላቆችህን አክብር፣ አንተም ባረጀህ ጊዜ ትከበራለህና ይላል፣ እና እስኪያስተካክሏት ድረስ መኪናቸውን ብትገፋላቸው ምንም ማለት አይደለም ... ለአንተም ስፖርት ነው" አለ ኮስተር ብሎ።

ማሚ የሆነውን ሁሉ እንደነገረችኝ አልጠረጠረም ነበር። አይ አባባ በሱ ቤት 'አሪፍ' መሆኑ ነው።

በኋላ መኝታ ቤት ሆኜ ማሚ እየሳቀች፣ "አንተ ፖለቲከኛ መሰልከኝ እኮ ... ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ..." ስትል ሰማኋት ለአባቴ። አብረው በሳቅ ፍርስስስስስስስስ...። አባባ እዳውን ለኔ ወርውሮ መሳቅ ጀመረ .. እኔ ለምቦጬን ጣልኩ።

አባቶቻችን በተለሳለሱ ምክር፣ በተሸምነምንኝ ተረት እነሱ መግፋት ያልቻሏትን ሰንት ጣጣ 'በፍቅር' አውርሰውናል !! ማሚ እንዳለችውም ፖለቲከኞች እንዲህ ይሆን እጥፍ ብለው በቲቪ ፈገግ ሲሉ የምናያቸው። የማሚ ሳቅ ይሰማል ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ እፎይ ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ ሚስኪን አብርሽ...

# አበበ በሶ በላ

አባቴ ትንሽ ቀበጠ። በእርግጥ አባት "ቀበጠ" አይባልም፣ ግን እናቴ ናት እንዲህ ያለችው!

"ይሄ ሰውዬ ቀበጠ" አለች አንድ ቀን።

"ማን?" ብላት

"አባትህ ነዋ !" አለችኝ ኮስተር ብላ

"ምን አደረገ?"

"ሥራ ከምፈታ ብሎ በር ላይ ቆቡን ቀዶ እየሰፋልህ ነው" ብላ እያጉተመተመች ወደ ጓዳ ገባች። አባቴ ቆብ እንደሌለው ባውቅም የእናቴ ንግግር ግራ አጋብቶኝ "እስቲ አባባ የምን ቆብ ቀዶ እንደሚሰፋ ልመልከት" ብዬ ወደ ውጭ ወጣሁ። እውነትም አባባ "ሥራ ከምፈታ" ብሎ ቆቡን ቀዶ እየሰፋ ነበር።

ይታያችሁ! ከአራት ዓመት በፊት አንድ የስልክ ምሰሶ ከእኛ ግቢ ውጭ አጥራችንን ተጠግቶ ወደቀ(በመኪና ተገጭቶ)። ,ታዲያ የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን ሠራተኞች አዲስ ምሰሶ ተክሉና አሮጌውን ምሰሶ "ነገ ተመልሰን እንወስደዋለን" ብለው የወደቀበት ትተውት ሄዱ። በቴሌ አቆጣጠር አንድ ቀን አራት ዓመት የሆነ ይመስል ይኸው ምሰሶው አራት ክረምትና አራት በጋ አሳልፎ ዛሬም እንደተጋደመ አጥራችን ጥግ አለ።

አባባ ታዲያ በጧቱ ተነስቶ ይሄን ግማሽ አካሉን አፈር ውስጥ የተቀበረ ግንድ ብቻውን ለማውጣት ይታገላል።

"አባባ ምን እየሠራህ ነው?" አልኩት፤

"የነዚህን ሌቦች ንብረት ወዲያ ካጥሬ ጥግ ልወረውርላቸው ነው"

"ቢቀመጥስ ምን አደረገህ አባባ?" አልኩት ግንዱን ከተቀበረበት ሊፈነቅል ሲታገል ላግዘው እየተጠጋሁ።

"...ስልክ አይሠራ ልጆቼ ጋር እንዳላወራ አቋራረጡኝ....ምነው ስንል ቴሌ ኔትዎርኩን አቋረጠው ይሉናል ! ባንክ ቤት ኔትወርክ የለ፣ ልጆቼ የላኩልኝን ብር እንዳላወጣ... ምነው ስንል ቴሌ! የቤት ስልክ ይኼው ከተቋረጠ ዘመን የለውም፤ እስካሁን ግን ቆጠረ እያሉ ይገፈግፉናል ...በየቦታው የወደቀ ንብረታቸውን አይሰበስቡና እኛ ላይ ቆጠረ እያሉ ብር መቆለል ብቻ። ታዲያ የነሱን ፊሳ ማን ይሸከማል? ላያችን ላይ ሞተውብናል እኮ!"

አባባ እንዲህ እያማረረ ምሰሶውን ከአንድ በኩል አነሳው። ለዓመታት የተቀበረው ግንድ ሲነሳ ከስሩ ልምዝምዝ ቢጫ ሳሮች በብዛት ታዩ። ትኩስ የአፈር ሽታም አፍንጫዬን ሰነፈጠኝ። በትኩሱ አፈር ላይ የጉንዳን ሰራዊት ተራወጠ፣ ተርመሰመሰ ...በህይወቴ እንዲህ ብዙ ጉንዳን አይቼ አላውቅም ...አባባ ጉንዳኖቹን ሲመለከት "ድሮውንም የሞተ አሰራር ተባይ መራቢያ ነው" አለ። አፈሩ ሽክሙ ሲነሳበት በአፎይታ የተነፈሰ እስኪመስለኝ የትኩሱ አፈር ሽታ ሽቅብ ወደ አፍንጫዬ ተነነ። ጥሎብኝ ይሄን ሽታ አወደዋለሁ።

"እኛም ኔትወርክ አጥተን፣ ሥራ አጥተን፣ ቤት አጥተን፣ ጥራት ያለው ትምርት አጥተን፣ ምክንያትና ሰበብ እንደዚህ ግንድ ተገምነን እንዲህ ነው የተጥመለመልነው፤" አለ አባባ የፀሃይ ብርሃን ያጠቆረው አልጌ መሳይ ተከሎች እየተመለከተ።

ወዲያው ግን ድንገት ግንዱ ከአባባ እጅ አመለጠ። ያመለጠው ግንዱ ላይ የደደረውን አፈር የግንዱ አካል መስሎት ሊጨብጠው ሲሞክር አፈሩ ስለተሸረፈ ነበር። አባባ የስቃይ ድምፅ አሰማ፤ በእርግጥም ግንዱ እግሩ ላይ ከፉኛ አርፎበት ነበር።

***

አባባ እግሩ ላይ ግንድ ወድቆበት በወጌሻ ታሽቶና በእናቴ ነጠላ ቁርጭምጭሚቱ ታስሮለት እንደተኛ አንድ ቀን ማለዳ ጠራኝ፤

"አብረሃም!"

"አቤት አባባ"

"ና!" አለኝ ቆጣ ብሎ፤ ለነገሩ አባባ ሲስቅ ራሱ ቆጣ ብሎ ነው። እውነቴን ነው፤ በማማሽ ፊቱ እየሳቀ፤ በማማሽ ፊቱ የሚቆጣ አባት ያለው ሰው በዚች ምድር ላይ እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም። ወደ መኝታ ቤቱ ሄድኩ፤ ያው እንደልማዱ ወጌሻው ያሰረለት ጥግን እግሩ ሳልቶበት "ነጠላውን ጠበቅ አድርገህ አሰርልኝ" ሊል ነው ብዬ ነበር ያሰብኩት፤ የጠበቀኝ ግን ሌላ ነገር ነበር፤ የፖሊስ ጥያቄ።

"እስቲ የእድራችንን ስም ንገረኝ፤ ድንገት ብሞት እንኳን የት ብለህ ሄደህ ነው ቅበሩልኝ የምትለው?" አለኝ።

"ኧረ አባባ በሰማም በል! የምን ሞት ነው!" አልኩት።

"ወዲያ የጠየቅሁን ብቻ መልስ! የእድራችን ሙሉ ስም ማነው?" አፈጠጠብኝ።

"እንዴ አባባ የእድራችን ስም እንዴት ይጠፋኛል ?" ብዬ ላመልጥ ሞከርኩ፤ አባባ ግን ወጥሮ ያዘኝ።

"ጥሩ ካወከውማ በል ንገረኛ!"

የእድራችን ስም በትክክል አላውቀውም፤ ግን "ትብብር" ይሁን "ኅብረት" የሚል ነገር እንዳለበት አስታወስኩ። ባወጣ ያውጣው ብዬ ሞከርኩ። "የተባበሩት ነዋ አባባ!" አልኩት።

"ጉድ!ጉድ! ጉድ!ጉድ!" አለ በጩኸት፤ እያንዳንዱን "ጉድ" በምብጨባ አጅቦት ነበር። እናቴ ጩኸቱን ሰምታ ተንደርድራ መጣችና "ምንድነው? ምን ኾናችኋል?" አለች፤ አንዴ አባባን አንድ ጊዜ እኔን እየተመለከተች።

"ይኼው ልጅሽ በቁሜ የተቃጠልኩት አንሶኝ ብትሞት ነዳጅ ማደያ አስቀብርሻለሁ አለኝ፤" አላት። እማማ ምኑም ሳይገባት ወረደችብኝ። "ምን ያለኸው ጨካኝ ነህ አንተዬ? እንዴት ተንከራቶ ባሳደገ ነዳጅ ማደያ...! በዚህ ዓይነት ለእኔም አትመለስ..." አለች።

"አንቺማ እንደውም ትቀይዋለሽ፣ እንክብክቦ ለጅብ ነው የሚሰጥሽ" አለ አባባ።

"በሰማ...ም!" አለች እናቴ። እየተቀባበሉ ወረዱብኝ። አባባ እናቴ ስላዘጋጀችለት ደስ አለው። እንዲ
ይሄ ሁሉ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ጩኸት አባባ ሲያዘኝ ከፈለገው ትእዛዝ በፊት ማሟሟ
ነበር። ወደ ጉዳዩ ሲገባ እንዲህ አለ፤

"በል አሁን ነገ ማለዳ የእድራችን ስብሰባ ስላለ እዚህ ቀበሌው ኋላ ያለው ሜዳ ሂድና እንደ
ተናግረህ የሚባለውን ሰምተህ ና! አንዲት ቃል እንዳታልፍህ፤ ነግሬያለሁ...!" አለና እስ
አባባን እንቢ ከማለት ተራራ መግፋት ይቀላል።

በበነጋታው ጧት ተነስቼ፣ ቅፍፍ እያለኝ ወደ እድሩ ስብሰባ አዘገምኩ። መንገድ ላይ ከውስጥ
ከላይ ካፖርት የደረቡ ሰዎች ወደ ስብሰባው እየሄዱ ነበር።. አልፎ አልፎ ውሻዎች እዚህም እዚ
ይታያሉ። ወደ አውቶቡስ ተራ የሚጣደፉ ሰዎችና መንገድ የሚያፀዱ ሴቶችም ነበሩ። ደግሞ
የሚቆጠቁጥ ነበር።

የስብሰባው ቦታ ስደርስ በርካታ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ቀድመው ደርሰው ወጋቸውን ይጠርቃ
ሰላም ማደራቸውን ይገማገማሉ። ማታ መንደሩን ሲያጠፉ ቀጥሯቸው ያደረ ጠላት የነበረ ይመስ
"መንደሩ እማን አደረ?" ይባባላሉ፤ መልሰው መላልሰው። አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ከአንዲ
ሴትዮ ጎን ተቀመጥኩ። ፊት ለፊት መዝገብ በየፊታቸው ያቀረቡ ሦስት ሰዎች ተቀምጠዋል፤
ሊቀመንበር፣ ፀሐፊ እና ገንዘብ ያዥ።

ስም ተጠራ!

"አስር አለቃ በላቸው!"

"አቤት!" አሉ ቶሎ የመሰለ ደምፅ ያላቸው ሰውዬ፤

"ሳጅን ገብሩ ደምሴ!"

"አቤት!"

"ወይዘሮ ጣይቱ ለገሰ!"

"የአባቱ ስም ለገሰ አይደለም፤ ገስሰ ነው። የምን ማምታታት ነው እሱ! " አለች አንዷት ነገረኛ መሳይ ባልቴት፤

"መቶ አሊቃ ዓለሙ!"

"አቤት!" አልኩ የአባቴ ስም ሲጠራ።

ሁሉም ሰው ወደኔ ዞረ። "መቶ አሊቃ ዓለሙ ከመቼ ወዲህ ልጅ ሆነ?" ብለው የተገረሙ ይመስሉ ነበር።

"ማነህ አንተ?" አሉ ሊቀመንበሩ፣ እኔን ለማየት አንገታቸውን አስግገው፤

"ልጁ ነኝ! ጋሼ አግሩን ወለም ብሎት መምጣት ስላልቻለ ልኮኝ ነው" አልኩ ቆፍጠን ብዬ፤

"ወንድሜን ምን አገኘው!?"፣ "ምን ሆነ?" ተራ በተራ ተንጫጩብኝ። አባቴ እንዲህ በእድሩ ተደናቂና ተወዳጅ ሰው በመሆኑ ኩራት ቢጤ እየተሰማኝ ስለ ወለምታው ማብራሪያ ሰጠሁ።

"እንዴ! ትልቅ ልጅ አድርሶ የለም እንዴ!? እሰቲ ና ሳመኝ፤" አሉ ፀሐፊው። ከዛማ ምኑ ቅጡ! እድርተኛውን ሁሉ እየዞርኩ መሳም ጀመርኩ። ጉንጬ እስኪግል። አዚች አገር ቢቃ ከእድር ጀምሮ እስከ_መሬ ከሳመህ ተከታዩም ይስምሃል፣ መሬ ከነከሰህም ... ለአባቴ የሚሄድ በርካታ መልእክትና 'እግዜር ይማርህም!' ተቀበልኩ። የአባቴ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር!!

ጶቶ

የዕለቱ የስብሰባ አጀንዳ በሊቀመንበሩ ሲነበብ ሳቁ ሊያመልጠኝ ነበር። እንግዲህ እድሩ የራሱ መዋዕለ-ሕፃናት አለው። በዚህ መዋዕለ-ሕፃናትውስጥ ለተማሪዎች መማሪያነት ሲውሉ የኖሩትን 'ያረጁና ያፈጁ!' ምሳሌዎች በአዲስና ዘመናዊ ምሳሌ ለመቀየር ነበር የዛሬው ስብሰባ የተጠራው። ከዚያ በፊት ግን ሪፖርት ይሰማ ነበር።

"በቅድሚያ አቶ ቀብድደው የእድሩን የስድስት ወር ሪፖርት ያሰማሉናል" ተባለ። እንደ ጉሬዛ ከግንባሩ ከፍ ብሎ ነጭ ፀጉር የጣለበት ቀጭን ሰውዬ በፊትም በኋላውም የተጻፈበት ወረቀት ከካፖርት የውስጥ ኪስ አውጥቶ ማንበብ ጀመረ።

"አመሰግናለሁ...! ክቡራን የኢድራችን ሊቀመንበር ሻለቃ ተስፋ አውግቸው፤... ክቡራን አባቶቻችሁን በመወከል የተገኛችሁ እንግዶች! ክቡራን እና ክቡራት! በቅድሚያ እንደምን አደራችሁ!"

"እግዚሃር ይመስገን!!" አሉ እድርተኞች በኅብረት።

"...እንደሚታወቀው ኢድራችን ሁሌም ግንባር ቀደምና ከዘመናዊ አሠራሮች ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑ እሙን ነው። ባለፉት ስድስት የሥራ ወራት እድራችን ሙታንን ከመቅበር የቆየ ኋላቀር ልማድ በመውጣት በእድራችን አባል የሆኑ ጎልማሶችና ሽማግሌዎችን በማታ በማስተማር የተማሩ ሟቾችን ማፍራት መቻላችን አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ማንም ከመሃይምነት ጋር እንዳይቀበር ባደረግነው ጥረት በእድራችን ከተቀበሩ አስከሬኖች መሀል ከአስረኛ ክፍል በታች የሆነ ሬሳ አልነበረም ማለት ይቻላል። ይህ አገሪቱ ለተያያዘችው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ሩጫ ትልቅ ግባት መሆኑን ባለፈው ወር ስብሰባችን ከወረዳ የመጡ ባለሥልጣናት አረጋግጠውልናል።

"...ክቡራንና ክቡራት!! እድራችን ሴት-ተቀን በመሥራት በመጪዎቹ አስር ዓመታት ውስጥ ኑዛዜያቸውን በእንግሊዘኛ የሚጽፉ ሟቾችን ለማፍራት እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህንንም ዓላማችንን ከመላኩ ቅዱስ ገብርኤል እርዳታ ጋር እንደምናሳካው ጥርጥር የለኝም" ሲል ጭብጨባው አስተጋባ።

"...እንግዲህ ከላይ በመግቢያው እንደተባለው በዚሁ ወደ ዛሬው አጀንዳ እናመራለን..." አሉ ሊቀመንበሩ፤ ቀጥል አድርገውም፡ "...በእድራችን ያሉ ሕፃናት በዳጀና ባፈጀ ምሳሌ መማር የለባቸውም በማለት ለዛሬ መወገድ አለበት ብለን ለጉባኤው ያቀረብነው አንድ ምሳሌ አለ። ይኸውም "አበበ በሶ በላ" የሚለው ሲሆን በምሳሌው ላይ ተወያይተንበት መቀየሩ ላይ ከተስማማችሁም ተተኪውን ምሳሌ መርጠን እንለያያለን ማለት ነው" አሉ ሊቀመንበሩ።

ወዲያው ቁጥር ስፍር የሌላቸው እጆች እንደ ጭራሮ ተንጨፈረሩ። "...እዚህ ጋ! ....እዚህ...! ጋ! ሐሳብ አለኝ...!" ይሄ ህዝብ ሦስት ሺ ዓመት ታፍኖ ዛሬ ገና ልጓሙ የተፈታለት ይመስል ለመናገር እርስ በእርስ ተራኮተ።

እድርተኛው እጁን እንዳንጨፈረረ የእድሩ ሊቀመንበር እስከርቢቶ በጨበጠ ቀኝ እጁ፤ የወጡትን እጆች እንደሚቆጥር ሰው አንድ ሦስት እጆች ላይ ኪቀጣ በኋላ "እሽ አቶ ተፈራ!" አለ።

"እድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ" አሉ በችኮላ እድሉን መልሰው እንዳይነጥቋቸው የሰጉ ይመስል።

ጓንግዴሀ የእኔ ሐሳብ ምንድን ነው... ይሄ 'አበበ በሶ በላ' የሚል ዓረፍተ-ነገር በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ያለው ታሪካዊ ዋጋ ከሳሊበላ፣ ከአክሱም፣ ከአባይና ሰፍ፡መር አይተናነስም። ...ይሄ ዓረፍተ ነገር ይቀየር ማለት ታሪክ መናድ ብቻም ሳይኾን ቅርስ ማጥፋት ነው።...ስንቱን አፍርሰን እንችለዋለን ጎበዝ? ወገኖቼ! ኧረ ምስላችን ቢጠፋ እንኳን ምሳሌያችን ይቆይ።" ሲል እንባ ቀረሽ በሆነ ልመና አድርተኛውን ለመነ።

"እሺ አቶ ዘውገ! " አለ ሲቀመንበሩ። የመጀመሪያው ተናጋሪ ንግግር ደስ እንዳላለው በሚጠቁም መመናጨቅ። አንድ ግንባሩ እንደ ከበሮ የተወጠረ ሰውዬ እፉን እየጠረገ ተነሳ። ክንዱ ላይ ዣንጥላና ከዘራ አንጠልጥሏል። ቢያስቀምጠው ምናለ? አንዳንዱ ሰው ተቀምጦም ምርኩዙን አያስቀምጥም፣ ባይዘንብም ዣንጥላውን ከእጁ አይለይም። ትላንት ያጋጠመው ውድቀትና ያበሰበሰው ዝናብ ዛሬም ሕይወቱን ተሸክሞ እንዲኖር ብርታት የኾነው ይመስል።

"መልካም እኔ እንደሚታወቀው ንግግሬ አጭር ነው።. አባቶቼ! እናቶቼ! ወንድሞቼና እህቶቼ! እንዲሁም ልጆቼ('ልጆቼ' ካሉ በኋላ ወደ እኔ ተመለከቱ)።...በበኩሌ ሦስት መንግሥት አይቻለሁ። መንግሥታት ቀድሞ የነበረውን መንግሥት ሐውልትና ምሳሌ ማፍረስ ቀድሞ የነበረውን ድህነት ማፍረስ ይመስላቸዋል።...አንዱ መንግሥት የአንዱን መንግሥት ቃል ሲቀይር፣ አንዱ የአንዱን ተረት በሌላ ተረት ሲተካ፣ ምሳሌ አፍርሶ ምሳሌ ሲገነባ፣ የዓይን ምስክር ነበርኩ! ዋናው ጥያቄ ቃልን መቀየርና መቀባባት፣ አገርን ይቀይራል ወይ? ትውልድን ያንፃል ወይ ነው! ...እንደኔ እንደኔ ጃንሆይ ያሉትን ደርግ ለወጥ አድርጎ ብሎታል፤ ደርግ ያለውን አሁን ያለው መንግሥት አሽሞንሙኖ ደግሞታል።

"...ኃይለሥላሴ ‹ከእግዜር ተቀባሁ› አሉን፤ እግዜርን ለምስክርነት አንጠራ ነገር ቸግሮን 'ይሁና!' ብለን ተገዛን። እግዜር ግን በሳቸው ሥልጣን እጁ የለበትም ነበርና ከሰው የሆነ ዙፋናቸው በሰው ተንኮታኮተ። ደርግ 'ጭቁኑ ቀብቶኛል!' አለን። ያው እግዜር ከድሆችና ከጭቁኖች ወገን ይቆማልና 'ለታሰሩ መፈታትን ይገኙ መጣሁ' ያለ ደርግ ከግዜር ተላኩ ማለቱ እንደሆነ ቅኔው ገብቶናል። እናም ለጭቁኑ የመጣው ጭቁኑን ፈጀው....።"

ዞር ዞር ብሎ ተመለከተና ድምፁን ቀነስ አድርጎ፣ "...አሁን ያለው መንግሥት ጭቁን ጨቋኝ ሳይል ሕዝብ የሚባል አምላክ ቀብቶኛል ይለናል። እኛ ሕዝቦች እንዳልቀባነው ግን እሙን ነው። ለምስክሩ ስራሱ ስለመቀባቱ መስክርሂል ማለቱ ነው፤ የቀባውን እግዜር ይወቅሰት!...ስለዚህ ቃል ጨዋታ

ነው። ምሳሌም ዘመን የማያንሳው ፈዝ ቃል ማገላበጡን ትተን ከኃላፊ እስከምንዝር በአንድ በኩል የተጣድነትን ሥርዓት በሰላማዊ መንገድ ቀያይረን ብናየው ይሻላል።" አለና ተቀመጠ።

"አሁን የተባለው ነገር ትንሽ የተምታታና እርስ በእርስ የሚጣረስ ነው። እንዴት ነው መንግሥት ሕዝብ አልቀባውም ማለት? ሕዝቡ 'ሆ!' ብሎ ወጥቶ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ በርስንት በካርዱ በድምጹ የመረጠውን መንግሥት ዝቅ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ለልማት ተሰብስበን አድራችንን የጠረ ልማት አጀንዳ ማራመጃ ማድረግ የለብንም።" አለ የቀበሌውን ባሕር ዛፍ ሁሉ ሽጦ ወደ ኪሱ አስገብቷል እየተባለ የሚታማው የቀበሌያችን ሊቀመንበር፤ አቶ በድሉ።

"አቶ በድሉ! ይሄ የሥራ ቦታህ አይደለም፤ እድር ነው። ለስብከትህ ቦታ ቦታ አብጅለት" አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ።

"ሁሉም ቦታ ቦታዬ ነው!" አለ ሊቀመንበሩ።

"እሱማ ልክ ነው፤ ሁሉም ቦታ ቦታህ ነው። ሲያሻህ በሊዝ፣ ሲያሻህ በዘመድ አዝማድ ይዘኸዋል" ብሎ በአሽሙር ወጋው።

ሊቀመንበሩ ንትርኩን አስቁሞ "እስቲ የሚበጅ ሐሳብ አንሱ፤...'እሽ እዛ ጋር ዙሪያሽ!' አለ ዙሪያሽ ታዋቂ አረቄ ነጋዴ ናት።

"አበበ ሁሌ በሶ ከማሻመድ አንዳንዴ እንደ ወንዶቹ አረቄ ፉት ቢል ምናለበት?" ስትል እድርተኛው በሳቅ አውካኩ። ሳቁ የቀልዱን ማሳቅ ሳይሆን የእድርተኛውን የአረቄ ደንበኛነት የሚያሳ ዘር፡ አንዳንድ ሰዎች መቼም ትልቅ ጉዳይ ላይ ቀልድ ካላቦታው ጥላው ነገር የማቃለል ክፉ አባ አለባቸው። ራሳቸው ስለሚነግዱት አረቄ በማውራት አንድም ገበያ መሳብ፣ ሁለትም ሕዝባችን ከሁ ዘሎ አረቄ ላይ ደርሷል አልፎሊታል ለማስባል የመፍጨርጨር ተጨማሪ አባዜ!

"እኔ ያልገባኝ ለምንድነው ዐረፍተ ነገሩ የሚቀየረው? ማንኛውም ዜጋ በፈለገው ጊዜና ሰዓት ያሻውን አቅሙ የፈቀደውን ምግብ የመብላት መብት አለው። ብሔራዊ የምግብ ሰዓት የሚባል የለም፡ አበበ ንጭ ቡራቡሬ የሆነ ሰውዬ።

ቲቸር ጉግሳ (አማረኛ አስተማሪ ናቸው) ገና በጧቱ ሁለት ጣሳ ኮረፌ ደብስቀው ጅብርር ብለዋል

እድሉ ሳይሰጣቸው ብድግ ብለው አንድ ጊዜ ናዳ የሚመስል ረዥም ሣሳት ካገሉ በኋላ፤ "የዚህ ዓረፍተ ነገር ባለቤትማ አበበ ነው፤ ግሱ ወይም ማሰሪያው 'በላ'" ብለው ሰዉን ግራ አጋቡት።

የጂወርቅ የምትባለው የወረዳው ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ የጽዳት ሠራተኛ፤ "የበሰው ባለቤት እንዴት አበበ ብቻውን ሊሆን ይችላል? በአዲሱ የቤተሰብ ሕግ አበበ ባለትዳር እስከሆነ ድረስ በሶው የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው" ስትል በእልህ ተናገረች፤ ከባሏ ጋር በቅርቡ የተፋታችው ይህች ሴት ንብረት ሳትካፈል በመውጣቷ ፍርድ ቤት በክርክር ላይ ናት።

አንድ በኦረታ የወጡ የታሪክ አስተማሪ እጃቸውን ሲያወጡ አድርተኛው ፀጥ አለ። የተከበሩ ሰው ናቸው። ንግግራቸው መሬት ጠብ የማይል ይባልላቸዋል።

"አመሰግናለሁ! ...ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ በአገራችን በሶን ለምግብነት ማዋል የተጀመረው በንጉሥ ኢዛና ጊዜ ነው። አበበ እስካሁን በነገሡበት የበሶ ዙፋን ላይ መቼ እንደተቆናጠጠ ማስረጃ ባይኖርም ከዘመናዊ ትምህርት ጅማሬ ጋር ተያይዞ ሊሆን እንደሚችል ግን አንዳንድ መላ ምቶች ይሰነዝራሉ" ብለው በእጃቸው የያዙትን መጽሐፍ ለአድርተኛው ከፍ አድርገው እያሳዩ ቀጠሉ።

"በዚህ ዶክተር አያልሰው ባንጃው ተፈራ ወልደሚካኤል በጣፉት '*የኢትዮጵያ ደረቅ ምግቦችና የሆድ ድርቀት*' በሚል መጽሐፍ ላይ ደረቅ የበሶ ጭብጦ ለሆድ ድርቀት የማጋለጥ እድሉ ከፍተኛ እንደኾነ ተጠቅሷል። በኢትዮጵያ በሶ ከሚበሉ ዘጠኝ ሰዎች አራቱ በሆድ ድርቀት፣ ሁለቱ በትንታ እንደሚሞቱ መጽሐፉ ያትታል።...እንግዲህ አበበ ያልነው በሶ በሊታ ሰው ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች በአንዱ እንደሞተ ከፍ ያለ ጥርጣሬ አለ። የአበበን ሞትና ምሳሌውን ምን አገናኘው ትሉ ይሆናል...።"

አንድ ቄስ የታሪክ መምህሩን አቋረጧቸው። "እዚህ ጋ አካሄድ...አካሄድ...አካሄድ!" አሉ ሊቀመንበሩ። እድሉን ሰጧቸው።

"እግዚያብሄር ይስጥልኝ!...መቼስ አሁን የተደረገው ንግግር መልካም መሆኑ ግልጥ ነው፤ ግን የበሶን አጀማመር ሲናገሩ ትንሽ ስህተት ያለ ይመስለኛል። በሶ ለምግብነት የተጀመረው በኢዛና ዘመን ሳይኾን በንግሥት ሳባ ዘመነ መንግሥት ነው።...አዎ እናታችን ሳባ የሰለሞንን ጥበብ ልታይ ስትሄድ፤ ለጥበብ ባላት ትልቅ ፍቅር ምህኛት ስንቅ እንኳን እስኪዘጋጅ መታገስ አልሆንልሽ ቢላት፣ ተንገርግቦ የተፈጨውን የገብስ ዱቄት ብቻውን አስይዛ መንገድ ገባች። እንግዲህ መንገድ ላይ ርሃቡ ሲጠናባቸው አጃቢዎቿ ያንን የገብስ ዱቄት በቀይ ባሕር ውሃ እየበጠበጡ በትልልቅ እንኮላ ይለጉት ጀመረ...።"

"...ጉዞው ቀጥሎ ጭልጥ ያለው የእስራኤል በረሃማ አካባቢ ሲደርሱ፣ በሶ የሚበጠብጡበት በማጣታቸው እንደነገሩ ዱቄቱ ላይ ጠብ አያረጉ ዱቄቱን ጨበጥ ጨበጥ አድርገው ቢቀምሱት ግሩም ሁኖ አገኙት። ንግሥት ሳባም በሰውን በልታ አገሳት፤ ንግሥት ናትና መቸስ እንደ… ዝም ብላ አታገሳም፤ አፏን ጋረድ አደርጋ በከፍተኛ "ብስስስስ!!" አለች።...እኛ ቢዎቹም ይህን… ምግቡን 'በሶ' አሉት!

*...እናታችን ሳባ ታዲያ ጠቢቡ ሰለሞን ጋር ከደረሰች በኋላ ጮማው ቢቀረብ፣ ጠጁ ቢንቆረቆር እንደበሰው አልጥማት አለ። አንድ ቀን ማታ ታዲያ ይቼንኑ በሶ በልታ የውኃ ጥሙ ሲጠናባት ውኃ ፍሊጋ ወደ ንጉሡ መኝታ ቤት ጎራ አለች። ምንም እንኳን ንግሥቷ ውኃ ፍሊጋ ወደ ንጉሡ… ቤት የገባችው ማታ ቢሆንም ፤ የተመለሰችው ግን ሲነጋጋ ሲል ነበር። የንግሥቷ አገልጋይ የ… ሴት "ንግሥት ሆይ! ወዴት ጠፉብኝ" ብትላት በፈገግታ፤ "የነፍሰ ውኃ ፍሊጋ መንግስተ ሰማያት… ተመለስኩ" ማለቷን ታሪክ ይነግረናል" አሉ መምሬ ሰሎሞን፣መኝታ ቤት የቸነውን እያሰቡ… ብለው።

ኢድርተኛው ግማሹ በመምሬ ወገን ግማሹ በታሪክ አስተማሪው ጎን ተሰልፎ ሌላ ንትርክ ጀመረ፡

"የመምሬ ታሪክ አሳማኝ ነው!"

"የለም በኢዛና ዘመን የሚለው ነው ልክ..."

"ኢዛና ማነው?"

"ማንም ይሁን ማን ታሪክ አስተማሪው ስሙን ከጠሩት ታሪካዊ ሰው መኾን አለበት"

"እንደ ታሪክ አስተማሪው መጠሃፍ ከሆነ ኢዛናም ሆነ ሳባ የሞቱት ወይ በሆድ ድርቀት… በትንታ ነው ማለት ነዋ። ነገሥታቶቻችን ሁሉ 'ለአገር አልሞቱም፤ ለሆዳቸው እንጂ' ልትሉ… አሉ አንድ ሽማግሌ ያሉ በውዬ እየተበሳጩ።

እስከ ምሳ ሰዓት የንጉሰ ኢዛናና የንግሥተ ሳባ የበሶ ፈጠራ ባለቤትነት ክርክር ቀጥሎ ዋለ።

የእድሩ ሲቀመነበር አንዱ አጨብጭቦ የእድርተኛውን ጫጫታ ፀጥ ካሰባለ በኋላ "...መልካም… ሐሳቦች ተነስተዋል፤ እድራችን ውስጥ ያለው ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ሲታይ ይ…

ኤሮፓ ወይም አሜሪካ ያለ እንኳ አገራችን ላይ ያለ አድር አይመስለም፡፡ እውነቱን ነው! የዚህ አድር ለቃመንበር በመሆኑ የሚሰማኝ ደስታ ወደር የለውም..." ብሎ ተናገረ፡፡ ቀጠል አድርጎም "እ...ይሄን 'አበበ በሶ በላ' የሚል ዓረፍተ ነገር እንቀይረው ወይስ እንዳለ እንተወው በሚለው ሐሳብ መግባባት ላይ ካልደረስን ያው ጉዳዩን በእጅ ብልጫ ብንወስነው መልካም ይመስለኛል፤ ካልሆነ እዚሁ መዋላችን ነው" ሲል ጨመረበት፡፡

"አይሆንም...እሁ እሁ እሁ..." አሉ ከንግግራቸው ሳል የሚያደናቅፋቸው ሽማግሌ፡፡ "...አይሆንም! አይሆንም! አናረንም ቢሆን በሐሳብ ብልጫ እንለያይ፡፡ እጅ እና ሐሳብ እዚች አገር ላይ ከተለያየ ሰነበቱ እኮ ክቡር ሊቀመንበር፤ ምን ነካወት?!"

"ልክ ነው! 'አበበ በሶ በላ' ከተራ ዓረፍተ-ነገር ወደ ቁም ነገር ተቀይሮ ክርክሩ ሲሟሟቅ የምን እጅ ብልጫ ነው ? 'ይሄን ያህል ዘመን አበበ ብቻውን በሶ ማሻመዱ ይብቃው፤ ፍትሐዊ የበሶ ክፍፍል ይኑር፤' ብሎ እጁን ያወጣ እዚህ አድር ውስጥ ማን አለ? ሲጀመር በሶ የገደለውን ሚስኪን ሁሉ እየተቀበለ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሲቀብር የኖረ አድር ለቁራጭ ዓረፍተ ነገር እጁን ሲያንከረፍፍ አያፍርም ? ወይስ እጅ የተሠራው እውጡ ሲባል ለማውጣት ብቻ ነው?" ሲል የጠየቀው ከሰል ነጋዴው ተፈራ ነበር፡፡ ከሰሉን ፊቱ ላይ ደርድሮ ይሸጥ ይመስል የፊቱ ቆዳ ጥቁርቁር ያለ ነው፡፡

"ይሄ ደግሞ የማን ነው ባካችሁ?! እንደሚሸጠው ከሰል ትንሽ ሲያርገበግቡት ይንቦጣል!" አለች ድምጧ ጣጣጣ የሚል ዓይነት ሴትዮ፡፡

እድርተኛው ሌላ ብሶት ያለበት ይመስላል፤ አንድ ተናጋሪ በተናገረ ቁጥር ሁሉም ራሳቸውን ያወዛውዛሉ፤ በሁሉም ንግግሮች ከተስማሙ በምንም አይስማሙም ማለት ነው፡፡ እና ታዲያ ሰሜንና ደቡብ በሆኑ ጉዳዮች አንድ ሰው እንዴት ለሁለቱም በመስማማት ራሱን ይነቀንቃል? ዓረፍተ ነገሩ ይሰረዝ ሲባል ራስን መነቅነቅ ! አይሰረዝ ሲባልም መነቅነቅ !

"ወገኖቼ ! እንዳንዴ አንድ ነገር ብቻውን አይቆምም፡፡ ብቻውንም አይፈርስም፡፡ ጅራት ይኖረዋል...፡፡" አለ ሌላው ተረኛ ተናጋሪ፤ በዚህ ጠዋት ሰፊ የሰሌን ባርኔጣ አናቱ ላይ ደፍቷል፡፡

"የምን ጅራት?" አሉ ሊቀመንበሩ፤ አለቀ ያሉት ጉዳይ ጅራት ሲቀጥል አበሳጭቷቸው፡፡ ሊቀመንበሩ የሆነ ቀጠሮ ሳይኖራቸው አይቀርም፤ ቸኩለዋል፡፡ አስር ጊዜ እጃቸውን ዘቅዝቀው የብረት ማሰሪያው የሚያብረቀርቅ ሰዓታቸውን ወደታች ወደ እጃቸው አንጓ ያወርዱና ክንዳቸውን አጥፈው ሰዓቱን

ዓይኖቻው ሶር ይደቅንታል። ለረዥም ጊዜ ሰዓቱ ላይ ሲያፈጡ አይበሉባቸው ላይ ያለውን ፀጉር የሚቆጥሩ እንጂ ሰዓት የሚመለከቱ ብቻ አይመስሉም።

"ለምን ማለት ጥሩ ነው፤ ክቡር ሊቀመንበር! ...እንግዲህ 'አበበ በሶ በላ' ስንል በሰውን ማን አዘጋጀው የሚል ጅራት ይከተላል። መቼስ ይሄን ሁሉ ዘመን የተበላ በሶ ጣዕሙ ልዩ መሆን አለበት። እንጂ ባለሙያ ሴት እንዳለች እንጠረጥራለን። አበበ በሶውን የት ነው የበላው? ቤቱ ከሆነ በሶውን ለማበጥበጫ ውሃ ከየት አገኘ? መቼስ በዛ ዘመን የቧንቧ ውሃ አይኖርም።...ለነገሩ ዛሬም ቢሆን ቧንቧ እንጂ የቧንቧ ውሃ እስከዚህም ነው።"

"እውነት ነው፤ ውሃ ተቸገርን እኮ!" አለች አንዷ ሴትዬ ከሰውዬው ተቀብላ።

"አንድ ጀሪካን ሁለት ብር እየገዛን" ተቀበለቻት ሌላኛዋ።

"የሞላልሽ ! እኛ ከነጭራሹ ላይናችንም አጥተናል" ተንጫጫ አድርተኛው። ዋናው መሰብሰብ ነው አጀንዳ እንደሆነ አንድም ሁለቱም ሆነው ከተሰበሰበ በመሃል ይከሰታል ።

"ሥነ ሥርዓት፤ ሥነ ሥርዓት!" አሉ ሊቀመንበሩ። ጫጫታው ጋብ ሲል ተናጋሪው ንግግሩን ከቆመበት ቀጠለ። "...እና ለበሰው ማበስበሻ ውሃ ከወንዝ መቀዳት አለበት። አያችሁ! ጫልቱ ብቅ የምትለው እዚህ ላይ ነው። 'ጫልቱ ውሃ ቀዳች' እንዲል ምሳሌው። ይሄን ሁሉ ዘመን ለዚህ ሆዳም አበበ ውሃ ማበስበሻ ውሃ ስታመላልስ የኖረች፤ ወገቧ በእንስራ ሸክም እየተላጠ የኖረች ሚስኪን ጫልቱ!" ሴቶቹ ከንፈራቸውን በሐዘን መጠጡ።

"ተከብሮ የኖረ አበበን ሆዳም ብሎ መዘለፍን ምን አመጣው?" አለ የቀበሌያችን ሊቀመንበር በብሽቀት ብሎ።

"አንድ ዓይነት ሆድ ያላቸው ወፎች በአንድ ላይ ይበራሉ፤ አንተ ከሆዳም ጎን ቆመህ ትከራከር የለ ማነህ?" አለው ሌላው።

"በቃ!" አሉ የአድራሻን ሊቀመንበር በቁጣ። ከዛም "ቀጥል!" ሲሉ የመጀመሪያውን ተናጋሪ አዘዙት።

"አያችሁ! ጫልቱ እናት አገራችን ኢትዮጵያ ናት! ውሃ እንዳሻው ሲጋልብባት ኖረ። ለም አፈሯ እንዲሁ እየበሰበሰ ተጋዘ። ውሃዋንና አፈሯን ተጠቅመው በሶቻቸውን የሚያሽሞነሙኑት ሌሎች ነበሩ። 'አባባ

በሶ በሉ፤ ጠግበው እደሩ፣' ሲባል የአገራችን ምሳሌ ግን ሜልቱ ውሃ በመቅዳትና በማመላለስ ርሃብ ጠበሳት፤ የነጠፈ ጡቷን እያጠባች ተንጋላ ቀረች፣ የተሸከመችው ውሃ ጠማት..."

"ኣይ ይሄ የአድርተኛውን ሐሳብ ከውስጥ ችግራችን በመቀለበስ ወደ ውጭ እንድናይ ሆን ብሎ የተነገረ ሴራ ነው። በሷችን የተበላው በእኛው በራሳችን ምሳሌ፡ በራሳችን መጣፍና ደብተር እንጂ ወንዛችን ወደ ውጭ ምናምን ስለፈሰሰ አይደለም። አበበ ግብፃዊ አይደለም ገበዝ፤" አሉ አንድ የስፖርተኛ አቋም ያላቸው፣ ሽበት የወረሰው ፀጉራቸው ብን ብሎ የተበጠበጠ ሽማግሌ። በዚህ ማለዳ ፀጉራቸው እንዲህ መበጠሩን ስመለከት ሌሊቱን ሲያበጥሩ ያደሩ መሰለኝ።

"አካሄድ !!" አለ የቀበሌው ሊቀመንበር፤

"ምንድነው" አለ የእድሩ ሊቀመንበር። ሊቀመንበርና ሊቀመንበር "ሊቀመንበር" በሚለው ቃል የአባታቸው ስም ይመስል እንደ ወንድማማች ነበር የሚግባቡት።

"አጀንዳችን ማኅበራዊ ችግራችንን መፍታት ነው። ቦለቲካ መወራቱ ተገቢ አይደለም" አለ የቀበሌው ሊቀመንበር።

"ልክ ነው ቦለቲካ አታውሩ" አለ የእድሩ ሊቀመንበር። እነጋገሩ ሁሉ ዝርው ነው አታውሩ፤ አታድርጉ እንዲህ አትበሉ ...

ሌላ ሰውዬ እጃቸውን አወጡና ልክ የሞተር ሳይክል በሚመስል ድምፅ መናገር ጀመሩ።

"ወገኖቼ! እኔ እኮ የሚገርመኝ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር ነብሳቸውን በአጠደ ገነት ያኑርልኝና (ወደ ቀበሌው ሊቀመንበር ገልመጥ አሉ፤ የአጠደ ገነት ቁልፍ በሊቀመንበሩ እጅ ያለ ይመስል) በቀን ሦስቴ ትበላላችሁ ብለውን ነበር። እሳቸውን የሚያህሉ በአንድ እጅ የማይነሱ ሰው እንኳ በቀን ሦስቴ እንበላለን ነበር ያሉት። ይሄ አበበ ግን ሙሉ ቀን ያሳምጻል። እንደውም እሳቸው ያልጀመሩትን ነገር በማን አለብኝነት የሚሠራ ብቸኛ ሰው ሳይሆን አይቀርም፤ ስለዚህ ዓረፍተ ነገሩ ይቀየር።"

አንዱ በሽማግሌው አስተያየት የተበሳጨ ሰው እጁን አወጣ። ሁሌም ንግግሩ መንግሥትን መቃወም ነው አሉ። ገና ሳይናገር የቀበሌው ሊቀመንበር፣ "አካሄድ!" ብሎ ጮኸ።

የእድሩ ሊቀመንበር፣ "እንደ፡ዴ፡ዴ፡ዴ፡ዴ ገና ሳይናገር የምን አካሄድ ነው?" ብሎ ተቆጣው።

"ዓይነውሃው በሰቲካ ይመስላል" የቀበሌው ሊቀመንበር መለሰ።

ተናጋሪው እንዳልሰማ ኾኖ ቀጠለ፣ "እመሰግናለሁ የተከበረው እድር አባላት ! ይኼ ሰውዬ ግን አካሄድ እያለ መሄጃ አሳጣን እኮ!" አለና ሊቀመንበሩን በነገር ወጋ አድርጎ ቀጠለ፡ "...የዚች አገር ነገር ይደንቀኛል፤ 'አበበ በሶ በላ' የሚለው ዓረፍተ ነገር ጎጂ ነው የምትሉት ምኑ ጎድቷችሁ ነው፣ እዚህ አፍንጫችሁ ሥር በአደባባይ ትሁት ዐረፍተ ነገር እየተናገሩ በየጓዳው ጉቦ የሚበሉትን ለምን አትቀይሩም? እንደው ዛሬን እየሸሸችሁ ታሪክ ላይ የምትበረቱት ለምንድን ነው? ይሄ ነገር በአገራችን ዲሞክራሲ እንደሌለ የሚያሳይ ነው።"

"ይሄው እንደፈራሁት፤ አካሄድ! በሕግ አምላክ አካሄድ!" አለ የቀበሌው ሊቀመንበር ከትከሻው የተንሸራተተ ጋቢውን እያጣፋ።

"እድሉን አልሰጠሁህም አንተ ሰው! ራስህ በሕግ አምላክ ዝም በልልን" አለው የእድሩ ሊቀመንበር ደሙ ፈልቶ።

ጋሽ ጫላ የሚባለው ሰውዬ እጁን አወጣ። የኔ ቢጤ ነው። ለምኖ ግን የእድር ክፍያውን በአግባቡ እየከፈለ የእድር አባል ሆኗል። አንድ እግርና አንድ ዓይን የለውም። ለብዙ ዓመታት በውትድርና አገልግሏል።

"...ወገኖቼ እኔ ለብዙዙዙዙዙዙ ዓመታት እነ አበበ በሶ ሲበሉ ጩቤ ጩቤፎ ድንበር ስጠብቅ ነበር። ምንም እንኳን ርጋፊ በሶ ባይደርሰኝም። ዋናው ነገር ዓረፍተ ነገሩ አይመስለኝም፤ በሶውን ለሕዝቡ ካከፋፈላችሁት ሕዝቡ ራሱ ዓረፍተ ነገሩን ይቀይረዋል። በሶውን ማንም ይብላው ማ፣ ሕዝቡ እያዛጋ የበይ ተመልካች እስከሆነ ድረስ፣ ሕፃናቱ በቂ ምግብ እስካላገኙ ድረስ፣ ዓረፍተ ነገ ብቻውን ትውልድ አይቀርጽም...!" አለና ሊቀጥል ነው ሲባል ጨርሶ ተቀመጠ።

ንትርኩ ቀጥሎ ወደ ሰባት ሰዓት አካባቢ ሲጠናቀቅ ሊቀመንበሩ እንዲህ አሉ፤

"ያው እንግዲህ ብዙኃኑ በተስማማው መሠረት ዓረፍተ ነገር ብቻውን ቢቀየር ዋጋ የለውም የሚል ወገን አለ..."

"ወገን አይደለም ቡድን ነው" አለ የቀበሌው ሊቀመንበር፤

"አንተ ሰው አናግረኝ እባክህ !...ልጆቻችንን ለማታዋ፣ ታታሪና ዘመናዊ ዜጋ አድርጎ ለማሳደግ ዓረፍተ ነገሩ ይቀየር የሚል ቡድን ደግሞ አለ..."

"ይሄማ ቡድን አይደለም፣ ወገን ነው" አለ የቀበሌው ሊቀመንበር። ሁሉም ሰው ሳቀ። ምን እንዳሳቃቸው አልገባኝም።

"እንግዲህ ይኼ ውይይታችን ለሌላ ጊዜ በይደር ይያዝና አብላልተነው የዛሬ ሳምንት እንነጋገርበት" አሉ ሊቀመንበሩ። አድርተኛው አፎይይ አለ! እኔም በሆዴ አሰይ አልኩ። እስከዛ አባባ እግሩን ይሻለዋል መቼስ።

ከስብሰባ መልስ እግረ መንገዴን ጓደኛዬ ቤት ሄጄ ቆየሁና በእዳኛ ሥጋ ቤት በኩል ሳልፍ የእድራችን ሊቀመንበርና የቀበሌዮችን ሊቀመንበር ጥሬ ሥጋ ፊታቸው ተቀልሎ በአዋዜ እያጠቀሱ ይሰለቅጡታል። በየፊታቸው ጃምቦ ተገትሯል። እሰፍ እንዳልኩ የእድሩ ለፋፊ አስማማው እንዲት በቀይ ፕላስቲክ የተጋረደች ሻይ ቤት ውስጥ፣ የተወላገደች ኩርሲ ላይ ተቀምጦ ምሳውን ሻይ በዳቦ ይበላል። ይቺን እየበላ ነው ጧት ጧት እንደዛ አገር በሚያናውጥ ድምፅ የሚጮኸው!? ለካ እዚች አገር ላይ የሚበላው አይጮህም!! ከልጅነት እስከ ዕውቀት "አበበ በሶ በላ" እያለ እንደ ቁራ የሚጮኸው በሰው የተበላበት ሚስኪን ነበር !!

ቤት ሲደርስ እናቴ በር ላይ አገኘችኝና፣"እህ እንዴት ነበር ስብሰባው?" አለችኝ፤ እጠያየቋ "አንተን ብሎ ተሰብሳቢ" የሚል የማሾፍ ቅላፄ ነበረው (የእናቴን ዓመል መች አጣኋት)

"የእድሩ ሰው በሙሉ ቆቡን ቀዶ እየሠፋ ነው" አልኳት በተሰላቸ አነጋገር።

# የከቴን ያላየ ኬቲን ያመሰግናል

እና ፍራንክ የተባለች ሙጥቅላ የአይሁድ ታዳጊ በዘመነ ናዚ ኮርኒስ ውስጥ ተደብቃ ፃፈችው የተባ የግል ማስታወሻ (የማስታወሻዋ ስም 'ኬቲ' ነው) በመጽሐፍ ተጠርዞ አነበብኩና "ዓለም የተንጫጫ ለዚህ ነው እንዴ ... የአያቴን ማስታወሻ ቢያዩ ምን ሊሉ ነው ?" ብዬ ተገረምኩ።

የአያቴ ማስታወሻ ደብተር የተገኘው በአንድ አድሜ ጠገብ ጎተራ ውስጥ ነው (ጎተራ ለማታውቁ አንዳንድ የከተማ ልጆች - ጎተራ ማለት የገጠር ፍሪጅ ማለት ነው !! ውስጡ እህል ይቀመጥበታል ከሳጠራ ተሰርቶ ዙሪያውን በጭቃ ወይም በእበት ስለሚለሰን ውስጡ የሚቀመጠው እህል በሙቀት ሳይበላሽ ለረዥም ጊዜ ይቆያል። አንዳንዴ መሬት ተቆፍሮ ጉድጓዱ እንደጎተራ ሊያገለግል ይችላል። እንግዲህ ጎተራው መጠኑ እንደ ባለቤቱ ኃብትና ፍላጎት ይወሰናል።)

እና አያቴ በድሮ ጊዜ ከአንድ አምባገነን የመንደር አስተዳዳሪ ጋር የከረረ ፀብ ውስጥ በመግባቱ እዚህ ጎተራ ውስጥ አርባ ቀንና አንድ ሌሊት አሳልፏል። ሌሊት ሌሊት ከጎተራው ወጥቶ ጫካ ይገባ ሳይነጋ ወደ ጎተራው ይመለሳል። ታዲያ በዘመኑ የነበረውን የየቀንና የየሌሊት ውሎውን ከብራና በተዘጋጀች ግሩም ማስታወሻ ደብተሩ ላይ ከቅጠላ ቅጠልና ከከሰል በተቀመመ ቀለም ያሰፍር ነበር የማስታወሻዋን ስም "የከቴ" ብሎ ነበር የሚጠራት !

እንግዲህ ከዚህ ማስታወሻ ብራናው ላይ ያገኘሁትን አንድ ከመቶየት ብዛት ተረት የሆነ አውነ እነግራችኋለሁ..

***

(ማክሰኞ ከቀኑ ፱፡00 ሰዓት)

ወዳጄ የኩቴ...

ዛሬ ጉድ ሆኜልሽ ነበር። ይሄ የንተራው ቅንቅን ሃሣምንቴ ሰውነቴን ሲያሳክከኝ ጊዜ፣ ቀስ ብዬ ከጉተራዬ መጣሁና በጠራራ ፀሐይ ወደ ወንዝ በረርኩ። ማንም ሰው የሌለበት ጅረት መርጬ ልብሴን ሳንቀረቅፍ አንድ የተራብ ጅብ ከአኔ ከፍ ብሎ መቆሙን አየሁ ... ይሄውልሽ የኩቱ በጠራራ ፀሐይ ሰው ነፃነት አጥቶ በየንተራው ሲታጀል መንደሩን ጅብ ይፈነጭበታል !! ድንገት ከወደላይ አንዲት አህያ ሰበር ሰካ እያለች መጣች። ፍርጥም ያለች አንኳን ለጅብ ለሰው የምታስጎመጅ አህያ !! አውቃታለሁ የአቶ አሰፋው አህያ ናት...

ድንገት የሆነ ገርገጭ የሚል ነገር ሰምቼ ብዞር በአካባቢው ምንም ነገር የለም ... ለካስ ጅቡ ምራቁን ሲውጥ የጉሮሮው ድምፅ ነው !! አህያዋ ከወፍጮ ቤት እንደመጣች ታስታውቃለች፣ አካላቷ ሁሉ ዱቄት ለብሷል ... ከእኔ ትንሽ ዝቅ ብላ ውኃውን በጉጉት ምጥጥጥ ታደርገው ጀመር።

ጅብ ከበላዬ፣ ነፃነት ያጣሁ እኔ መሰልኩ፣ አህያ ከበታች ... ሕይወት እንዲህ ያለ ምድጃ ላይ ይጥድሻል አንዳንዴ !! ጅቡ ያጉረመርም ጀመረ።

"ምን አዘሀ ከየትም እየመጡ ያደፈራርሱብናል..." አለልሻ !! እኔ ደግሞ፣ *ልብሴን የማንቀረቅፍበት አንዳድ ሽቅብ መሄድ ጀመረ አንዴ ብዬ...*

"አይ ጅብ ... ወይ ዝቅ ልበል አንዴ ካደፈረስኩብህ" አልኩት።

"ኧረ አንተ ምን አደረግክ ! አንተ'ማ የኛው ነህ ወዳጄ" ብሎኝ አርፍ። ይታይሽ የኩቴ፣ ተራሽ እስኪደርስ ጅብም 'የእኛ' ይልሻል። በፍርሐት ቀን ተደብቀሽ ለሊት ሰትወጪ ለሌሊት ፈጥሯቸው ቀን ያወጣቸው ሁሉ እንደኛ ሆንች ይሉሻል!!

ይንቆራጠጥ ጀመረ ጅቡ...

"ዱቄታሟ" አለ።

የሚመልስለት ሲያጣ ድምጺን ከመጀመሪያው ከፍ አድርጎ፣

"አመዳም ሁሉ ... የማንም ወዛደር ... ኩሊ እዚህ እየመጣ ውኃችንን ይጨልጣል ... አሁንማ ጅረቱ ሁሉ ሊያደርቁት እኮ ነው" አለና ጎደሩ ! አህያ እንዳልሰማች ዝም ብላ ውኃዋን ትጠጣለች፣ ጅረቱ አቁማ በቁረጣ የጅቡን እንቅስቃሴ እየተቆጣጠረች...

"ደንቆሮ ሁሉ፣ ለስሙ ሐውልት የሚያክል ጆሮ ያውያ ሁለት ሰጥቷቸዋል እንጂ አይሰሙም አለ ብሎ ከት ብሎ ሳቀ። አህያ አሁንም አልመለሰችለትም፤ ዝም ብላ ውኃዋን ትጠጣለች። ይሄን ውኃ የምትጠጣው እንዳያው ፈርታ ይሆናል እንጂ ፈልጋ አልመሰለኝም...

ጅቡ ትንሽ አንገቱን ሰገግ አደረገና፣ "ከነዱቄታቸው እየመጡ ወንዛችንን ቡሀቃ አስመሰሉት..' አለ አህያ የተበሳጨች ትመስላለች ... እንደ ምንም ራሷን ተቆጣጥራ ዝም አለች። አያ ጅቡ ግን ከለላው በጎላ ድምፅ፣ "ከዛሬ ጀምሮ እዚህች ወንዝ አካባቢ አንድም አመዳም፣ ጆሯም፣ ዱቄታም ... ደንቆሮ አህያ ሁሉ ይደርሳትና ውርድ ከራሴ !" አለ። ማለት ብቻ ሳይሆን ፈንጠር ብሎ አህያ የመጣችበት መንገድ ዘግቶ ቆመ።

አህያ እንዳለቀላት አወቀችው ... ስለዚህ ዘና ብላ ጅቡን እያየች፣

"መብላት ሲፈልጉ አዋጅ ያበዛሉ..." አለች።

አሁን ጅቦ ገባመው፣

"የማንም አመዳም አህያ አዋጃችንን ያናንቃል ... ወይ ግዜ ... መታገሳችን አስናቀን" አለ ቶሎ በሚመስል ድምፅ መንገዷን የባሰ እየዘጋ !

"ኤዲያ ... አዋጁ ቀርቶብን የማንም ግማታም ጥንብ እንኳ ወንዛችንን ባላቆሸሸብን..." አለች አለ በሚገርም ድፍረት። አህያዋ ጅብ መሰለችኝና ቀጥ ብዬ ሳያት ያው አህያ ናት፤ ታዲያ ይሄ ድፍ ከየት መጣ...

ጅቡ ወደኔ እየተመለከተ፣ "ልብ አድርግ ... አዋጃችንን ሲታጣጥል ..." አለኝ።

"እረ የጅቦች ትዕግስት በዛ" አልኩ፤ ምናባቱ ላድርግ !!

"ኢድ አባክህ የአንተ አዋጅ ... መጀመሪያ ለዚህ ወሰን አልባ ሆድህ ገደብ አብጅለት ... ለእኛ አዋጅ ከማስነገብ !! ደግሞ እንመጣለን ወንዞቻችንን የማንም አነፍናፊ ጅብ አይከለክለንም..." አለች።

"ይሄ አዋጃችሁን በጉልበት ከመናድ አይተናነስም..." አለና ጅቡ አፈጠጠባት።

አህያ ኮራ ብላ ወደ ጅቡ ሄደችና፣ "አሳልፈኝ" አለችው።

እለቃላት ብዬ ሲበጭቃት ሳለማየት በፍርሐት ስሸማቀቅ፣ ጅብ መንገዱን በፀባይ ለቀቀላትና፣ "እኛ ማንም ተራ አህያ ተናገረ ብለን መንገድ አንዘጋም..." አለ።

ጅብ እንዴት ነው የተሰወጠው ብዬ ገረመኝ።

አህያ ራሷ ባለማመን ዞር ብላ እያየች ሄደች። በእፎይታ ተነፈስኩ !

ጅቡ እንዲህ አለኝ፣ "ደገርምሃል እኛ ጅቦችን ብዙ እንስሳት ካለሥማችን ሥም ደስጡናል፡፡ ሆዳም፣ ራስ ወዳድ፣ ጨካኝ አድርገው ስለሚስሉን ሌላው ቀርቶ ሳያየን ሲያብጠለጥለን ይኖራል !!" አለ አዝኖ ብሎ።

"እረ ተገቢ አይደለም፣ አሁን እንኳን ምን ያህል ታጋሽ እንደሆንክ አስመሰከርክ እኮ" አልኩት ከልቤ በሆነ አድናቆት። ስንሜውት ቀይተን እኔም ልብሴ ሲደርቅ ወደ ጉተራዬ ተመለስኩ።

***

(ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት)

የቢቄ ! የከቴ !! አሁን ለሊት ነው - ሰበር ዜና - ጉተራዬ ውስጥ ሆኜ መንደርተኛው ሲንጫጫ ሰማሁ፣ "የአቶ አሰፋውን አህያ ከጋጣዋ ጎትቶ ጅብ ወሰዳት" እያሉ...

# አይ ዶንኬር

አንድ ቀን እናቴ ተከራይቶ ወደምኖርበት ኮንዶሚኒየም ልትጠይቀኝ መጣች። እኔ ጋር መቆየ የፈለገችው ለአምስት ቀናት ነበረ። አቤት እንዴት ደስ እንዳለኝ። እንዲህ ቤት ተከራይቼ ራሴን ችዬ እናቴን በእንግድነት ራሴ ቤት መቀበል በእርግጥም የሚፈጥረው ስሜት ልዩ ነበር። እንደውም በር ያገኙኝ ሁሉ፣ "አብርሽ ዛሬ ምን ተገኘ፣ ፊትህ በራ እኮ" ይሉኛል። እንዴት ነው የማይበራው፣ እኔ ደመራ ችቦ ቢልል ብዬ አለመንበልበሌም እኔ ሆኜ ነው።

በእርግጥ አሷ ስለ ቤት እያያዜ አንድ ሚሊየን 'ኮሜንት' መስጠቷ አይቀርም፣ "ኢዲያ የምን መዝረክረ ነው ይሄ ... አሁን ወንበር እንዲህ ይቀመጣል" ልትል ትችላለች። ወይም የኔ የምለውን ይሄን ምንጣፍ "እዛ አውራ ጎዳናው ላይ አንጥፈኸው ነው እንዴ የሰነበትከው ... ታዲያ ምንድን ነው ይሄ ሁሉ አቧራ ልትልም ትችላለች። ቢሆንም የእናቴ መማረር የተለየ ውበት አለው። አቤት መማረር እኔ እናት ላይ ሲያምር። እናት እኮ ቢቃ አትታዘብም። እዛው ልክ ልካችሁን እየነገረቻችሁ እዛው ነገሩን በሰ መቃብር ትከትተውና የፍቅር አፈሯን ትመልስበታለች ! ውሸን ያነሳ ውሸ ይሁን ! እናት ናት ! እና እንደ እናት ምሬት የሚጥም ምን ነገር አለ ... ምንም !!

እናቴ ኮንዶሚኒየም የሚባል ነገር በቅርበት ስታይ የመጀመሪያዋ ስለነበር ደረጃውን ፈራችው እንደውም እዚህ በመኖሬ በጣም ተበሳጨችብኝ፣ (እዩት እንግዲህ አስተያየት ያላስብኩበት ቦታ ደረጃው ላይ ሲጀምር...)

"ሰው ሳይመገን ደብረዳሞ ላይ ወጥቶ ይኖራል ወ ቶ ጉ ድ ..." እያለች በከፍተኛ ፍርሃት ነበር የምስ ፎቅ ደረጃ የወጣችው። የከፍታውን ፍርሃት ቤት ስትገባ ረስታው ሌላ ግርምት ደግሞ ተጫረባት በቃ አንዱን ስትታዘብ አንዱን ስታመሰግን አመሸች። አንድ ሁለት ቀን አላምኛት እየተወጫት ...

ሥራ መሄድ ጀመርኩ። ደግሞ ሥራ በዝቶብኝ ስለነበር ብቻዋን ጥያት ጠዋት የወጣሁ ማታ ነው የምገባው። ልክ በሁለተኛው ቀን ማታ ስንገናኝ ታዲያ እንዲህ አለችኝ፣

"ይሄ አማሪካ የሚሉት አገር እንዲህ ነው እሉ"

"እንዴት" አልኩ ወደ ቴሌቪዥኑ ዞሬ። ቴሌቪዥኑ የሚያሳየው ሌላ ነገር ነው። "ይሄ እኮ 'ታች አርማጭሆ ወረዳ' ነው የሚለው አሜሪካ አይደለም" አልኳት በቴሌቪዥን ከሚታየው አዝመራ ሥር የተፃፈውን አንብቤ !

"ማን እሱን አለህ" አለችኝ።

"እና እንዴት ነው ያልሽው"

"እንዲህ እንዳንተ ቤት ነዋ ... ዝግትግት ያለ ጉድ፣ ቡና የሚጠራራ የለ፣ ደህና ዋላችሁ የሚል የለ፣ ሁሉም ቤቱን ዘግቶ ቁጭ ... የሚጫወት ሕፃን እንኳን የሌለበት ጉድ ! እስር ቤት ... እስቲ አሁን ሲያረጉ አየን ብለው እንጂ ሁሉም አበሻ ናቸው ምናለ ቢያወጉ፣ አብረው ቡና ቢጠጡ ኤዲያ ... ኤዲያ ያየነው አይቅረን ማለት ምንድነው" ብላ ተማረረች።

"ምን ችግር አለው ማሚ ሁሉም የራሱን ኑሮ ዘና ብሎ መኖር ነው።"

"እላየንም ዘና እቴ ... እትዬ የብር ጓል ልጃቸው አገር ላስጎብኝሽ ብላ ወስዳቸው አይደለም እንዴ እንዲህ ቁሱም ዝም፤ መጽሐፉም ዝም ቢሆንባቸው ተበለሻሽተው የመጡት ... ያች ደግ እመቤት ... ባዶ ቤት የፈረንጅ ሰይጣን የተጣላቸው" አለችና ከንፈሯን በሐዘን መጠጠች ... !! ዝም ብለን እንደቆየን፣

"እቡቹ ... እንግዲህ ከዚህ ከቆጥህ ወርደህ መሬት ካልተደላደልክ ወዳንተ እግሬን አላነሳም" ብላኝ ወደ ቤቷ ልትሄድ ተነሳች። ብለምናት ላግባባት ብሞክር፣

"ሆሆ በስተርጅና በተከበርኩበት አገር እንደ እማማ የብርጓል ጉድ ልታደርገኝ"

"እረ ማሚ አካበድሽው በቃ ቅዳሜና እሁድ እረፍት ነኝ ዘና እንላለን። ሥራ በዝቶብኝ እኮ ነው..." አልኩ።

"ግዴለም አከበድኩም አቀለልኩም መሬቱ ላይ አሳርፈኝ፤ ጠዋት ወሰደህ አቤቴ ጣለኝ" ብላ እንቢ

አለች። ቢቃ በእንተቱ ቢለዋ ቢጋደም እዚች ቤት አልቆይም ብላ በጠዋት ወደ ቤቷ ተመለሰች ! እና ትቶኝ ስትሄድ እንደ ሕፃን ልጅ ሆድ ባሰኝ። በመሐል ግን የእማማ የብርጓል ታሪክ ትዝ ሲለኝ በትዝታ መሳቅ ጀመርኩ። እማማ የብርጓል የተወለዱበት ሰፈር ታዋቂ ጠላ ነጋዴ ነበሩ። አንድ ቀን ታዲያ አሜሪካ የምትኖረው ልጃቸው አስቴር ደውላ፣

"እማዬ አሜሪካን ላስጎበኝሽ ነው፤ ተዘጋጅተሽ ጠብቂኝ" አለቻቸው።

"እስቱ ... እንደው ገንዘብሽን ካስከሰርኩሽስ አይቀር ... ተአማሪካው ይልቅ እየፋሳሲያምን አሳልመሽ በመለሽኝ" ይሏታል።

አስቴር ግን፣ "አይ እማዬ ደሞ፣ እኔ አንቺን ለማስደሰት ብዬ..." ብላ ስታኮርፍ እማማ የብርጓል አሜሪካ ለመሄድ ተስማሙ። መቼም የአስቴር ነገር አይሆንላቸውም። አንድ ልጃቸው ናት ያውም ካለ አባት ጠላ ሸጠው ያሳደጓት። እሷም ጎበዝ ነች። ቁንጅናዋ ሳያታልላት አንገቷን ደፍታ ተምራ የሕክምና ዶክተር ሆነች። ከአገር ከወጣች አስራ አምስት ዓመት አለፋት። አላገባች፣ አልወለደች። አሁንማ እድሜዋም ሄደ። አንዳንዴ ውጭ አገር የሚያስጠላው ትንሽ ሳንቲም ወርውሮ ትልቁን የተፈጥሮ ሐቅ መንጠቁ ላይ ነው !

እማማ የብርጓል አሜሪካ ለሦስት ወር ጉብኝት ሲሄዱ የሸኛቸው ሕዝብ ብዛት ለሰላማዊ ሰልፍ የወጣ ይመስል ነበር። አንድ የተቃዋሚ ድርጅት አባል የሆነ ጎረቤታችን ታዲያ፣ "ይሄ ሕዝብ ነፃነቱን ለመቀበል ሰልፍ ሲጠራ አይወጣም እንጂ ለማባረርና ለመሸኘትማ ይንጋጋል" ብሎ መንደርተኛውን ዘለፈ አሉ።

"ቆይ ያች ምርጫ ትድረስ ብንመርጠው ሞተናል" ሲል ፎከረ ጎረቤቱ ! ስጡዬው ታዲያ ይሄን ሲሰማ ኮት ብሎ ሳቀና እንዲህ አለው መንደርተኛውን፣ "ቀድሞ መቸና ሲዳቃሽ ይውጣ አሉ ... በምርጫው እንደሚኖር ሕዝብ አልመርጥም ብላችሁ ትፎክራላችሁ ሃሃሃሃሃ"

እማማ የብርጓል ልክ አየር መንገድ ሲደርሱ መንደርተኛውን ሁሉ ተሰናበቱና በመጨረሻ፣ "እንች የዝና..." ብለው ሰራተኛቸውን ጠሯት፣

"አቤት እትዬ..." አለች፤ ለከት የምትለብሰው ሸንሸን ቀሚስ አደምቋታል !

"እይው የለችልኝም፣ እታዋኙም ብለሽ ማጀቱን ብታድፋፊ ... ነግሬያለሁ ... አማሪካ እዝች ናት ሩቅ

እንዳትመስልሽ" ብለው አስጠነቀቋት። ሁላችንም ሳቅን። ሰፈር ውስጥ የእማማ የብርጓል አሜሪካ መሄድ እንደጉድ ተወራ። ደግሞ ጊዜው አባማ የምርጫ ቅስቀሳ የሚያደርጉበት ሰሞን ስለነበር ብዙሃኑ የመንደራችን ነዋሪ አሜሪካ ከነጥቁር መሪዋ ሁለተኛ አገሩ መስላ እየተሰማችው ነበር። የሆነች የናት አገሩ አሀት አገር ... እክስት አገር !!

ምን ያደርጋል እማማ የብርጓል አሜሪካ በሄዱ በወሩ ብቻቸውን ማውራት ጀመሩ። አስቴር ቤት እየዘጋችባቸው ስትሄድ ጭንቀቱ ነው ይባላል። መጀመሪያ ሲጀምራቸው መፃፍም ማንበብም የማይችሉት ሴትዮ ከመሬት ተነስተው እንግሊዘኛ ተናገሩ ... ያለ ምንም ስህተት ጥርት ባለ የአገሬው ልሳን፣ "አይ ዶንኬር" ብለው ጮኹ !!

በእውነቱ አስቴር እናቷ ሲያዝናኗት የሞከሩ መስሏት በሳቅ ፈረሰች። "ወይ ማሚዬ ተጫዋች እኮ ነሽ" እያለች።

ከዛ በኋላ ግን ሙሉ ቀንና ሌሊት ከእማማ የብርጓል አፍ ሌላ ቃል አልወጣ አለ፣

አይዶንኬር...

አይዶንኬር...

አይዶንኬር ብያለሁ

አይዶንኬር...

አማምላከን አይዶንኬር...

ጭራሽ አንድ ቀን ሸክ ብለው በባሕል ልብሳቸው ዘንጠው፣ "እኔ እናትሽ ይሄ ወጠጤ ካሸነፈኝማ ሞቻለኋ" ብለው መንገድ ጀመሩ።

አስቴር ደንግጣ፣ "ማነው ወጠጤው ማሚዬ" ብትላቸው።

"ወባማ ነዋ ... ከአገሬ ድረስ የመጣሁት በምርጫው ለመሳተፍ መስሎኝ" እያሉ የቀን ቅዠት ውስጥ ገቡ። በቃ እንዴ ለአሜሪካ ፕሬዝደንትነት ሊወዳደሩ እንደሄዱ አድርገው ራሳቸውን እጩ ተወዳዳሪ ያደርጋሉ ... ሌላ ጊዜ ከጎረቤት የሚሰማው ጩኸት ረበሸኝ ይላሉ። ምንም ዓይነት ጩኸት ግን አልነበረም !

ጭራሽ አንድ ቀን በኢፓርታማው መስኮት ብቅ ብለው፣ "እይዶንኬር" አሉና ከኢትዮጵያ አሟሽተው የወሰዱትን ገንዘ የሚያህል ጀበና ቁልቁል ቢያምዘገዝጉት ወደ ሥራው የሚጣደፍ አንድ ፈረንጅ አናት ላይ ዷ ብሎ ፈነዳ ! ፈረንጁ ከዛ የሮጠ ሴላ ሰፈት ሊገባ ስንዝር ሲቀረው ነው አሉ የቆመው ! (መቼም የኛ ሰፈር ሰዎች ነገር ሲያወሩ ያማሙቃሉ)

አስቴር እናቷን ወደ ሃኪም ወሰደቻቸው። ሃኪሙ እማማ የብርጓልን መርምሮ፣ 'ባይፖላር ዲስ ኦርደር' ምናምን ... ነው አላት ለአስቴር። "ያው 'ሃሉሲኔት' ሊያደርጉ ማለትም የሌለ ነገር ያለ መስሎ ሊታያቸው ይችላል ... ብቻቸውን አትተዪቸው ... ወጣ እያደረግሽ አገናኚያቸው" እያለ የአስቴር ጡቶች ላይ ዓይኑን እንከራተተ። አስቴር መቼስ ውብ ልጅ ነች። (ዶክተሩ በአስቴር ጡቶች ምክንያት ሃሉሲኔት አድርጎ ስለ ገነት ምናምን ማውራት ሳይጀምር አልቀረም...)

ሕክምናው አንድ ዓመት ሊወስድ እንደሚችል በመግለፅ ቅል በሚያህል ነጭ የፕላስቲክ ሰንዱቅ ነጫጭ ኪኒን ሰጣቸው ... 'በቀን አንድ እስከ ምፅዓት !' እማማ የብርጓል ታዲያ በቀጣዩ ቀን ቤት ተቀምጠው ድምፃቸው ቢጠፋባት አስቴር ከመኝታ ቤቷ ብቅ ብላ አየቻቸው። መርፌና ክራቸውን አቅርበው የታዘዘላቸውን ኪኒን እየበረበሩ እና በክር እየወሰወሱ ምን የመሰለ መቁጠሪያ ሰርተው አገኘቻቸው ! አንድ ኪኒን በበሱ ቁጥር፣ "ኢይዶንኬር" እያሉ !

አስቴር ታዲያ የኃኪሙን ምክር በመስማት እናቷን ልታዝናናቸው ይዛቸው በሰው አገር ጎዳና ላይ ትዞራለች።

"ይሄ እየሩሳሌም ነው ... አይደለም እንዴ" አሏት ኮስተር ብለው።

"አዎ ማማዬ እየሩሳሊም ነው" አለች አልሄድም እንዳይሏት ፈርታ።

"የተረገምሽ ! የተቀደሰችውን ምድር በጫማ ታስረግጭኛለሽ ?" አሉና ጫማቸውን አውልቀው በማንካራቸው አስፓልቱ ላይ ተደፍተው መሬቱን ሳሙ። በባዶ እግራቸውም ጉዞ ጀመሩ። ወዲያው ከየት እንደመጣ ያልታወቀ የጋዜጠኛ መንጋ አስቴርና እማማ የብርጓልን ከብቦ በፎቶ ያጣድፋቸው ጀመር ... በለጭ በለጭ በለጭ በለጭ ... በቀጣዩ ቀን የወጣው ዋሽንግተን ፖስት የፊት ገፅ ላይ የማማ የብርጓልን ፎቶ አትሞ ከናቱ እንዲህ ሲል ፃፈበት አሉ (ያው የኛ ሰፈር ሰዎች ወሬ ባይታመንም...)

"የጀግናው ኢትዮጵያዊ ሯጭ የአበበ ቢቂላ ታናሽ እህት በባዶ እግራቸው ዋሽንግተን 'ወክ' ሲያደርጉ"

እማማ የብርጓል ከጉብኝታቸው በአንዱ ቀን ኋይት ሐውስ ፊት ለፊት ደረሱ። እልልታቸውን አቅልጠው እንደልማዳቸው ቤተመንግሥቱ ፊት ለፊት በግንባራቸው ተደፍተው ምድሩን ከሳሙ

በኋላ፣ "ጌታዬ የተሰቀለው እዚህ ነው ?" ሲሉ አስቴርን ጠየቋት። አስቴር ትክዝ ብላ ነፍሬን ሕንፃ እያሻገራ እየተመለከተች፣

"ዓለም ሁሉ ለዝዞ መኖቱ የተሰቀለው እዚሁ ነው ማማዬ ... ምንም ንፁህ ልብ ሰጡን ገረመው እንጂ ሁሉም ከያለበት የሚሰግደው ለዚሁ ነው ... ሴቱ፣ ወንዱ ... ያልተማረው፣ የተማረው ... አገር ያለው፣ አገር አልባው ... እንጀራ የጎተተው፣ ጥላቻ የገፋው ... ፖለቲከኛው፣ ነጋዴው ... ነፍሰ ገዳዩ፣ ዘራፊው ሁሉም እዚሁ ነው ልቡ የተቸነከረው ... በተምታቱ ወንበዴ ጋሳቦቹ መሃል ሁሉም የራሱ መሲህ ሆኖ የተሰቀለው እዚሁ ነው" አለቻቸው።

አስቴር ስትናገር እንባዋ በዓይኗ ሞልቶ ነበር። የተቸነከረችበት ሚስማር፣ ለአስራ አምስት ዓመታት ያንጠለጠላት የኑሮ መስቀል ላይ ዛሬም ሕመሙ፣ ዛሬም የማንነት ቀውሱ ሲቃይ እያንገበገባት...። ከምር ለራሷም ይሄ ነጭ ሕንፃ የዓለማዊያን የኑሮ ቀኖና የሚሰበክበት ቤተክርስቲያን መስሎ ተሰማት ! ይሄን ቢነግሩት ትውልዱ ቶማስ ነው ... የኑሮ ችንካር የበሳውን መዳፍ ካላየ ወይ የራሱ መዳፍ ካልተቸነከረ አያምንም !

አስቴር እማማ የብርጓልን ወደ ኢትዮጵያ መለሰቻቸው። ሰው ይሆናሉ ብላ አላሰበችም ነበር። ኢትዮጵያ ሲደርሱ ግን ቡና ተፈልቶ ጎረቤቱ ተሰብስቦ እያገላበጠ ሲሰማቸው ባይሾጎር ዲስ ኦርደር የለ፣ ዲፕሬሽን የለ ጂኒ ጃንካ የለ ጤነኛ ሆነው ቁጭ !! በእርግጥ አልፎ አልፎ (ሙሉ ጨረቃ ሲሆን ነው አሉ...) የዋሽንግተኑ ጂኒ ይነሳባቸዋል።

እኔም ይሄንን ነገር ለማመን የተገደድኩበት አንድ አጋጣሚ አለኝ። እንግዲህ እማማ የብርጓል የምተበትን እፅናኝ፣ የታመመን አስታማሚ የመንደሩ አድባር መሆናቸውን ማንም ያውቃል። ሰው ታመመ ከተባለ ነጠላቸውን አንጠልጥለው መሮጥ ነው። ጎረቤቱም ከላይ እስከታች "አስታማሚዬ ... ጠያቂዬ" ነው የሚላቸው።

አንድ ቀን ታዲያ እናቴ፣ "እማማ የብርጓል" አለቻቸው።

"እመት"

"ጋሽ አሰፋው አባታቸውን ተረድተው ተቀምጠዋል አሉ ኑ ለቅሶ እንድረስ እስቲ" ... ጋሽ አሰፋው በመንደራችን የተከበሩ የአገር ሽማግሌ ናቸው። የእማማ የብርጓልም የጠላ ደንበኛ። እማማ የብርጓል ታዲያ ጮክ ብለው እንዲህ ብለው መለሱላት ለእናቴ፣

"አይ ዶን...ኬር !!"

# አድዋ ዛሬ ናት፣ አድዋ ትላንት...

(እንቀፅ 17 ፡ - እኛም መስኮታችንን አንከፍትም፣ እናንተም ሚስቶቻችንን አትዩ !!)

ጣሊያን ኢትዮጵያን ወርራ አምስት ዓመት ፍዳዋን በሊታ፣ ፍዳችንን ስታበላን አያቴ አሉላ ገዛ የውስጥና የውጭ አርበኛ ነበር። በጦር ሜዳ ብትሉ አንድ ባታሊዮን ጦር ጭምጭምታ ያደርግ ጀግና ሲሉት፣ "ኢዲያ ምን አሳት አቺ" ይላል !! በከተማ ብትሉ ጠላት መኝታ ቤት ሳይቀር የተቃጠ ሚስጥር ፈልፍሎ ሲያወጣ አጀብ ያስብል ነበር። ታዲያ በአያቴና በቆራጥ አርበኞች ትግል ፋሽ ኢጣሊያ ካገር ከተባረረ በኋላ፣ ለአገር በሠራው ታላቅ ጀብዱ፣ በድል አጥቢያ ጃንሆይ ራሳቸ አስጠርተው አሁን የጣልያን ኤምባሲ የሚባለው የተገነባበትን ቦታ በሙሉ ከታላቅ ክብርና ሽልማ ጋር በሽልማት ለአያቴ ሰጡት !

አያቴ እዚሁ በሽልማት የተሰጠው ቦታ ላይ ትንሽ ጎጆ ቀልሶና፣ የተረፈው ሜዳ ላይ በቆሎ ዘር ሲኖር፣ አንድ ቀን የጃንሆይ መልዕክተኞች ሲንሰግሉ ቤቱ ድረስ መጡና፣

"እዚህ በቆሎ የዘራህበት ቦታ ላይ 'የምባሲዮን' ሊሰራበት ነውና መድረሻህን ፈልግ ብለውሃል ጃንሆ አሉት።

"እረ ውሰዱት ደሞ ለሞላ ቦታ" አላቸው። ትንሽ ቆይቶ፣ "ይሄ ግን 'የምባሲዮን' ያላችሁት ነገር ምን ነው ?" ሲል ጠየቀ።

"አይደለም !"

"እሃ ተማሪ ቤት መሆን አለበት !"

"አይደለም...!!"

ታዲያ ምንድነው ቤተሰኪዮን ይሆን እንዴ? ሲል ግር ብሎት ጠየቀ።

"ምባሲዮን ማለት ንጉሡ የፈቀዱላቸው የውጭ አገር መኳንንት እና መሳፍንት አገራቸውን ጠብቀው የሚቀመጡበት እና አንዳንድ የመንግሥት ሥራዎችን የሚከውኑበት ማረፊያ ነው" አሉት መልዕክተኞቹ እንዱ።

"ቤቶ?" ሲል ጠየቀ አያቴ በግርምት።

"ቤቶ!"

"እኮ ፈረንጆች ይሄን ሁሉ ቦታ አጥረው ቁጭ ሊሉ ነው" አለ እንደገና በታላቅ ግርምት።

"አዎ! ይሄ የምባሲዮን... የወከላቸው አገር የማይደፈር ግዛት ነው"

"ታዲያ ድንበራችን ላይ ያባረርነውን ጠላት መናገሻችን ላይ 'እርደንለት ጋርደንለት' ልናስቀምጠው ነው ዘሎ" አለ አያቴ በቁጭት።

መልዕክተኞቹ አያቴ ላይ ሳቁበት። ስለኤምባሲ ያለው እውቀት አነስተኛ መሆኑን በመገንዘባቸው ለድፍን ሁለት ሰዓት ስለኤምባሲ ተግባርና ለአገራችን ስላለው ጠቀሜታ በዝርዝር አወሩት።

ተግባብተው ሊለያዩ ሲሉ ግን ነገር ተበላሸ። ጉድ ፈላ። አገር ተሸበረ። ድንገት ነው ነገሩ የተመሰቃቀለው...

"ለመሆኑ የማን አገር ኤምባሲዮን ነው?" ሲል ጠየቀ አያቴ፣

"የጣሊያን" ብለው መለሱለት።

"ጣሊያን ጥሊያን ... እኮ ጥሊያን ይ....ሄ ፋሽስት የነበረው" አለ አያቴ ማመን አቅቶት።

"እንደ‐ታ አሁን በሰላም መጥተዋል"

አያቴ ሰይጣኑ ተነሳ። ተንደርድሮ ምንሽሩን መዥረጥ አደረገና ለማማሽ ሰዓት ያህል ፎከሮ ሲያበቃ፣ "ባንዳ ሁሉ..." ብሎ የጃንሆይን መልዕክተኞች ማሳደድ ጀመረ!

"ሁሉብን መከተል እንወዳለን። መንገድ ላይ ድንገት አያቴን ያዩ ሁሉ፣ ገና የአርበኝነት ስሜቱ የሰበረደላቸው፣ እንዲሁም አርበኝነት ያመለጣቸው፣ እንደገና እድሉን አገኘን በማለት ምንሽራቸውን

አፈፍ እያደረጉ፡ "ያዘው..." እያሉ ቢስ ላይጠቅማቸው አያቴን ተቀላቅለው የንጉሡን መልዕክተኛ ማሳደድ ጀመሩ። ሙቼስ አዲሳባ እንደዛን ቀን ተፎከረባትም፣ ተሸለለባትም አያውቅም ይላ ሁኔታውን የታዘቡ።

አያቴ ቁጣው መለስ ሲል ዞሮ ቢመለከት ድፍን የአዲስ አበባ ወንድ ተከትሎታል።

"ምን ሆናችሁ" ቢላቸው አያቴ፣ "አይ ... ሩጫው ወደ ቤተ መንግሥት መሆኑን ስንሰማ ነ የተከተልናችሁ" አሉ !!

አያቴ የተከታዩን ብዛት አየና በዛው ሸፈተ ! ስሙ የገነነ ሽፍታም ሆነ ! ስሙ ከተጠራ እንኳን ኢትዮ ምድር ያሉት ሮም የተቀመጡትም ጥልያኖች ወባ እንደያዘው እየተንዘፈዘፉ ንስሃ ይገባሉ ! ጥል የኢምባሲው ግንባታ ሲጀመር በወርም በሳምንትም በል ሲለው በየሦስት ቀኑ ብቅ እያለ ይሄን ግዚ ሁሉ ይፈጀው ጀመረ !!

ጃንሆይ በበኩላቸው አያቴን በዲፕሎማሲ ማሳመን መርጠው መልዕክት ላኩበት። በድፍረት ከነ ጸጉሩና ከነምንሽሩ ፊታቸው ቀርቦ፡ "ጃንሆይ ትላንት ይሄን ፋሽስት፣ 'እንኳን አባረርከው' ብለው የሸለሙኝን ቦታ ዛሬ ከኔ ነጥቀው ላባረርኩት ሰላቶ በመስጠትዎ ተቀይሜዎታለሁ !! እማማ ተቀይሜዎታለሁ። እንዴት እንዴት ነው ነገሩ ... እዚህች አገር አባራሪው ከተባራሪው ተደባለቀ እ. ዳር ላይ ያባረርነው ከመሐል እያባረረን ተቸገርን" አለ።

ጃንሆይ በጥሞና ሲያደምጡት ቆዩና፡ "ቅሬታህን ሰምተናል። ካንተ የሚበልጥብን የለም። የ አንተ ዳር ላይ ልክ ያስገባሃቸው ናቸው ዛሬ ወዳጅነታችንን ፈልገው በእንብርክክ ደጅ የጠኑ እንደምታውቀው ጀግና በጡብ የመጣበትን እንጂ በፍቅር የመጣን አይነካም" አሉና የአያቴን ቁ አበረዱት።

"በል አሁን በቃህ ለማን ብለህ ነው መሬትህን ጥለህ የምትሄደው። እነሱ እያዩህ ይሸማቀቁ እንጂ" ብለው እዛው ኤምባሲው ጎን ለአያቴ ሰፊ ቦታ ሰጡት።

እርቅ ወረደ ! ንጉሡ ብልህ ነበሩ። አንዳንዴ አያቴን ይጠሩትና፣ "ጎረቤቶችህ ሰላም ናቸው ?" ብለ ይጠይቁታል። አያቴን ሰላይ አደረጉት...

###

እንግዲህ የአያቱ ጎጆ እና የጣሊያን ኢምባሲ በግንብ አጥር ብቻ ነበር የሚለያዩት። አያቴ ጣልያኖቹን በያቸው ቁጥር ደሙ እየፈላ፣ "ወይ ነዶ የማንም ፋሽስት ጋር እንዲህ ትክሻ ለትካሻ እየተጋፋሁ ልኑር" እያለ በብስጭት ሲግል ሚስቱ ወይዘሮ ቢልጅጌ መኮንን (የፊታውራሪ መኮንን እጅጉ የመጀመሪያ ልጅ) እያባበለች ወደ መኝታ ቤታቸው ትወስደውና ከብስጭቱ አብርዳ በሌላ ጉዳይ ትለኩሰዋለች ! አቤት ማባበል ስታውቅበት ... ገና ስትታይ ነገር ታበርዳለች ... እሳት ፈገግታዋ እሳት ያጠፋል ...! ይች ውብና አስተዋይ ሴት ሲበሳጭ ስታባብለው፣ ሲበሳጭ ስታባብለው ... አምስት ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ወለዱ። ይሄ ብቸኛ ወንድ ልጅ የእኔ አባት ነበር።

አያቴ ምንም እንኳን የልጆቹን አእምሮ በምክር እርሶና አለስልሶ የጣሊያንን ጥላቻ ቢዘራበትም አልፀደቀም። በተለይ ሴት ልጆቹ ያማረ መኪና ይዘው የሚገቡና የሚወጡ የጣልያን ጎረምሶች ላይ ልባቸው አልጨከን እያለ፣ ዓይናቸውም እየተንከራተተ አስቸገረው። ጭራሽ ይለይልህ ብለው ከአባቱ በስተቀር ሁሉም 'ሶላቶ' አግብተው ቁጭ አሉ። በዚሁ ብስጭት ሙሉ ቦታውን ለአባቴ ብቻ አውርሶና ጥሊያን ያገቡ ልጆቹን ሁሉ ክዶ ሚስኪን አያቴ በደም ግፊት ሞተ !! አባቴም፣ 'ሙሉ' የምትባል ውብ ሴት አግብቶ እዚሁ ነገረኛ የውርስ ቦታ ላይ ቤት ሰርቶ መኖር ጀመረ (ሙሉ እናቴ ናት...)።

እናቴ ሙሉ መቼስ ወላ በቁንጅና፣ ወላ በባሕሪ ቢባል ይሄ ቀረሽ የማይሏት ውብ ናት። ስትገባ ስትወጣ ተመልካቿ ብዙ፣ የሚመኛት እልፍ ነበር። አባቴ ታዲያ እናቴ ስትደነቅና ስትሞገስ ደስ ቢለውም፣ ከተመልካቹ ሁሉ ደሙን የሚያፈላው የጣልያኖቹ አስተያየት ነበረ። እንግዲህ ጣልያኖቹ እናቴ ስታልፍ ፊታቸው እንደ ቲማቲም ቀልቶ አፋቸውንም፣ ዓይናቸውንም በልጥጠው በአጥራቸው ላይ እየተንጠላጠሉ በአጉል ምኞት ሲመለከቷት አባቴ ይበሳጫል፤ በላቸው በላቸው ይለዋል። (ደግሞ ለማለት፣ አያቴ እንደሆን ምንሽሩን አውርሶታል - መታገስ ደግ ነው ብሎ እንጂ...)

ምድረ ሶላቶ ከዘበኛ እስከ አምባሳደር ማፍጠጣቸው ሳያንስ፣ "ለደህንነት" በሚል ሰበብ ፊታቸውን ወደ እኛ ግቢ ያዞሩ አራት ካሜራዎች ተከሉ። እናቴ ግቢ ውስጥ በተንቀሳቀሰች ቁጥር አራቱም ካሜራዎች ወደሄደችበት ተከትለዋት ይዞራሉ (የምታጠባቸው መንታ ልጆቿ ነበር የሚመስሉት)። ሌላ ሰው ሲንቀሳቀስ ካሜራዎቹ ግዑዝ ናቸው። ካሜራዎቹ የተተከሉት ለደህንነት ይሁን ላጉል ምኞት አባቴ ግራ ገባው...

ጭራሽ ጥሊያኖች ባሳተሙት አንድ ዓመታዊ መጽሔታቸው ላይ እናቴ አንገብሳ እሮጌ የመኪና ጎማ ላይ በተቀመጠ ጥሰት ልብስ ስታጥብ ከኋላዋ (ያውም አጭር የውስጥ ልብስ ብቻ ለብሳ) የሚያሳይ

ባለቀለም ፎቶ ተካትቶ ነበር። ከእናቴ ፎቶ ጎን አንዲት ጥላ ቢስ፣ ሽርጥ ያሸረጠች ጣልያናዊት ኮረዳ ዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ደገፍ ብላ የሚያሳይ ፎቶ አለ።

ከፎቶዎቹ ሥር፣ "ኢትዮጵያ ከጣልያን ስድስት ዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች በእርዳታ አገኘች፤ ይህም የኢትዮጵያዊያንን ሴቶች ድካም በመቀነስ ጊዜያቸውን ለሌላ ጉዳይ እንዲያውሉት ይረዳል" የሚል ጽሁፍ ሰፍሯል። 'ሌላው ጉዳይ' ምንድነው ሲል አባቴ አሰበ።

እንዴት የሚስቴን ፎቶ ካለ እሷም ካለእኔም ፍቃድ መጽሔት ላይ ያትማሉ፣ ሲል ተብከነከነ፤ እንደውም አምባሳደሩን ራሱን ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊጠይቀው ወሰነ። ሰውን ካለፍቃዱ፣ ያውም በገዛ ግቢው ውስጥ፣ እንዴት ፎቶ ያነሳሉ … ያውም በአጭር የውስጥ ልብስ ብቻ - ይሄ ንቀት ነው፤

አባቴ በቀጥታ ወደ ኤምባሲው ዋና በር ሄደና እንደ ግለሰብ መኖሪያ ቤት አስፈሪውን የብረት በር አንኳኳ፤

ጓጓጓጓጓ

ዘበኛው አጮንቁሮ አባቴን ከተመለከተ በኋላ በሩን ከፍቶ ባለማመን እያየው፣

"ምን ፈለግክ ?" አለው እርዳታ የፈለገ ኢትዮጵያዊ ይሆናል ብሎ፣

"ጌታህን ጥራው ! ባልቻ በርህ ላይ ይፈልግሃል በለው" አለ አባቴ ቆፍጠን ብሎ። ዘበኛው ግራ ተጋባና፣

"ማንን ነው የጥበቃ አለቃውን ነው ?" አለ።

"እሱ ምን ያደርግልኛል ? አምባሳደሩን ነው ያልኩህ"

"እ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ … በል ሂድ ወደዛ ደፋር !" ብሎት እርፍ አባቴ ባልቻን !!

በመንደሩ የተከበረውን አባቴን እንደ ምጽዋት ፈላጊ የሶላቶዎቹ ዘበኛ፣ ሂድ ወደዛ አለው !! በዛችው ቅፅበት ከአባቴ የተሰነዘረ ብርቱ ጥፊ ዘበኛውን አባቴ እግር ሥር ኩርምት አደረገው። የጥፊው ድምጽ ሮም ድረስ ስለተሰማ፣ የወቅቱ የጣሊያን መንግሥት፣ ኢትዮጵያ ዓለማቀፉን የኤምባሲዎች ጥበቃ እና አሰራር በመተላለፍ የተከበረ ዜጋዬን በጥፊ በመደርገም በሊዮዋ ከደረሰችብን ውርደት የበለጠ ውርደት አደርሳብናለች ሲል ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አቤት አለ።

ጃንሆይም በዚሁ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተጠይቀው፣ "በአርማጥ አፍሪቃ በኤሮፓዊያን ቅኝ ግዛት እየታመሰችበት ባለችበት በዚህ ወቅት፣ ብዙሃን የአፍሪቃ ልጆች በቆዳቸው ቀለም ምክንያት በግፍ እየተገደሉ እና እየተገፉ ባሉበት ወቅት፣ በአንዲት ኤሮፓዊት አገር ኤምባሲ የጥበቃ ሰራተኛ ላይ፣ ያውም በራሱ ስህተት፣ በተሰነዘረ ጥፊ ዓለም ይህን ያህል መንጫጫቱ ገርሞናል። ይህ ጥፊ የኢትዮጵያ መንግሥትን የማይወክል፣ በዕለት ግጭት የተከሰተ ድንገተኛ ፐርቀማ በመሆኑ ግለሰቡ በቀላል ሽምግልና ችግሩን እንዲፈቱት እናደርጋለን። አገራችንም ከጥፊው ባሻገር ለአፍሪቃ ብሎም ለዓለም ያበረከተችው በጎ ተግባር በዚህ ጥፊ ምክንያት ሊጠለሽ አይገባም" በማለት ዓለምን ያስደነቀ፣ አገሬውንም ያኮራ ንግግር አደረጉ።

በዚህ ንትርክ መሃል የእናቴ ፎቅ ጉዳይ ተድበሰበሰ።

በጣልያኖች ተንኮል እልህ የተጋባው አባቴ፣ "ልጆቼ ስለበረከቱ ፎቅ ቤት እሰራለሁ..." አለና ማንንም ሳያስፈቅድ ባለ ሁለት ፎቅ ቪላ ወደ ኤምባሲው አጥር አስጠግቶ መሥራት ጀመረ።

ይሁንና ባልያኖች ለደህንነታችን ያሰጋናል በማለት ክስ አቀረቡ።

ኤምባሲ ሃን ፎቅ መሥራት ክልክል ነው ተብሎ አባቴ ታገደ !

"አገሬ ላይ እስከ ጨረቃስ ፎቅ ብሠራ ምናገባችሁ ?" በማለት ጠየቀ።

"ለወዳጃችን የጣልያን መንግሥት ስጋት ስለሚፈጥር፣ ለደህንነታቸውም ስለሚያሰጋ አይፈቀድልህም አቶ ባልቻ"

"እሄሄ እነሱን ለመግደል ማን ፎቅ ይሰራል ... ውቤ በረሃ ሲያውደለድሉ አይደለም የሚውሉት..."

"ሥርዓት ጌታው፣ እንግዶቻችንን ማክበር የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው"

ጉዳዩ በጣም ተጋነነና በአባቴና በጣልያኑ አምባሳደር መካከል የሁለትዮሽ ድርድር ቢካሄድ የተሻለ ነው በማለት በጃንሆይ ልዩ አማካሪዎች አስተባባሪነት በጣልያን መንግሥትና በአባቴ ባልቻ መካከል ታሪካዊ ድርድር ተካሄደ።

ይህ ድርድር በታሪክ፣ "አንቀጽ 17 - እኛም መስኮቶችን እንከፍትም እናንተም ሚስቶቻችንን አትዩ" በመባል ይታወቃል ।

የውሉ ዋና ዋና ነጥቦች...!

አንቀፅ 1. አቶ ባልቻ ደመቀ ኢምባሲያችን ጎን የሚሰሩት ፎቅ መሰኮቱ ወደ ጣልያን ኢምባሲ ላይዞር ከዞረም ላይከፈት።

አንቀፅ 2. ጣልያኖች ወደ ኢምባሲው ሲገቡና ሲወጡ አሁን ያሉትንም ሆነ ወደፊት የሚወለዱትን የአቶ ባልቻን ቤት ልጆች በቃልም ሆነ በድርጊት ላይተናኮሉ፤ በመኪናም ሆነ በእግር በር ላይ ላይገናኙ፤ ሆን ብለው ስሜት ቀስቃሽ እና አማላይ ድርጊት ላይፈፅሙ።

.

.

.

አንቀጽ 17. ወደ አቶ ባልቻ ቤት የዞሩት የኢምባሲው የቪዲዮም ይሁኑ የፎቶ ካሜራዎች ሙሉ በሙሉ ሊነሱ።

የዚህ ውል 17 ኛው አንቀጽ የጣልያንኛ ትርጉም ግን እንዲህ ይል ነበረ፤

"የኢምባሲያችን የቪዲዮም ይሁኑ የፎቶ ካሜራዎች፤ የሙሉን እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ፎቶ ሊያነሱ ፈቃድ አላቸው" ይላል።

ታሪክ ራሱን ይደግማል !!

እናቴ ሙሉ ታዲያ ከንፈሯን ሸርመም አድርጋ የተንከል ፈገግታ ፈገግ አለች። ማንም አላያት ከለይጣን እና ከእኔ በስተቀር። ትንሽ ወንድሜ አባቴን አለመምሰሉ እንደውም ፈረንጅ መምሰሉ አስቋት ይሆን?

# 39ኛው ዕቅድ

ዮርዳኖስ ከእስራኤል መጣች። ድንገት ነው ማታ ደወለችና፣ "ሄይይይይይ" አለችኝ።

"ሔይይይይይይይይ" ብዬ በድንጋጤ ጮህኩ። አንዳንድ ቃል፣ አባባል፣ ድምጽ ... አንድን የሆነ ሰው ብቻ የሚወክልበት ጊዜ አለ አይደል ? ልክ እንደዛ ሄይይይይ የሚለው ድምጽ ዮርዳኖስን ይወክላል !! እና ከብዙ ዓመት በኋላ ሄይ ስትለኝ ማነሽ ምናምን ሳልል ዮርዳኖስን አወቅኳት። የዓመታት ትዝታዬ ጋጣው እንደተከፈተለት የበግ መንጋ ከሕሊናዬ ማህደር ተግተልትሎ ወጣ። የሚገርመው ገና ዮርዳኖስን ሳስባት ሳቄ ቀደመኝ። እንደውም ትንታ የምትመስል ሳቅ ቡፍ ከሚል ድምጽ ጋር ከንፈሬን ጥሳ ወጣች !

"አልናፈቅኩኝም ?" አለችኝ።

"መናፈቅ እንኳን አልናፈቅሽኝም፣ ግን አሁኑ ብርርርርርር ብዬ አጠገብሽ ብገኝ ደስ ታዬ..." ሳቀች።

"ወሬኛ ! በል ነገ ምሳ አብረን ነን" ተቀጣጠርን።

###

ዮርዳኖስ ሸዋንግዛው በክንድህ ትባላለች። አስረኛ ክፍል እንደነበርኩ ያፈቀርኳት ልጅ ነበረች። የእኔ የፍቅር ታሪክ ለምን ነበር ብቻ እንደሚሆን አይገባኝም። አፍቃሪ ሳይሆን የፍቅር ታሪክ አውሪ ሆኖ መኖር ቢሰለችም ቅሉ አማራጭ የለኝምና ግጣሜን እስከማገኝ ኢጋጣሚዬን አወራችኋለሁ !! በቀጣዩ ቀን እኔና ዮርዷ ... ስላሳለፍነው ነገር እያወራን ቢቃ በሳቅ ስትፍለቀለቅ ዋለች ! በተለይ ለምን እንደተለያየን ስነግራት የምትጠጣው ስፕራይት ትን እስኪላት፣ ሰው ሁሉ ምን ትዝለፍጣለች ብሎ

እስኪገላመጥ በሳቅ ተንከትክታ ልትሞት !! ለካስ እስካሁን ለምን እንደወጣሁ እንደቀረሁ አታውቅም ነበር!

ያው እንደነገርኳችሁ ፍቅረኞች ነበርን። በእርግጥ የእኔና የዮርዳኖስን ፍቅር ከሌሎች ለየት የሚያደርገው ዮርዲ ጋብቻ የሚባለውን ነገር አቅድ አውጥታ ለት መንቀሳቀሷ ነበር። እንደ ዮርዲ እቅድ ከሆነ ከአምስት ዓመት በኋላ ህዳር 13 ቀን እንጋባለን፤ ቀልድ እንዳይመስላችሁ ... በእያንዳንዱ ዓመት ምን እንደምናደርግ በሰፊውና በዝርዝር አንድ ሁለት ብላ አስቀምጣዋለች። ቀልድ የለም ዮርዲ ጋ!

የመጀመሪያው ዓመት፣ የመጀመሪያ ሦስት ወራት ... እርስ በርስ መተዋወቅና ፍላጎትን እና ባሕርይ መነጋገር፤ ለዚህም በአካል፣ በስልክ፣ በደብዳቤ አልያም እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ መንገድ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ አስቀምጣዋለች። የአምስት ዓመቱን እቅድ ወደ ሰባት ገፅ ወረቀት ላይ ነበር የጻፈችው፤ ስንጠረዥ ምናምን ሁሉ ነበረው !

"አብርሽ ይሄን አንብበውና ያልተስማማህበት ነጥብ ካለ መጨረሻ ላይ ባያያዝኩት ባዶ ወረቀት ላይ አስቀምጠው" ከሚል ቆፍጣና መመሪያ ጋር ያን ሁሉ ጽሁፍ ሰጠችኝ - የመርሕ ሰው ዮርዲ !! የሰጠችኝን ገና ስመለከተው እየቀለደች መስሎኝ ሳቄ ሊያመልጠኝ ነበር ኮስተር ያለ ፊቷን ስመለከተው ግን ሳቄን አከሸፍኩት - ንመን በጤና። ካለ ቦታው ሳቅ ደሟን እንደሚያፈላው አውቃለሁ። ዮርዳን ስወዳት ልክ አልነበረኝም፤ ልለያት አልሻም፤ ለዛ ነው በጥፍሬ የምታቆመኝ።

ሳላያት ከዋልኩኝ ሁሉም ጓደኞቼ እንደምንጫነጭ ስለሚያውቁ፣ "ሱሴ" እያሉ ያሾፉብኝ ነበር ! ንጋት ማለት ለኔ ዮርዲን የማይበት አዲስ ቀን ሲሆን ምሽት ማለት ዮርዲን የማላይበት ረዥዥዥዥዥዥዥዥዥዥዥዥም ዘመን ነበር። ታዲያ እንቅልፍ ወስዶኝ ቶሎ እንዲነጋ በጊዜ መተኛት ብዬ ቻልኩት። ግዴለም ያለሰት ለፍቅር ይሞታል እንዴ

ማታ ቤቴ ቁጭ ብዬ የዮርዲን እቅድ ስመለከተው እንደ እብድ ብቻዬን እየጮህኩ ሳቅኩ። እናቴ ባይገባትም እናቴ እኔ ከሳቅኩ ትስቃለች። እልትሺ አላውቅም እንጂ ባለቅስም የምታለቅስ ነው የሚመስለኝ ! ታዲያ፣ "አቡቹ የዛሬውን የቤት ሥራ የሰጣችሁ ከበበው ገዳ ነው እንዴ ..." አለችና ሳቀች። ምክንያቱ

"በተማሪ አሌክስ አብርሃምና በተማሪ ዮርዳኖስ ሽዋንግዛው በኩንደህ መካከል ለሚፈፀመው ጋብ

የለምነት አመት ቅድመ ዝግጅት እንደ" ይላል የዮረዲ 'ጥራዝ' !! ጽሁፏ ቀጥ ቀጥ ብሎ የቆመ ስለሆነ በእስክርቢቶ ቀለም ሳይሆን የክብሪት እንጨት እየገጣጠሙ የፃፉት ነበር የሚመስለው። በተለይ 'ለ' የተባለው ፊደሏ ያስፈራራል ! የሆነ ከባድ ስብሰባ ላይ አስደንጋጭ ንግግር ሲናገር እጁን ቀጥ አድርጎ የመጣ ቁጡ ወታደር ነው የሚመስለው የዮረዲ 'ለ'። ዜግነቱን ቀይሮ ኢትዮጵያዊ የሆነ ትንሹ 'ሔቻ ነበር የዮረዲ 'ለ'። ፊደሎቿ እንደ ፍቅሯ አዕምሮ ውስጥ እንደ ቅርስ ተደላድለው የመቀመጥ የተለየ ኃይል ነበራቸው።

አቅዶቹን ሳትብ በዝርዝር እንዲህ ይላሉ፤

1. መተዋወቅ ... በቅንፍ "ተከናውኗል" ይላል፤

2. የአብርሃምን ፍላጎት፣ ዓላማና ራዕይ ማወቅ ... በከፊል ተከናውኗል፤

.

.

.

23 . አብርሽን ከአባባ ጋር ማስተዋወቅ፤

24. የቤት ዕቃዎችን ማሟላት፤

.

.

.

37. ቀለበት

38. ጋቢቻ

39. (((ወደ አሌጋ መሄድ)))

40. ለእርግዝና የሚያስፈልጉ ልብሶችና ምግቦችን ማዘጋጀት ... እያለ ይቀጥላል። የሚገ... የልጆችን ስም ሁሉ እቅዱ ውስጥ ስለተካተተና በስሙ እየጠራች ስለፃፈችው የተወለደ የሚ... ነበር። በእርግጥ ዮርዳ ቀላል ልጅ አልነበረችም። ያሰበቻትን ካላደረገች እንቅልፍ አይወስዳ... ታዲያ ሰላሳ ዘጠነኛው እቅድ አቅል አሳጣኝ ! በውስጤ መፎከሮች ይሰሙኛል። መኝታ ቤቴም ግ... የተለያዩ መፎከሮችን ጽፌ ለጠፍኩ...

"ሰላሳ ዘጠነኛውን እቅድ በታላቅ ተጋድሎ እናሳካለን !!"

"ዮርዳኖስ ሽዋንግዛው በከንድህ ለቀረፀችው ሰላሳ ዘጠነኛ እቅድ ቀን ከሌሊት እንሠራለን !!"

"ከሰላሳ ዘጠነኛው እቅድ መሳካት የሚያስተጓጉለን ምድራዊ ኃይል አይኖርም !"

ያለምንም ደም እቅዱ ይቅደም !!

ሰላሳ ዘጠነኛው እቅድ ለዘላለም ይኑር !

ሰላሳ ዘጠነኛው እቅድ ሙሉ ሰው ያደርጋል !

ትልቅ ነበር ትልቅም እንሆናለን ...!!

እሜን ሃሌ ሉያ ! በጣም እጅግ በጣም ለሰላሳ ዘጠነኛው እቅድ ጓጉቼ ነበር !!

በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በርካታ ዕቅዶቿን አልፈን ሃያ ሦስተኛው ላይ ስንደርስ እንደማ... እርግጠኛ ሆኜ ነበር። እቅድ 23፤ "የዮርዳ አባት ጋር መተዋወቅ" ነበር። ጦር ኃይሎች አ... ወደሚገኘው የዮርዳ ቤት ስንደርስ ልቤ በፍርሃት ዝቅ ከፍ የምትል ይመስለኝ ነበር። ግቢያቸ... ስመለከተው ደነገጥኩ። በሕይወቴ እንደነዮርዳ ግቢ ዓይነት ሰፊ ግቢ አይቼ አላውቅም። ከግቢ... ያለ ነበር የሚመስለው። ከእኛ ቤት ጋር ሳወዳድረው እልቅስ እልቅስ አለኝ፤ "መሬት ላራሹ" ... የማገዙት በሳቹ ከጓደኞቻቸው አንድ ቀን ቀድመው ይሰሙ ነበር። ... እንድ ሦስት የሚሆን አህያ ጣል ቢያደርግበት ፓርክ በሉት ! ሙሉ አዲስ አበባ ብሄራዊ ፓርክ ... በኢትዮጵያ ብቻ የምትገኝ ድንቅዬ ብርቅዬ ዮርዳኖስ የምትባል ፍጥረትም አለችበት !

ወደ ውስጥ ስንገባ ስምንት የሚከራዩ ቤቶች በግራ በኩል አሉ፤ ከዋናው ቤት ቢታከሉ ተሂዶ የሚፀዳዱበት የሚመስል ሽንት ቤት አ.......ዛ ወዲያ ብቻውን ተኮፍሷል ! አቤት አራራቁ ! መቼም አንድ ሰው ሆድ ቁርጠት ቢይዘው፣ ማራቶን ሮጦ ነው እፎይ የሚለው !! ብቻ ሆድ ቁርጠቱ የዮርዲዩን አይያዝብኝ ! ዋናው ቤት መሃል ላይ ኩፍስ ብሏል ! ከዋናው ቤት በቀኝ በኩል በቆሎ የተዘራበት ሜዳ ... ይሄ ሁሉ ሆኖ፣ የዮርዲ አባት "ልጆቼ ሲያድጉ ሆንግ ይሰሩበታል" ብለው የከለሉት ሰፊ ቦታ ደግሞ አለ ! እንግዲህ ከዚህ ቦታ ዝቅ ብሎ ያለውም ጫካ የራሳቸው ግዛት ነው ! ግቢው የክብር፣ የማንነት እና የእውነት መንፈስ የሰፈነበት ይመስላል ... እንዲሁ እንደዛ ተሰማኝ !

ወደ ሳሎን እየመራች ወሰደችኝ። ወለሉ ከጣውላ ስለተሰራ በረገጥነው ቁጥር ሲጥ ሲጥ እያለ ያረገርጋል። ደግሞ የወለሉ ጣውላ ቢጋዝ ስለተወለወለ ነው መሰል ቤቱ ጋዝ ጋዝ ነበር የሚሸተው። ከሁሉም የገረመኝ የኮርኒሱ ርቀት። በስማም ርቀቱ ... ጨረቃና አንድ ሁለት ኮከቦች ጣል ቢያደርጉበት ሰማይ ነው የሚመስለው ! በዚህ ሐሳብ ተመስጬ የዮርዲ አባት ወደተቀመጡበት ሳሎን ስገባ በሩ ላይ በቁሜ ደርቄ ቀረሁ !! ቢድንጋጤ !!

የዮርዳኖስ አባት ስለቱ የሚያንፀባርቅ ጎራዴ ከፍ አድርገው ይዘው እያገላበጡ ይመለከቱታል። ተመልሼ ልሮጥ አሰቤ የዮርዲ መናገር ስትጀምር እንደምንም ተረጋጋሁ !

"አባባ ጓደኛዬ መጥቷል፣ ይሄው አብርሃም ይባላል" አለቻቸው በፈገግታ። መቼስ የዮርዲ ፈገግታ እንኳን ጎራዴ ራስ ያስረሳል !

አባቷ ጎራዴውን በጥንቃቄ ወደ ቀኝ ዘወር አድርገው በመነፅራቸው አናት አትኩረው ተመለከቱኝና ጎራዴውን ወደ ግራ እጃቸው አዘዋውረው ቀስ ብለው ከተቀመጡበት በመነሳት ቀኝ እጃቸውን ለሰላምታ ዘረጉልኝ። አቤት ቁመታቸው - እዚያ ላይ !! ሰው ቤቱን የሚሰራው ለካ በልኩ ነው። ኮርኒሱ የመራቁ ሚስጥር አሁን ገባኝ !! መቼም በዚች ምድር ጎራዴ ከያዘ የፍቅረኛው አባት ጋር በድፍረት የተዋወቀ "ጀግና" ታሪክ አልሰማሁም ! (እናንተ ሰምታችኋል ? እኮ - የለም !!) የእኔና የአባባ' አቋቋማችንን ድንገት ላየው የቆንጆ ልጃቸው ጓደኛ ሳልሆን ተፋላሚያቸው ነበር የምመስለው !

እግዜር እጄን በሰላም ይመልሰው ብዬ ለሰላምታ ዘረጋሁ። ተጨባበጥን። መዳፋቸው እንደ ግቢያቸው ሰፊ ነው፤ ግን እንደ የዮርዲ ለስላሳ - ሰፊና ለስላሳ ... ቢሆንም ለስላሳ እጆች ጎራዴ እስከጨበጡ ድረስ ለስላሳ ናቸው ለማለት ያስቸግራል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እጃቸውም ቃላቸውም ለስልሶ ነፍሳቸው እንደ ብርጭቆ ወረቀት ይሻክራል ! (ይሄን ሁሉ የምቀባጥረው ስለተጨነቅኩ ነው)

"አብርሃም መልካም ስም ነው ..." አሉ የዮርዲ አባት - ተርፈያለሁ !! ዮረዲ ፈገግ አለች። ፈገግታ ጎራዴ ያስረሳል። የኔ ዮርዲ ፈገግታዋ ጋሻ ነው፤ አባቷ የጨበጡት ጎራዴ ፊት ይገዝው የምቆመው፣ አባባ ጣጣ የሚያበዙ ሰው አይደሉም ! ሥራህ ምንድን ነው ምናምን እያሉ አላጨናነቁኝም፣ "ዮርዳኖስ ቆንጆ ሻይ አፍይለት..." ብለው ወደኔ ዞሩ !! "ተጫወት" አሉኝ ጎራዴያቸውን እየወዘወዙ፣ ከዛም በጎራዴው ጫፍ ግድግዳው ላይ የተደረደሩትን ኒሻኖች እየጠቆሙ ለአገራቸው የሰሩትን ጀብዱ በሚያሲደምም አተራረክ ያወጉኝ ጀመረ። በኒሻኖቹ መሃል ያለው ከፍት ቦታ ላይ በእጃቸው የጨበጡት ጎራዴ ማስቀመጫ ቦታ ነበር። ለካስ ጎራዴው ሳሎናቸው ውስጥ የተቀመጠ ታሪካዊ ዕቃቸው ነው፣ መቼስ አንዳንዴ ተሰቅሎ የኖረ ታሪክም ወርዶ ማስፈራሪያ ይሆናል !

ዮርዲ ወደ ጓዳ ገባች ጉድ ጉድ ስትል አባቷ ግቢውን ሊያስጎበኙኝ ይዘውኝ ወጡ...

"ይሄ ወደፊት ልጆቼ፣ የልጅ ልጆቼ ሀንፃ የሚሰሩበት ቦታ ነው። ይሄኛው ሰርግ ሲኖር ዳስ የሚተከልበት ቦታ ነው ... እነዮርዳኖስን ስንድር ... እነዳንኤልን ስንድር ... እነኤርሚያስን ስንድር ... እነበለጠን ስንድር ... እነየትምወረቅን ስንድር ... እነ..." አረ ጉድ ይሄ ሁሉ ልጅ ... ብዬ ተገረምኩ። ሰዉ ቀጠሉ፣ "ይሄ ቦታ ... ወደፊት በዘመናዊ መንገድ ከሰሩበትም ብዙ ነገር ይሆናል። ያ የምትመለከተው ... እኔው ራሴ ችግኝ በትከሻዬ እየተሸከምኩ የተከልኩት ነው። ነገ ከነገ ወዲያ ልጆቼ ይጠቀሙበታል። ዋናው ለትውልድ አንድ ነገር መትው ነው..." እያሉ አንድ በአንድ አስጎበኙኝ። ጎራዴውን እስከሁን በእጃቸው ስለያዙት አንዱን ከፍት ቦታ፣ "ይሄ ያንተ መቃብር ነው" ብለው አንገቴን ያበሩት ይሆ እያልኩ ስጋት ውስጥ ነኝ ! ጎራዴ ይዞ ስለድንበር ማውራትኮ አደገኛ ነው ! ቢያንስ ካርታ ... እንደመነጋገር አይቀልም !

የዮርዲ አባት ለእኔ የሚሉት ነገር የለም ! ለዛሬም ብለው አያውቁም ... ለልጆቼ፣ ለልጅ ልጆቼ ይተርካሉ። ስለነገ መልካሙን ሁሉ ያልማሉ። ነፍሰ ሲያከብራቸው የሚችል ዓይነት ትከሻ ... ሰው ነበሩ። እኔ እኔ እኔ የሚል ውትወታ የበዛበት ከተማ ውስጥ ለነገ ማሰብ እንዲህ ጎራዴውን ... ይንጎራደዳል።

በግቢው ሰሜን አቅጣጫ አንድ ትልቅ ሕንፃ የተሰራበት ቦታ በጎራዴያቸው እየጠቆሙኝ በ... በሚንቀጠቀጥ ድምጽ እንዲህ አሉኝ፣ "ያ የምትመለከተው ህንፃ የተሰራበት ቦታ እስከዛ እስከ መንገዱ የእኔ የአባትህ መሬት ነበር፣ ነጥቀው ወሰዱት። አልከራከር አቅም አነሰኝ። ልጆቼም በየሰው ...

"አብርሃም መልካም ስም ነው ..." አሉ የዮርዲ አባት - ተርፌያለሁ !! ዮረዲ ፈገግ አለች። ፈገግታ ጎራዴ ያስረሳል። የኔ ዮርዲ ፈገግታዋ ጋሻ ነው፤ አባቷ የጨበጡት ጎራዴ ፊት ይገርው የምቆመው አባባ ጣጣ የሚያበዙ ሰው አይደሉም ! ሥራህ ምንድን ነው ምናምን አያሉ አሳጨናነቁኝ። "ዮርዳኖስ ቆንጆ ሻይ አፍይለት..." ብለው ወደኔ ዞሩ !! "ተሚወት" አሉኝ ጎራዴያቸውን እየወዘወዙ ከዛም በጎራዴው ጫፍ ግድግዳው ላይ የተደረደሩትን ኒሻኖች እየጠቆሙ ለአገራቸው የሰሩትን ያዜሙ በሚያስደምም አተራረክ ያወጉኝ ጀመረ። በኒሻኖቹ መሃል ያለው ክፍት ቦታ ላይ በእጃቸው የጨበጡ ጎራዴ ማስቀመጫ ቦታ ነበር። ለካስ ጎራዴው ሳሎናቸው ውስጥ የተቀመጠ ታሪካዊ ዕቃቸው ነበር። መቼስ አንዳንዴ ተሰቅሎ የኖረ ታሪክም ወርዶ ማስፈራሪያ ይሆናል !

ዮርዲ ወደ ጓዳ ገብታ ጉድ ጉድ ስትል አባቷ ግቢውን ሊያስጎበኙኝ ይዘውኝ ወጡ...

"ይሄ ወደፊት ልጆቼ፣ የልጅ ልጆቼ ሀንጎ የሚሰሩበት ቦታ ነው:: ይሄኛው ሰርግ ሲኖር ዳስ የሚተከልበት ቦታ ነው ... እነዮርዳኖስን ስንድር ... እነዳንዔልን ስንድር ... እነኤርሚያስን ስንድር እነበለጠን ስንድር ... እነየትምወረቅን ስንድር ... እነ..." ኸረ ጉድ ይሄ ሁሉ ልጅ ... ብዬ ተገረምኩ። አሁን ቀጠሉ፣ "ይሄ ቦታ ... ወደፊት በዘመናዊ መንገድ ከሰሩበትም ብዙ ነገር ይሆናል። ያ የምትመለከተው ጫካ እኔው ራሴ ችግኝ በትከሻዬ እየተሸከምኩ የተከልኩት ነው። ነገ ከነገ ወዲያ ልጆቼ ይጠቀሙበታል ዋናው ለትውልድ አንድ ነገር መተው ነው..." እያሉ አንድ በአንድ አስጎበኙኝ። ጎራዴውን እስከሁን በእጃቸው ስለያዙት አንዱን ክፍት ቦታ፣ "ይሄ ያንተ መቃብር ነው" ብለው አንገቴን ያበሩት ይሆ እያልኩ ስጋት ውስጥ ነኝ ! ጎራዴ ይዞ ስለድንበር ማውራትኮ አደገኛ ነው ! ቢያንስ ካርታ ላይ እንደመነጋገር አይቀልም !

የዮርዲ አባት ለእኔ የሚሉት ነገር የለም ! ለዛሬም ብለው አያወሩም ... ለልጆቼ፣ ለልጅ ልጆቼ ለትውልድ፣ ለነገ፣ ለወደፊት _ የሚል ቃል ከአፋቸው አይለይም። በእልህና በፍቅር ስለትውልድ ይተርካሉ። ስለነገ መልካሙን ሁሉ ያልማሉ። ነፍስ ሊያከብራቸው የሚችል ዓይነት ትክሻ ከባድ ሰው ነበሩ። እኔ እኔ እኔ የሚል ውትወታ የበዛበት ከተማ ውስጥ ለነገ ማሰብ እንዲህ ጎራዴውን ይ ይንጎራደዳል።

በግቢው ሰሜን አቅጣጫ አንድ ትልቅ ሕንፃ የተሰራበት ቦታ በጎራዴያቸው እየጠቆሙኝ በሐዘን በሚንቀጠቀጥ ድምጽ እንዲህ አሉኝ፣ "ያ የምትመለከተው ህንጻ የተሰራበት ቦታ እስከዛ እስከ መንዝ የእኔ የአባትህ መሬት ነበር፤ ነጥቀው ወሰዱት። አልከራከር አቅም አነሰኝ። ልጆቼም በየሰው አገ

ተበትነው የእለት እንጀራቸውን ሲያሳድዱ ጊዜ ያነሳው ኃብታምና ጉበኛ ባለሥልጣን ተመሳጥረው ገስቱን እየሸራረፉ ነጠቁኝ" አሉና በቁጭት ጎራዴያቸውን ነቀነቁት።

'አንዱ ልጄን 'እኔ አቅም የለኝም ና ና ይሄን መሬት አስመልስ' ብለው፣ 'ያለውን መች ሠራህበት አባባ' አለኝና አረፈው። አየህ የትውልዱን መዳሸቅ ... መሬት ህልውና ነው ! ድንበር፣ ማንነት ነው ! ድንበሩ የተሸረፈ ትውልድ፣ ማንነቱ የተሸረፈ ታሪክ ነው ያለው ! የረገጠውን መሬት እየተነጠቀ ለአግሩ ዘመናዊ ጫማ የሚደነቅር ትውልድ፣ መሬት ማለት የሐንሃ መስሪያ ነው ለእርሱ ... መሬት ማለት ትልቅ እርሻ ሆኖ እህል የሚያመርት ነው ለሱ ! ሆዳም !"

'መሬት ... ከሕንፃውም ከእህሉም በፊት ማንነት ነው። እንዳይመስልህ ልጄ፣ ፈጣሪ ስንዘር መሬት ከለነገር አይፈጥርም ! ይሄ ስለገባን ነው ምንም አይፈይድም ለሚባል በረሃ እና ጭንጫ ሕይወታችንን፣ አካላችንን ስንገብር የኖርነው። እንኳን ጠላት መሬትህን ነክቶት ይቅርና ነፋስም አፈርህን ወደ ሰው አገር ሲወስድ ሊያምህ ይገባል። አፈር ማንነት ነው ልጄ ... ወንድምህ ሥራ ቢሠራ ባይሠራ ወንድምህ ነው፣ እናትህ አማረች አላማረች እናትህ ናት፣ አባትህ ኃብታም ሆነ ደሃ ያው አባትህ ነው፣ ሚስትህ ድንግል ሆነች አልሆነች ያው ሚስትህ ናት፣ ሰው ዝቅ አለ ከፍ አለ ያው የእግዜር ፍጥረት ነው ... 'ሰውን ከአፈር ሠራው' ሲል'ኮ ቃሉ ሚስጥሩ ወዲህ ነው ! አፈርህ ሰው ነው። የሰው መፈጠሪያ፣ የትውልድ መፍለቂያ ማዕድህ ነው ማለት ነው። አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ሲል ቃሉ ... መሬት፣ ወደ አፈር የተመለሱ አያትና ቅድመ አያቶችህ ስጋ እና አጥንት ነው ማለት ነው። ይሄውልህ የአያት ቅድመ አያትህን፣ የአባት እናትህን ስጋ ነው ሸርፌህ የምትሰጠው !! ቆንጥረህ የምትሸጠው !"

'መሬት ቢረባም ባይረባም ወንድምህ ነው፣ እናት አባትህ ነው፣ ወዳጅህ ነው፣ ሚስትህ ነች ... መሬቱ ሲነካ ይሄ ሁሉ እውነት ተነካ ! ድንበርህ ሲጣስ ይሄ ሁሉ እውነት ተጣሰ ! እንዴት መሬት ይቆረሳል ? እንዴት አይጠቅምምና ለእነ እከሌ ይሰጥ ይባላል ? እንዴት መሬት እንዳሞሌ በገንዘብና በቁስ ይለወጣል ? ... እናቱን ሸጦ መኪና ልግዛ ትላለህ ? ... አባትህን ሸጠህ ንብረት ሳጠራቅም ትላለህ ? ... ሚስትህን ለሌላ ወንድ ሰጥተህ ሰላም ለመፍጠር ነው ትላለህ" የዮርዲ አባት ሰውነታቸው በእልህ እየተንቀጠቀጠ ቀጠሉ...

'አገር ማለት ሰው ነው እያሉ በትውልድህ አንቀልፍ ላይ ብርድ ልብስ ይደርባሉ። አገር ማለት አፈር ነው። ሰውም ማለት አፈር ነው። ኢትዮጵያ ከተፈጠረች ጀምሮ የሞቱት ሰዎቿችን ስጋና አጥንት አፈር ሆኖ ይሄው" አሉና መሬቱን በጎራዴው ጫፍ ጫር አደረጉት። "አየህ አሁን አፈር አይደለም

የሚርከት፣ የሰው ስጋ ነው ! ሲሜር የሚያመው፣ ሲወጋ የሚያቃስት ሰው ነው አፈሩ !! ይሄንን ቆርሰው የሚወስዱት። አገር ማለት ሰው ከሆነ፣ ሰው አፈር ነውና አፈርህን ሲነኩ አንቢ ልትል ይገባል ልጄ. ሕንፃ እና መንገድ አይግረምህ፣ የሰው እጅ የሚሰራው የእጅ ጥበብ ሁሉ አይድነቅህ ነገም ልጆችህ ከአንተ በተሻለ ይሰሩታልና ! ልጆችህ መቼም ለማያገኙት ስንዝር መሬት ግን ያለህን ሁሉ ክፈል !

"ስንዝር መሬት ሰጥተህ ዘመናዊነትን ከምታመጣ፣ ቅንጣት አፈርህን ሳታስነካ እድሜ ልክህን በዛፍ ሥር ኑር ! ለልጅህ መቀመጫውን ተውለት። ዛሬ ተሰርቶ ነገ የሚፈርስ መንገድና ድልድይ፣ ሕንፃና ግንብ ለልጅህ ጉብት አይደለም። መሬት መሬት መሬት - ምንም ቃል፣ ምንም ስምምነት መሬትህን ከማጣት የታሪክ ጉድፍ ነው። መሬትህ ሲነጠቅ አጨብጭበው የሚሉህም የታሪክ አተላ፣ የማንነት ጉድፍ ናቸው ያለህን ይብርከው ሲሉህ፣ ምርቃት መስሎህ አሜን እንዳትል ! ከዚህ የባሰ መርገምት የለም ! የተሻለ ባርኮት፣ ከርግማን እኩል ነው !"

"ቶሽስት ጥሊያን ሰላልሰለጠነ አይደለም መሬት ፍለጋ አገር አቋርጦ የመጣው፣ እስራኤል በእምነቱም በዕውቀቱም ከእኛ የመጠቀች አገር ናት፣ ስንዝር መሬት ልትነጥቃት ብትሞክር ግን ያላትን ሐብት ያላትን ሰው ሁሉ ሰውታ ዓለምን ታናውጣለች። የስልጣኔ ጥጉ መሬትህን እንዴት እንደሰጠህ በሚ ቋንቋ ማስረዳት አይደለም። መሬትህን በምንም ምክንያት ለማንም አለመስጠት ነው !!" አሉና ትከ ብለው ወደተወሰደው እና በመስተዋት የተሽቆጠቆጠ ሕንፃ ወደተሰራበት ቦታቸው አተኮሩ። የከበ ወጣቶች በእግር በመኪና ይገባሉ ይወጣሉ። ሕንፃው ጫፍ ላይ፣ "የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ" የሚል ጽሑፍ በደማቁ ይታያል ! አባባ እንዲህ አሉ፣ "ቦታዬን መልሱ ብላቸው፣ የመጠሃፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ይፍረስ የሚል መናፍቅ ነው አሉኝ" በጣም ተከዙ አባባ !

ላጽናናቸው ስለፈለግኩ ቀስ ብዬ እንዲህ አልኩ፣ "አባባ ያለውን ቦታ ይባርክሎት እዚህም ላይ ከተሰ ብዙ ነው ... ምን ያረጋል ካልተጠቀሙበት፣ ይተዉት፣ ይሄው ይሄስ ከፍት አይደል፣ መች ተሰራበት ... ዋናው እርስዎ ደህና"

የዮርዲ አባት ዓይናቸው ተጎለጎለ፤ ደም ሥራቸው ማንባራቸው ላይ ተመሰቃቅሎ ተዘረጋ...

"ምናልክ አንተ ? ... ውጣ ከዚህ ግቢ ! ... ውጣ አልኩህ አንተ ... ከንቱ የከንቱ ከንቱ ..." ብለው በጎራዴው አጠገባቸው የነበረውን ኮባ ቢገነድሱት ከነዮርዲ ቤት የሮጥኩ (እንደ ቀነኒሳ ወይም ገልሙጥ አያልኩ) ታክሲ ተራ ቆሞ ያገኘሁት ሚኒባስ ውስጥ በመጣሁበት ፍጥነት ዘልዬ ገባሁ። ምንም እንኳን መዳረሻዬ ስቴዲየም ቢሆንም፣ ታክሲው ዓለም ባንክ ሲጥለኝ ቅር አላለኝም። ለምን ዓለም

አይጥለኝም፣ ብቻ ነፍሴ ተርፏል። የዛን የከባ ቀን ቢሰጠኝስ ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር ... ሆሆ !

ከዛ በኋላ ዮርዳኖስ የምትባል ልጅ ዓይኗን ሳላይ ይሄው ከስንት ዓመት በኋላ እርሷም ከእስራኤል መጥታ፣ እኔም እሮጌ ተመንድጌ ሥራ ይዤ፣ "ሙሉ ሰው ሆነን"፣ ሁኔታውን እያወራን ስንስቅ፣ ስናዝን፣ ስንገረም ቆልን !

"አባባ ደህና ናቸው ግን ዮርዲ ... " አልኳት። ትንሽ ተከዝ ብላ፣

"ታመዋል" አለችኝ።

"ምነው ምን አገኛቸው"

"አባከህ ብስጭት ነው ... ያንን በቆሎ ተዘርቶበት የነበረውን ቦታ ለመንገድ ብለው ወስደውበት ሲበሰጭጭ ነበር። ደግሞ አሁን ዛፍ የነበረባቸውን ቤታች በዋናው መንገድ በኩል ያለውን ቦታ ለባቡር መንገድ ብለው ወሰዱበት - ቢቃ አልጋ ላይ ውሏል" አለች ዮርዲ።

ቀጠል አድርጋም፣ "ለምን አብረን ሄደን አትጠይቀውም" አለችኝ ፊቷ ሲፈነዳ የተዘጋጀ ሳቅ እርግዞ ነበር !

ሁለታችንም ሳቃችንን ማቆም አልቻልንም ! በሳቁ መሃል አንድ ነገር ጠየቅኳት፣

"እኔ የምልሽ ዮርዲ፣ ይሄ የአባባ ቦታ ተሸርፎ ተሸርፎ ለኢሻናቻቸውና ለጎረቤያቸው ማስቀመጫ ቦታ ሳያጡ አንድ ነገር ብታደርጊ አይሻልም ?"

"ምን ላድርግ" አለች በታከተው ድምጽ።

"ቢያንስ ማስመለስ የሚቻለውን መሬት፣ አቅም እጥተው ማስመለስ ያቃታቸውን ቦታ እንኳን ለማስመለስ ብትሞክሪ፣ ልጅ ለመቼ ነው ታዲያ"

ዮርዲ በረኘርሙ ተነፈሰችና፣ "ባከህ ያለውን ይባርከው ... ይሄስ መች ተሰራበት !!"

የእናት ልጅ አመድ !!

# ቀስ ብሎ ይቆማል !

ሙና ትባላለች። መጀመሪያ እንዳየኋት የወደድኳት ቀይ ልጅ ስለሆነች ነው። ቀይ ሴት ቀልቤን ነ... የምትነሳኝ። ከልጅነቴ ጀምሮ ነው ቀይ ሴት ላይ እንደ አንድ ነገር የሚያደርገኝ። "የቀይ ሴት አ... አለብህ" ይሉኛል ጓደኞቼ። እንዲህ ስላችሁ 'ልክስክስ' ትሉኝ ይሆናል፣ ግን ለፍርድ አትቸኩሉ። እጠ... ቀይ ትሁን ጠይም፣ ጥቁር ትሁን የቀይ ዳማ እንዲትም ሴት ጋር ተሳስሜ አላውቅም። አብረውኝ ይማ... የነበሩ ሴቶች፣ "ይሄ ዝም ብሎ ያፍጥጥ እንጂ በየትኛው ወንድነቱ ነው ሴት የሚጠይቀው" እያ... ያሽሟጥጡኛል። ሴት መጠየቅን ማይጨው ከመዝመት እኩል የወንድነት መለኪያ ሲያደርጉት እ... ነው! የእኔ ማይጨው ሴት መጠየቅ አይደለም፤ ከጠየቅት ጋር በፍቅር መዝለቅ እንጂ። (ለትፈ... ይሉኛል እንዲህ ስል...) ማፍጠጥን ለምን እንደ ወንድነት እንደማያዩት አይገባኝም። ስንቱ ነው ሴት ለማየት እያፈረ አንዴ ወደ ሰማይ አንዴ ወደ መሬት ዓይኑን የሚያቅበዘብዝ? እና በዕናት ማፍጠ... በራሱ እንዴት ወንድነትን ግምት ውስጥ ይከትተዋል ?

በእርግጥ ቀንጆ ስለሆንኩ፣ ማለቴ በጣም ቆንጆ ስለሆንኩ አየከጀሉኝ እንደሆነ አውቃለሁ፤ (ጉ... አይደለም)። ወንዶች የከጀልናትን ሴት ማግኘት ሲያቅተን በአደባባይ "ደግሞ ይቺ መጣች ቀረ... እያልን እንደምንተርረውና ቤታችን ገብተን እንደምናለቃቅሰው፣ በምኞትም እንደምንቃትተው ሁሉ አንዳንድ ሴቶችም የከጀሉትን ሲያጡ ስም መለጠፍና ማሽሟጠጥ ይቀናቸዋል። "ይሄ ልክስክስ ሴ... አይተርፈውም" እያሉ (ሴት ካልተረፈው እነሱ እንዴት ተረፉ ?) ... "ይሄ ምን ወንድ ነው ሴታሴ... እያሉ፣ "ይሄ በባዶው ይከፋሳል፤ ቤሳቤስቲን የለውም እኮ" እያሉ፤ ከውሸት ሳቅ ጋር ደባልቀው እር... በእርስ "እውነትሽን ነው ... ሙች" እየተባባሉ ይበሻቀጣሉ። ደግነቱ ሆድ ለሆድ ስለሚተዋወቁ ከ... ለካቢ እየተያዩ ነው የሚበሻሹቁት። ሴቶች ከጠሏችሁ ለለ'ኑንተ ከፋም ደማም አያወሩም፣ በቀማች... ለሦስት ሰዓት ያህል ስለሆነ ወንድ ያወሩና ሲያሙት የዋሉት ወንድ ሲደውልላቸው፣ "ከነመፈጠርህ... ረስቼሃለሁ" ይሉታል። ሙና ግን ልዩ ልጅ ናት።

ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት ባንክ ቤት ነበር። ገንዘብ መክፈያው ባለጌ ወንበር ላይ ተቀምጣ። ይሄ ባለጌ ወንበር ለካስ መጠጥ ቤት ብቻ አይደለም ድንበሩ! ለነገሩ ከብር የበለጠ ምን አልኮል አለ?! ሙናን ፊት ለፊት ሳያት የባንክ ሒሳብ 'ቡኪ' ከእጄ አምልጦኝ ወደቀ። ብዙ ብር የያዘ ይመስል ሲወድቅ ጢ ብሎ ጮኸ። ድሮም ባዶ ነገር እንደሚጮኽ ነው። አነሳሁት። ቀና ስል እንደገና ስልኬ ከእጄ ላይ ወደቀ፤ ...ባትሪው እዛ ጋ ... ቀፎው እዚህ። እንዳወዳደቁ ብርታት ቀፎው ብቻ ሳይሆን ስልክ ቁጥሬም የተበታተነ ነው የመሰለኝ። 09 እዛ 11 ደግሞ እዚህ ... ተዝረከረከኩ፣ ድንብርብሬ ወጣ። ምናባቴ ላድርግ ... ቅ ላ ት "ባንክ ቤት ብር ሳይሆን ፀሐይ ማስቀመጥ ጀመሩ እንዴ!" ያስብላል። የፀጉሯ ጥቁረት በዛ ላይ ማብረቅረቁ፣ ጥቁር አልማዝ በብዙ ሺ ክሮች እንደጨሌ የተሰከሰከ፣ ዓይኖቿ ልብ ላይ የሚፈጥሩት ውጋት ነገር አለ፣ አፍንጫዋስ ቢባል ቀጥ ብሎ ወደታች ወርዶ ከንፈሯን መሻገር ፈርቶ ቀጥ ብሎ የቆመ ነው የሚመስለው። ቆንጆ ናት ነው መቼስ የሚባለው ሌላ ምን ቃል አለ ?!

በኋላ ሙና እንደነገረችኝ ከሆነ አሷም ስታየኝ፣ "ድንግጥ" ብላ እየቆጠረችው የነበረው ብር ቁጥሩ ተምታታባት። ደግሞ ከፋቱ ልክ 666 ብር ላይ ስትደርስ ነበር ቁጥሩ የጠፋባት። "ይሄ የሰይጣን ልጅ አለበት" ብላ አሰበች። ለነገሩ ጨዋታውን ሊታሳምረው ፈልጋ ይሆናል እንጂ 666 ላይ ደርሳ ከጠፋት 667 ብላ መቀጠል ነበር። ሰው መቼስ ሰይጣን አሳሳተኝ ለማለት መጠጋጊያው ብዙቱ። ታዲያ አልፎ አልፎ ሳበሳጫት፣ "ድርስ 666 ላይ አስቁመኸኝ ምን ጤና ሊኖርህ" ትለኛለች። አንዱ ስድስት እኔ፣ አንዲም ስድስት እርሷ፣ መሀላችን ያለችው ስድስት ፍቅር ትመስለኛለች። እኔ የምለው ለሰይጣን ቁጥር ሲሰጠው ለፍቅር ቁጥር አለመሰጠቱ አይገርምም? ይመስለኛል ፍቅር ቁጥር የሌለው ስለማይደመር፣ ስለማይቀነስ ፍቅር ራሱ ውጤት ስለሆነ ሳይሆን አይቀርም።

ሙና ባንክ ቤት ስትሠራ ሰዎችን በሚያስገቡት አልያም በሚያወጡት ብር እንጂ በሌላ መነፅር ተመልክታቸው ኢታወቅም ነበር። ለእኔ ግን መለይከያቹ ምን ሹክ እንዳሏት እንጃ ቀልቧ ወደደኝ።

"ስምህ ?"

"አብርሃም"

"የምትልከው ለማን ነው ?"

"ለእናቴ" ፈገግ ብላ አየችኝ። ዓይኗ ውስጥ ወዳጅነት ይንበለበላል።

"የእናትህ ስም?"

"አሰለፈች በዙፋኑ ከልካይ ጃና ..."

"ኧ...ረ በቃ!" ብላ በሳቅ ፍርስስስስ (ሳቅ ትመስላለች ስትስቅ)

"ስልክህ?"

"ስልኪ ኖኪያ ነች" ከትከት ብላ ሳቀችልኝና በወዳጅ ድምፅ "አድርቅ ነገር" ብላኝ ሳቋን ቀጠለች። እውነቱን ለመናገር የተናገርኳት ቀልድ ከጓደኛዬ የሰማኋት ያረጀች ያፈጀች ቀልድ ነበረች። ግን ሙና ካሰብኩት በላይ ሳቀችልኝ። ሴቶች ቀልባቸው ከወደዳችሁ ስታስነጥሱ ሁሉ ፍርፍር ብለው እንባቸው እስኪፈስ ይስቁላችኋል፤ ሴቶች ለቀልዱ ሳይሆን ለቀላጁ ማንነት የሚመፀውቱት ሳቅ የሆነ የነፍሳቸው ኪስ ውስጥ ሳይኖር አይቀርም !! ከጠሏችሁ ደግሞ በጭንቅላታችሁ ቆማችሁ እንደ ኳስ ብትነጥሩ የተቋጠረ ፊታቸው አይፈታም። ጥርቅም ! እንደተረገመ ጥቁር ሰማይ።

ለሙና ስልክ ቁጥሬን ሰጠኋት። እና እንዲህ አልኳት፤ "ያንቺስ?"

አሁን የራሴ ቀልድ ለእኔም አስቆኛል። ሙና በኋላ...ቆይቶ...ከተግባባን በኋላ፤ "ደፋር እኮ ነህ ... ባንክ ቤት ሄደህ ስልክህን ስትጠየቅ 'ያንቺስ' የምትል" ትለኛለች። ስልኳን ሳታንገራግር ነበር የሰጠችኝ፡ ከሳምንት በኋላ ተመልሼ እዛቸው ባንክ ሄድኩ (ዐሐይ ልምቅ...) ሙና ገና ስታየኝ፤ "ለማሚ ነው?" አለችኝ በፈገግታ። ስትፈግግ ዓይኖቿ አነስ ይሉና ከንፈሯ ከፈት ይላል። ከንፈሯ ቀይ አይደለም፡ ጥቁርም አይደለም፡ ምንም አይደለም። የሆነ የብርጭቆ ጠርዝ ነው የሚመስለው። በከቡ ከፈት ብሎ ጥርሶቿ ብቅ ሲሉ ብርጭቆ ውስጥ የተሞላ በረዶ ያስታውሳል። ስትስቅ ጥርሷ ቀን ይወጣለታል። ነጭ ብርሃን ከጥርሷ፣ ጥቁር ብርሃን ከፀጉሯና ከዓይኗ ብሌን ይ ነ ሳ ና ልቤ ላይ ይቀላቀላል። ነጭ አባይና ጥቁር አባይ የት ላይ ይቀላቀላል ቢባል ሚስኪን ልቢ ላይ።

"ለማሚ ነው?" ስትለኝ ስላፈርኩ "አዎ" አልኳት። እውነቱን ለመናገር የሄድኩት አግሬን መቆጣጠር አቅቶኝ ነበር፡ በደመ ነፍስ። ያለችኝን እራግፌ ለእናቴ ላክኩ። ስወጣ ግን እየተነጫነጭኩ ነበር። ምናለ ሙናን ሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ባገኛት ኖሮ? ቢያንስ ማስቲካ እየገዛሁ በየቀኑ አያት ነበር። ባንክ ቤት በምን ሰበብ ይኬዳል? አንድ የእኔ ቢጤ ኢትዮጵያዊ በየቀኑ ባንክ ቤት የመሄድ እድል የሚኖረው ባንክ ቤት ከተቀጠረ ብቻ ነው። "ለምን ቁጠባ አልጀምርም?" ስል አሰብኩ። በየቀኑ የታክሲ መልስ ሳንቲሞቼን ይዤ ጎራ ማለት ነው...። ግን ደግሞ ሙና ሳንቲም ይዤ ስመላለስ ሥራዬ ደጅ ሰላም ተቀምጦ መመፀወት ቢመስላትስ ? ኤዲያ !

ኅብዙ ሀብታሞች ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ሀብታቸው የተቀመጠበትን ባንክ ቤት በልባቸው ይሳለሙታል" ሲባል ከንቱ ሐሜት ይመስለኝ ነበር። ይሄው በራሴ ደረሰና አረፈው። እዚህ ባንክ ቤት ውስጥ የማይመነዘር ተቆጥሮ የማያልቅ ሀብት ያለኝ ሰው ነኝ። ሰብዓዊ ሀብት። የወደድኳት ልጅ። ተመልከቱት የእኔን ስዊዝ ባንክ፤ በአደራ ከናስተመጠልኝ ፀሐይ ! ልቤ ጣት ላይ ፍቅሬን ቱ ቱ ብዬ ረብጣ ረብጣውን ስቆጥረው ነው የምውለው። ዓይኗ ረብጣ፤ ጥርሷ ረብጣ፤ ድምጽዋ ረብጣ ... ድምፅ ብል ምን ትዝ አለኝ? የሙና ድምፅ የሴት ድምፅ አይደለም፤ የወንድም አይደለም፤ መሀል ላይ የቆመ ነው። መልክና ባሕሪ ብቻ ሳይሆን ድምፅም ከእናትና አባቷ እኩል የወሰደች ይመስለኛል። ታዲያ ደምጽዋ የሆነ ጉሮሮዋ ላይ ያዝ የሚያደርገው ነገር አለ፤ ያንን እኮ ነው የምወደው - ግርማ ሞገስ ያለው ድምፅ።

## ክፍል ሁለት

ቅርርቡ የነፍስ ሆኖ ነው መሰል ብዙ ውጣ ውረድ ሳይጋረጥብን ከሙና ጋር ሻይ ቡና ለመባባል ቢቃን። ከዛማ ማን ያቁመን፤ ከሙና ጋር አንድ ድፍን ዓመት አብሮ ባለ ፍቅር ቆየን። እንደው በመተቃቀፍ፤ እንደው በመገባበዝ፣ እንደው በመተያየት፣ እንደው በመሳሳም እና በመደዋወል። አንድ ቀን ታዲያ፡

"ሙናዬ" አልኳት።

"ወይዬ" አለችኝ በዛ በሚነዝረኝ ድምጽ።

ዝም ብዬ አየኋት - ገባት !! እናም እንዲህ አለችኝ፤

"አይሆንም፤ ስንጋባ ብቻ !!" ቅር አለኝ። ቢሆንም ግን እንደዛው በፍቅር ማበዳችንን ቀጠልን። እንደውም የሆነ ጊዜ አንዱን ደንበኛ አቁማ ከእኔ ጋር በስልክ ስታወራ ክስ ቀርቦባት የደመወዟን አስር እንደውም የሆነ ጊዜ አንዱን ደንበኛ አቁማ ከእኔ ጋር በስልክ ስታወራ ክስ ቀርቦባት የደመወዟን አስር ፐርሰንት ተቀጣች። ኃላፊዋ ባለጌ ነው፤ ምሳሌው ሁሉ አያምርም። ምን አላት ? (ኧረ ያሳፍራል...)

"ስሚ ሙና፣ አንድ የተላከለትን ብር ሊያወጣ ወደ ባንክ የመጣ ኢትዮጵያዊን ለግማሽ ደቂቃ ከማቆም መኝታ ቤት ምንትሱን አቁሞ የሚጠብቅ ፍቅረኛን ሙሉ ቀን ማስጠበቅ ይሻላል" ሙና ቤተፍረት ቀይ ፊቷ ቀላ። እሁን እስቲ ከመቆም ጋር የሚያያዝ ስንት ምሳሌ እያለ ሙና ፊት ይሄን ብልግና መናገር ምን ያስፈልጋል ?!

እኔም ከቅጣት አላመለጥኩም። ሥራዬን ትቼ እሷ ጋር ዘና ብዬ በመዋሌ አለቃዬ አምስት ፐርሰንት ቀጣኝ (ባንኮች ከፍ አድርገው የሚቀጡት የብር ጥቅም ስለሚገባቸው መሰሎኝ ነበር)። ባንድ ወሬ አስር ፐርሰንት ለቀጣ ብዬ ከሥራ እየጠፋሁ ከሙና ጋር (ለሙሉ ከሰዓት አትሰራም) ስውል አለቃ ምንም ብር ሳይቀጣኝ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የሚል ደብዳቤ ሰጠኝ። በእርግጥ አለቃዬ ራሱ ከድርጅቱ ባለቤት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ሰው ነበር። "ተያይዘን እንውጣታለን" ብዬ በሆዴ ፎከርኩ። ቀድሞኝ ተባረረ። የቅጣት ደብዳቤዬን ኪሱ ውስጥ አስቀምጠት ነው መሰል ከዛ በኋላ የግል ማህደሬም ላይም ይሁን ሌላ ቦታ አልተገኘም። ይሄ ሲደስት ሰልሳ ሲደሰት የሆነ ፍቅ ሰውሮትም እንደሆነ እንጃ...

ከስድስት ወራቶች በኋላ ሙናን እንደገና ትኩ ብዬ አየኋት !!

"ኪጋብቻ በፊት አታስበው" አለችኝ ቆጣ ብላ። ግን በቁጣዋ መሃል የሆነች ትንሽ ሠላላት ውልብ ስትል ያየሁ መሰለኝ። ጨለማ ቤት ውስጥ ትንሽ ብርሃን እንደምታሳልፍ ሰንጥቅ ዓይነት ቀጭን የይሁንታ ስርጥ። ቢሆንም በእንቢታዋ ተበሳጭቼ አስር ቀን ዘጋኋት። አበደች ! ስልክ ብትደውል፣ ቤት ብትመጣ በቃ ዘጋኋት። ከአስረኛው ቀን በኋላ መደወል አቆመች፤ ከቤትም ቀረች። ስትቀር እኔ ሄድኩ። ዘጋችኝ !! የምትሰራበት ሄጄ ስቆም ኮስተር አለች፣

"አረ ደንበኛ ከቡር ነው አትገላምጪኝ..." አልኳት። ሳቋ ፈነዳ፣ ታረቅን። መልሰን በፍቅር ማበድ ሆነ። እንኳንም ተጣላን ! ፍቅራችን ጠፍታ ከርማ እንደመጣች ውኃ ኃይሏ ጨምሮ ተንዠቀዠቀች (ፍቅረኞች ሆይ አልፎ አልፎ ተጣሉ... ደመ መራር ሆናችሁ በዛው ተለያይታችሁ እንዳትቀሩ ጠንቀቅ ብላችሁ...)

በመጨረሻ ሙናን እንዲህ አልኳት ... (ምን እንዳልኳት እኔ'ጃ) ግን ለድፍን አራት ሰዓታት አውርቼ አሳመንኳት!

"ግን ወደ አጉል ነገር ውስጥ ከገባን በኋላ ብትተወኝስ" አለች ዓይኗ ስልምልም ብሎ። ሰውነቷ መሉ ሰሙሉ ተሸንፎ አፏ ብቻ ነበር የሞት ሽረት ትግል ላይ የነበረው። ሚስ...ኪን !

"የሁሉም ሴቶች ጥያቄ ነው"

"አትቀልድ"

ጓና ይሄ መያዣ ነው እንዴ ? ከተውኩሽ የአያቶቼ አጥንት አሸህ ሆኖ ይውጋኝ ሙናዬ ..." ብዬ ማልኩ። እነዚህ አያቶቻችን ስንቱን ይውጉ ? ድርቡሽን ወግተው፣ ጣሊያንን ወግተው፣ ሱማሌን ወግተው አሁን ደግሞ...

ጓሺ በቃ አትነዝንዘኝ" አለችኝ። አትነዝንዘኝ የምትለው ቃል "እሺ" የምትለዋን ሽንፈት የምትደግፍ ከዘራ መሆኗ ነው ! "እሺ የኔ ቆንጆ እናደርገዋለን፣ በደስታ፣ በፍቅር፣ ያውም በሙሉ ልቤ ... ወደፊት" ቢባል ምን አለበት ? መሆኑ ሳይቀር የምን በዘወርዋራው መናገር ነው ... ሃሃሃሃ ኡፍፍፍፍ ብዬ በደስታ ለቀቅ።

ጓንዴዴዴ ! አንትት አሁን ነው እንዴ ?" ብላ ሁለታችንም በሳ......ቅ። ያለነው እኮ የሆነ ካፌ ውስጥ ነበር። እና ቀን ተቆረጠ። እርብ ማታ እኔ ቤት ትመጣና ታድራለች፣ (በታድራለች ውስጥ ስንት ጉድ አለ) ቅዳሜ ትውላለች፣ (በትውላለች ውስጥ ቤቴ የጦርነት ቀጠና ሲመስል ታየኝ - ጦርነት ያለበት ገነት) ከዛ ታድራለች ... እሁድ ወደ ቤቷ። "እንዴት ነው የምለያት" ብዬ ካሁኑ ናፈቅኩ።

## ክፍል ሦስት

እርብ ማታ ቤቴን አበባ አስመስዬ ለራሴም ሌላ ሰው ቤት የሄድኩ እስኪመስለኝ አሳምሬ ጠበቅኳት .. እየተንቆራጠጥኩ። ኮቴ ሰማሁ፣ የሴት ጫማ ተረከዝ ቋ ቋ ቋ ሙና ናት፣ መጣች !! በሩ ተንኳኳ ... ኳኳኳኳኳኳ ኳኳኳኳኳ ኳኳኳኳኳ ... ማማቹ ኳኳታ ልቤ ሲመታ መሆን አለበት።

ሙና በሬ ላይ ቆማለች። በሩን ስከፍት ረዥም ቀይ ቀሚስ በባለ ረዥም ተረከዝ ጫማ ለብሳ በረዥም ቁመቷ ከላይ ወደታች የሚፈስ ፏፏቴ መስላ (እኔ'ኛ ለምን እንደሆነ እንደዛ መሰለችኝ። አንዳንዴ የሆነ ቅዕበት አለ እዛው ፊታችን ቆሞ ትዝታ የሚመስለን) እየቸኝ፣ ተያየን፣ ገባች። እንደወትሮው አልተሳሳምንም፣ አልተቃለድንም፣ አልተሳሳቅንም ... ፈርተናል። በጣም ፈርተናል። ተፈራርተናል። በሩን ደገፌ እንድታልፍ ወደ ጎን ዘወር ስልላት እንደቆምኩ ታከካኝ አለፈች። ለስላሳ ጠረኗ አፍንጫዬን አወደው። ጫማዋን እንደቆመች ስታወልቅ ገደገድ አለች። ሁለቱንም ጫማዎቿን አውልቃ በባዶ እግሯ ስትቆም የቀሚሷ ጫፍ ምንጣፉን ነካው።

ቀስ ብላ ገባች። ተከትሏት ወላፈን ገባ። እንደ ኤርታሌ ዓይነት ነገር ቤቴ ውስጥ ተፈጠረ። እቃዎቼ

ሁሉ እየቀለጡ የፈሰሱ መሰለኝ። ሙና ዝም ብላ ተቀመጠች። ሄጄ አጠገቧ ስቀመጥ ሰውነቷ ከምላ
እለ ... ፈርተናል ! "ፈራን፣ ፍቅር ፈራን" አለ ባለቅኔው።

"እሺ እንዴት ነበር ውሎ" አልኳት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ። ድምፄ ለዛ ቢስ ሆነብኝ። እጇን እጄ ላይ ጣል አደረግኩት። ዝም አለች። ሌላኛውን እጄን ትከሻዋ ላይ ... ዝም ! ሦስተኛውን እጄን የሆነ ነገር ላይ፣ አራተኛውን እጄን ፀጉሯ ላይ፣ አምስተኛውን እጄን ... እጅ በእጅ ሆንኩ። ሁሉንም ነገሯን ባዶ መንካት ስለፈለግኩ ፈጣሪ ይውጣልህ ብሎ ብዙ እጅ ያበቀለብኝ እስከሚመስለኝ። እና ተነሳችና ሳ አደረግኳት፣ ተከተለችኝ። ድክም ያላት ትመስል ነበር። በሕይወት ውስጥ አለ የሆነ ጊዜ፣ አዕምሮአችን ትተን በወደድነው ሰው አዕምሮ የምንመራበት። ሙና ዝም ብላ እንደማደርጋት ሆነች።

ወደ መኝታ ቤታችን...

ምን እንደሆነ ባይገባኝም አንድ የጎደለ ነገር እንዳለ ይሰማኛል። ማለት እንዲህ አልነበረም መጀመሪያ ይሰማኝ የነበረው። ፍላጎቴን የሆነ የማልገልፀው ዓይነት ቅዝቃዜ ወርሮታል። ተሳሳምን ... ሙና በስሜት አበደች። ደነገጥኩ። እንዲህ እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ ትመጣለች ብዬ በምን አባቴ ጠርጥሬ፤ ልብሷን ከሰውነቷ ላይ በትብብር እየገፈፍን ጣልነው፣ የእኔንም ልብስ ሽቅብና ቁልቁል ገፍፎ እንደፈጠረን እርቃናችንን ቆምን። በየት በኩል እንደገባን እንጃ አንሶላው ወስጥ ተገኘን።

###

የሆነ ነገር ጎድሏል። አንድ የሆነ ነገር ጎድሏል። ሙና እየቃተተች፣ እንደምትወደኝ እየነገረችኝ፣ ሰውነቷ እሳት ሆኖ እኔ ምን እንደነካኝ እኔ'ጃ በሚያስደነግጥ ፍጥነት ቅዝቅዝ አልኩ። ቅዝቅዝ ! የሞትኩ መሰለኝ ነበር። ሙና ለብቻዋ የሆነ ነገር የምትሰራ መስሎ ተሰማኝ። ቢቃ ሲታዘቢኝት የቀበሮ ይመስል የምታደርገውን ግራ በመጋባት ማየት ሆነ ስራዬ። እንዴት የሚያስቅቅ ነገር ነው ? ምንድነ ነው የሆንኩት ? ሙናን በቀስታ ገፋ አደረግኳት። ከሆነ ከሰጠምኩበት ውኃ ውስጥ አውጥታ ዓየር በአፏ የምትሰጠኝ እንጂ ምንም ምንም ስሜት የሚሰጥ ጉዳይ ሆኖ አልታየህ አለኝ።

"ምን ሆንክ?" አለችኝ።

"ምን ሆንኩ ?" መልሼ ጠየቅኳት። ሳላስበው ኮስተር ብዬ ነበር። በቀስታ እጇን ልካ በለስላሳ መዳፏ ጉንጬን ዳሰሰችኝ። ከአንገቴ ዘንበል በማለት እጇን ሸሸሁት። ግራ በመጋባት ስትመለከተኝ ቆየች ቀዝቀዝ ብላ በጀርባዋ ከጎኔ ተኛች። ከዛም እጅግ በጣም በሚያስፈራ፣ ከሩቅ የሚመጣ በሚመስል

ድምፅ፡ "ደስ አላልኩህም ?" አለችኝ። ዝም ! አንድ የገባኝ ነገር ሙናን መጉዳት እንደሌለብኝ ነበር። ግን በዛ ቅፅበት እንኳን እሷን ሳፅናናት ራሴም የሆነው ነገር ግራ ገብቶኛል። እንደምንም ብዬ፡ "ሙና ለ...ሪ የሆነ ሐሳብ ውስጤ ገብቶ ነው ... አፈቅርሻለሁ፡ ልጎዳሽ አልፈልግም። ፈራሁ ... ይህ ነገር የመጀመሪያ ነው ... የሆነ ነገር እንዳትሆኝብኝ ፈራሁ..." ቀበጣጠርኩ። ሙና ቀስ ብላ ወደኔ ዞረችና፡

"እኔም ነቅቼብኃለሁ" ብላ በሳቅ ፈረሰች። ሳቋ እብደት ይመስል ነበር። ከፍርሃት እና ካሰበችው መገፋት የመትረፍ ደስታ የተሸከመ ሳቅ። ጠጋ አለችና አቀፈችኝ። ጡቶቿ ለብቻቸው አቀፉኝ፤ ከንፈሯ ከንፈሬ ላይ ነው። ዓይኖቼን ከድኜ፡ "ሙና ልብሶቿን አውልቃ ራቁቷን እኔ ቤት እኔ አልጋ ላይ ነን" አልኩት ራሴን፤ ምን ዋጋ አለው - ቅዝቅዝ ! ለምን ? ... እንኳባቴ !! ገጣሚ ወዳጄ፡ "የሚወዱትን ሰው ቀብሮ እንደማጠበቅ የሚያሳቅቅ ነገር የለም..." የሚል ግጥሙ ትዝ አለኝ። እንዲህ የቀጠሩት ወንድነት ከራስ የጠሮ ሲቀር ቢያይ ምን ብሎ ይገጥም ይሆን ? ከሙና ጋር አብረን አደርን፤ ምንም ነገር የለም። ጠዋት ላይ ሙናን እንዲህ አልኳት፡

"ለምን ኪጋብቻ በኋላ አናደርገውም ?"

"አሁ ሃኒ እንዳንተ ስሜቱን የሚቆጣጠር ወንድ በማግኘቴ እድለኛ ነኝ ! መቼም ቢሆን በፈለግኩበት ሰዓት ያንተ ነኝ" አይገርምም? ሙና እስካሁንም ነገሩን ማድረግ የማልችል ልፍስፍስ መሆኔ አልገባትም። ጭራሽ ከዓለም ወንዶች ሁሉ አንደኛ ታጋሽ አድርጋኝ ቁጭ አለች ! ግዴላችሁም ሴቶች አዕምሮ ውስጥ የተጫነው መዝገበ ቃላትና የወንዶቹ የሆነ ልዩነት አለው።

ከሙና ጋር ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ቤት እንውልበታለን ባልናት ቅዳሜ ከተማውን ስናካልል ዋልን። የምትወዳቸውን ኬክ ቤቶች ስንገበኝ። ሙና ከሚገባው በላይ ለእኔ ያላት ፍቅር ጨምሮ ነበር። (ታጋሽ ወንድ አግኝታ ሞታ ! ጠንጋራ መገምገሚያ ፍቅርን ያጠናግረዋል) እንደው መንገድ ላይ ሁሉ ብትስመኝ ደስታዋ። ጮክ ብላ የታጋሽነቴን፤ ራስ የመግዛት ብቃቴን ልክ ለሕዝቡ ብታውጅ ደስታዋ።

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ቅዳሜና እሁድ አዳሯ እኔ ቤት ሆነ - ወይ ንከች ! ልቤና ሰውነቴ ተለያዩ። ልቤ ሙናን በሰትኳ ይመኛታል፤ ሳላቋርጥ ሚሊዮን ጊዜ እስማታለሁ፤ ትኩሳቱን ከመጨመር ውጭ ምን ዋጋ አለው ! ቢቆይ መሳሳሙም እያስፈራኝ መጣ። የውበች ውብ የሆነች፤ ስንቱ የሚቋምጥላት ልጅ ቤቴ አልጋዬ ላይ፣ እንሶላዬ ውስጥ፤ ደረቴ ላይ አስቀምጬ ከመቀዝቀዝ በላይ ምን መርገምት አለ። ...ብሽቅ ! አልኩት ራሴን። የባሰው ነገር ሳይቆይ ተከሰተ። ሙና ከቀን ወደ ቀን የእኔን ጥያቄ የራሷ አደረገችው !

ትክክክክክክ ብላ ስታየኝ ... እንዲህ አላታለሁ፣

"ከጋብቻ በኋላ"

## ክፍል አራት

በዚህ የጭንቅ ሰዓት ላይ እያለሁ ሙናን የምትሰራበት ባንክ ወደ መቀሌ ቅርንጫፍ ቀየራት። ይሄማ የእግዜር እጅ አለበት። ደስ አለኝ። ስሸኛት አለቀሰች። ለአዲስ አበባ ሳይሆን ከእኔ በመለየቷ፤ እና ደግሞ ከብረት የጠነከረ መሻትን ድል ለመታ በ"እሳት ለተፈተነ ትዕግስቷ" (እሷ እንደዛ ነው የሚመስላት)። ለእኔ ግን ጉዳዩን ለራሴ እንኳን ማመን ባልፈልግም ገብቶኛል። ስንፈተ ወሲብ !! ያውም እንደ ሚረ ለራሴም ድንገት ዱብ ብሎ የተገለጠ። ለሙና ምን ብዬ ልንገራት ? ልጅቱ ከቀን ወደ ቀን ጉዳያ እንድንፈፅመው አፍ አውጥታ በፅኑ መሻት ትጠይቀኛለች። እንደውም ከሌላ ሴት ጋር አንዳች ጉዳይ የጀመርኩና የገፋኋት እየመሰላት መጠራጠር ጀምራ ነበር - *ምነው ባደረገው...*

መቀሌ እየሰራች ቢያንስ በየወሩ እርሷ ወይም እኔ እየመጣችና እየሄድኩኝ እስደሳች ጊዜ እናሳልፍ ነበር። ግን ምን ያደርጋል ይሄ የእኔ ነገር ጥላውን አጠላብን።

"ከዚህ በላይ መታገስ አልችልም። ችግር ካለብኝ ንገረኝ፤ ወይም ካስጠላሁህ ቢቃ አሳውቀኝ ፐ.....ሲበ" አለችኝ አንድ ቀን የአይጥና ድመት ድብብቆሻችን አሰልችቷት። እናም ማስጠንቀቂያ ጨመረችበት፣ "ለሚቀጥለው ስመጣ ካላደረግን የእኔና ያንተ ጉዳይ አበቃ !" ሙና ታደርገዋለች። ጭካኔዋ በፍቅሯ ልክ ነው፤ ቀልድ አታውቅም። ተንቀዠቀዠ አነሳሴ በምን ላስቁማት ? ቆይ ሰው ንብረቱ እንደሚሠራ እና እንደማይሠራ ሳያረጋግጥ እንዲህ ዓይነት እዳ ውስጥ ይዘፈቃል ?! ቢጨንቀኝ ነው እንጂ እሰማ እንዴት ይረጋገጣል ? እንደ ደም ግፊት አይለካ ነገር።

ሳወጣና ሳወርድ አድሬ ለሃኒባል ላማከረው ወሰንኩ። ሃኒባል አብሮ አደግ ጓደኛዬ ነው፣ የልብ ጓደኛዬ። ከሙናም ጋር በደንብ ይተዋወቃሉ። እናም ላሳውቀው ወሰንኩ። ሃኒባል ቢያንስ ለምንም ነገር አይጨነቅም። መፍትሄም አያጣም። ከድሮውም ልጅ ሆነን እኮ ነው ... ቢታ ችግር በሃኒባል ፊት የቱንም ያህል ቢገዝፍ እንደ ዝንብ ነው በመፍትሄ ጭራ የሚያባርረው። ደወልኩለትና፣ ና ፊቱን ውሰድ... ሌላው እስቤ ተውኩት፤ "እፈልግሃለሁ" ብቻ አልኩት።

###

"ምን ጉድ ተፈጥሮ ነው እንዲህ እያግለበለብክ ያስመጣኸኝ ጃል ?" አለ ሃኒባል ያዘዘውን ቡና እያማሰለ።

"ባክህ ችግር ገጥሞኛል"

"ችግር የሚባል ነገር የለም ባክህ፤ የመፍትሄ እጥረት በለው" አለ (አላልኳችሁም ?)

"ኧ...እንዴት መሰለህ ከሙናጋ የሆነ ትንሽ ችግር ... ኧረ ምን ትንሽ ... ትልቅ ችግር ውስጥ ገብተናል" አልኩት።

ቡና ማማሰሉን አቆመና ኮስተር ብሎ፣ "የምን ችግር..." አለኝ።

"እኔ ለካ ... እንትን ... ማድረግ አልችልም - አሁን ነው ያወቅኩት"

"ምን ማድረግ ?"

ኤጭ ሥሙን ቁስ ይጥራውና እንዴት እንደቀፈፈኝ፣

"ግንኙነት ማድረግ አልችልም"

"የምን ግንኙነት ?"

"የምን ግንኙነት ትለኛለህ እንዴ ... ወሲብ ነዋ !" ስል አፈረጥኩት።

"ኧ...ንዴ ! እና እስከዛሬ ከሙና ጋር ስታድሩ ምን እየሰራችሁ ነበር የምታድሩት ?"

"በቃ ትኝት ነዋ አርፈን ... ማለቴ አርፌ"

"ትኝት ትኝት ... ለሽሽ ?"

"አዎ !"

"አንተስ እሺ ... ሙና እንዴት አስቻላት ?"

"ደብተራ ግዛውማ ቦሌ ምን የመሰለ ቢላ ቤት ገዝቶ ሄደ አናትዬ፤ ዛሬ ጆሮውን ቢቆርጡት የማይሰማ ኃብታም ሁኗል። ሰው ሁሉ በባዶ አግሩ ከገጠር እየመጣ እንዲህ ባለፀጋ ይሆናል፤ እኛ ነን የአርባ ቀን እድላችን ከአፈር አትነሱ ብሎን..." እያለ ብሶቱን ይዘረግፈው ገባ።

ተመለስን...

"እንዳንከራተትሽኝ አላህ ያንከራትሽ" አለ አሉ ሰውየው፤ ጨረቃን መግቢያዋን እያለሁ ብሎ ሲከተላት ከርሞ አልሆን ቢለው እኮ ነው። ስንመለስ ሃኒባል እንዲህ አለኝ፣ "አቡቹ አየህ የዚህን አገር ነገር፣ አንተ በቀን ስምንት ሰዓት ቆመህ በየወሩ የቤት ኪራይ መክፈል የማትችል ደመወዝ ትከፈላለህ አጅሬ እንትን አቁሞ ቪላ ይገዛል ያውም ቦሌ"

"ተናግረህ ሞተሃል፤ አንትን ከማቆም በላይ ለአንዲት አገር ምን ትልቅ ሥራ አለ" ብዬ ገላመጥኩት፡

"አብርሽ እንዲህማ አትናሜንጭ፤ ይቆማል አይዞህ"

###

ቦሌ የደብተራ ግዛውን ቤት (ቢተመንግሥት በሉት) ስናገኘው ሪፈራል ሆስፒታል እንጂ የአንድ ሰው ቤት አይመስልም። ሰራተኛ ትሁን ነርስ ያልገባኝን ሴት እየመራች ወደ ሰፊውና ሙሉውን ነጭ ቀለም ወደተቀባው ውብ ሳሎኑ ወሰደችን። ኧረ ጉዴ ! እኔ ጥምጣሙን አሳምሮ በጋቢው ላይ ካፖርት የደረበ የእግዜር ሰው አገኛለሁ ብዬ ... ሰውዬው ምቹ የሌዘር ሶፋው ላይ ተንጋልሎ የግድግዳውን ሩብ ያህል በያዘ ትልቅና ጠፍጣፋ ቴሌቪዥን ኳስ ጨዋታ ይመለከታል። የቴሌቪዥኑን ስፋትና የኳስ ሜዳውን በዛው ልክ መንጣለል ስመለከት ሰውዬውን ቤት ውስጥ ሳይሆን የሆነ መስክ ዳር ጋደም ብሎ ያገኘሁ መሰለኝ። ጎንና ጎኑ ላይ ኪስ ያለው የዘመነ የጨርቅ ቁምጣ ለብሷል፤ ነጭ ካልሲ አድርጓል፣ ከላይ ፈርጣማ ጡንቻውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ፓከ አጡት ለብሷል። ገብተን ቆመን ሁሉ ከቁም ነገር አልቆጠረንም። በስሜት ብቻውን ያወራል።

"አይ አርሴናል ... እንዲህ ተጨማልቀህ ትቀር ? እኛ ስንት ቦታ ትደርሳለህ ስንልህ ? ምነው ያኔ ደጋፊ ከምሆን በጽንሴ እናቴ ማህጸን በቀረሁ..." አለ እና የሌዘር ሶፋውን በብስጭት በቡጢ አቀመሰው። እኔና ሃኒባል ተገርመን አርስ በእርስ ተያየን።

ደንገት ወደኛ ዞር ብሎ፣

"ተቀመጡ" አለንና ወደ ቴሌቪዥኑ ተመለሰ። እነጋገሩ 'ተቀመጡ' ሳይሆን 'ውጡ' ያለን ነበር ሚመስለው፤ አመናጨቀን ቢባል ይቀላል።

ዘገሜት ኳሱን ሲመለከት ቆይቶ ድንገት ወደኛ ዞረና፣

"ወጣቶች ምን አግር ጣላችሁ ?" ሲል ፈፅሞ አክብሮት በሌለበት የሚያበሳጭ ሁኔታ ጠየቀን። አነጋገሩ ኳሱን ለመልከትበት ውጡሉኝ ይመስላል።

"እይ … እንትን ነበር…" አለ ሃኒባል ድንገት ስለተጠየቅን ተደናግጦ እየተሽቆጠቆጠ።

"ምን … ስንፈተ ወሲብ ነው ?"

"እዎ አዎ" አለ ሃኒባል እየተጣደፈ። እኔማ ሰውዬው አብግኖኝ እንደ ሐውልት ደርቄያለሁ። ጭራሽ እኮ ወደኛ አይመለከትም - ሰው ጤፉ…

"ታዲያ ምን አስፈራችሁ ? ባሁኑ ጊዜ ካ'ዲሳባ ወንድ አስራ አንድ ነጥብ ዘጠኙ ስንፈተ ወሲብ ችግር ያለበት ነው። ባገር የመጣ ነው፤ እይዟችሁ ! ከሆነስ ሆኖ የማንኛችሁ ቆ** ነው አልቆምም ያለው ?" ሲል ጠየቀ።

አሁንም ዞሮ አላየንም።

"ኛሱ ነው" አለ ሃኒባል ወደ እኔ እየጠቆመ። ከሰውዬው ድንገተኛ አጠያየቅና ከሃኒባል አመላለስ ድርቅና ተነስቼ የኔ አይደለም ብዬ ልከድ ነበር። ሁኔታው አሳቃቂ ነበር። የሰውዬው ድፍረትና ትዕቢት ያበሳጫል። ከዋናው ጉዳይ በላይ የሰውዬው ንቀት አበገነኝ።

"ታዲያ ምን ይዘጋዋል፤ ራሱ አይናገርም … ወይስ ምላሱም ሰነፈ ?" ይሄ የውሻ ልጅ ! ልናገረው አፌን ሳሞጠሙጥ ሃኒባል ገላመጠኝና ዝም አሰባለኝ። ሰውዬው ጋደም እንዳለ በርቀት መቆጣጠሪያው የቴሌቪዥኑን ድምፅ ለአመል ያህል ቀነስ አደረገና ከተንጋለለበት ተነስቶ ፊቱን ወደኔ አዞሮ ተቀመጠ። እንደ ከእግር እስከ ራሴ ፊቱን አጨፍግጎ ቃኘኝና፣

"እ… ተረምሳው መቼ ጀመረህ ?" አለኝ። (በቃ ምርመራ ተጀመረ ማለት ነው ?) ሰውዬውን በትኩረት ስመለከተው ለካስ ዓይኑ ልክ አይደለም፤ ትንሽ ሸውረር ያለ ነው። ታዲያ መጽሔት ላይ ከየት አባቱ የመጣውን ፎቶ ነው የለጠፈው ?

"መቼ እንደ ጀመረኝ አላወቅኩም ድንገት ከፍቅረኛዬ ጋር..."

"እ ... ድንገት ከፍቅረኛህ ጋር ዓለምህን ልትቀጭ ... ሱሪህን አውልቀህ ... ቡታንቲህን አውልቀህ ገድ ስትለው ... ባባቴም የለ ብሎ ድፍት፣ ቅዝቅዝ አለብህ ... እ? አዋራጅ እኮ ነው! አዋ ራ ጅ!! ስንቴ በዚህ ዓይነት አጉል ጊዜ በሴት ፊት መዋረዱ አሸማቅቆት ገመዱን ቋጥሮ ራሱን ሲጥ አድርጓል መሰለህ! እኔ እንኳን ሁለት ምን የመሳሰሉ ልጆች በዚሁ ጠንቅ ታንቀው የሞቱ አውቃለሁ ... አንዱ እንኳን ሚስት ጠጥቶ ነው ... ያው ነው! ቀላል ነገር እንዳይመስላችሁ፣ ሴቶቹ ደሞ ይችን ወሬ ካገኙ እየዞሩ ነገር ነው የሚያወሩት..." አለ ከአፌ ላይ ነጥቆ። ይሄ ሰውዬ እንዴት ነው የሚቀባጥረው በእግዚአብሔር፡ በአንድ ጊዜ መንፈሴንም አኮላሸው እኮ።

"እና...እንዴት ነው ትንሽም አይላወስ፣ ወይስ ጀማምሮ መሃል ላይ ወዘቤን ነው የሚለው?" ቢል ጠየቀኝ።

"ምኑ?" ብዬ ጠየቅኩት።

"ቆ**ህ ነዋ" ብሎ ቃሉን እንደተፈጠረ አፈረጠው! ሰድ!

"አይ ምንም የለም" አልኩ እየተሸማቀቅኩ።

"ከዚህ በፊት ሌላ ሴት ጋር እንዴት ነው ... አልጀማመርክም?"

"ሌላ ሴት ጋር ሄጄ አላውቅም"

"ተው ተ...ው! ለጋኪምና ለንቡጋ አባት ሚስጥር አይደበቅም ... ሃሃሃ እስቲ አንተኛው ወደ ውጭ ውጣ" አለና ሃኒባልን አዘዘው። ሃኒባል ሾከክ ብሎ ወጣ (ይሄ ደግሞ ምን ያሽቆጠቁጠዋል...)

ሃኒባል እስኪወጣ ጠበቀና፣ "እ ... ጓደኛህ እንዴት ናት?"

"እንዴት ናት ማለት?" አልኩት ጥያቄው ግራ አጋብቶኝ።

"እንደው መልኳ፣ ጸባይዋ ... ማለቴ ነው። አንዳንዷ ሴት እኮ ትዘጋለች። እውነቱን ነው ዛላዋ እምርህ! መልኳ ስቦህ ስትቀርባት አንዳንዷ ሴት እንኳን መተቃቀፍ ምግብ ትዘጋለች"

"እ ... ፀባይማ እናት ናት...መልኳም ቢሆን..." አልኩና ዋሌቴን አውጥቼ ፎቶዋን ሰጠሁት። መጽሃፍን

ፊስነ ጎይኑ ላይ ሰካና ፎቶውን በትኩረት ወደ ዓይኑ ቀረብ ራቅ እያደረገ ተመለከቶ፡

"ጃረግ … ጃረግ … ጃረግ ወንድሜን ! እውነትም ተይዘሃል። ይችን የመሰለች ልጅማ ካመለጠችህማ ነውም አትሆን…" ብሎ አፉን ጠረገ። ዝም ብዬ አየዋለሁ። የሙናን ፎቶ እስኪበቃው ተመለከተውና ኦሮውን ገርገጭ አድርጎ ምራቁን ከዋጠ በኋላ…

"እንደው ትንሽም አልሞከራችሁ ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ኧረ ምንም የለም" ፎቶዋን እንደገና ተመለከተው።

"ምናምን አዘራብህ እንዳይሆን" አለኝ።

"ምንድነው ምናምን ?"

"ብዙ ሰው አይታመንም። አንዳንድ ሴቶች ሌላ ሴት ጋር እንዳትሄድባቸው ሌላ ሌላ ነገር እንዳታደርግ ያሰሩብሃና፣ ሲቆይ ለነሱም ይተርፋል ጠንቁ። እንደው አቋም ብቻ ሆንክ እንጂ አንተም ብትሆን ሸበላ ነህ። እንጂ እንዳትቀማት አዘራብህ ቢሆን ማን ያውቃል"

"ኧረ እኳ…" ሰለቸኝ ሰውዬው። እውነቱን ለመናገር ራሱን ቁልል ያደረገ ዘላባጅ ነገር ነው። ለስጋዬ ፈውስ ብመጣ ጭራሽ ነፍሴንም ያቆስሊታል እንዴ ?!

"ቀላል ነው አይዞህ !! የሰው እጅም ሆነ ሌላ መፍትሄው በእጃችን ነው" ሲለኝ ብስጭቱ ሁሉ ብን ብሎ በፍቶ ጀርዬ ቆመ። አውርቶም ተሳድቦም ብቻ ያቁምልኝ፤ ሌላው ትርፍ ነው።

"እውነትዎትን ነው ቀላል ነው ?" አልኩት በጉጉት።

"እዎ ! ይች ምናላት ?" አለ ልክ ወደ ብልቱ አቅጣጫ በእጁ እየጠቆመና በማጣጣል ዓይነት ከንፈሩን ወደ ታች ጣል እያደረገ። "እንኳን ይችን ስንቱን አቁመነዋል ! ይ…ሄ ወዲህ ስትመጡ መታጠፊያው ጋ ያለውን ቀልቀሎ ሆቴል ታቀው የለም?"

"እዎ አውቀዋለሁ" አልኩ በጉጉት። ደግሞ አንድ የሆቴል ሕንፃ ከእኔ ጉዳይ ጋር ምን አገናኘው ብዬ።

"ይሄውልህ የሱ ሕንፃ ባለቤት እንዲህ አንዳንተ ፀሐይ የመሰለች ሚስት አለችው። መቼስ ብር አለን ባለው ጉዳቸውን ሳይፈትሹ ነው ትዳር ውስጥ የሚዘፈቁት። አቅፎ ቢለው ቢሰራው ወንድነት ከየት

ይምጣ ? ጭራሽ አኛሪት ውጭ ውጭ ታይ ጀመረልሃ ... ይሄን ሲሰማ ሲያብድ ሆነ። ቢ...ኋላ እኔ ጋ በሰው በሰው መጣና እንደሚሆን አድርጌ ላኩት። ይሄው ዛሬ እንኳን ለሚስቱ ለውሽሞቿም ተርፏል። ሚስቱ እንዴት እንደምትንሰፈሰፍለት አገር የሚያውቀው ነው" የተቸገረ ሰው ምኝ ነው፤ ዝም ብዬ ሰውዬውን አሰማዋለሁ። አወራሩ ድራማ የሚሰራ ነው የሚመስለው።

"አንተ እሱን ትላለህ ! ይሄ በየቀኑ ቴሌቪዥን ላይ 'አንትን' ፕሮግራም ላይ የሚቀርበው አውግቶ ራሱ ... በቴሌቪዥን ሲናገር ድምጹ ሲያስገመግም አንበሳ ገዳይ አይመስልም ነበር ? ሃሃሃሃ ማታ ማታ ሚስቱ እያንከላፈተችው ስንት ዓመት አልቀዐል መሰለህ። እንደውም ይሄ ትልቁ ልጁ የሱ አይደለም እየተባለ ይታማልኮ። እሃ ምን ታርጋ ታዲያ ያችን የመሰለች ቆንጆ በአምሮት ትሙት አንጂ ! የሱ እንኳን ሽንፈተ ወሲብ ነው"

"ሽንፈተ ወሲብ ምንድን ነው ?" አልኩ መጽሔቱ ላይ አይቼው ያልገባኝ ነገር ትዝ ብሎኝ።

"እሱማ እንግዲህ ... አገር አማን ብለህ ልትተቃቀፍ ገና ሴቷ ሰላም ብላ እጅህን ስትጨብጥህ አንተ ጥንቅቅ ብለህ በቆምህ ጨራርሰሃል !! ቢበዛ እስከመሳሰም ብትዘልቅ ነው። አንዳንዱማ የተምናደ ዳሌ፤ ሎሚ የመሰለ ተረከዝ ሲመለከትም በቁሙ ሱሪው ላይ ይለቀዋል። ባንድ ፊቱ እንዲህ አንዳንተ መዳፈን ይሻላል እንጂ፤ ሴቶች ሽንፈተ ወሲብ ያለበት ወንድ ላይናቸው ነው የሚቀፉቸው ... ላይናቸው ! ወይ አይተወው ወይ አያደርገው ... አንዱስ ነካክቶ የሰው አምሮት መቀስቀስና ሥም ነው ትርፉ ክፉ ችግር ነው። ያንተ በስንት ጣዕሙ፤ ያንተማ ምናላት ቢሆንልህ አሰየው ባይሆንም ሴት ቀርቶና አትሞት"

"ላይሳካ ይችላል እንጂ ?" ስል የነበረችኝ ተስፋ ኩስምን ብላ ጠየቅኩ።

"ምሳሌውን ማለቴ ነው እንጂ ... አንተማ ታሰታውቃለህ፤ የአገር ሴት አይመልስህም ቀ ! ማዘሙ ምናለ በለኝ። ከዚህ ቤት እግርህ ሳይወጣ ነው እንደ ሚዳቋ ቀንድ ቀ...ጥ ብሎ የሚቆመው። ወሎላት ሰዘን ሚስኪን" አለና የሙናን ፎቶ አንደገና ወደ ዓይኑ አስጠግቶ ተመለከተው። ተስፋዬ መለሰ አለልኝ

"እንግዲህ ሁለት ዓይነት አሰራር አለ፤ አንዱ ... ይሄ እንኳን ላንተ አይሆንም" አለ መልሶ።

"ለምንድነው ለኔ የማይሆነው ?"

"ውድ ነዋ ! ውድ ነው ... ዋጋውን ብትሰማ ከወንድነትህ በፊት ትንፋሽህ ነው እዚሁ የሚቆመው

ዶሻ"

ግዴለም ይንገሩኝ ?!"

ኋይ ይቅርብህ። አሁን ጓጉተህ ነው፤ በኋላ ፍቅሩም አምሮቱም ሲወጣልህ የከፈልከው ገንዘብ ትዝ ገህ ቁጥር እንኳን ለንትንህ ነፍስህም ጭምር ነው የሚሸማቀቀው። እንደውስ ተመልሰህ መጥተህ ብሬን መልስልኝ ባትል ነው ? ቅቅቅቅ" ሳቁ ይቀፋል። የሆነ ነገር ሲፈጠጥ የሚወጣው ዓይነት ድምጽ ነው።

ኢ..ያ ሁለተኛውስ ?"

ባይሆን እሷ ትሻላለች ! አንድ ሐያ ሺ ታስከፍልሃለች እንጂ ፍቱን ናት"

ን.. ሐያ ሺ ...?"

ኣዎ ! ምነው ?"

ኣልተወደደም ?"

ኣኮ ! የመጀመሪያውን ብትሰማ ያልኩህ ለዚህ እኮ ነው ! ቢሆንም ዓይንን ባይን ለማየት ሐያ ሺ ምናለት ? እንኳን ለማቆም የቆመበት ልከስከስ ሁሉ እዚህ እኛ አካባቢ ላሉ ቤተኛ አዳሪዎች ሐያ ሺ ይከፍል የለም እንዴ ?! ያውም ላንድ ሌሊት። መቼስ ሐያ ሺ ብር ሳይኖርህ ይችን የመሰለች ቆንጆ ላይ ለትንጠሳጠልም፣ እንግዲህ ምርጫው ያንተ ነው።" ብሎ ፎቶውን መለሰልኝና ወደ ቴሌቪዥኑ ዞሮ ፒርቶት መቆጣጠሪያው ድምጹን ከፍ አደረገው።

ሙናን ፎቶ ሳየው እንባዬ መጣ። ሐያ ሺ ብር ? በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ሐያ ሺ ብር ኖሮኝ አያውቅም። ያው በዛም አለ በዚህ፣ "ፍቅርን ብር አይገዛውም" ይሉት ዲስኩር ካፈር ተቀላቀለ ? ሙናን ላጣት አልፈልግም፣ እፈቅራታለሁ። በሐሳብ ተውጬ መሬት መሬት ስመለከት የሰውዬው ድምጽ አባነነኝ...

"ይችን የመሰለች ቆንጆ እንዴ ወንድ 'ከቀመሰች' አበቃ ! አጠገብህ አትደርስም። ወዳጄ እፈላልግና ይሰራልህ" አለኝ። ይሄ ደነዝ አቤት ቃሉ እንዴት እንደሚያም ! ጉዳዩ የወሲብ አይደለም፣ ጉዳዩ የሴትና የወንድ ጣጣ ብቻ አይደለም፣ ጉዳዩ የሙሉ ሰውነት ጉዳይ ነው። በፍቅር ጢም ብሎ የሞላ እኔነት እንደተነደለ በርሜል ቀስ በቀስ ፍቅሩን ማንጠባጠብ ሳይሆን እንደፈረሰ ግድብ ሙልጭ ብሎ ውስጡ

ያለው የፍቅር ሙላት ፈሰሰ ባዶ መሆን፣ ባዶ የመሆን አፋፍ ላይ ነኝ።

"ሴት ልጅ እንዴ የወንድ ጠረን ቀምሳ ትመለሳለች ብለህ እንዳታስብ ?!" ይለፈልፋል ደብተራ ማው... ድከም ባለ እርምጃ ከተንጣለለው ቪላ እግሬን እየጎተትኩ ወጣሁ። ከኋላዬ የሰውዬው ... ተከተለኝ፣ "ሴት እንዴ ... ከቀመሰች... " ከዚህ በላይ ብቆይ ይሄን ሰውዬ አፍንጫው ላይ በ... ሳላቀምሰው አልቀርም ነበር።

## ክፍል ስድስት

ቀጥ ብሎ ቆመ!!

አዎ የነበረኝ ተስፋ ቀጥ ብሎ ቆመ !!

ሙና ደወለች። ሰው ማታ ይደውላል፣ እሷ በደረቅ ሌሊት ስምንት ሰዓት ላይ ! ምን ሆንች ብ... ደነገጥኩ።

"ተኝተህ ነው አብርሽ ?" አለችኝ ስልል ባለ ድምጽ። ያ የምወደው ድምጿዋ የጦር ከተት እየ... ከሆነብኝ ሰንብቷል። ወሬዋ ሁሉ ሄዶ ሄዶ ለንትን እየሆነብኝ ተቸግሬያለሁ። እስቲ በዚህ ሰዓት "ተኝተህ ነው ?" ማለት ምን ማለት ነው ? እና ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ምን አበራለሁ ? እንኳን ብቻ... እሷም ከጎኔ ኖራ በዚህ ሰዓት ድብን ያለ እንቅልፍ ላይ ነው የምሆነው !!

አንዳንድ ሴቶች ፍቅረኛቸውን እንቅልፍ የመንሳት መብት ያላቸው መስሎ ይሰማቸዋል ! ድምፃቸ... ፍራሽ፣ ሹክሹክታቸው አንሶላ፣ ሳቃቸው እንቅልፍ ሆኖ እረፍት እንደሚሰጥ ዓይነት፣ የምንሰለቻቸ... !! ደግሞ የሆነ ጊዜ አለ፣ ሴቶች እንቅልፍ የሚያጡበት። እውነቴን ነው፤ ምክንያቱን ራሳቸው... አያውቁትም። ሌሊት ተነስተው ቁልጭ ቁልጭ ይላሉ። ቀን የጣሏትን ማኪያቶ፣ መንገድ ... የፎገሯቸውን ወንዶች እያስታወሱ ካለ እንቅልፍ የሚያሳልፏቸው ሌሊቶች አሉ። በ... የሚዛብሩባቸው ! ነጭናጫ ሆኛለሁ።

"ናፍቀሃለሁ አብርሽዬ"

"እስካሁን አልተኛሽም ?"

"ተኝቼ ነበር፤ ድንገት ቀሰቀሰኝ"

"ማነው የቀሰቀሰሽ ?"

"ፍ....ቅ....ር....ሀ" አለች ሞልቀቅ ብላ። ሙና ቆንጆ ናት። ድምጿዋም ያምረኛል፤ ግን መሞላቀቅ አያምርባትም ! መሞላቀቅ የሚያምርባት ሴት አለች፣ መሳቅ የሚያምርባት አለች፣ መኮሳተር ውበቱን የሚደፋባትም አለች፤ መሞላቀቅ ግን የሙና መክሊት አይደለም። ሙና የሚያምርባት የጣውላ መሰንጠቂያ ማሽን በሚመስል የጠዋት ድምጿ፣ "ሂድ ወደዚያ" ስትል ነው።

"ምነው ዝም አልክ ?"

"ኧረ አላልኩም !"

"ምነው ኮስተር አልክ ?"

"ኧረ አላልኩም"

"አልናፈከኝም...?" ማውራት ፈልጋለች። ማውራት አልፈለግኩም። ማውራት አልፈለግኩም ማለት ሙናን አልፈልጋትም ማለት አይደለም። ይሄ ሆታዊ ሰካራም ሐሳብ ቅፅበትን እንደዘላለም እየደመረ የተወናገረ ድምፁን በሰው ሕሊና ይቆልላል። ነገ ሥራ እገባለሁ፤ መተኛት አለብኝ። ሙና ሕይወት አይደለችም፤ የሕይወት አንድ ክፍል ናት። ሕይወት አገር ቢሆን ... ፍቅረኛ፣ ሥራ፣ ዕውቀት፣ መዝናናት፣ ሐዘን፣ ደስታ፣ ቤተሰብ ብሔር ብሔረሰቦች ናቸው።

አገርን ለማቆም እኩል ድርሻ፣ እኩል አስተዋፅኦ ያላቸው የአገር ክፍሎች፤ እና እንቅልፍም አንድ ብሔር ነው። ሙና የምትባል ብሔር እንቅልፍ ለሚባል ብሔር ክብር ልትሰጥ ይገባል። ዝም ብላ ሰምንት ሰዓት ደውላ የእንቅልፍ ብሔርን ከአልጋ ከሰሉ እንድታባርር ማን መብት ሰጣት ? ቀን እንክቷት ስለተፈቀረች ብቻ፣ ቀን በኪነጥበቡ ልቡ ዙፋን ላይ ስላስቀመጣት ብቻ፣ ያሻትን ማባረር፣ ያሻትን መግፋት ምን የሚሉት አንባገነንነት ነው ? የድሃ ርስቱ እንቅልፍ ነው፤ ደሃ ሰደሬ አይዝናና ዱባይ፣ በእንቅልፉ ነው ሲጋና ነፍሱን የሚያሳርፈው - በህልሙ ነው ቅቤ እየጠጣ የሚወዛው። ነጭናጫ ሆኛለሁ።

"ተኝቼ በህልሜ አየሁህ" (ኡኡ ! ሰምትን ህልም አብዝታለች) ሰው ለካ አንዱን ህልሙን መፍታት ሲያቅተው ነው ብዙ ህልም የሚያንጋጋው።

"እረ....እየሸኝ ? መቼም ያንን የምትወጂውን ኬክ እየጋገርሽ መሆን አለበት ያየሽኝ ... አንቺና ኬክ ብዬ አዎ እንድትለኝ እያማለልኩ ተማፀንኩ።

"አ...ይ...ደ...ለ...ም ! እንደገና ሞክር" እደግመዋለሁ ሙና መሞላቀቅ አያምርባትም !

"እ እ እ ስፐረስ እየጠጣን ?" ስፐረስ ትወዳለች ... ይሄ ድምጽ ግን የስፐረስ እንዳልሆነ አውቀዋለሁ።

"ሂድ ! ...በቃ መብላትና መጠጣት ብቻ ነው እንዴ የምታውቀው ? እስኪ ሌላ...ፍቅረኞች የሚሰሩት ነገር ገምት ?"

"ፍቅረኞች የሚሰሩት ? ... ምክ እያደረግን ይሆናላ" መለስኩ።

"እፍፍፍፍፍ ... ቤት ውስጥ ... መኝታ ቤት ውስጥ..." ቆጣ ብላ ጠየቀችኝ (ህልሟን እኔ ያየሁ መሰላት እንዴ! የፈለግኩትን ብገምት ምን አገባችበት) ሰው ለካ ከመኝቱ ሲፈጠር፣ ከምኞቱ አብሯት እንደኛ ሲወለድ ሕፃን ይሆናል። ሙና ሕፃን ሆነች !

"መኝታ ቤት ፍቅረኞች የሚሰሩትን ነገር ገምት" አታበሳጭም ? በሷ ቤት በእሷ ኩርፊያ ከተናገርኩት፣ በልቤ የማምንበት ሃቅ የሚሆን መሰሏታል ! ደግሞስ ለአንትትን ወኔው ካለ ማነው መኝታ ቤት ብቻ ይደረጋል ያለው ?

"እኔ የምልሽ ... የጠየቅሽውን የሥራ ዝውውር እምቢ አሉሽ በቃ ?"

"አሁን ማን ስለሱ አወራህ ?" ተበሳጨች። እኔ ደግሞ ሰለቸችኝ።

"አሁን ምን እያደረግሽ ነው ?"

"አ....ሁን ልብሴን ውልቅልቅ ... አድርጌ፣ ብርድ ልብሴ ውስጥ፣ አንሶላዬ ውስጥ፣ በቃ አንተን እያሰብኩ ትራሴን እቅፍፍፍፍፍ አድርጌ እገላበጣለሁ - አላሳዝንህም ?" (ምነው ይች ልጅ እሳት አደረጋት ! እስከንጋባ ምናምን ስትል አልነበረ እንዴ ?) ሕይወት እንዲህ ናት እንግዲህ፣ በተሸነፍንበት ነገር ላይ ደንዝዙን ስሜት ሁሉ ውኃ ውስጥ እንደገባ ውሻ ድንዛዜውን አርገፍግፎ እንዲነሳብን ታደርጋች፡

ድምጽዋ ውስጥ እኔ አለሁ፣ ማድረግ የማልችለውን በምኞት እያደረግኩ። እኔ ... ከትራስ የማልሻል እኔ።

አንዳንዴ የሙና ችግር የምታፈቅረው ሰው ማውራት የማይፈልገው ነገር ላይ መሟዘዝ መውደዷ ላይ ነው ! ሙዝዝዝ ! ምን ያህል ለእኔ ስቃይ እንደሆነ አይገባትም ! በቃ ማውራት የምትፈልገው ስትመጣ ማድረግ የምትፈልገውን ብቻ ነው። እኔ ደግሞ ማውራት የምፈልገው ምንም ማድረግ አለመቻሌን ነው። "ሙና ካንቺ በላይ ችግሬን የሚረዳ ሰው በምድር ላይ የለኝም፣ ችግር አለብኝ ወሲብ ማድረግ አልችልም" ልላትና ጭንቄን ልገላገል እፈልጋለሁ፣ ግን የፍላጎቷ ግዝፈት ግልፅነቴን ደፈጠጠው ! ዝም !!

"ምነው ዝም አልክ ?"

ኡፍፍፍፍፍፍፍ ! እድሜ ልኬን ዝም ብል፣ ሰፈራችን እንዳለው ከተወለድኩ ጀምሮ እንደማውቀው ድንጋይ ዝም ብል ብዬ ተመኘሁ። "ሴት አሳዳጅ" ይላል ሞኝ ሰው፤ በራሱ ችግር መሸሻ እጥቶ እንዲት ሴት ያውም የምታፈቅረው የሚያፈቅራት ሴት የምታሳድደው ሚስኪን እዚህ ያላየ ሁሉ። ሰማይ ዝም ያለው ምድር ፍቅሩን ሽታ ቀን ከሌት ስለነተረከችው መሰለኝ። ተራሮች ዝም ያሉት ሴት ተራሮች ሕልማቸውን እያወሩባቸው ፍቺው ቢጠፋባቸው መሰለኝ። ሰዎች የሚጮኹት መሻታቸውን ከማይሻ ሕይወት ስለተሳተሙ መሰለኝ። እውነተኛው ሕይወት ከሸፎ አሻንጉሊት ኑሮ አቅፈው እዩዩ እያሉ።

ሙና ጆሮ ላይ ስልኬን ዘጋሁባት።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሙና ላይ ስልክ ዘጋሁባት። ነፍሴ የሚራብውን ድምጽ ቋቅ ብሎ ተፋው። "ኔትወርክ ተቋርጦ ነው" አልኩት ለራሴ። ራሴ የሙና ጠበቃ ሆኖ እንዳይሞግተኝ ፊት ስነሳው መሆኑ ነው። ከራስ የተረፈንን ነው መቼስ ለሌሎች የምንዋሸው።

ጠዋት ሙና ደውላ ምንም እንዳልተፈጠረ፣ "ይሄ ኔትወርክ ምቀኛ እኮ ነው፤ ስራ ጆሮህ ላይ ተዘጋ የኔ ቆንጆ" ብትለኝ ልቤ ተፈራገጠችብኝ። ከመኝታዬ መነሳት አልቻልኩም። ስንት ነፍስ አለ ግራ ቀኝ የማያይ፣ በተቆፈረለት የፍቅር ቦይ ኮለል ብሎ የሚፈስ ቢኝን !! አመመኝ ! ስንት እርግብ ነፍስ አለ በእግዚአብሔር !! እንደ ውሸት ትልቅ ጉልበት የሚጠይቅ ጉዳይ ምን አለ ?

# ክፍል ሰባት

ከሃኒባል ጋር ሆነን ያልረገጥነው የባሕል ሕክምና አዋቂ ቤት የለም፤ ደከመን። ሃኒባል ለእኔ ሲሉ ያለችውን የዓመት እረፍት ጨርሶ ካለ ክፍያ አንድ ሳምንት ከሥራው ቀረ። ግን ምን ያደርጋል፣ ሁሉም ነገር ከንቱ ልፋት ብቻ ሆነ። የሄድንባቸው ሁሉ ለእኔ ችግር መፍትሔ ማምጣት ይቅርና፣ ማፅናናት እንኳን ያልፈጠረባቸው ኢጋሰሰ ነጋዴዎች ነበሩ። ቢጨንቀን አንድ ሁለት የልብ ጓደኞቻችንን ጨምር ጉዳዩን ነገርናቸው። አንዱ ጓደኛችን ለትምሕርት ውጭ ቆይቶ ገና መመለሱ ነበረ፤ ማይክሮባዮሎጂስት ነው።

ጉዳዩን በጥሞና አዳመጠና፣ "...እስቲ አንዲት ውጭ አብረን የተማርን የስነልቦና ባለሞያ አውቃለሁ" አለ። ደስ የምትል የተረጋጋች ልጅ ጋር ወሰደኝ። ቢሮዋ ይገርማል፤ ሁሉም ነገር ነጭ - ከእስክርቢቶና ወረቀቱ ውጭ። ተነስታ ተቀበለችን። ከአንድ ሰዓት በላይ ያወራሁ ሳይመስለኝ ብዙ አስወራችኝ።

"እኔ የምልህ አብርሃም"

"እ ?"

"ፍቅረኛህ ምናልባት ከቤተሰብህ አንድኛቸውጋ በመልክ ወይ በባሕሪ ትመሳሰል ይሆን ?"

"ኧረ በጭራሽ ! እህቴ አፍንጫ የሚባል ነገር አልፈጠረባትም፣ ሙናኮ ሰልካካ ናት። እህቴ ከማጠሯ ብዛት ከራሷ ቦርሳ ቻፕስቲክ ለማውጣት እንኳን ወንበር ላይ ቆማ ነው፣ ሙናኮ መለሎ..." ፈገግ አለች የሥነልቦና ባለሞያዋ። ጥርሶቿ ያማምራሉ (ልብ ሊይዎት አሁንም ሴት አደንቃለሁ)

"እናቴም ብትሆን ቁመቷ በእህቴ ነው የወጣችው። በዛ ላይ እናቴ ጠይም ሙና እኮ..." ዝም አልኩ!

"እ...ምናልባት የወሲብ ፊልሞችን ትመለከት ነበር እንዴ ?"

"ኧረ አይቼ አላውቅም" እውነቴን ነበር።

"ቤተሰባችሁ ውስጥ የሚበዙት ሴቶች ናቸው ወንዶች ?"

"ልጆቹ እኔና እህቴ ነን... በቃ !" የሥነልቦና ባለሞያዋ የሆነ ነገር ቀይ ወረቀት ላይ በቀይ እስክርቢቶ ስትጽፍ ቆየችና፣ (እንዴት እንደሚታያት እኔ'ጃ)

"ኃይማኖት ላይ እንዴት ነህ - ታጠብቃለህ ?"

"ኧረ የለሁበትም። ቤተክርስቲያን የሄድኩት ራሱ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር የበቅሎ ቤቱ ፍንዳታ ጊዜ፣ እናቴ ሚካኤል ልትደበቅ ስትሄድ እጇን ይዣኝ ነው ... ከዛ በኋላ ሄጄ አላውቅም"

"ፍቅረኛህ ሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት አላት ብለህ ታስባለህ ?"

"ማን መና ... ኧረረረረረረረረረረረ"

"ከዚህ በፊት ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ ያልፈጸምከው ለምንድን ነው ?"

"አላኝ"

"ሴቶችን ትፈራለህ እንዴ ?"

"መፍራት ሳይሆን እንዲሁ መቅረብ ብዙም አልፈልግም።" ወንበሯ ላይ ተመቻችታ ወደኔ ዘንበል አለችና (ጡቶቿ አፈጠጡብኝ)

"ለምን ?" ስትል ጠየቀችኝ፣ ቁልፏን ያገኘችው ሳይመስላት አልቀረም።

"ለዓም ሰዓት በስልክ እንዳያወሩኝና ሸናኝ እንዳይሉኝ ... !!" ስል መለስኩላት። እንደው ይህ ምላሽ መታበይ ይመስል ይሆናል እንጂ ማንንም እንደመሸኘትና እና በስልክ እንደማውራት የምጠላው ነገር የለም። እኔም ሲሸኑኝ አልወድም፣ ሰውም መሸኘት ያንገሸግሸኛል። ምንድን ነው መጓተት፣ ምንድን ነው ስልክ ላይ ተለጥፎ ማላዘን ? እንዴት እንደሚያስጠላኝ ! ስልክ አልወደም።

"እኪ አብርሽ ጨርሰናል፣ ስልክህን ስጠኝና እደውልልሃለሁ" እርፍ !!

የመጓልቦና ባለሞያዋ እየደወለች ልትረዳኝ ብትሞክርም ነገሩ ዋጋ አልነበረውም። የበለጠ ስለጉዳዩ ባሰብኩ ቁጥር በእግሮቼ መሃል ሳይሆን በፍርሃት መሃል ቁም ነገሩ ጠፋ። ቁሉም ዝም መጽሐፉም ዝም !! ወይ ነው አበሻ፣ "ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ" የሚለው። ትውልድን የሚሻገር ሕያው ድምጽ ሚፈጠረያው የት እንደሆነ ቢገባው እንጂ ! ኡፏያ ! ወንድነት ደገፍ ብሎ የሚኮፈስበት ከዘራ ሸንበቆ ሲሆን አለ ከልብ የሚሰጠር ወኔ፣ ከተራ ብልግና የገዘፈ ሃቅ፣ ቃጭሉም ዝም ! ቤቴ ውስጥ ካሉት ዕቃዎች ምን አስጠላህ ብባል አልጋዬ። የተሸነፍኩበት፣ የተማረክኩበት፣ የቆሰልኩበትና የተሰዋሁበት

ጦር ሜዳ መስሎ ታየኝ። "ወኔዬን ያፈሰስኩበት አልጋ እኮ ነው" ብዬ የልጅ ልጆቼ ላይ እኮፈስበት ይሆናል። ያኔ ወኔው የፈሰሰ ትውልድ ነፍ ነው የሚሆነው ፤ ወኔ ቢስነትም ክብር!

## ክፍል ስምንት

መና ልትመጣ አስራ አንድ ቀናት ቀሩ። አስራ አንድ የሸብር ቀናት ! "አብርሽ ፈራህ እንዴ ? ሂሂሂሂ" እንደ ቀልድ ትጠይቀኛለች። ለምን ጀግና ለመምሰል እንደምጣጣር ለራሴም አይገባኝ፤ ፈርቻለሁ አይደል እንዴ ? "አዎ ፈርቻለሁ" ብላት ምን ነበር ? እኔ ግን ኩስተር ብዬ እንዲህ አልኳት፤ "ለምን ነው የምፈራው ?"

"ለብር አምባሩ ነዋ !" አለችና ትንፋሽ እስኪያጥራት በሳቅ ፈረሰች። ሳቋ ውስጥ "ሺ ጊዜ ፍራ እንጂ አሁንማ ቁርጥ ነው" የሚል ንዝረት አለ። እኔ'ኮ የሚገርመኝ "ብር አምባር" ከ"እንትን" ጋር ምን አገናኘው ? እውነቱን እኮ ነው ... ብዙ ወንዶች ከአንዲት ሴት ጋር ወሲብ ሲፈፅሙ "ፈረሱም ሜዳውም ያውላችሁ" ሲባሉ በስሜት ስለሚባክሩ እንኳን ቃል ሊሰነጥቁና ሊመረምሩ አልጋ ላይ ይሁኑ ዓየር ላይ የሚያውቁት ከተረጋጉ በኋላ ነው። ከዛ በፊትማ ብር ይሰበር አምባር ይሰበር ብርጭቆ ይሰበር ቅስም ይሰበር ምን ግዳቸው ! "ሰማዩን ሰበረው ጀግናው" ቢባልም አይሰሙም፤ እኔ ግን የያዘ ይዞኝ ቀልቤን አሰባስቤ አድርጓታልና "ብር አምባር" ከድንግልና ጋር ምን አገናኘው ብዬ አስባለሁ ... (ሰው ወዶ ፈላስፋ አይሆንም) መቼስ ይሄ ሁሉ ሚዜ እና ታዳሚ ሳንቃው እስኪደርቅ በየሰርግ ቤቱ "ብር አምባር ሰበረልዎ ጀግናው ልጅዎ" እያለ ይዘፈነው እንጂ "ድንግልናን ከብር አምባር ምን አገናኘው" ለሚለው ጥያቄ መልስ ያለው አይመስለኝም።

እኔ ግን ዝም ብዬ ሳስበው፤ "ብር አምባር መስበር" አስገድዶ ከመድፈር ጋር "ጥብቅ ቁርኝት" ያለው ጉዳይ ይመስለኛል። ልጅቱ የብር አምባር እጇ ላይ አጥልቃለች፤ (ያው ሴት የብር አምባር ማድረግ ከጥንት የተለመደ ነገር ነው) እና ባሏ ወላ ወዳጇ እጇን ይይዛታል ... (ያዝ እጇን ...) እንዲል ዘፋኙ፤ ከዛ ለማምለጥ ወይም ራሷን ለማዳን እንዳትሞክሯ መታገሏ አይቀርም፤ መቼስ ዝም ብሎ ያውልህ አይባልም። በሩን ይዘጋል (ዝጋ ደጇን) እንዲል ቀጣዩ የዘፈኑ ስንኝ፤ ትግሉ ከበረታ እጇን ጠምዝዞ ጉንጯን ሳም (ሳም ጉንጯን) የሚለው ልክ መጣ። ለከንፈሯ ያሞጠሞጠው ከንፈር በልጅቱ መወራጨት ስተ ጉንጯ ላይ አርፎም ሊሆን ይችላል፤ ወይም አየር ላይ እንደ ርችት የከሸፈ መሳም ብትን ! ሲታገላት እጇ ላይ ያለው አምባር ሰብር ! ክሽ ! "ይሰበር የታባቱ ቅዳሜ ገበያ ስወጣ ሌላ አገዛልሻለሁ የውም

ወርቅ የመሰለ" እያለ ወደ ጉዳዩ !

እንዲህ የሚያስለፈልፈኝ ወድጄ አይደለም፣ አምባሩ እኔ እጅ ላይ ያለ እስኪመስለኝ መዘዜ ሊመዘዝ አስራ አንድ ቀን ቢቀረኝ እንጂ። ሙና ይቅርታ አታውቅም ! በአሁኑ ጉብኝቷ ጉንጯን ስሜ ብልካት አርቧም እንደ ይሁዳ ስሞ ነው ሰብቶኝነት ስቅላቱ የምትሸጠኝ። ሙናን እኮ አፈቅራታለሁ። እንደ ቀልድ ሳጣት ነው በቃ ? እሺ አሁን የእኔ ጥፋት ምንድን ነው? የሙና ጥፋትስ ? እግዚአብሔር ግን ምን አደረግኩት ? እስኪ አሁን ማን ይሙት ሲቀጣኝ ፊልጎ ከሆነ ሌላ ልምጭ አጥቶ ነው !? ለምሳሌ ሰፈራችንን በጎርፍ አጥለቅልቆ እኔን ብቻ በመግደል ዜና ማድረግ አይችልም ? መንገድ ላይ ሱክ ሱክ ስል መብረቅ አውርዶ ድምጥማጤን ማጥፋት ያቅተዋል ? ምን አድርጌው ከማን የተለየ ጥፋትና በደል ሰርቼ በውርደት የምወዳትን ልጅ ዓይኔ እያየ ያስነጥቀኛል ? አባታችን አብርሃም እንኳን በዘጠና ስንት አመቱ ተሳክቶለት ልጅ ሲወልድ እኔን ሚስኪኑ በሃያ ሰባት አመቴ እንዲህ ጉድ ስሆን እግዜር እንዴት ሆዱ ቻለ ?

"አብርሽ" አለኝ ሃኒባል፣

"እ"

"ግን ችግሩ ከሙና ቢሆንስ ?"

"እንዴዴዴዴዴ ምን አገናኘው ከሙና ጋር"

"እይ እንደው ካልደበረህ ... ሌላ ሴት ጋር ብትሞክር ምናልባት ነገሩ ሊቀየር ይችላል"

"ምናልክ አንተ ? ... ችግር አለብህ እሺ ... ሁለተኛ እንዳትደግመው"

"ሰሪ" ብሎ ዝም አለ። እሱ ዝም ይበል እንጂ አዕምሮዬ ግን ሃኒባል የለኮሳትን ችቦ አንስቶ ሩጫውን ተያያዘው። ሌላ ሴት፣ ሌላ ሴት፣ ሌላ ሴት ... ሌላ ሴት ለሙከራ የምትሆን ሴት ... ሴት ... በቀላሉ የምትገኝ ሴት ... ሰራም አልሰራም ከሙከራው በኋላ ዳግም አጠገቤ የማትደርስ ሴት ... ሴት ... ወሬ የማታበዛ ሴት፣ በቃ በቀጥታ ወደ ገደለው ስትባል ቀሚሷን ወላ ሱሪዋን የምታወልቅ ሴት ... ሴት ... ሴተኛ አዳሪ ! ቡምምም ! አዕምሮዬ ውስጥ ቤተሙከራውን የያዘ ሐሳብ ፈነዳ። ሴተኛ አዳሪ ጋር መሄድ ! አዕምሮ የሰው ልጅ የገጠመውን ችግር ሁሉ መፍቻ ሐሳብ አመንጭቶ ሽቅብ እንደሚተኩስ ሁሉ የሕይወት ክርፋት ውስጥ በእናታችን የሚከት ሐሳብም እንዲህ ይዞልን ከተፍ ይላል። ሰው

የራሱን አዕምሮ ካሻው መምጣቱን ረሳች፤ ከሌላም መቀበሩ የአስኪሬን ሳጥኑ ሊያደርገው ይችላል።

ሊድፍን ሳምንት ይሄ ሃሳብ ከአዕምሮዬ ሊወጣ አልቻለም።

እንደውም አንድ ሌሊት በህልሜ ምን አየሁ ... ቡና ቤት፤ አንዲት ከምድር ወጣብ ማለትም የረዘመ ቀይ እግር ያላት ሴት ባለኔ ወንበር ላይ ተቀምጣለች። እግሯ ከመርዘሙ ብዛት ባለኔ ወንበሩ ላይ ተቀምጣም መሬቱን ረግጣለች። እኔ ከጓላዋ ወደ እሷ እየሄድኩ ነው፤ እየተራመድኩ ሳይሆን ወ በካሜራ ከሩቅ አጉ ሱት እንደሚሉት ባንዴ በዓይኔ በቤቶት እጠጋ ቆምኩ። ሽቶዋ ሽተተኝ፤ ይጣ የሚገርመው ወንድነቴ ሱሪዬን የወጠረው ይመስለኛል። ማድረግ የቻልኩ ይመስለኛል። ልጅቱ ወደ ዞረች፤ መና ነበረች። ባንኮኒው ላይ ብር ከምራ እየቆጠረች። ወዲያው ቡና ቤቱ ባንክ ቤት ሆነ።

ጓደኛዬ ሃኒባል አግዜር ይደልህ ! (የዋልከልኝን ውለታ አቆይኝ...)

ረጅም ጊዜው ሸመጠጠ ! ሦስት ቀናት ብቻ ቀሩ መና ልትመጣ።

ሃኒባልን "ሦስት ቀን ቀረ ምናባቴ ላድርግ ?" አልኩት።

"በሦስት ቀን ... ሊደረግ የሚችለው ብቸኛ ነገር መፀለይ ነው አብርሽ"

"አትቀልድ ባክህ"

"እውነቴን ነው ... 'አምላኬ ሆይ ጉድ ልሆንልህ ነው፤ የሰጠኸኝ ሐዋን እንደ ሰሜን ኮከብ ያውም እሷ ጅራታም እየተንቀለቀለች ሰማዩን ሰንጥቃ አዲስ አበባ ላይ ልታርፍ ነው ... እባክህ በረዶ ከምር ላይ ተከስክሳ እንዳትከሰም እርዳኝ' በልና ድፍት ብለህ በሩ ላይ አልቅስ !" እየቀለደ መሆኑን ለቡጭ ተዘጋጅቼ ፊቱን ሳየው ሃኒባል ከምሩ ነው !

"እና 'እንትኔን አቁምልኝ' ብዬ ልፀልይ ? ... ባለኔ ብሎ ነው እዛው የሚቀብረኝ" ብዬ ሃኒባልን ገላመጥኩት።

"ለምን ባለኔ ይልሃል ? ለምን ይቀስፍሃል ? 'ብዙ ተባዙ' ብሎ አዝዞ ሲያበቃ መባዣውን መንሳት ከፈጣሪ አይደለም። ይሄ የሰይጣን ሥራ ነው። ይልቅ ያልኩህን አድርግ። ሰው እንዲራመድ እግር ሲሰጥ፣ ሰይጣን እየዞረ ሽባነትን ያድላል፤ እግዜር ውብ ተፈጥሮን ትመለከትበት ዘንድ ዓይን ሲፈጥር፣ ሰይጣን በሰበብ አስባቡ እንዴ በትራኮማ፣ እንዴ በአይጋ ሰበብ አይታህን ይቀማሃል፤ ቢ

የሚኖሩም ጓደኞቹን ይጋርደዋል፤ እግዚአብሄር የማንም አካል እንዲጎድል አይሻም። ሙሉ ስለሆነ ማንም ሙሉነት እንዲኖር ነው ፍላጎቱ፤ ለዛም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በፈውስ ታሪክ የተሞላው። ሰይጣን ግን ጎዶሎ ነገር ስለሆነ አትታሎም ይሁን እጭበርብሮ ለሰዎች ጉድለት ያድላል። ይሄ ጎዶሎ ምን ይሻለዋል ነገሩ ? ግዴለህም አብርሽ … ሂድ ምድርን ያለካስማ ሰማይን ያለባላ ያቆመ ጌታ ያንተን እንትን ማቆም አያቅተውም። ሂድ ብያለሁ ሂድ !!" ሃኒባል እኔ ላይ በደረሰው ነገር በጣም አዝኖ ተቆጥቶ ነገረኝ። ግንባሩ ላይ ሲበሳጭ የሚጋደመው የደም ስር ይመሰክራል። እኔ ግን በሳቅ ፍርፍር አልኩ፤ ለነገሩ በጣም ነው ያሳቀኝ።

## ክፍል ዘጠኝ

ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ቤተክርስቲያን ሄድኩ። እንደ እብድ ብቻዬን ማውራት ጀምሬ ነበር። ቀጥ ብዬ ዋናውን በር አልፌ ገባሁ። ትዝ ሲለኝ አልተሳለምኩም፤ ተመልሼ ግራ ቀኝ በሩን ተሳለምኩ። ዘው አይባልም ዘሎ፤ ፈጣሪ የተጎዳ ልቤን ቢመለከትም ቅሉ እዚህ ድረስ ልብ ውልቅ መሆኔ ለእኔም ደግ አይደል። ወደ ውስጥ ስገባ የቤተክርስቲያኑ ድባብ፣ የቤተመቅደሱ ወፋፍራም የጣውላ ከፈፎች ላይ ከፈሩት ዋኖሶች፣ እድሜ ጠገቦቹ ዛፎች፣ ከምንም በላይ ደግሞ ዝምታው ከውስጥ ብሶቴ ጋር ተዳምሮ እንባዬን አመጣው። ከምርም የሰው ልጅ ምናምኒት አቅም እንደሌለው የሚያውቅበት የሆነ ጭብጦ ነገር መሆኑን የሚረዳበት ቦታ ቢኖር ቤተክርስቲያን ይመስለኛል።

ፈጣሪን ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ገባኝ። "ታቆምልኛለህ ወይስ አታቆምልኝም…" አይባል ነገር። ቆይ ግን ከዘፍጥረት ጀምሮ በዚህ ጉዳይ እግዜር ፊት ቆሞ የፀለየ ሰው ይኖር ይሆን ? በሐሳቤ ስቀላምድ ቆይቼና ዞር ዞር ብዬ አካባቢዬን ቃኘሁ። ከእኔ ወደ ግራ ሲል ቢጫ ልብስ የለበሱ መነኩሴ ተቀምጠዋል። ምን እንደገፋኝ እንጃ ወደሳቸው ገሰገስኩ፤ ምናልባት እዛው እንደ ደንቡ እግዜርን በሚያዝንበት ቋንቋ ቢያናግሩልኝ ብዬም እንደሆን እንጃ ! አጠገባቸው ስደርስ፣

"አባ" አልኳቸው።

"አቤት የኔ ልጅ፣ እንደምን ዋልክ" አሃ ! ለካ ሰላምታም ነበር።

"ጓደኛዬ ልትመጣ ሦስት ቀን ቀራት፤ ከመቀሌ ከሦስት ቀን በኋላ ትመጣለች፤ ሙና ነው ስሟ …

ሦስት ቀን ብቻ..." ቀና ብለው በእርጋታ አዩኝና ከጎናቸው ያለውን ግንድ መቀመጫ በሆዛ እጃቸው እያመለከቱኝ፤

"ና እስቲ እዚህ አረፍ በል የኔ ልጅ" አሉኝ።

"እይ እሄዳለሁ" ብያቸው ያመለከቱብኝ ቦታ ላይ ተቀመጥኩ። (ሁለት ሰው የሆንኩ መሰለኝ፤ የምናገረው ሌላ የማደርገው ሌላ)

"ምን ሆነህ ነው የምታለቅስ ልጄ ?" ቢሉኝ እጄ ወደ ዓይኔ ሄደ - አይገርምም ? እየተነፋረቅኩ ነበር ለካ። እንባዬን በእጄ ምዥቼ እባን የሆነውን ሁሉ ነገርኳቸው። አቤት መስማት ሲችሉበት !!

በጥሞና ሲሰሙኝ ቆይተው፣ "የኔ ልጅ እንግዲህ ዋናው ነገር ... እግዜር የጊዜ አምላክ ነው፤ የሰውና የእግዜር አሰራር ልዩነቱ ይሄ ነው። ሰው የቻላትን ባሰኘው ጊዜ ያደርጋል፤ እግዜር ግን ሁሉን ይችላል፤ የሚያደርገው ግን ለልጆቹ በሚጠቅመው ጊዜ በሚጠቅመው ልክ ነው። ካለጊዜው እንዲህ ያለው ነገር ውስጥ እንዳትገባ ሊያስተምርህ ወድዶ ይሆናል ... አንድም ደሞ የምድር ጠቢባን ያቃታቸውን ሁሉ የሚችል መሆኑን ሊገልጥልህ ቢወድ እንደሆንስ ምን ይታወቃል ልጄ..."

"እና ምን ላርግ አባ፤ ሦስት ቀን ብቻ ቀራት እኮ"

"መምጣቷ መልካም ነው ! ታዲያ መውደድ ሲሞላ ብቻ አይደለም፤ ሲጎድልም እንጂ፤ ሙላትህን ብቻ እያሳየህ በወዳጅህ ፊት ትልቅ አትምሰል ልጄ። ሰው ነህ ድካሙት አለብህ፣ ድካሞትህን ለሷ ንገራት፤ እውነቱን ተናገር። የውሸትና ማስመሰል ዙፋን ከእንቧይ ገንብተህ ንገሽ ብትላት እሷም ተንዶ ጉድ ይሰራታል፣ ላንተም ፀፀት ነው። የውሸት እና ማስመሰል ካባ ከነፍስ ከረምት፣ ከመንፈስም ቁር አያስጥልም፤ አትድከም ! ግራ ቀኝም አትበል፤ እሷን ሸፋፍነህ ብታሳምናት ከራስህ ልብ የሚሸው እተካራ አያባራም። እውነቱን ንገራት፤ ከእውነት የበለጠ ፈውስ የለም የኔ ልጄ።"

"ከዛስ አባ ?"

"ከዛማ እውነት ከተናገርክ ሰውም ምክርም አያሻህ፤ እውነት ራሱ መንገዱን ይመራሃል።" ብለው ወደ መቁጠሪያቸው አቀረቀሩ። ደህና ዋሉ ልበላቸው አልበላቸው እንጃ ወደ ቤቴ ተመልሼ ጥቅልል ብዬ ተኛሁ። "እውነት መንገዱን ይመራሃል?" እውነት ዋጋ ያስከፍላል ያውም ከነወለዱ። ከሆነስ ሆኖ እውነት ዋጋው ስንት ነው ?

እውነት ዋጋው ስንት ነው?

እውነት ዋጋው ስንት ነው?

እውነት ዋጋው ስንት ነው?

የቱንም ያህል ዋጋው ቢወደድ፣ ቢቃ ለሙና እውነቱን እነግራታለሁ። ወሰንኩ !!

## ክፍል አስር

የቁርጥ ቀን !

እነሆ የተንኳኳ በሬን ከፈትኩ፣ ልብ የሚያቀልጥ የሙና ውበት ከወትሮው ሰባት እጅ ደምቆ በሬ ላይ ቆሟል። ሙናን አፈቅራታለሁ፣ ልለያት አልፈልግም። ሳያት ልክ ብርሃን ጨለማ ከፍልን ድንገት ቦግ ብሎ እንደሚሞላው ውስጤን የሚሞላው አንዳች ነገር አላት፣ እንደ ባዶ ፊኛ የሚሽሽ መንፈሴ ሙናን ሳያት በዓየር እንደተሞላ ባሉን በፍቅርና በደስታ ሕዋ ላይ ይንሳፈፋል። ይሄው የእውነት ዋጋው በሬ ላይ። እውነት ዋጋው ይሄን ያህል ውድ ነው። አቅሜን ተናግሬ የነፍሴን ግማሽ ሙናን መከፈል፣ አልያም ሰቆቃዬ ላይ ስቃቀቅ በየዕለቱ በማስመሰልና በሽሽት ሚሰማር የፍርሃት ጉልላቴ ላይ መቸንከር።

ቢሉሴት የሚንሳፈፍ የነፍሴን ባሉን፣ ከፉ አሾህ ጠቅ አድርጎ ሊያተነፍሰው ወደኔ ቢወነጨፍም እከላከልበት ዘንድ በእጄ ያለው መሳሪያ እባ ያስታጠቀኝ ጋሻ ብቻ ነው - እውነት !! እውነቱን ተናግሬ የመሸበት አድራለሁ። እስከመቼ የነገር እንጀ ሳመነዥክ ልኑር ? ቢቃኝ !!

ምን እንዳረጋጋኝ እንጃ በውስጤ "ሙና ብትሄድ ሺ ሙናዎች ይተካሉ" ስል ረጋ ብዬ ፎከርኩ። ሳንዲት ሙና ያልሆንኩ እኔ ለሺ ሙና ስፎክር የሰማ ራሴ ቢታዘበኝም ግድ አልሰጠኝም። ፉከራ ከጀግንነት ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ከሆነ ፍርሃትም እንደሚመነጭ የገባኝ ያኔ ነው።

ሙና በእቅፏ ሙሉ እፍላኝ በሞቃት ከንፈሯ በናፍቆት ግጥም አድርጋ ስትስመኝ ነፍሴ ከተወዘፈችበት ከርፈያ ተመንጥቃ ልትወጣ ተጣጣረች፣ ቢሆንም እንቅ አድርጌ ነፍሴን ያዝኳት። መቆጣት አለብኝ ! መኮሳተር አለብኝ። ሙና "የሆነ ነገር ሆኗል ዛሬ ልለፈው" እንድትል የሆነ ነገር የሆንኩ መምሰል አለብኝ። ተሸከማ የመጣችውን እሳት በቁጣ ውኃ በር ላይ ማጥፋት፣ መደርገም አለብኝ። ቦርሳዋን

ጠረጴዛ ላይ ወርወር አደረገችና በናፍቆት እንዴ ቤቱን ከእግር እስከ ራሱ ዙሪያውን ቃኝታ በረዥሙ ተነፈሰችና ለሞላ ቦታ መጥታ ጉልበቴ ላይ ተቀመጠች። ደረቷ ላይ አስጠግታ አቀፈችኝ፣ ለሞ የሰውነት ክፍል ፀጉሬን ሳመችኝ።

"ፀጉርህ አድጓል" ብላ በጣቷ መንጨር መንጨርጨር አደረገችኝ። ወይ ነዶ ልጅቱማ የፍቅር ሰው ነበረች፤ ካለቦታው ተከሰተች እንጂ። ተነስታ ወደ ውስጥ ገባችና የእኔን ቁምጣ ለበሰች፤ ቁምጣ የተሰራው የሙና ዓይነት እግር ላላቸው ሰዎች ይመስለኛል። የእኔን ቲሸርት ለበሰች፤ ቲሸርቱ የተፈጠረው የሙና ዓይነት ጡት ላላቸው ሴቶች ብቻ ይመስለኛል። ከዛም ወደ ኪችን። ዝም ብዬ እያታለሁ፤ ፊቷ ላይ ምንም ነገር የለም፤ ረጋ ያለ ለስላሳ ፊት፤ ትረጋጋ እንጂ እሷ ምን አለባት የመጣው ቢመጣ ሁሉ በጇ፤ በአንድ እይታ ብቻ ወደ እሳት ነበልባልነት የሚለወጥ አረር ሰውነት ይ ምን አስጨነቃት።

እያጠናኋት ነበር፤ መለያየታችን እንደማይቀር አንድ ነገር ሹክ ስላለኝ አድሜ ልኬን እንዳልረሳ እያጠናኋት ነበር። ሙናን መቼም ቢሆን መርሳት አልፈልግም፤ ፍቅረኛዬ ስለሆነች አይደለም በሕይወት ውስጥ የመሰላል እርከን ሆነው አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርጉን ሰዎች አሉ፤ ሙና እንደ ናት ለእኔ። ምን ያህል ልትናፍቀኝ እንደምትችል አሁን ላይ ሆኜ እወቀዋለሁ። ዝም ብዬ እያታለሁ፡ ድንገት ዞር ስትል ዓይናችን ተገጣጠመ - ሳቀች። ፍፁም ገራገር እና ንፁህ ፈገግታ። እኔ ግን ደነገጥኩ፡ ወይ ጉድ፡ ሰው በሰላም አገር እንደ ሌባ ደንጋጭ ሆኖ ይቀራል ?!

በዓለም ላይ ሁለት ሰዎች አሉ፣ ሙና እና አብርሃም የሚባሉ። ወደፊት ሰዎች ሲመረቁ፡ "ጋብቻችሁ ወላ ፍቅራችሁ የአብርሃምና የሙና እንዳይሆንባችሁ" የሚሉ ይመስለኛል። ይበሉ ! ሰዎች ግን ማለት ሲወዱ። ማለት... ማለት... ለቃቃ... ሙና ቤቴ ውስጥ ጉድ ጉድ ስትል፡ ድንገት ድብርቴ ድራሹ ጠፋ መሳሳቅ ማውራት ጀመርን። ግዴላችሁም ሴቶች የሆነ ድግምት ነገር አላቸው፣ ምኞት ያረገዘው ሶፋ ገዝታችሁ፣ ቡፌ እዛጋ ጎትራችሁ፣ በለምናምን ኢንች ቲቪ ገጥግጣችሁ፣ ኳስ ሜዳ የሚያክል እልጋ፣ መስከ የሚመስል ምንጣፍ አጭቃችሁበት ጭር ያለ ቤታችሁ አንዲት ሴት ምንም ሳትናገ ምንም ሳትሰራ ቤታችሁ ውስጥ በመገኘቷ ብቻ የሆነ ነገሩ ይቀየራል። ድምቅምቅምቅምቅ ይላል፣ ይፍለቀለቃል ቤቱ። ወዙ ግጥም ይላል ቤቱ፣ ይስቃል ቤቱ። አመዳም ቤት፤ እስከዛሬ ዳቦውን የነጠቁት ሕፃን መስሎ ለንቦጩን ጥሎ የከረመ ቤት፤ እንደተወረረ ከተማ በዝምታው በጭርታው ሲያስፈራኝ የከረመ ቤት፤ ልክ እንደ ድግስ አሳላፊ አደግድጎ አሸሸውን አስነካው። ይሄው ሴት ሴት ብለን እንድንሞት የሚያደርገን አንዱ ነገር !

ሙና ቀጥ ብል መጣችና የሆነ የጓዳ ጣጣ በነካካው መዳፏ እንዳትነካኝ ተጠንቅቃ በእጆቿ ተጠማጠመችብኝ። ጡቶቿ መሃል ተቀበርኩ። እዚሁ ብቀር ደስታዬ፤ ጨለማው ጠረኑ እና ምቾቱ። ቀና ብላ እያችኝና በእግሮቼ መሃል ቁጢጥ ብላ ተቀምጣ (ማነሽ በሱጋ ማለፍ ክልክል ነው ! እንኳን እንቿ ባለቤቱም ማለፍ አቅቶታል) ወደ ላይ ቀና ብላ እያየችኝ፤ "ዛሬ ምን ሆንሻል አቡቹ ፍዝዝ አልሽ" አላች። በጣም ስትቀርበኝ ሰንቿ ነው የምትለኝ። እጣን እጣን ትሸታለች፤ ታምራለች እና ታሳሳለች _ የኔ ሰው። ምን ዋጋ አለው፤ የሆነ በአዳ ተይዛ ልትወስድ ቀጠሮ የተያዘላት መሰለችኝ። መልሴን አልጠበቀችም ጉንጬን ሰማኝ ወደ ሥራዋ ተመለሰች።

ከደቂቃዎች በኋላ ቤቱ በእጣን ደመና ተውጦ፤ ቡና ፈልቶ፤ የሙና እጅ የሚያስቀረጥም ዓይነት ብዙ ምሳ ቀራረበ። ለሙና የተለመደው የፍቅር ውሎ፤ ለእኔ የሽኝት ፕሮግራም የመሰለ ሰመመናም ምሳ።

ቡናው እንዳለቀ የተቀመጥኩበት መጥታ ተቀመጠች፤ እጄን እንሰታ ሳመችኝ (ለየው ነገር ሲጀምር...)

"ለምን እንደምወድህ ታውቃለህ ?" ጠየቀች ሙና።

"በደንብ ነዋ !" መለስኩ ኮራ ብዬ። ሳቋን አዘጋጅታ ጠየቀችኝ፤

"እሺ ንገረኝ"

"የድሮ ፍቅረኛሽን ስለምመስል" ቤቱ ውስጥ ያለው ትራስ ሁሉ ተወረወረብኝ። ድብድባችን ጀመረ፤ ሞቅ ካለ ሳቅ ጋር። ሆን ብላ ሰውነታችን እንዲነካካ ታደርጋለች፤ ጡቶቿ ደረቴ ላይ ይጨፈለቃሉ፤ እና "ተሜንከኝ" ትላለች። ይታያችሁ ሳይንስ ሲገለበጥ፤ እሷ እኮ ከላይ ናት እና ታሜንከኝ (ገብቶናል)። አንድ የገረመኝ ነገር፤ ሙና የማትወደው ነገር ቢኖር ልፊያና ድብድብ ነበር። ጫፏን እንኳን ለቀልድ ቢነኳት ታብዳለች። ቢቃ ሰውነቷ የፈንጂ ቀጠና ነበር። ይሄው እኔ ጋር እኔ ፈንጂ አምካኙ፤ የራሴንም ስሜት የሰውም ባሕሪ አምክኜ ሰላፋት።

መሽ !! "ቀኑ ጨለመብኝ" ያሉት አበው እንደዚህ ዓይነቱን ቀን ሳይሆን አይቀርም። ስናወራ፤ ስናወራ (ምን ስናወራ እንደነበር እኔ'ጃ) ብቻ የመኝታ ቤት ሰዓታችንን ለማሳጠር ብዙ ሳልለፈልፍ አልቀረሁም።

"አብርሽ አንቅልፌ መጣ" አለች ትልልቅ ውብ ዓይኖቿን እያንከባለለች (እኔኔ እንቅልፍ ሲመጣ እንደዚህ ነው እንዴ ? ይህቺ አይነቷ መስለምለም የሌላ ጉዳይ ናት)

"ትንሽ እናውራ ናፍቀሽኛል"

"ከመቼ ጀምሮ ነው ወሬ የወደድከው ግን ?" አለችኝ። ትዝ ሲለኝ ለካ ለሙና ዝምተኛ ልጅ ነበርኩ (ሰምንተኛው ሺ አሉ እኚያ ሰውዬ)። እጄን ይዛ እየጎተተች ወሰደችኝ። መኝታ ቤት እንደገባን መሬ ሜዳው ላይ ቆማ ልብሷን በቁሟ ብትጥለው ማታ እኔ መኝታ ቤት ፀሐይ ፏ ብሎ ወጣ። ፀሐይ ከምስራቅም ከምዕራብም ሳይሆን፣ በቃ ከልብስ ውስጥ ፍንትው ብሎ ወጣ። እስቲ አሁን እዚህ ዐለይ ላይ ቆሞ የማይፍታታ ወንድ የት አባቱ ሄዶ ሊፍታታ ነው ? ሲጀመርስ ምናባቱ ሊሰራ ወደዚች ምድር መጣ ? ቀስ ብዬ ልብሴን ማወላለቅ ጀመርኩ። አወላለቄ ከመንቀርፈፉና ከፍርሃቴ ብዛት፣ "ልብስህን አውልቅና አርባ ጅራፍ ትገረፋለህ" የተባልኩ እንጂ ውብ ፍቅረኛዬ ጋር ልተኛ የምዘጋጅ አልመሰልም ነበር። የእሷ ልብሱን ወደታች ገፈፍኩት፣ ብርድ ልብሱን፣ አንሶላውን፣ መቃብሬን የምቆፍር ነበር የመሰለኝ።

ቀስ ብዬ አንሶላዬ ውስጥ ገባሁና (ሙና ገና ከመግባቴ እንደ መኾርገር ተለጠፈችብኝ - ምን አስቸኳይት ሰመርዶ) አንሶላና ብርድልብሱን ወደላይ ስቤ ስደርብ የመቃብር አፈር በላዬ ላይ የመለስኩ መሰለኝ።

"ውይ አፈንክኸኝ" የተሸፋፈንበትን ብርድ ልብስ ገለጠችው። ገብቶኛል በነዛ ዓይኖቿ እየተስለመለመች የፈራሁትን አጀንዳ ልትከፍት ነው። ተንጠራርቼ መብራቱን አጠፋሁት፣ ትልቅ ስህተት ! ሙና መብራት ሲጠፋ በብርሃን የፈራሁትን በጨለማ ልዘምትበት መስሏት የበለጠ ተጠጋችኝ። ሰውነቴ ላይ ከመጣበቋ ብዛት ሁለት ሰውም አንድ ሰውም ሳይሆን ግማሽ ሰው መሰልን። አንድ እግሯን በታፋዬ ላይ ደርባ ተጠመጠመችብኝ። አሁን እንግዲህ ... እርማጊዶን !!

"እና ለምን እንደምወድህ ሳልነግርህ አረሳሳኸኝ" ሙና በጨለማው ውስጥ አንሾካሾከች።

"ለምንድን ነው ?"

"ርጋታህ ! ማንም ወንድ እዚህ ድረስ ይታገሳል ብዬ አስቤ አላውቅም። ስምቼም አላውቅ። ልዩ ነህ እብርሽ ... ላሟ" (ምኔን እንደሳመችኝ እኔ'ጃ) እኔኮ ግራ የሚገባኝ ካለሥማችን ስም እየሰጡ ሰምን ጨዋ ያደርጉናል ?! ኧረ የቸገረ ቸግሮን ነው ቀዝቀዝ ያልነው (ለስካሁን ለገር ሰላም ቢሆን በሩጫ ምፃል ደርሰን ነበር አሉ ጋሽ ምትኩ)። ስለጋሽ ምትኩ ማሰብ ጀመርኩ። ጋሽ ምትኩ በሕፃንነታችን ሰፈራችን ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የድሮ ወታደር ናቸው። ቆይ ግን ጋሽ ምትኩ የሚማቸው አበቃቀል አይገርምም ? ልክ እንደ ፍየል ፂም ሹጥጥ ያለች ሆና ደረታቸውን ትነካለች። ጋሽ ምትኩ እኮ በሕፃንነቴ ከእማማ

ሊበናስ ፅድ ላይ ወድቆ የግራ ክንዷን ተሰብሮ አሽተው አድነውናል። የግራ ክንዴ ስል ትዝ አለኝና ላነሳው ስሞክር ሙና ተኝታበታለች። ሙና ትዝ አለችኝ። አሁንም እንጉቴን እየሳመችኝ ነው። ሙቀቱ ሙቀት አይደለም። እሳት ተነስቷል እዚህ ብርድ ልብስ ውስጥ። (ደመወዜን የሚከፍሏት እሳት ነው እንዴ፤ አጠራቅማ ይዛው መጥታ ይሆን...)

ቆይ ግን የዓለም ሙቀት መጨመር ... ብዬ ሌላ ሐሳብ ውስጥ ልገባ ስል ድክ.....ም ባለ ድምፅ የሆነ መከከለኛው አፍሪካ አካባቢ ቆማ ስሜን የጠራችው እስኪመስለኝ በራቀ ድምፅ...

"አ...ብርሽ" አለችኝ።

"አብርሽ የለም ! አሁን ወጣ" ማለት አምሮኝ ነበር።

"እ"

"እወድሃለሁ" ውይ ! ይሄ ሁሉ ጥሪ ለዚች ነው ? ብዬ መውደዷን ሳንኳሰስ ብሞክር አልተሳካልኝም።

"እኔም እንደ ራሴ ነው የምወድሽ ሙና" ብዬ ዓየር አስኪያጥራት ከንፈሯን ሳምኳት። እግሯ ተንቀሳቀሰ (ወዶት ነው...ባለህበት ቁም ብያለሁ የሙና ግራ እግር !) እንግዲህ ፊት ሲሰጧቸው...

በእንግሊዝኛ እንዲህ አለችኝ፣

"አር ዩ ሬዲ ?" እንደው አማርኛችን መሲብ ላይ ሐሞቷ የሚፈስሰው ለምንድን ነው ? ወሲብ ነክ ነገር ላይ እንግሊዝኛ ይቀለናል። "ሴክስ" "ኪሲንግ" - ቋንቋችን መከበር አለበት ! በራሳችን ቋንቋ የራሳችንን ጉድ ማውራት አለብን ! የራሱ ጉዳይ ... ! አሁን በዚህ ሰዓት አማርኛ ፣ ምንኛ ላይ ምርምር ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው ? ቁም ነገሩ በአማርኛ ይሁን በእንግሊዝኛ ይሁን በጀርመንኛ ወላ በእብራይስጥ ትናገረው እኔ እንደሆንኩ ለንትንጓላይ የለሁበትም !!

እንግዲህ ሙና ከመጠጋቷ ብዛት አልፋኝ መሄድ ቀራት፤ እኔ ዝም !

ሳመችኝ

ዝም

ነካካችኝ

ዝም

እፍ እውጥታ "ቢቃ እናድርግ" አለች

ዝም !

በመጨረሻ ሰውነቷን ከሰውነቴ ቀስ አድርጋ አላቀቀች። ሰውነታችን ሲላቀቅ ፕላስተር ከሆነ ነገር ላይ ሲላጥ የሚያሰማውን ዓይነት ድምፅ አሰማ። ላባችን አጣብቆን ነበር። ምንም ላልተፈጠረ ቅጡ ያጣ ሁሉ ላብ በከንቱ። መና ተንጠራርታ መብራቱን አበራችውና ቀጥ ብላ ፊቴን ተመለከተችኝ - አቤት ስታስፈራ፡ አቤት ስታምር...

"ምንድን ነው የሆንከው ስለኔ የሰማኸው መጥፎ ነገር አለ ?" አለችኝ በሚንቀለቀል ቁጣ። ዝም ብዬ አየኋት። ዝም ብላ አየችኝ። ፊቷ ላይ ግራ መጋባት ይሁን ፍርሃት ያልገባኝ ስሜት ያንዣብባል።

"ሌላ ሴት ጋር ጀምረኸል አይደል ግልፁን ንገረኝ ?" ቁጣዋ ተንቀለቀለ። እኔ ደግሞ አፌ ተያዘ - ዝም፡ ብርድ ልብሱን በንዴት ገፍፋ ወደዛ ጣለችውና ቤቱን በሚያደበላልቅ ጩኸት፣

"ምንድን ነው ችግርህ፣ ለምን ትዘጋኛለህ ... ላንተ እንዲህ መሆኔ ለሁሉም ወንድ እንደዚህ የምሆን ልክስክስ እንድመስልህ አድርጎህ ነው ወይስ ... ለምን ትገፋኛለህ፣ ለምን ዝቅ አድርገህ ታየኛለህ - አንድ ቀን እንደ ሰው፣ እንደ ፍቅረኛ አይተኸኝ አታውቅም። ሁልጊዜም ሴትነቴን፣ ክብሬን ባዶ ዝቅ አድርጌ ላንተ ነው የኖርኩት። ሰንት እና ሰንት ርቀት ተሰቃይቼ የምመጣው አንተን ብዬ ነው፡ ምንድነው ችግርህ ንገረኝ፣ አስጠላሁህ ? ያስቀየምኩህ ነገር አለ ? ለምንድነው እንደዚህ ቅዝቃ የምትለው ? ችግር ካለ ንገረኝ። ልርቅህ አልፈልግም፡ አፈቅርሃለሁ ... አፈቅርሃለሁ ... አፈቅርሃለሁ' እንባዋ ተዘረገፈ። ከወገቤ በላይ ራቁቴን እንደሆንኩ አልጋው ላይ ተቀመጥኩ። መና ሁሉም ሰውነቷ ተራቁቶ ነበር። የአልጋ ልብሱን ሳለብሳት ስሞክር ከነእጄ ወደዛ ወረወረችው፤ ፈራኋት። ተፋጠጥን!

አሁን ነው ጊዜው ! እውነት እርቃኗን አልጋ ላይ ይቻት ! ይህ ጊዜ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ መሻ ጊዜ ነው። አለ አይደል ላይመለሱ በስደት ከአገር ሲወጡ ዞር ብለው ተራራ ሸንተረሩን፣ ያደጉበትን ሰፈር የሚመለከቱባት ቅፅበት። መና ለእኔ ሰፈሬ ናት፤ ፍቅር እየተራጨሁ በፍቅር ያደግሁባት፡ አ አይደል የደከመች እናት በመጨረሻ እስትንፋሷ ከአልጋ ላይ ሽቅብ ልጇን ተመልክታ በተስፋ መቁረጥ ዓይኖቿን የምትጨፍንበት፣ አለ አይደል አብሮን የተፈጠረ አብሮን ያደገ የኖረ እግር፣ እጅ በበሽታ ምክንያት ሊቆረጥ የመጨረሻው ማደንዘዣ ሲሰጥ ... ይሄ ጊዜ ያ ሁሉ ነው። በዚህች ቅፅበት ሰተ

ብትጄር ሴት ትተካለች አይባልም። ሙና ሴት ብቻ አይደለችም። ማንም ሴት ሳፈቀራት ወንድ መልዓክ ለምትሆንባት ነገብ አለች። ማንም ሴት በአካል የማይደገም ግልባጩን ልብ ላይ የምታትምበት ቅፅበት አለ። ጣጣ የለኝም የሚለውና የምትለው ሰዎች ሁሉ ጣጣ የሚኖርባቸው፣ ውጋት የሚለቅ ቅፅበት አለ. ይሄው ያ ቅፅበት።

ሙናን ወደኔ ስቤ ከንፈሯን ሳምኳት። የሆነ በቀል የሚመስል አሳሳም። ልቧ ሳይፈራ አልቀረም። በፍርሃት አየችኝ። ፊቴ ላይ ምን እንዳየች እንጃ።

"ሙና"

"ወ_ይዬ አብርሽ" ፈርታለች። ለምን እንደፈራች አላውቅም። ብቻ አንድ ነገር መኖሩን የጠረጠረች ይመስለኛል።

"ስንፈተ ወሲብ የሚባል ነገር አለብኝ፣ ሴክስ ማድረግ አልችልም። በጣም ብዙ ቦታ በዘመናዊም በባሕልም ሕክምና ለማድረግ ሞክሬ ነበር፤ ግን አልቻልኩም። ልለይሽ አልፈልግም፤ አፈቅርሻለሁ። አንቺን ብለይሽ ምን እንደምሠራ፣ ምን እንደማደርግ አላውቅም። የማውቀው ሥራ ነው፤ ከሥራ ሌላ አንቺን። ቢቃ ! ያልነገርኩሽ እንዳትለይኝ ስለፈራሁ ነበር። አሁን ግን አማራጭ የለኝም። በዚህ ወር ከመምጣትሽ በፊት የተቻለኝን ሁሉ ሞክሬያለሁ። ምንም ለውጥ የለውም። እውነቱ ይሄው ነው" ስል ነገርኳት። የራሴ ድምጽ ለራሴ እንኳን አስፈርቶኝ ነበር። ይሄው እውነቱን ተናገርኩ ! እንግዲህ "መንገድ ይመራሃል" የተባለው እውነት ይሄውለት መንገደኛው !!

ሙና ዝም ብላ በግርምት ሲታዳምጠኝ ቆየችና ድከም ባለ ድምፅ "አብርሽ" አለችኝ። አብርሽ ብቻ፤ እንዲሁ ስሜን ማረጋገጥ እንደፈለገች ዓይነት። ዓይኗ ውስጥ ግን ምንድነው የማየው ... ደንግጣለች ? ፈርታለች ? ወይንስ ምንድነው ይሄ ወልጣቃኝ አይታ ?

"ሁልጊዜም እንደ ሩቅ ሰው አጠገቤ ሆነሽ ትናፍቂኛለሽ። ሰውነትሽ ይናፍቀኛል። ግን ምንም ማድረግ አልቻልኩም። እኔ ታጋሽ አይደለሁም ሙና፤ ስላልቻልኩ ነው። እኔ ምንም ትዕግስት የለኝም። ስላልቻልኩ ነው። አፈቅርሻለሁ፤ እንዲህ ሞራሌ ተንኮታኩቶ ተሸማቅቄም አፈቅርሻለሁ።" ሙና ፀጥ ብላ በግርምት ይሁን በሐዘን ሲታየኝ ቆየች። አንዴ ወደዛ አንዴ ወደዚህ ዓይኖቿ ቃበዙ። ተደነጋገረች። ዓይኖቿ በእንባ ተሞሉ። እንባዋ ሊዘረግፍ ነው ብዬ ስጠብቅ፤ ዓይኗን የሞላው እንባ ድራሹ ጠፋ። ተጨነቀች። ተናግራ እንዳታሳዝነኝ ፈርታ፣ ዝም ብትል ይሄ እንደ ጥቁር ጭስ የሚያፍን

መርዶ ቃላትን ከአንደበቷ እንደ ባል አስፈንጥራሽ አውጥ እያላት፣ ሙና የኔ ፍቅር ተጨነቀች። የጉን ፊቷ ላይ አረበበ። የማደርገው ጠፋኝ። ትንፋሿ እሳት መስለው ቀሉ። ብዙ ጊዜ ስታፍር ነበር እንዲህ የሚቀሉት።

"ቆይ አብርሽ ምንድን ነው … ማለቴ… ተወው ቢቀ" ግራ ተጋባች። እናም እንዲህ አለችኝ፣ "ችግር የለውም እንዳታስብ፣ ምንም ነገር እንዳታስብ!" ስትናገር ዓይኔን ማየት ፈርታ ነበር። ጸጉሯ እስከ ቁንጆ ጣቶቿ በሆነ ፍርሃት ሲንቀጠቀጡ ይታዩኛል። ብርድ ልብሱን ከጎኔ ገልባ ሾርተት ብላ ገባች። ወዲያው ተመልሳ ተነሳችና የሌሊት ልብሷን ከትራስኔ በኩል አንስታ ለበሰች፤ ተመልሳ ተኛች። ድንጋርብ ወጥቶ ነበር። በብርድ ልብስ ቢታፈን ድምፅ "ችግር የለውም" አለች እንደገና።

"ሙና" አልኳት ጀርባዋን ስጥታኝ ነበር የተኛችው። ልክ ሰይጣን የጠራት ይመስል ድንግጥ ብላ፣

"እ" አለችኝ። ድንጋጤዋ እኔንም አስደነገጠኝ።

"ይቅርታ እስካሁን ስላልነገርኩሽ"

"ችግር የለውም ! ይሄ ማንንም ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው እንተኛ።" አነጋገሯ ምንም ለዛ የሌለውና የሸሸት ይመስል ነበር፤ ዝም ላለማለት ያህል። ተኛች፤ እንቅልፍ የወሰዳት መሰለኝ። ልነካት ፈራሁ። የሆነ እተኛንቷ ራሱ ትንሽ ከሰውነቴ ራቅ የማለት ነገር ነበረበት። ይሰማኛል እባብ የሆነ ነፋስ በመሐላችን በተፈጠረ ሰርጥ መሰያየት ሲባብ …

ተነስቼ ከአልጋዬ አጠገብ ያለ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ። ከፊቴ ትንሽ ጠረጴዛ አለች፤ መፃፍ ሲያምረኝ ከመኝታዬ ተነስቼ የምፅፍባት። ለምን ያህል ጊዜ እንደተቀመጥኩ እንጃ፤ ሙና በእንቅልፍ ልብ ስትንቀሳቀስ ብርድ ልብሱ ተንሸራትቶ ግማሽ አካሏ ተራቆተ። ህልም የሚመስል ቀይ ሰውነት፣ ከውስጡ ብርሃን የሚያመነጭ ሙሉት ያለ ሰውነት፤ ውብ ሰውነት። …በዚህች ቅፅበት ውስጤ በቅናት አረረ። የማላየው የወንድ እጅ እዚህ ሰውነት ላይ ሲያርፍ አሰብኩ። የሙና ሰውነት የደረቀ መሬት መስሎ ተሰማኝ። ውሃ የናፈቀ፣ የተቃጠለ፤ ማንም መቼም ቢዘንብበት ምጥጥ የሚያደርግ ምድረበዳ፣

ዝም ብዬ እያታለሁ። ልቤ ታፍኗል። መረረኝ፣ ሕይወት አስጠላኝ። ሙና ስዕል ብትሆን ብዬ ተመኘሁ። የትም የማትሄድ፣ ለዘላለሙ እዚሁ ተቀምጣ የማያት ስዕል፣ የምትታይ ብቻ። የስዕል፣ የማጥም፣ የዘፈን … የሁሉም ጥበብ መነሻ አለመቻል መሆኑ የገባኝ እዚህች ነጥብ ላይ ነው። ሰው አለመቻሉን ሲገልፅ መግለጫው መንገድ ላይ ይጠበብና ጥበበኛ ይባላል። ሰው በአካል ያልደረሰበትን

ጥማ ነው በጥበብ እጆቹ ተንጠራርቶ ለመንካት የሚፍገመገመው።

ሙና ተንቀሳቀሰች። ብርድ ልብሱ ሙሉ ለሙሉ ወደ አንድ ጎን ተሰበሰበ። በስስ የሌሊት ልብስ፣ ሰውነቷ ፍም መስሎ ቀልቷል። እዛጋ ሆና እዚህ ያለሁ እኔን ወላፈኗ ፈጀኝ። "እንቁልልጭ የምታጣትን ልጅ ተመልከት ... እንዴት ውብ እንደሆነች እይ" የሚለኝ ሰይጣን ጭንቅላቴ ውስጥ የተቀመጠ መሰለኝ።

አየኋት ... ትክክክክ ብዬ አየኋት። ሕሊናዬ ትልቅ ሸራ ሆኖ መንፈሴ በማይጠፋ ቀለም ሙናን እየሳለ ነበር። ልቤ ትልቅ ብራና ሆኖ ሙናን እየፃፋት ነበር። ከወንበሬ ተነስቼ የሙናን የእግር ጣቶች ተራ በተራ ሳምኳቸው፤ አስሩንም። የተለኮሰ የሲጋራ ጫፍ የሳምኩ ይመስል የእግሮቿ ጣቶች ከንፈሬ ላይ ረመጥ ሙቀታቸውን አተሙት። ደግሞ የእግሯ ልስላሴ ! ወደ ቦታዬ ተመለስኩ። ብርድ ልብሱን አላለበስኳትም፤ ላያት ፈልጌያለሁ።

ወንበሬ ላይ ቁጭ ብዬ ሙናን ስመለከታት የገጣሚ ኤፍሬም ስዩም ግጥም ልክ ጎረቤት እንደተከፈተ ዓይነት ከነድምፁ ጥርት ብሎ እንደ ጅረት ውኃ አዕምሮዬ ውስጥ ይፈስስ ጀመረ። ያውም በዓይኖቼ ሞልቶ በሚፈስስ እንባዬ ታጅቦ። ሶሊያና የእኔ ኑዛዜ ... የማጥም አልፋና ኦሜጋዬ ... እያንዳንዱ ግጥም የኑሮ ዝባዝንኬ ድንጋዩን ቢጭንበትም አለ ጊዜ እንደ ክርሰ ምድር ውኃ የሚፈነዳበት። ገጣሚው እዚህ ተቀምጦ ሙናን እየተመለከተ የፃፈው አስኪመስለኝ፣ ሶሊያና የሙና የቤት ስሟ፣ የመኝታ ቤት ስሟ አስኪመስለኝ ... ገጣሚው የእኔን ሙሾ በደረቀ ሌሊት አወረደው ...

ሶ ሊ ያ ና

*እኔን ከወንበር ላይ፣*

*ቀን ያየሁት እንባ*

*ቀን ያየሁት ደባ*

*እንቅልፍ አሳጥቶኝ፣*

*ወረቀት ላይ ወሰዶኝ.....*

*እርሷን ካልጋችን ላይ፣*

*እንቅልፍ አሸክርምሟት፣*

ቀን ያየኘው ሁሉ በቅዠት አልፎላት፣
እኔ ከቃላት ጋር ጦርነት ገጥሜ፣
በሰው ልጆች ጭንቀት ላይም ተዳክሜ፣
በሌሊት ጭንቀቴ የቀን ሲቃይ ሳበርድ፣
ከደጋው ሐሳቤ በረሃ ስሰደድ፣
አንባን በፊደላት፣
ፊደልን በቃላት፣
ቃላትን በሐሳብ፣
ወረቀት ላይ ልወልድ፣
ወረቀት ላይ ፅፌ ወረቀቱን ስቀድ…
እንዲህ እየፃፍኩኝ እያሰብኩኝ ሳለሁ፣
"የኔ ነሽ" የምላት "ያንተ ነኝ" የምትል፣
ፍቅሬ ስሊያና ተናገረች መሰል በቅዠቷ መሃል…
"ተመልከት ወዳጄ እኔም ካሊጋዩ ላይ፣
አንተን በመናፈቅ በስሜት ስሰቃይ"
ቀ…ና ብዬ ባያት እውነት አለው ቃሏ፣
ፍም መስሏል አካሏ፣
ከሌሊት ልብሰቿ ጡቷ ሾልኮ ወጥቷል፣
እጇ ተዘርግቶ አግሯ ተከፋፍቷል፣
እኔን በመጓጓት ደሟ ተቆጥቶ፣
ፍቅሯ ተሰውቶ፣
ስሜቷ ተጎድቶ፣
አንዳች ነገር ሊይቶ እንደፈራ ሕፃን፣

ፊቷ ሲሸማቀቅ ፀጉሯ ሲበታተን፤

ካሊጋው ላይ ተፅፎ ያየሁት እውነቷን፤

ፍ ቅ ሬ  ሶ ሊ ያ ና  እወራችኝ መሰል በቅዝቷ መሃል ...

ኣስተውል ወንድሜ...

ባንተ የቀለም ቅብ በድርሰትህ ዓለም፤

የሰዎች ጥላ እንጂ አካላቸው የለም!

ባንተ ከንቱ ድርሰት በወረቀትህ ላይ፤

የሰው እንባ ሳይሆን ያንተው ነው የሚታይ፤

በሌሊት ትጋትህ በድርሰት በግጥም በቀለም ሸራህ ላይ፤

እኔ ውብቱ ነኝ በፍቅርህ ስሰቃይ...

ይህ ሁሉ ቢሆንም!

ይህ ሁሉ ቢሆንም... ወደህ እንዳትመጣ፤

በሌሊት ትጋትህ ሐዘን ሳይቀጣ!

በኔ ያልጋ ድርሰት ቅፀበታቶች አሉ፤

ከየሰዉ ዓለም የሚመሳሰሉ፤

ባንተ ቀለም ሸራ በድርሰትህ ፅሁፍ!

ዘመን ይታየኛል እኔን የሚያሳልፍ!

ይህ ሁሉ ቢሆንም...

የሰዎችን እንባ አትቁፍ ግዴለም!

የፍጥረትን ሐዘን ስለህ አትዘለቅም!

እውነት አለው ብለህ ሐዘንን አታልም!

((ያለቀሱም ሰዎች ሐቀኞች አይደሉም))

ይልቅ የኔን ስሜት!

*ያንተንም አንባዎች ሁለቱን አሳየኸኝ፣*

*በድርሰት*

*በግጥም*

*በቀለም ሸራህ ላይ እኔን ብቻ ሳለኸኝ! እኔን ብቻ ፃፍኸኝ!*

*"ያልተደሰተች ቤት" በሚል መጽሐፍህ*

*ዘ ላ ለ ም  አሻገርኸኝ፣*

*ዘ ላ ለ ም  ውብደኸኝ፣*

*ዘ ላ ለ ም  አኖርኸኝ!!"*

*"የኔ ነሽ" የምላት፣ "ያንተ ነኝ" የምትል፣*

*ፍቅሬ ሶሊያና ተናገረች መስል በቅዠቷ መሃል።*

ቁሞ ያልኩበት ወንበር ላይ እንቅልፍ ወሰደኝ...

## ክፍል አስራ አንድ

ሊነጋጋ ሲል...

"አብርሽ" የሙና ድምጽ እንደ ህልም ተሰማኝ። ዓይኖቼን ስገልጥ ራቁ ቆማ ነበር። ልብሷን ለባብሳ፣ አንድ እርምጃ የሚሆን ከእኔ ራቅ ብላ ቆማ ነበር። ሙና ስትቀሰቅሰኝ እንዲህ አልነበረም። ከተኛሁበት የምትቀሰቅሰኝ በከንፈሯ ነበር። በተኛሁበት ስትስመኝ ነበር የምነቃው። እና አዛሬ ምን አቆማት? ሁሉን እንቅልፍ ባበረሳው በደበዘዘ አዕምሮ አያታለሁ።

"ተነስ ቁርስ ሰርቼልሃለሁ"

በዝምታ እንቁላል ፍርፍር በላን፣ ሻይ ጠጣን፤ (በዝምታ) ዕቃዎቹን አነሳስታ አጣጠበች እና መጥታ

ን ተቀመጠች። ሁለታችንም በአስፈሪ ዝምታ ውስጥ በዝምታ እንደተቀመጥን ድንገት የሙና እንባ ተዘረገፈ፤ እናም አቀፈችኝ። ከሙና እንዲህ ዓይነት ጉልበት ያለው እስተቃቀፍ አልጠበቅኩም ነበር። ጥብቅ ! አውቄያለሁ ሙና እየተለየችኝ ነው። ተነሳች ... በርሳዋን አነሳች ... ፊም ብላ አይታኝ ወደ በሩ አመራች፤ ከፍታ ስትወጣ አላየኋትም።

እስከ ምሳ ሰዓት ከተቀመጥኩበት ሳልንቀሳቀስ ቁጭ ብዬ፡ ምንም ሳላስብ፡ ምንም ሳላይ ምንም ሆኜ ቆየሁ። የሆነ የመሬት ስበት የሌለበት ሕዋ ላይ እንደመንሳፈፍ ዓይነት ስሜት።

"ቻው ሙና" አልኩ ቁርስ ሰዓት ላይ የወጣችውን ልጅ ምሳ ሰዓት ላይ ... ቻው !

በሕዋ ላይ እየተንሳፈፍኩ ሥራ እሄዳለሁ፡ እመጣለሁ፤ እሄዳለሁ፡ እመጣለሁ ... ከሙና ጋር ከተለያየን ...1...2...3...4...5...6...7... ወራ ት ! "ግን ምክንያቱ ያለያይ ነበር እንዴ ?" እላለሁ አንዳንዴ። ሙና ቢያንስ የእኔ ችግር አለመሆኑን አውቃ፡ "እንዴት ሆንክ አይዞህ" አትለኝም እንዴ ? እላለሁ። ቅዳሜ ሁልጊዜ የምትመጣ ይመስለኛል። ሁልጊዜ ከመኝታ ቤት ስወጣ ሳሎን ተቀምጣ የማገኛት ይመስለኛል። ሙና አለመደወሏ ይገርመኛል። ለድፍን ሰባት ወራት ስልኬ ሲጮህ ሙና እንደምትሆን እርግጠኛ ሆኜ አነሳው ነበር። ሙና ግን ተወችኝ !! (ተወችኝ ቃሉ እንዴት ያማል) ስልኳን ከሄደች ከሳምንቱ ጀምሮ እሞክር ነበር፤ አይሰራም - ቁጥር ቀይራ ይሆናል።

*** **** ****

ከሙና ጋር ከተለያየን ከዓመት ከምናምን በኋላ ሃኒባል እንዲህ አለኝ፤ "አብርሽ ከሌላ ሰው ሰምተህ ከምታዝን ራሴ ልንገርህ ብዬ ነው"

"ምንድን ነው"

"ሙና ልታገባ ነው። ነገ እሁድ ነው ሰርጓ። አልደነገጥኩ፤ አልተከፋሁ፤ አልተደሰትኩ፤ አላዘንኩ !! ደንዝዤ !!

"እና ይሄ ምኑ ያሳዝናል" አልኩት ሃኒባልን።

"እ ? ሙና እኮ ነው ያልኩህ" አለ በግርምት እያየኝ።

"አይገርምም ደገምኩለት ! የፍቅረኛ ሌላ ሰው ማግባት የመጨረሻው ጭካኔ የሚመስላቸው

የሚጨረሽ የዋህ ሰዎች አሉ። በፍቅር ውስጥ የሚጨረሸው ሀቅታ _ ጀርባን መስጠት ነው። መና ጀርባዋን ስታሳኝስት። በእርግጥ አውነት አላት፡ መሳ ሰሙሳ እኔ ችግር ውስጥ ነኝ። መና ጀግና ሰው ናት። ስለዚህ መሚዘዙ እርሜኝም ሰሜትነም ማብስ ነው፡ ደግ ጃደች ! እንዲንም ሰቀም ነገ አበቃት። ቢቃ ! መና ድል ባለ ሰርግ አገባች። የበርጃ ቀን እዚህ ብሌሩዊ መናፈሻ ውስጥ ተቀምጬ ዝም ብዬ ያንን የድንጋዩ አንበሳ ሳየው ቀልኩ። 'አንበሳው አንበሳ ቢሆንበትም የበላው ብር አንኳ ያስመስለዋል' አሉ እሉ ነው። ወንድነታችን ወንድ ቢሆንም ወንድ ለመምሰል ያቃጠለ ጊዜ ወንድ ስለመሰለናል። ማእበረሰብ የከፈለልን የምራልና የቢሕል ዋጋ ወንድ ያደርገናል _ ተቀሳሌ ቀን !! ቢኢትዮዉት ውስጥ እንዲህ አይር ድኒ በሚያስበለ ሽንፈት ያለሆን ሁሉ ተነጥቀህ በዶሀ ሐውልት ሆነህ ሐውልት ፊት የምትቀመጥበት ጊዜ አለ። ያው ሐውልቱም የራሱ ታሪክ አለው፡ አገር የሚያውቀው። እንተም ታሪክ አለህ ማንም የማያውቀው፡ ብቻህን የሚያንገበግብህ። የእኔና የዚህ የአንበሳ ሐውልት አንድነታችን ሁለታችንም የምንመስለውን አለመሆናችን ነው። እሱም አንበሳ እኔም ወንድ አይደለሁም፡ መምሰል ብቻ።

## ክፍል አስራ ሁለት

አንዲት የመና ጓደኛ አለች ሐዋን የምትባል። ከጥቁረቷ ብዛት የመና ጥላ የምትመስል። ጀበና ሐዋ ጎን ቢቀመጥ ጠይም ይባላል። ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ የመሰለች። ድሮ አንዲን ብዙም አልቀርባትም ነበር፡ ከመና ጋር ከተለያየን ጀምሮ ግን መና ስትናፍቀኝ አገኛታለሁ። አንዳሁ የጋራ ጉዳያችን መና ሆነ።

"መና ደህና ነች ?" አልኳታለሁ።

"ደህና ነች"

"በሐይሌ ሲመታት ፈዳን ያምታት ነበር፡ አሁን እንዴት ነች ?"

"ደህና ናት ! ባሏ መኪና ገዝቶላታል፡ በሐይሌ የት ያገኛታል ብለህ ሃሃሃሃ"

"ማንስትሬሽን ላይ ስትሆን በጣም ነበር የሚያማት አሁን እንዴት ሆና ይሆን ?"

"ኣይ አብርሽ ! እሱማ ያው በየወሩ ነው አይቀየር ነገር፤ ስትወልድ ይተዋል ይባላል ... ባይ ሀ ቋይ ሙና እርጉዝ ናት !" ልቤ ላይ የሆነ ነገር ሲሰካ ይሰማኛል። አገባች ሲባል ምንም ያልተሰማኝን፤ ልክ እርምህን አውጣ ዓይነት መርዶ ይመስል ይሄንኛው አመመኝ፤ በጣም አመመኝ።

"ከመቀሌ ወደዚህ ለመምጣት ቅያሬ ጠይቃ ነበር ተሳክቶላት ይሆን ?"

"ጠይቃ ነበር እንዴ ? እኔ ይሄንን አላወቅኩም ... አሁን ግን ሥራ አቁማለችኮ" አለችኝ በማርምት (ምን አስገረማት)። በቃ ስለሙና ጥግብ እስክምል አጠይቃታለሁ፤ ሳትሰለች ታወራኛለች። መተንፈሻዬ ነች ሔዋን። በጣም ተቀራረብን፤ ቤቷ ሁሉ ወስዳኝ ቡና ታፈላልኛለች። መቼም መድረሻ ቢስ ሆኛለሁ። ሙና ከሄደች በኋላ ለጎተተኝ የምጎትት ከርታታ ዘባተሎ ነገር ... የት ነበርክ ብባል እዚህ የማልል...። የቱንም ያህል ጥብርር ያላችሁ ብትሆኑ፤ ሰው ለዓይኑ የሚናፍቃችሁ እንኳን ብትሆኑ፤ የሆነ ጊዜ አለ እንደምናምንቴ የትም የምትገኙበት፤ ምነው በዛህ የምትባሉበት ...

አንድ ቀን ታዲያ ሔዋን ቤት ሄደን ከተደረደሩት ሲዲዎች አንዱ ላይ ዓይኔ አረፈ። የሙና የሰርግ ቪዲዮ ! እንድትከፍትልኝ ሔዋንን ጠየቅኳት። እንገራግራ ተለምና በመከራ ከፈተችልኝ። ሙናዬ የኔ ቆንጆ እንዴት ነው ያማረችው በእግዚአብሔር ! ባሏም ቆንጆ ኃብታም ነው። እንደኔ ኮሳሳ ሳይሆን የሆነ ግርማ ሞገስ ያለው፤ በጣም ነው የሚመጣጠኑት ! ቀናሁ፤ አደገኛ የበታችነት ስሜት ደቆሰኝ። ቪዲዮውን እያየሁ ነው፤ ባሏ ለቤተዘመዱ ዲስኩር እያሰማ ሙና ከጎኑ ቆማ በአፍረት ትሽኮረመማለች (ስትሽኮረመም ስታምር !)

እና የሙና ባል በኩራት እንዲህ አለ፤ (እጁን የሙና ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ ... የእኔ ትከሻ ላይ እጁ ያረፈ ያህል ከበደኝ)

"ከሙና ጋር የዛሬ (((ሦስት ዓመት)))) ፍቅር ስንጀምር፣ ለእኔ የከፈለችውን መስዋትነት ባትከፍል ኑሮ ለዚህ ቀን ባልበቃን ነበር። እኔ መቀሌ፤ እሷ አዲስ አበባ ሆነን ((((ለእኔ ስትል ቅያሬ ጠይቃ መቀሌ ድረስ መጣች))))። የፍቅር ጀግና ናት ሙንዬ" ... ታዳሚው አጨበጨበ ጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟ ጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟ ጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟጟ

ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አብርሽ ምኑ ሰው አማች...እንደ እብድ ነው የሳቅኩት።

አስታወስኩ...አንድ ጊዜ መቀሌ ሄጄ የሙና ቤት አከራይ፤ "ደህና ዋልክ አክሊሉ" አሉኝ። ወደ እርሳቸው ዞር፤ "የኔ ነገር ያንዱን ስም ከአንዱ ሚጋጩት" ብለው ሳቁ። የሙና ባል አክሊሉ ነው ሥሙ !

ተቀበል አዝማሪ ...

እረ ሙና ሙና ሙና አቶብኑኝ!

ሲቃ ገደለችው ወንዱን ሲጅ ሲቲት !

አሁን ሰሜን ደቡብ ምን ያሰኝዋል ሰው፤

አሁን ቆላ ደጋ ምን ያሰኝዋል ሰው፤

እንዴት ዞሮ ማየ እንትቱን ያጣል ሰው!

እንዴት ማስተዋየ ዓይኑንስ ያጣል ሰው፤

ያጣል ሰው...

ያጣል ሰው... ሚሊየን ጊዜ እስከ ምፅዓት ድገመው !

አንድ ሰው አራት የሚሆንበት ምናይነት ዘመን መጣ ?! ይሄ የሰርግ ቪዲዮ አይደለም። ስምንተኛው ሺ በራችንን እያንኳኳ መሆኑን የሚያረዳ "ዶክመንተሪ" እንጂ !! ቱ ! አፈርኩ እግዚአብሔርን - አፈርኩ ! ሐፍረቱ አሸማቀቀኝ። ቅናት ሳይሆን ሐፍረት ! የዛሬ ሦስት አመት ማለት እኮ ከሙና ጋር በፍቅር ያበድንበት ጊዜ ነበር። አንዲት የባንክ ሰራተኛ ከመቀሌ አዲስ አበባ በአውሮፕላን ስትመላለስ ብሩ ከየት መጣ እንዴት አላልኩም ...ቱ ! አፈርኩ በራሴ ! አንዲት የባንክ ሰራተኛ የወርቅ ሃብል ገዝታ ስትሰጠኝ እንዴት ብሩ ከየት መጣ አላልም፤ ይሄው አንገቴ ላይ የለማዳ ውሻ ሰንሰለት መስሎ - ቱ ! አንዲት የባንክ ሰራተኛ ከአዲስ አበባ መቀሌ ተቀይራ ስትሄድ፤ "ምንም እቃ አላንዘፋዝፍም እዛው የሚያስፈልገኝን እገዛለሁ" ስትል፤ ቤቷ በውድ ዕቃዎች ተሞልቶ ስመለከት 'እንዴት?' አላልኩም ... ቱ!

እኔ ደግሞ፤ "እንዳንተ የሚታገስ ወንድ አይቼ አላውቅም" ስትለኝ ካየችው ማወዳደሯን በምን አባቱ ጠርጥሬ። ሰው ትንሽ እንኳን ምልክት ሳይታይበት ጣናን የሚያህል የፍቅር ሐይቅ ፍቅረኛው እፍንጫ ስር ተደብቆ ይገድባል ? ኧረ ገረመኝ፤ ከምር ገረመኝ ! የሆነ ፀሐይ ወርዳ እዚህ አራት ኪሎ ላይ ለሁለት ወንድ ይካፈላል እንዴ። አሺ እኔ ያጎደልኩባት ነገር እንዲህ የበቀል ብትር የሚያሰነዝር ነበር ? ... በቀል ይሁን ምናባቴ አውቃለሁ ? እንደው ምን እንደምለው ቸግሮኝ እንጂ ...

ሐዋን ቀስ ብላ መጥታ ጎኔ ተቀመጠች - ሐዋን የሙና ጓደኛ። እናም ትካሻዬ ላይ እጇን ጣል አድርጋ

"ባከሽ አሏን ተያት" አቅፍ አቅፍቅፍ ... አቅፍፍቅፍቅፍ !! ያልታቀፈበት ዘመናችንን ቀይ የሙና ገላ በጥቁር የሔዋን ገላ መቀያየሩ አሏጋ ላይ የተዘረፈ ቅኔ ነገር ነው ... ይነጋል ይመሻል እንደማለት !

"እ ን ተ አ ፈ ን ከ ኝ ሂሂሂ" ሔዋን የሙናን ፍቅረኛ በፍቅር አሸንፋ ራሷን የድል ማማ ላይ አስቀምጣ ተፍነሸንሻለች። የሙና ባል እኔን አሸንፎ፣ ሙናም እኔን አታልላ በብልጠት አልፋኝ እንደሄደች ሳይሰማት አልቀረም። እኔም ደስ አላለኝ አልከፋኝ፤ እንደው ደርበብ ባለ አብሮነት ዝምታን መረጥኩ። ለምን ደስ ይለኛል? ማፍቀር ተኮላሽቶ ወንድነት ስለቆመ? እንዲህ ዓይነቱን ደነዝ ወንድ የሚያመርተው፣ ደነዝ ክህደት ... በሙና ሆነ!! መቼም ቢሆን ለፉ አልላትም፤ ምክንያቱም አፈቅራታለሁ።

# በክራንችና ጭብጨባ የቆመ ወንበር...

ወደ ሰፈራችን የምትወስደው ፒስታ መንገድና ዋናው አስፓልት የሚገናኙበት ቦታ፣ ልክ መጋጠሚያዋ ላይ በግራ በኩል የአበራ ድንጋይ አለች !! የአበራ መቀመጫ ናት። "ውድድር የሌለባት ወንበር" ይላታል አበራ ራሱ። ከሷ ላይ አይጠፋም !! ድንጋይዋ የአክሱምን ሜፍ የምትመስል ግማሽ ኩብ ሆና ስሯ መሬት ውስጥ የገባ ስለሆነ አክሱምን እስከ አንገቱ ቀብር አናቱ ላይ የተቀመጠ ነው የሚመስለው አበራ !!

አንግዲህ አበራ ታዋቂ የሰፈራችን 'የኔ ቢጤ' ነው። አንድ እግር የለውም። ለዚህ ሰው ሳንቲም ሳይሰጡ ማለፍ ከባድ ነው !! የመብራትና የውሃ ወርሃዊ ክፍያ ሲመጣ ድንኳን አስጥለው ሐዘን ሲቀመጡ የሚታጣቸው አባባ ገዳሙ እንኳን አበራ አጠገብ ሲደርሱ ስድስት ኪሳቸውን ፈትሸው (ሁለት የሱሪ ኪስ፣ ሁለት የኮታቸውን የውጭ ኪስ፣ አንድ የውስጥ ኪስ እና አንድ የደረት ኪሳቸውን) ሰባተኛዋ በደርያቸው ኪስ ውስጥ የሚያገኟትን አስርም አምስትም ሳንቲም ሳይሰጡት አያልፉም።

ይሄንን የአላፊ አግዳሚ ፍቅር (ከሳንቲም ጋር) ያገኘው በሚለምንባቸው አስገራሚ የልመና ግጥሞቹና ስመፅዋቾች በሚያበረክተው ምርቃት ነው። የአበራ ምርቃት እንደደረሰኝ ይቆጠራል !! ማንም ሳንቲም ወርውሮ ሊሄድ ቢል፣ "ጋሼ ደረሰኝ ረስተሃል" ብሎ መፅዋቹን እየተከተለ ይመርቃል !!

በልመና ግጥሞች ላይ የመመረቂያ ፅሁፉን የሰራው የሰፈራችን ምሁር ተመስገን (የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሽዮሎጂ ምሩቅ እና በአሁኑ ሰዓት የኮልኮሌ ሆቴል ገንዘብ ተቀባይ ሆኖ እየሰራ ያለ) የአበራን የልመና ግጥሞች በሦስት ይከፍላቸዋል፣

ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ በማለት፣

ኢኮኖሚያዊ ግጥም ብሎ ከፈረጃቸው መካከል አንዱ እንደሚከተለው ነው፣

ደብቀው ቢያኖሩት፣

ብሩም እንደ 'ሰልቫጅ' ዋጋው ይቀንሳል፣

ሊደሃ ቢሰጡ በሰማይ ያንግሳል ...!!

ማሕበራዊ፣

ይደኸያል እንጂ ይለብሳል ድሪዮ...

ሰው ባለበት አገር እንዴት ሰው ይሞታል፣

የሰው ፍቅር አጥቶ...

ፖለቲካዊ...

ሳገሬ ሰጠኋት አንድ እግሬን እንስቼ፣

በእጅ ነው የሚኬደው ይሉት ወግ ሰምቼ...

ሳገሬ ሰዋሁት አንድ እግሬን አንስቼ፣

በብረት ይተካል ይሉት ወግ ሰምቼ...

አበራ ሊድፍን 20 ዓመት እዚህቹ ቦታ ላይ በልመና ቆይቷል (በቀደም ሃያኛ ዓመቱን ምክንያት በማድረግ 20 ቁጥር ሻማ አብርቶ በልዩ ሁኔታ ሲለምን ነበር) አንድ ቀን ታዲያ ለዓመቱ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ውሎ ሲመለስ አንድ ጠጉረ ልውጥ ግዙፍ የኔ ቢጤ እዚች ድንጋዩ ላይ ቁጭ ብሎ ልመናውን ሲያጧጡፍ አገኘው።

በሰውዬው ድፍረት ተበሳጨ አበራ !! ራቅ ብሎ ሰውዬውን ከነአስቀያሚ ድምፁ እየታዘበ፣ "ይሄ ሰው ልመና ተሰጥኦው አይደለም" አለ።

ምን አበራ ብቻ የመንደሩ ሰው ተበሳጨ - ደነገጠ። የመንደሩ ወሬ ሁሉ የአበራ ወንበር ሆነ። ሐየ ዓመት

የተሰመነበት ድንጋይ በአንድ አዳር ለሊላ ለዛ ቢስ ልመና መዋሉ መንደርተኛውን ደስ አላሰኘውም። የመንደሩ ሰው፣ እስካሁን ለአበራ የመፀወትከው በቂ ነው የተባለ ይመስል ለአዲሱ ሰው ሰባራ ሳንቲም የጣለለት አልነበረም - ከአኔ በስተቀር። እኔም ሐሳብ ውስጥ ገብቼ ሳንቲሟን ከወረወርኩ በኋላ ነው አበራ አለመሆኑን ያወቅኩት። በአስፈሪ ድምጹ በወረወረው፡ "ጠላትህን ይወርውረው እንበሳዬ" በሚል ምርቃት።

አበራ ወደ ሰውዬው ተጠጋና፣ "ጌታው ማን ፈቅዶልህ እዚህ ተቀመጥክ" ቢለው፣

"ማን ይፈቅድልኛል ... እግዜር ፈርዶብኝ ነው እንጂ" አለ ፀጉረ ልውጡ። አበራ ተበሳጨ።

"በል ተነስና መሄጃህን ፈልግ ይሄ የኔ ቦታ ነው" አለው።

"የቱ ይሄ ድንጋዩ..." አለ ሰውዬው በማናናቅ።

"ሰውዬ በሕግ አምላክ የከፉ ቀን ማረፊያዬን አታናንቅ ... ከፉ ደግ ያየሁበትን ሀልወናዬን ... ራቴን ... ወንበሬን ... የሕዝቤን መገናኛ መድረኬን - ድንጋይ አትበል"

ፀጉረ ልውጡ አበራን በግርምት እያየ፣ "የባርላማ ወንበር አስመሰልከው እኮ ወንድሜ" አለ።

"አንተ ነህ እንጂ እንደ ባርላማ ወንበር መቀመጫዬን በጉልበት ጨምድደህ አልለቅም ያልከው..."

"ወዲያ አታላዝንብኝ..." አለ ሰውዬው በቁጣ።

ንትርካቸውን የሰማው መንደርተኛ ቀስ በቀስ ከበባቸውና ፀጉረ ልውጡን ሰው ያመናጭቀው ጀመረ፤ "እሱ አካል ጉዳተኛ ነው፤ ደግሞ ቦታውም ነው ... ለኛም የለመድነው የኔ ቢጤ ይሻለናል..."

"ማን ያልተጎዳ አለ፣ ሁላችንም ውስጣችን ቢታይ አልቀናል። ባገራችን ድንጋይ ላይ ለመቀመጥ የግድ መፈለጥ፣ መቆረጥ አለብን እንዴ እንዴዴዴ" አለ ሰውዬው ኮስተር ብሎ። ቀጠል አድርጎም፣ "እንደው እዚች አገር ሁሉ ነገር ቀድሞ በያዘ ሆነኮ ጎበዝ፣ ምናለ አንዳንዴ አዲስ ነገር እየተቀበልን መንፈሳችንን ከዝገት ብንከላከል..."

ከርከሩ በተጧጧፈበት ቅፅበት አበራ ገላጋዩን ተገን በማድረግ አንካ ቅማሰ ብሎ በከራንቹ ሰውዬውን ትከሻው ላይ ነረተው። ያ የገደል ሰባሪ የሚያህል ሰውዬ በድንጋይ ጨረሰን ብሰን ስንፈራ ድሪቶውን

እየጎተተ እግሬ አውጭኝ አለ...

ከረዥርም ጊዜ በኋላ ያንን ሰው ስድስት ኪሎ ልብሱን ጥሎ ከጣውላ የተሰራ ከራንች ይዞ አየሁት፤ "መራመድ አይችሉም ብለን ከራንች ብንሰጣቸው ተራማጁን መደብደቢያ አረጉት..." እያለ ብቻውን ያወራል። እኝኑ ነው የሚደጋግማት።

ማታ ወደ ሰፈር ስመለስ አበራን ወንበሩ ላይ አየሁትና ጠጋ ብዬ በቀልድ፣ "አቤ ... ያ ሰውዬ ካንተ የበለጠ ከራንች ይዞ ወደዚህ ሲመጣ አየሁት" አልኩት። ከራንቹን መሽረፕ አድርጎ የቀልድ ሰነዘረብኝና፣ "ከኔ የበለጠ ከራንች ከያዘ ከእኔ የበለጠ ተጎድቷል በለኛ" አለና ተሳስቀን ለየን ... ሳንቲም ወርውሬለት .. ምርቃቱ እየተከተለኝ ... "አነሰም አበረም ከራንች አጠገብህ አይድረስ..."

አንድ ቀን ታዳያ ዝነኛው ዘፋኝ፣ "ተውረግረጊ የኔ ቆንጆ" ለሚለው ዘፈኑ 'ክሊፕ' ሊሰራ ወደ መንደራችን መጣና የአበራን ግጥም በተመሰጦ ቆሞ አዳመጠ። ከሱ የዘፈን ግጥሞች የተሻሉ ግጥሞችን ከአበራ በመስማቱ ተደምሞ ለአበራ አስር ብር በመመፅወት እንዲህ ሲል መከረው፣

"የግጥም መክሊት ውስጥህ ይታየኛል ... አጭርና ዜማቸው ከመልዕክታቸው የተሰናሰለ ... ግጥሞች ውስጥህ ... እ ... ይመረታሉ ማለት ይቻላል። ዋናው ነገር ...እ... ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ተጠንቀቅ. ጭብጨባን በ....ጣም ተጠንቀቅ" ብሎት ሄደ።

አበራ አስር ብሯን ወደ ኪሱ እያስገባ ብቻውን ያወራ ጀመር፣ "ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ? አጨብጭበው ወታደር ቤት ላኩኝ ... አጨብጭበው ጠላት ጋር አፋለሙኝ ... አጨብጭበው ፈንጂ አስረገጡኝ .. አጨብጭበው እግሬን አሳጡኝ ... አጨብጭበው ጡረታ አስወጡኝ ... ሃሃሃሃሃሃሃሃ ከዚህ ሁሉ የጭብጨባ የጥፋት ውኃ በኋላ ሰላማዊ ጭብጨባ እንጀራዬ በሆነበት ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ይሉኛል ... አጥፍተው እንዳትጠፉ ይላሉ..." ብሎ የተቆረጠ እግሩን እየተመለከተ ድንጋዩ ላይ እንደተቀመጠ በሐሳብ ጭልጥ አለ...

ከሩቅ ያለች ሙዚቃ ቤት፣ "ተውረግረጊ የኔ ቆንጆ" የሚለው ዘፈን ይሰማል...

"ቾብ ቾብ አርጉላት ዳሌዋ ይውረግረግ፣

ጭብጨባ አይደለም ወይ የሴት ሁሉ ማገረግ"

ጓደው ሴቱን በጭብጨባ ሲያጠፉት — ጭብጨባ እንዳያጠፋችሁ ከማለት ጭብጨባችንን እንዳትሸጡ አይሉንም ታዲያ አለ አበራ ከእንቅልፉ እንደተነሳ ሰው ከሐሳቡ ብንን ብሎ።

በንብቶ በቴሌቪዥን ከሊፑ ላይ፣ ‘ተውረግራጊዋ ቆንጆ ለአበራ ሳንቲም ልትመፀውት ጎንበስ ስትል ከማጀራው የተራቆተ ታፋዋን ከጉልህ መቀመጫዋ ጋር የሚያሳይበት ትዕይንት ተከተቶ ነበር። የልጅቱ ስፊ ዳሌና ራቁት ታፋ የአበራን ከራንች፣ የድንጋይ መቀመጫና የተቆረጠ ቀኝ እግሩን ከልሏቸው ነበር !!

# ባለ ዋሽንቱ ሰማዕት

የመሥሪያ ቤታችን ጥበቃ ጋሽ አባተ ሰላምታ ሲሰጡኝ ከሰላምታቸው ቀጥሎ ሃያ ጊዜ መድፍ የሚተኮስ ይመስለኛል። ገና ሲያዩኝ ቀኝ እግራቸውን እስከ እንብርታቸው ያነሱና ቁልቁል እያምዘገዘጉ አውርደው በወታደር ጫማቸው በሲሚንቶ የተለሰነውን ወለል ያጓስሙታል ! ገ......ጭ !! በቀን አስር ጊዜ ቢያገኙኝ በቀን አስር ጊዜ ገ......ጭ ! ይች ምድር መቻም ቻይ ናት። ወላ በወታደር ጫማ፣ ወላ በነጠላ ጫማ፣ ወላ በባዶ እግር ብትወቀጥ፣ ብትወገር ዝም!! እኔ እርግጫው ለበዛበት ወለል እንዲሁም ለጫማቸው እዝኜ እና ደግሞ ለዚህ ዓይነት ሰላምታ ምላሹ ሁልጊዜ ስለሚያደናግረኝ ወደሳቸው እግር አላበዛም።

ዛሬ ታዲያ ቢሮዬ ለሆነ ጉዳይ ጎራ አሉ (ላጋነው እንጂ ... ? እሺ !) ከጠረጴዛዬ ፊት ለፊት ያንን መዓተኛ ሰላምታቸውን ሲሰጡ እግራቸውን ሲያነሱት ጆሮዬንም፣ ዓይኔንም ልደፍን አሰብኩ፣ ለሁለቱም ሳልደርስ ገ...ጭ !!!!!!! ጭ ጭ ጭ ጭ ... ጠረጴዛዬ ላይ የተቀመጠው ቀን መቁጠሪያ ባስነሱት ንፋስ ተገለባብጦ ሚያዚያ ላይ የነበረው ገፅ፣ ቀድሞ ግንቦት ላይ ተገኘ። ግንቦት ሐያ በቀይ ደምቋል - ሥራ የለም (ማለት ሥራ ላላቸው ሥራ ዝግ ነው)። ስፒሎች ጠረጴዛው ላይ እንደ ሰፌድ ላይ ቆሎ ተንቀረቀቡ፣ ወረቀቶች በእርጋታ ተንቀሳቀሱ። ጋሽ አባተ ገና ሳይቀመጡ፣ "ጉዳያቸውን ጨርሰው ሲወጡ ይሄን ሰላምታቸውን ይደግሙብኝ ይሆን" ብዬ አሰብኩ።

ወታደሮች ሰላምታቸው እንዲህ ኃይል የሚበዛበት ለምንድን ነው። ዞሮ ዞሮ ሰላምታውን የሚያቀርቡት ለወዳጅ ነው። ሰላምታ ከእጅ ወርዶ እንዲህ በእግር ሁሉ መሬት እስኪደቃ በሚደረግ እንቅስቃሴ መደረጉ ሰላምታ የሚያቀርቡለትን ሰው ብትፈልግ በሰላም፣ ካልሆነም በነገር ምከረኝ የሚል መልዕክት ያዘለ ይመስለኛል።

ጋሽ አባተ ሰላምታቸውን ጨርሰው በተጠንቀቅ እንደቆሙ የመጡበትን አሳወቁኝ። በእውነቱ አገራችን

ኢትዮጵያ ተሻሽላለች። እኔኮ ቢሮዬ መጥተው በመድፍ ቀረሽ ሰላምታ ሲያሸብሩኝ ልክ እንደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ደርጎች ቤተ መንግሥታቸው ድረስ ሄደው እንዲህ ዓይነት ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ወረቀት መዥረጥ አድርገው፣ "ለእርስዎ ደህንነት ሲባል ወደተሻለ ቦታ እንዲዘዋወሩ ተወስኗል" እንዳሉት፣ ጋሽ አባተም 'ለእኔ ደህንነት ሲባል ከሥራዬ መባረሬን' (መፈንቅለ ሥራ መደረጉን) ሊያረዱኝ ነበር የመሰለኝ !

እሳቸው ግን በወታደራዊ ሰላምታ መንፈሳዊ መልዕክት አቀበሉኝ፣ "አቶ አብረሃም ለሚመጣው መድኃኒያለም እቤቴ ዝክር ስላለ ከባለቤትዎት ጋር መጥተው ጠበል ጠዲቅ እንዲቀምሱልኝ በማክበር ጠርቼዎታለሁ"። ይሄ ሁሉ መድፍ ቀረሽ ሰላምታ ለሌላ ሳይሆን ለሚመጣው ሃያ ሰባት ቤታቸው ዝክር ሊጠሩኝ ነው ! አነጋገራቸው ቆፍጠን ስላለ ነው መሰል፣ "ከባለቤትዎ ጋር" ሲሉኝ ያገባሁ መሰለኝ !

ነገረ ሥራቸው ዘና ስላደረገኝ እንዲቀመጡ ጋበዝኳቸውና ቡና ለሁለታችንም አዘዝኩ። ከዛ ወግ። ፊት ለፊት የተከፈተው ቴሌቪዥን ናሽናል ጂኦግራፊን ያሳያል። አንድ ነብር አንዲት ሚዳቋ ያሳድዳል። አሯሯጡ የሚሮጥ ሳይሆን የሚበር ነበር የሚመስለው። ጋሽ አባተ ቡናውን እንደያዙ ነብሩ ላይ ተመስጠው ቆዩና፣ አፋቸውን ጠርገው፣

"አቶ አብርሃም ነብር እኮ ጉድ ያለው ፍጥረት ነው..." አሉ።

"እንዴት"

"ካልደረሱበት አይደርሰማ"

"አሁን ሚዳቋዋ ደርሳበት ነው የሚያሳድዳት" አልኩ ፈገግ ብዬ።

"ሃሃሃሃሃሃሃ እነሱማ በይና ተበይ አርጎ ፈጥሯቸው ምን መደራረስ ያሻቸዋል። ግና ነብር ሰው ጋር በፍቅር ይኖራል። አያቴ ነብር ነበራቸው ... ያውም ሁለት ! ሃዲያ አጎቴ ዋሽንት ሲጫወት ለብቻው ነው ... ወፍ ከሰማይ ያወርዳል ... መኔ ይቀሰቅሳል ... የድሮ ጠላትህ ሳይቀር ነው ትዝ የሚልህ ... ነብር ደሞ ዋሽንት ይወዳል"

"እ" አልኩ ሰምቼ ስለማላውቅ ገርሞኝ።

"መድኃኒያለምን ! ነብር ዋሽንት ከሰማ ኩተፍ ነው። ዋሽንት ተጫዋቹ እግር ሥር እንደ ድመት ቁጭ

ብሎ በትዝታ ራሱን እየነቀነቀ ንቅንቅ ሳይል ይውላል..."

"ሰምቼ አላውቅም ይሄንን"

"አዎ እኔም ያወቅኩት አጎቴ ሲሞት ቀብሩ ላይ ነው" አሉና ተከዙ።

"ባለዋሽንቱ አጎትዎ ናቸው የሞቱት ?"

"አዎ"

"በምን ምክንያት ሞቱ"

"በዚሁ በዋሽንት ጠንቅ"

"እንዴት" አልኩ የበለጠ ለወሬ ጓጉቼ።

"አንድ ቀን ከብት ከሚያግድበት ሜዳ ቁጭ ብሎ ዋሽንት ይጫወታል። አጎቴ ደሞ ጥሎበት ዋሽንት ሲጫወት ዓይኑን ጨፍኖ ነበር። ተጫውቶ፣ ተጫውቶ፣ ተጫውቶ፣ ተጫውቶ ፋታ ሊወስድ አረፍ ሲል ከጎኑ አንድ ነገር ጎኑን ነካ ነካ ... ቧጨር ቧጨር ... ቧጠጥ ቧጠጥ አደረገው ... ዞር ቢል አህያ የሚያህል ነብር እንደ ደህና ወዳጅ ጎኑ አረፍ ብሎ በፊት እግሩ ነበር ለካስ የነካው"

"በስመዓብ ... እሺ" የእውነት ገርሞኝ ነበር።

"ከዛማ አጎቴ ገርሞት ሲያፈጥ እንደገና በእግሩ ዋሽንት የያዘ እጁን ነካ አደረገው፣ 'ምን ነካህ ተጫወት እንጂ አታቋርጥ' ማለቱ እኮ ነው። አጎቴ ነብር የጠራ ችሎታው አኩርቶት እንደገና ዋሽንቱን አነሳና አስረቀረቀው። ነብሩም፣ አጎቴም ዓይናቸውን ጨፍነው በዋሽንቱ ድምጽ ተመስጠው ቆዩና ዓይናቸውን ቢገልጡ ሌላ ነብር ተገትሮ !! ይሄኛው ደግሞ ከመጀመሪያው ይገዝፋል። አጎቴ ደነገጠ። ዋሽንት መጫወቱን ሲያቋርጥ ነብሮቹ በቁጣ ያጉረመርማሉ። አጎቴ ታዲያ እንዳይጫወት ደከመው፣ እያቋረጠው ነገር የነብሮቹ ቁጣ ... እንደ ምንም ይሄን ዋሽንት ሲነፋ ... ሲነፋ ... ሲነፋ ... ሲነፋ - ድምፁን ቀነስ ሲያደርግ ነብሮቹ ያጉረመርማሉ።"

"ሲነፋ ... ሲነፋ አሁንም ሲነፋ፣ ትዝታ ... አምባሰል ... ባቲ ... ሲነፋ፣ አንቺ ሆዬ ... ሸምንሟይ ... ሽለላ - ጉብልዬ ... የባሕሩ ቀኘን ... የፍሬው ኃይሉን ... የሒሩት በቀለን ሲጫወት መሸ ! 'ብሎ እንግዲህ ወርቁቹ

መቻ ሚስቱ ትሲጋለች ሲሂድ የነገ ሰው ይብለን' ብሎ ሲሄድ ሲነሳ ነብሮቹ የቁምጣውን ጫፍ ለሁለት ከከሰው ጎተቱና መልሰው አስቀመጡት። (የት አባህ ልትሄድ ነው የሰው ትዝታ ቀስቅሰህ እንደማለት) እንደው ምን ቀን ነው ይሄን ዋሽንት የለመድኩት ምነው በቀረብኝ እያለ ሲነፋ ሲነፋ ነጋ !! አሁንም ነብሮቹ ወይ ፍንክች ! ሲነፋ፣ ሲነፋ ልክ አስር ሰዓት ሲሆን ልቡ ጦሽ ብላ እዛው ድፍት አለ ! አይ እትቴ" ብለው ተከዙ።

እጎታቸው መድረክ ላይ የሞተ፣ ለሙዚቃ የተሰዋ ሰማዕት መስሎ ታየኝ !

ወሬውን ጨርሰው፣ ስለቡናውም አመስግነው፣ ፀበሉን እንዳልቀር አሳስበውኝ ፊት ለፊቴ ቆሙና ...ጎ......ጭ ! ቀን መቁጠሪያው ወደ ሚያዚያ ተመለሰ ! እርግጫ የወሰደውን ቀን እርግጫ መለሰው !! ከወዲያኛው ክፍል የጸሐፊዬ ፍሬዘውድ ኮምፒውተር አሁንም ይዘፍናል ... ዘፈን የማይሰለቻት ጉድ ናት ... ነብር አጠገቧ ቆሞ ዘፈኑን እንዳትዘጋ የከለከላት ይመስል ! ለነገሩ ኑሯችን ራሷ እንደ ባለዋሽንቱ የጋሽ አባተ እጎት ናት። በግዳጅ ዘፈናችን ተመልካች 'ደስተኛ ናቸው' እያለን ድንገት ጦሽ የምንል ሚስኪኖች - ከንብል የምንል እንደ ውኃ ! ስንት ነብር አለ ለራሱ ደስታ ጉልበታችንን ሲመጠን የሚኖር። ድፍት ከነዋሽንታችን፣ ከሌትው ከነዘመናት እንጉርጉሯችን። እንደ ቀልድ ለራሳችን የጀመርናትን ዘፈን ለማቆም የሌሎች ፈቃድ ተነፍገን !!

አጀንዳዬን አንስቼ ከቢሮዬ ወጣሁ። ስብሰባ አለብኝ። አለቆቼ ለተሰብሳቢዎች እንድናገር ያዘዙኝ መልዕክት በአጀንዳዬ ተከትቧል። ነብሮቹ በቃ ካላሉኝ መስማት የሚፈልጉትን ዘፈን ስደጋግም መኖሬ አይቀርም። እንግዲህ ስብሰባው ላይ ይሄን ዋሽንት ስነፋ ስነፋ ስነፋ ... በቃ ኑሮ ይቀጥላል ... በባለዋሽንቶችና በነብሮች መንደር። አንዱ አለቃዬ ጠገብ ብዬ ዓይኔን ስገልጥ፣ ሌላው በሌላ ዘፈን ከበላዬ ተከምሮ "ንፋ..." እያለኝ !! በምን ቀን ነው ይሄን ዋሽንት እኔነት የተለማመድኩት ?! ባለዋሽንቱ ሰማዕት እኔም ነኝ፣ ሕዝቤም ነው !! ቁጭ ብለን የሰቀልነውን፣ ቆመን ማውረድ የተሳነን እኛ ... አዎ እኛ ነን።

# ሚስቴን አከሸፏት

"አብርሃም!"

"አቤት!"

"እ...ና ለዚች ተልካሻ ምክንያት ብለህ ነው ሚስቴን ልፍታ የምትለው ?" ስትል ዳኛዋ ጠየቀችኝ። እዩት እንግዲህ ከብርት ዳኛ ቋጥኝ ሴትነቷ ተንዶ ሕዝብና መንግሥት በአደራ የሰጣትን የዳኝነት ኃላፊነቷን ሲጫንባት! እስቲ አሁን ችሎት ላይ የቀረበን የአመልካችን ብሶት 'ተልካሻ!' ብሎ ማጣጣል ተገቢ ነው? አይ መብቴማ ሊከበር ይገባል! ያ...ሌባ ትዝ አለኝ። አንዱ ልማደኛ ሌባ ነው አሉ። ለሠባተኛ ጊዜ ስልክ ነጥቆ ሊያመልጥ ሲምክር ተይዞ ፍርድ ቤት ይቀርባል...፤ ታዲያ ዳኛው በብስጭት፣

"አንተ ልክስክስ ዛሬም እንደገና ሰርቀህ መጣህ ?" ቢሉት ሌባው ኮስተር ብሎ፣

"ክቡር ዳኛ... እንዲህማ አይዝለፉኝ...ደንበኛ ክቡር ነው!" አለ አሉ።

እውነቱን ነው'ደንበኛ' መከበር አለበት። የግድ ጉዳዬ እንዲካበድ ሚስቱን ከሌላ ወንድ ጋር አልጋ ላይ ማግኘት አልያም በገጀራ ጨፍጭፌያት ፍርድ ቤት መቆም ነበረብኝ እንዴ ? ለምን ምክንያታችንን ያናንቃሉ...? ምክንያቱን ያቀል ዘንድ የማንን ምክንያት ማን በትክሻው ተሸክሞ መዝኖታል? ደግሞ ስንት ጊዜ ነው ለዚህች ዳኛ ስለጉዳዩ የምነግራት? ከዚህ በፊትም ደጋግማ ጠይቃኝ ደጋግሜ መልሼለሁ...።

"አይ ምክንያቱ ለእኔ ከበቂ በላይ ነው ክብርት ዳኛ" ስል በትህትና 'ተልካሻ' ብላ ያናናቀችውን ምክንያት ሚስቴን ለመፍታት በቂ መሆኑን ለማረጋገጥ ሞከርኩ። (ክብርት የሚለው ቃል ከብረት የተሠራ ይመስል አፌ ላይ ከበደኝ።)

"እኮ ሚስቴ ካለፍቃዴ ፀጉሯን ተቆረጠች ብለህ የፍች ጥያቄ ይዘህ ፍርድ ቤት ድረስ መጣህ?" አለች ዳኛዋ አሁንም ተገርማ። ምን አስገረማት?

"አዎ!" ስል ኮስተር ብዬ መለስኩ። ዳኛዋም ዝም ! ችሎቱም ዝም ! ሁሉም ሰው እንደእብድ እየተመለከተኝ ነበረ። ዳኛዋ እንደዳኛ ብቻ ሳይሆን እንደሴት መናገር ጀመረች (ዶታዋን ወግና)፤ ሰልችት ያለኝን ዝባዝንኬ የሞራል ወግ...

"ሰማ አብርሃም ! ባለቤትህ እኮ ሕፃን ልጅ አይደለችም። የሚጠቅማና የሚጎዳትን ነገር በሚገባ ራሷ ታውቃለች። ስትቆም ስትቀመጥ አንተን ማስፈቀድ የለባትም። ምንም እንኳን ባሏ ብትሆንም ያገባሀት በባርነት ልትገዛት እና የአንተን ብቻ ፍላጎት ልትሞንባት አይደለም። ይህ ዘመናዊ አስተሳሰብም አይደለም። አንተ ወጣት ነህ፡ የተማርክ የከተማ ልጅ ነህ። በመቻቻልና በመተሳሰብ እንዲሁም እንድናችሁ የአንድኖችሁን ፍላጎት በመረዳት ትዳራችሁን አክብራችሁ..." በለው! ሰውነቷ በእልህ እየተንቀጠቀጠ ምክር ይሁን ግሳፄ ያልለየለት ንግግሯን አንተረተረችው።

አሁን ኩብርት ዳኛ የተናገሩት ነገር እንዲሁ ከላይ ሲታይ ትክክል ይመስላል። ግን ይሄ ሁሉ ዝባዝንኬ በፍትሐብሔርም፡ በወንጀለኛም፡ በቤተሰብ ሕግም ላይ በቀጥታ የሰፈረ አይመስለኝም። ችሎት ውስጥ ሳይሆን የእኛ ሰፈር የሴቶች እድር ውስጥ የቆምኩ መሰለኝ። ለነገሩ ዳኛዋ ሴት በመሆኗ ሲጀመርም ፈርቼ ነበር። በኋላ ሳስበው *ሙያ መቼስ ፆታ የለውም፡ ሴት ዳኛ እንጂ ሴት ዳኝነት የለም፡ ሴት ሐኪም እንጂ ሴት ሕክምና የለም...።* ቢሆንም ፆታው ሙያው ላይ የሚያሳርፈው የራሱ ተፅዕኖ ይኖራል፤ ልክ እንደዚች ዳኛ! ደግሞ"ሚስትህ ሕፃን አይደለችም" ትላለች እንዴ፤ ምነው ችሎቱን የሕፃን ችሎት አደረገችው !

"ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ!" ብዬ ተረትኩ። የተረቱ አንድምታ እኮ ስለሴት አይደለም። ብዙ አዋቂ ሲበዛ ሁሉም ጉዳዩን በራሱ እውቀት ልክ እየጎተተ በቀላሉ ሊሠራ የሚችለውን ነገር ማክረም ይከተላል ለማለት ነው። እንኳንም ተረትኩ። ችሎቱን የሞሉት ሴቶች ናቸው፤ ሚስቴን ጨምሮ (ሚስቴ ስል እንዴት እንደሚቀፈኝ...።)

እስቲ አሁን *ባለቤትህ እኮ ሕፃን ልጅ አይደለችም፡ የሚጠቅማና የሚጎዳትን ነገር በሚገባ ራሷ ታውቃለች...* ማለት ይሄ ምን የሚሉት ከንቱ ንግግር ነው። እንዴት ሴት ለራሷ ይጠቅመኛል ያለችውን ማወቅ ብቻ ሙሉነት ይመስላችኋል። ይሄ እኮ ነው የዘመኑ ችግር። 'ለራሴ አውቃለሁ!' የሚሉት 'ለራሴ የሚጠቅመኝን እኔ አውቃለሁ' ማለት የትዳር አጋርን ፍላጎት ካላገናዘበ የማይረባ መኮፈስ።

ምኑን ትዳር ሆነው ?!

'ሕፃን ልጅ አይደለሁም፣ የሚጠቅመኝን እኔ አውቃለሁ' ብዬ የፈለግኩበት ባድር ሚስቴ ደስ ይላታል? የሚጠቅመኝን እኔ አውቃለሁ' ብዬ ፀጉሬን ሳላበጥር፣ ጥርሴን ሳልቦርሽ ብወጣ ሚስቴ ዝም ትላለች፣ የሚጠቅመኝን እኔ አውቃለሁ' ብዬ የጨርቅ ሱሪዬን እንደጊሾ ካልሲዬ ውስጥ ጠቅጥቄው ብወጣ ሚስቴ ዝም ትላለች... ? በተራ አሸከላለና የሞራል ጩኸት ፍቅር ፀንቶ የሚቆም ሲያስመስሉ ሲቀባጥሩ ይገርሙኛል።

ይሄ እኮ ሁሉም ሴቶች ከሰውነት መንበር የተገፈተሩ ሲመስላቸው ጮምድደው እንዳይወድቁ የሚንጠላጠሉበት የተረት ገመድ ነው ! ትዳር ማለት ራስን ማወቅ ብቻ አይደለም፣ የትዳር አጋርንም ጠንቅቆ ለማወቅ መሞከር ነው። የራስን ፍላጎት ብቻ አንጠልጥሎ ትዳር የለም። እንደዛማ ከሆነ ሁሉም በየራሱ የእውቀትና የፍላጎት አጥር ውስጥ ከመሽገ ምን አብሮነት አስፈለገ።

ይሄው ነው እውነቱ !!

"ክብርት ዳኛ ያሉት ነገር ከእኔ ጉዳይ ጋር አይገናኝም። እኔ ሚስቴ ፀጉሯን በአጭሩ ስለተቆረጠች ሕፃን ናት አልወጣኝም! እኔ ፀጉሯን በመቆረጧ መፋታት አፈልጋለሁ፣ ከእርሷ ጋር መኖር አለፈልግም ነው እያልኩ ያለሁት። ቀድሜ ፀጉሯን እንዳትቆረጥ ነግሬያት ነበር። የራሷን ምርጫ ተከትላለች። እኔም የራሴን ምርጫ እከተላለሁ !! ደግሞስ የቤተሰብ ሕጉ ሚስትን ለመፍታት የግድ ምክንያት መቅረብ አለበት ይላል ? አይልም !! አንድ ሰው መፋታት ከፈለገ በቃ ይፋታል። ስለዚህ ከቦር ፍርድ ቤቱ ጥያቄዬን በመቀበል ፍቺውን እንዲያፀድቅልኝ በማክበር እጠይቃለሁ!!" አልኩ።

"ለመሆኑ ስትፋቱ ያላችሁን ንብረት እኩል እንደምትካፈሉ ገብቶሃል ?"

"እረ በሙሉ ትውሰድ ... ብቻ እንፋታ" አልኩ በምሬት እየተንገሸገሸኩ። ሚስቴ ፊቨን ከኋላ ስታለቅስ (ስትነፋረቅ ነው እንጂ...) ይሰማኛል። ጩኸቱን ቀማችኝ፣ ማልቀስ የሚያምርብኝስ እኔ ! ነጋቸውን የፍቅር እና መከባበር ባሕር ከፊታቸው ተዘርግቶ መሊቃለቅን ይንቁና እንዲህ ነገር ከእጃቸው ሲያፈተልክ በራሳቸው እንባ የጨው ባሕር ሠርተው ነፍሳቸውን ይዘፈዝፋሉ። እንባቸውን ገድበው ቁጭት ያመነጩበት አዛው። እንዴት እንደጠላኋት ! የአባቴንም ገዳይ እንዲህ አልጠላ።

ዳኛዋ በትኩረት ተመለከተችኝ፣ እኔም በትኩረት ተመለከትኳት። ፀጉሯ ባጭሩ ተቆርጦ ደማቅ ወርቃማ ቀለም ተቀብቷል፣ ልክ እንደሚስቴ። ወርቃማ ቀለም ውስጥ ነክረው ያወጡት ቡርሽ ነው

የሚመስለው፤ ችፍርግ! ፊቷ ላይ ልክ የሌለው ጥላቻ ይንቀሳቀሳል። ጠላች አልጠላች በሕግ እንጂ በፍቅር አትፈርድ ድሮስ ! ሕግ አይጥላኝ። ጠረጴዛው ላይ በተቀመጠው መዶሻ እናቴን ብትፈጠርቀው ደስታዋ...። ኧረ ጎበዝ እኔ ስለሚስቴ ፀጉር ማጠር ሳወራ ለካስ ዳኛዋ ስለራሷም ፀጉር ነው የምትሚገተኝ። ግን ሕግ ነውና እንደምንም ብስጭቷን ዋጥ አድርጋ ጉዳዬን በሌላ ጊዜ ለማየት ቀጠሮ ሰጠችን። ሦስተኛ ቀጠሮ መሆኑ ነው። ቆይ ይቺ ሴትዮ በቀጠሮ ብዛት የሚስቴ ፀጉር የሚያድግና ሐሳቤን የምቀይር መስሏት ይሆን እንዴ ? መከሸፍ አይገባትም ...? በቃ ሚስቴ ለእኔ ከሽፋለች !!

ከችሎት ስንወጣ ሚስቴ ከእናቷ (እኔም ማሚ ነበር የምላቸው) እና ታናሽ ወንድሟ ጋር በር ላይ ቆመው ነበር። እናቷን ሄጄ ሰላም አልኳቸው፤ ለእኔ እናት ማለት ናቸው።ወንድሟ በጉርምስና ደም ፍላት ፌጥ ፌጥ ይላል። ከጥንቱም ነገረ ሥራው አያምረኝም፤ ዘመናዊ ወሊጋዳ። እኔን ሰላም ላለማለት ሸፈፍ ሸፈፍ እያለ ራቅ ብሎ ሄደ። ለምን እህቱን እስከትሎ አስከምድር ዋሊታ አይሄድም። መንደር ለመንደር ከመዋል ይሻለዋል። ሚስቴ ፌቨን ዓይኗ እንባ ተሞልቶ ፍዝዝ ብላ ታየኛለች። እኔ ደግሞ በተቻለኝ አቅም ሁሉ እሷን ላለማየት እሞክራለሁ። ፀጉሯን ከተቆረጠች ጀምሮ ሚስቴ ሳትሆን የሆን የተወለድኩበት፣ ያደግኩበት፣ ብዙ ጣፋጭ ትዝታ ያሳለፍኩበትን ሰፈሬን በግሬደር ካፈራረሱት በኋላ የማየው የፍርስራሽ ቁልል መስላ ነው የምትሰማኝ !

ፌቨን በሥልጣኔ ግሬደር፣ በፋሽን ትራክተር ዳግም ላትሠራ ፈራርሳለች !! መፍረስ ቃሉ ያማል ! "እቃቃው ፈረሰ ! ዳቦው ተቆረሰ" ሲባል የልጅ ነገር አይደለም ለካ። ድፍን ዳቦ ላይ ያለው ግርማ ሞገስ፣ ምራቅ የሚያስውጥ ጉምዥቱ ሲቆረስ ከሚኖረው ጋር እኩል አይደለም። 'ያም ዳቦ ይሄም ዳቦ' ማለት የዋህነት ነው። ያ ዳቦ፣ ይሄኛው ሙሉነቱን የሚሸነሽን ስለት ያረፈበት የዳቦ ቁራሽ፣ የዳቦ ፍርፋሪ። ፌቨን የፈራረሰ ሰፈር፣ የተቆራረሰ ዳቦ ሆናለች - ለእኔ። የጎኔ ሽራፊ ሳትሆን ከሙሉነት ጎን የተሸረፈች የዳቦ ሽራፊ። እጠላታለሁ? አዎ ! ቆንጆና በአበባ የተዋበ ግቢውን በግዴለሽነት ያፈራረሰበትን ሰው ማን ይወዳል ?! ፌቨንን በማፈቅራት ልክ ጠላኋት - በቃ !

*"ማናባቱ ያዘኛል ምን የጎበረበት፣*

*በገዛ ትዳሬ ውኃ ብደፋበት"* ብላለች ዘፋኝዋ !

###

አራት ዓመት በፍቅር ቆይተናል፤ ከፌቨን ጋር። እድለኞች ነበርን፤ ለድፍን አራት ዓመት ያልቀዘቀዘ

ፍቅር ነበረን። አስር ደቂቃ አብረን ለመቆየት የአንድ ሰዓት መንገድ አቆራርጠን እንገናኛለን። "ዓይኔን ልየው ብዬ ነው የመጣሁት፣ በጣም እቸኩላለሁ" ብላኝ ሳባችን ሳይደርቅ ወደየመጣንበት። ሳባት እፈልግ ነበር። ርሷ ደግሞ አግባኝት አላገባኋት አያሳስባትም። ቀልቧ የትም እንደማልሄድ ነግሯታል። ቀልቧ ታዲያ ልክ ነበር። ደግሞ ሌላው የእድለኝነታችን ገፅ ሁለታችንም የሚታይ ለውጥ በሕይወታችን እየተከሰተ በሁሉም ነገር ስናድግ ነበር። ፌቨን አካውንቲንግ ተምራ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ሥራ አገኘች። እኔም ልክ ተመርቄ እንደወጣሁ ሥራ ያዝኩ። ትዳር ሲታሰብ አንዳች ኃይል ነገሮችን ያገጣጥማቸዋል (እግዜር እንዳልል የዛሬውን ፍች ሳስብ ፈርቼ ነው...)፣ እናም እንዲህ አልኳት፤

"ፌቢ!"

"ወይዬ" ሁልጊዜ ስጠራት ከዓይኗ ብርሃን ይረጫል። ስሜ ላይ የጨመርኩበት አንዳች ነገር ያለ ይመስል፣

"ላገባሽ ነው"

"እኔ ... አላምንም... አብረን ልናድር ነው?" ብላ ተጠመጠመችብኝ። አቤት ደስታዋ።

በእርግጥ ለሌላ ሰው ይህ አባባሏ ሳያስቀው አይቀርም። ለእኔ ግን የሆነ አስደሳች እና በስሜት የሚገ ነገር ነበረው። አብረን ውለን "ቢቃ ልሂድ" ስትል እንዴት ይቀፈኝ እንደነበረ የማውቀው እኔ ነኝ። አብሮ ማደር የቀለለባቸው ይሄ ተራ ነገር ይመስላቸዋል። ፌቨን ከእቅፌ ውስጥ ቅር እያላት ስትወጣ የዓለም ቅዝቃዜ ሁሉ ወደኔ ይጋልብና አንጀቴ ውስጥ ገብቶ ያንዘፈዝፈኛል። ሸኝቻት ወደቤት ስመለስ ቤቱ ቤት አይመስለኝም፣ በረንዳ።

ለአራት ዓመት በፍቅር ሰንቆይ እንኳን ማደር ምሽቱ ምን እንደሚመስል አብረን አይተነው አናውቅም። የፌቨን እናት ናቸው ምክንያታችን ... የሚገርሙ ሴትዮ ... ልጆቻቸውን ኢታምሹ አይሉም፤ ግን የእናትነት የፍቅር መብታቸውን በትክክል ተጠቅመውብታል። ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ፌቨን ቡና ታፈላላቸዋለች (የቤቱ ደንብ ነው)፣ ሁለት ሰዓት ራት ይበላሉ...ልጆቹ ካልተሟሉ ራት አይበሉም እንደውም ሰዓቱ ካለፈ ልጆቻቸው ቢሟሉም ራት ሳይበሉ ነው የሚያድሩት። ፌቨን ታዲያ ይሄው ነገር ተከትሏት መጥቶ እኔ ቤት ካልገባሁ እህል በአፏ አይዞርም፤ እንግዲህ ፌቨን ርሃብ እንደማትችል አውቃለሁ። ከራባት እንስፍስፍነው የምትለው፤ ዓይኗን እንኳን መግለጥ ያቅታታል! (አቤት ስታሳዝነኝ እንደነበር) ታዲያ እንዴት አባቴ ብዬ ለአራት እዘገያለሁ ...በጊዜ ወደ ቤቱ ጥድፊያ ነው! የፌቨን

እናት ባለነዚህ የማይዛነፉ ሕጎች ልጆቹን የማይዛነፍ የቤት መግቢያ ሰዓት ደንበር አስምረውላቸዋል። ከለአባት ስላሳደጓቸው እናታቸውን እንደ አባትም እንደ እናትም ነው የሚያይዋቸው።

ታዳጊ !! ትዳራችን በሚያስከር ፍቅር የተሞላ ነበር ! እድለኛ ነኝ ያልኩት ለዚህ ነው። ልክ ላንደፍቅረኛ ነበር የምንኖረው። ከቤታችን መውጣት አንፈልግም። ሰውም ወደቤታችን ባይመጣ ደስታችን..እውነቱን እኮ ነው። ከፉ ሆነን ሳይሆን ፍቅር የሚባለው ስካር አልሰከነልንም ነበር። ሰዓት አይቤታንም። ቅድም ነግቶ ቁርስ በልተን ... ምን እንዳወራን ምን.እንደሰራን እንኳን ሳናውቀው አንዳንዴ እንዲያውም ምሳ ሰዓት ሁሉ በየት እንዳለፈ ሳይገባን ብቅ ስንል ማታ ሆኗል። በቃ!! እንዲህ ነበርን እኔና ፌቨን ! "ሁሉም ሲጀምረው እንዲሁ ነው" ይባል ይሆናል፤ ግን ለድፍን ሦስት ዓመት ስንኖር ደስታችን ሳይሸረፍ፣ ሲቃችን ሳይከስም ፍፁም ደስተኞች ሆነን ነበር።

ደግሞ አማረብን እንጂ ! ፌቨን ድሮም ቆንጆ ናት ጭራሽ አበባ መስላ አረፈች። እኔ እንኳን እንድ ሁለት ተበሎ አግንቴ የሚቆጠር ፍጥረት ትንሽ የተገለበጠች ጎድጓዳ ሰሃን የምታህል ቦርጭ ተከሰተችብኝ !

እንደ አዳምና ሄዋን የቀደመ ሕይወትም ትዝታም ሳይኖረን እዚሁ ቤት በዚሁ እድሜ የተወለድን ይመስል ያለፈውን ዓለም፣ ቤተሰብ፣ ጓደኛ ምናምን ሁሉ ሁላታችንም ረሳነው። የፌቨን እናት ይደውሉና፣ "እረ እናንተ ልጆች ድምጣችሁ ጠፋ ...በደህናችሁ ነው ?" ይሉናል።

እኔና ፌቪ ታዲያ ልክ ስልኩ ሲዘጋ፣ "በደህናችን ነው ግን ?" ተባብለን እንሳሳቃለን። ከዛ ፕሮግራም እናወጣለን። በቀጣዩ ቅዳሜ የፌቪ እናት ጋር፣ በዛኛው ደግሞ እኔ ቤተሰቦች ጋር፣ 'እንዴ ከሰው ተለየንኮ' እንባባልና፤ በቀጣዩ ቅዳሜና እሁድ ወፍ የለም !! እንደውም ቅዳሜና እሁድ ማለፉን የምናስታውሰው ሰኞ ነው ! እኛ ሌላ ዓለም ውስጥ ነን !

ሲጨንቃቸው የፌቨን እናት ራሳቸው መጥተው ጠየቁን፤ እና መከሩን፣

"ታፍናችሁ አትዋሉ፣ ወጣ እያላችሁ ይንፈሰባችሁ ፊታችሁ ፈረንጅ የመሰለው ጠሃይ አጦት እኮ ነው ምፃት እንዳይመስላችሁ።" ምን ያደርጋል ምክራቸው ራሱ ነፈሰበት። ምናባቱ ሳድርግ እኔ ራሱ ከቤት ስወጣ ገና ትላንት ከገጠር እንደመጣ ሰው እደናበራለሁ። ቤቱ ይናፍቀኛል ...ፌቪ ትናፍቀኛለች። ሩቅ ለሃገር የሄድኩ፣ የማልመለስ ይመስለኛል። ት ና ፍ ቀ ኛ ለ ች - እንዲህ ዓይነት ትዳር ከመቶው አንድ ነው እሱ። ለምን ግማሽ አይሆንም። የበረከቱ ተካፋዮች እኔና ፌቨን ነበርን።

ሳወራው ያመኛል። ሰዎች የበሰጠ በተፋፋና ቁጥር እንደሰስት መስተዋት ራሳቸውን ከቀላልም

ከከባድም ማፍኑት መብበቅ ይኖርባቸዋል። አንዱ ቻልተኛ ሆኖ ሳት ካለው ፍቅር ሲንኮታኮት ያሰቅቃል። ደግሞ ብቻውን አይንኮታኮትም፤ ጣፋጭ ትዝታንም ይዞ ነው አፈር ድቤ የሚበላው። የጨነገፈ ፍቅርን እንደማሰብ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ምን ሰቆቃ አለ...?

ፌቨንን እወዳት ነበር፣ አከብራት ነበር፣ አፈቅራት ነበር። ትንሽ ነገር፣ ይሄ ነው የማይባል ምክንያት በውስጤ እሳተ ገሞራ የሚያህል ቅያሜ አፈነዳ። "አሁን ይሄ ምኑ ይካበዳል ? እንኳን ለፍች ለተራ ኩርፊያም አያበቃም'ኮ" ይባል ይሆናል። "ያልደረሰበት ግልግል ያውቃል" አሉ።ይሄ ትንሽ የተባለው ምክንያት ለተመልካች ትንሽ ይምሰል እንጂ ፌቨንን ዓይኗን ማየት ድምፅዋን መስማት የጠላሁት በዚሁ ምክንያት ነው።

ፍቺ ፈለግኩ። ምክንያቱም ፌቨን ፀጉሯን በአጭሩ በመቆረጧ ነበር ...!! ቢቃ ይሄው ብቻ ነው ምክንያቴ. ሚስቴ ፀጉሯን በአጭሩ መቆረጧ። የፌቨን ፀጉር ምን ቢሆን ነው እንዲህ ጉድያ ፈላው፣ ጎጇችንስ በሚንቀላቱ ያቆመው ?

###

"ፌቨን!" አልኳት ሚስቴ ፀጉሯን ተቆርጣ የመጣች ቀን፤

"አቤት"አላለችኝም !! እንደ ወትሮዋ "ወይዬ" አላለችም። ፊቴ ላይ የነበረው ጥላቻ ቅስሟን ሰብሮታል። እንዲህ ሙሉ ስሟን ደግሞ ጠርቻት አላውቅም። ሙሉ ስሟን ከምጠራት ሙልጭ አድርጌ ብሰድባት ይሻላታል። በምርጥ ፍቅረኞች መሀል እኮ በሙሉ ስም ከመጥራት የበለጠ ስድብ የለም።በአገራችን አቶ፣ ወይዘሮ ምናምን ከሚባሉት ተቀፅላዎች ይልቅ ስማችን ሲቆናጣ ሐሴት ማድረጋችን ሳይታለም የተፈታ ነው። አቶ ጉልማው ከመባል ጉሌ፣ "ጉልዬ" ብንባልም ደስ ነው የሚለን መቼስ። ፍቅረ - ቅንጦት !

ፌቨን ነገሮች ወዴት እየሄዱ እንደሆነ ገብቷታል። ገና በሰላሙ ጊዜ፣ "አብርሽ አንተ ከምትጠላቸው ሰዎች አንዷ ከምሆን ሞቴን እመርጣለሁ" ትል ነበር። ታውቃለች ስወድም ስጠላም ልክ እንደሌለኝ። ታውቃለች ሳፈቅር ሁሉንም ነገሬን ሰጥቻት የምትረግጠውን የእግሯን ጫማ፤ ከአናቷ በላይ የምትዘረጋውን ግንጥላ እንደምሆንላት። ስወዳት በምድርላይ የዕይታዬ አልፋና ኦሜጋ እሷ ብቻ እንደምትሆን ታውቅ ነበር፤ ቢቃ ፀባዬ ነው። ሳፈቀርኩት እኔን ራሴን ጥቅልል አድርጌ እንደምሰጥ።

አንዳንዱ ሰው "በአምላኬማ አትምጡብኝ" ይላል። እኔ ግን ፌቨንን ሳፈቅራት ከእግዚአብሔር

ከሷ በለጥኝ ርቧን ነበር የምመርጠው። እንደውም እግዜርን ራሱን በፈቪዴማ አትምጣብኝ ባልለው ነው። እግዜር በዚህ ተቆጥቶ ቢያሻው ምድሩን በመብረቅ ይረሰው፣ ከፈለገ ዳግን እሳት ያውርድ እንጂ ከፈቀርኩ እውነቱ ይሄው ነው። ቤቴን ከሩቅ ስመለከተው የሚንቀዠቀዠር መንፈሴ ደብር እንዳየ አማኝ ይረጋጋል። እዛ ደብር ውስጥ የነፍሴ ፅላት ነበረች - ፊሸን !

ፊሸን ሥርዓት ያላት ትሁት ልጅ ነበረች። ደግሞ ሰርዓቷ ሰው አለ የለም ብለው ግራና ቀኝ ዓይተው በሕሻንነሲት ቀሪል፣ በአስመሳይ ጨዋነት እንደሚሰለመለሙ ሴቶች አልነበረም (ሊዲያ ነበር ስማሉት በቃን...)። አንዳንዴ እንዲህ ትለኛለች፣ "ታውቃለህ...! ካንተ ጋር ስሆን ተጨማለቂ ተጨማለቂ ይለኛል ሂሂሂሂ"። እንዲህ ነኝ ሳፈቅር። ራሴን ሳፈቅርኩት የደስታ ማቅረቢያ ሰሐን አደርጌ የምሰጥ። እና ሳፈቅር ጆርጅ ዓለምን አይሰማም። ደግሞ ሁሉ እሷን ነበር የሚመስለኝ። ብቻዋን ያለች ያህል እስኪሰማት ልክ የሌለው ነፃነት ነበራት ፊሸን፤ እናም ጓደኛዋ (ያች ናዚላ ጓደኛዋ) እንዲህ ትላታለች፤

"እናትዬእንቺየንጉዝጓዙ ላይ ገጥሞሻል። ቢደስታ ለሽሽ ብለሽ የፍቅር አንቅልፍሽን ለጥጭሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ"። ስታወራ ዓይኗ ውስጥ መርዘኛ ቅናት አለ። ሳቋ በቡና ቤት በር ላይ ደንበኛ ለመጥራት እንደሚጮኹ የቡና ቤት ሴቶች ዓይነት ሳቅ ነው፤ ምኗም አያምረኝም።

ስለ ጓደኛዋ...

የፊሸንን ጓደኛ አልወዳትም። ቢቃ ሲታይ የሚኮሰኩስ ሰው የለም ? እንደዛ ናት። አባጨጓሬ መንፈስ የለበሰ ነገር ! ድምፅዋ ራሱ ይኮሰኩሳል። ንግግሯ ከቃል ሳይሆን ከአባጨጓሬ የተሠራ ነው የሚመስለው። በተለይ ሳቋ እንደዚህች ልጅ ሳቅ የሚቀፍ፣ እንደዚህች ልጅ ወሬ የሚያቅለሸልሽ ነገር በምድር ላይ ያለ አይመስለኝም። የሆነ ከዓይኗ የሚወጣው የውድቀት ጨረር ሰላም ይነሳል። እሷን ለማየት ትልቅ የትዕግስት መነፅር ያሻል !

'ማሚ' ነው ስሟ። እንደው ሳስበው የሆነ ከብ ስም ይመስለኛል፤ ተመልሶ እዛው ዓይነት። ለማያድግና ሰንዝር እልፍ ለማይል ስብዕና የተሰጠ ሽከርከሪት። ሽከርከሪት የሚያስደስታቸው ሕፃናት ብቻ ናቸው። ያደገ ሰው እልፍ ማለት ያስፈልገዋል። ዞሮ ሲመለከት ከትላንትናው ትንሽ እልፍ ማለት አለበት። ትላንትም ...ትላንት ላይ፣ ዛሬም ትላንት ላይ፣ ነገም ትላንት ላይ የሚቆም ሰው ሌላው ቢቀር ትንሹ ነገር ትዝታ እንኳን በውስጡ የሻገተበት ይሆናል።

ትላንት የሆነ ወንድ ጋር ሰደፈ፣ ዛሬ የሆነ ወንድ ጋር ሳኗጋኖ፣ ነገ የሆነ ሰውዬ...ን ምንትስ ሆቴል ራት

... ዛሬ እንትና ሰርግ ላይ ሚዜ ... ከነገ ወዲያ እከሌት ቀለበት ላይ አጃቢ ... ጠዋት ሳሙና፣ ስቲም ገለመሌ ... ከሰዓት ፀጉር ቤት፤ ከውስጥ የቆሸሸ ሥጋ እንደዶሮ በሙቅ ውሃ ተዘፍዝፈው ስለዋሉ ይጠራ ይመስል። ሕይወቷ እንደዛ ነው። በዛ ሄዳ በዚህ ወጥታ ተመልሳ እዛው። እንዲሁ እንደዞረባት፣ ሳታስበው የእድሜ ሰዓቷ ዞር ዞሮ ሠላሳ ስምንት ሆነ ! ዕድሜ በየትኛውም ደረጃ መጥፎ አይደለም። እንደ ዕድሜ ካለመሆን በላይ በሽታ ግን ምን አለ። ሰው በዕድሜው ገንዘብ፣ ፍቅር፣ ዘመድ፣ ጓደኛ በተለያየ ምክንያት ላያፈራ ይችላል። ግን ለዕድሜው የሚገባ ጥሩ ባህሪ መኖር ማንን ገደለ?

አሁንም በርሳዋን እንጠልጥላ መንደር ለመንደር ከመዞር ሌላ ሥራ የላትም። እንዳንዴ ሳስባት የሰላሳ ስምንት ዓመት ሰይጣን ትመስለኛለች። ዝናብ ጠራራ ሳይል ኮሲ ለኮሲ ሲዞር የሚውል ሰይጣን ! በዚህ እድሜዋም የሚገርም አቋም ነው ያላት። ወንዶቹን እንደ ለማዳ ውሻ ነው የምታስከትላቸው። ሕይወቷም ይሄው ነው፤ ወንድ ማስከተል፣ ወንድ መከተል - ቢቃ ! ሰውነቷ ከብዙ ወንዶች ኪስ በተዋጣ ቁርጥራጭ ሥጋ የተገነባ ነው የሚመስለኝ። የየድርሻቸውን ቢያነሱ 'ማሚ' የምትባል ሴትዮ በምድር የማትኖር ዓይነት !

እንግዲህ የዚህች ዋጋ ቢስ ፍጥረት የልብ ጓደኛ ናት፤ ሚስቴ ፌቨን ! እዚህች ሴትዮ ጋር ተይ ይቅርብሽ አላልኳትም። ቤታችን ስትመጣ ፊት አልነሳኋትም። ቤቱ "ሽቶ" በምትለው ቅርናታም ነገር ሲታፈን፣ ስማቸው ተጠርቶ በማያልቅ መንጋ ወንዶች ተረት ጆሮዬ ሲደነቁር ፊት አልነሳኋትም። ለምን...የምወዳት ሚስቴ ጓደኛ ስለሆነች ! በዛ ላይ ፌቨንን እንደምትቀናባት አውቃለሁ። አስተያየቷ ይነግረኛል። የፌቨንን ፀጉር በእጇ እየነካካች፣ "እኔኮ የሚገርመኝ ከርዝመቱ ብዛቱ" ትላታለች።

የፌቨንን ሰውነት ስትነካ ይቀፈኛል። አብሯቸው በየሥርቻው የወደቀቻቸው ወንዶች መንፈስ ሁሉ ሚስቴ ላይ የሰፈረ ነው የሚመስለኝ።

የሚስቴን ለስላሳና ጠይም ጉንጭ እየነካች፣ "እስቲ አንድ ቀን ስቲም እንግባ፤ እኔ አጋብዝሻለሁ ፌቭዬ! አፈር ስሆን...!" ስትላት ትንፋሽ ያጥረኛል። *አፈር መሆን ከፈለገች ለምን ብቻዋን አፈር አትሆንም።* የኔ ሚስት ስቲም ስላልገባች...።

ከዚህ ሁሉ የሚከፋው ግን ወሬዋ ...! ወይኔ ወሬዋ ! ሰው እንዴት በቅሌቱ 'እንትቴ' ለመባል ይጥራል በእግዚአብሔር። እኔ ጥሎብኝ 'ዋው! እሷ እኮ ተጫዋች ምናምን...' ለመባል ብሎ የሚቀባጥር ሰው ያስመርረኛል።

ሞው እንትናዬ ! እንዴት አባቱ የሚጥም ተጨዋች መሰለሽ ...! ሙድ ያለው ጨዋታው ብትይ፣ የሚወስደኝ ቦታ ብትይ፣ በዛ ላይ አሏጋ ላይ ሂሂሂሂሂሂሂሂሂ" አፏን እስከመጨረሻው ከፍታ ታሽካካለች...። ይህቺን ሴትዮ ሳስባት ከእናትና ከአባት ሳይሆን እንደሙጃ ሕይወት ይሉት ዝናብ ዘንበባት ድንገትሜዳ ላይ ብቅ ብላ የበቀለች አረም ነው የምትመስለኝ - የሰውአራሙቻ !

ከፌቨን ጋር የተዋወቁት በአንድ የግል ድርጅት ሲሠሩ ነበር። "አ ማሚ ማለትኮ እናት ማለት ነች"ትላታለች ሚስቴ ይህቺን ሴት ስታደንቃት ...! ይታያችሁ እናት ! ለነገሩ "እናት" ናት።

"ፌቪዬ የኔ ማር...! ይሄን ሸንኩርት የሚባል ነገር እየከተፍሽ ቆንጆዬ እጆቿን ልታበላሺው ነው...።" ትላታለች። ፌቨን ልታስተናግዳት ጉድ ጉድ ስትል እኮ ነው፤ ምክሯ ሁሉ ግራ ነው የሚያጋባው።

አንዳንዴ ደግሞ እኔና ፌቨንን እያተመለከተች፣ "እንዴ እናንተ ሁለታችሁ ብቻ ናችሁ፤ የምን እንጀራ መጠፍጠፍ ነው ... የቀን ሠራተኛ ቅጠሪና ወጥ ምናምን ሥርታ ፍሪጅ ውስጥ ማስቀመጥ፣ እንጀራ ከሱቅ ገዛ አድርገሽ 'መጠቀም'፤ እንደው አበሻ ጓዳ ገብቶ ፍዳውን ካልበላ ካላበካ፣ ካልተጨማለቀ እሳት ላይ ካልተጠበሰ የበላ አይመስለውም፤ ... አይደል እንዴ አብርሽ? ሂሂሂሂሂሂ ...ይህቺን የመሰለች ማር የሆነች ልጅማ ሽንኩርት አታስከትፋት...።"

ፌቨን ምሳ ሥርታ ይህቺ 'መካሪ' በደንብ እያጣጣመች ከበላች በኋላ መልሳ እንዲህ ትላለች፣

"ላለለት ሰውማ ማን እንደ ቤት ምግብ እናቴ ትሙት (እናቴ ትሙት ብሎ መሐላ አይቀፍም?) ... ውይ እንዴት ርቦኝ ነበር። ጥግቦኝ በላሁ። ፌቪዬ ከአልሜዋ ትንሽ ጨምሪልኝ" ትላለች። እውነቱን ለመናገር ሴት ራበኝ ስትል አልወድም። በዛ ላይ አንዲት ሴት ያውም ኢትዮጵያዊት እንደዚህ ስትል ታሳዝነኛለች። ሴት ራበኝ ስትል አልወድም። በዛ ላይ አንዲት ሴት ያውም ኢትዮጵያዊት እንደዚህ ስትል ታሳዝነኛለች። እንድ ሴት የፈለገ የሞራል ውድቀት ውስጥ ብትገባ የዚህ ዓይነት አኗኗር የምትመርጥ አይመስለኝም። እንድ ሴት የፈለገ የሞራል ውድቀት ውስጥ ብትገባ የዚህ ዓይነት አኗኗር የምትመርጥ አይመስለኝም። አንድ ሴት የፈለገ የሞራል ውድቀት ውስጥ ብትገባ የዚህ ዓይነት አኗኗር የምትመርጥ አይመስለኝም። ወይም አንዱ ደደብ የሕያውነት እንቀጿን በከፋት ከሕይወቷ መጽሐፍ የተገነጠለ የኑሮ ገጽ ይኖራል፣ ወይም አንዱ ደደብ የሕያውነት እንቀጿን በከፋት ሰርዞታል። ወዶ አይደለም ወሬዋ የሚምታታው...

ብጣም ቆንጆ ናት። ያውም ውብ የሚባል ዓይነት። ላግባ ብትል እግሯ ላይ ወድቆ የሚያገባት ሺ ከሚሊየን ነው (በዚህ ዕድሜዬዋ እንኳን ላግባ ብትል የሚሸማባት ጎረምሳ ብዙ ይመስለኛል...) ግን ከርታታ ናት። ቢቃ እዛ ስታድር፣ እዚህ ስትውል፣ ሽሽቷን ልታዘምነው እንዴ ትልልቅ ሆቴሎች፣ ሌላ ጊዜ ሌላ የመዝናኛ ቦታዎች ብትንከራተትም ዓይኗ ላይ እንደ ሩቅ አገር እሳት ቢል ቢል ሲል የሚታየው እምሮት ... እሮይ ማያ ጎጆ መናፈቋ ነው!!

እናም ፈሽንን ፊቴ እንዲህ አለቻት፣ "ፌሺ ማር...!ይሄ እንቁላል ቅርፅ ያለው ፊትሽ በዚህ ፀጉርሽ ባይሸፈን ኖሮ መልክሽ የሚያሳብድ ይሆን ነበር። ብዙ ሳይሆን ትንሽ አጠር ...፤ ምን አሁን እኮ ፀጉር ደርባ ላይ ለቅቆ አንበሳ መምሰል ትንሽ ጊዜው አልፎበታል። ዳሩ አንቺ ወጣ ብለሽ አታዪ...፤ እዚሁ ባልሽ ጋር ታፍነሽ እየዋልሽ ሂሂሂሂሂሂ"። ቀልድ አልብሳ መርዟን ረጨችው።

ማታ እንደተኛን ፈሽን ድንገት ከጎኔ ቀና ብላ ደረቴ ላይ አገጯን አስደገፈች። ጥቁር ፀጉሯ ፊቴ ላይ ተነሰነሰ።ዓይኖቼን ጨፍኜ የፀጉሯን ሽናብ ተጠመቅኩት - በደስታ ... እንደ ሩፋኤል ፀበል።

"አብርሽዬ...!"

"እ!"

"ዓይንህን ግለጥ" አለች፤ ገለጥኩ። ከጥቁር ደመና ውስጥ ብቅ ያለች ጠይም ፀሐይ ከበላዬ።

"ማሚ ያለችው ነገር ግን አልገረመህም፤ እንዴት እስከዛሬ አላሰብኩትም...?!"

"ምኑን?" አሁን እኔም ነቃ አልኩ።

"ፀጉሬን ባሳጥረው እንደሚያምርብኝ ፀጉር የምትሠራኝ ልጅም ደጋግማ ነግራኛለች" ፊቷ ላይ ያለው ስሜት የመጠየቅ ሳይሆን ፀጉሯን የምትቆርጥበት መቀስ እንዳቀብላት የመጠየቅ ዓይነት ያበታለተ መርዶ ነበር። ሁሉም ነገር ቅድሚያ የሚቆረጠውም የሚቀጠለውም ልብ ላይ ነው።

"ፀጉርሽን እንድትቆረጭ አልፈልግም። እንኳን መቆረጥ ፀጉርሽን ስታበጥሪ ማበጠሪያው ላይየሚቀሩት የፀጉር ዘለላዎችሽ ያሳዝኑኛል። እና ለእኔ የምታምሪኝ እንደዚህ ስትሆኝ ነው። ፀጉርሽን ከዓይኖችሽ፣ ከአፍንጫሽ እና ከእነዚህ ውብ እጅና እግሮችሽ እኩል እወደዋለሁ፤ እንደ አንድ የሰውነትሽ ክፍል ነው የማየው" አልኳት ጣቶቼን ፀጉሯ ውስጥ እያርመሰመስኩ።

"እንደዚህ  አንበሳ ስመስል ነው የምትወደኝ?" ብላ በማሾፍ ከተናገረች በኋላ ፀጉሯን በጣቷ መነጨረችውና ከነፈረን ስማኝ ደረቴ ላይ ልጥፍ ብላ ተኛች። (ይሄ መሳም ቃሌን መስማት ይሁን ወይስ ሰም መሸጥ ዓይነት ይሁዳዊ መሳም አልገባኝም)። አተኛኘቷን ሳየው የልብ ምቴን የምታደምጥ ነበር የምትመስለው፤ እንቅልፍ ወሰዳት።ስንተኛ ፀጉሯን ስለማታስይዘው እንዲሁ ነው የምትተኛው፡ በእንቅልፍ ልቧ ስትንቀሳቀስ ቁጥር የፀጉር መዓበል ትራሱ ላይ ሲነሳ ከትራሱ ላይ እየተንሸራተተ

ፊቴ ላይ ሲርመሰመስ ነፍሴ ሐሴት ታደርጋለች።

ፀጉር እኮ መንፈስ ነው። በተለይ የሴት ልጅ ፀጉር። የቅዱሳን ሥዕል ላይ ከራሳቸው በላይ እንደሚታየው የብርሃን አምድ ... የሴት ልጅ ፀጉርም ባፈቀራት ወንድ ብቻ የመንፈስ ዓይን የሚታይ የውበት አምድ ነው ! የሴት ልጅ ሰውነት በማይታይ የክብር ብርሃን የተከበበ ሕያው ቅድስና ነው። ትልቁ ችግር የብዙ ሴቶች ፍላጎት ለብዙኃኑ ቆንጆ ሆኖ የመታየት መሆኑ ነው። ብዙኃኑ አድናቂ ነው። ብዙኃኑ ጠባየ አብርንቱ ከንይን ሲርቁ አብሮ ይከስማል። ብዙኃኑን የኔ ከምንለው ሰው ጋር በአንድ ሚዛን ስናስቀምጠው አይገባም። ለብዙኃኑ ብዙ ሆኖ መገኘት በመፈለጋቸው አንዱንም ሳይዙት ምንም ሆነው እንዲቀሩ ያደረጋቸው ብዙ ናቸው።

ፌቨን ተኛች። ስትተኛ የተመጠነ እስትንፋስና ሰላም ያለው እረፍት ፊቷ ላይ ይረብባታል። የፌቨን እንቅልፍ ሰላም ባለው ሰፊ ባሕር ላይ ያለ ምንም እንቅስቃሴ በጀልባ እንደመንሳፈፍ ይመስለኛል። ሳትታ ሳያት ታሳሳኛለች። እና ቀስቅሳት ቀስቅሳት ይለኛል። ለብቻዬ ትታኝ ወደሆነ ሰላም ወዳለው ዓለም የሄደች ይመስለኛል፤ እኔ ግን በሐሳብ ነጎድኩ። ወደኋላ ... ፌቨንን ዓይቻት ፍቅር የጀማመረኝ ለምን ከሩቅ ስመለከታት የሚገርመኝ ፀጉሯ ነበር። ድብን ያለ ጥቁርና ጠንካራ ፀጉር። ከርዝመቱ ብዛቱ።ከተዋወቅንና ከተቀራረብን በኋላ ደግሞ ፀጉሯ መሐል ጣቶቼ ጠፉ ማለት ዘበት ነው። አንገቷን ወደግራ ዘንበል ሲታደርግ ፀጉሯወደ ግራ ይናድና በግራ ትከሻዋ አልፎ እየተርመሰመሰ የግራ ጡቷን ይሸፍነዋል።

ፀጉር ቤት ቆይታ ስትመለስ የሆነ የተቃጠለ ፀጉር ሽታ አፍንጫዬን ያውደዋል። ያንን ሽታ እወደዋለሁ። እንደውም በሴቶች ፀጉር ቤት ሳልፍ ይሄ የተቃጠለ የፀጉር ሽታ ሲሸተኝ ፀጉር ቤቱ ውስጥ ፌቨን ያለች ይመስለኛል። ፀጉር መተኮስ ማለት እኮ ለውበት አምላክ የሚቃጠል የፀጉር መስዋዕት እንደማቅረብ ነው። (የመረረ የፋሽን ጥላቻ ኖሮብኝ ሳይሆን ውበት ዋጋ እንደሚያስከፍል ለመግለፅ...)

ጠዋት ከእንቅልፌ የቀሰቀሰችኝ ፌቨን ናት - ቁርስ ሰርታ - ሁልጊዜም እንዲሁ ነች። ቁርስ እየበላን ፎካት ፍርፍሩ ውስጥ አልያም እንቁላል ጥብሱ ውስጥ የፀጉር ዘለላ ማግኘቴ አይቀርም። ዛሬም ይሄው አንድ ቢመዘዝ የማያልቅ የሄቪን ፀጉር አገኘሁ።

ሳቀቅን።

በግራ እጇን ጣቶች ወደ ዓይኗ እስጠግታ እየተመለከተች እንዲህ አለች፣ "ይሄ ሽንኩርት እጄን

አሻከረው"።

ዝም አልኩ።

ዝም ተባባልን።

የዘች ዋጋ ቢስ ፍጥረት መንፈስ ቃል በቃል በመካከላችን ሥራውን እየሠራ ነው።

ማታ ከሥራ ስመለስ ፌቨን ፊቷ በሳቅ ተጥለቅልቆ ሶፋ ላይ ተቀምጣለች። ቤቱ በአጣን ታፍኖ በና ቀራርቧል። ፀጉሯን ተቆርጣ ወደ ቢጫ የሚያደላ ወርቃማ ቀለም ተቀብታዋለች። ዙሪያውን ጆሮዋ አካባቢ ተቀልብሶ ሲታይ ወርቃማ ኮፍያ ያጠለቀች ነበር የሚመስለው። ፊቷም አላማረባትም። የሆነ ነገሯ ተገፍፎ እርቃን ነገር ሆናለች። አንገቷ ወደ ላይ የተመዘዘ ይመስል ረዝሟል (የዚህች ልጅ አንገት እንዲህ የመሞቻዋን ቀን እንዳወቀችወፍ የሰለለ ነበር እንዴ?)። ትከሻዋ የሆነ የተራቆተ ተራራ መስሏል። ትላንት ገና ዛፉ የተቆረጠ ...። ፌቨን ነፍስ ይማር ! ዘጋኝ። ማየት ዘጋኝ፤ መሳቅ ዘጋኝ፤ መኖር ራሱ ዘጋኝ !

ጉዳዩ የፀጉር አይደለም...

"እሺ አሁንስ እንደሚያምርብኝ አመንክ...?" አለችኝ ድንገት ቆማ ወገቧን በመያዝ አንዴ ወደፊት አንዴ ወደኋላ እየዞረች በመውረግረግ ... ውበቷን ለማሳየት። እጄን ልኬ ፀጉሯን ነካሁት፤ ማረጋገጥ ፈልጌ ነበር። እንደው የሆነ ተዓምር ነገር ሆኖ ጥቁር ፀጉሯ ከወርቃማው ኮፍያ ውስጥ ቁልቁል እንዲዘንብ በልቤ እየፀለይኩ። የፌቨን ፀጉር በቦታው የለም። ቢቃ የለም። ፀጉሯ ናፈቀኝ። ፌቨን ናፈቀችኝ። የኔ ፌቨን ከነጥቁር የፀጉር መጋረጃዋ... በእጇ ወደ ኋላዋ መለሰ የምታደርገው ጥቁር ዘንፋላ ፀጉሯ ጠፋ.. ተገለጠች ! ተገላለጠች። እናም ልዩነቷን አስቆርጣ ጥላ መንገድ ለመንገድ ትርፍርፍ ያሉትን ሁሉንም ሴቶች ሆነች ! ሁሉንም ለመሆን ወደ መንጋው ለመቀላቀል ነበር ይሄ ሁሉ ሩጫ ! እኔና ሁሉም ባለቀለም ፀጉሮች አንድ ቤት ያለን መሰለኝ። ቢሮ ... ሱፐር ማርኬት ... ካፌ ውስጥ ... ታክሲ ውስጥ .. ቡና ቤት ውስጥ ...የዘፈን ክሊፖች ውስጥ ሰልችት ያሉኝ ሴቶች ቤቴም !! ቤቴ አደባባይ የሆነ መሰለኝ!! አካባጅ ሆኜ ነው ?... አይደለም !

"ተቆረጥሽው!" አልኳት፤ጥያቄ አልነበረም።

"አብርሽዬ ፀጉር ቤት የሚሰሩኝ ልጆች እንዴት እንደተገረሙ። ይሄን ያህል የሚያምርብሽ አልመሰለኝም

ነበር አሉ...፡፡" አሉ አሉ አሉ አሉ አሉ ... የፀጉር ቤት ሰራተኞች ብዙዎቹለሚሠሯቸው ሴቶች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር፣ "ከምሠራቻው ሴቶች ፀጉር ያንቺ ይለያል ...ለተፈለገው ስታይል የሚሆን ምርጥ ፀጉር ... ምናምን" ሴቶቹ ደግሞ ያምናሉ፡፡ ይገርመኛል፡፡ እናም ፌቨንን ዝም ብዬ ስመለከታት ድንግልናዋን የሆነ ሌላ ሰው የገሰሰው ዓይነት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ድንግልና ማለት የእኔ የግሌ ብለን የምናምንበት ጉዳይ እንዳይሆን የገባኝ አሁን ነው፡፡

ድንግልና የሥጋ ጉዳይ አይደለም፡፡ ማንም ሴት እድሜ ልኳን የምታስቀምጠው የቃል ድንግልና አለ፡፡ ለብሷ ብቻ፣ የኔ ሳለችው ሰው ብቻ የምትናገረው፡፡ ደግሞም የውበት ድንግልና አለ፡፡ ፋሽንም ዘመንም የማይገስሰው፡፡ የኔ ለምንለው ሰው ብቻ ርካታ የተፈጠረ፡፡ ያንን ድንግልና ነው አስረክባ የመጣችው፡፡ ለካቢጅ አይደለሁም፡፡ ፌቨን ራሷ ምስክር ናት፡፡ ስንቱን ጉድ፣ ወሰኝ የሕይወት ስንክሳር በቻልታ ሰልፈው ታውቀኛለች፡፡ ይሄ ግን... ከዛ ቀን ጀምሮ ዘጋኝ ! ሁሉም ነገር ዘጋኝ፡፡

"አዝናለሁ!" አልኳት፡፡ የፊቴ መቀያየር አስደንግጧታል፡፡ ድንጋጤዋ ደደብ መሰላ እንድትታየኝ አደረገኝ፡፡ ሚስቴ ደደብ ከመሰለችኝ ቃሉን በማሰቤ ራሱ ወይ እኔ በቁሜ ሞቻለሁ፣ አልያም የሚስቴ ሕልውና በውስጤ አከትሟል፡፡ የሆነ ዓለም ግማሽ ጎኗ የተሸረፈመሰለኝ፡፡ ከብር ራሱ ግማሹ ተሸርፎ በንቀትና በጥላቻ ምድር ላይ የተከሰከሰ...

"አብርሽ አልወደድከውም ?"አለችኝ ግራ ገብቷት እንደቆመች፡፡ እንዴት ነው እንዲቷ ተመዝዞ የሆነ ቆቀ ነገር የመሰለችው፣ በእግዚአብሔር፡፡ ወደሷ ማየት ቀፈፈኝ፡፡ መኝታ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ፡፡ ልክ እንደብርሃን በሆነ ቀዳዳ ገብታ ፊቴ የምትቆም ይመስል ጥቅልል ብዬ ዓየር እንኳን እንዳይገባ ታፍኜ ተኛሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል በጨለማው ውስጥ ወርቃማ ፀጉሯ እያብረቀረቀ አእምሮዬን ሞላው !

"እንዴ ራት አንበላም እንዴ?" አለች፤ እንባ እየተናነቃት ነበር ድምፅዋ ያሳብቃል፡፡ አብረን በትዳር በቆየንባቸው ጊዜያት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር እንዲህ መጥፎ ፊት ያሳየኋት፡፡ በቀጥታ መጥታ የለበስኩትን የአሊጋ ልብስ ገፍፋ ወደዛ ጣለችው፡፡ እሪብ ነበር ሆና ነበር፡፡ "አንተ ራስህን በምን ሒሳብ ነው የምታስበው፤ ማንኛዋም ሴት የምታደርገው ተራ ነገር ነው ይሄ፤ ለምን ታሳቅቀኛለህ...?"

ይሄው "ማንኛዋም" ሴት ሆነች ሚስቴ !

"ያልወደድከው ነገር ካለ መናገር ትችላለህ፡፡ ምን ተፈጥሮ ነው እንዲህ የሚቀያይርህ?"በእልህ ዓይኗን ገልጣ ነበር የምትናገረው፡፡ እንዲህ ጮኻ ስትናገር ሰምቻት አላውቅም፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው፤

ጩኸትም ቁጣም የሚያስደነግጠው ለካ ለተቆጪው ባለን ክብርና ፍቅር ልክ ነው። ይሄ ባንዴ ከውስጤ የተነነው የፌቨን ነገር ግርማ ሞገሷንም ድራሹን አጥፍቶት ይሄን ሁሉ ጩኸቷ በሰፈራችን እያሰፈ "ቁራሊ" ከሚል ሰው ጩኸት እንኳን ለይቼ አላየሁትም።

ድንገት ውስጤን ፈንቅሎ በወጣ ጩኸት፣ "አስቀያሚ" አልኳት። በድንጋጤ ሽምቅቅ አለች። አቤት ብልግና። ከየት አባቱ ነው እንዲህ መዥረጥ አድርጌ ያወጣሁት! ለካ ጨዋ የምንሆነው በትርፍ ጊዜያችን ነው። ወደ ዋናው እኛነታችን በቁጣ አልያም በደስታ ስንዘፈቅ ብልግናችን እንዲህ እርቃኑን ይቆማል። ፌቨን የጨው አምድ ሆና ቀረች። የአሊጋ ልብሱን ገፍፌ እየጎተትኩ ወደ ሳሎን ሄድኩና ሶፋ ላይ ተኛሁ። አልተከተለችኝም። እንኳን ያልተከተለችኝ። ተቀያይሬ ነበር። የሆነ ነገር ባደርጋት ደስታዬ ነበር። ከሆነ ረኸርም ሕንፃ ላይ ብገፈትራት ነገር (ጭካኔ ይመስላል እይደል ... ግን ቦታው ላይ ካልሆኑ ስሜቱ አይገባም ... ለካ ሰው ሚስቱን በገጀራ አንገቷን አላት ምናምን የሚባለው በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ነው ... ትህትና፣ ዘመናዊነት፣ ሴትን ማክበር ቅብርጥስ የሚባሉት ጣጣዎች ለካ አልገቡንም ... ገና አልዘመንንም ለካ !)

ከዛ በኋላ ፌቨን ትኑር ትሙት አላውቅም። ሶፋ ላይ አድሬ ጠዋት ወደ ሥራ እሄዳለሁ።ማታ ጓደኞቼ ጋር አምሽቼ እኩለ ሌሊት አካባቢ ወደ ቤት እመለሳለሁ። አልጠጣም፤ ግን ፌቨንን ላለማየት ያለኝ አማራጭ እጅግ በጣም የምጠላቸው መጠጥ ቤቶች ለስላሳ ይዤ መቀመጥ ነበር። ... ለዛ ቢራውን የሰከራምክ መለፋደድ ማዳመጥ ነበር። እኔ ሚስቱ አበሳጨችኝ ብዬ መጠጥ የምጋት ሰው አይደለሁም። ስወድም በራሴ አዕምሮ፣ ስጠላም በንፁህ አዕምሮዬ መጥላት እፈልጋለሁ። ከሚስቴ ጋር ተጣላሁ፣ ፍቅረኛዬ ካደችኝ፣ ቅብርጥስ በሚል ሰበብ የጠርሙስ አንገት አንቀው የሚጨማለቁ ሰዎች በራሳቸው ሕይወት ላይ ድራማ የሚሰሩ ይመስለኛል።

አንድ ቀን የፌቨን እናት ደውለው በጥብቅ እንደሚፈልጉኝ ነገሩኝ። አከብራቸዋለሁ ግን በቀጠሩኝ ሰዓት ሳልሄድ ቀረሁ። በቀጣዩ ቀን አምሽቼ ቤት ስገባ የፌቨንን እናት ቤት መጥተው አገኘኋቸው። ፌቨን ጎናቸው ተቀምጣለች። ፀጉሯን በጥቁር ሻሽ አስራዋለች። እንዲህ ግራ ከመጋባት ... አስቀያሚ !

"አብርሽ ምንስ ቢሆን እናትህ አልነበርኩም" ብለው ወቀሱኝ እናቷ። ከልቤ አዘንኩ። ግን ስለፌቨን ማውራት አልፈለግኩም። "የሆነውን ሁሉ ሰምቻለሁ፣ ልጅ ናት ሴቶቹ የሚያደርጉት ነገር ያምራታል፤ በዕርግጥ ተይ ስትላት መስማት መመካከር ደግ ነበር፤ ግን እንደሌሙኑ ሆነ። ሁለተኛ እንዳይደገም መመካከር እንጂ እዚህም የሚያደርስ አልነበረም" ብለው ነገሩን ቀለል ሊያደርጉት ሞከሩ። አልገባቸውም

ማዘር። ማንም የእኔ ጉዳት አይገባውም። ማንም የእኔ ጥልቅ ስሜትና ሐዘን አልገባውም።

"ማዘር በጣም የማከብርዎት ሰው ነዎት። ልጅዎትንም አከብረው ሰጥተውኛል። እኔም አንድ ነገር አስቀይሜዎት አላውቅም"

"አውቃለሁ አብርሽ" አሉ ፊታቸው ላይ ሐዘን ነበር።

"አሁን ግን ከፌቨን ጋር አብሬ መኖር አልፈልግም። ዓይኗን ማየት አልፈልግም። መፋታት ነው የምፈልገው" አልኳቸው። ፌቨን ያቃሰተች መሰለኝ። እናቷ በድንጋጤ ወደ ፌቨን ዞረው አፈጠጡባት።

አስተያየታቸው፣ "አንቺ ሌላ ያደረግሽው ነገር አለ እንዴ" የሚሉ ይመስላል። እውነቱን ነው ፌቨንን መፍታት ብቻ ነው የምፈልገው። ለሞተው ትላንታችን ፍቺ የቀብር ስነስርዓቱ ነው ለእኔ! ምን ያደርጋል የበከተ የፍቅር ሬሳ ተሸክሞ ማንዘፍዘፍ። ወደዛ ቀብር አርም ማውጣት ነው እንጂ። አርሜን ማውጣት እፈልጋለሁ። አካባቢ እባላለሁ አውቃዋለሁ። ግትር እንደምባል አውቃዋለሁ። በዘመነው ዘመን ኋላ ቀር እንደምባል አውቃለሁ። ዘመናዊ ለመባል ግን ስሜቴን ማፈን አልፈልግም ... ፍቺ ፍቺ ፍቺ !!

እዚህ ምድር ላይ መናቅ፣ መገፋት የበዛብን እኛ ቢያንስ ቤተሰባችን ያልነው ካልሰማን፣ ተንቆ ከመኖር፣ ፍላጎታችንን ሲቆርጡ ሲገንጥሉ፣ እኛነታችንን ማንነታችንን ያልሆነ ቀለም ቀብተው "አሳመርንላችሁ" ሲሉን "ገደል ግቡ አንፈልግም" እንል ዘንድ ቢያንስ በትዳራችን ላይ ሥልጣን ሊኖረን ይገባል !! ገደል ትግባ ፌቨን የምትባል ደንዝ ! እሷን ብሎ ሚስት። የትዳር አጋር ክቡር ቃል ነው። ቃሌ ከመንደርተኛ ቃል ካልተሻለ፣ እኔ ተራ ጎረቤቷ እንጂ ባሏ አይደለሁም። ገደል ትግባ !! ገደል ትግባ ... ገደል ትግባ ! ጭራ አድርጋኛለች። እንዲት ሚስት የባሏን ስሜት መረዳት ካቃታት፣ ያውም ሺ ጊዜ የነገራትን ... ወጥ መውጥወጥና ቀለበት ሰክቶ መንከርፈፍ ትዳር ነው ያለው ማነው ... የማትረባ !! እኔ ቁጡ ነበርኩ ? አልነበርኩም !! እና ሳቄን ማን አከሰመው፣ በውስጤ ማን ቁጣ ዘራ ... ራሷ ፌቨን።

###

የፌቨን እናት ተቀየሙኝ። ሊያስታርቁን መጥተው፣ "ልጅዎትን ከዚህ በኋላ ማየት አልፈልግም" ስላልኳቸው ተቀየሙ። ማንም ወላጅ ቢሆን ይስማማል። በደካማ አቅማቸው ከየትና የት ድረስ መጥተው ለማስታረቅ ሲሞክሩ እንቢ አያለኝም ብለው ነበር ያሰቡት። የእኔ ፌቨንን መጥላት ... ርጥውን መናቅ መሰላቸው ! "እንዴት ሴት ፀጉሯን መቆረጧ ትዳር እስከማፍረስ ካደረሰ ከፍቺው ኋላ ፀጉር ብቻ ሳይሆን ሌላ ምክንያት አለ ማለት ነው" ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል። እውነት ነው

ከፈሸን ፀጉር ኋላ ሚሊየን ምክንያቶች ነበሩ፤ ሁሉም ምክንያቶች ግን መነሻቸው ፍቅር ነበር።

"ፍቅር ይታገሳል" ይሉኛል ጉዳዩን የሰሙ ሁሉ፣

ሰው በሰላሙ ቀን አግዜሩንም መጽሐፉንም አሽቀንጥሮ እሽሼ ሲል ይከርምና የቁርጥ ቀን ሲመጣ በየሥርቻው የጣለውን የሕይወት መጽሐፍ አቧራውን አራግፎ እያነሳ ሁሉም ሰባኪ፣ ሁሉም ቃል አጣቃሽ ካልሆንኩ ይላል።

"ፍቅር ይታገሳል"ይለኛል መካሪ። እንዲህ ሲሉኝ ተናገር ተናገር ጩሀ ጩሀ ይለኛል። "እስቲ እንዲህ ለነፍስህ ያደርክ ከሆንክ ቃሉ እንደሚለው አታመንዝር ! እዎ አንተ ራስህ ይሄን የምትመክረኝ … እስቲ በየስርቻው ራሳቸውን ነጥቀህ በቀለም የምታቸፍጉረጉራቸውን የወሲብ እቃዎችህን እንደሰው ቁጠር ! እዚህች አገር እንደ ሴት መጫወቻ የሆነ ፍጥረት አለ … ? የማንንም ወጠጤ መጥቶ የብልግና ብሩሹን እንከርፍፎ መንገድ ላይ እንደተሰጣ ሸራ ሴቶችህ ላይ ብልግናውን ሲስል የት ነበርክ…" ማለት ያምረኛል።

እዎ ውስጤ በቁጣ ይሞላል፣ "ትላንት 'መብታቸው ነው' እያልክ በየመጠጥና ጫት ቤቱ እንደ ጥራጊ ማንም ሲረግጣቸው የነበሩ ሴቶችህን ስታልፍ … ዛሬ ሴተኛ አዳሪነት፣ ወሲብን ኢቃልሎ ማየት፣ በፋሽን ሥም ሴትነትን መንገድ ዳር አቅርቦ መቸብቸብ ስተት ብሎ ጓዳህ ገባ! ሴቶች በጓዳ አይቅሩ አደባባይ ይውጡ ከሚለው የሚበዛው ለሴቶች መጨቆን ያዘነ እንዳይመስልህ። በአደባባይ እንደ ፋሲካ በግ ዳሌና ሽንጥ በዓይኑ እየመተረ ለማምረጥ ነው! ምነው የሚመች ጓዳ፣ ከብር ያለው ጎጆ አግኝተው ሴቶች ጓዳቸው ውስጥ አርፈው በተቀመጡ። ግን ባትለውም ኑሮ ራሱ እየመዘዘ አደባባይ ያሰጣቸዋል። ያውም የኛ ኑሮ…" ብዬ በአደባባይ ድፍን የአበሻ ወንድ ላይ መጮህ መደንፋት ያምረኛል።

"ለመሆኑ የሴቶችን ልብስና ጫማዎች ታዝበሃል ? ለዙረት የሚመች አይደለም - ሁሉም። ሴት ልጅ ከቤቷ ወጥታ ወደ መኪናዋ ከመኪና ወደ ሥራ ረጋ ያለ ሕይወት እና እንቅስቃሴ እድትኖር ታስበው የተሰሩ ናቸው። እንዳንተ ስኒከር፣ ሸራ ጫማ፣ ከስከስ አይደለም የሴቶች ጫማ ! ሴቶችህ ራሳቸው ለአደባባይ ማንነት "መብት" የሚል ሽፋን ይሰጡታል እንጂ በብዙሃኑ የከተማ ሴት አዕምሮ ውስጥ ያለው እውነት ጥሩ ሥራ አግኝቶ ወይም አንዱን ኃብታም አግብቶ "እርፍ" የሚል ሕልም ነው፤ (ይሄ አንዳንዶችን ያበሳጫል ግን ምን ይደረግ - እውነት ነው። ከተማውን ከሰኞ እስከ አርብ የዘነጠ ሽቅርቅር ትውልድ ሲሞላው ሥራ አጥነት ጣራ እንደነካ አስተውል። የታደሉ ዜጎች የቆሸሸ እጅ፣የሥራ ቱታ የለበሱ ሰውነቶች የታደሉ ናቸው። ከሰኞ እስከ አርብ መዘነጥ ከሰኞ እስከ አርብ አዕምሮ

ሰውነትም ሥራ መፍታቱን የሚያሳይ የውድቀት ባንዲራ ነው !" እንዲህ ብዬ የማምግተኝን ሁሉ መሞገት ያሳኛል። ምክራቸው መከራ ከመጨመር ውጪ ወንዝ የማያሻግር እንቶፈንቶ ይሆንብኛልና ሁሉም መጽሐፉ እንደሚለው "የሚያደክሙ አፅናኞች" ናቸው።

በሚስቴ ሰርግ እልፍ ወደ ሰፈው የስትንት ባሕር ስመለከት ሴቶች ባሕሉ ብቻ ሳይሆን ልብስና ጫማቸው ሲደተር ካቴና ሆኖባቸው ይታየኛል። ፋሽን ነፃነታቸውን ነጥቆ፣ ምቾታቸውን ቀምቶ፣ ወንዱ ፊት የእይታ እምሮት እንዲያሳረፍ ይደረድራቸዋል። እነሱም ፍልቅልቅ እያሉ በካቴናቸው ይኮራሉ ... ፋሽን ነዋ። እንደውም ትክክለኛው ዘመቻ መሆን ያለበት ሴቶች አደባባይ ይውጡ ሳይሆን ወደ ጓዳ ይመለሱ ነው ! ጓዳቸው ምቹ ይሁን ነው !! እማሯ አስኪቀኖን ከተማውን የምታካልል ቀንጆ የሆነ ቀን "እፎይ ዞረት ሰለቸኝ" ስትል ትሰማታለህ ... ዞረት የሴት ልጅ ተፈጥሮ አይደለማ ! በተሰጣቸው የተፈጥሮ ፀጋ ልጆችን ሲያሳድጉ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ልጅን ለማሳደግ እግርን ሰብስቦ ቤት ውስጥ መቀመጥ፣ ደስታን አሳልፎ መስጠት ይጠይቃል። ልጅ ጭፈራ ቤት ውስጥ አያድግም። ይሄ የዘመናችን እጉል ዘመናዊነት እንዲህ ተጣምሞ ካደገ፣ ልጆቻቸውን በጋሪ እየገፉ በደረቅ ሌሊት ጭፈራ ቤት የሚሰየሙ እናቶችን መፍጠሩ አይቀሬ ነው።

ደግሞ እንደ ደንቃራ በመብት ስም ስለእንዝላልነት ልትሞግተኝ ፊቴ የምትደቀን አንስት ብሰሙቱን ጣራ ታስነካዋለች። "አንቺ ራስሽ እስቲ ራስሽን ተመልከች፣ ለምንድነው ፀጉርሽን ቀለም የተቀባሽው ... 'ከፊትሽ ከለር ጋር እንደሚሄድ' ባለሞያዎቹ ነግረውሽ ... ወይስ እንዲሁ ሲያደርጉ አይተሽ ... ምኝ ነገር ነሽ ... ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት አጠቃላይ የፀጉር ሞያተኞች ሰንት ይሆኑ በሙያው ጥልቅ እውቀት ያላቸው። ጥቂቶች - በጣም ጥቂቶች። ሌላው የተከበረ ፊትና ፀጉርሽን ቤተ ሙከራ የሚያደርግ የለምድ አዋላጅ ነው ! እንግዲህ ይሄ መደዴ ፀጉር ተኳሽ ነው የፊትሽ ቅርፅ፣ የቆዳሽ ልስላሴ፣ ይሄን ቀለም ተቀቢ፣ ያንኛውን ሜካፕ ተለቅለቂ እያለ ቅዠቱን የሚመክርሽ !

እየውልሽ የፀጉር ፍሽናው እንቺን እጥፍቶ የሆነች ሌላ ሴት ማስመሰል እንጂ፣ ያለሽን ውበት ማጉላት አለመሆኑ የሚገባሽ የፍሽናውን ስም ስትሰሚ ነው፣

ቢዮንሴ ሹርባ፣

ሪሃና ቁርጥ፣

ዊትኒ ስታይል...

አንቺ ግን ስምሽ አረጋሽ ነው፣ ወላ ነጃት፣ ወላ ነፊሳ፣ ሄለን፣ ሲቲ፣ ቲቲ ሁኚ ብትፈልጊ...። ካናትሽ ላይ ቆሞ ፀጉርሽን የሚሰራ የሚመስልሽ የፀጉር 'ባለሞያ' በካውያው ፀጉርሽን እየተኮሰ በማያገባ ለፋፊ እንደበቱ ግን አዕምሮሽን ነው በኋላ የውበት እና ፋሽን ካውያው የሚተኩስሽ ! አንቺነትሽን ሊያተን ነው። ከዛ ምንም ከሌሎቹ ሴቶች የተለየ ውበት አይጨምርልሽም። መጨረሻ ላይ እንደሌሎቹ ሴቶች ትሆኛለሽ። በቃ ይሄው ነው። ደግሞ ወንዱ ባንቺ ውበት ይደነቃል ብለሽ አትድከሚ። ወንዱ በሚገረገረው ስልኩ መለዓኪ የመሰሉ ሴቶች ፎቶ ላይ አፍጥጦ ነው የሚውለው፣ ምንም ብትሆኚ አይደንቀውም። ጉዳዩ ከሰውነትሽ ነው። ከስልኩ ወዲያ አምሮት የቀሰቀሰበትን ገላ ሲያጣ አጠገቡ ያለሽውን አንቺን እንደማስታገሻ ከማይረባ የፍቅር ዲስኩር ጋር ይወስድሻል ! የአንቺን ሥጋ አቅፎ መንፈሱ በተመለከተው ገላ ላይ ነው የሚቃገረው..." ብቻዬን ተቀምጬ እንዲህ ነው የማስበው። ሴት ወንዱ በሽተኛ የሆነ ይመስለኛል። ለከርከር የሚያሞጠሙጠው አፉ ለምን ራሱን ለመጠየቅ እንደማይጠቀመው ግራ ይገባኛል።

"እንደ ኳስ መካሪው ወደ ፋሽን ... ፋሽኑ ወደ ወንድ፣ ወንዱ ወደ አልጋ፣ አልጋው ወደተዘባረቀ ሕይወት እየተቀባበለ በሴት ልጅ ሕይወት ጨዋታውን ያሞቀ ዘመን እንደዚህ ዘመን ከቶ አልተከሰተም። ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ነውና ዘመኑ ራሱን 'የሰለጠነ' የሚል ስም አከናንቦታል። ከከንብንቡ ስር ... በስልጣኔ መዳፍ አፋቸውን የታፈኑ 'ስልጡን' የፋሽን ባሮች ዓየር አጥሯቸው ይወራጫሉ። ለዚህ መፍትሄው ራስን መሆን ነው። በዚህ ዘመን በትክክል የሚያስፈልገው "ራስሽን ሁኚ" የሚል መካሪ ነው። ልድገመው ራስሽን ሁኚ ! የነፈሰው ንፋስ ጋር ልንፈስ ካልሽ አብድ የበላው በሶ ሆነሽ ትቀረያለሽ ... የኔን ሚስት አታያትም ... ይቺን አስቀያሚ ! በክብር ካኖርኩባት ዙፋን ላይ ቁልቁል በአናቷ ወርዳ ስትፈጠፈጥ።" የሚል ሆድ የባሰው መካሪ... ባይሰማም ኡኡ ብሎ የሚጮህ... ቃል አንድ ቀን ሥጋ መልበሱ አይቀር። ከፉ ስጋ ለብሶ ፍልጥ ከማንሳቱ በፊት በዘመን ፈሊጥ ቃሉን የማያቀሉ ብፁዓን ናቸው።

በዕርግጥ ይሄንን ስል ሊመክረኝ የሞከረ 'ትሁት' ወዳጅ ነበረኝ። ምን አልኩት ? "ሄድ አባክህ .. አንተን ብሎ መካሪ ! አንተ ስለሚስቴ ፀጉር የምታውቀው አንድ ነገር የለህም ! እንደውም ራስህ በየጓዳህ የምታለቅስበትን እውነት ነው እዚህ በአደባባይ ፉራ ላለመባል የምትቃወመው ! እኔ ለሚስቴ ታማኝ ነኝ ! በዚህም እኮራለሁ ! ለፈጅን ታማኝ ነኝ። እንኳን ከትዳሬ ውጭ ሌላ ሴት ልነካ፣ ለሚስቴ የምጠቀመውን የአድናቆት ቃል ብሞት ለሌላ ሴት አልጠቀምም። ስለማያምረኝ አልነበረም። አምናኝ እኔጋ የሆነች ሚስቴን ማክበር ራሴን ማክበር መሆኑን ስለማውቅ ነው። ደግሞም ደስተኛ ነበርኩ፡ ፍፁም ደስተኛ።"

"አያንዳንዱ ቃሉ በሚስቱ ፊት ሞገስ እንዲኖራት አፈልጋለሁ። በትዳር ውስጥ በጋራ ጉዳይ ላይ የግል አመለካከት የሚባል ነገር የለም። በሚስቴ ሰውነት ላይ ስለምትደረግ እያንዳንዱ ነገር ያገባኛል። ምክንያቱም "አንድ አካል አንድ አምሳል ሆናችኋል" ብለው ያጋቡንን ቄስ ተሳልፌ ሲመቸን አንድ ላይ ሳይመቸን በየግላችን እንድንዳክር አልፈቅድም። በምንም ነገር 'ስለኔ አያመለከትህም' የምትል ሚስት ወይ በሽተኛ አልያም የትዳር ኃላፊነት ያልገባት መደዴ ሴት ናት። መከባበር በሌለበት ውበት ገደል ይግባ። የስጋ ከምሯ ስላማለለህ ዘለህ አልጋ ላይ ትወድቃለህ፣ ከአልጋህ ስትወርድ ምድርህ አሳት ለብሶ ይጠብቅሃል። ፍቺ በማሕበረሰብህ ጸያፍ ነገር ነውና እያስመሰልክ ትኖራለህ። ማስመሰል ደግሞ ያንገሸግሻል። ራስህን በእሳት ልምጭ መግረፍ በለው። በዚህ ዓይነቱ ኑሮ እንኳን ሚስት ተብዬዋ ያጠለቀችልህ ቀለበት፣ ቀለበት የተጠለቀበት ጣትህም ይቀፍሃል።"

"ሚስቱ ስለእርሱ ሕይወት የት ድረስ እንደሚያገባትና የት ድረስ የእርሱ ጉዳይ እንደማይመለከታት መስመር የሚያሰምር ወንድም ድድብና ከነጓዙ የሰፈረበት ደነዝ ይመስለኛል።ይህን የምለው ወንድ በመገሰፅ ሚዛናዊ ለመሆን አይደለም፤ የነፍስ ሐቁ፣ የኖርኩበትም መንገድ ስለነበር እንጂ። ይጠየቅ ጎረቤት። ይጠየቅ ቤተሰቤ። እረ ራሷ ፌቨን ትጠየቅ። ምርር ቢልም ተገደን መዋጥ ያለብን እውነት ይሄ ነው። ባልም ለሚስቱ፣ ሚስትም ለባሏ ተገዥ ናቸው። ውልፍት የለም። አንዱ ካለአንዱ ፍላጎት ስንዝር ሊራመዱ አይገባም። ሚስቴ እኔ ላይ በዚህ ምድር ካለ ማንኛውም ሰው በላይ ኃላፊ ነች። እኔ የርሷ ነኝ፣ ርሷም የእኔ ናት። ፋሽንም በለው ዘመን አመጣሽ ቅራቅንቦ በጎጀዬ ውስጥ የጥፍር ቁራጭ የሚያክል ቦታ እንዲኖራቸው አልፈልግም። ለምን መሰለህ ...ከሦስቱ ጉልቻ አንዱም ከውጭ አይመጣም፤ አንተ፣ ሚስትህና ፍቅር ብቻ ናችሁኮ ጉልቶቹ..." መካሪዬን በደም ፍላት ደንፍቼበት አመንኩበት ባልኩት ሐቅ አከላፍቼው አጠገቤ ድርሽ እንዳይል አባረርኩት።

ምን ላድርግ ... ሳሎን የተቀመጠ ስልኩ ሲጠራ ሚስቱ እንዲታነሳበት በአፉ እስኪደፋ ከሻወር ወደ ሳሎን የሚሮጥ ወንድ ልምከርህ ሲለኝ ምን ላድርግ ታዲያ። መተዋወቃችንኮ ነው ችግሩ። ሐቅ ሙጄስ ለራስ ነው ሰላም የሚሰጠው። እኔ እንዳይሆን የምፈልገውን ነገርም ሚስቴ ከእኔ ፍላጎት ውጭ ሊታደርግ አንዳች ስልጣን የላትም። የራሴ የምትለው ሰውነት የላትም። የዘመናችን በሽተኛ ሴታዊ አምባገነንነት፣ 'በሽተኛው ፌሚኒዝም' እሳቤ ውስጥ ገብተው የተነከሩ ለፋፊዎችን በአማርኛ መስማት ከትርጉሙ ሳይሆን ከመንፈሱ አቀባበል የማይነቀል ደዌ ሴቶቻችን ልብ ውስጥ ዘራ። እነሱም ያሰቡትን ነፃነት ሳያገኙ እኛም ካንዷ ወደ ሌላዋ ያደግንበትን የወንድነት ክብር ፍለጋ ስንዘል ዘመን ጣጥሎን አብስ ! የሴት ልጅ ክብር በፍቅር እንጂ በትግቅ ትግልም በአደባባይ ጩኸትም አይመጣም !! በቤቱ ሚስቱ የገፋችው፣ ፍቅረኛው ያቀለለችው ወንድ ሺ ሕግ ፤ ሚሊየን መመሪያ ቢወጣ ሴትን ያከብራል

ማለት ዘበት ነው።

አባትና እናቱ ሲደባደቡና ባለመከባበር አፍ ሲካፈቱ እያየ ያደገ ሕፃን በባቱ ሲወጣ እያዩ፣ 'ልጅ የፍቅር ገመድ ነው' ይሉናል። በጥላቻና በመናናቅ ትዳር ውስጥ የበቀለ ሕፃን የፍቅርሳይሆን የማሕዘረሰብን ሕግና ባሕል ማነቂያ ገመድ ነው ! ብዙዎቹን 'ዘመናዊነት' ፍዳቸውን የሚያበላቸውን ሴቶች ታዛቢ እስቲ ፤ መነሻቸው ፍቅሩን አሟጥጦ እየተቋሰለ የኖረ ግድ የለሽ ቤተሰብ ነው። ካልተፋቀርን ምን አመላለደን!! ልጅ አሻንጉሊት አይደለም !! ቃላችንን ማፅናት ሲያቅተን፣ ሥጋ ለበስ ሐውልት ቤታችን ውስጥ ተክለን ልናመልክ ይዳዳናል ! "ልጅ ወለድን" ብለን እንመፃደቅ። በልጆቻችን እናት ካልተደበትን የልጆቻችንን ግማሽ ክፍል አንወደውም ማለት ነው። እናቶቹም ቢሆኑ፣ "ለልጄ ስል እንዲህ ሆንኩ፣ ለልጄ ስል ተፈለጥኩ ተቆረጥኩ..."፤ እስቲ መጀመሪያ ለእኛ ለባሎቻቸው ሲሉ ይፈለጡ ይቆረጡ። የልጅሽ ግማሽ አካል እኛ ባሎች አይደለንም እንዴ ?! እነዚህ ኮተታም ዘፈኖችና ፈልሞች በቀጥታም በተዘዋዋሪም የወንድን ልክስክስነት ለሴቶቻችን ሲሰብኩ፣ "ታዲያ ለማን ብለሽ ነው የምትታመኝው" እያሉ ለመደዴነት ሚስታችንን፣ እህታችንን እያዘጋጁት መሆኑን ዘግይቶ ነው የሚገባን።

እና ሚስቱ ካለፍቃዱ ፀጉሯን ተቆረጠች ስል፣ 'መብቷ ነው ቀብርጥስ' የሚለኝ መብዛቱ መልሶ እኔኑ ይገርመኛል። ትዳርም ይሁን ፍቅር ለወደዱት ሁሉን ነገር መስጠት ነው። ግማሽ መስጠት የሚባል ነገር የለም። እዚህ አዲስ አበባ ብልጣብልጥ ነፍሶች ፍቅርን እንደሚሸቅጡት ዓይነት ማለቴ ነው። እንዳሻኝ እዘልላለሁ ማለት የፈለገ ዓዞን ጠቅልሎ እዛው ተራ ዝላዩ ላይ !! ሲጀመርም ጭብጨባው አምሮት እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ኢጋር የትዳር ወኔው የለውም !! ልክ በመንፈሳዊው ዓለም፣ "አንድም ከእግዜር አንድም ከሰይጣን" እንደሚባለው በትዳርም አንድ እግርን ትዳር ውስጥ ሌላኛውን አጉል ምኞት ውስጥ ማቆም የለም!! ጥቅልል ብሎ መስጠት ካልሆነ ጓዝን ጠቅልሎ ወደመሄጃው !! ኩተልካሻ አብሮነት ከጠነዛና ከደነዘዘ የሁለትዮሽ ስብሰባ ብቸኝነት በስንት ጣዕመው።

በዚህ ሆድ በባሰው ለዛ ቢስ ጊዜ ጋብቻን የልጅ ማሽን አድርገው የሚመለከቱ ወላጆች ከፉኛ ተበራክተዋል። ይሄ ነገር ይቆጨኛል (ሆድ እንደባሰኝ ላውራው)። የፍቅር ሰንሰለት ያላቆራኘው ልባቸውን በመውለድ ሊያጣምሩ የሚደክሙ ! ቃል ነው ማሰሪያው - ልጅ አይደለም ! ቃል ነው ስጋ ለባሶ ልጅ የሚሆነው ! 'አብርሽ ውለዱ ልጅ ቢኖር እንዲህ 'በትንሽበትልቁ አትጋጩም' ይሉኛል .. !! እንኳን ካለፍቃዱ ፀጉሯን ተቆርጣ ... የአንዲት በየቤቱ መዞርን ትዳር ያደረገች ሴት ምክር ሰምታ ይቅርና ... ሳሰነጥሰ ይማርህ አላለችኝም ብዬ መፍታት እችላለሁ !! ልጅም ምንም አያግደኝም ! "ዋናው ያልበጀ ቅራሪው ሰው ፈጀ"

ሚስቱ ካለፍቃዴ፣ ፀጉሯን ስለተቆረጠች አፊታታላሁ ...

እንኳን ፀጉሯን መቁረጥ እኔ በማልወደው "ስታይል" ማበጠርም እንደሌለባት የጉልበት ሕግ ሳይሆን የአብሮነትና የመተሳሰብ መርህ ሊያስገድዳት ይገባል ! ይህ ካልገባት ሚስቱ ደንዝዛለች፣ የሆነ የማስተዋል ችሎታዋ ተወስዷል ! መተሳሰብን እና ፍቅርን ችላ ከማለት ሕግን ችላ ብትል ይሻለሃል! መብቴ ነው' ይሉት ጥራዝ ነጠቅ እንቢከረዩ ሕጋዊ ቢሆንም ከሰብዓዊ ጥላቻ ግን አያድንም። ህግ ኑሮህን ከእንከን ይከላከላል እንጅ ራሱ ኑሮ አይሆንም ። የአንድ ፍቅረኛ ትልቁ ብቃት መርታት ሳይሆን ያፈቀረውን ሰው በፍቅር መርታት መቻሉ ላይ ነው።

###

ፊሸን ከዛ ቀን በኋላ የፀጉሩ ነገር እንዳበታለት ሲገባት ያማልለኛል ያለችውን ነገር ሁሉ እያሳየች የተንከታኮተ ፍቅሬን ልትመልሰው ተፍገመገመች። እንደ አጭር ቀሚስ ለብሳአግሯን እስከታፋዋ ታሳየኛለች፤ (እግርሽ ያምራል አላት ነበር ድሮ እንደዛሬው እያንቀዠቀዠ አልባሌ ቦታ ሳይወስዳት በፊት)የእጇን ጣቶች ብታወናጭፍ፣ ዓይኗን ብታፈጥ፣ ከንፈሯን ብታሞጠሙጥ ... ውሉን ቆርጣ ጥላ ትርፍራፊ ውበቷን ብታግተለትል ወይ ፍንክች። እንደውም የባሰ አስጠላችኝ። አይናገረውም እንጂ ሁሉም አፍቃሪ ለዘላለሙ የሚያመልከው የሚያፈቅረው ሰው ላይ በየቀኑ ዓይኑ የሚፈልገው የውበት አማካይ ቦታ አለው። ሌላው ሁሉ ካለዚህ ነጥብ ባዶ ነው። ለእኔ የፊሸን አማካይ የውበት ቦታ ፀጉሯ ነበር። ፊሸንን እንደከተማ ብመለከታት ማሐል አደባባይዋ ፈርሷል። አንጋፋ ፍቅር አዲስ ከተማ ላይ መኖር ያንገሸግሸዋል።

የዘመናዊው ፋሽን ትልቅ ችግር የሴቶችን ፀጉር የሚያደንቁ ተፈጥሯችንን በግድ ጠምዝዞ ሴቶች ዳሌ ላይ ለማሳረፍ መጣሩ ነው። ሴቶች እግር ላይ ሴቶች ጡት ላይ ዓይናችንን በግድ ማስተከል። እንቢ ማየት አንፈልግም ስንል ውበት የማይገባን ገገማዎች መሆናችንን በማሳመን ስልጡን አይደላችሁም ይሉናል ! ምላ ያለች ሴት እይታችንን ትሰበው ይሆናል። ፋሽን ተብዬው ግን የትከሻዋ አጥንት ካልተሰረጎደ ሴት ምኑን ሴት ሆነች ብሎ ሊያሳምነን ይጥራል። ፋሽን ጉልበተኛ ነው። በተለይ ሴቶች ላይ ከንዱ ይበረታል። ዛሬ ፋሽን ለመከተል ፀጉሯን የቆረጠች ሴት ነገ የላይኛውን የፊት ጥርስ አስነቅሎ በባዶ ድድ መገለፈጥ ያምርብሻል ብትባል ጥርሷን ከማራገፍ አትመለሰም። የተጋነነ ይመስላል እንጂ ባለፉት አስር ዓመታት በአገራችን አይሆኑም ያልናቸው ጉዳዮች ዛሬ ላይ ለትውልዱ ተራ ጉዳዮች ሆነዋል። ደግሞ ፍጥነታችን...

የፌቨንን ፀጉር መቆረጥ ከሴት ልጅ ግርዛት ለይቼ አላየውም። ልዩነቱ የሴት ልጅ ግርዛት በሴቷ ስሜት ላይ መቀለድ ሲሆን ይሄኛው በእኔ ፍላጎትና ስሜት ላይ መጫወት መሆኑ ነው። እናም ፌቨንን አፈታታለሁ !! እሷን ብሎ ሚስት። የፍርድ ቤት ቀጠሮዬ ነገ ነው። ፌቨን እናቷ ጋር ከሄደች ሃያ ቀናት አልፈዋል። አልናፈቀችኝም። እንደውም የተሰማኝ ሰላም ልክ አልነበረውም። ትንሽ የተሰማኝ ፌቨንንም ሆነ እናቷን በገንዘብ የምረዳቸው እኔ ነበርኩ በዚህኛው ወር ግን ምንም አልሰጠኋቸውም። ከፌቨን ጋር ስለተጣላሁ ሳይሆን ብሩን ብልክላቸው ፌቨንን የመፈለግ ስሜት ያደረብኝ እንዳይመስላቸው በማሰብ ብቻ ነው...

ከፌቨን ጋር ከተለያየን በኋላ ብዙዎች እንዳሰቡት ስትናፍቀኝ "ማረኝ" ብዬ ቤቷም አልሄድኩ። ስልክም አልደወልኩም። እንደውም አንዳንዶች፣ "ሚስቱ ቤቱን ጥላልኝ ስትሄድ ቤቱ ሊበላኝ ደረሰ፣ ጭር አለ እና ሆነ" ምናምን የሚሉት ነገር ለምን እንደሚባል ገረመኝ። በጣም ነው ቤቱ የተስማማኝ ! ገነት ነው የሆነብኝ ! ምግብ ራሴ አበስላለሁ፣ ቤቱን በደንብ አፀዳለሁ፣ እነባለሁ፣ ፊልም አያለሁ (እንደውም ከዚያ ፌቨን ከምትከፍተው አሰልቺ የቴሌቪዥን ድራማ ተገላገልኩ) እና ደግሞ ሰላም ሆንኩ!! እንደውም ባልና ሚስት የፈለገ ቢፋቀሩ፣ ትንሽ መለያየት፣ ራሳቸውን የሚያደምጡበት "ሱባዔ" መሰል ብቸኝነት ታስፈልጋቸዋለች ብዬ አሰብኩ።

ፌቨንን ለራሴ እንኳን ስሜን በውስጤ መጥራት ይቀፈኛል። ቢታ በተፈጥሮዬ ወግ አጥባቂ ነገር ነኝ ማለት ነው ብዬ አሰብኩ። እና እንዴት ይሄን ሁሉ ዓመት አብራኝ የኖረች ሴት ያውም በፍቅር .. ተነስታ ስትሄድ  ምንም ሳይመስለኝ ቀረ። ለደቂቃ መኝታ ቤታችን ውስጥ ስትበር የነበረች ትንኝ እንኳ በሆን ሽንቁር ስትወጣ የሚናፍቅ ነገር አላት። አይ ጤነኛ አይደለሁም ማለት ነው። ወይስ የሆነ ውስጣችን ሳያውቀው የሚሰለችው አብሮነት አለ ... ምክንያት ፈልጎ የሚፈነዳ ... ፌቨንን ሳላስበው ውስጤ ሰልችቷት ይሆን ? ዓይቷት የማይቋምጥ ወንድ የለም ... ቁንጅናዋ እንግዳ ነገር ነው .. መኝታ ቤት ገብታ ወደ ሳሎን ስትመለስ እንኳ አዲስ ቆንጆ ሴት እንዳየ ጎረምሳ ልቤ ይደነግግላት ነበር .. እና እንዴት ነው ነገሩ ... እንዲህ ልክ የሌለው ግዴለሽነት የሞላኝ ...ወይስ እየቆየ እንደተዳፈነ እሳት ሊያንገበግበኝ ይሆን ..

ለነገሩ ቆንጆ ሴቶች ቶሎ ነው የሚሰለቹት ይባላል። በጥናት ባይረጋገጥም የሆነ እውነት እንዳለው በብዙ ቆንጆ ፍቅረኛ ባላቸው ጓደኞቼ ታዝቤያለሁ። በተለይ ከተጋቡ በኋላ ቆንጆ ሚስቶች ሰውም ተመልካች እንጂ ለባሎቻቸው ያን ያህል አስገራሚም አስደሳችም ነገር የላቸውም እየተባለ ከፉኛ ይታማሉ። ሚስቶቹም ራሳቸው ይሄ ነገር ግራ ይገባቸዋል። አንድ ጓደኛዬ እንዳለኝ ከሆነ እንደውም

ቃል በቃል፣ "ለዛ ቢስ ናቸው !!" ነበር ያለው። እንግዲህ ከሰፌ የብሶት ምክሩ የተወሰነውን ሳስታውስ ...(ያኔ እንኳ ችላ ብዬው ነበር)

"...ቋንጆናቸው ይስብሃል፣ ቁንጅናቸውን ትፈልጋለህ፣ ታገኛለህ፣ ቁንጅናቸው መጋረጃ ሆኖ ስለሚጋርድህ ከማግኘት ቀጥሎ ያለውን ሕይወት አታስበውም። መጋረጃውን ስታልፍ ግን ጭው ያለ በረሃ ይጠብቀሃል ... ሰሐራ ! ምንም አይኖርም ወላ ሃንቲ !! ሁሉም ነገራቸው ወዲያው ነው የሚሰለችህ ... እንደውም እነሱን ለማግኘት የደከምከው ድካም ከንቱ ሆኖ ስለሚታይህ ነጭናጫ ትሆናለህ። ድሮ ይቺን ሚስትህን አፍቅረህ ስትንከራተት ፊት የነሳሃት በፍቅር ዓይን ስትስለመለምልህ የነበረች ጎራዳ ሽቦ ፀጉርልጅ ሁሉ ትናፍቅሃለች ! ለዛ ነው ብዙውን ጊዜ "ልዕልት የመሰለች ሚስት አስቀምጦ ሰራተኛው ጋር..." ምናምን ሲባል የምትሰማው። እንጅማ ሚስትህ ልዕልት ባትመስልም ሌላ ሴት ጋር ሂድ የሚል ፍርድ የለም መቼስ።" የጓደኛዬ ምክር ይከሰትልኝ ይጀምራል። የበላኝን እንደሚያከልኝ ሁሉ ንግግሩን የራሱ ልምድና አመለካከት አድርጌ ከማድመጥ በላይ ዓለምአቀፍ የቆቶች ባህሪ አድርጌ ልቀበለው ይዳዳኛል። ማንም ሰው በጋራ ብሶት ውስጥ ሲኖር በእዕምሮው ልክ ሳይሆን በብሶቱ ልክ ያስባልና።

"ሴትን ልጅ ለማየት ይሄ ደካማ ሥጋዊ ዓይን በቂ አይደለም። ድፍን የስሜት ሕዋሳቶችህ፣ በአካባቢህ ያለው እውነታ፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና፣ ኃይማኖት፣ አስተዳደግህ፣ የትምሕርት ደረጃህ ሁሉ "ተቀናጅቶ" መሥራት ይኖርበታል። በደመ ነፍስ ዘለህ ከገባህ በደም ግፊት ዘለህ መቃብር ጉድጓድህ ውስጥ ነው የምትገባው - ያውም በጭንቅላትህ። ፍቅር ላይ ያለህ ነገር ከተበላሸ በምድር ላይ ያለህ ማንኛውም ነገር እንደተበላሸ ቁጠረው። ሌላው ቢቀር እየቆየ የሚያገረሽ የተበላሸ ትዝታ ይኖርሃል። ልብህን ለፍቅር ስትሰጥ ወሲብ ያዘረው ናላህን አሽቀንጥረህ መጣል አለብህ። እሱ ነው እንደጋሪ ፈረስ ሸብቦ አንድ ነገር ብቻ እንድታይ የሚነዳህ። ለምን እቅጩን አልነግርህም ያኔ አንድ ቤት የሁለትዮሽ ስብሰባ ላይ ስትገናኝ ተረከዝ አይመስጥህ፣ ዳሌ አያማልልህ፣ ከንፈር አያስጎመዥህ፣ ስርቅርቅ ድምፅ ቀልብአያሰጣህ፣ ጉች ጉችም ይበል ዝርግፍም ይበል ጡት ከመጤፍ አይቆጠር ሃቂቃዋ የፍቅር ዘርልብህ ውስጥ ከሌለች አለቀልህ !!"

"የተዝዛዛ እና የሚያዛጋ የሕይወት ድራማ ውስጥ ራስህን ታገኛለህ። አቤት ሲያስጠላ። አንድ የማይመሽና የማይነጋ ረዥም ቀን ላይ ያለህ ነው የሚመስልህ። ሁልጊዜ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት የሚመስል የሆነ ጠራራ ሕይወት ! በቲቪ፣ በመጽሔት ምናምን ታዋቂ ሰዎች፣ "ሚስቴን አወዳታለሁ፣ ባሌን አወደዋለሁ" ሲሉ ሰምተህ ታውቃለህ አይደል ? እስቲ ዝም ብለህ አሰበው ሚስቱን ካልወደደ

ማንን ሊወድ ነበር ታዲያ። እሷስ "ባሌን እወደዋለሁ" ... ፓ ተናግራ ሞታለች እና ምን ይጠበ። ባልን መውደድ የተለየ ብቃት የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲያስመስሉ ያገርመኛል። መዋደድ ምንም የሚስትህም ብቃት አይደለም። (ሰምተኃል) ፍቅር ለሁሉታችሁም ያደላችሁ ፀጋ ብቻ ነው ! ፍቅር የተጠራሞተበት የውሻሸት አብሮነት የተሸከመ ጎጆ ሁለት ያልተመቻቹው ሬሳዎች ያቀፈ የአባቢ ሳጥን ነው !! ለስንቱ በነጭ ሸሉ ስር ጥቁር የውስጥ ልብስ ለለበሰ ትዳር ሃይሎጋ ብለናል !"

"እና በዚች ምድር በጥልቀት ማሰብ ያለብህ ነገር ፍቅርህን ማን ላይ እንደምትጥል ነው። መቋጠ የከበረውን እንቁ አሳሞች እግር ስር አትጣሉ ሲልህ ቀልድ መስሎህ ችላ እንዳትል። ይሄ ለሴትም ይሰራል። ስንቷ መሰለችህ ያላትን ማንነት አራግፋ ለአንዱ አሳማ አፍቃሪ ሰጥታ አፍንጫሽ ብ ስትባል አይሟ ልኳን ከራማዋ እንደተገፈፈ የውሻሸት ኖራ ያለፈች ! ካላመንክ እዚሁ አዲስ አበባ አንዷን ኑሮ የተመቻት የምትመስል ቆንጆ ጠጋ በልና "እህ..." ብለህ አድምጣት። ከአድማዋ በላይ ብሶት ትዘረግፍልሃለች። ብሶት የሌላት ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት ካገኘህ ወይ አድማዋ ለአቅመ ብሶት አልደረሰም አሊያም ከባቄላ ፍላት ያመለጠች ጥሬ ባቄላ አጋጥሞሃልና ፈጣሪህን አመስግን። ሆ ይፍጀው ብሎ እየተሸቀረቀረ ነው እንጂ ከተማው ሁሉ በፍቅር ቁስለኛ የተሞላ ማገገሚያ ሆስፒታል እኮ ነው። ሁሉም አንድ ቀን ባንድ ላይ የብሶቱን ያህል ሰቅሰቅ ብሎ አስኪ.ወጣለት በያለቅስ አዲስ አበባ ሳይብቻ ትልልቁን ሕንፃ ሁሉ እንደጀልባ የሚያንሳፍፍ የእንባ ባሕር ይፈጠር ነበር !!"

ደግሞ አንተ ቀለል አድርገህ የምታየው ነገር ለሴቶች እንዴት ትልቅ ታሪክ መሰለህ ... እደዋ ነው እውነቱን ነው። በቅርቡ የተዋወቅካትን ፍቅረኛህን ያለፈ ሕይወት ብትጠይቅ (ባትጠይቃም የካዳትን ፍቅረኛዋን ርኩሰነት፣ እርዮሰነት ያሳያል ብላ ያሰበችውን ተረት ብቻ ነው) ሰምቶ ትነግርሃለች ... ችግሩ የምትነግርህ መናገር ያለባትን ሳይሆን የርሷን ታማኝነት፣ ታጋሽነት፣አፍቃሪነት፣ እያወራችሁ እያለ ትክዝ ብላ እንዲህ ልትልህ ትችላለች፣

"ዘነበ የሚባል ፍቅረኛ ነበረኝ። ስምን መልዓክ ያወጣዋል። ቢያገኘበት የሚዘንብ። እና አንድ ቀን እዚህ ቶታሉጋ አበራሽ ሥጋ ቤት ከራሴ ጓደኛ ጋር ... ማንትስ ድርጅት ሴክሬቴሪዋ ... ከእሷ ጋር እየተጎራረሱ ቅቅል ሲበሉ በዓይኔ በብረቱ አየኋቸው ... ድሮም ወንድ ማመን' ብላ እንባዋ በዓይኗ ግጥም፡ እኛ ታዲያ፣ ቅቅል መብላት ምን ይገርማል... ብለህ ካሰብክ አለቀልህ። 'ቅቅል' ቅኔም ሊሆን ይችላል፤ እኛ ጠበስኳት ስትል እሷ ትልቅ የተረት ብረትድስት ውስጥ እየቀቀለችህ !"

ወይኔ ጉዴ ብቻዬን ባዶ ቤት ተቀምጬ በሐሳብ ሰባዝን ማበዴ ነው መሰል። ፊቨን እያሳቸከ ማሰ

አልቻልም ነበር። ትንሽ ዝም ካልኩ፣ "ምን ሆንክ የኔ ማር ... መሥሪያ ቤት ተጋጨህ... አመመህ ... ራበህ..." ቢቃ ንዝንዝ ነው። እሁን እስከነገ ወዲያ ባስብ ማን ከልካይ አላብኝ - ሃሌ ሉያ !!

እና ከሚስቴ ፌቨን ጋር ልፋታ የመፈኤረሻው የፍርድ ቤት ቀጠሮዬ እንደነገ ሆኖ እንደዛሬ ማታ አንድ ቦግ ላይ ኩርምት ብዬ እንዲህ የባጥ የቆጡን ሳስብ ሌሊቱ ተጋመሰ። "አብርሽ እስካሁን አልተኛህም" የሚል ድምጽ ሰምቼ ቀጥ ብል ማንም በቤቱ የለም ... ግን የሆነ እናቱ ላይ እሳት የመሰለ ወርቃማ ፀጉር የሚንቀለቀልበት ፍጡር ውልብ ሲል ያየሁ መሰለኝ ነበር። በስመአብ ("የማርያምን ብቅል ፈጭቻለሁ እንቺ ...")። በራሴ አባባል በደረቅ ሌሊት ኩት ብዬ ሳቅኩ። እስቲ አሁን ምን አሳቀኝ። አይይይይይ ያ እኛ ሰፈር የነበረው ጃንቦ የሚባለው ሰውዬ ልክ የዛሬ ሃያ አመት መወፈፍ ሲጀምር ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት እንዲህ እንደኔ ከትከት ብሎ ስቆ ነበር አሉ። ማበዱንስ ልበድ ... ግን እንጀራ ፋሽኑ ያለፈበት እስተባበድ አብዳለሁ...

ሰነገሩ የሳቅኩት ነገ ዳኛዋ ስታፋታን ምን እንደምንል እስቢ ነው። ቆይ ሰው ሲጋባ በሐዘን ቢሆን በደስታ፣ በጤና ቢሆን በሕመም አብሬያት ... አብሬው ልሆን ምናምን ተብሎ ቃል ይገባል። ባልና ሚስት ሲፋቱ ምን ይሆን የሚሉት። ሰው ሲፋታ አይቼ ስለማላውቅ ግራ ገብቶኛል ...

*በመንገድ ቢሆን በሥራ ቦታ፣ በፒያሳ ቢሆን በመርካቶ፣ የደረሰችበት ላልደርስ ... ሃሃሃ*

እኔና ፌቨን ስንጋባ ያጋቡን የእናቴ ንስሃ አባት መምሬ አምሳሉ ነበሩ። እሳቸውየሚሉትን እየተከተልኩ እንድል አዝዘውኝ ነበር። በነገራችን ላይ መምሬ እኔን ስለማያምኑኝ ቶሎ ቃሌንብቼ በቀለበት ሲታሰር ለማየት ቸኩለው ነበር። እናቴንም ብለዋታል፣

"አዬ አብርሃም ሳገባ ነው ሲልሽ አምነሽ በሬ አስገዛሽ፣ እንጀራ ጋገርሽ፣ ዳስ አስጣልሽ..."

እና ሲያጋቡኝ መስተዋቱ በተሰነጠቀ መነፅራቸው እናት በጥርጣሬ እያዩኝ ነበር ቃል ያስገቡኝ፣

"በጥጋብ ቢሆን በርሃብ ከጎኗ ልሆን ቃል እገባለሁ!" አሉ።

"ብጠግብም ባልጠግብም ቃል እገባለሁ!" አልኩ ተቀብዬ፤ እኔ አሳጠርኩ ብዬ ነው።

"አብርሃም ... ተው በሰርግህ ቀን እንኳን ያላዘዙህን አታውራ" በማለት ስርገኛው ሳይሰማ ወደእኔ ጠጋ ብለው አንሾካሾኩ። ፌቨን በሳቅ ፍርስስስስ ! ፌቨን ያሳቃት ገብቶኛል። ብዙ ጊዜ ትለኛለች፣ "አብርሽ

አንተስ እንዳንዴ ወሬ ስትጀምር ከጉዳዩ ጋር የማይያያዘውንም፣ የሚያያዘውንም ትቀላቅለዋለህ ስለደገመላት ነው የሳቀችው። መምሬ ግን በፈሽንም ሳቅ ተቆጡ፣

"ኤዲያ አንቺ ደሞ እስቲ ለሰርግሽ ቀን እንኳ በልኩ ሳቂ..." ብለው የሆነ ነገር በግዕዝ ተናገሩና በአማርኛ ተረጎሙት፣ "ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳሉ።" መምሬ የሚሉትን እኔና ፈሽን ተከትለን ገባን። ምነው የዛን ጊዜ፣

"ባሌ ሳይፈቅድ ቅንጣት ፀጉር ላልቆረጥ" የሚል ቃል ጨምረውልኝ በነበረ...

***

ፍርድ ቤት ስደርስ ግቢው ውስጥ የፈሽን እናት፣ ወንድሟ፣ ፈሽንና ያች ማሜ የምትባል ተደርድረው ተቀምጠዋል። በቀጥታ ሄጄ ማዘርን ሰላም አልኳቸው። "አብርዬ" ብለው በሁለት እጃቸው ሰላም አሉኝ። ልዘ እንደሆን ባለሥልጣን ነበር ያከበሩኝ። ውስጤ የሆነ ሕመም ተሰማው። የባሰ ያገኘሁት ደግሞ ወንድሟ በስርዓት ሰላም ሲለኝ ... ከሌታው ንትብ ያለ ሸሚዝ ለብሷል። እያለሁ፣ እያለሁ ግን በስርዓት ሰላም አሉኝ። ዛሬ ሰዉን ሁሉ ምን ነካው ብዬ ተገረምኩ። ችሎቱ እስከሚጀመር እስክ ተቀመጥን። ፈሽን በፍርሃት እልፍ አልፎ ቀጥ እያለች ታየኛለች። ፀጉሯን በጥቁር ሻሽ አስራዋለች።

ዳኛዋ እንዴ እየት አድርጋኝ ገባች ...

"እና ሐሳብህን አልቀየርክም አብርሃም" ንግግሯ ተለሳልሷል።

"አልቀየርኩም"። ዳኛዋ እንደማሰብ አለች እናም ያለምንም ውጣ ውረድ ከሰዓት ቀጠሮኝ ልታፋታን። ከችሎቱ ስወጣ ፈሽን እንደ ጀቢራ ድንገት ፊቴ ተገተረች። ሁሉም ነገር ስለቻት እንዳገባ ታስታውቃለች። እናም አየችኝ፣ በጣም አየችኝ። ዓይኖቿ በእንባ ተሞሉ። ከንፈሯ ይንቀጠቀጥ ልታብድ መስሎኝ ነበር።

"አትረባም ...አብርሽ አትረባም" ብላኝ ልትሄድ መንገድ ከጀመረች በኋላ ተመልሳ እጇን ስትዘረጋ በጥፊ ልትመታችኝ ብዬ ዓይኔን አጨናበስኩ። ፈሽን ግን ምን እንዳደረገች ታውቃላችሁ። ፀጉሯ ላይ ያየችውን የሆነ ነቀጥ ነገር አንስታልኝ ቀስ እያለች በርቀት ወደሚጠብቋት ቤተሰቦቿ አዘገመች። ምን ማለት ነው። ማንም ይሄ ምን ማለት እንደሆን መግለፅ አይችልም። ደግሞ ልታስመስል አልሞከረም

አውቃታለሁ ፌቨንን።

ፈዘዝ እንዳ ጥግ እንደቆምኩ ማሜ የምትባለው ደንቃራ ቤትዮ ፊት ለፊቴ እየተውረገረገች መጣች። የለበሰችው አጭር ቀሚስ ለመራመድ እስትግሯታል። ያደረገችው ጫማ ረዥምቋመቷን የባሰ ብቅል አውራጅ አድርጎታል። ሁሉም ሰው እየተገላመጠ ያያታል። ቅላቷ የሚያንበገብግ ነገር ነው። አጠገቤ ስትደርስ የዙሪያዬ ዓየር በሽቶ ጠረን ተሞላ - የሚያፍን ነገር።እንደወትሮው አላሽካካችም፣ አልሶኮችም፣ በታፈነ ግን በሚያስፈራ ጠንካራ ድምፅ እንዲህ አለችኝ፣

"አብርሃም ... እንደማትወደኝ አውቃለሁ። የራስህ ጉዳይ ነው፤ ወደድከ አልወደድከ ምን ልትቀንስብኝ። ደግሞም ማንም እንዲወደኝ አልፈልግም ለየትኛው ኢድሜ" አለችኝ። አነጋገሯ በታሪክ ከቧ ይወጣል ብዬ አስቤው አላውቅም። ኧረ መኮሳተር ! ቀጠለች፣ "ፌቨን ላንተ ብላ ሥራ አንዳቋረጠች አያወቅከ፣ ከነቤተሰቧ በርሃብ እየቀጣሃት ነው። ብትጠላኝም እኔ አከብርሃለሁ። እንዲህ ዓይነት ተራ ሥራ ትሰራለህ ብዬ አላስብም። ፌቨን እየተራበች ነው ...ይገባሃል አብርሽ"። በቃ ይሄን ተናግራ ተመልሳ ሄደች - መርዝ ! በሰከንድ አዕምሮዬን ገለባበጠችው። ርሃብ አልወድም። በተለይ የሴት ልጅን ርሃብ አልወደም። ካፌ ገብቼ እንኳን ሴት ልጅ ቶሎ ቶሎ ስትበላ ካየሁ ታሳዝነኛለች። ርሃብ አልወድም። ርሃብ ማለት ምግብ አለመብላት ብቻ አይደለም። በምድር ላይ በጣም ትንሹን ነገር የዕለት ጉርስን የሚሰጠን ሰው ማጣት ማለት ነው ለኔ ... ርሃብ አልወድም !

ፌቨን ራብኝ ካለችኝ ምንም ልሥራ ምን እርግፍ አድርጌ ትቼ ወደ ምግብ !! ፌቨን እኮ ስትራብ ስታሳዝን በእግዚአብሔር ! እነዛ የሚያማምሩ ጣቶቿ ሳይቀሩ ኢቃ ማንሳት አይችሉም። በቃ በተፈጥሮዋ ረሃብ አትችልም። ቆይ ግን ስንት ቀን ተርባ ይሆን ...የኔ ተራ ኩርፊያ ስንት ቀን አንድን ቤተሰብ አስርቦ ይሆን ...እግዜእ እንዴት ዓይነት ድድብና ውስጥ ነኝ ! የፌቨን እናት ማሉትኮ አገር ያወቃቸው የተራበ ሁሉ ቤታቸው ገብቶ ጠግቦ የሚወጣ ደግ እናት ነበሩ። ዛሬ ጊዜ ጥሏቸው የአንድ ጭንጋፍ እጅ ጠባቂ ሆነው እኔም ወጉ ደርሶኝ አንድ ቤተሰብ አስርባለሁ። ትላንት የበላሁት ፒዛ ግማሹን ነካክቼ የመለስኩት፣ ዛሬ ጠዋት የበላሁት ቋንጣ ፍርፍር ትዝ አለኝ - ሆዳም ነኝ ! ደደብ !!

ምሳ መብላት አልቻልኩም። ቀጠሮው እስኪደርስ ውኃ አገዝፍ እዛው አካባቢ ያለ ካፌ ቁጭ አልኩ።

ከሰዓት ፍርድ ቤቱ ስደርስ ወደነ ፌቨን ሄድኩ።

"ፌቨን" አልኳት። ቀጥ ብላ አየችኝ እና መጣች ወደኔ።

"ሳናግርሽ ነበር..."

በጓሮ በኩል ወዳለ ቦታ ሄድን። እኔ ከመናገሬ በፊት የፌቨን እንባ ተዘረገፈ። በእንባዋ ውስጥ እያየችኝ እንዲህ አለች፡

"አብርሽ ይቅርታ፣ ሁሉም ነገር ይቅር በማርያም አትለየኝ - እወድሃለሁ" አሁን እኔ እንዲህ የሚለመን ምን ነገር አለኝ፤ ምንም። ራሴ አስጠላኝ ከምር። ቀስ እያልን ወደ ዋናው በር አዘገምን። ማለት ፌቨን አንድም ቃል ባትናገር ደስታዬ ... የእሳት አለንጋ ... ነገሮች ሁሉ አንዳንዴ ይገለባበጣሉ። ዝም ብለን ወደ ውጭ፡ ከኋላዬ ምን ሰማሁ፣

"አቶ አብረሃም ዓለምሰገድ እና ወ/ሮ ፌቨን..." የቸሎት ተራችን ደርሶ ሥማችን እየተጠራ ነበር። (እንዳልሰማ ከግቢው ውልቅ፣ ሁሉንም እዛው ጥለናቸው) አንድ የምንወደው ሬስቶራንት ነበር እኔና ፌቨን የምንሄድበት። እዛ ተገኘን፡፡ ፊት ለፊቴ ተቀምጣ ፌቨን ታየኛለች። እናም በሚንቀጠቀጡ እጆቿ እጄን ያዘችኝ።

"ተሳስቻለሁ"። ስትገርም፣ ይሄን ሁሉ የምታደርገው አንድ ተራ ወንድ መለማመጥ ፈልጋ እንዳልሆነ አውቃለሁ። ፌቨን ምንህዜም ከሴትነቷ ሰው መሆኗ የሚቀድምባት ልጅ ስለሆነች እንጂ። እና ሳላስበው መለፍለፍ ጀመርኩ - ያውም ሳላባራ። ፌቨን ዓይን ዓይኔን እያየች እንዲወጣልኝ ታዳምጠኛለች።

###

"አራት ኪሎ ፈርሶ ውብ ሕንፃ ተገነባበት። ትዝታው አብሮ ፈረሰ። ኧረ ትዝታችን ሲባል ፀሐ ልማት ተባልን። ከዛ ጭርንቁስ የጭቃ ቤት ይሄንኛው ውብ ሕንፃ መሻሉን ሳናውቅ ቀርተን ነው ? አይደለም ፌቪ ... ሰው ከሲጋና ከደም ብቻ አይደለም የሚሰራው። ማንነቱን ደግፎ የያዘው የትዝታ አፅም የመላመድ አጥንት በውስጡ አለ ! እሱን ነው ያፈራረሱት ! መቼም የማይለማ ማንነታችንን ነው ያወደሙት። አሁንም ፀጉርሽ ትዝታችን ነበር ... ትዝታችን ሲፈራርስ ... ፋራ የሴቶች አኩልነት ያልገባው ምናምን ይሉኛል ፌቪ ... ያኔ በፍቅረኛነት ዘመናችን የቀጠርሽኝ ቦታ ስትመጪ እዛ ማነው ስሙ ኪዎስክ ጋር ስትደርሽ ፀጉርሽን ንፋስ ሲበትነው ... ከሩቅ ጥቁር ፀጉርሽ ንፋስ ሲያራውጠው ... በእጅሽ መለስ እያደረግሽው ወደ እኔ ስትመጪ ... ፀጉርሽ የፍቅር ባንዲራ ነበር የሚመስለኝ - ባንዲራዬን ነው የቆረጡብኝ ፌቪ..." ፌቨን እጆቼን እያሻሸች ዝም ብላ ታየኛለች። አውራ ጣቴን ይዛ የምታሰለፈልፈኝ ነበር የሚመስለው...

ላሚታየው እና ለሚዳሰሰው ማንነታችን ስንት የማይታዩ ጥቃቅን ማንነቶች አሉ ... እነዚያን እየቀፈቀፍን ባዶ ግንዱ የቀረ እንቧቴት በመብት ስም እንድናቅፍ ለምን ይገፋፉናል - አልፈልግም ! ባንዲራዬን መሬት ጥላ ቆሻሻ አድርጋዋለች ብዬ አዝኜብሻለሁ። ከጥራጊ ጋር ያንውብ ፀጉሯን ወደ ግንዳ እንዲወረውሩ ፈቀድችላቸው ብዬ አዝኜብሻለሁ ፌቪ ... እራት ኪሎን ሲያፈርሱት በታው የኛ ስላልሆነ ዝም ብለናል ... ሚስቴ ግን የኔ ነች ... የጋራችንን ትዝታ ስታፈራርስ እንደ መንገደኛ መኼስ ምን ይደረግ ብዬ ዝም አልልም።የአጂ ልሰሳሴ፣ የከንፈሯ ጣዕም፣ ፈገግታዋ ሁሉ ሕዝብን ነው የሚወክለው በፀጉሯ ባንዲራ ... ይሄን ፀጉር መቁረጥ ድንበር ከመገንጠል ሳይቼ አላየውም ብዬ በቻዬን ተማርሬብሻለሁ ፌቪ" ፌቨን እንባዋ ጉንጯ ላይ እየፈሰሰ ዝም ብላ ታየኛለች...

"ፌቪ አስጠልተሽኛል፣ አበሳጭተሽኛል፣ የናቅሽኝ የገፋሽኝ መስሎ ተሰምቶኛል። እኔን ከሕይወትሽ ገፍትረሽ ሌላ ሰው ከሰውም ሰው ማሜ የምትባል ሴትዮ የኔን ቦታ የሰጠሻት መስሎኛል። እና አፈቅርሻለሁ !!"

ፌቨን ትንፋሽ እስኪያጥረኝ ከንፈሬን...

ቅድም ሲያፋታን የነበረው ሕግ በአደባባይ ከንፈር ለከንፈር መሳሳም ወንጀል ነው ይላል አሉ! ይበላ ...!

የፌቨን እንባ ይፋጃል !!

# አረንጓዴ መፈክሮች!!

ይሄ አዲሱ የመሥሪያ ቤታችን 'አትክልተኛ' ለተክሎች ዕድገት የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮችን ጥቀስ ቢባል "አየር፣ ውኃ እና መፈክር" ሳይል አይቀርም። እንዴ...! በመፈክር ግቢውን ሞላው እኮ...! ወደ የትም ቢዞር መፈክር ነው። "...እናደርጋለን፣...እናሳካለን፣...እንደማስሳለን፣...እንንዳለን...፣ ...ተረት እናደርጋለን..." ፣ ያውም በደማቅ ቀይ ቀለምና በተወላገደ የእጅ ጽሑፉ። ይኼስ ባልከፋ ! ጭራሽ በየቢሮው እየዞረ "ዛሬ የለጠፍኳትን መፈክር አያችኋት ? ስትወጡ አንብቧት፤ ወቅታዊ ናት" እያለ ማስቸገሩ።

መሥሪያ ቤታችንን ድፍን አገር የሚያውቀው በሁለት ጉዳዮች ነው። አንዱ በሚሰጠው ዝርክርክ አገልግሎት፣ ብሎም ተገልጋዮችን እግራቸው እስኪቀጥን በማመላለሱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ሰፊና ውብ በሆነው የአትክልት ቦታው ነው !! ሁለቱን እውነታዎች በመቀላቀል "ግቢያችን የለመለመው ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጣችን ተማረው በየቀኑ በሚያፈሱት እንባ ይመስላል" የሚል የተጋነነ ልቦለዳዊ ዓረፍተ ነገር መፍጠር ይቻላል። እንደ አትክልተኛው መፈክር ቢረዝምም !!

የመጀመሪያው አትክልተኛ ሙቶ አሊቃ (ዋና ስማቸውን አላውቀውም) ቀን ከሌት ቢሰሩ የማይደክሙ ፍጡር ነበሩ። ከኃላፊያችን ጀምሮ የእጅ እጣቢውን ወደአትክልት ቦታው የረጨውን ሁሉ 'የልማት አርበኛ' እየተባለ የሚሞካሸበትን ግቢ ያቀኑት ድኼው ሰውዬ ነበሩ፤ ያውም አምስት ሳንቲም በጀት ሳይያዝላቸው፤ በራሳቸው ጥረት።

የዛሬ አስር ዓመት መንግሥት "ጥቢቃና አትክልተኛ" የሚል ስም ብቻ እስታጥቆ፣ በአራት መቶ ምናምን ብር ደመወዝ፣ በወዳደቁ በርሜሎች፣ ባረጁና አገልግሎት መስጠት ባቆሙ መኪናዎች፣ የመኪና ጎማዎችና ባራሙቻ ወደተሞላው አስቀያሚ ግቢ ለቀቃቸው፤ ሙቶ አሊቃን። እዉነት ለመናገር እነዚህ ሥጋቸው አልቆ በአጥንታቸው የቀሩ ሽማግሌ ያኔ ምንም ይፈይዳሉ ብሎ የጠበቃቸው ሰው አልነበረም፣ ግን በጥቂት ዓመታት ውስጥ አስማት በሚመስል ሁኔታ ግቢውን ወደ ግሩም መናፈሻነት ቀየሩት።

ሲበዛ ዝምተኛ እና ብቸኛ የሆኑት መቶ አለቃ ከየመንደሩ ችግኝ እየለመኑ፣ አፈር በጆንያ እየተሸከሙ ይህን ግቢ እንደገና ፈጠሩት። "ኤዲያ ግቢ ብቻ...! አትክልት ብቻ!" ይላል በአገልግሎታችን የተበሳጨ ባለጉዳይ። መፈክር ሲደርት የኖረ አለቃ እና ምንዝር ሁሉ ቃል ከማይተነፍሱት ሽማግሌ የሥራ ፍቅርንና የለውጥ ሃዋሪያነትን ተመለከቱ። ያላየ ቢመስልም !! ደግነቱ መቶ አለቃ አዩኝ አላዩኝ ብለው የሚጨነቁ ሰው አልነበሩም። የእርሳቸው ብቸኛ ደስታ የተከሉት ሲበቅል፣ ትላንት የተከሏት ችግኝ ላይ አበቦች ሲፈነዱ ማየት ነው። ዛፎቹ ላይ ወፎች ጎጇቸውን ሲቀልሱ፣ አሞራዎች ከረዥም በረራ አረፍ ብለው ሲያልፉ መመልከት ነው።

የግቢዮችን ውብት ተዓምር ነበር። የዛፎቹ በቁመትም ይሁን በግዝፈት እኩል መሆን፣ የአከረካከማቸው አለመዛነፍ፣ ራሳቸውን ዛፎቹን በሆነ መንገድ አባዝተው የደረደሯቸው እንጂ እውነት የተለያዩና ራሳቸውን ችለው ያደጉ ዛፎች ናቸው ለማለት ይከብድ ነበር። የአበባ መደቦቹ ዓይንን ለመንቀል የሚፈትን ውበት የፈሰሰባቸው ነበሩ። የግቢው አየር የተለየ አፎይታን የሚፈጥር ድባብ ነበረው።

ታዲያ የዛሬ ዓመት አካባቢ መቶ አለቃ ወደ ኃላፊው ቢሮ ድንገት ተጠሩ። ትኩስ አፈር የለበሰ ቁታቸውን ጭቃ ባዘለ ቡት ጫማቸው ለብሰው ወደ ኃላፊው ቢሮ ገቡና የተሰበሰብነው የማኔጅመንት አባላት ፊት እጃቸውን ወደኋላ አጣምረው ቆሙ። ልክ ፍርድ ቤት ዳኛው ፊት እንደቆመ ተከሳሽ ነበር አቋቋማቸው። እርጌ ኮፍያቸውን አውልቀው በእጃቸው ስለያዙ የሚበዛው ነጭ ሽበት የወረረው ስስ ፀጉራቸው ዕድሜያቸውን ያሳብቃል።

"መቶ አለቃ !" አላቸው ኃላፊያችን በሥርዓት ተቀመጡ እንኳን ሳይላቸው፤

"አቤት ጌታዬ !" በአክብሮት ከወገባቸው ጎንበስ ቀና እያሉ፤

"ዛሬ ያስጠራንዎት የመሥሪያ ቤቱን ሕግና ደንብ የሚፃረር ድርጊት እየፈፀሙ መሆኑ 'ስለተደረሰበት' ስለሱ ለመነጋገር እና ለመተራረም ነው" አለ ኮስተር ብሎ። "ፈገግ ካልክ ሥልጣንህ ይከስማል" የተባለ ይመስል ከመሬት ተነስቶ ግንባሩን መቋጠር ይቀናዋል አለቃችን።

"ማ ...እ...እኔ ነኝ የሚፃረር ድርጊት የፈፀምኩትን?" አሉ መቶ አለቃ ደንገጥ ብለው።

"እዎ....! በሥራ ሰዓት መጠጥ ጠጥተው ነው የሚገቡት የሚል! 'ኢንፎርሜሽን' ደርሶናል። ይሄ ደግሞ ከአንድ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ አይጠበቅም..." አላቸው።

"እ… ለዚህ ነው እንዴ!" አሉ የተጨነቀ ሰውነታቸውን ዘና አድርገው፤ የተመጣጠነ የሽማግሌ ፈገግታ ፊታቸው ላይ እየታየ። ሁላችንም በአባባላቸውና በሁኔታቸው ግራ ተጋባን።

"እንዴት ለዚህ ነው አንዴ…?" አለ አሊቃችን ይበልጥ ቆጣ ብሎ። ድርም ከባድ ብሎ የሚናገረውን ነገር እካብደው ካላዳነቁለት ይከፋዋል።

"አጠጣለሁ…! ይሄ እኮ ድብቅ አይደለም፤…ጧት ስገባ አንድ ብርሌ ሸተት አድርጌ ነው የምገባ… ለምሳም ቢሆን…ያው ለማወራረጃ አንድ መቅመሴ ዛሬ የተጀመረ ነገር አይደለም…" አሉ ዘና ብለው፤

"ይሄ በጣም … በጣም ትልቅ ስህተት ነው፤ …ከራስዎ ተርፎ ለሌሎችም ሠራተኞች መጥፎ አርአያ መሆን ነው እኮ…! መቶ አሊቃ ምን ነካዎት!?"

"እሃ! ምን ያደራርሰኛል? ሽተተን አንዳይሉ እነሱ የሚውሉ ቢሯቸው ነው፤ እኔ የምውል ውርማ ለውርማ…፤ ሳርም ስኮተኩት 'ሰክሮ ተናገረን' አይሉ ቃል ከአፌ ወጥቶ አያውቅ፤ ምኑ ላይ ነው ስህተቱ…?" አሉ በኃላፊው በሉቶ አሥራት ቁጣ ቅንጣት ታህል ሳይሸበሩ።

ኃላፊው ግንባሩ ላይ ደም ሥሩ በግልጥ እስኪታይ ተጋድሞ "እንግዲህ መቶ አሊቃ እኛ ብዙ ሥራ አለብን፤ ባጭሩ ሁለተኛ ይህን ስህተት እንዳይደግሙት፤ ጨርሻለሁ!!" አለና ወደማኔጅመንት አባላቱ መልከት ሲል ሁላችንም ተስማምተን ሳይሆን መስማማታችንን ኃላፊው እንዲያይልን አንገታችን እስኪንቀጫቀጭ ራሳችንን ናጥን፤…ልማዳችን ነው !!

መቶ አሊቃ ኮስተር ብለው "እንግዲህ እኔ ከልጅነቴ ነው የማር ጠጅ መጠጣት የጀመርኩት…፤ ካልጠጣሁ ጅማቴም አይፍታታልኝ…፤ ዓይኔም አይገለጥ፤ እርስዎ ፊት እሺ! እሺ! ብዬ… ተደባብቆ ኑሮ አላውቅም፤…ሰው ላይ አልደረስም…፤ሥራዬንም አላስተጓጉልም፤ ግ…ን ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያደገብኝን ነገር ዛሬ ተነስቼ ….እኔም ልተውህ አልለው…እሱም እሺ ብሎ አይተወኝ፤ …እህሱስ ከጉሮሮዬ እንዴት ይወርድልኛል…?!!" አሉና እቅጩን ተናገሩ።

ከዛች ቀን ጀምሮ ኃላፊያችን የመናቅና የመዋረድ ስሜት ስለተሰማው በየምክንያቱ ቢሮው እየጠራ ይነተርካቸው ጀመረ። በመጨረሻ ንትርኩ ሲበዛባቸው ከኖሩበት ግቢ የእጃቸውን አቢራ አራግፈው ቀሩ - ቀሩ!!

"አንድ ሰካራም መጣ ቀረ !!" አለ ኃላፊያችን። በመስማማት ራሳችንን ናጥን 'የማኔጅመንት' አባላት !! ልማዳችን ነው !!

###

አዲስ የተቀጠረው አትክልተኛአቶ አውግቸው ይባላል፤ (ሰምን መልአክ ያወጣዋል)። ይሄ ሰው ሁለት አንድ ሐሙስ የቀራቸው ችግኞች ይተክልና ዙሪያቸውን አምስት መፈክር የተፃፈባቸው የባውላ ሰሌዳዎችን ያቆማል። ችግኞቹ በሰፋፊዎቹ የመፈክር ሰሌዳዎች ስለሚከበቡ ፀሐይ እንዴት ያግኙ? ደግሞ መፈክሩ፡ከመንዛዛቱ ለዛ ቢስነቱ !! አትክልቶቹን እንደመፈክሮቹ በሚገባ ስለማይንከባከባቸው ከጥቂት ወራት በኋላ አትክልቶቹ ሁሉ ደርቀው መፈክሮቹ በደረቁ አበቦች መሀል ከፍ ብለው ታዩ።

"አረንጓዴ ተክሎች የሕይወት መሠረት፡ ለምድራችን የህልውና አውታር እንዲሁም የዓይን ማረፊያ ናቸው !!" አሁን ይሄ ገና ድሮ በጋርዮሽ ሥርዓት ጊዜ የነበሩ ሰዎች የሚያውቁት የቀረፈደ ሃቅ አይደለም? ብራና የሚያስፍቅ፡ ቀለም የሚያስበጠብጥ ጉዳይ መሆን ነበረበት ? አንድ ቀን ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት የድርጅቱ ስብሰባ ላይ 'አትክልተኛው' "ቢመቻችልኝ አርሶ አደሮችን ስለዘመናዊ የጓሮ አትክልት ልማት ባስለጥን ፈቃዴ ነው፤ በሙያችን አገራችንን ማገልገል አለብን፤ ዝም ብሎ ቢሮ መኮፈስ ዋጋ የለውም" አለ።

ሾፌራችን አቶ ዘለቀ ታዳጊያ እንዲህ አሉ፣ "...ይሄ ሰው አርሶ አደር ሳሰለጥን የሚለው የቤቱን ማሳ ሁሉ በመፈክር ሞልቶ በርሀብ ሊጨርሰን ነው እንዴ?"

###

ግቢው በመፈክር ሰሌዳዎች ተጥለቅልቆ፣ ግድግዳው ላይ ቁጥር ስፍር የሌለው መፈክር ተለጥፎ መሥሪያ ቤታችን በመፈክርና በመልካም አስተዳደር እጦት ታዋቂ ሆነና አረፈው። አንድ ቀን ከቢሮዬ ስወጣ አዲስ መፈክር ቢሮዬ ፊት ለፊት እንደባለጉዳይ ቆሞ ተመለከትኩ። እንዲህ ይላል፡ 'የወለድናቸውን ልጆች እንደምንንከባከበው የግቢያችንን አትክልቶች እንንከባከብ !!" እንዲህ አሰብኩ፣ "ይሄ አትክልተኛ ሚስቱ ብትወልድ የእመጫቷን አልጋ በመፈክር ሳይከበው አይቀርም፤ ትውልድ በመፈክር የሚያድግ መስሎት።"

ትንሽ ቆይቶ አትክልተኛው በሰላም የኖረውን ግቢ በዘር ያናቀረው ገባ። ነገሩ የሆነው እንዲህ ነው።

የቤሔር ብሔረሰቦች ቀን በመሥሪያ ቤታችን በተከበረበት ሰሞን በዓሉን አስመልክቶ አትክልተኛው በተለያዩ ቋንቋዎች መፈክሮችንና ማስታወቂያዎችን ሰጠፈ። በማግስቱ በመሥሪያ ቤታችን የሚሠሩ አራት የደቡብ ክልል ተወላጆች ከየሥራ ክፍሉ ተጠራርተው በመደዳ በመቆም የአትክልት መደቡ

ላይ ሽንታቸውን ሲሸኑ በመታየታቸው በአትክልተኛው ተከሰሰው ኃላፊው ዘንድ ይቀርባሉ።

"እንዴት እዛ ቦታ ሽንታችሁን ትሸናላችሁ ? እናንተ የተማራችሁ አይደላችሁም እንዴ ? ፊት ለፊት 'መሸናት ክልክል ነው !' የሚል ጽሑፍ በግልፅ ተሰጥፎ ሕግ መተላለፍ ምን የሚሉት ቸልተኝነት ነው?" ሲል ኃላፊው እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ደነፋባቸው።

ሠራተኞቹም በብስጭት መለሱ።

"እንዳሉት ፊት ለፊታችን አትክልተኛው 'ሽንት መሸናት ክልክል ነው !' ብሎ መለጠፉን አይተናል። ግን ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ያረጋገጠልን በቋንቋችን የመጠቀም መብት በአትክልተኛው ተጥሶብናል። ማስታወቂያው በአማርኛ፣ በኦሮምኛ እና በትግርኛ ተለጥፎ በእኛ ቋንቋ ግን አለመለጠፉ ትልቅ የሙብት ጥሰት ነው። ስለዚህ ቋንቋችን እስኪከበርና እንደ ሌሎች ብሔሮች ሁሉ ማስታወቂያው በቋንቋችን እስኪለጠፍ እንሸናለን ! በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ መሸናታችንንም ጥያቄያችን እስኪመለስ አናቆምም !!" በማለት ተናገሩ።

ኃላፊውም ጉዳዩን በጥሞና ካደመጠ በኋላ ወደ አትክልተኛው በመዞር "ያቀረቡት ሐሳብ ተገቢ ይመስለኛል። አሁኑኑ በቋንቋቸው 'መሸናት ክልክል ነው !' የሚል ማስታወቂያ ቦታው ላይ ይለጠፍላቸው፤ ጨርሰናል!" ብሎ ከወሰነ በኋላ፤ "ምን ሁሉ ዓመት በበረሃ የታገልነውኮ..." በማለት ሰፋ ያለ የብሔሮችና ብሔረሰቦች እኩልነት ላይ ያተኮረ ጥልቅ ትንታኔ ሰጠ። ጥያቄያቸው መልስ ያገኘላቸው የደቡብ ተወላጆችም አለቃውን 'ሥልጣን ያዳብር !' ብለው እርስ በእርስም ተቃቅፈው በመሳሳም ደስታቸውን ከገለጹ በኋላ በመጭው ምርጫም ግንባሩን ፓርቲ እንደሚመርጡ ቃል በመግባት ወደ ሥራቸው ተመለሱ።

በቀጣዩ ቀን ግን በመሥሪያ ቤታችን ውስጥ ሌላ ነገር ተከሰተ። አትክልተኛው ቁጥራቸው ሰባት የሚደርስ ሠራተኞችን በጥበቃ ሠራተኞች እያስነዳ ይዟቸው ኃላፊው ቢሮ ደረሰ።

"ምን ጉድ ነው ይሄ ሁሉ ሰው !"አለ ኃላፊው፤

"ጌታዬ! የሚያሳፍር እኮ ነው ! እነህ ሁሉ ዛሬ አትክልት ቦታው ላይ ሲሸኑ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ሠራተኞች ናቸው" አለ አትክልተኛው።

ሰዎቹ ለምን እንደሸኑ ሲጠየቁ እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "እኛ የአፋር፣ ሐረሪ፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላና

ሱማሌ ክልል ተወላጆች ስንሆን አትክልት ቦታው ላይ የሸናነው ሌሎች ቢሔሮች ሁሉ በቋንቋቸው የተቀዳጁትን መብት ባለማግኘታችን፣ እንዲሁም በእኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ 'መሸናት ክልክል ነው!' ተብሎ ባለመፃፉ የተሰማንን ቅሬታ ለመግለፅ ነው። አሁንም ቢሆን እንደሌሎች ብሔሮች ሁሉ በየቋንቋችን ማስታወቂያው እስካልተፃፈ ድረስ በዘር፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አመለካከት ሳንለያይ እጅ ለእጅ ተያይዘን በመሸናት በራሳችን ቋንቋ የመጠቀም ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን እናስከብራለን!!" ሲሉ ከፍ ባለ ወኔና ቆራጥነት ተናገሩ።

ኃላፊው በዚህ ጉዳይ በመበሳጨቱ ማኔጅመንቱን ሰብስቦ ከመከረ በኋላ፣ በግቢው ውስጥ ማንኛውም ማስታወቂያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ እንዲለጠፍ ተወሰነ። በዚህም መሠረት ከማኔጅመንት አባላት የተውጣጣ 'የሽንትና ተያያዥ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ' ከተዋቀረ በኋላ ማስታወቂያዎችን በማዘጋጀት በየቦታው እንዲለጠፉ ተደረገ። በእርግጥ ይህ ውሳኔ መፈክር አምራቹን አትክልተኛ ልክ በማስገባት ግቢው ከመፈክር እፎይ ቢልም ከሳምንት በኋላ ግን ራሱ አትክልተኛው እዛው ቦታ ሲፀዳዳ በኃላፊው እጅ ከፍንጅ ተያዘ።

"እንዴት አንተ ራስህ እንዲህ ያለውን ሥራ ትሠራለህ?" ቢባል፣

"ጌታዬ ! እኔ እንግሊዘኛ ማንበብ አልችልም" ሲል ይቅርታ እንዲደረግለት ተማጸነ።

# ፀረ - ሰላሙ ሰርግ ቤት

"ለወንድም ጋሻው ዘሰቀ፣

ባለህበት…

የዘንካታዋ ልጄ አዛለች ለጥይበሉ ባንጃውና የጅግናው ልጃችን በላቸው ድግሙ ሰጥእርጌ የጋብቻ ሥነ ስርዓት የሚፈጠመው የፊታችን ሕዳር ሚካኤል ስለሆነ፣ ጠብ ርግፍ ብዬ እርጄና ጋርጄ ባሰናዳሁት የአንድ ልጄ ሰርግ ላይ ከአቶማቲክ ክላሽ ጠመንጃህ፣ ካልሆነም ከነዲሞፍተርህ፣ እሱም ባይሆን ከነምንሽርህ፣ ቢጠፋ ቢጠፋ ሽጉጥ ይዘህ ድግሴ ላይ እንድትገኝ በአክብሮት ጠርቼሃለሁ። ባዶ እጅህን ትመጣና ጊወርጊስ አይለመነኝ፣ ቀብርህ ላይ አልቆምም ዋ !

አክባሪህ ለጥይበሉ ባንጃው !"

ቢቃ እንዲህ ነው ሰርግ የሚጠራው ታዳሚው…

እንግዲህ በአካባቢው ባህል መሰረት አንድን ሰርግ ሰርግ የሚያሰኘው ተኩስ ነው። ከተማ አካባቢ የሰርግ መጥሪያ ካርድ ላይ፤ "ከነባለቤትዎ እንዲገኙልን" እንደሚባለው በዚህ አካባቢም ሰርገኛ ባዶ እጁን አብምሮ መገኘት ነውር ነው። ሰርግ ጠሪው ታዳሚውን ሲጠራ የመሳሪያን ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ በቀይ አስከሪብቶ ነው የሚያሰፍረው !

ሰርግ ላይ መተኮስ ያገሩ ደንብ የሕዝቡም ባህል ነው፤ ሲወርድ ሲዋረድ ከአያት ቅድም አያት የመጣ! ታዲያ የእለቱ ዕለት ሙሽራ ሲገባና ሲወጣ ምድር ቃጤ ትሆናለች። ሁሉም ለሰርጉ ያዘጋጀውን ጥይት እየፎከረና እየሸለለ ወደ ሰማይ ያንጣጣዋል። የደሃ አገሬት ጦርነት እስኪመስል። አገሬው የሰርግን

ውብት ሲለካ "አይ ድግስ" አይልም ! "አይ የአከሌ ሰርግ ላይ የነበረ ተኩስ!" ነው የሚለው። እንደውም ሰው ሲሞት ሙሾ የሚወርደውና የሚገጠምለት በየሰርጉ ቤት በተኮሰው የጥይት መጠን ነው፤

"ተኳሽ ተኳሽ ... አድባሩ እንቀላፋ ማን ይተኩስበት፣

አንዴ ቀና ብለህ እስቲ እንደቅድቅበት"

እየተባለ ደረት ይደቃል እንባ ይራጫል። ብዙ ጥይት ሰርግ ላይ መተኮስ የቸርነት መለኪያ፣ የባለፀጋነትም መስፈርት ነው። ለወጣቶች ደግሞ ከዚህም ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው። ወጣቱ ሰርግ ቤት የሚተኩሰው የጥይት መጠን ውሃ አጣጩን ኮረዳ የመሳቢያ ዋናው መንገድም ነው። የኮረዳዎቹን ልብ ቁመና አያስደነግጠውም፣ ገንዘብ አያማልለውም ... ተኩስ ሲሰማ ነው ዘራፍ ብሎ የሚነሳው - የከጃሎት ቀልፍ ናት ተኩሷ ! ለዛም ነው የአካባቢው ወጣቶች ጠንክረው ሰርተው ጠመንጃና ጥይት የሚገዙት።

አቶ እርገጤ ታዲያ እዚህ መንደር ውስጥ ታዋቂ ሰው ነው። የተፈራ፣ የታፈረ። ግማሹን የመንደሩን ተጋቢ ሽማግሌ እየሆነ ያዳዳረው ይሄው ጋሽ እርገጤ ነው። አንዱን ወጣት ይጠራና፣ "አንተ እንደው ቆመህ መቅረትህ ነው ቢቃ ? ምናለ የአቶ አከሌን ልጅ አየት ብታደርጋት ? አበባ የመሰለች..." ቢቃ ወጣቱ ቀልቡ ይቆማል። የአቶ አከሌ ልጅ ወንዝ ውሃ ስትቀዳ፣ ጫካ እንጨት ስትለቅም እስኪሰለቸው ዓይቷት ፉንጋ መሆኗን ገና ድሮ ለጓደኞቹ ነግሮ የተዋት ብትሆንም አቶ እርገጤ ሲመሰክሩላት መልዓክ ሆና ትታየዋለች። አቶ እርገጤ ከማዳዳሩ ጎን ለጎን ታዲያ ይሄን ሁሉ ዘመን ለመንደርተኛው የጥይትና የመሳሪያ ፍላጎቱን በማሟላት የቀኝ እጅ የሆነ ታዋቂ የጦር መሳሪያ ነጋዴ ነበር። ምንም እንኳን ሥራው ሚስጥር ቢሆንም ማንም ያውቀዋል ! በቀኝ ያዳድራል በግራ ጥይት ይሸጣል ! ይሄው ነው ሰጥቶ መቀበል !

አንድ ቀን ታዲያ መንደርተኛው የሚያጓጓ ወሬ ሰማ፣ "አቶ እርገጤ ሴት ልጃቸውን ሊድር ነው" የሚል።

"እገር ነደደ በለው" ተባለ።

"ለማን ነው የሚድራትሳ ?"

"ከዚህ ተኛ ወረዳ ራቅ ያለ ቢታ ወዲህ ወደ ቆላው አባቱ ታዋቂ የመሳሪያ ነጋዴ የሆነ ጉብል ነው አሉ"

"አ ... ሁን ተኩስ ቀን ወጣላት ! አድባራችን የተኩስ ጥሚ ቁርጥ ሊልሳት ነው" ይላል አንዱ። "እንኳን መንደራችን ድፍን ጦቢያ ድፍን አፍሪቃ ቃጤ መሆኗ ነው" ይቀበላል ሌላኛው እያጋነነ አፍሪካ የተኩስ ድምጽ የናፈቃት ይመስል ! ሹክሹክታው እውነት ሆነና መጥሪያ ለሁሉም ተልኮና ድግሱ በሰፈው ተሰናድቶ ሽር ጉድ ሲባል የወረዳው አስተዳዳሪ ከባድ ጉዳይ መኖሩን ገልፆ ነዋሪውን ለስብሰባ ጠራ። የስብሰባው ዓላማዎ ከበላይ አካል የተላከ እና አዲስ የወጣ ሕግ ለሕብረተሰቡ ለማሳወቅ ነበር።

ሕጉ እንዲህ ይላል፣ "በአንዳንድ ወረዳዎች በደስታና በሐዘን ጊዜ ጥይት የመተኮስ ልምድ መኖሩ ይታወቃል። ይሁንና ይህ ድርጊት የነዋሪውን ሰላም የሚያደፈርስ፣ ሕገወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን የሚያበረታታ ሆኖ ስለተገኘ ከዛሬ ጀምሮ በጥብቅ የተከለከለ ተግባር መሆኑን እናሳውቃለን !!"

የወረዳው ነዋሪ ተንጫጫ። ለጥያቄም እጁን እንደ ጭራሮ ወደላይ እንጨፈረረው። ሊቀመንበሩ ተራ በተራ ዕድል እየሰጡ የነዋሪውን ቅሬታ መቀበል ጀመሩ፣

"እሺ. አዛጋ አቶ እርገጤ..."

"እግዜር ይስጥልኝ ... ይሄ ሕግ በ'ውነቱ የሕዝብን ባሕል፣ ወግ፣ ወንድነትም ለማኮላሸት ሆነ ተብሎ የተሰናዳ ነው ... በፍጡም የወረዳው ነዋሪ አይቀበለውም።" ሕዝቡ አጨበጨበ። ሌላው ሰው ቀጠለ፡ "እኔ አስታራቂ ሐሳብ አለኝ ! መንግሥት መሳሪያውና ጥይቱ ሕገወጥ ነው ካለ ባሕላችንን ከማስቆም ይልቅ እንደ ማዳበሪያ፣ እንደ ስኳርና ዘይት ለምን ሕጋዊ ጥይትና መሳሪያ በሕብረት ሱቃችን በኩል በየወቅቱ አያቀርብልንም ?"

"የኔ አስተያየት ደሞ..." አለ ሌላው፡ "ሕጉ ሲወጣ መንግሥት አላማከረንም ! ቢሆንም አማራጭ ሳያቀርቡ ተኩስ አቁሙ ማለት ተገቢ አይደለም። ለምሳሌ ከተሜው ሲያገባ በእሳት እየለኮ የሚተኩሰው ... ምንድነው ስሙ ይ...ሄ ..." ስሙ ጠፋባቸው አስተያየት ሰጪው...

"ርጭት..." አለ አንዱ ወጣት።

"ርጭት አይደለም ርችት ነው የሚባል" ሌላው አረመው።

"አዎ ርችት ... ! እሱን እንደ አማራጭ ያቅርብልን እንጂ መተኮስማ ምን ሲደረግ ይቆማል ... አባቶቻችን አያቶቻችን ምን ይሉናል ... እንዲህ በየሰበቡ ካልተኮስንስ የመተኮስ እምሮታችን ተጠራቅሞ ድንገት አንድ ቀን ቢወጣ አገር ይተርፋል እንዴ ጌታው ?"

ጥኑ እንኳን አስተያየት ፃ"ነድን ነው..." አለ አንድ ጎልማሳ፣ "የኛ ወረዳ እንደሌላው ወረዳ ወደ ሰው አይተኩስም ... ይሄን ያህል ስንኖር ሰውም ሙቶብን አያውቅ ጌታው ... እና ከሌላው ወረዳ እኩል ሕግ ከምትጭኑብን የኛን ተሞክሮ ወደ ሌላው ወረዳ በማስፋፋት ሁሉም ወደ ሰማይ ብቻ እንዲተኩስ ቢፈቀድለት መልካም ነው" ጭብጨባ !!! "ሰርግ ባሩድ ካልሸተተው ሙሽራዋን ሰይጣን ይጣላታል፣ ትዳሩም አይሰምር ።ይሄ አትተኩሱ የሚል ትዛዝ መዳኒት እንደመከልከል ያለ በደል ነው..."

ተሰብሳቢው ለማግሽ ቀን ተቃውሞሙን ሲገልፅ ከዋለ በኋላ ሊቀመንበሩ በአጭርና ቆፍጠን ያለ ንግግር ስብሰባውን ደመደሙት፤

"ወገኖቼ እንግዲህ እኛ ይጠቅማል ብለን ጠብቀን እዚህ ያደረስነውን ተኩስ የበላይ አካል ለልጆቻችሁ አታውርሱ ታለን ምን ይደረግ ! የበላይ አትተኩስ ካለ አትተኩስ ነው፤ ተኩስ ካለም መተኮስ ነው ... በዕርግጥ ተኩስ ባሕላችን ነው ... ይሁንና ባሕልም እንደ ሰው ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል !"

ከስብሰባው ጥቂት ቀናት በኋላ የአቶ አርገጤ ደግስ ላይ ሕጉን በመጣስ መሳሪያ ይዞ የሚመጣ ሰው መኖርና አለመኖሩን የሚያጣራ የቀበሌ ሰው ቃፊር ቆሞ ነበር። ይሁንና ነዋሪው ሕግ በማክበር ሁሉም ባዶ እጁን አንገቱን ደፍቶ ወደ ሰርጉ ሲገባ ታየ። ሰርጉ ቤት ውስጥ ጎን ለጎን የተቀመጡ ወዳጆች በሹክሹክታ ያወራሉ፣ "እንደው ጭር አረጉን አይደለም ጭር ያርጋቸውና"

"አሄ የወዳጄን ሰርግማ ጭር አያረጓትም እኔ እያለሁ" አለ ሌላኛው።

"ምን ልትሆን መሳሪያ እንደሁ የለን ፣ እንደ ሴት ባዶ እጃችንን..."

"እሱን እንኳን ተወው ተመልከት ይሄን..." እለና ጋቢውን ገለጥ ሲያደርገው እጁ ላይ ሁለት እስራኤል ሰራሽ የእጅ ቦንቦች እንደ ስኳር ድንች ቁጭ ብለው ታዩ !

"ወይ የሃሳብ መግጣጠም እናትዬ" እለና ሌላኛውም ከቁምጣው ውስጥ ባርኔ ጨርቅ የተጠቀለለ የእጅ ቦንብ መሻረጥ አድርጎ አወጣ ! .

ሰርጉ ቤት ውስጥ የሚበዛው የእጅ ቦንብ ይዞ ገብቶ ነበር - ባሕል ነዋ። የሙሽሪት አባት ታዳሚው ፊት ቆመው እንዲህ አሉ፣ "ወገኖቼ አክብራችሁኝ ስለመጣችሁ ደስስስ ብሎኛል። እንግዲህ መንግሥት ባሕላችንን ከልክሎ ሰርጋችንን ጭር ሊያደርገው ሞክሮ ነበር። ይሁንና አስተዋዩና ብልሁ የወረዳችን

ሊቀመንበር እንደነገሩን፣ "ባሕል ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል ... እውነት ነው ይሄው የትላንቱ የጭለ ወከፍ መሳሪያ የማንገባበት ባሕላችን አድጎ ዛሬ በምወዳትና በምኮራባት ልጄ ሰርግ ላይ ተኩሱ ወደ ፍንዳታ ተቀይሯል። ባሕል እኔ ቤት አድጉቱን በመጀመሩ ደስታዬ እጥፍ ሆኗል" በማለት ከኪሳቸው በምብ መኽረጥ አድርገው ተንደረደሩና ፊት ለፊታቸው ወደተዘረጋው አርሻ ላይ አፈጉት።

ሙሉ ቀንና ሙሉ ሌሊት ወረዳው በፍንዳታ ሲናጥ ውሎ አደረ !

መንግሥት፣ "ፀረ ሰላም ኃይሎች የልማት እንቅስቃሴውን ለማደናቀፍ ሰርግ ቤትን ከለላ በማድረግ ሰላማዊ ሕዝብ ለመጨረስ ቢሞክሩም በሕዝብና በወረዳው ፖሊስ ትብብር እቅዳቸው ሳይሳካ ቀርቷል" ብሎ ዘገበ። ሕዝቡ ግን "ሰርግ አቶ አርገጤ ቤት ተሰረገች" እያለ በአድናቆት ያወራ ነበር።

# እግር በእግር

አንድ ቀን ሰይጣን በመንደሩ ወደሚፈሩት እና ወደሚከበሩት አስር አለቃ ደባልቄ ግዛው ቤት ሄደና ቀዳሚም ተከታይም ሳያደርግ፣ "ደባልቄ !!" ብሎ በስማቸው ጠራቸው።

አስር አሊቃ ፊታቸውን በቁጣና በግርምት እያማተረው ድምፁን ወደሰሙበት ዞር ቢሉ በአካባቢው ሰው የሚባል የለም። እዚህ ሰፈር አንድም ሰው የአስር አለቅነት ማዕረጋቸውን ሳያስቀድም፣ የአባታቸውንም ስም ሳያስከትል እንዲህ ንፋስ እንዳነሳው ፈስታል ስማቸውን ለብቻው አንጠልጥሎ የሚያነሳ ሰው የለም። እንኳን ሰው የዚህ ሰፈር ሰይጣን ቢሆን ራሱ እንደዚህ አስር አለቃን ኢቃሎ እና አበሻቅጦ ይጠራቸዋል ተብሎ አይታሰብም። እንዴት ሆኖ! ምን ሲደረግ..!

እንግዲህ አስር አሊቃ የተጣሉ ባልና ሚስት አስታርቀው ገና መመለሳቸው ነበር። ልክ በራቸው ላይ ሲደርሱ ነው ሰይጣን የጠራቸው። ምን ይጠራቸዋል፣ ያዋረዳቸው እንጅ! ቢሆንም 'ጆሮዬ ነው' ብለው ወደ ቤታቸው ግቢ ሊገቡ ርምጃ ሲጀምሩ፣

"አንተ ደባልቄ! የሚደባልቅ ይደባልቅህ! ሲጠሩህ አትሰማም!? ደንቆሮ!!" ብሏቸው እርፍ። በዚህ ቢበቃማ ጥሩ ነበር፣ "ምን ያሯሩጠኻል? ያች መንሽ እግር ሚስትህ እንደሆነች የትም አትሄድብህ፤ ተውዘፋ ነው የምትጠብቅህ" ሲል ዘለፋቸው። አስር አሊቃ መጀመሪያ በተናጋሪው ድፍረት ግርርርርርርርርርርርርርርም አላቸው፤ ቀጥሎ የንግግሩ ትርጉም እልፍኞቻቸው ውስጥ ሲተረጎም ደማቸው ፈላ። ላለፉት አርባ ዓመታት እንዲህ ተንቀውም፣ እንዲህ ደማቸው ፈልቶም አያውቅም። ከዘራቸውን ጠበቅ አድርገው ጨበጡና ድምፁን ወደሰሙበት ፎክረው ዞሩ።

"ያንበሳው ግልገል!" በአካባቢው የሰው ዘር የለም!!

"እንኳን ራሴ ያላገኘሁት፤ ደሙ ከሌብ አድርጎው ዘብጥያ መውረዱ ነበር።" አሉና ከዘራቸውን ወደ ግራ እጃቸው አጋብተው ከዘራ በያዘበት እጃቸው አማተቡ።

"ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ..." የሰይጣን የሚያበሳጭ እና የሚሰቀጥጥ ሳቅ ጆሯቸው ጋር ተቅጨለጨለ...

"ድሮም ከአማዞራችሁ በፊት ዱላችሁ ነው ትግ የሚላችሁ... ነውጠኛ ሁሉ፤...የምትገርሙው ስታጣ ታማትባለህ? አይ ሽፋፋው አስር አለቃ...ሂሂሂሂሂሂ ሁሁሁሁ ቂቂቂቂቂቂ..." አለ ሰይጣን ቀድሟቸው ግቢያቸው ውስጥ ገብቶ ከጀርባቸው ከቆመ በኋላ። አስር አለቃ ግራ ተጋቡ። ንዴታቸውን ቀጥ አድርገው እየተጣደፉ በቁጣ ወደ ቤታቸው በር ገሰገሱ።

አስር አለቃ አቋማቸው እንደ ሰምበሌጥ ቀጥ ያለ ስፖርተኛ አቋም ነው፤ ሰው ሁሉ "አቤት ቁመና!!" ይላቸዋል። ሰይጣን ግን ወደ ቤታቸው ሲጣደፉ በሚያበሽቅ ንግግር፣

"ሽፋፋ ...ሽፍፍ ሽፈፍ ትላለህ! ሲራመዱ አይተህ...ደግሞ ወታደር ነኝ ይላል እንዴ? ይሄን ደጋን የመሰለ እግር ይዞ...፤ሂሂሂሂሂሂሂሂሂ... እንኳን አገር ልትጠብቅ፣ በዚህ ሽፋፋ እግርህ ሚስትህንም አትጠብቅ፤...ተመልከት የእግርህን ክፍተት፣ በልጅነትህ ፀሐይ አላሞቀችህም ያች ጨብራራ እናትህ!! ኪኪኪኪኪኪኪ..." አስር አለቃ ከሳቸው አልፎ እናታቸውን ማዋረዱ ቢያንገበግባቸውም የተናጋሪው ማንነት ስለገባቸው እንደገና አማተቡና፣

"የማሪያምን ብቅል ፈጭቻለሁ! ቱ! ቱ! አንተ ሥራፈትከኛ ሰይጣን!" ብለው አንዴ ወደ መሬት፣ አንዴ ወደሰማይ ትፍ! ትፍ! ቀጠል አድርገውም፣ "አንተ ከቶ አውቄሃለሁ፤ እንዲህ አቅልሎ የሚጠራኝ እንዳንተ ያለው ቀላል እንጂ ሌላ እንደማይሆን መች አጣሁት?" ካሉ በኋላ፣ ቆይ ላገኝህ በሚመስል ዛቻ ከዘራቸውን ነቀነቁና ነጠቅ ነጠቅ ብለው በመራመድ ወደ ቤታቸው ገቡ።

ሰይጣንም አጀንዳውን ከፍቶ፣ "አስር አለቃ ደባልቄ" በሚለው ፊት ለፊት በቀይ ስክርቢቶ 'ራይት' አደረገ። መንገዱንም ቀጠለ! እየሳቀ እና እየፏጨ...! "ይሄ ሽፋፋ ለዛሬ ይበቃዋል ሲበሳጭ ይደር። ነገ ደሞ በተመቸኝ ሰዓት ብቅ ብዬ ነድቸው አሄዳለሁ።" አለና እየሳቀ መንገዱን ቀጠለ። ከአስር አለቃ ቤት ግራና ቀኝ ባሉት ሜዳ ቤቶች ተኮልኩለው ሜዳ የሚቀመጡትን ወጣቶች በኩራት እየተመለከተ፣

"ርስቴ እየተስፋፋ ነው!" ብሎ እየኮራ ቁልቁል ወደ ወንዙ!

###

በእርግጥም ሰይጣን እንዳሰበው አስር አለቃ ሌሊቱን እንቅልፍ በዓይናቸው ሳይዞር ነበር ያደረው። እንደዛ ያበሻቀጣቸው ሰይጣን ነው ለማለት ጥርጣሬ ገባቸው፤ "እኔ የትኛው ቅድስና ኖሮኝ ሊፈትነኝ ይመጣል?" አሉ ለራሳቸው። እንደውም አንዱ ጎረቤታቸው ተደብቆ እንደሰደባቸው ጠረጠሩ። "ማን ሊሆን ይችላል ?" ሌሊቱን ሙሉ ተብሰለሰሉ።

"ይች ጎረቤቴ የትነበርሽ ትሆን እንዴ? የለም ድምፁ የወንድ ነው። ግንበኛው አሰፋ መሆን አለበት፤ እሱ ለካ ለሥራ ከፍለ ሀገር ከሄደ ሁለት ወሩ፣ ...እና ማናባቱ ነው...።" ወደ ንጋቱ ላይ አንድ ሐሳብ ብልጭ አለላቸው። አረጋ!! ድንበር እየገፋ የበጠበጣቸው ጎረቤታቸው !! አረጋ ! ኧረ እሱስ ሚስታቸውንም በምኞት ዓይኑ የሚቃኝ ጥጋበኛ ነው፤ ድምፁም መጣላቸው፤ ራሱ ነው!

"አገኘሁት" ብለው ዘለው ከአልጋቸው ተነሱ። ሚስታቸው እማማ የውብዳር በአስር አለቃ አነሳስ ደንግጠው፤

"በስማም ምን ሆኑ?" ሲሉ ጠየቁ፤

"ዝም በይ! ሽፋፋ!" ሲሉ ሚስታቸውን ሰደቧቸው፤ ከሰይጣን በተዋሷት ያደረች ስድብ። አስር አለቃ ከዛ በፊት ሚስታቸውን ሰድበው አያውቁም ነበር። ልብሳቸውን ለባብሰው እየተጣደፉ ሲወጡ ሚስታቸው አልጋቸው ላይ ሆነው አሰቡ፤

"ይሄን ሁሉ ዘመን ዓይቶት የማያውቀውን የእግሬን መንሻፈፍ ዛሬ እንዴት ታየው? ምናልባት ውጣት ሴት ዓይቶ ይሆን? ማን ያውቃል...?" ባላቸውን ካገቧቸው ጀምሮ ዛሬ ገና ተጠራጠሩ። ልጃቸው ሰንቄ እንደ ሁልጊዜው ከመኝታዋ ተነሳታ እያንጎራጎረች ነበር። ለሙዚቃ ከፍተኛ ፍቅር ያላት ሰንቄ፣ በተለይ የአስቴር አወቀን ዘፈኖች ስትዘፍን ታስደምማለች። ዛሬ ግን እናቷ ድንገት አንባረቁባት፤

"ወዲያ ዝም በይ! ምን በጧቱ ታንቋርሪብኛለሽ!"

ሰንቄ በእናቷ ንግግር ከቶኛ ተበሳጨች። እስከዛሬ ሲያደንቋት ነበር፤ "የኔ ልጅ ድምጿ ብቻ የወፍ ዘር የሚያረግፍ..." እያሉ፤ ዛሬ ታዲያ ምን ነካቸው? ሲታምሰለስል ድንገት ጓደኛዋ ሊበን ደወለ።

ዛሬ "ሰርፕራይዝ" ሊያደርጋት ጓደኞቹን አዘጋጅቶ እየጠበቃት ነው። እንድታገባው ሊጠይቃት

ወሰኗል፤ ጓደኞቹ ጋር ቤቱ ቅልብጭ ያለ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ድንገት ሲነግራት የቃል ኪዳን ቀለበቱን አዘጋጅቶ በጉጉት እየጠበቃት ነው...፤

"ሄሎ !" አለች እንደከፋት፤

"ሄሎ ...! ምነው ድምፅሽ ?" አላት፤ እንባ ተናንቋት ስለተናገረች ድምጿ በአርግጥም ድክም ብሎ ነበር።

"ድምፄ ምን ሆነ ?" ስትል ጠየቀችው።

"ተንቋረረ ልበል?" አላት ፈገግ ብሎ። ስልኩን ጆሮው ላይ ጠረቀመችበት።

ዘፋኝነትም ከዚህ በኋላ ዋጋ እንደሌለው ገባት። እርፉ የፀሐፊነት ሥራዋን ለመሥራት ወሰነች። "እንቋራሪ ድምፅ" ያውም በእናቷና በምትወደው ፍቅረኛዋ የተመሰከረበት...። እስከዛሬ ሰው ፊት 'ስታንቋርር' ሁሉም ሲታዘባትና በሹክሹክታ ሲቀልድባት እንደኖረች ተሰማትና አፈረች !!

###

ኡኡኡኡኡኡኡኡኡ... ከወደ ውጭ ድምፅ ተሰማ። አስር አለቃ ጎረቤታቸውን በዱላ አናቱን ብለው በሩ ላይ ደፍተውት ነበር።

ሰይጣን አጀንዳውን ይዞ አስር አለቃ ግቢ ሲደርስ ነገር ተደበላልቆ ጠበቀው። ጉዳዩን በጥንቃቄ አጣራና አጀንዳው ላይ እንዲህ ሲል ከተበ፤ "የአስር አለቃው ጉዳይ ከእቅድ በላይ ተፈፅሟል።"

ሦስት ፖሊሶች ኮሌታቸውን ጨምድደው ወደያዟቸው አስር አለቃ ጆሮ ጠጋ አለና፤ "አንተ ሽፋፋ! ስማ...! አሁን በግደያ ሙከራ ዘብጥያ ትወርዳለህ፤ የተደበደበው ጎረቤትህ ተሽሎት ወደ ቤቱ ይመለሳል...። ያች እንቋራሪ ልጅህም የትም ስታንቋርር ስለምትውል ቤትህ ሰው የለም። ሚስትህና ጎረቤትህ ብቻቸውን እዚህ ሰፊ ግቢ ራስህ አልጋ ላይ...ሂሂሂሂሂሂ ቂቂቂቂቂቂቂቂቂቂቂቂቂቂ...አይ ሽፋፋው !! ይልቅ ሚስትህ ዓይንህ እያየ ከምትወስድ አንዱን ፖሊስ በካራቴ ድፋውና አምልጥ...፤ ወታደር አይደለህ...? አስር አለቃ አይደለህ?... ኮማንዶ ነኝ እያልክ በየጠላ ቤቱ ስታወራ አልነበር...? ወይስ እንደው ዝም ብለህ ስትወሸክት ነው...።"

አስር አለቃ ቀስ ብለው ከጎናቸው የቆመውን ፖሊስ ተመለከቱት። ክስት ያለ ነው...። በዛ ላይ የያዘው መሣሪያ የከበደው ይመስላል። ሁለቱም ፖሊሶች ቢሆኑ ያን ያህል የሚያስፈሩ አይደሉም፤ ቀድሬ

ቀላል ነገር ናቸው። "ይሄንንስ መሣሪያውንም መንጠቅ አያቅተኝ፤" ሲሉ አሰቡ። ፖሊሶቹ እስር አለቃን እያጣደፉ ወደ ጣቢያ ወሰዷቸው።.

ዱ...!! ዱ...............!! መንደርተኛው ከሩቅ የተኩስ ድምፅ ሰማ

ሞንድን ነው...?"

"እስረኛ ሊያመልጥ ሞክሮ ....ፖሊሶች እግሩን ሰንክለው አቆሙት..."

ሰይጣን በሳቅ ፍርስ አለ። እናም አጀንዳው ላይ እንዲህ ሲል ፃፈ፣ "የእግሩ ጉዳይ አልቋል፤ አሁን ነፍሱን ማንሻፈፍ ይቀረኛል !!"

ከዛም ሰይጣን ቀይ እስክርቢቶ አወጣና እየተፍነከነከ እንዲህ ሲል ጻፈ፣

"እስር አለቃ...፣ አምሳ አለቃ....፣ መቶ አለቃ...፣ ሻለቃ...፣ ሻምበል...፣ ጀኔራል...፣ ሚንስትር.... ጠቅላይ ሚንስትር...፣ ሁሉም እግር አላቸው። እንኳን እነርሱ አገርም እግር አላት፤ ስንፈልግ...እናንሻፍፋታለን !!!"

# ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን...

ሽማግሌው አንድ ማለዳ ተነሳና ባዶ ሜዳ ላይ 'የሆነ ነገር' መሥራት ጀመረ። መንደርተኛው ሁሉ ሽማግሌው የሚጎትተውን ትልልቅ ግንድ በግርምት እያየ ጠየቀው፣

"ምን እየሠራህ ነው?"

"መርከብ!!" አለ ቆፍጠን ባለ ድምፅ። ዙሪያውን ያሉት ሰዎች እንደ ውትሮው እየተሳሳቁና እየተሜወቱ ነበር የሚያዋሩት፣ ሽማግሌው ግን እንጨቶቹን እየጠረበ ያለወትሮው ሳቂታና ተጫዋች የነበረ ፊቱ ቡሐዘን ተኮማትሯል፤ ፍርሐትም አርብቦበታል።

"መርከብ ....መርከብ ደግሞ ምንድን ነው ?" አለ መንደርተኛው፤ ከዚያ በፊት መርከብ የሚባል ነገር አይቶም ሰምቶም አያውቅም።

"መርከብ ?...መርከብ ማለትማ... ያው መርከብ ነው።" አለ ሽማግሌው። ቁጥብ ነው ሲናገር፣ መንደርተኛው የባሰ ግራ ተጋባ።

"ይሄ መርከብ ያልከው ነገር ለምን ይጠቅማል?" ሽማግሊውን ከብበው በጥያቄ አጣደፉት።

"መርከብ...መርከብ እንግዲህ ለምን እንደሚያገለግል የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው።" ጎረቤቶቹ ለዚህ የአምስት መቶ ዓመት ሽማግሌ አዘኑ። 'በቃ ወፈፍ አድርጎት ነው' አሉና ወደየጉዳያቸው ተበታተኑ - "ካረጁ አይበጁ" እያሉ...።

ይሄ ሽማግሌ ሰው ግን ከምድር ሁሉ ሕዝብ ተመርጦ ሊጠፋ በተደገሰለት ዓለምና እንደገና ሊፈጠር በታቀደለት አዲስ ዓለም መሐል ትውልድ መቋጠሪያ ክር ተደርጎ የተመረጠው ፃድቁ ኖህ ነበረ።

ጠፊውን ከለሚው የሚያነናኝ ድልድይ። አዳሜ ድልድዩን 'ወዴት ትሄዳለህ...?' ይለዋል፤ በድልድዩ "እናንተ የት ደረሳችሁ...?" የሚል የጅል እንቶ ፈንቶ ንትርክ እየከፈትን!

###

የኖህ መርከብ የጎረቤቱ ዓይን እያየት ግንባታዋ ተፋጠነ። ሽማግሌው አንዲት ሰዓት ዝንፍ ሳይል እንጨቶችን በመገጣጠም፣ በመጥረብና በማሰር በጣም ብዙ ዓመታት ሠራ።

አንድ ቀን ታዲያ ከወደ ሰማይ፣ "አባታችን ኖህ! እንደ ምን ዋልክ!" የሚል ድምፅ ሰማ፣

"እግዚሃር ይመስገን! እንደምን ዋልክ...!" ብሎ ፀሐይ ለመከላከል እጁን ግንባሩ ላይ ጣል አድርጎ ቀና ቢል አንዱ የመርከብ ምሰሶ ላይ ያረፈ ቁራ ሆኖ አገኘው።

"ኧረግ...! ቁራ አንተ ነህ እንዴ?... ምን እግር ጣለህ?" አለ ኖህ፤ ወደ ሥራው እየተመለሰ።

"ኧረ እኔስ በዚሁ ሳልፍ ይህቺ ያረፍኩባት ምሰሶ ትንሽ ተጣምማ ባያት ጊዜ እንድታስተካክላት ልነግርህ ብዬ ነው" አለ ቁራ።

"እሃ! ምኗ ተጣመመ ?" አለ ኖህ ምሰሶዋን እየቃኘ።

"እይ ከላይ ሆነህ ካላየሃት አታስታውቅም። ወደ ሰሜን አዝምማለች።" አለ ቁራ ቁልቁል ኖህን እየተመለከተ። ኖህ በደንብ ሲያስተውል፤ እውነትም ምሰሶው የተተከለበት ጉድጓድ ውስጥ ተስተካክሎ ስላልገባ ማዝመሙን ተመለከተ። ጉድጓዱ ውስጥም ጨለም ያለ ሰፊ ክፍተት ነበር...።

"እውነትክን ነው ጃል!" አለና ምሰሶውን አስሮ የሚጎትትበት ገመድ ሊያመጣ ዘወር አለ። በዚሁ ቅፅበት ከጨለማዋ ጉድጓድ ውስጥ እባብ ፈትለክ ብሎ ወጣና በአንድ እንጨት ሥር ተደበቀ። እባብ በስህተት የተፈጠረችው ጉድጓድ ምቹና የምትሞቅ መቀመጫ ሆናለት ነበር። በቁራ ጥቆማ ቤቱን ሊያጣ በመሆኑ እጅግ በጣም ተበሳጨ።

"ይሄ አቃጣሪ ቁራ!" አለ ደሙ ፈልቶ።

ኖህ ምሰሶውን አስተካክሎ ጉድጓዱ ውስጥ እንዳስገባ ቁራ ባናቱ ላይ እየበረረ፣ "አሁን ግሩም አደረግህ

አስተካክልከው - በል ሰላም ዋል!" አለ።

"እግዜር ይባርከህ ቁራ...! ሰላም ዋል!" አለ ኖህ።

አባብ ተብሰከሰከ...

"እሺ. የት አባቴ ልሂድ ? ሰዎች ሲሳሳቱ ብቻ ነው ለእኔ ቦታ የሚፈጠረው።" አለ። በቁራ ከፉኛ ጭም እንደቋጠረ ወደ ቀዝቃዛው የድንጋይ ካብ በቁጣ ተምዘገዘገ። ፍጥነቱን ለተመለከተው እግር ያለው ይመስል ነበር።

###

ጎረቤቱ ግራ ገባው። ኖህን 'አብድ ነው' ብለው እንዳይተዉት፣ ይህች መርከብ የተባለችው ጉድ በራቸው ላይ እያደገች ጭራሽ ተራራ አከላ ተኮፈሰች።

"እች ነገር ቤትም ትመስላለች፣ መስኮት አላት" ይላሉ።

"እረ የከብት በረትም ልትሆን ይዳዳታል" ይባባላሉ። መንደርተኛው በግምትና በትንታኔ ልቡን ሲያደርቅ፣ ሞቱ ላይ ቆሞ ሲፈላሰፍ፣ ኖህ ላይ ሲዘባበትና ሲቀልድ ይህ ብርቱ ሽማግሌ ግን ደቂቃ ሳያዛንፍ፣ ከንድፉ ስንዝር ሳይገድፍ፡ መርከቧን ሠርቶ ጨረሰ።

መንደርተኛው ከጅማሬው ይልቅ በመርከቧ ፍፃሜ የባሰውን ግራ ተጋባ።

አንድ ሶሻ የፈታ ሽማግሌ ቀዶ የሰፋት ቆብ እያለ ያሽሟጠጣት መርከብ ሦስት መቶ ክንድ ርዝማኔ፣ አምሳ ክንድ ወርድና ሠላሳ ክንድ ከፍታ ያላት ግዙፍ ጉድ ሆና መንደሩ መሀል ሌላ መንደር ሆና እንደ ተራራ ተገተረች።

አሁን መርከቧን ከመንደሩ ነዋሪ አልፎ የከተማው ሕዝብ እየጎረፈ ይጎበኛት ጀመረ።

"ይህቺ ነገር፣ ወይ እንደ ቤት መሠረቷን ከመሬት አልቀበረች... እንደው ምን ይሆን ፍጥረቷ" ይባባል ጀመረ።

"ይሄ ሽማግሌ እንጨቱን ሲቀጠቅጥ በድካም መሞቱ ነው" አለ ሞቱን ተሸክም የሰው ሞት ተጓጓዥ ጎረቤት።

"ኖህ... ይህቺ ነገር ምን ትሆናለች?... እንደው መጨረሻዋ ምንድን ነው...? ማንስ ነው የሚያንቀሳቅሳት። እዚሁ በሰብሳ ከፈር ልትቀበር ነውን ?"

"ከፈር ቢታች በስባሹንም፣ ከፈር በላይ ነዋሪውንም እግዜር ነው የሚያውቀ፤ ልጆቼ !" አለ ኖህ እያዘነ...

***

ኖህ ሲድስት መቶ ዓመት ሞላው። ጎረቤቱ የልደት ድግ ሊበላ በልደት ድግስ ሊጨፍርና ሲዳራ እንዳሰፈሰፈ፣ ኖህ ብቻ ማንነቱን የሚያውቀው አስፈሪ ድምፅ ከሰማይ ተሰማ። የቁርጥ ቀን ከተፍ አለች።

"ኖህ!" አለ አስገምጋሚው ድምፅ።

"እነሆ ጌታዬ ባሪያህ በፊትህ ነው!" ብሎ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፋ።

"ወደ መርከቡ ልጆችህን፣ የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ግባ። ካንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሥጋ ካለው እንስሳት ሁሉ ሁለት ሁለት ተባዕትና እንስት ይግቡ"

ኖህ እግዜር በሰጠው ሥልጣን አዘዘ።

የዱር አራዊት፣ የሰማይ ወፎች ወደ መርከቧ ተንጋጉ። እነ አንበሳ እንደ ጥጃ መስሰ ብለው ገቡ...፤ ማማሳት የለ መጎድራት፣ እነ ነብር ... እነዝሆን - ሁሉም ገብቶ እንዳለቀ ኖህ በሩ ላይ ቆሞ ቃኘት ቃኘት አደረገና፣

"ቁራ የት ሄደ?" ሲል ጠየቀ።

"ቁራ እኮ የአንተን የአባታችንን ትዕዛዝ የማይሰማ ትዕቢተኛ ነው ጌታዬ" አለ እባብ ፈጠን ብሎ።

ኖህ ወደ ውጭ ሲመለከት ቁራ ሰውነቱ በጭቃ ተጨመላልቆና ተዳክሞ ሲበር ከሩቅ ተመለከተው። በጥፍሮቹ እንዳች ከባድ ነገር አንጠልጥሏል። እየበረረ መርከቧ በር ላይ ሲደርስ ከነሸከሙ ወደቀ። ተሸክሞ ያመጣት ኢሊ ነበረች።

በድካም እያለከለከ፣

"አባታችን! ይህቺ ኢሊ ጥሪውን ሰምታ ቀሉ ለመምጣት ስላልቻለች ይገባት ለመምጣት ስሞክር ነው የዘገየሁት" አለ ቁራ በፍፅም ትህትና።

"መልካም አደረግክ!" አለ ኖህ ኢሊን አንስቶ ወደ ውስጥ እያስገባት።

ሁሉም በየወገናቸው ወደ መርከቧ ውስጥ ገብተው ቦታቸውን እንደያዙ፣ ጎረቤቱ እንደ አስገራሚ ድራማ ቆሞ ጥርሱን እየፋቀ ትርዒቱን ሲመለከት፣ ማን እንደዘጋው መንደርተኛው ሳያውቅ የመርከቧ ትልቅ በር ከውጭ በኩል ተጠረቀመ።

በቅፅበት ደመና አንዣበበ። ካለማስጠንቀቂያ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ። ዝናብ ሳይሆን ወንዝ ከሰማይ ዘነበ...

ቅደም ደረቅ መሬት የነበረው ሜዳ ወደ ባሕርነት ለመቀየር አፍታ አልፈጀበትም። መንደርተኛው ተራወጠ። ቤቱ ጣራ ላይ ወጣ፣ ቤቱ ሰጠመ። ዛፍ ላይ ተንጠላጠለ፤ ዛፎች ሰጠሙ። ተራራ ሜዳ ላይ የወጣው ሕዝብ አመለጥነው ብሎ ሳይጨርስ ተራራዎች በባሕሩ መዋጥ ጀመሩ። ውኃው በዚህ ሁሉ ጥፋት ውስጥ የኖህን መርከብ ጨቅላ ልጁን እንደሚያቅፍ የእናት ክንድ ተንከባክቦ ከፍ አደረጋት።... ከፍ ... ከፍ ... ከፍ ... ከፍ...

መርከቧ ውስጥ ንቅናቄው ያንገዳገዳቸው ፍጥረታት በየወለሉ ላይ ተለሸለሹ። ቁራ ከሚስቱ ጋር ወለሉ ላይ ተንደፋደፈ። እባብ አንድ ምሰሶ ላይ ተጠምጥሞ ከወደቁት ሰፍር ቁጥር የሌላቸው እንስሳት መካከል መርጦ ቁራን እንዲህ አለው፣

"ልፍስፍስ ሊቃጣሪ፣ ለነገር ሲሉህ አንደኛ ነህ፣ ለችግር ግን ይህች ጠቋራ ሚስትህን ይዘህ ትንደፋለህ - ውዳቂ" ቁራ የእባብ ዘለፋና የስድብ ውርጅብኝ ግራ አጋብቶት፣

"እኔን ነው?" አለው።

###

ውኃው እስኪሞላና መርከቧም ከፍ እስኪል እንስሳት፣ ሰው እና ዕቃ በየሥርቻውና በየወለሉ ሲወድቅና ሲነሳ ቆየ። አንዱ በአንዱ ላይ ሲወድቅና አቅም የሌለው በባለ ጉልበቱ ሲጨፈለቅ ሥጋት መርከቢቷን አስጨነቃት። ከአፍታ በኋላ መርከቧ መናወጧን አቁማ በከፍታ ስትንሳፈፍ በመሳቧ

የነበሩት ሰዎችና እንስሳት ሁሉም ከየወደቁበት ተነስተው በታ በታቸውን ያዙ። በነውጡ ወቅት የሆኑትን ጀብድም ይተርኩ ጀመር፤

"መርከቧ ወደ ግራ ስታዘምም በቀኝ በኩል ሆኜ ወጥሬ ባልይዝ እስካሁን አዳሜ አልቆልሽ ነበር።" አለ ጎንዞ በመርከቧ ቀኝ በኩል ተዘርሮ በፍርሐት ሲናጥ እንዳልታየ።

"ጣራዋ ተደርምሶ ሊሜንን ሲል በኩንቢዬ የያዝኩት እኔ ነበርኩ" እያለ ዝሆን ፉከራ ቃጣው።

"ምሰሶው ላይ ተጠምጥሜ ባልይዘው ኖሮ ይህቺ መርከብ እስካሁን እንጦርጦስ ነበረች" አለ እባብ።

ኖህ ሁሉንም በዝምታ ሲያዳምጥ ቆይቶ፤ "የሁላችሁንም ፉከራና ጀብዱ ሰማሁ...፤ ግን ከእናንተ መሐል ከመርከቧ ውጪ ቢሆን ኖሮ በብርታቱና በጉልበቱ የሚተርፍ ማን ነበር? እስቲ ይኼን መዐበል እስቲም መርከቧን አንዴ ወደ ግራ፣ አንዴ ወደ ቀኝ ከመባዘን የሚያድን ጀግና ማነው?" አለና ጠየቃቸው።

ምድረ ፎካሪና አሽቃራሪ... አንበሳ ነሽ አቦ ሸማኔ፤ ዝም ጭጭ። ስለመርከቧ ተፈለጥኩ፣ ተቆረጥኩ ባይ ሁሉ የምር ጥያቄ የተሰነዘረች ቀን አፉ ተለጎመ። የትላንትን መፈለጥ መቆረጥ እያወሩ ዛሬ ግራ በገባው ማረፊያውን ባላወቀ ሚስኪን ተሳፋሪ ፊት ራሳቸውን የሚቆልሉ ሁሉ ጭጭ !!

ኖህ ቀጠለ፤ "...አያችሁ! መርከቧን ያቆመ ፈጣሪ ነው። መርከቧ ውስጥ ያሉትን ጠባቂም ራሱ ፈጣሪ ነው። ሁላችንም የምንራወጠው በሕይወት ማዕበል እየተናጥን እንጂ በጀግንነታችንና በብርታታችን አይደለም። ማዕበሉ አንዱን ከላይ አንዱን ከታች ያደርገዋል። አንዱን ይጥላል፣ አንዱን ያነሳል። የቆምክ ዘላለም የምትቆም መስሎህ አትጀነን። 'ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ' እንደተባለው። ውኃ የበላቸው ወገኖቻችንም እንደ እናንተ በትዕቢት ሲወብሩ ነው ዝም የወረዱት። እንዴት የቆመው ከሞተው አይማርም? ያተረፈን ፈጣሪ ብቻ ነው" አለና ትቷቸው ወደ መኝታው ሄደ።

ዝምታ ሰፈነ።

መርከቧ በቀስታ ምድርን ባጥለቀለቀው ውኃ ላይ ትንሳፈፍ ጀመር። እንደ ቁራጭ ቅጠል... ማረፊያዋ ናፍቋት።

***

ጠዋት ቁርስ ሰዓት ላይ ኖህ እና ልጆቹ እንስሳቱ የሚበሉትን እንደየድርሻቸው ሲያድሉ ቆይተው ቀጥ ብሎ ለወትሮው የሚስገበገቡት እንስሳት በኩርፊያ ፊታቸውን ኮስ አስመስለው የቀረበላቸውን መኖ ንክች ሳያደርጉ ቆመዋል። ከድፍን የመርከቧ ፍጥረት ቁራና ሚስቱ ብቻ ነበሩ የተበተነላቸውን ስንዴ በፍቅር እየተጎራረሱ በደስታ ሲበሉ የነበሩት። በኋላ ግን የሙሉ መርከቧ ዝምታ እና ኩርፊያ አስፈርቷቸው የማንቋርታቸውን ጥሬ ጥለው ግራ በመጋባት ቆሙ።

"ምን ሆናችኋል? አትበሉም እንዴ?" አለ ኖህ ግራ ተጋብቶ።

"አንበላም" የሚል የቁጣ ድምፅ መርከቧን አናወጣት።

"እሃ ለምን ቢባል ?" የበለጠ ተገርሞ።

"አባታችን ኖህ፣ በእውነት ታላቁ እና መሐሪው፣ ሩህሩሁና አዛኙ አምላካችን እግዚአብሔር ተሰዶብ እንዴት እህል ልንበላ ይቻለናል...?" አለ አንበሳ በአሰፈሪ ቁጣ።

ኖህ በሰማው ነገር ደነገጠ።

"ማነው እግዚአብሔርን የሰደበ ከመካከላችሁ?" አለ ኖህ በቁጣ ዓይኑ እየተንተገተገ።

አንበሳ ወደ አባብ እያየ፣ "እባብ ... ያየኸውን ለአባታችን ኖህ ሳትቀናንስ ንገረው!" አለው በትዕዛዝ ዓይነት ድምፅ።

አባብ በደረቱ አንድ ሁለቴ ሳብ ሳብ ብሎ ወደፊት ወጣና፣ "እድሉ ስለተሰጠኝ እግዜር ይስጥልኝ። እንግዲህ ጌታዬ መቼም ሁላችንም ለዚህ የበቃነው በአምላካችን፣ በታላቁ፣ በሁሉን ቻዩ፣ በአዳኙ እና በጥበበኛው እግዚአብሔር ነው፣ አይደለም እንዴ ጓዶች...?" አለ ወደ እንስሳቱ ዞሮ።

"እውነት ነው!"፣ "መልካም ብለሃል!"፣ "አይ መማር ደጉ...!"፣ "እሰይ የኔ ንግግር አዋቂ...!"፣ "እንደበተ ጣፋጬ"... እያሉ አባብን በታላቅ ጭብጨባና ሁካታ ደገፉት፣ አደነቁት፣ አበረታቱት። በዚህም የልብ ልብ የተሰማው አባብ ንግግሩን ቀጠለ፣

"እናም አባታችን ኖህ! ትላንት በጉልበታችንና በአቅማችን የተረፍን መስሎን ስንፎክር፣ አንተ የተባረክ እና በእግዜር የተመረጥክ አባታችን፣ 'ታላቁ እግዚአብሔር ነው ያዳናችሁ፣ የተናገራችሁት ሐጢያት ነው' ስትለን ስህተታችን ገብቶን ሌሊቱን በታላቅ ሐዘንና የንሰሐ ጸሎት፣ 'ይቅር በለን' እያልን ስናለቅስ

ነው…፣ ስቅስቅ ብለን ስናለቅስ … ጌታዬ አዎ እንዲያ ነው ያደርነው … አዎ ተንበርከክን … ስንጸልይ" አለ አባብ እንባውን እየጠረገ።

"ሌሊት ጸሎት ነበር እንዴ?" አለች የቁራ ሚስት ወደ ባሏ ጆሮ ጠጋ ብላ።

"እረ እኔ አልሰማሁም…፤ ተኝተን አልፎ'ን መሆን አለበት" አለ ቁራ ተገርሞ።

አባብ ቀጠለ፣ "ይሁንና ጌታዬ በዚህ መሐል ፈጣሪያችን ሲሰደብ ሰማሁ…" አለና ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ ሁሉም ይላቀሱ ጀመር።

"ቆይ እስቲ አንዴ…! ማነው ተሳዳቢው…? ምንስ ብሎ ተሳደበ?" አለ ኖህ በቁጣ።

"ይሄ ቁራ ነዋ!" አለ አባብ ወደ ቁራ በመርዙ እየጠቆመ። ቁራ በድንጋጤ ከሰፈረበት ቆጥ ላይ ሊወድቅ ከንፉን አርጉበግቦ ተረፈ።

"ማን እኔ?" አለ ቁራ።

"ዝም በል…! አፍ አለኝ ብለህ ልታወራ ነው?!"፤ እንስሳቱ ሁሉ ወደ ቁራ ተንደርድረው ለጸብ ተጋበዙ። ቁራና ሚስቱ በፍርሐት ተቃቅፈው ኖህን እንዲያድናቸው በዓይናቸው ተማፀኑት።

"በቃ!" አለ ኖህ በጩኸት። ሁሉም በርግገው ወደ ቦታቸው ተመለሱ።

"ምን ብሎ እንደተሳደበ ተናገር!" አለው አባብን፣

"ጌታዬ እኔ በእግዜር ላይ የስድብ ቃል ከአፌ ላወጣ እንደሉ ድፍረት የለኝም" አለ ወደ ቁራ እየጠቆመ።

"…ይሁንና ተናገር ካልከኝ ቁራ ሌሊት አጠገቡ ሰው የሌለ መስሎት ለሚስቱ እንዲህ ሲል ነበር፣ 'ይሄ ኖህ የሚባል ሥራ ፈት ሽማግሌ 'እግዜር ነው ያተረፋችሁ' ይላል እንዴ፣ እግዚያብሔር ምን ያተርፈናል? እንቁቻችንን፣ አክስቶቻችንን፣ አብሮ አደግ ጓደኞቻችንን እና ጎረቤቶቻችን ሁሉ በውኃ አስበልቶ፣ እኛንም እዚህ ሳጥን ውስጥ አሽጎ አስቀመጠን እንጂ፣ አላየንም ማዳን' ሲል ቃል በቃል ሰምቼዋለሁ" አለ አባብ።

"ወይ ነዶ!" አለ አህያ በእግዜር መሰደብ ተቆጭሁ ሲል፤ ከወደ ጥግ ሌሎቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ተንሜጩ።

ኖህ በጥሞና ሲያብሰለስለ ቆየና ቁራን፣ "ና እስቲ ወድ ውስጥ!" ብሎት ለሰዎች ወደተዘጋጀው ክፍል ወሰደው - ገባ።

ቁራ ከነሚስቱ ኖህን ተከተለው…

"ምንድነው የምሰማው…! እውነት ነው ይሄ ፀያፍ ቃል ከአንተ ወጥቷል?" አለ ኖህ በጥርጣሬ ቁራን እየተመለከተው።

"ኧረ ጌታዬ እኔም ያለ ዛሬ እንዲህ ያለ ነገር አልሰማሁ! - እንኳን ከአፌ ሊወጣ"

"እና ከየት አምጥተው አወሩት"

"ኧረረረረ ምን አውቄ ጌታዬ!"

"የለም ! ካለነገሩ ነገር አይወራም… ሐቁን ተናገር!" አለ ኖህ ተቆጥቶ።

"ይሄው ከምወዳት ሚስቴ ከቁሪት ይለየኝ…! ቀብሬን ባሕር ላይ ያርገው…! ቃል አልተነፈስኩም አለ ቁራ እንባ በዓይኑ ሞልቶ ያሰም'ነበት ቃል ጠፍቶበት። ኖህ መንፈሱ የቁራን ሐቀኝነት ሹክ አለው - ቁራ ነፃ ወጣ።

ይሁንና ቁራና ሚስቱ ቁሪት ከመላው እንስሳ ተገለሉ። አብሯቸው የሚያወራ፣ አጠገባቸው የሚደርስ አንድ እንኳን ፍጥረት ሳይኖር ወራትን ገፉ - ፍቅራቸው ብቻ አፅናኝ ሆኗቸው… ! አባብ በዚህም ተንገበገበ…፣ ቀና …፣ ተብሰከሰከ። ቁራና ቁሪት እርስ በእርስ በፍቅር ሲተካከሉ፣ 'ቅንቅናችሁን አታራግፉብን ወዲያ እያለ ያሾሙራል። የራሱ የቅናት እና ተንኮል ቅንቅን ማከኪያ ጥፍር ጠፍቶለት፣ ማራገፊያ መላ ታጥቶለት… 'ቅንቅናም !' ይላቸዋል ሲያልፍ ሲያገድም።

መከራ አንድም ፍቅርን ይሰላል፣ አንድም ፍቅርን ያዶለዱማል። የነቁራ ፍቅር በመከራ ውስጥ ሰለቶ አብለጨለጨ። ከመርከቡ ታዳሚ እንዲያሥራቸው የተወረወረባቸውን የመገለልና የብቸኝነት ገመድ የፍቅራቸው ስለት እየበጣጠሰ ተንኮል በነገሠበት መርከብ፣ ማግለል በተንሠራፋበት የመዳን ቆሻ የነቁራ ፍቅር ፈካ !

በዚህች ምድር የትኛውንም ዓይነት የሚታይም ይሁን የማይታይ ጦር እና ፍላፃ የሚከላከል ወደር የለሽ ጋሻ ፍቅር ነው። ቁራና ቁሪት በዚህ ጋሻ ከእንስሳ ፋከራ፣ ከአባብ ተንኮል፣ ከተኪታይ እርግማንና

ጫሚታ ተከልለው በርካታ ወራቶች ኖሩ። እንስሳቱ አባብን ከብበው ይቆሙና ዘር ብለው እንቁራን አይተው በሳቅ ያውካካሉ። በእርግጥ ቅስም የሚሰብር ውስጥንም የሚነካ ነገር ነበር።

አንዳንዴ ደግሞ ቁራ እንዲሰማ አድርገው፣ "ይሀች በቋራ ሚስቱ እኮ የለየላት አለሌ ነበረች። ትዝ አይላችሁም አንትና ጫካ፣ አንትን ወንዝ ከጅግራ ጋር ስትዳራ፤ ከአርግብ ጋር ስትሳሳም፣ ከጥንብ አንሳ ጋር በየሜዳው ከንፏ፥ እስኪቀጥን ስትበር፤ ዱርዬ - የጠየቀ የማያጣት፥ የወፍ ዘር ሁሉ የድርሻውን የዘነላት፣ ወፍ አውል" እያሉ ያወራሉ።

ቁራ እየሰማ ችሎ ዝም ይላል።

ሌላ ቀን ቁራትን ቅዱስ ያደርጉና ቁራን ይቦጭቁታል። "ይሄ ለከስከስ...! ሴት ወፍ ተከትሎ ዓለም መጨረሻ ድረስ ይሄዳል። እንደው ይህችን የመሰለች ቁራት ምን ነክቷት ነው እዚህ ኢቃጣሪ፣ ወልጋዳ፣ ጠቋራ፣ አመዳም ቁራ ጋር የተለጠፈችው በናታችሁ!" ይባባላሉ።

ቁሪትና ቁራ ግን የሰሙትን እንደ እሳት የሚለበልብ አሽሙር በፍቅር መወድስ ያጠፉታል።

እንዲህ ይላታል ቁራ ቁራትን፣

"የእኔ እመቤት የእኔ ጥቁር አልማዝ አውቅሻለሁ...፤ ፀሐይን በእጅሽ የነካ ማነው? ሁሉም ግን ይመኛል። የአንችንም የክንፍሽን ጫፍ የነካ የወፍ ዘር የለም !! እንኳን ሰውነትሽ የበረርሽበት ሰማይ፣ ያረፍሽበት ዛፍ ቅዱስ ነው፤ የኔ ንፁህ። የልቤ ፅላት ነሽ የፍቅር ቤተ መቅደሲ" ይላታል ከልቡ። የዛን ሁሉ ሐሜተኛ፣ ከፉ፣ ሸራኛ፣ ነጃሳ፣ ተሳቢ፤ ተራማጅ፣ ተንፏቃቂ ሐሜትና አሽሙር ሁሉ ከልቧ ድራሹን ያጠፋዋል። ድምፁ ብቻ ሳይሆን ነፍሱ ቃል ሆኖ ወደ ነፍሷ ሲፈስ ልቧን ደቅና ትቀዳዋለች...፤ እንዳሉባት መርከብ በመወድሱ ትንሳፈፋለች፣ በፍቅሩ ማዕበል ልቧ ይናወጣል።

"አውቅሻለሁ! ከሃዲ እንዳልሆንሽ። ያኔ አነር ነክሶኝ ታምሜ የተኛሁ ጊዜ ቁራጭ ሥጋ በአፍሽ አንጠልጥለሽ አልፍ አእላፍ ርቀት ተጉዘሽ የምትመግቢኝ ፍቅሬ ነሽ። አውቅሻለሁ አየር ቀዛፊ ክንፋቸው ልብ የሚያርድ የወፍ ዘሮች እንደ መልአክ ዙሪያሽን ሲያረብቡ ደመናውን ስትጥቀሽ ወደ እኔ ስትበሪ...፤ እንዳንቺ ታማኝ ለፍቅር ሟች በምድር የለም የኔ ወለላ" ይላታል።

ዓይኖቿን ጨፍና ደረቱ ላይ ፍስስ ትላለች። ምድረ እንስሳ በቅናት ድብን ! አባብ በብስጭት ዞሮ ጅራቱን እስኪነድፍ።

አንድ ቀን ሌሊት እንስሳው ሁሉ እንደተኛ እርግብ ቀስ ብላ ወደ ቁራ ሄደች።

እንስሳቱ፣ ከአደራችን ተለይታ ያወገዝነው ጋር ታዩች እንዳይሏት ፊርታ ቀን ባታናግረውም ሌሎች ወፎች ተካፍለው የሚበሉትን ነገር ሁሉ በዚህ ዓይነት ሌሊት ላይ ለቁራ ታቀብለዋለች።

ቁራና ቁሪት ያሳዝኗት ነበር።

ቀስ ብላ ቁራን ቀሰቀሰችውና ወደ አንድ ጥግ ወስዳ የአሳ ቁራጭ ሰጠችው። "አይዟችሁ" ብላው ሄደች። አባብ በዚህች ቀን እንደ አጋጣሚ ሲቀባበሉ ተመለከታቸው። ሰይጣን ቀስቅሶት መሆን አለበት!

አባብ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር አደረ። እርግብና ቁራ የተቀባበሏትን ቁራጭ አሳ በቅናት ውኃ በተጥለቀለቀ ባሕር አእምሮው ውስጥ አሳድጎ አሳ ነባሪ አሳከላት። ይህቺን ቅብብል እንዴት አድርጎ መርከቧን የምታናውጥ ወሬ እንደሚያደርጋት አወጣ፣ አወረደ።

'ለምን እግዚአብሔር እንዳትበሉ እርኩስ ነው ያለውን ሥጋ ሲቀባበሉ አየሁ አልልም' ሲል ሐሳቧን አምሰለሰላት። 'አዎ ... ቁራጭ አሳ ሃይማኖታዊ ጭራ ከተቀጠለላት ባሕሩን የምትንጥ፣ መርከቧን የምትገለብጥ አሳ ነባሪ መሆን ትችላለች' አለና ሴራሉ አረጋገጠ።

ግን ሐሳቡ አልዋጥ አለው። 'ምክንያቱም እነአንበሳ እነዝሆንና እነነብር እምነታቸው ጉልበት ነው። ለሃይማኖት ግድ የላቸውም። ብነግራቸውም ችላ ሊሉት ይችላሉ። ሌላ ስስ ብልት መፈለግ አለብኝ፣ የሚያጋጭ .. የሚያናጭ' አለና መልሶ በሐሳብ ተዘፈቀ።

'ለምን ፖለቲካ አላደርገውም። ይሄ በትክክል ፖለቲካ መሆን የሚችል ጉዳይ ነው !! ቁራጭ አሳን ፖለቲካ የማድረግ ጥበብ ቀላል ነው። ይህች መርከብ በውስጧ ያለው ትንሽ ምግብ በመሆኑ እንሰሳው ሁሉ እስኪጠግብ እንደማይበላ የታወቀ ነው። ታዲያ ሌሊት ሌሊት የአሳ ስጋ ሲቆርጡና ሲተኙ ጨለማን ተገን በማድረግ ጮማ የሚገባበዙ ሆዳሞች በመሃላችን አሉ...፤ ይሄ ብቻ አይደለም ጮማ እየቆረጡ ይህችን የሰላም መርከብ ከጉዞዋ ሊያስናክሉ በሌሊት ይመካከራሉ ብል ሁሉም ሆድ ይብሰዋል' አለና፣ አባብ ባቀናበረው ሐሳብ ተደሰተ።

ቆይቶ ግን ይሄኛውንም ሐሳብ ውድቅ አደረገው፤ "እዚህች መርከብ ውስጥ ፖለቲካ ማለት የነፈሰበት ጨዋታ ነው...፤ ማን ግድ ይሰጠዋል?" አለና ተኘ።

አባብ ሲያሰላስል ቆይቶ ቁራጯን እሳ ከ'ዘር' ጋር ሲያያይዛት ወሰነ። እንዴት እስካሁን እንዳልመጣለት ገረመው።

ከዛም ነገ ለመርከቡ ነዋሪ እንዴት ጉዳዩን አካብዶ እንደሚነግራቸው ማሰላሰል ጀመረ።

'ጀግናው የአንበሳ ዘር፣ የዝሆን ዘር፣ የነብር ዘር፣ የነሽና የጉማሬ ዘር ሁሉ ስማኝ...፤ ተደፍረሃል። አንተ በቀናኸው ሚካ፣ ደምህን ባፈሰስክበት ምድር፣ ሲበር የኖረ መድረሻ ቢስ የወፍ ዘር ሁሉ አንተን አስተኝቶህ እሳ ይገባበዛል። እሳዎችም ስሙ! አንድ ባንድ ከውኃ እያወጣ፣ እየለቀመ ሲጨርሳችሁ፣ ዘረኛው የወፎች ቡድን ሊሊት ሊሊት እየተመሳጠረ ነው..." አባብ እሳከቶ ባዘጋጀው ንግግር ረካ።

ይህቺ መርከብ ነገ የጦር ቀጠና ስትሆን የት ላይ እንደሚቀመጥ ገለልተኛ ቦታ መረጠ።

ከዛም በእርካታ ሰጥ ብሎ ተኛ...

###

ኖህ የዘወትር ጸሎቱን እያደረሰ ባለበት ማለዳ መርከቧን የሚያናውጥ ታላቅ ድምፅ ተፈጠረ።

በድንጋጤ ጸሎቱን አቋርጦ ወደ እንስሳቶቹ አዳራሽ ቢገባ 'ምድር ቀውጢ' ሆናለች። ፎካሪው... አሽቃራሪው...ባለመፈክሩ... ታሪክ ነጋሪው ሁሉ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል። ገላጋዩ ሲረባሽ፣ ረባሹ ይገላግላል ...፤ ወዲያው ደግሞ ገላጋዩ ረባሽ፣ ረባሹ ገላጋይ ይሆናል። ግርግሙ ሁሉ ተሰባብሮ ጎርፍ የዘለለበት ከተማ መስሏል መርከቡ ...!!

"ምንድን ነው?" አለ ኖህ። ከእግዜር የተቸረው ግርማ ሞገስ አስፈሪ ነውና ሁሉም የኖህን ድምፅ ሲሰሙ ዝም አሉ።

"ጌታዬ! ተከባብረንና ተፋቅረን የምንኖርባትን መርከብ ዘረኞች በጠበጧት" አለ ነብር።

"እንዴት ማለት?" አለ ኖህ። እንስሳው ሁሉ እየተቀባበለ፣ እየተሽቀዳደመ ስለቁራና ርግብ 'የሌሊት ግብግብ' ለኖህ ነገረው።

ኖህም እባብን ጠርቶ ስለ ጉዳዩ እንዲያስረዳ አዘዘው።

"ጌታዬ የሆነው ነገር ሁሉ ህልም እንጂ እውነት አይመስልም። ቁራ ከመርከቧ ተነስቶ ወደ ርግብ መኝታ ሄደና ባለቤቷ መተኛቷን ካረጋገጠ በኋላ ቀስ ብሎ ቀሰቀሳት። እሷም ተከትላው ወደዛ ወደ ውጭ ማስቀመጫው ሄዱ። እኔ ደግሞ 'እንደ ሁልጊዜው ሊሳሳሙና ሊዳሩ ነው' ብዬ ችላ አልኳቸው። እሰና በቅርጫ የቁራን ማስት ዓየት አደረጋት።

ተሳክቶለት ነበር። ፊቷ ተቀያይሮ ቁራን በቁጣ ስታየው ተመለከትኩ።

"ከዛ ከየት እንዳወጡት ያላየሁትን እሳ አወጡና እየተጎራረሱ እየተግባበሁ ዋጥ ስልቅጥ አደረጉት። እኛ በቁጠባና በፈረቃ እየተመገብን፣ እነሱ ተርፏቸው ሁሉ ሲያጫውቱበት ነበር። ቢቃ በዚህች መርከብ ውስጥ የወፍ ዘር ካልተሆነ መኖር አልተቻለም ጌታዬ!" አለና በሙሸት ምሬት ተንዘፈዘፈ።

"ለመሆኑ ይህን ነገር ያየ ሌላ መስካሪ አለ...?" ሲል ጠየቀ ኖህ። ሁሉም ዝም አሉ።

"እስቲ የሌሊት ወፍ ወዲህ ነይ ... ሌሊት የት ነበርሽ ?" ብሎ ጠየቃት። "እዚሁ አካባቢ ስዞር ነበር ጌታዬ!" አለች የሌሊት ወፍ።

"የተባለው እውነት ነው?"

"ኧረ ጌታዬ አላየሁም...! እኔ ያየሁት እንደ ሁልጊዜው ርግብ ለቁራ የተራረፈ ቁራጭ እሳ ስትሰጠው ነው። ይህ ደግሞ ከማዘን የመጣ እንጂ ሌላም ተንኮል ያለበት አይመስለኝም" አለች።

እባብ ዓይኑን አጉረጠረጠባት።

ኖህ ቢታላቅ ቁጣ፣ "አንድ ጩኸትና ግርግር እንዳልሰማ !" ብሎ ወደ እባብ እና ወደ ሌሎቹም እንባረቀባቸውና ወደ ውስጥ ገባ። ነገሩም በዚሁ በረደ። በእርግጥም ኖህ እባብ እንደዋሸ በሚገባ አውቆ ነበር።

ምንም እንኳን ግጭቱ በጭር ቢተኮስም ቁራት ልብ ውስጥ ግን ከፉኛ ቅሬታ አድሮ ነበር። ባሏ እሷን አስተኝቶ ርግብ ጋር መዳራቱን አምናለች። እባብን ባታምን እንኳን የሌሊት ወፍም ሁልጊዜ እንደሚገናኙ መሰከረላት። ሕዝብ ይቅር አለህ ማለት ሚስትህ ይቅር አለችህ ማለት አይደለም፣ ሚስትህ ይቅር አለችህ ማለት ሕሊናህ ይቅር አለህ ማለት አይደለም። እናም ይህቺን ክፍተት አስፍቶ

ቁራና ቁሪትን ሲለያይ አባብ ቆርጦ ተነሳ !!

አባብ ወደ ቁሪት ሄደና እንዲህ አላት፣ "እንደማትወጅኝ አውቃለሁ፤ በእርግጥ እኔ ማንም ወደደኝ ጠላኝ ግድ የለኝም። ግን እዚህ ሁላችንም ወገኖቻችንን ጥለን ነው የመጣነው። እርስ በእርሳችን ካልተረዳዳን ማንም አይመጣልንም። ለዛ ነው እንጀቴ አልችል ስላለ አንድ ነገር ልመክርሽ የመጣሁት። ወንዶች ሲባሉ በፍቅር ሲወድቁላቸው፣ ሲታመኑላቸው ሴትን እንደጅል የማየት ክፉ አባዜ አለባቸው። ለንቿ ውብ ነሽ እዚህ ያለ የወፍ ዘር ሁሉ የሚመኝሽ፣ የሚሰግድልሽ ... ገና ለገና ጠቆር አልሽ ብሎ አፍንጫሽ ሥር ከርግብ ጋር ሲዳራ ማየት ያማል። ሁላችንም እህት አለን፤ ለምን እንዲህ ይሠራል?" ሲል ሰበካት።

"ሰማ አባብ ... የፈለገውን ቢያደርግ ቁራን አምነዋለሁ" አለች ርግብ። ድምፁ ግን እንደወትሮው በፍቅርና በራስ መተማመን የተሞላ አልነበረም። ገብቶታል አባብ። ሲጀመር ለክፉ አፍ መከፈት ትርፉ ሌላ ክፋት እንዲወልድ መርዳት ነው።

አባብ ቀጠለ፣ "የገረመኝ ደግሞ ርግብን ሲያደንቃት ለነገሩ አለማለቱ። 'የኔ ማር...! የላባሽ ንጣት እኮ በረዶ ነው የሚመስለው። ሚስቴ ቁሪት ጋር ስውል ቀኑ ጨለማ ይመስለኛል። አንቺን ሳይሽ ግን ሌሊቱ ቀን ይሆንልኛል' ... ይላታል። ርሷ ደግሞ ደረቱ ላይ እየታከከች ዓይኖቿን ጨፍና በደስታ ስክር ..."

ቁሪት ዝም አለች።

"በእርግጥ እርግብ 'ኧረ ቁሪት እንዳትሰማ!' ብላው ነበር ባልሽን ወዳንቺ እያሳየች። እሱ ግን በንቀት ወዳንቺ እያየ 'ባክሽ አንዴ ከተጋደመች አትነቃም፤ ገና በጊዜ ትሰፍራለች፣ ስታንኮራፋ ታድራለች' ብሏት ተሳሳቁ...።"

"ደደብ በላቸው ሳቁ አልሳቁ ..." አለች ቁሪት በእልህ።

"እኔ እንድትበሳጭ አይደለም የነገርኩሽ...። ያው ማንም ሲጠቃ ስለማልወድ ነው። ይቅርታ አሳዘንኩሽ። በቀረብኝ ባልነገርኩሽ..." አለ አባብ ያዘነ ለመምሰል ፊቱን ከስክሶ።

"ኧረ አንተ ምን አደረግክ አባብዬ ! ለእኔ ብለህ ነው" አለች ቁሪት።

"እኔ የምልሽ ቆንጆ...!" አለ አባብ በተበረገደው የዋህ የቁሪት ልብ ሙሉ ከፋቱን ሊያንጋጋው እየተዘጋጀ።

"ወይዬ..." አለች ቁሪት በጉጉት።

"ለምን ለዚህ ከሃዲ ልከሽን አታሳይውም...?" በሚያደፋፍር ድምፅ።

"እእ ... እኔማ ከትላንት ጀምሮ ዘግቼዋለሁ'ኮ!" አለች።

"ኤዲያ መዝጋት ምን አላት... እሱ እንኳን አንቺ ሁላችንም ዘግተነው መች ተሰማው...። ደልቶ የነቀሰ ያህል ከሱ የተሻለ ወንድ 'ጠብሰሽ' አሳይው። በቅናት ይብገን ...፤ አግርሽ ላይ ወድቆ ይቅር በይኝ ይበል" አላት።

"አይ እንደዛ እንኳን ..." አለች ቁሪት ፈፅሞ ያላሰበችው ነገር ሆኖባት።

"ባክሽ አታካብጅው! እስቲ አሁን ማን ይሙት ከንሥር የበለጠ ጀግና... ልበ ሙሉ ወንድ ወፍ አለ? ንገሪኝ አለ ? ... ታዲያ በፍቅርሽ ማበዱን አታውቂም ?"

"ማን ... ንሥር ... በእኔ ፍቅር ...?" አለች ቁሪት ልቧ መምታቱን ሲያቆም ነበር በድንጋጤ።

"አዎና ሁሉም ያውቃል ,ጀሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው አሉ!... አልሰማሽም ?"

"እረ እኔ ..."

"ቢቃ በኋላ እናወራለን ..." ብሎ መንገድ ሲጀምር።

"እንዴ አውራኝ እንጂ እንዲህ ልቤን ሰቅለህማ ..."

"በኋላ እናወራለን..." ብሏት ሄደ...።

ቁሪት ሐሳቧ ሁሉ ስለ ንሥር ሆነ። ዓይኗን ከእርሱ ላይ መንቀል አልቻል አለች። እንደውም በአጋጣሚ ዓይናቸው ደጋግሞ መጋጨት ጀመረ። 'ውይ ዓይኖቹ ሲያምሩ' አለች በውስጧ። ስለንሥር ጀብዱ ሲወራ ብዙ ሰምታለች። እናትና አባቷ ሳይቀሩ ከዘመን ጫጩትነቷ ጀምሮ ንሥርን ሲፈሩና በስሙ ሲርበደበዱ ታውቃለች። የወፎች ንጉሥ መሆኑን ... ከደመና በላይ በግርማ ሞገስ እየተንሳፈፈ ጠላቶችን ድባቅ እንደሚመታ። እንደውም ሰዎች ሳይቀሩ ሲደናነቁ 'እንደንሥር ብርቱ' እንደሚባባሉ...፤ ብቻ ነገር ሰምታለች። እና ይሄ ታላቅ ፍጥረት በፍቅሯ መውደቁን ስትሰማ ተሸበረች።

በቀጣዩ ቀን አባብ ወደ ንሥር ጠጋ አለና፣ "ማን አንተ! ያዩህ ሴቶች ሁሉ እንዲህ በፍቅር ውድቅ የሚሉልህ ለምንድን ነው ?" ሲል ጠየቀው።

"ለማን ሰጿ...?" አለ ንሥር ተገርሞ።

"ታዲያስ ... ቁሪት ባንተ ፍቅር አብዳ የባሏ ዓይን ሁሉ አስጠሏታል፣ አላወቅኩም ልትል ነው...?"

"እኔ አላውቅም !" አለ በጉጉት ወደ አባብ ጢጋ ብሎ ሌላ ወግ ለመስማት።

"አትን ይወዳል ... በቃ አንተን ካላየች ምግብ ሁሉ አትበላም ስልህ...እንደውም 'በፍቅሩ ቧት ማታ ከመብቃየት በአንዱ ቀዳዳ ከዚህ መርከብ ወጥቼ ውሃ ይብላኝ' እያለች ነው "

"አሃ... ለካ ሰሞኑን የምታፈጥብኝ ..." አለ ንሥር በሐሳቡ።

ንሥር ቀጥ ባለ ቁጥር ቁሪት ጋር መፋጠጥ ሆነ። ዓይናቸውን እየሰለመለሙና ሆን ብለው ሊተያዩ የሚችሉበት ቦታ መርጠው በመቀመጥ ፍቅር የመሰላቸውን የተንኮል መረብ በጋራ ሰበሱት። ሲተላለፉና ባገጣሚ ሲቀራረቡ ሆን ብለው መነካካት ጀመሩ። በተለይ ቁሪት ሰውነታቸው በተነካካ ቁጥር የሚነዝራትን አንዳች ስሜት መቋቋም ፈተና ሆነባት።

አንድ ሌሊት ቁራ ከእንቅልፉ ሲነቃ ቁሪት ከጎኑ አልነበረችም። ግራ ቀኝ ሲቃኝ ልክ ርግብ ጋር ቁራጭ አሳ የተቀባበሉበት ቦታ ላይ 'ታላቁ ንሥር' ደረት ላይ የእርሱ ቁሪት በሰመመን ደገፍ ብላ ዓለሟን ስትቀጭ እንደሀልም ብዥዥዥ ብላ ታየችው ... ቁራጭ አሳ እየተቀበለች አልነበረም፣ ሙሉ እቧነቷን እያበረከበች እንጂ !

ቁራ በዚህች ምድር ላይ አለችኝ የሚላትን ሚስቱን አጣ። የንሥርና የቁሪት ወዳጅነት በድፍን የመርከቡ ታዳሚ ተደነቀ።

'እንዲህ ነው እንጂ ሲያጣጥም!' ተባለለት። ቁሪትና ንሥርም በወረት ፍቅር ሳባቸውን ጥለው አበዱ። ሲበሉ አብረው፣ ሲጠጡ አብረው። ሌላው ቢቀር "ንሥር" ተብሎ ሲጠራ ቁሪት "አቤት..." እስከማለት ደረሰች። የተዘፈቀችበት እግር እጅ የሌለው እልህ ከተከበበችበት ጋር ተዳምሮ የቁራን የነፍስ ጩኸት እንዳትሰማ አደነቆራት !!

###

ፍቅር ተራቁቶ መለመላውን ሲቀር፣ ማንነት ስለሚበርደው ድራቶ ይሰበሰባል። የእድናቆት ድራቶ፣ የስም ድራቶ፣ የአጃቢ ድራቶ፣ የቁሳቁስ ድራቶ...! ፍቅር ውስጥ የምትፈጠር ቀዳዳ በፍቅር ካልተደፈነች

በምንም አትደፈንምና ስለድሪቶ ፍቅራቸውን መሰዋዕት ያደረጉ፣ መደራረብ ሙቀት የሚሆን መስሏቸው ኢድሜ ልካቸውን እንደተንኳተቱ ይኖራሉ። ሥጋ ላይ የተደረበ ድሪቶ የነፍስን ገመና ይሸፍን ይመስል!! ቁሪት ዝንኛ ሆና ነበር፣ ግን ዝናዋ ባዶነቷን የማይደፍን ሆኖ ነፍሷ ለማዛጋት እፍታ አልፈጀበትም። ወደ እቅፊ ልትመለስ ከቅገቷ ስትባንን አባብ እና ብጤዎቹ በተስፋ ጭብጨባ ከነፍስ ጥያቄዋ ያጣሏታል። 'አቤት ንሥሮና ቁሪት የሚወልዱት ልጅ...' ኢያሉ ዘር መርጠው፣ ማንነት አነፍንፈው፣ ድሪቶ ትውልድ ስለፈጠሩ ምድር ላይ ቅድስና ያሰፍኑ ይመስል ድሪቷም ተስፋ ይደርታሉ።

ቁራ በአንድ ወር ውስጥ ጀርባው ጎበጠ፤ ዓይኖቹ በዘዙ፤ ለሁለት ለሦስት ቀናት አንድ ቃል ሳይናገር የሚቆይበት ጊዜ ነበር። ከባድ ዝምታ ውስጥ ተዘፍቆ የማያዩ ዓይኖቹን አፍጥጦ ቆጡ ላይ በትካዜ ይውላል። ቁሪት ቁራን ለማነጋገር እፍታ ጊዜ እንኳን ማግኘት አልቻለችም። ሁልጊዜ እጀብ ውስጥ ናት። ሁልጊዜ አባብ አጠገቧ አለ። ሁልጊዜ ንሥር ደረት ላይ ናት። ቁራ፣ "አንድ አድል..." ይላታል እንባ በቋጠሩ ዓይኖቹ እያያት ... አታየውም!!

ቁራ ከቆ ደግ አልወጣውም። ቀስ በቀስ የምግብ ፍላጎቱ ቀንሰና ቅሰሙ ተሰብሮ አንዳንዴ ብቻውን ማውራት ሁሉ ጀመረ። ርግብ ሁኔታው አንጀቷን ቢበላውም ርሷም በባለቤቷ ዘንድ ታላቅ ወቀሳ ደርሶባት ነበርና ልትረዳው አልቻለችም።

አንዴ ቁራ በጣም ስለተራበ ከሚታደለው ምግብ አንዲት አንስቶ ወደ ቆጡ ሊበር ሲሞክር አቅም ከድቶት መሐል መንገድ ላይ ወደቀ። ጥቁር ክንፉን በረዥሙ ዘርግቶ ሊነሳ ሲንደፋደፍ የወለሉ አቧራ ዙሪያውን ተነሳ። ድፍን የአንስሳ ዘር በሳቅ አውካካ። ቁራ ካለቁራ ወጉ መብረሩን ትቶ በቀስታ እርምጃ ወደ ቆጡ አዘገመ። ቀጥ ብሎ ቆጡን አየ፣ ራቀበት። ከሥር ቆሞ ያመጣትን ምግብ በቀሲታ መብላት ጀመረ።

አባብ በሳቁ መሐል ቁሪትን አያት። ፊቷ ላይ ቅሬታ ነበር። አልሳቀችም። 'እቺ እስቀያሚ ፍቅሯ አሁንም አለ' ብሎ አሰበና ልቧ የሚቆርጥበትን አንድ ሌላ ተንኮል ወጠነ። "አባቶቻችን ሰውን ከእግዚአብሔር ለያይተዋል፤ እኔ ልጃቸው ቁራን ከቁራ መለየት እንዴት ያቅተኛል። ይሄ ጠቋራ መቀመጫዬን እንደነሳኝ መቀመጫውን ነው የምነሳው" አለና ፎከረ።

###

መርከቧ በውኃ ላይ ስትንሳፈፍ ሠባት ወር አለፋት። የመርከቡ ውስጥ ኑሮ አሰልቺ ቢሆንም እንስሳቱ

በፈጠሩት የእርስ በርስ ትስስር ሕይወትን ሊያጣፍጧት ይጥራሉ። ኖህና ቤተሰቦቹም ከእንስሳቱ ጋር መልካም ወዳጅነት መሥርተው ነበር። አንዳንዴ እንደውም ኖህ እንስሳቱ መሀል ተቀምጦ ዙሪያውን ከብበውት በፍቅር ያወጋቸው ነበር። እንስሳቱም ስለሚሻካ ውሏቸው ይተርኩለታል። ኖህ የተረዳው ነገር ምድራዊው የሰው ልጆች አኗኗር እምብዛም ከእንስሳቱ ዓለም ሸኩቻ እንደማይሻል ነበር።

በዚህ የኅብረት ሳቅና ጨዋታ ውስጥ ቁራን ያስተዋለው አልነበረም ... ኖህን ጨምሮ።

አንድ ቀን ጠዋት ኖህ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደ ቁራ መጣ።

"ስማ አንተ እንደፌት ብትንቀኝ ነው እንዲህ ዓይነት ፀያፍ ነገር መናገርህ?" አለና ቁራ ላይ አፈጠጠበት።

ቁራ ለመናገር እንኳን አቅም አጥቶ ስለነበር አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ።

"አንተን እኮ ነው ምን አንገትህን ትደፋለህ!"

"ደ...ግሞ አሁን ምን አጠፋሁ አባታች...ን" አለ ቁራ እንደ ምንም ተጣጥሮ።

"ለሚስትህ ምንድነው ስለኔ ያልካት ?"

"ሚስቴ ... ሚስቴ እኮ ከሄደች ... ከተወችኝ ... ብቻዬን ከተወችኝ ሰነበተች!" አለ ቁራ፤ ፊቱ ላይ ሰቃይ ነበረ።

"እሱ የራስህ ጉዳይ ነው። ድሮስ በዚህ አመልህ ከአንተ ጋር ልትቆይ ኖሯል ?"

መከረኛው ቁራ ተናገረ ተብሎ የተወራበት ይህ ክስ በእርግጥም ኖህን የሚያሳምን ነበር። ቅሉ እባብ ቢሆንም የወሬው መነሻ ጉዳዩ ግን አሳማኝ ነበር።

ትላንት ማታ እባብ ወደ ኖህ ሄደና፣ "ጌታዬ ይህች መርከብ ባሕር ላይ ተበታትና ነው የምትቀረው እየተባለ ይታማል..." አለ።

"ማነው እንዲያ የሚለው...?"

"ቁራ ነዋ ... 'አባታችን ኖህ ምሰሶ እንኳን አስተካክሎ መትከል አቅቶት፣ እኔ ነኝ ያስተካከልኩለት' ብሎ ለሚስቱ ነግሯታል" አለው።

ቁራት ተጠርታ ስትጠየቅ፣ "አዎ ብሎኛል!" አለች። ፖለቲካ የነበረች ቁራጭ አሳ፣ ሃይማኖት የነበረች ቁራጭ አሳ፣ ዘር የነበረች ቁራጭ አሳ ... የሴት ቅናት ስትሆን ግድቁን ኖህ አበሳጨችው። በእርግጥም ምስሶው የተጣመመ ጊዜ ከቁራና ከኖህ በስተቀር ማንም አልነበረም ብሎ ኖህ በማመኑ በቁራ በጣም አዘነ።

ቁራ ይሄን ሲሰማ ራሱን ስቶ ወደቀ! ኖህ ደነገጠ። ከእግዚአብሔር የተሰጠው ከባድ አደራ እና ትእዛዝ አንድ ሁለት ተብለው በቁጥር ከተሰጡት ፍጥረታት አንድም እንዲጎድል አይፈቅድምና ቁራን እንስቶ አቀፈው። ወደ ራሱ መኝታም ወስዶ በጭንቀት ይንከባከበው ጀመረ...።

*ታላቁ ስብሰባ...*

ኖህ ሁሉንም እንስሳት ሰብስቦ ጠራና እንዲህ አላቸው፣

“እንግዲህ መዳረሻችን ሳይደርስም አልቀረ፣ እግዜር በራዕይ ተናግሮኛል” አልልታው አርስ በርስ መተቃቀፉና ፈሽታው ቀለጠ።

ኖህ የመርከቧን መስኮት ከፈተ። እንስሳቱ ብርሃኑን መቋቋም አልቻሉም። ፀሐይ በባሕሩ ላይ ታንፀባርቅ ነበር። ምንም ፍጥረት በሌለበት ምድር ላይ ምን ተፈጥሮ ይሆን...? አሁንስ ያለነው የት ነው? በጣም አጓጊ ነበር። ስምንት ወር በአንዲት መርከብ ውስጥ ታጉረው የኖሩ እንስሳት ቀጣይ እጣ ፋንታቸውን ናፈቁ። ተዘግታ በኖረች መርከብ ውስጥ መላ ምት ሲደረድሩ ከመኖር ሌላ አንድም ተጨባጭ ነገር አልነበረምና የሚታይ የሚዳሰስ ምድር ናፈቃቸው።

“እንግዲህ ያለንበትን እናውቅ ዘንድ ከእኛ መካከል አንድኛችን ውጭውን መቃኘት ሊኖርብን ነው። ለመሆኑ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ጀግና ማነው...?” ሲል ጠየቀ ኖህ።

ሁሉም ወደኋላ አፈገፈጉ። ማን ሞኝ አለ ዓለሙን ዋጥ ስልቅጥ ባደረገ መዕበል የሚቀልጥ።

“እባብ ውጪውን አይተህ ትመጣለህ ?”

“እንዴ ጌታዬ ውኃ በተሞላ ምድር ... እኔ እግር የለኝ አልሮጥ፣ ክንፍ የለኝ አልበር፣ ዋና ደግሞ አልችልም። ከሕፃንነቴም ውኃ አልወድም” አለ፤ ትወረወራለህ የተባለ ይመስል እየሸሸ።

"እንበሳ ?" አለ ኖህ።

"ዋና አልችልም ጌታዬ፣ ባይሆን ከንፍ ያላቸው ቢሄዱ ይሻላል..."

"ንሥር፣ አንተ በመቃኘት ወደር የለህም..." ብሎ ኖህ ንግግሩን ሳይጨርስ፣

"እንዴ እኔን ለማን ትቶ ?" አለች ቁራት አንገቱ ላይ ተጠምጥማ።

ኖህ ግራ ገብቶት እንደ ቆመ፡፡

"ጌታዬ እኔ እሄዳለሁ !" የሚል ድምፅ ተሰማ። እንስሳቱ ሁሉ ድምፁ ወደ ተሰማበት ዞሩ ... ቁራ ነበር።

"አይሆንም አንተ በደንብ አላገገምክም፤ አሞሃል..." አለ ኖህ።

"ጌታዬ በሚገባ ደኅናለሁ። እስከ ምድር ጥግ መብረር እችላለሁ። በዛ ላይ ዋና አሳምሬ ነው የምችለው..." አለ በሚገርም ድፍረትና በጠንካራ ድምፅ።

ኖህ አሰብ አደረገና፣ "መልካም እንግዲህ _ ባይሆን ርቀህ እንዳትሄድ" አለው።

ቁራ ወደ መስኮቱ ተንደረደረና ቁብ ብሎ እንጨቷ ላይ አረፈ። ከዛም ዞር ብሎ ቁራትን በጥልቀት አያትና በእፎይታ ተነፈሰ።

ፊቱ በታላቅ ሐሴት ተጥለቀለቀ።

ዓይኖቹን ከድኖ የውጭውን አየር በረዥሙ ሳበው..

በጥላቻ፣ በወገንተኝነትና በመገለል ከተሞላ መርከብ ይልቅ ምንም ወዳልታወቀ ዓለም በነፃነት መብረር እንደሚሻል ያመነ ልቡ ደም ሳይሆን ሐሴት ረጨ። ወደ ሰፊው ባሕር...፣ በውኃ ወደተሞላው ምድር በረረ።

አያነሰ ..... እያነሰ ... እያነሰ .. ከአድማሱ ወዲያ ማዶ እስኪሰወር ኖህ በትካዜ ተመለከተው።

መሸ...፤ ቁራ አልተመለሰም። ነጋ፣ መሸ...፤ ቁራ የለም። ሠባት ቀናት። የውኃ ሽታ ሆነ፤መልእክተኛው።

እርግብ ወደ ኖህ ሄደችና፣ "ጌታዬ እኔ ወደ ባሕሩ ሄጄ እንድቃኝ ይፈቀድልኝ !" ስትል ጠየቀች።

የቁራ ቀልጦ መቅረት ስላሳዘነው ለመፍቀድ አንገራገረ። ይሁንና የእርግብ ውትወታ ፋታ ስላሳጣው ሁለተኛዋ እንስሳ ወደ ባሕሩ በረረች።

###

ወደ እመሻሹ ላይ ንሥር በመስኮቱ አሻግሮ እየተመለከተ፣ "የሆነ የሚንቀሳቀስ ነገር ይታየኛል" ሲል ጮኸ።

በመስኮቱ ለማየት ምድረ እንስሳ ተራኮተ። አንደኛ መስኮቱ ላይ የደረሰችው ግን ቁራት ነበረች፤ እንደውም ከአበራረሯ ፍጥነት የተነሳ መስኮቱን አልፋ ወደ ባሕሩ ከመውደቅ ያዳናት ንሥር ነበር።

"የታለች ? እርግብ መሆን አለባት መቼም" አለ አባቡ።

በእርግጥም እርግብ ነበረች። ኖህ እጁን በመስኮቱ ዘረጋላትና ተቀበላት። በአፏ እርጥብ የወይራ ቅጠል ይዛ ነበር። በደስታ ሲያቅፏትና ሲስሟት ፊቷን አጨፍግጋ ወደ ቁሪት ሄደችና የያዘቻትን የወይራ ቅጠል እግሯ ሥር ወረወረችላት...።

እርግብ ከመርከቧ እንደወጣች ወደ ምዕራብ ተጓዘች። ባሕሩ በሚንሳፈፍ የሰው እና የእንስሳት አስከሬን ተሞልቷል። ሕይወት ያለው ፍጥረት አይታይም። ግማሽ ቀን እንደበረረች ንፁህ ቢሔር ከሥሯ ተዘረጋ፤ ምንም ነገር አይታይበትም ነበር።

ድንገት ጥቁር ነገር ነጥብ አክሎ ባሕሩ ላይ ሲንሳፈፍ ታየት። ቁልቁል ተወርውራ ወረደች። እግሯ የውኃውን ጫፍ ሳይነካ ነበር ጥቁሩ ነገር የቁራ ሬሳ መሆኑን ያወቀችው። ወዲያው ግን ቁራ የተንቀሳቀሰ መሰላት። ውኃው ላይ እየተንበጫረቀች ቀና አደረገችው። በእርግጥም ቁራ ዓይኖቹን ገለጠ።

"ቁሪት" አላት ርግብን።

"እርግብ ነኝ" አለችው። ውስጧ በሐዘን ተኮማተረ።

"ቁራ ትሰማኛለህ...? ለምንድነው ያልተመለሰከው...? ለምን ከሞቀ መርከብህ ወደዚህ ቀዝቃዛ የሞት ምድር መጣህ?" አለች እንባዋ በዓይኗ ሞልቶ።

ቁራ ከውኃው ውስጥ አንድ እግሩን አወጣ።

በጥፍሩ ርጥብ ቅጠል ይዞ ነበር።

"ይሄን ለቁሪት ሰጪት" አለ በደከመ ድምፅ። "ለመጀመሪ ጊዜ የተገናኘነው የወይራ ዛፍ ላይ ነበር። ያ

ቁራት ወዳኝ ነበር ... ዛሬ ንሥርን እንደምትወደው ..." አለና ከት ብሎ ሳቀ።

"ብሏ ተጠናከርና ወደ መርከባችን እንሂድ...! አይዞህ ደህና ነህ አኮ ቁራ" አለች ርግብ።

"አልሄድም"

"አብደሃል ... እዚህ በረዶ ላይ ... በዚህ ውሽንፍር ውስጥ ወድቀህ አልሄድም ትላለህ" አለች ርግብ በቁጣ።

"ከሰው ፊት የተፈጥሮ ፊት ቢገርፈኝ ይሻላል...፤ ከወገኖቼ ከፋት ወገኔ ያልሆነ ቅዝቃዜ ቢገድለኝ ይሻላል።"

ይህቺን ተናግሮ አንገቱን አቀረቀረ።

ቁራ ለዘላለሙ አሸለበ...።

ርግብ የወይራዋን ቅጠል በአፏ ይዛ ወደ መርከቧ ስትመለስ በርካታ ተራሮች ጫፋቸው ከውኃው በላይ ብቅ እንዳለ ተመለከተች።

የጥፋት ውኃ በሆነ ሰምንተኛ ወር፣ በወሩም በስምንተኛው ቀን መርከቧ በአራራት ተራራ ጫፍ ላይ አረፈች።

ሰዎች...እንስሳት... በከፍታቸው ውስጥ የነበረ ክፋታቸውን ይዘው ወደ ዝቅታቸው ተመለሱ።

እግዚአብሔርም አለ፤ "ክፋዎች ከፍ ስላሉ ከክፋታቸው አይመለሱም። ደጎችም ዝቅ ስላሉ ከደግነታቸው አይመለሱም። የአኔም ዓይን በከፍታ ይሁን በዝቅታ አብራችሁ አለች።"

# በግ...እልም !!

አንዳንድ ታሪኮች አሉ፣ የማያስደስቱ ግን ምን በወጣኝ ብቻዬን መሸከሜ ተብሎ ለሌሎች የሚነገሩ፡፡ ልክ እንደዚሀ...

አንዳንድ ታሪኮች ደግሞ አሉ፡ እንኳን ለግጥም፣ ለአግዜር ሰላምታ አፉ የማይፈታለትን ሰው በሐዘን ኮርኩረው ገጣሚ የሚያደርጉ፣ ልክ እንደዚሀ...

*ብቻኝነት ማለት ...*

*ብዙዎች መካከል*

*አንድ ሆኖ መገኘት ?*

*ብቻኝነት ማለት ...*

*ለሕዝብ እየታዩ ደምቀው እንዳበበ፣*

*በራስ ማንነት ውስጥ መቅለል ከገለባ ?*

*ብቻኝነት ማለት ...*

*የብዙኃኑ ቀልብ ወደን ሲንሰፈሰፍ፣*

*ራስን ረግጦ ወደ ምንም ማለፍ ?*

*ብቻኝነት ማለት ...*

*ዘላለም በሚያስንቅ ረዥም ፈገግታ፣*

*በነገ አምላኪዎች በተሰረኞች መሐል፣*

*ከፍ ብሎ መቆም በስቆቃ ማማ።*

*ለኩሰው ለብቻ የትዝታ ኩራዝ፣*

*በትላንት ሰንሰለት ተቃይዶ መያዝ ?*

*ብቻኝነት ማለት ...*

*በዝምታ ጀልባ ከባሕር አለምሮ፣*

*ትላንት ላይ መቆም ዛሬን ወዲያ አባሮ ...*

*ብቻኝነት ማለት . . .*

ይህ ታሪክ ያስጠላል። በተለይ እኔ ስጽፈው ያስጠላል። ምክንያቱም በተቻለኝ አቅም ሁሉ እንዲያስጠላ አድርጌ ስለምጽፈው ነው። ለምን ? ትንሽ እንኳን ላላምረው ብጥከር ሀጢያት የሠራሁ ስለሚመስለኝ ።

ከዓመት በፊት ነው፣ ጓደኛዬ ደወለና "አብርሽ 'ሚስ ክሪስመስ' ሞተችኮ" አለኝ። በቃ እንዲህ ነው ያለኝ። እውነቱን ለመናገር አዞረኝ። ትንፋሽ ሁሉ ነው ያጠረኝ። ስልኬ ከእጄ ላይ ሊያመልጠኝ ነበር። "ክሪስመስ" ያላት ሰምረትን ነው። እኔ እንኳን እትዬ ሰምረት ነበር የምላት።

"አትቀልድ ባክህ" አልኩት። ቀልድ አለመሆኑ ግን ገና ድሮ ገብቶኝ ነበር።

"ማሪያምን ! አሁን ራሱ ፖሊሶች ቤቷ መጥተው በሩን ሰብረው ገቡ። ሬሳዋን ወደ ምርመራ ሊወስዱ እያዘገጃጁት ነው፤ እኛም እዛው ነን" አለኝ በተጋነነ ድምፅ። የድምፁ መጋነን ጦር ሜዳ መሐል ሆኖ ጦርነቱን የሚዘግብ ጋዜጠኛ እንጂ የአንዲትን ሚስኪን ሴት ሞት የሚያረዳ ጎረቤቷ አይመስልም። አንዳንዱ ሰው መርዶም ይሁን የምሥራች ቀድሞ ስለተናገረ ራሱን ጀግና አድርጎ ይቆጥራል ልበል? ግራ ተጋባሁ። እትዬ ሰምረትን መቼሲታ አንድ የገበያ አዳራሽ ውስጥ የገና ዛፍ ገዝታ ስትወጣ አይቻት ነበር። አ እትዬ ሰምረት...!!

***

መጀመሪያ ሥራ እንደያዝኩ አካባቢ ቤት ልከራይ ሳፈላልግ አንድ ቆንጆ ግቢ ውስጥ አንዲት ክፍል

ቤት አገኘሁ። ደላላው አግድድሮ ካስገባኝ በኋላ ሒሳቡን ወስዶ ከዛ አካባቢ ጠፋ። በኋላ ስሰማ ባለቤቷ "አብድ ናት" አሉኝ። እንደውም ከእኔ በፊት የነበረውን ሰው "ነገሮት ቤቱን ለቀህ ውጣ" ትለዋለች፣ ሰውየው ችላ ይላታል። ማታ እንደተኛ የሆነ ጭስ ይሸተውና ከአንኮልፉ ሲነሳ ቤቱ በጭስ ታፍኗል። እንደውም በሩ አካባቢ ነበልባል ይመለከታል። በርግጎ ከአሊጋው ይነሳና መስኮቱን በርግዶ ለብቻ ይወጣል፤ አርቃትን። እትዬ ሰምረት የጋዝ መያዣ ጀሪካን ይዛና በቀኝ እጇ ክብሪት እንደጨበጠች የሚንቀሳቀሰውን እሳት እየተመለከተች በስስ ፒጃማ መልአክ መስላ ቆማለች። ራሷ ናት ቤቱን እሳቱ የለቀቀችበት። እሳቱን በጎረቤት ትብብር አጥፍተው፣ ዕቃውን ሌሊቱን አውጥቶ፣ ሰውዬው ጠፋ ብሏል።

ይኸው ከስንት ወር በኋላ ቤቱን አሳድሳ ለእኔ አከራየችኝ። ይሄን ታሪክ ስሰማ ደንግጬ ደላላውን አፈላለግኩና፣ "እንዴት እብድ ቤት ታስገባኛለህ አንተ?" ብዬ ጮኽኩበት።

"ባክህ ሰው ሲያጋንን ነው፤ ሰምረት እብድ አይደለችም። በእርግጥ ትንሽ ወፈፍ ያደርጋታል፣ ምን ችግር አለው? ሰው ላይ አትደርስ" አለኝ።

"እንዴት ነው የተኛ ሰው ላይ ጋዝ አርከፍክፋ እሳት የምትለቅ ሴትዮ ሰው ላይ አትደርስም የምትለው?

"እሱን አትስማቸው፤ ሰውዬው ተተናኮሏት ይሆናል..." ብሎ ብዙ ብዙ ነገር አወራኝና አሳመነኝ፤ ደላላ ሰባል ...።

###

የግቢው ፀጥታ ያስፈራል። ዙሪያውን የበቀሉት ረግረጅም የፅድ ዛፎች ዕድሜ ጠገብ ስለሆኑ ቤቱ የቤተክርስቲያን ግቢ አስመስለውታል። ባለቤቷ እትዬ ሰምረት ሲበዛ ውብ የሆነች እድሜዋ ከ35 እስከ 40 የሚገመት ሴት ነበረች። ታዲያ ስትገባም ስትወጣም ሰው ሰላም አትልም። ማንንም ሰላም አትልም። ቤቷ እንግዳ አይመጣም። አንድ ግቢ እኔና እሷ ብቻ እየኖርን እኔንም ሰላም አትለኝም "ምን ያምበጣርራታል...?" እያልኩ በውስጤ ስበሳጭቅት ብዙ ወራት አለፉ። የቤት ኪራይ ካልሰጠኋት አትጠይቀኝም ነበር። ማንንም ባስገባ ባስወጣ ግድ የላትም። ውኃ ፈሰሰ፣ መብራት በራ የሌ ቤቱ መኖሬን የረሳች ሴት ነበረች። መኖሬን ስለረሳችው ነው መሰል እኔም አከራይ መኖሩን ረስቼ በነፃነት መኖሬን ተያያዝኩት።

ግቢው ውስጥ ከእኔ ቤት ፊትለፊት ያለ አንድ የፅድ ዛፍ ኪታች እስከ ላይ የገና መብራት ተጠምጥሞበት ሁልጊዜ ማታ ማታ ይንበገበጋል። ለምን እንደዚህ እንደሚሆን ይገርመኛል። በጣልም ይሁን አውቶ

መብራቱ ከዛፉ ላይ አይነሳም። ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀበት አለመቃጠሉም ይደንቀኛል። አንዳንዴ መብራቱ በጣም እልም ሲል ግቢውን የአይጋ ቀጠና ቢያስመስለውም ለስላሳ ብርሃኑን ግን እወደው ነበር።

ቤትዬዋ የምትኖርበት ግዙፍ ቪላ ሁልጊዜም በሩ ዝግ ነው። ሥራዋ ምን እንደሆነ እግዚአብሄር ይወቅ። አንዳንዴ ዘንጣ ትወጣና በትልልቅ ፌስታሎች ብዙ ዕቃ ይዛ ትመለሳለች። ከዛ በሯ ይዘጋል። ግታግታ በቤቷ መስኮት በኩል ከመጋረጃው ጀርባ ፈዘዝ ያለ የገና መብራት ዓይነት ረጋ ብሎ ሲበራና ሲጠፋ ይታያል። ግቢ ውስጥ የቆመች አንዲት አዲስ መኪና አለች፣ ሰማያዊ። ሁልጊዜ ቅዳሜ ጧት ሲቧ ታጥባታለች። መኪናዋን ግን ነድታትም አስነስታትም አታውቅም። እንደውም መኪናዋ ጎማ ሥር ሳር በቅሏል። ለአንድ ዓመት ያህል እዛ ቤት ስቆይ አንድ ቃል ተናግራኝ አታውቅም። አሁን ይሄን ማን ያምናል ...? ዝም... ቄሱም ዝም፣ መጽሐፉም ዝም። ቤቱ፣ እርሷ እና ግቢው በአጠቃላይ ይጨንቃል።

አንድ ቀን ቃዲያ እምሾቴ ወደ ቤት ስገባ፣

"አብርሃም!" አለችኝ በረንዳ ላይ ቆማ እየጠበቀችኝ ነበር።

"አቤት...!" ሰማ ጠፋብኝ። ደግሞ ልክ ጣረሞት እንደጠራኝ ነበር የደነገጥኩት።

"እንኳን መጣህልኝ፤ መብራት ተበላሽቶብኝ ነበር..." አነጋገሯ በጭንቀት የተሞላ ስለነበር የሆነ ሰው የታመመባትና ድንገተኛ ክፍል ደውላ "እባካችሁ በነፍስ ድረሱልን!" የምትል ያስመስላት ነበር።

"ኧረ ምን ችግር አለው..." ብዬ ወደ ትልቁ እና ተዘግቶ ወደኖረው ቤቷ ገባሁ። ሁሌም ወደዚህ ቤት ለመግባት እጓጓ ነበር። ከገባሁ በኋላ ግን ያየሁትን ነገር ማመን አልቻልኩም።

ሰፊው ሳሎን ውስጥ በትንሹ ሃያ የሚሆኑ ሰው ሠራሽ የገና ዛፎች ተደርድረዋል። ኮርኒሱን ሊነካ የደረሰው ትልቅ ዛፍ፣ እስከ ትንንሽ ዛፎች ቤቱ ከዳር እስከዳር ተሞልቷል። ምን ይሄ ብቻ ግድግዳው እንደሸረሪት ድር በተወሳሰቡና የተለያየ መጠን ባላቸው የገና መብራቶች ተወርሯል። የቤቱ መብራት በሙሉ እየበራ ስለነበር የተበላሸው የትኛው እንደሆነ ጠየቅኳት። ወደ መኝታ ቤቷ መራችኝ። ማመን አልቻልኩም። መኝታ ቤቱ ሰፍር ቁጥር በሌላቸው የገና አባት አሻንጉሊቶች ተሞልቷል። መልበሻዋ ላይ የተቀመጠ የሚወዛወዝ ጌጥ ነገር በቀጭን የሚቅጨለጨል ድምፅ የገና መዝሙር ያወጣል። ድምጹ ይጨንቃል። አንድ የገና መብራት ነበር የተበላሸባት። ስመለከተው ተቃጥሏል። ይህንኑ ነገርኳት። ፊቷ ግርጥት ብሎ "ሊሠራ አይችልም? እባክህ እርዳኝ" አለችኝ። ስትናገር እንባ እያተናነቃት

ነበር። ግራ ተጋባሁ። በጣም ርካሽ የሆነና ያን ያህል የማያሳስብ የገና መብራት ይህን ያህል ለምን እንዳስጨነቃት ማወቅ አልቻልኩም።

"ቢቃ ተቃጥሏል ... ባይሆን ያን ያህል የሚያስፈልግሽ ከሆነ ነገ ከቢሮ ስመለስ አገዛልሻለሁ" አልኳት።

"እሰይ የኔ ጌታ፣ እባክህ ጥሩውን መርጠህ ግዛልኝ፣ እጠብቅሃለሁ..." ብላ ቦርሳዋን አነሳችና ብር ለማውጣት ስትከፋፍት እጆቿ ይንቀጠቀጡ ነበር። ሁኔታዋን ስመለከት እኔም ተረባበሽኩ። ቦርሳዋ ከእጇ ወደቀ። አነሳችው። ሦስት መቶ ብር አውጥታ ሰጠችኝ።

"ይበቃ ይሆን...?" አለችና አንድ መቶ ብር ጨመረችልኝ። ቦርሳዋ በጣም በብዙ ድፍን መቶ ብሮች የተሞላ ነበር።

በቀጣዩ ቀን የተቃጠለውን የሚመስል ገዝቼላት መጣሁና ሰጠኋት። እየተጣደፈች ተቀብላኝ ወደ ውስጥ ገባች። አመሰግናለሁ እንኳን አላለችኝም። መልሱንም አልተቀበለችኝም። ከፍቱን በተወችው በር ገብቼ መልሱን ጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጬላት ወጣሁ።

እዛው ጎረቤት ያለ ዓለማየሁ የሚባል ባለሱቅ ደንበኛዬ ነበር። አንድ ቀን አብረን ቆመን እያለ ይህችው ሴት ትልቅ የገና ዛፍ ለቀምጨው አሸክማ ስትገባ እየናት ተና በወሬ ወሬ ስለአከራዬ ታሪክ አወራልኝ።

"አከራይህ ... ትንሽ አእምሮዋ ንፋስ ሰርቋል ..." አለኝ።

"እንዴት..." አልኩት ለወሬ ጓጉቼ።

"እየውልህ፣ እትዬ ስምረት በጣም አሪፍ ሴት ነበረች። ገና መኪናዋ ብቅ ሲል የሰፈር ሕፃናት ይንጫጩ፣ ደግ ናት፣ የደግ መጨረሻ። ሰውን ሁሉ ማብላት ማጠጣት ነበር ሥራዋ፤ የዛሬን አያድርገውና፣ ደግ ባሏ ከሷ የባሰ መልዓክ ነበር። መሳጣ ነው፣ ረጅም፣ ሳቅ ብቻ የሚያጠግብ። ፍቅራቸው ለብቻው ነው። ቢቃ ሲገቡ ተቃቅፈው፣ ሲወጡ ተቃቅፈው፣ ሁልጊዜ ሙሽራ ነበር የሚመስሉት። እሷም ቅናት ያለች ቆንጆ ነበረች..."

ባለሱቁ ነገር ያረዝማል...

"...እናልህ የዛሬ አስር፣ በሰራ ሁለት ዓመት አካባቢ ይሆናል። እትዬ ስምረት እርጉዝ ነበረች። ቢቃ የአንሱን ልጅ አይተን የሁለት ቆንጆ ባልና ሚስት ልጅ፣ እያለ ጎረቤቱ ሲያወራ፣ መጀመሪያ ብዙ እና

ከቃ ነው፣ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ባለቤቷ ራሱን ሰቅሎ ተገኘ።"

"ምን...!" አልኩት ደንግጬ።

"አዎ...ግቢያቸው ውስጥ ያለ ዛፍ ላይ ራሱን ሰቅሎ ተገኘ። እንደውም እትዬ ስምረት እስካሁንም ዛፉ ላይ የገና መብራት እድርጋበታለች። አላየሁትም እንዳትል ብቻ እዛው እየኖርክ" አለና ሜቱን በጥርሱ ቀረጣጥፎ ወሬውን ቀጠለ ...

"እትዬ ስምረት ራሷን ስታ ሆስፒታል ገባች። ለቀብሩ እንኳን አልነቃችም ነበር። ያረገዘችውም ልጅ አስወረዳት። ከዛ በኋላ በቃ ይሄን ሁሉ ዓመት ሰው ሰላም አትል፣ ከሰው አትደባለቅ፣ የገና ዛፍ እየሰበሰበች ግቢዋን ዘግታ መኖር ነው። ድንገት ከተነሳባት ከግቢዋም ልታባርርህ ትችላለች" አለና ፈገግ አለ።

"ዘመድ የላትም እንዴ...?" አልኩት።

"ሞልቷት ! ያውም የናጠጡ ሀብታሞች። እንትን ነዳጅ ማደያ የአባቷ ነው፣ ምንትስ ሱፐርማርኬት የወንድሟ ነው፣ ምንትስ አስመጪም የባሏ ነበር አሁን ቤተሰቦቿ እያስተዳደሩ ብር ለእሷ እንደፈለገች ይሰጧታል። ባይሰጧትም ስጡኝ አትልም። ሰው ስለማትፈልግ ማንም ቤቷ አይረግጥም። ብዙ ተጥሮላት ነበር። ፀበልም ወስደዋት ነበር። አማኑኤልም ወስደዋት 'ጤነኛ ናት ጊዜ እያለፈ ይሻላታል' አሉ፤ ይሄው እሷ እንዳለች አለች...፤ እንዴ አለመለከፍ ነው አብርሽ ...።" አለና ወደ ሜቱ ዞረ።

የነገረኝ ታሪክ ውትሮም የሚቀፈኝን ግቢ እንዲከብደኝ አደረገኝ። እየቀፈፈኝ ወደ ቤት ስገባ ግቢው ከነተለመደ ዝምታው ጋር ጣረሞት ሰፍሮበት ጠበቀኝ። ከቤቱ ፊት ለፊት ያ ቀፋፊ ዛፍ የገና መብራት እንደ እባብ ተጠምጥሞበት በግ እልም ይልበታል። በጨለማው ውስጥ ዛፉ ላይ የተሰቀለ ሰው በቀስታ የሚወዛወዝ መስሎ ታየኝ - ረዥም መላጣ ሰው...።

ስቅስቅ ብላ የምታለቅስ ሴት ነበረች። ጀርዬ አንድ ሌሊት የሰው ለቅሶ ሰምቼ ከእንቅልፌ ነቃሁ። ክረምት ነው፣ ስስ ካፊያ ነበር። ቀስ ብዬ ከአልጋዬ ተነሳሁና ቆምኩ። በእርግጥም የሴት ለቅሶ ነበር። እትዬ ስምረት ባሏ የተሰቀለበት ዛፍ ስር ቆማ በዚያ መጋረጃዬን ገለጥ አድርጌ ተመለከትኩ። ጨነቀኝ። ውጥኜ አይዞሽ ልላት በሚያንዘፈዝፍ ካፊያ ስስ የውስጥ ልብስ ብቻ ለብሳ ታለቅሳለች። ኡኡታ ! ኩርምት ብላና ጡቶቿን በእጆቿ ፈለግኩ፤ ግን ደግሞ ፈራኋት። እሊቃቀፏ አስፈሪ ነበር፤ ሰዓት ተመለከትኩ፤ ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት። በግ እልም አቅፋ ካፊያው እየወረደባት ትንሰቀሰቃለች።

...ቦግ እልም ቀይ፣ አረንጓዴና ቢጫ ቀለማት ያሉት መብራቶች እችን ሚስኪን ኮከብ በደረቅ ሌሊት ካፊያ ላይ የብርሃን መልኩን ይረጭባታል።

እትዬ ስምረት ሲታለቅስ ካየኋት ከአራት ወር አካባቢ በኋላ ማታ ላይ በሬ ተንኳኳ። እሷ ነበረች...።

"አብርሃም ደህና አመሸህ?"

"ደህና አመሸሽ እትዬ..."

"ቤት ፈልግና በዚህ ሳምንት ቤቱን ልቀቅ" ብላኝ ተመልሳ ወደ ቤቷ ሄደች።

ምንም አልተቀየምኳትም።

እንዲያውም አዘንኩ።

ብጠቅምም ባልጠቅምም እዚህ አስፈሪ ግቢ ውስጥ እኔ መኖሬ ለእሷም ጥሩ ነበር። ዝም ብዬ ሳስበው፣ ብቻዋን በዚህ ግቢ ውስጥ...አሰቃቂ ነገር ነው። ለማንኛውም በዛው ሳምንት ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ። ቀስ በቀስም እትዬ ስምረት ከአእምሮዬ ደበዘዘች። ቤቱን ከለቀቅኩ ከአንድ ዓመት በኋላ እትዬ ስምረት መሞቷን ሰማሁ። ሞታ የተገኘችው ባለቤቷ የተሰቀለበት ዛፍ ስር ነበር - በስስ የውስጥ ልብስ ብቻ! አስከሬኗ ተመርምሮ ምንም ሕመም የለባትም፤ የሞቷ ምክንያት ግልፅ አይደለም ተባለ አሉ።

ቀብሯ ላይ ሄጄ ነበር። የተሰለፈ መኪና፣ ያልተያዘ የእትዬ ስምረት ፎቶ አልነበረም። የባሏም ፎቶ ሲለቀስበት አይቻለሁ። ቤተሰቦቿ ከምር አሳዝነውኝ ነበረ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ የገና ዛፍ፣ የገና መብራት በተለይ የገና አባት የሚባሉትን አሻንጉሊቶች አልወዳቸውም!

ቦግ እልም ...ቦግ እልም ...የሰው ልጅ ገናው ፍቅር ነው። ቦግ ሲል መፋቀር- በደስታና በተድላ መኖር፣ ፍቅር እልም ሲል በቁም አልያም የማይቀረውን ሞት እንደወረደ መሞት። ቦግ...እልም፣ ቦግ እልም!!

# ቀለም አልባው ቀለም !

አዲስ የተከራየሁትን ቤቴን ቀለም ለማስቀባት አፈላልጌ ያመጣሁት ቀለም ቀቢ በጣም "አካባጅ" ከመሆኑ የተነሳ የአዲሱን ቤት ግድግዳ ሲመለከት አማተበ። ቀጠል አድርጎም፡ "ወዳጄ፡ ቤት ነው የተከራየሽው ወይንስ መዋዕለ ሕፃናት?" አለና በራሱ ቀልድ ፈገግ አለ። ፈገግታው አሽሙር ይመስላል። ለነገሩ ትንሽ አጋነነው እንጂ የቤቱ ግድግዳ ላይ የሚታየው ነገር በእርግጥም ቤቱን የልጅ ቤት አስመስሎታል። ከእኔ በፊት ይኖር የነበረው ሰውዬ አንድ ልጅ ነበረው። ይሄው አንድ ልጅ ነው ቤቱን በቀለማ ቀለም ያዥጎረጎረው። የግድግዳውን ላይ መሞጫርጫርሽ እና የቀለም ድር ብዛት ለተመለከተ 'ይሄ የልጅ ነው ወይስ የሽረሪት' ያስብላል።

በተለይ በግራ በኩል ያለው ግድግዳ ላይ የነበረው ጽሑፍና ሥዕል ብዛት ይገርማል። አክሱም ሐውልትን እንደ ደጋን አጉብጦ ሥሎታል። በጥቁር ቀለም ይሁን በከሰል የሣለው አንጃለት ብቻ የጎበጠ ጥቁር አክሱም ይታያል። አንዲት ጥንቸልም በፊት እግሯ ብቻ እየሮጠች ተስላለች። የኋላ እግሯ ላይ ግን ተኝታበታለች። ጥንቸሏ ተዘጋጅ የተባለ የአጭር ርቀት ሯጭ ዓይነት አቋቋም ነበር የቆመችው።

አለፍ ብሎ ኤ...ቢ...ሲ...ዲ በ'ስሞል'ና በ'ካፒታል ሌተር' ከዳር እስከ ዳር በባለቀለም እርሳስ ተጽፏል። የተጻፈበት ቀለም አረንጓዴ ስለነበረና እያንዳንዱ ፊደል ላይ የሚታየውን የቀለም መደፍደፍ ሲመለከቱት ልጁ በተጨቀጨቀ ቅጠል የጻፈው ነበር የሚመስለው። ከዛ ቀጥሎ ደግሞ በቀይ የማርከር ቀለም ከ1-37 ቁጥር ተጎጥግጧል። ከ34 ቁጥር ጀምሮ ቁጥሮቹ እየፈዘዙ ስለሚሄዱ ልጁ 37 ላይ ያቆመው ቀለም አልቆበት ሳይሆን አይቀርም።

"እና ሰንት ትቀባልኛለህ ?" ስል ጠየቅኩት።

“ያው እንግዳህ ... ይሄ ቀላል ሥራ አይደለም። ትምህርት ቤትን ወደ መኖሪያ ቤት መቀየር በላው ካለ በኋላ ጫን ያለ ዋጋ ነገረኝ። የእኔን ዋጋ ነገርኩት፤ ተስማማን። ለምን እንደሆነ ባላውቅም ዋጋ ላይ ብዙ አልተከራከረኝም። ባልኩት ዋጋ ቶሎ ሲስማማ “ምነው ከዚህም ዝቅ አድርጌ ነግሬው በነበር” ብዬ ተቆጨሁ።

ቀለም ቀቢው ብዙ ያየ ሰው ይመስላል። ለዛም ሳይሆን አይቀርም ብዙ የሚያወራበት ርእስ የነበረው። ደግሞ ሥራውንና ወሬውን እኩል ነበር የጀመረው። ነገሩ እንኳን ወሬውን የጀመርኩት እኔ ራሴ ነበርኩ። ያው ዝም ከመባባል ብዬ እንደ ቀልድ፣ “በዚህ ሥራ ላይ ምን ያህል ጊዜ ቆየህ ?” ስል ጠየቅኩት።

“ሃያ ሁለት ዓመት ሆነኝ” አለ ቀለል አድርጎ።

“ሥራ እንዴት ነው ታዲያ...?”

“ያው እየዋሸን እያስዋሸን አለን!” አለኝ። መልሱ ከጠየቅኩት ጥያቄ አልገጥም ቢለኝ አፍጥጬ ተመለከትኩት። እርሱ ግን ተረጋግቶ ወጉን ቀጠለ።

“...ያው እንደነገርኩህ ላለፉት ሃያ ሁለት ዓመታት በዚህ ሙያ ውስጥ ቆይቻለሁ። የአንድ ቀለም ቀቢ ዋና ሥራ መዋሸትና ሰዎች እንዲዋሹ መንገድ መክፈት ነው። የነበረውን “የለም”፣ ያልነበረውን “አለ” ማለት እና ማስባል። እንዲሁም የሰዎችን ዕይታ ጥልቀት እንዳይኖረውና ባጭሩ እንዲገታ ማድረግ። የምርጥ ቀለም ቀቢ ትልቁ ብቃቱ ይሄው ነው። እስቦበትም ይሁን በደመ ነፍስ የማንኛውም ቀለም ቀቢ ሥራ ከእነዚህ ሁለት ነጥቦች አይዘልም” አለኝ። አወራሩ ለእኔ አይመስልም። እንደው አጠገቡ ባልኖርም ዝም የሚል አልመሰለኝም።

“እና አሁን አንተ እ...” አልኩ፤ ትልቅ ሰው ስለሆነ “እየዋሸህ ነውን ?” ብዬ ለመጠየቅ ከብዶኝ።

“አዎ ... እኔ እየዋሸሁ ነው ወዳጄ !” አለኝ። ይሄ ሰው አእምሮው ልክም አልመሰልህ አለኝ። ከኋላው ቆሜ ስመለከተው የቁመቱ ርዝመትና የአቋሙ መስተካከል፣ በተለይ የፊርጣማ ከንዶቹ ርዝመት ለቀለም ቀቢነት የተፈጠረ ያስመስሉታል። ፀጉሩ እኩል በእኩል ነጭ ከጥቁር የተቀላቀለበት ነው። ነጭ አንድ ቦታ ላይ፣ ራቅ ብሎ ደግሞ ጥቁር አንድ ቦታ ... ነጭና ጥቁር ቡራቡሬ ፀጉር። ፀጉሩ ከአቆራረጡ ከብነት ጋር ተዳምሮ ከአሜሪካ ላም ቆዳ የተሠራ ኮፍያ የደፋ አስመስሎታል።

"አየህ ብዙ ቀለም ቀቢዎች በዚህ ሐሳብ አይስማሙም። 'የእኛ ሥራ ማስዋብና ማሳመር ነው' ይላሉ" አለና ቀለሙን በውኃ በረዘው። ከዛም ብሩሹን አጥቅሶ የቀለሙ ቆርቆሮ ጠርዝ ላይ የቀለሙን ለሐጭ ጠረገና ብሩሹ ላይ የሚዝለገለገውን ቢጫ ቀለም ካረጋጋው በኋላ ግድግዳው ላይ ሞከረው። ችምችም ያሉ ቢጫ መስመሮች በብሩሹ ፀጉሮች ልክ የብሩሹን ዳና ተከትለው ግድግዳው ላይ ተሰመሩ። ብሩሹን ባለፈበት መስመር ሲመልሰው መስመሮቹ ጠፉና ጥቅጥቅ ያለ ቢጫ ቀለም ተከሰተ።

"ከዚህ የባሰ ውሸት ምን አለ ?! ለምሳሌ አንድ ግድግዳ ቀይ ነው ስንል ግድግዳው ቀይ ስለሆነ አይደለም፣ ቀለም ቀቢው በቀይ ቀለም የግድግዳውን ተፈጥሯዊ መልክ ስለሸፈነብን እንጂ። ግድግዳው ግን ዓይንህ ላይ ካልሆነ በስተቀር ሰፋት አይጨምር፣ ወርድ አይቀጥል። በቀለም ቀቢ ውሸት ግርጣታሙ ግድግዳ ግርጣቱን ሸፍኖ በፊትህ ይፍለቀለቃል - የደላው ግድግዳ ይመስላል !"

ከወሬው እኩል ግድግዳዬን መቀባቱን ግን አላቆመም። በአንድ በኩል ያለው ግድግዳ ሩብ የሚሆን ክፍሉ የደላው እየመሰለ ነው የተቀባው። ቢጫ ቀለም ተስማምቶታል። ጫፉ ባጠቀሰው ቀለም ቢጫ በሆነ ብሩሹ ግድግዳው ላይ የተሞነጫጨሩትን ጽሑፎች እየጠቆመኝ ፡ "አሁን ይሄ ልጅ እዚህ ግድግዳ ላይ የመሰለውንና የታየውን ጽፏል፤ እኔ ደግሞ አንተ ከፍለኸኝ የልጁን ጽሑፍ ድራሹን እያጠፋሁ ነው። በቀለም እየቀበርኩት ነው። ይሄ ልጅ ነገ ትልቅ ሰው ቢሆንና 'መጻፍ ከየት ጀመረ?' ቢባል የሁሉም ሰው መልስ የሚጀምረው ከሌላ ቦታ ነው። ሆን ተብሎም ይሁን ሳይታወቅ ታሪክ ተጣመመ ማለት ይሄ ነው። ዛሬ እኔ የቀባሁትን ቀለም ደግሞ ነገ ሌላ ቀለም ቀቢ አልያም ራሴ በሌላ ቀለም እጠፋውና፣ 'አንተስ ቀለም መቀባት የት ጀመርክ?' ብባል መልሴ ተረት ይሆናል፤ ማስረጃው የለማ !"

"...ቀለም ቀላል ነገር እንዳይመስልህ ወዳጄ ..." በማለት ቀለም ቀቢው አፉን ከፍታታ በኋላ ቀጠለ፣ "...የቀለም ታሪክ ግድግዳ ላይ ተጀምሮ ግድግዳ ላይ የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም፤ ቀለም በራሱ ታሪክ ነው፣ ቀለም ፖለቲካ ነው፣ ቀለም እምነት ነው፣ ቀለም ፍቅርና ጥላቻም ነው ! ቀለም የሌለው ነገር አለ ነው፤ ... ለምሳሌ ፈጣሪ ጥቁር ይሁን ነጭ፣ ቢጫ ከተባለ እሱ ከተፈጥሮም ከዕውቀትም በላይ የሆነ ነው፤ ... ለምሳሌ ፈጣሪ ጥቁር ይሁን ነጭ፣ ቢጫ ይሁን ቀይ ማን ያውቃል?"። ቀለም ቀቢው ይሄን እያወራ ግማሹን ግድግዳ አዳርሶታል። የወሬውና የእጁ ፍጥነት እኩል ነበር።

ከግድግዳው ራቅ ብሎ የቀባውን እየተመለከተ እንዲህ አለ፣ "ሸብር ራሱ ቀለም ከሌለው በደንብ አያሸብርም። እንዱ የሸብር ቀለም በሌላ የሸብር ቀለም ካልተደመሰሰ ታሪክ ምኑን ታሪክ ሆነው ?!"

"እ? ደግሞ የሸብር ቀለም የሚባል አለ እንዴ?" አልኩ ደንገጥ ብዬ። ይሄ ሰው ቤቴን በሸብርተኝነት

የተፈረጀ ቀለም ቀብቶ ባጣውን እንዳያመጣብኝ ፈርቼ።

"እንዴታ!! ያንተ ብቤ አፍላ ወጣቶች ነጭ ሽብር አሉና ደርጉን አሸበሩት። እንደ ደግ ወዳጅ መንገድ ላይ 'ደህና ዋልክ?' ብለውህ፣ 'እግዚሃር ይመስገን' ብለህ ኮፍያህን ስታነሳ ሣንጃቸውን በሽጉጥ ቀንጭሰውህ መንገድ ላይ ደመ ከልብ ያደርጉሃል። እንግዲህ ይሄ ነጭ ሽብር እንዴ ከሰማኸው ሰሙ ከአእምሮህ አይነቀልም። ለምን መሰለህ ወዳጄ? ዓላማው ምናምኑ ገብቶህ አይደለም። ዓላማው እንኳን ላንተ ለተኳሹም ጠርቶ አይታየው። ቀለሙ ነው ሽብሩ ... ቀለሙ ላይ ደግሞ ፍርሃትህ አለ።"

"...የባህል ልብስህ ነጭ ነው። በዓል በሆነ ቁጥር ሕዝቡ ነጭ ሲለብስ መንግሥት ይሸበራል። በወር ሠላሳ ቀን፣ ያውም ጠዋትና ማታ ነጠላውን አጣፍቶ፣ ጋቢውን ደርቦ ቤተክርስቲያን የሚስም ሕዝብ ያለባት አገር ከነጭ ቀለም ጋር የጠበቀ ዝምድና ነው ያላት። ነጭ ነገር ውልብ ባለ ቁጥር ካድሬው ሁሉ ነፍሱ በድንጋጤ ይውለበለባል። ነጭ አርግብ ሳይቀር ያስደነብረዋል። ጓድ ሊቀመንበር ታዲያ ሽብሩ ሳይሆን የሽብሩ ቀለም ገናናነት አሸበራቸው፤ የሕዝባቸው ልብ ነጭ ሽብር ተቀባ!"

"ደርጉን ሰበሰቡና በቁጣ፣ 'ጓዶች ከሁን ጀምሮ ማንም ነጭ ልብስ እንዳይለብስ፣ ሽሮ ሜዳ ያሉ ሸማኔዎችም ነጭ ነጠላ እንዳይሠሩ፣ ነጭ እጀ ጠባብ እንዳይሸምኑ ለማወጅ አስቤያለሁ። ከዛ በፊት ግን ነጭን አሸንፎ ሕዝቡ ሕሊና ውስጥ የሚቀመጥ ቀለም ካለ እስቲ ተናገሩ! ሕዝባችን ከነጭ ቀለም ሌላ ምን ዓይነት ቀለም ይወዳል ? ይህች አገር አብዮታዊ ቀለም ያስፈልጋታል !' ሲሉ ጠየቁ፤ በቀለሙ ላይ እንቢ የሚል ሌላ ቀለም ፈለጉ !"

"...ጌታዬ ያው ጀግና ሕዝብ የደም ቀለም ሲመለከት ደሙ ይፈላል ... በዛ ላይ ቀይ የጀግንነት ምልክትም ነው። የመስዋዕትነት ምልክት ነው። ባንዲራችን ላይ ሁሉ ቀይ ቀለም አለ። ነጭ እኮ ባንዲራችን ላይ የለም፤ ከየት አባታቸው እንዳመጡት እንጃላቸው..." ሲል የቀይ ቀለምን ገናናነትና የነጭን ቀለም ኮሳሳነት አንድ የደርግ አባል ኢጋንነው ተናገሩ።"

ሌላው ቀጠለ፣

"...አሁን የተናገሩት ጓድ ጥሩ አስቀምጠውታል። እውነት ነው ቀይ ቀለም ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ መሰረት አለው። በተጨማሪም ቀይ የእሳት፣ የነበልባል ምልክት ነው። ጓድ ሊቀመንበር፣ ቀይ ደግሞ ባህላዊ ቀለማችን ነው ... ከጥሬ ሥጋ ጋር ይያያዛል። ሕዝቡ መቼስ ለበዓላት ነጭ ለብሶ፣ ያለው ጥሬ ሲጋ፣ የሌለው ቀይ ወጥ መብላቱ አይቀርም። ቀይና ነጭ አይነጣጠሉም፤ ወንድማማች ናቸው !"

ሲል አብራራ።

"...ጓድ መንግስቱ ታዲያ እሱብ አደረጉና 'መልካም ጓዶች፣ አብዮት አደባባይ ሕዝቡን በነቂስ አስወጥታችሁ ሰብስቡልኝ !' አሉ። ሕዝቡ እንደተሰበሰበ ጓድ መንግሥቱ ድንገት መሾረጥ አደረጉና በጠርሙስ የተሞላ ቀይ ቀለም ሕዝቡ ፊት ሲያፈጉት ወላ ነጭ ሽብሮች፣ ወላ አገር ሲሰልሉ የመጡ ነጫጭ 'ቱሪስቶች' ከራማቸው ተገፈፈ። መቼስ ያኔ ቀለሙን ለተመለከተው ሲቀመንበሩ እሰፋልቱን የፈነከቱት ነበር የሚመስለው። ሕዝቡ ቀዩ ቀለም መንገዱን አልብሶት ሲመለከት እፉን ደም ደም እያለው ቀይ ጭብጨባሙን ለሊቀመንበሩ ለገሳቸው።"

"ቀይ ጭብጨባ?" አልኩ ግራ ገብቶኝ።

"አዎና! ደም ያሰከረውን ሰው ፈርተህም ይሁን ተሳስተህ 'አይዞህ በርታ !' የምትልበት ደመኛ ጭብጨባ አለኩ። እሱን ነው የምልህ። በተለይ በአገራችን ታላላቅ የሚባሉት ጥፋቶች ቀደም ሲል የሕዝብ ቀይ ጭብጨባ ያበረታታቸው ነበሩ። ቀይ ሽብር ራሱ የቀይ ጭብጨባ ውጤት ነው።" አለና ወደ ሌላኛው ግድግዳ ተሻገረ።

"...እናልህ ያንን ደም የመሰለ ቀለም ሊቀመንበሩ ሕዝቡ ፊት ሲያንቧቹት ሕዝቡ ደነገጠ። ምን ሕዝቡ ብቻ ይሄው ቴሌቪዥኑም ምኑም እስከዛሬ ድንጋጤው አልለቀው ብሎ የሊቀመንበሩን ቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ እና እሰባበሩን እንደ ድንቅ ትርዒት በየቀኑ ያሳየዋል። ታዲያ ከአብዮት አደባባይ የተፈነጠቀው ቀይ ቀለም ኢትዮጵያን ከዳር እስከ ዳር ቀይ አለበሳት። ቀለም ያመጣው መዘዝ ሰይፍ እማዘዘ። ነጭ እና ቀይ የሚሉትን የቀለም ሽፋኖች ብትተዋቸው ያው ሽብር ይሄም ሽብር ነበር። እና ይሄ ባለ ኅብረ ቀለም ሽብር ሰንቱን ንፁሃን በላ ወዳጄ። ሕዝቡ እንደሆነ በዛም በዚህም ነጭ አይታየው ቀይ አይታየው ... ባጭር ለቀረ ልጁ፣ ቤተሰቡና ወዳጁ ጥቁር የታሪክ ማቁን በልቡ ሰብሶ እህህ ተረፈው።" አለ ቀለም ቀቢው፣ ሁለተኛውን ግድግዳ ኢጋምስ ነበር።

"...እና ወዳጄ፣ የበሰበሰውን ግድግዳ በቀለም እየሸፈንን ብር እንቀበላለን። የሰውም ዓይን ቀለሙ ላይ ይቆማል። ወደ ውስጥ ጠልቆ የግድግዳውን መሠረት አይመለከትም። ቀለም ቀቢው አታልሎታላ ! ቀዩ፣ ቢጫው ግድግዳ እያለ ይኖራል። ከቤት ጀምረህ መንደሩን ይዘህ ወደ አገር ሽቅብ ብትጓዝ የማደስ ትርጉም ትላንትን ከመሸፈን እንደማያልፍ ይገባሃል ! ይሄው አሁን የዛን እንቦቀቅላ መሞጫጫር ጽሑፍ በቢጫ ቀለም መታሰቢያውን አበፋነው። ማንም አዲስ ሰው ወደ ቤትህ ቢመጣ ከቢጫ ቀለምህ ሥር አንድ ጨቅላ ሐሳቡን ለመግለፅ የተፍገመገመበትን ግድግዳ አይመለከትም !" አለ ቀለም ቀቢው።

ቤቱን ሙሉ ለሙሉ ቀብቶ ጨርሶ ነበር።

መጨረሻ ላይ የተቀባውን ግድግዳ ስመለከተው ቢጫው ቀለም እንዳሰብኩት ደማቅ አልነበረም።

"ይሄ ቀለም ግን እንዳሰብኩት አልደመቀም፣ ትንሽ ፈዘዝ አላለም ? አልኩት ቀለም ቀቢውን። እሱ ግን የማይገናኝ ጥያቄ ጠየቀኝ፣

"አግብተሻል ?"

"አይ አላገባሁም" አልኩት ድንገተኛ ጥያቄው ገርሞኛል።

"እየውልህ ወዳጄ፣ ቤትን የሚያደምቀው ቀለም አይደለም። ፈገግታዋ ከቀለም በላይ የሚያበራ ቆንጆ ሚስት ፈልግና አግባ። ትልቁ እና ወደር የሌለው ደማቅ ቀለም ፍቅር ነው። የፍቅር ቀለም አይደበዝዝም። በሌላም ቀለም አይጠፋም። ሕያው ሆኖ የሚኖር የፍቅር ቀለም እስኪገኝ ሰው ቀለም ሲያሳድድ ይኖራል" ብሎኝ እጁን ይታጠብ ጀመረ።

"ፍቅር ቀለሙ ምንድን ነው?" አልኩት ባለቀ ሰዓት ቀለም ቀቢው እንዲያወራኝ ፈልጌ ነበረ።

"የፍቅር ቀለም ምን መሰለህ... ፍቅር ቀለም የለውም !! እውነተኛ ነገር ሁሉ ቀለም የለውም።"

ቀለም ቀቢው ዕቃውን ሸካክፎ የተዋዋልንባትን ብር ከተቀበለኝ በኋላ የሥራ ዕቃዎቹን የጫጠረበትን ከረጢት በግራ ትከሻው በኩል አንጠልጥሎ እያፏጨ ከቤቴ ፊት ለፊት ያለችውን አቀበት መንገድ ተከትሎ ነጎደ። ቱታው ላይ የተፈነጣጠቀበት የቀለም ዓይነት ተደበላልቆ ተዘርቷል። የእኔንም ቤት ሲቀባ የተፈናጠቀበት ቢጫ ቀለም ቱታው ላይ አለ። ፀጉሩም ቡራቡሬ ነው።

ነጭ እና ጥቁር...

# ሊሆን ይችላል !!

ለሚስቴ ያለኝ ፍቅር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ነው የሚሄደው። ችግሩ ፍቅሩ የሚጨምረው ብቻውን አልነበረም፤ እግር እጅ ከሌለው ቅናት ጋር እንጂ። በእኔ ልብ ውስጥ ፍቅርና ቅናት እንደመንትያ ልጆች እኩል ነበር የሚያድጉት። እየቆየ ግን የፍቅር አቅም እየኮሰመነ፣ የቅናቴ ጡንቻ እየፈረጠመ ሄደና ቅናቴ እንደ ምርቃት ቆብ ከነመነሳንሱ በፍቅሬ እናት ላይ በኩራት ጉብ አለ።

አያድርስ ነው! ርኩሳዊ ቅናት የሰይጣን አንዱ ሥራ ሳይሆን ሰይጣን ራሱ ሳይሆን አይቀርም። ሚስቴ መዓዛ ጨዋነቷን አገር ይመሰክርላታል። ግን ምን ዋጋ አለው። የእኔ የባሏ ሆድ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ሻከረል።

"ምን ስታደርግ አይተሀት ቀናህ?" ብባል መልስ የለኝም። ግን እቀናለሁ። ስቀና እበሳጭባታለሁ። አንዳንዴ እንደውም ከመሬት ተነስቼ ሁለት-ሦስት ቀን እኮርፋታለሁ፤ ግራ ይገባታል። የምትይዝ የምትጨብጠውን ታጣለች። አንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ እየኖርን ስዘጋት የምታደርገውን ነገር ታጣለች። ...ደስ ይለኛል። ጭንቀቷ ነፍሴን ያረካታል። አንዳች የመበቀል እርካታ ይሰማኛል። ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠና ቀይ ጉንጯ በርበሬ መስሎ ግራ ተጋብታ ስመለከታት በኩራት ኩፍስ ብዬ በስቃይዋ እዝናናለሁ...!

*ብዙ ጊዜ፣ በተለይ ወንዶች በፍቅረኝነት ለየት ቅናት ያጠቃቸዋል። ያፈቀሯትን ሲያገቡ ግን በቁጥጥራቸው ሥር የዋለች መስሎ ስለሚሰማቸው ለይቀትም* ሲባል ነበር የሰማሁት። የእኔ ቅናት ግን በቁጥጥራቸው ሥር የዋለች መስሎ ስለሚሰማቸው አይቀንስም ነበር። ለዛም ሳይሆን የተገላቢጦሽ ነው። በፍቅረኝነት እንደነበርንም ይሁን የትጋባን ሰሞን አልቀናም ነበር። የኋላ ኋላ ግን ቅናት ከነ አይቀርም መዓዛን ብዙም ትኩረት ሰጥቼ የት ገባች፣ የት ወጣች የማልለው። የልጅ ልጅ ሰፈረብኝ።

የቅናት ትልቁ ችግር የሚቀናበት ሰው እንደሚያስቡት መሆን አለመሆኑ ላይ አይደለም። የሚቀናውን ሰው ራሱን በቢታችንነት ስሜት አንለቅልቆ ያልሆነውን ማድረጉ እንጂ። መዓዛ ፊልም እየተመለከተች እንዱን የፊልም ተዋናይ ካደነቀች የጨጓራ ሕመሜ ይነሳል። ቢቃ ስለሆኩና፣ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀውን ጎበዝ የፊልም ተዋናይ ማጣጣል እጀምራለሁ። መዓዛ ከተከራከረችኝማ ቢቃ ሰውነቴ ሁሉ በብስጭት ይንገበገባል፤ እቀናለሁ !

"ምናባቱ ይሄ ሴታሴት ካሜራ ፊት ጀግና ይመስላል፤ ልክስክስ፣ እዚህ ካዛንችስ መጠጥ ቤት ለመጠጥ ቤት፣ ጫት ቤት ለጫት ቤት ሲዞር አይደል የሚውለው!? እሱ ያልተኛቸው ሴተኛ አዳሪዎች የሉም።

"ኧረ አብርሽ በእግዚአብሔር፣ የተከበረ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነው..." ትላለች መዓዚ።

"አንቺ ስለ እሱ ሕይወት ሲታጣሪ ነው የምትውይው? ምን ታውቂያለሽ..."

"እኔማ ምን አውቃለሁ ራሱ ነው በቲቪ ከነሚስቱ ቀርቦ ኢንተርቪው ሲሰጥ ያየሁት።" ትላለች ጨኸቴ አስደንግጧት።

"እና በቴሌቪዥን ቀርቦ እጠጣለሁ፣ እቅማለሁ፣ ሴት አይተርፈኝም ይበል...?" እልና መዓዚ ላይ አፈጥባታለሁ። መዓዚ በግርምት እየተመለከተችኝ ዝም ትላለች። ፊልም በተከፈተ ቁጥር መዓዚ የምታደንቀውን ሰው ስዘልፍና ሳጣጥል ፊልሙን በቅጡ ሳናየው ስለሚያልፍ መዓዚ ቀስ በቀስ ማድነቋን አቆመች። እኔ ግን መቅናቴን አላቆምኩም። አንዱ ወንድ ተዋናይ በተናገረው ነገር ከሳቀች ወይም በመደነቅ ራሷን ከነቀነቀች ቅናቴ ያስለፈልፈኛል፤ "እነዚህ የጠላ ቤትና የጫት ቤት ቀልድ እየመጡ ይቀባጥራሉ፤...አይ የኢትዮጵያ ፊልም ! እንዲህ የዱርዬ መናኸሪያ ሆኖ ይቅር...! ምን የፊልም ኢንዱስትሪ ነው፣ የዱርዬ፣ የሥራ ፈት ኢንዱስትሪ ቢሉት ይሻላል...።"

ይሄ ባህሪዬ ሲያስመርራት መዓዚ ከእኔ ጋር ፊልም ማየት አቆመች። በፊት ፊልም ሲከፈት ተንደርድራ መጥታ ጎኔ ትቀመጥና ራሷን ትከሻዬ ላይ ዘንበል አድርጋ ነበር የምትመለከተው። የሚያስቅ ነገር ስትመለከት አንገቴ ሥር ገብታ ፍርፍር ብላ ትስቅ ነበር። ዕድሜ ለቅናቴ! ይሄው ፊልም ከእኔ ጋር ማየት አቆመችና አረፈችው። ፊልም ሲከፈት ወይ ጓዳ ገብታ ትንጎዳጎዳለች፣ ወይ መኝታ ቤት ትገባና ትተኛለች፣ ወይም ታነባለች።

"ፊልም አታይም እንዴ...?" እላታለሁ።

"አይቼዋለሁ።"

"የት አየሽው?"

"ባለፈው እማዬጋ የሄድኩ ጊዜ።"

"እማዬ ቴሌቪዥናቸው ተበላሽ አላልሽም...?"

"ሌላ ገዙት።"

"ማን ገዛላቸው?"

"ኧረ አብርሽ በእግዚአብሔር አታጨናንቀኝ!" ትልና በምሬት ታየኛለች። ቤታ እናቷ ቤት አይደለም ያየችው ... የሆነ ወንድ ጋር ትከሻው ላይ ራሷን ጣል አድርጋ (በየመሀሉ እየተሳሳሙም ሊሆን ይችላል)፣ ቤቃ እንደዛ ነው ያየችው፣ ... ልክስክስ ውይ ሴቶች !! እብሰለሰላለሁ። ትከሻውን የተደገፈችው ወንድ ማን ይሆን...? ምናልባት አብረውም ተኝተው ሊሆን ይችላል፣ አብራ ፊልም ለማየት ያልተመለሰች... አሺ ለእናቷ ማን ቴሌቪዥን ገዛላቸው? ይሄው ታሪኩ ሲገጣጠም...መንዛ ሀብታም ወንድ ጋር ሄደች...፣ ቤቱ ሄደው ፊልም አብረው አዩ፣ (ሶፋ ላይ አብረው ተቀምጠው፣ ጫማዋን አውልቃ፣ የሚያማምሩ እግሮቿን ሶፋው ላይ ሰብሰብ አስቀምጣ፣ ልክ እንደ ቤቷ ዘና ብላ...)፣ ከዛ አብረው መኝታ ቤት ገቡ ...፣ ኧረ ሶፋውን ማን ይዘባቸው... ከዛ ነፍሳቸው መለስ ሲል አወሩ፣

"ፊልም ትወጂያለሽ የኔ ቆንጆ" ሊላት ይችላል፣ ግን "የኔ ማር" ነው የሚላት፣

"ብ...ጣ...ም!!" ትለዋለች ደረቱ ላይ ተለጥፋ፤ ይች መኸገር። ሁለቱም መኸገር ናቸው እንጂ እሷም እሱ ላይ እሱም ትዳሬ ላይ የተጣበቁ መኸገሮች!!

"እና በየቀኑ ትመለከቻለሽ...?"

"በፊት ነበር፤ አሁን ባሌ እየተነዛነዘ በየት በኩል ሊያሳየኝ ብለህ።"

"አ...ባልሽ ግን ምንይነት ደደብ ቅል ራስ ነው ባክሽ። 'ሙቪ' አይየችሁ ይነዛነዛል ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አሜዚንግ !"

"ብ...ጣ...ም ...! ምን ቅል ብቻ! ድንጋይ ...! ባልሰቤት ራስ ነገር ነው እንጂ። ሊገባ ሲወጣ መነዛነዝ ነው።

*እንዳልተሳካለት ተምኔር ያየውን ተምኔይ ሁሉ መዝለፍ ነው ሥራው" ትለዋለች።*

አቧን ባሬቀርኩ፣ ቤቴን ትዳሬን ባልኩ የማንም ዱርዬ ጋር ስታማኝ አያበሳጭም? ውስጤ ይብከነከናል፤ ላብ ላብ ይለኛል! በላዘ የጨቀየ መዳፌን በእልህ ጨብሬው ሶፋውን በቡጢ እነርተዋለሁ! መካ በድንጋጤ ከራማዋ ተገፍፎ እያማተበች ትቀርበኝና ጭንቀት በወረረው ፊቷ ላይ እንባ በቋጠሩ ዓይኖቿ እየተመለከተችኝ፣

"ምነው ፍቅር ምን ሆንክ? ከሰው ጋር ተጣላህ እንዴ? ላብ በላብ ሆንክ እኮ፤ አመመህ እንዴ የኔ ፍቅር...?" ጉንጬ ላይ እጇን ልታሳርፍ ስትልክ እጇን ወደዛ አሽቀንጥሬ ተነስቼ ወደ መኝታ ቤቴ አገባና የቁም ቅዝቃዜን ተኝቼ እቀጥላለሁ። እሷም ግራ በመጋባት ወገቧን ይዛ መኝታ ቤት በር ላይ ቆማ ትቆያለች፣ "ምን እዳ ገባሁ!" እያለች።

እቀናለሁ...! እቀናለሁ...! እቀናለሁ ! እንዳንዴማ በህልሜ ሁሉ ስለምታኘ መዓዛ ፀበል እንሂድ ትለኛለች። *ቢመቻት አብድ ነው ብላ አማኑኤል አሳሰራኝ ዓለሚን ከሌላ ወንድ ጋር ልትቀጭ እንዳሰበች እጠረጥራለሁ... ተገኝቶ ነው ? አሁን ሌላ ወንድ ጋር ብትሄድ ሰው ሊያስቀምጣትም፤ እስኪ ምን አጣች ጥጋብ ልከስከስነት እንጂ ቀ...ይሄን የመሰለ ሸበላ የጠገበ ደመወዝ የሚበላ ባል ትታ ... ወይ ጥጋብ' ይላታል ... ካበድኩላት ግን እንዳሻት ትዘላለች ሰውም ሊይቃወማትም "ምን ታድርግ አብድ ጋር ትኑር እንዴ ታዲያ ? ወጣት ናት! ቆንጆ ናት! ሰንት ነገር ያምራታል! ምን በወጣት..." ሊሉ ይችላሉ። እኔ ደግሞ ለእልኳ አላብድ ! ሲያምራት ,ይቅር...!!*

ሌላ ቀን ደማቅ ሰማያዊ ሹራብ በቢጫ ሱሪ ለብሼ ልወጣ ስል፣ "እረ አብርሽ እብሮ አይሄድም! ሱሪውን ቀይረው የኔ ቆንጆ፤ ፊትህ ጥቁር ቢሆን እንኳን ያምርብህ ነበር፤ ካንተ ,ጋር ግን አይሄድም።" ብላ በሳቅ ፍርስ አለች። *ቆይ እሷ ስለወንድ አለባበስ እንዴት አውቃች? ይሄ ስለ ልብስ ቀለም ሳይሆን ስለእኔ ምርጫ አለማወቅ ለመናገር ሆን ብላ የተናገረችው ነገር መሆን አለበት...* እንዳልሰማ ሰው ትቻት ወጣሁ! እዛ ላስቀመጠችው ለእናቷ ቴሌቪዥን ለሚገዛው ደይብ ውሽማዋ ትንገረው ... ምናልባት ጥቁር ሊሆን ይችላል ... ትቻት ወጣሁ። ለምን እንደሆን እንጃ እንደማላከብራት ማሳየት እፈልጋለሁ።

በር ላይ አንድ የማልወደው ጎረቤቱ ደረቱን ገልብጦ በጠዋቱ ቢፕከ አውትና በቁምጣ ኮንዶሚኒየም ደረጃ ላይ አገኘሁት። እኔ ስወርድ እሱ ሲወጣ ነበር የተገናኘነው። በእጁ የመዝለያ ገመድ ይዟል፤ ከስፖርት እየተመለሰ ነው።

"ሰላም አብርሽ!" አለኝ በፈገግታ።

"ሰላም ሰለሞን!" ብዬው ሳልፍ ስል፣

"ምነው ይሄ አለባበስህ ትንሽ አልደመቀም...?" አለና ፈገግ አለ። *ቃሉዶ ሞቷል ለዛ ቢስ ለካሬ ሁሉ!!* እንዳልሰማሁ አለፍኩት። *ግላ ራስ! አሉ ስለኔ አለባበስ ምን አገባው!?* ይሄ በዘኔ ጎረቤቱ ሥራው ምን እንደሆነ እንጃለት (*ሥራ እንኳን ያለው አይመስለኝም*) ሁልጊዜ የምንጋራው በረንዳ ላይ ወንበር ያወጣና ዝሆኔ የያዘው የሚመስል (*ፈርጣማ ይሉታል አንዳንዶች*) ጠብደል ግንዲላ እግሩን ዘርግቶ ጋዜጣ ያነባል። ኑሮው ዘና ያለ ነው። አንዳንዴ ውድ የሆነ ሙሉ ልብሱን ይለብስና ዲኤክስ መኪናውን አስነስቶ ይሄዳል ... አፍታ ሳይቆይ ይመለሳል። ቤቱ ውስጥ የቀበረው ነገር ሳይኖር አይቀርም፤ ከቤቱ ርቆ አይሄድም። ይዞት ይሂድና ! ቆይ ግን ቤት እየዋለ እንዲህ ተዝናንቶ የሚውልበትን ገንዘብ ከየት አባቱ ነው የሚያመጣው። ሌባ ይሆን...? ወይንስ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ...?

ድንገት አንድ ሐሳብ አእምሮዬ ውስጥ ፈነዳና ቀጥ ብዬ ቆምኩ፤ - ፉዕውዕውዕውዕውዕውዕ እንደ መኪና! እቋቋሜ ድንገተኛ ስለነበር ከኋላዬ የነበረች ልጅ ልትጋጨኝ ለትንሽ ተረፈች። ቆይ ይሄ ጎረቤቴ ቤት ሲውል ምን እያደረገ ይውላል? መደዳውን አራት ቤቶች አሉ። ጥግ ላይ የኔ ቤት። መሃዛ ሥራ ስለሌላት ቤት ነው የምትውለው። ቀጥሎ ሁልግዜ ዝግ የሆነው እንደኔ ከርታታው ጎረቤቱ (ፊልድ ነው ሥራው)፤ ቤቱ ሁልግዜ ዝግ ነው፤ የሸረሪት ድር ሁሉ በሩ ላይ ያደራል። ቀጥሎ ይሄ በዘኔ አለ። በዘኔው መልኩ ጥቁር ነው። ልክ እንደ ፊልም የሚስቱ ንግግር በምልሰት ታየኝ፤ *"ጥቁር እንኳን ብትሆን..."* ነው ያለችው አይደል?...ቢንጎ !!!

በዘኔው ቤት ነው የሚውለው። ምን ቤት ... እኔ ቤት ልበል እንጂ !! መቼስ በአንድ ዝግ ቤት ዳርና ዳር በዘኔውና ሚስቴ ብቻቸውን ሲውሉ አይነካኩም ማለት ዘበት ነው። እንዴ አብረውም ፊልም ሊመለከቱ ይችላሉ እንጂ። በእኔው ቴሌቪዥን፣ በእኔው ዲቪዲ፣ እኔው ሶፋ ላይ !! ... ሊሆን ይችላል !!

ተመልሼ ወደ ቤቴ ሮጥኩ !

*ጉድና ጅራት እሉ ! ወይ ድፍረት...!*

*በራሴ ... በራሴ ቤት ... በራሴ አልጋ ... በራሴ ብርድ ልብስ ... በራሴ አንሶላ ... በራሴ ፍራሽ ... በራሴ ሚስት በራሴ ... ! ባፍጢሜ አስከምደፋ ተጣደፍኩ። ምን ዋጋ አለው አስከሁን ነገር የተበላሸውን ! አሊጋውን አንደሆን አኔ ሚስቴን አኔ ራሴ አንደ መኪና አሙቄ ትቼለት ወጥቻለሁ። መጣሁንም ቢሆን*

ለሊቱን ሊታቀፈኝ ስትሞክር በኩርፊያ እጇን እየገፋሁ ጀርባዬን ሰጥቻት በእምሮት ሊታገዩት ነው ትቻት የወጣሁት። በስስ ፒጃማ የሞቀ አልጋ ውስጥ እሳት ሆና ትጠብቀኛለች። በቃ ምን ችግረው ቁምጣውን ወለቅ አድርጌ በጠዋቱ ገነት መግባት ነው !!! ጉድ ጉድ ጉድ - እሚመጣው ለሰው። ወይ ነደ !! ሮጥኩ! ኮቴ እንደ ክንፍ እየተውለበለበ ...ወደ ቤቴ ... ምን ቤት አለኝ ቤቴ ፈራርሶ ! ሱናሚ አውሎ ንፋስ ከምር መሠረቱ ቤቴን ነቅሎ የሚጥል ጎርፍ - ከጎረቤት አገር !

መንገዱ ረዘመብኝ። የመጓዣ ደረት የተላጠ ሸንኮርት መስሎ ታየኝ። ጡቶቿ ስስ ፒጃማዋን ወጥረው ሜፋቸው ባቁላ ባቁላ መስሎ... ቀይ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ ከሥር ተንጋልላ... የሚያማምሩ እግሮቿ በጠረንገሎው ዙሪያ ተጠምጥመው ታዩኝ። እግሮቿማ ለምን እያምሩ፤ እሾህ አይወጋቸው ጋሬጣ ...። ሎሚ መስለው እንደተቀመጡ ሳይወጡ ሳይወርዱ ቤታቸው። መኝታ ቤታቸው ድረስ ካንድ እየሉ ሁለት ባል ሲመጣላቸው ...፤ ያ የነደለ ሰባሪ የሚያህል ባዘኔ ጎረቤቴ ከነላቡ፣ ከነጠረኑ አልጋዬ ላይ ታየኝ። ምናለ ሻወር እንኳን ቢወስድ...፤ የሰው አልጋ መድፈሩ ካልቀረ ለወጉ ለሥርዓቱ ሰውነቱን ለቅለቅ ብሎ ቢዳፈር ምናለ...!ሥራ ውዬ ደክሞኝ ነው የምገባው ለኔስ እያዝኑም...? እንሰላ መጋረፉን ቢተውኝ እንኳን ለብቻ ኩርምት የምልባትን አልጋ ምናለ ቢተውልኝ? ወይ ጭካኔ ! ታየኝ ባሁ እንደማስቲሽ መዓዛ ውብ ሰውነት ላይ ተመርጎ አለለቅም ሲል። ማን ያውቃል የራሴ ሚስት በስሜት እየተሰረቀረቀች 'ዋኔ ጌታ! ጠረንህ የናርዶስ ሽቶ ነው!' እያለችው ይሆናል! ፍቅር እንኳን አፍንጫን አእምሮን ይዘጋ የለ !

ሊሆን ይችላል!!

ደግሞ እንደ አባወራ ቤት አለኝ ብዬ ሶፋ ላይ ተንልቼ የማላውቀው አገር እሳተ ገሞራ ሲፈነዳ በሐዘን ከንፈሬን እየመጠጥኩ ቢ.ቢ.ሲ. አያለሁ... የዋህ አባወራ እሳቱን ጎረቤት አስቀምጦ እሳተ ገሞራ በዜና ያያል...። እኔን ራሴን ዜና አደረጉኝ፤ ዕድሜ ለሚስቴ፤ እኔን ራሴን ዜና ...! ያውም ሰበር ዜና ...! ሞራሌንም ቅስሜንም የሚሰባብር የሚያንከከት ሰበር ዜና ! ምን ጋዜጠኛ አለ እዚህ አገር ... ቢኖርማ ካሜራቸውን ይዘው ከኋላዬ ተከትለውኝ በሮጡ ነበር !! ዝም ብለው ስለማይደብ ያውሩ ... እዚህ ስንት ሚሊየን ሜጋ ዋት እሳት ከመኝታ ቤቱ ሲመነጭ መቼ በቁም ነገር ተመለከቱት...!!

ቤቴ ስደርስ በሩ ብርግድ ብሏል ...!

እግዚኦ ድፍረት ! ምናለ በሩን እንኳን መለስ ገርበብ ቢያደርጉት ... ሰው ባይፈሩ ነፋስ እንኳን አይፈሩም ... ወይስ የመኝታ ቤቱን በር ቆልፈው...

*ሊሆን ይችላል !!*

በተከፈተው በር ተወርውሬ ስገባ መዓዛ "አብርሽዬ ድረስ...!" ብላ በእጇ የያዘችውን የዱቄት ሳሙና በቁሟ ለቀቀችው፤ (*ባትለኝም ደርሼ ነበር እኔማ...*) ...፤ ዱቄት መስሎ ሳሎኑ ምንጣፍ ላይ ተዘራ። ራቅ ብሎ ሊታጠብ የተዘጋጀ የእኔ የቆሸሸ ልብስ ተከምሯል! በዚህ ሌሊት ልብሴን ልታጥብ እየተዘጋጀች ነበር፤ መዓዛ ! የሐፍረቴን ወደ መኝታ ቤት ገብቼ ኮሜዲናውን ከፈትኩና የረሳሁትን እቃ የወሰድኩ መስዬ ተመልቼ ወደ ሥራዬ ሮጥኩ። ትንሽ ሐፍረት ቢሰማኝም አእምሮዬ ውስጥ ግን አንድ ሐሳብ መጣብኝ ...

*መዓዛ ልብስ አጥባ ካስጣጣች በኋላ እስከሚደርቅ ምን ትሠራለች ... በተሰጣው ልብስ ውስጥ ጠረንገሎው ጎረቤቴ እየተሽሎከለከ ወደ ቤቴ ሲገባ ... በሩ ሲዘጋ ... ታየኝ !*

*ሊሆን ይችላል !*

ከሰዓት ከምሠራበት አየር መንገድ ቢሮዬ ሆኜ ለመዓዛ ስልክ ደወልኩላት። አንዴ ጠራ ... 2... 3... 4... 5... "*የደወሉላቸው ደንበኛ ስልክ አይመልሰም ! አባክዎ ...*"

*ወይ እባክዎ ... ምኑን ተከበርኩት ... ምኑን ለአንቱታ በቃሁት ... ኮት መልበስ ብቻውን አንቱ አያስብል ... ቢሮ ያማረ ወንበር ላይ መነሰት አንቱ አያስብል ... ዳዳዬ እየፈረሰ ... ቤቴ እየተገረሰሰ ... ሦስት ጉልቻ ያልኩት ትዳሬ ሲድሰት ጉልቻ እየሆን ወይ አንቱታ...! ስልኩ ያለው ሳሎን፤ ሚስቴ እስካሁን መኝታ ቤት ... ወይም ጠረንገሎው ጎረቤቴ ቤት ትሆናለች ... ማን ያንሳው ስልኩን ...፤ ዘመድ እንደሌለው ሐዘንተኛ ብቻውን ያልቅስ እንጂ ...፤ ብቻውን ስልኩ...!*

ስብስክለክ ስልኬ ጠራ ... መዓዛ ነበረች።

"የት ሄደሽ ነው ስልኩ ይሄን ያህል ሲጠራ..."

"ልብስ ሳጥብ ውዬ አሁን ገና ጨረስኩና ሻወር ገብቼ እኮ ነው...፤ ከነሳሙናዬ ራቁቴን ነው አሁን የቆምኩት ... ፍቅር ብታየኝ ሳሰቅ...!"

"ማን አለ?"

"ማን አለ? የትጋ" አለች በግርምትና ግራ መጋባት። ያመለጠኝን ጥያቄ አልደገምኩትም። መዓዛም ከዛ

በኋላ አላነሳችውም።

ቅናቱ ሲጨምር ልፍስፍስና በራሴ የማልተማመን ሰው ሆንኩ። በፊት በቀላሉ የምሠራውን ነገር ሁሉ መሥራት አልቻልኩም። ቅናት አቅም ያሳጣል። አንድ የማይረባ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር በዙሪያችን ያሉ መልካም ነገሮችን ሁሉ ይጋርድብናል።

አንድ ቀን ከመዓዚ ጋር ሻይ ቡና እንበል ብለን ወጣንና አምሽተን ስንመለስ እኔ ይዤው የነበረው የቤት ቁልፍ ጠፋ። ውጭ ቆመን አማራጭ መፈለግ ጀመርን። እኔ ሰብረን እንግባ ስል፣ መዓዚ ሳይመሽና ታክሲ ሳናጣ እናቷ ቤት ሄደን እንድናድር ሐሳብ አቀረበች። ልሰማት አልፈለግኩም፤ ቁልፉን ለመስበር መታገል ጀመርኩ። ታች አንደኛ ፎቅ ላይ ካሉ 'ጎረታች ቤት' (ለኮንዶሚኒየም የታች ጎረቤቶች የሰጠሁት ስም ነው… ላይ ያሉትን 'ጎረላይ ቤት' … ጎን 'ሰው የለም እንጂ ጎረቤት' ይሆን ነበር…) እና ከጎረታች ቤት ቢላዋ፣ ፒንሳ፣ መፍቻ ተውሼ መጣሁና መታገል ጀመርኩ - ወይ ፍንክች በሩ ! መዓዚ ረዥም ሰዓት ምንም ስላደረገችና ስላልቻልን ለመሆን መቆም ደከማት፣ የለበሰችውም ቀሚስ አጭር ስለነበር ብርድ እያንሰፈሰፋት ከጎኔ ትንቆራጠጣለች።

አንድ ሰዓት የሚሆን ታግዬ ላብ በላብ ሆኜ እና እጄ ደም አርግዞ ያተረፍኩት ነገር ቢኖር በሩ ሊከፈት እንደማይችል ማረጋገጥ ነበር !

"በቃ አይከፈትም!" አልኳት።

"ነግሬህ ነበር እኮ ፍቅር…! በቃ እማማ ጋር እንሂድ" አለችኝ እየተቻኮለች። በዚች ቅፅበት የጠረንገሎው 'ጎረቤት' በር ተከፈተ። በሩ ሲከፈት በበሩ ስፋት ልክ የብርሃን ምንጣፍ በሩ ፊት ለፊት ያለው በረንዳ ላይ ተነጠፈ። ጠረንገሎው የደረቱን እና የእጆቹን ጡንቻ አጉልቶ የሚያሳይ ጉርድ ቲ ሸርት ከቁምጣ ጋር ለብሶ ብቅ አለ።

የብርሃን ምንጣፉ ላይ ቆሞ ወደ እኛ አየት አደረገና፣

"ደህና አመሻችሁ አብርሽ!" አለ። እሱን ሳይ እልሄ ከየት መጣ ሳልለው ከንብል አለብኝ። ለሰላምታው መልስ ሳልሰጥ ኮቴን አውልቄ 'ያዥ…!' አልኳትና ቢላውን እንስቼ ቁልፉን መገርገር ጀመርኩ።

"ሰላም አመሸህ አቶ ሰለሞን። ቁልፍ ጠፍቶብን ለመክፈት እየታገልን ነው ይሄውልህ" አለች መዓዚ ምን አስለፈለፋት…። እየተንጎራደደ መጥቶ አጠገባችን ሲቆም ጥላው ከበደኝ።

አያያዜን ትንሽ ተመለከተና፣ "እስኪ መፍቻዋን ስጭኝ...!" ብሎ ከመዓዛ ተቀበለ።

እንዳቀረቀርኩ ገመትኩ ...

*መፍቻውን ስትሰጠው እጆቻቸው ተነካክተዋል ... ዓይኗን ዓይኑ ላይ ተከላ ፈገግ ብላም ሊሆን ይችላል። እጁ ሲነካት ብርድ ላይ የመሽ ሰውነቷ በደስታ ተፍታትቶ ሙቀት በሙቀት ሆናም ሊሆን ይችላል ... 'በዚህ ብርድ ይሄ ደናዳፋ ባሌ ድራሹ ጠፍቶ አንተ ቤት ገብቼ አቅፍ ብታደርገኝ' የሚል መልእክት በዓይኖቿ ልትነግረው ትችላለች፤... እሱም በጉርድ ቀሚስ ያልተሸፈኑትን ውብ እግሮቿን ተስገብግቦ እየተመለከተ ይሆናል ...፤ እግሮቿን ሊስማቸው እያለመ እንደሆን ማን ያውቃል?*

"አብርሽ እንዴ ልሞክረው እስኪ..." አለኝ ወደ በሩ ጠጋ ብሎ።

"እይ አይከፈትም፤ ሞከርኩትኮ ...፤ በቃ ነገ በባለሞያ እናስከፍተዋለን። ቁልፉን ቢሮም ረስቼው ሊሆን ይችላል።" ብዬ ቀበጣጠርኩ።

ጠረንገሎው ግን እኔ ስናገር ወደ በሩ ጠጋ ብሎ ጆርባውን ሰጠኝና በሰከንዶች ዕድሜ ... ምኑን እንደነካው እንጃ *ቀጭ ብሎ በሩ ተበረገደ። ካለባለቤቱ ፈቃድ አለቃ ባለቤት ሆኖበት የለ ቤቱን ... ገና ሲነካው ተበረገደ !*

ውስጤ በብስጭት፣ በመበለጥ ስሜት በቅናት ተንገበገበ።

"አ እግዚአብሔር ይስጥልን...!" አለችው። ይሄ መዓዛ በሳቅ እና ደስታ በታጀበ ስርቅርቅ ድምፅ፣ ድምጿዋ ከነፍሷ ስትደሰት ነው ከውስጧ የሚወጣው። ለምሳሌ እግቢኝ ያልኳት ቀን "ኦ ማይ ጋድ !" ብላለች፤ ከወሲብ በኋላም በጣም ስትደሰት "ኦ ማይ ጋድ !" ትላለች። አሁንም ይሄው ይሄ ጠረንገሎ እኔ ያላላሁትን ስለከፈተ ደገመችው።

"አባክህ ግባና ሻይ ጠጥተህ ትሄዳለህ!" እያለች ትለምነው ጀመረ። ይሄ ጠረንገሎ በሩን ብቻ አይደለም፣ የሚስቴንም ልብ ነው የበረገደው፤ ቀናሁ ! ለማትግናለሁ እንኳን ማለት አልቻልኩም። ገብቼ ወደ መኝታ ቤቴ አመራሁ። በዚህ አያያዛቸው ቀድመው መኝታ ቤቱን ሳይዙብኝ አረፍ ልበል ብዬ... መዓዛ ሰውዬዋን ሸኝታ ወደ መኝታ ቤት መጣችና ፊቷ ተቀያይሮ ፊቴ ቆመች። ያላዩኋት መስዬ ዓይኖቼን ጨፈንኩ !

"ስማ አብርሽ...! ለምን ይሄን ያህል ባለጌ ትሆናለህ። ሰው ጎረቤቱ ሲረዳው ማመስገኑ ቢቀር እንዲህ መገላመጥ አለበት...? ለምን እኔንስ ታሳፍረኛለህ...?"

"ምንድነው የረዳን...? የሰው ቤት ቁልፍ ስለፈለቀቀ...? ወሮበላ !! ይሄ እንደውም ልምድ ያለው ቤት ፈልቃቂ ሳይሆን አይቀርም።"

"ኧረ በእግዚአብሔር አብርሽ ሥርዓት ይኑርህ!"

"ሥርዓት አንቺ ነሽ የምታስተምሪኝ? መጀመሪያ ራስሽ ሥርዓት ይኑርሽ። ሌላውን በሌለሁበት የምታደርጊውን ሁሉ ያላወቅኩ መስዬ ብችለው ጭራሽ የማንንም ቤት ሰርሳሪ እየጠራሽ ቤቴን ማሰበር ጀመርሽ...።"

መዓዛ ትክ ብላ እየተመለከተችኝ በተረጋጋና በሚያስፈራ ድምፅ፣ "ምንድነው በሌለህበት ያደረግኩት ?" አለችኝ።

"አላውቅልሽም ! ሌተኛበት !" ብዬ ልብሴን ማወላለቅ ጀመርኩ።

"ምንድነው በሌለህበት ያደረግኩት?" ብላ ከበፊቱ ጠንከር ባለ ድምፅ ጠየቀችኝ።

"ቁልፍ ሰባሪ ጓደኛሽን ሂጅና ጠይቂው" አልኳት በእልህ።

በዚህች ቅፅበት በራችን ተንኳኳ። የነለሳለችብኝ ዓይኗን እንደተነለሰለ በሩን ልትከፍት ሄደች።

"ረስቼው መፍቻውን ይዤባችሁ ሄድኩ!" ሲል ሰማሁት ጠረንገሎው።

*ምን ትረሳዋለህ ... በየምክንያቱ ዓይንሽን ሊይ ላትልም ...!?* አላለሁ በውስጤ።

"ውይ መጥቼ እወስደው አልነበር፤ ምን አመላለሰህ!" ስትል ሰማኋት፤ ከበፊቱ ሻከር ባለ ድምፅ። ይሄን የመዓዚን ድምፅ ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ሰምቼዋለሁ። ለሁለት ዓመት ትምህርት ሌላ አገር ልሄድ ስትሰናበተኝና እናቴ እንዳላገባት ፊቷ የነገረችኝ ቀን። ይሄን ድምጿን እፈራዋለሁ። መኝታ ቤቴን ከውስጥ መቀርቀር ከጀለኝ። ... ማንን ደስ ይበለው ብዬ !

መዓዛን ጠበቅኳት፤ ወደ መኝታ ቤት አልመጣችም። ቀስ ብዬ ወደ ሳሎን ሄድኩ። ሰፋ ላይ ቁጭ ብላ ባዶው ላይ አፍጥጣለች።

ተመልሼ ተኛሁ።

ሌሊት ወደ ዘጠኝ ሰዓት ከእንቅልፌ ስነቃ መዓዛ አሁንም ጎኔ የለችም።

ወደ ሳሎን ሄድኩ፤ ማታ እንዳየኋት ከነልብሷ ከነሜማዋ ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ባደው ላይ አፍጥጣለች።

ተመልሼ ተኛሁ።

ጠዋት ተነስቼ ወደ ሳሎን ሄድኩ። መዓዛ የተተኮሰ ልብስ ...፤ ቁርስ አላዘጋጀችልኝም። እዛው ቦታ በዛው ሁኔታ ተቀምጣ እንቅልፍ ወስዷታል።

እንደተኛች ወጣሁ።

*ምን ቢያኮርፍ ፆሙን ያድራል አሉ ... ጠረንገሎው መኪና ማቆሚያው አካባቢ ገመድ ይዘላል። ቁንጣን ያዘለለውና !*

*ማታ ወደ ቤት ስመለስ መዓዛ ቤቱን ትታልኝ ሄዳለች። አሁን ቅናት ሙሉ ሆነች። ማሰብ ጀመርኩ ... ሻንጣዋን ይዛ ስትሄድ የሆነ ባለ መኪና አገኛት... 'ቆንጆ ወዴት ነው ልሸኝሽ?' ይላታል፤... ትሣበለች፤ ... እያለቀሰች ታሪኳን ትነግረዋለች...፤ አቅፎ ያባብላታል...።*

መዓዛ ንፁህ አፍቃሪ መሆኗን ባውቅም ሁለት ሰው የሆንኩ እስኪመስለኝ አእምሮዬ የቅናት ቅዠቱን ሊያቆምልኝ አልቻለም።

ልቤ ይገስፀኛል ...! ልቤን ገደል ግባ ስለው ነው ድሮም ራሴ ገደል የገባሁት።

መዓዛ አልተመለሰችም። እናቷ ቤት የለችም። ጓደኛም ከእኔ ሙጭ አልነበራትምና ማን ጋር ሄጄ ልጠይቅ ...

*ሌላ ሰው አግብታ ይሆን እንዴ...? ምናልባት ከእኔ ጋር እያለች ይገናኙ የነበረ - ሀብታምሊሆን ይችላል !!*

ከሦስት ዓመታት መለያየት በኋላ አየር መንገድ ሥራ ላይ እያለሁ ከሳኡዲ ታፍሰው ከተባረሩ ኢትዮጵያዊያን ስም ዝርዝር መካከል የመዓዛን ስም ተመለከትኩት። ከሌላ ሴት ጋር ፍቅር ጀምሬ ነበርና ከዚህ በላይ ስለ መዓዛ ማሰብ አልፈለግኩም ...

*ግን አዲሷ ፍቅረኛዬ ዛሬ እንዴት ሳትደውል ቀረች ? ... ያ በጸሐፊነት የሚያሠራት አለቃዋ ሀብታም ጋር ... ???*

*ሊሆን ይችላል !!*




2009